# የመንጌ ውሽማሚት

## እና ሌሎችም ውብ ታሪኮች



በተስፋዬ አለነ አባተ

የቴሌግራም
ቻናላችንን
በመቀላቀል ሌሎች
ልብወለድ
ትረካዎች
ለማግኘት

@amharicbooks24

ወይም

ይሄን ይጫኑ

# ማውጫ


1. የመንጌ ውሽሚት ..... 1
2. የጢቢኛ ፍቅር ..... 10
3. ቆጮ ..... 20
4. ዲናሬ ..... 25
5. አወይ ቀላድ አምባ ..... 37
6. ድብቅ ..... 46
7. የድድ ማስጫ ልጆች ..... 61
8. ለከፋ ..... 72
9. ምኞት ..... 84
10. ፈረንሳይ ካራቴ ..... 96
11. ዓለም ገምታለች ..... 105
12. ከእብደት በስተጀርባ ..... 116
13. ስጥ እንግዲህ ..... 128
14. ጋሽ በረደድ ..... 135
15. ቁልቢ ..... 144
16. የግንቦት ልደታ ..... 161
17. የቡዳ መድኃኒት ..... 172
18. የፍቅር ደብዳቤ ..... 183
19. ርችት ..... 189
20. ዱርዬው ባንድ ..... 201
21. ኤልፓ ..... 217


@BOOKALEM

# ምዕራፍ አንድ

## የትሁኔ ምስጢር

የጠይሜ አባት በጣም የሚገርሙ ሰው ናቸው ። የመቶ አለቃ በቀለ ይባላሉ ። የመቶ አለቅናውን ማዕረግ ያገኙት ከዓፄ ኃይለ ሥላሤ ዘመን መንግሥት ጀምሮ ወታደር ስለነበሩ በመሆኑ በሰፋት ይወራል ። ኮስታራና ጨካኝ በመሆናቸው እንኳንስ ልጆቻቸውና የኛም አባቶች ይፈሯቸዋል ። «በቁን በርቀት ካልሆነ ከቀረብከው እንደታጠበ ጨርቅ ጠምዝዞ ነው የሚያንጠለጥልህ !» ይላሉ የጋሽ በቁን ጉልቤነት ሲያሠምሩበት።

ጋሽ በቂ አንዳንዴ አመላቸው ግራ ያጋባኛል።እኛ ልጅ ልጆቹ « መቶ አለቃ !» ስንላቸው ያሯሩጡናል። « አባትህ አርባ ዓመት አገልግሎ ጡረታና ጅብ የማይበላው ከስክስ ነው ያተረፈልህ። ምን ታደርግ ?» ይሉናል ። የዕድሜ እኩዮቻቸውና የሞያ አጋሮቻቸው ደሞ « ጋሽ በቂ !» ሲሏቸው ይጣላሉ ።

« ለፍቼ ያመጣሁትን ማዕረጌን የት አባክ ጥለህ ነው ጋሼ የምትለኝ ?» ብለው አምባጓሮ ያነሳሉ ።

ቀማቴ ናቸው ። የሚገርሙ የጫት ወፍጮ ። በፌስታል የሞሉትን ጫት ቅርጥፍጥፍ አድርገው፣ ጥርሳቸውን ጠንከር ባለ የጫት እንጨት እየፈተጉ ከቤት ሲወጡ ያስፈራሉ ። በምርቃና ብዛት ፊታቸው ወርዝቶ ፣ ግንባራቸው ተኮሳትሮ ፣ ዓይኖቻቸው ፈጥጠው ፣ ደጋግመው ምራቃቸውን ጢቅ እያደረጉ ለተመለከታቸው አይጣል ።

ከምግብ ጫት የሚያስቀድሙት እኚህ መቶ አለቃ ልጆቻቸውን ግን « ጫት የሚባል ነገር ቀምሳችሁ ወይ ይዛችሁ ያገኘኋችሁ ቀን እኔን አያርገኝ ። እንደ እባብ ጭንቅል ጭንቅላታችሁን ቀጥቅጬ አደፋችሁና እጄን ለመንግሥት እሠጣለሁ !» ይሏቸዋል ። አቤት የዚያኔ ያለ መርበትበት !

ከምርቃና በኋላ በቀጥታ የሚያመሩት ወደነ እማማ ትሁኔ ቤት ነው ። እማማ ትሁኔ በመንደራችን የታወቁ አረቄ ሻጭ ናቸው ። ከስል ያሉ ጥቁር ፣ እንደ አሎሎ ድብልብል ያሉ ወፍራም ፣ እብጥ ያለባቸው ቂጣም መሆናቸውን ሳስበው እማማ ትሁኔ ይገርሙኛል ።

የእማማ ትሁኔ ቀሚስ ጉርድም ሆነ ሙሉ ሁሌም ከኋላ በኩል ጠልጠል ማለቱ የግድ ይመስላል ። የቂጣቸው ትልቀት የቀሚሳቸውን ቅርፅ አጓድሎ ጠርዝ ያዛንፋል ። ሲያወሩ ደሞ ትንሽ ምላሳቸውን ያዝ ፣ ኮልተፍ ስለሚያደርጋቸው ለቸኮለ አይመቹም ። እንዲያውም አንድ ቀን እያቴ «ከትሁኔ ጋር ማውራትስ አረፍት የሆኑ ቀን» ስትል ሠምቻታለሁ ።

ጋሽ በቂ የእማማ ትሁኔ ደንበኛ ስለሆኑ ከምርቃና በኋላ ማረፊያቸው አረቄ ቤቱ ነው ።



@BOOKALEM

ከመሠሏቸው ጋር መስለው ይጠጣሉ ። በዚያች ቀጥ ብለው ገብተው እየተንገዳገዱ በሚወጡባት ጎጆ ውስጥ መጠጣት ብቻም ሳይሆን መጣላትም አለ ። እንዲያው መጣላት እንደ መጠጣት ገንዘብ የሚያስከፍል ቢሆን እማማ ትሁኔ ከጠበኞች በሚያገኙት ገንዘብ በስም ብቻ የማውቃቸውን አላሙዲንን በበለጧቸው ነበር ።

አረቂ ቤቷን በመበጥበጥ ከሚታወቁት ሰዎች ዋነኞቹ ጋሽ በቄ ፣ ኢዶሳና ጋሽ ቶሌራ ነበሩ ። ኢዶሳ ሹፌር ፣ጋሽ ቶሌራ ደሞ የትምህርት ቤታችን ዘበኛ ናቸው ። በቄና ቶሌራ ዱላ ከእጃቸው አይጠፋም ። የበቄ ከፌሮ ብረት የተሠራና በፕላስቲክ የተለበጠ ከዘራ ሲሆን የቶሌ ደሞ ተፍቆ የተለሠለሠ የወይራ ዛፍ እንጨት ነው ።

ቶሌራ እግራቸው አንከስ አንከስ ስለሚል ዱላቸው እንደ ሦስተኛ እግር ሆኖ ያገለግላቸዋል። እንዲህ እንድል ያበቃኝ አንድ ጊዜ ጓደኛችንን በዱላቸው ቅጥቅጥ አድርገውት ቤተሰቦቹ ቀበሌ ይከሷቸዋል ። የቀበሌያችን የፍርድ ሸንጎ አባላትም ቶሌራን ያስጠሯቸውና

«ለምንድን ነው የሰው ልጅ በዱላ የደበደብከው ?» ይሏቸዋል ።

« ኧረ እኔ በዱላ አልመታሁትም ጌቶች ! » ይመልሳሉ ።

« እና ታድያ በምንህ ነው የመታኸው ?»

« በእግሬ !»

« በእግርህ እንዴት አርገህ ? » ይሏቸዋል ከሸንጎ አባላት አንዱ

« እንዲህ ነዋ !» ብለው በያዙት ዱላ ጠያቂውን መማታት ሲጀምሩ በቀበሌው የነበረ ሕዝብ ተባብሮ ይዞ ለሦስት ወራት ታስረው ወጡ ። ከዚያ ጊዜ ወዲህ ያቺ ዱላ «የቶሌራ እግር!» ተብላ መጠራት ጀመረች-ስሟን ባታውቀውም ።

ጋሽ ቶሌራ የመጠጣት ብቻ ሳይሆን የመማታት ሱስም አለባቸው ። ይህን ሱስ ያዳበሩት ደሞ ከየትም ሳይሆን ካሳለፉት ሕይወት መሆኑ ይወራል ። ቀድሞ የደርግ አቢዮት ጠባቂ ነበሩ። «ኢህአፓ» ወይም «መኢሶን» ናቸው ተብለው ተይዘው ወደ ቀበሌ የመጡላቸውን ወጣቶች ስምንት ቁጥር ገልብጠው እያሰሩ ይገርፉ ነበር ። እንዲያውም ሲፈትሉባቸው «አንዳንዴ የሚገረፍ ሲያጣ እራሱን በራሱ እየገረፈ እራሱን ያስምል ነበር» ይሏቸዋል ።

የሆነ ሆኖ ግን እኔም እርኩስነታቸውን እመሰክራለሁ ። የትምህርት ቤታችን የጥበቃ ሠራተኛ ሆነው ሲሠሩ አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ ። ፍሬዓለም የሚባለውን ጓደኛችንን ጥይት ተኩሰው ሳቱት። ሌላ ጊዜ ደሞ የነፃ ክፍለ ጊዜ ስለነበረን ከክፍል ውስጥ ተቀምጠን እንለፈልፋለን ። ከፍላችንን ብቻ ሳይሆን ጎረቤቶቻችንንም እንረብሻለን ። እዚያኛው ክፍል የነበረው መምህር መጥቶ ዝም እንድንልለት ጠየቀን ።

መምህሩ እንደወጣ ወሬያችንን ቀጠልን ። ለነገሩ አዲስ አስተማሪ ስለነበረ መሰለኝ የናቅነው ።



@BOOKALEM

ለካንስ በቅርብ ርቀት ጋሽ ቶሌራ ይከታተሉን ነበርና የበር ጥቢታቸውን ትተው ፣ ከፍ ዝቅ በሚል አረማመዳቸው እየታገዙ ፣ ዱላቸውን እያወዛወዙ ወደ ከፍላችን ሲንደረደሩ ኅሊና ታያቸውና «ቶሌራ መጣላችሁ !» ትለናለች ።

በቃ ! ማን « ወንድ ነኝ !» ያለ ትንፍሽ ይበል ። ሁላችንም ፀጥ ። የሰውዬው በቅፅበት ከዘበኝነት ወደ አስተማሪነት መለወጥ እያስገረመን ሳለ

« ተናገሩ ! ማነው ከፍሉን የሚበጠብጠው ?» አሉን አፍጥጠውብን ።

« ፍሪ ፔሬዳችን ነው » ስትል ኅሊና መልስ ሠጠች ።

«ና ውጣ ! ፍሪ ፔሬድ የምትባለው ሰው ሳልሰባብርህ ከዚህ ከፍል ውጣ » እያሉ ወንድ ወንዶቹ ላይ ሲያጉረጠርጡብንና የእያንዳንዳችንን ስም ሲጠይቁ የአማርኛ መምህራችን ድንገት መጥቶ ገላገለን ። ከዚያም ለመምህራችን የ 'free Period'ን ጉዳይ ነገርነውና ተጋግዘን በጋሽ ቶሌራ ሳቅን።

ጋሽ በቆና እማማ ትሁኔ አርቦሽ ናቸው ። በጣም ከመግባባታቸው የተነሳ የጋሽ በቋን የመጨረሻ ልጅ ትርሲትን ክርስትና አንስተዋል ። ቢሆንም ግን ካልከፈሉ አይጠጡም ።

በነገራችን ላይ እማማ ትሁኔ ዱቤ አይሰጡም። እንዲያውም ግድግዳቸውን የሸፈነ አንድ ጽሑፍ እንዲህ ይላል።

« ዱቤ ከመንግሥቱ ወዲህ ...»

ታላቅ ወንድሜ ሁሌም « ሆዴን ስለቆረጠኝ ከእማማ ትሁኔ ቤት ሁለት መለኪያ የሀበሻ አረቂ አምጣልኝ » ሲለኝ ያቺን ፅሁፍ በዓይኖቼ እለቅማታለሁ ። « መንግሥቱ ማነው ?» ስልም መጀመርያ እራሴን ከዚያም በድፍረት እማማ ትሁኔን ጠየቅኩ ።

« አባትህ ነዋ ! ደሞ ብለህ ብለህ መንግሥቱን አጣኸው ?» አሉኝ ደነገጥኩ።

« ኸረ ! የኔ አባት እኮ መንግሥቱ አይደለም ስሙ !» መለስኩላቸው ።

«ነው እንጂ ! አባትህማ መንግሥቱ ነው ! እና ያንተ አባት ኃይለ ሥላሴ ሊሆንሉህ ትፈልጋ ለህ ጭንቅሎ ? የኒያ የደጉ ሰው ፣ የኒያ የለምለሙ ፣ ምቀኛ ከዙፋን አውርዶ በትራስ አፍኖ የደፋቸው የዋህ ሰው ልጅ መሆን ያምርሃል ?»

« እንዴ ሴትየዋ ምን ነካቸው ? ሥለ ምንድን ነው የሚያወሩት ?» እያልኩ ሳሠላስል

« ሲያምርህ ይቅር እሺ ጭንቅሎ ! ያንተ አባት ያ ከኔ የባሰ ጠቋራ ነው ። የተወለድከውስ ቢሆን በሱ ጊዜ አይደል ? አትሳሳት ወያኔ እንጀራ አባትህ እንጂ አባትህ አይደለ ችም ተስፋህን ቁረጥ !» አሉኝ ።



@BOOKALEM

« ታድያ ዱቤና መንጌን ምን አገናኛቸው ?»

« ጥገና !»

« የምን ጥገና እማማ ትሁኔ ?» ወንበራቸው ላይ ቂብ አልኩ ::

« ቆይ አንተ ይሺ ታሪክ ምን ያደርግልሃል ጭንቅሎ ? አርፈህ ትምህርትህን አትማርም እንዴ ?»

« ኧረ ! እማማ ትሁንዬ በናትዎት!» ጉልበታቸውን አቅፌ ለመንኳቸው ::

ሳቃቸውን ለቀቁት ::

እንዲህ ያደረግኩት በመንደርተኛው የሚታወቀውን የመንጌ ውሽምነት ታሪካቸውን ከራሳቸው ሰምቼ ለማረጋጋጥ ነበር :: በሠፈራችን እማማ ትሁኔና መንጌ የከንፈር ወዳጅነት እንደነበራቸው በሰፋት ይወራል :: እንዲያውም የሚጠግነውን መኪና እየተወ ፣ የታንከ ብሎኖቹን በቱታ ኪሱ እያንከላወሰ ከእማማ ትሁኔ ቤት አሳቻ ሰዓት ላይ ከተፍ ሲል የማይበረግግ ጠጪ አልነበረም ::«የሚስቀው ከሳቸው ጋር ሲሆን ብቻ ነው» ይሉታል የጥገና ከፍል ባልደረባዎቹ :: ሴትየይቱ በዕድሜ ታላቁ ቢሆኑም ወድዷቸዋል :: ማንም ድርጊቱን ቢቃወመውም ወድዷቸዋልና ሊርቃቸው ፣ ከሌላም ሆነው እንዲያያቸው ልቡ አልፈቀደም ::

እሱ ባለበት እሳቸውን በፍቅር ዓይን ካየ ጠጪ ጋር ሁሉ በስማቸው ተቧቅሷል :: ባላንጣዎቹን አንድ በአንድ በቡጢ አጋድሟቸዋል :: አፍንጫውን አጠፍጥፈውለት ከናፍሮቻቸውን ሠነጣጥቋል :: ቅንድቡን ተርትረውለት ጥርሳቸውን ከብረት በሚታገል ቡጢው ሸራርፏል፤ አወላልቋል :: ባደባባይ «ትሁኔን የተመኘሽ የጥገና ቤት ወታደር ሁሉ ቂጥሽን በሳንጃ ፣ ማዕረግሽን በመቀስ አስደነግጥልሻለሁ !» ይላቸዋል :: ይቺ ዛቻው የመንጌ መለያው ሆነች :: እንዲህ ብሎ ከዛተ ለማንም እንደማይመለስ ሁሉም ያውቁታል ::

የሁሉ ሀገር ፣ የሁሉ ማረፊያ የነበሩትን እማማ ትሁኔን የብቻው አደረጋቸው :: እርሳቸውም ቢሆኑ «ከቶ ምን ተገኝቶ ነው ከዚያ ባርያ ጋር እንዲህ እፍ ከድን ያላችሁት ?» ሲባሉ «እኔ ያየሁትን ስላላያችሁ ያሻችሁን ብትሉ አይጎረብጠኝም » እያሉ ጀግንነቱን ያጎሉለታል :: ወፋፍራም ከናፍሮች የሸፈኑት ፈገግታ በርግጥም ልብ የሚያስሸፍት ነበር ::

አጎቴም ሥለ መንጌ ወሬ ከተጀመረ ከእማማ ትሁኔ ጋር የነበረውን ወዳጅነት አውርቶ አይጠግብም :: እስኪያንገሸግሸኝ ፣ በወሬው ደከሜ እንቅልፍ እስኪያዳፋኝ ይነግረኝ ነበር :: ከትምህርት ቤት ጓደኞቹ ጋር ሲመለሱ በእማማ ትሁኔ ደጃፍ ያልፋሉ :: በጠራራ ፀሐይ መንጌ በጠላ ብርጭቆ አረቂ አስሞልቶ እማማ ትሁኔን እቅፍ አድርጎ እያጎረሳቸው ሲበላ ተደብቀው አይተዋቸዋል :: ጡታቸውን እየጎነተለ ፣ በሳቅ እያፍነከነካቸው ፣ በሳቅ እየተፍነከነከ ግጥም አድርጎ ሲስማቸው ፣ እሳቸውም ከተሳሙ በኋላ በቀሚሳቸው እጅጌ ከናፍሮቻቸውን በፈገግታ



@BOOKALEM

ታጅበው ሲጠራርጉ ተመልከተዋል ::

የሆነ ቀንም ይኸው አጎቴ አረቄ እንዲገዛ ተላከ :: ገርበብ ተደርጎ የነበረውን ቤታቸውን በርግዶ ዘው ሲል ባልተነጠፈው አልጋ ጠርዝ ላይ ቁጭ ብሎ የወታደር ጫማውን ዚፖች ሽቅብ ሲቆልፍ አግኝቶታል :: በድንጋጤ ቀና ብሎ እያየው «ማሙሽ ደህና ነህ ?» ሲል በሚያስገመግም ድምፁ ጤናውን ጠይቆታል :: ያየውን ለማንም እንዳይናገር አስጠንቅቆታል :: ማስጠንቀቂያውን ማስከበርያም ሃያ ሳንቲምና ዛቻ በቀብድ መልክ ተቀብሏል :: አጎቴም ውሉን ለማፍረስ ሁለት የስራና አስራ ሰባት የሠይጣን አመታትን ጠብቋል ::

«ለመሆኑ ስታድግ ምን መሆን ነው የምትፈልገው ጭንቅሎ ?» አሉኝ ፀጉሬን በእናትነት እያሻሹ።

« ጋዜጠኛ !»

« ጎሽ ! እሰይ ! ለዚያች ለምስኪን እናትህ ስትልስ ሁንላት ። ምናልባትም ስታድግ፣እንደምኞትህ ጋዜጠኛ ሥትሆን ገንዘቤን ከመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ላይ ታስመልስልኝ ይሆናል ። እንትፍ! እንትፍ !» ብለው የዕድሜ ልክ ጭርት ያስያዘኝን ወፍራም ምራቃቸውን ፊቴ ላይ ለደፉብኝ ።

« ይኸውልህ የኔ ልጅ ...መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ያኔ ገና ወታደር ሳለ እዚህ ጥገና የሚባለው የወታደር መሥርያ ቤት ውስጥ ነበር የሚሠራው ። እንዴት ያለ ጎበዝ መካኒክ ነበር መሠለህ ። እና ታድያ እኔም ስወደው ለጉድ ነበር ። ብታየው እኮ ጭንቅሎ እጠቋቆሩ ፣ ወንዳወንድነቱ ፣ እንዷን መለኪያ አረቄ በአንድ ትንፋሽ ኸው ሲያደርጋት አቤት ሲያስደስት !

« ታድያ አንድ ጊዜ ደመወዝ እስኪወጣ በዱቤ ጠጣልህ ። ከዚያ ከዛሬ ነገ ይከፍለኛል ስል ሲቀር ፣ ስጠብቅ ሲቀር ኋላ ላይ እጂያን ደግ አባት ከመንበረ ስልጣናቸው ገልብጦ ገድሏቸው ነገሠ። ግሪሱን ጠራርጎ ዙፋን ላይ ተቀመጠ። «ከዛሬ ጀምሮ ኢትዮጵያን የሚያስተዳድራት እሱ ነው» የሚል ወሬ ሠማሁ ። ያው ቅንነቱን አውቅ ስለነበር መንጌ መቼም ጨክኖ ብሬን በልቶ አይቀርም ። እጥፍ አድርጎ ይመልስልኛል ብዬ በተስፋ ጠበቅኩ ። ለአንድ የሀገር አስተዳዳሪ አረቄ በብድር ያጠጣሁ መሆኔን በኩራት ለሐረር ሕዝብ እያወራሁ ከረምኩ ። በመጨረሻ ምላሴ ሌላ ዕዳ ይዛብኝ መጣች ።»

« የምን ዕዳ ? ሌላም ተበዳሪ ነበረዎት ?»

« ዝም ብለህ አዳምጥ ! የምን ወሬ ማጨንገፍ ነው ። ታጋሽ ጆሮ ከሌለህ ጋዜጠኛ መሆን አትችልም !» አሉኝ የሚያሻሹት ፀጉሬን ነጨት አድርገው ።

ታሪኩ ስለተመቸኝ የራስ ቅሌን ሕመም ቻል አደረግኩት ።

« እናልህ ጭንቅሎዬ ... አጅሬ አዲሳባ ሲገባ የድሮ ጠባዩ ልውጥውጥ አለልህ ። ወጣቱን እያሳደነ መድፋት ፣የናቀውን መግፋት ሲጀምር ግራ ገባኝ ። መላዋ ቀላዮ አምባ መንጌን በምስጢር



@BOOKALEM

አኮረፈችው ። መቼም በድህነት ውስጥም ቢሆን እንደ መኖር የሚያጓጓ ነገር የለምና ለመኖር ጓጓሁ ። ' አብድሬዋለሁ ' እያልኩ በኩራት ያወራሁትን ቢሠማ እንደሚያስገድለኝ አረጋገጥኩ ። በየጊዜው የአብዮት ጥበቃ አባላት በየተራ እየመጡ ' አጠጪን ! ያለበለዚያ መሪያችንን ያለ ስሙ ስም ሥለሠጠሽብን ጨለማ ቤት እናስርሻለን ' እያሉ እያስፈራሩኝ ያለችኝን አስጨረሱኝ ።

« እንዲህ እንዲህ እያለ ጊዜው ሲኼድ እኔም ፣ ብሬም ፣ ጉልበቴም ደከምን ። ወያኔም ከነ ኮተቷ መጣችና መንጌን ሳይታሠብ መነገለችው ። ጉድ ሠራችው ። እኔም ታድያ የአስራ ሰባት ዓመታት እልሄን ተወጣሁበት ። ወዳጄ ለመምሰል ለዓመታት ግድግዳዬ ላይ ሠቅዬው የነበረውን ፎቶውን አውርጄ በምትኩ 'ዱቤ ከመንግሥቱ ወዲህ...' አስብዬ አስጻፍኩና ለጠፍኩት ። ይገርምሀል ጭንቅሎ... አስራ ሰባት ዓመታት ሙሉ የመንጌ ፎቶ ግድግዳዬ ላይ ሲኖር ለኔ በጥፋቱ ተፈርዶበት የተሠቀለ ወንበዴ ለተመልካች ወዳጅነትን ማሳያ መስሎ ነበር ።»

እውነታቸውን ነበር ያወሩልኝ ። አላቋርጣቸውም ብዬ እንጂ በእያንዳንዷ በሚነግሩኝ ታሪከ ውስጥ ያሳለፉትን የመከራ ጊዜ እንባቸው ገልፆልኛል ።

ድንገት ካጠገቤ ብድግ ብለው ከምሳ በተረፋቸው እንጀራ ላይ ኩርማን አከለውበት በሚጣፍጥ ከከ ወጥ ሠጡኝ ። እንደ ውሻ ተጣድፌ መብላት ጀመርኩ ። ርቦኝ እንደነበር ያወቅኩት የሠጡኝን ስልቅጥ አድርጌ ከጨረስኩ በኋላ ነበር ። ለካንስ ወንድሜ «ምሳህን የምትበላው አረቄውን ገዝተህልኝ ከመጣህ በኋላ ነው » ብሎ እንደላከኝ ወጥቼ ነበር የቀረሁት ።

« ግን እማማ ትሁኔ ! » አልኳቸው ።

« አቤት ! ደሞ ምን ቀረኝ ልትል ነው ጋዜጠኛው ?»

« አባባ መንጌ እኮ 'ፍሬንድ'ዎት ነበረ እየተባለ ይወራል ። ሰምተው ያውቃሉ እንዴ ?»

« እሱ ደሞ ምንድን ነው ? »

« ምኑ ?»

« አሁን ያልከው ።»

« ፍሬንድ ?»

« እህ ! »

« እንግሊዝኛ አያርፉም እንዴ ?»

« የት ተስተምሬ ብለህ ነው ጭንቅሎ ? ዕድሜዬን ሙሉ መንደራችንን በጨኸት ሲያምሷት ለሚያድሩት ወንዶች ዕብደት እየለካሁ ስሸጥ ፣ ጊዜያዊ ዕብድ አቡኩቼ እያነጋገርኩ ሳዋጣ ነው የከረምኩት ።»



@BOOKALEM

«እና ፈረንጅ አረቄ ሊጠጣ ቢመጣ እንዴት ያስተናግዱታል ?»

« ምን ችግር አለው ። በመለኪያ ይቀዳለታል ። የጠጣውን አይቼ የገዛቡን ልክ በኔ ብር ቆጥሬ አሳየዋለሁ ይከፍለኛል ።»

«ፐ ! ዘዴኛ ነዎት ! ግን 'ኮ የፍሬንድነቱን ነገር አልነገሩኝም ።»

« እኮ ! የአማርኛ ትርጉሙን ንገረኝና ልንገርሃ ። »

የተለካችልኝን አረቄ በእጄ ያዝኩ ። አንድ እግሬን በራቸው ላይ አደረግኩና « ማታ ማታ እየመጣ እንትን ይል ነበር ይባላል » አልኳቸው በተጨበጡት እጆቼ ታግዤ

« ምን ይል ነበር ይባላል ጭንቅሎዬ ?»

« ማታ ማታ እየመጣ እ ...» መናገር አፍሬ እየሳቅኩ አፌን ስይዝ

« አፈር ብላና አንተ የእህል ጠንቅ ። ጨዋ መስለህ እንጀራዬን ውጠህ ስታበቃ ሰደብከኝ አይደል? የሴት ልጅ ! ድሮም የሴት ልጅ የሴት ነው ። አንተ እንኳንስ ጋዜጠኛ ጋዜጣ አዟሪም አትሆን ። ሌባ የሌባ ልጅ ! »

ከዚህ በኋላ ያሉኝን ፣ የረገሙኝን ፣ የሠደቡኝን አልሰማሁም ። ስላናደድኳቸው ደስ ብሎኝ እየሳቅኩ ወደ ቤቴ ኼድኩ ። ከጓደኞቼ ጋር ስንገናኝ የማወራላቸው ወሬ እንዳገኘሁ ስረዳማ ደስታዬ ቅጥ አጣ ። እኛ ሠፈር እማማ ትሁኔ « ልጃችሁ ሰደበኝ !» ብለው ለወላጆቻችን ቢከሱንም አንገረፍም ። ወላጆቻችን « እሷ'ኮ ሠከራ ነው የምትዘላብደው ። ባላጠፉት ጥፋት ልጆቻችሁን አትቀጥቅጡ እንጂ !» ሲባባሉ እኔና ጠይሜ ሰምተናቸዋል ።

ጋሽ በቂ እማማ ትሁኔን እንዳናደድኳቸው ከሰሙብኝ ስለሚገድሉኝ ከነ ጠይሜ ቤት ቀረሁ። ከጠይሜ ጋር በጣም የምንዋደድ ጓደኛሞች ብንሆንም አንዳንዴ ነገረ ሥራው ያናድደኛል ። ከአባቱ የወረሠው የቧንቧ ሥራ ሞያ አለው ። አንዳንዴ የአባቱ ረዳት ሆኖ ይሠራል ። ብዙ ጊዜ ቅዳሜና እሁድ ደሞ እኔና ጠምበለል የሱ ረዳት ሆነን እንሠራለን ። ከላይ እታች እብረነው ስንለፋ ውለን የሠራንበትን የጉልበታችንን ዋጋ በጥሬ ብር አይከፍለንም ። በዕድሜ ትንሽ ስለሚበልጠን ለሚለን ነገር ከመታዘዝ ማፈንገጥ የለም ።

ቀኑን ሙሉ ሠርተን ውለን እነ ዘየደ ሱቅ አምጥቶ ትኩስ ዳቦ ይገዛልናል ። ዘየደን ጀንጅነን ዳቦው ውስጥ ስኳርና ዘይት እናስደርግበታለን ። ከዚያ ያንን ዳቦ በስኳር እየገመጥን እኔና ጠምበለልም ሌሎቹን የሠፈር ልጆች እናስቀናለን ። « ስጡን !» ብለው እጃቸውን ሲዘረጉልን « እዘሉንና !» እንላቸዋለን ። በጉልበት የምንበልጣቸው ከሆነ አዝለውንም እንሠጣቸውም ።

ጠይሜ ጉልቤ ስለሆነ በተለይ እኔና ጠምበለልን እንደ ልቡ ነው የሚጫወትብን ። ከሱ ጋር መጣላት ደሞ የገቢ ምንጫችንን እንደማድረቅ ይቆጠራል ። ሊታላላቅ ወንድሞቻችን ተናግረን ካስወገርነው ማን ዳቦ በስኳር ይገዛልናል ?



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

አንድ ቀን በጠዋት ጠይሜ ከተኛሁበት ቀሰቀሠኝ ። ፊቴን ሳልታጠብ ፣ የተኛሁበትን ሳላነጥፍ ተከትዬው ወደ ሜዳ ኼድኩ ። ተራ በተራ መተዛዘልን አልፈልግኩም ። በአንፃሩ ዳቦ በስኳር አምሮኝ ስለነበር በምግብ እንድንጫወት ተስማማሁ ።

የሆነ ርቀት አደረስኩትና የመጀመርያዋን አጎረሠኝ ። ከመቼውም ጊዜ በላቀ መልኩ ጣፈጠችኝ ። በባዶ ሆዴ ስለበላኋት ይሆን ? ስኳሯም ምላስና ጥርሴን ነካከታ የጥፍጥና ልኳን አሳየችኝ ። ቶሎ ቶሎ እያዘልኩ ቶሎ ቶሎ ለመጉረስ ቋመጥኩ ። ጠይሜ የገዛውን ዳቦ በስኳር ከሱ በላይ ልበላበት ወሠንኩና በትልቅ ጉርሻ ረጅም ርቀት ሳደርሠው ተስማማሁ ።

አዝዬው ከተለካው ርቀት ግማሽ እንደደረስኩ ላብ በላብ ሆንኩ ። አማጥኩ ። ወገቤ በአጥንታሙ ጠይሜ ከብደት እየተሠበረ መስሎ ተሠማኝ ። እግሬ መራመድ ተሳነው ። እግሮቹን ያቀፉት እጆቼ ዛሉ ። ከተላከው ርቀት ላይ ሳላደርሠው ካረፍኩ « ፎረሽክ » እንደሚለኝ አውቃለሁ ። ስለዚህም መላ መፍጠር ነበረብኝ ። ዕረፍት እንዲሆነኝ በሠበብ ቆም አልኩና « ዳቦውን አሳየኝ » አልኩት ። አሳየኝ ። ወደ አፍንጫዬ ጠጋ አድርጎ አሸተተኝ ። የተደበቀ ጉልበቴን ተጠቅሜ ከተለካው ርቀት ላይ አድርሼ አወረድኩት ። ዳቦውን በልቶ ጨርሶታል ። ተናደድኩ ። ከዚያም ምርር ብዬ አለቀስኩ።

ለቅሶዬን ተከትላ የመጣችው እያቴ ነበረች ። ምን እንደሆንኩ ስትጠይቀኝ የሆንኩትን ነገርኳት ። ሳቀችም ተናደደችም ። ለቀልድ እንደዚያ እንዳደረገና ሌላ እንደሚገዛልኝ ነገራት ። እሷ ስትኼድለት ያደረገው ግን ተቃራኒውን ነበር ። ዳቦ በስኳሩን ገዛና ዓይኖቼ እያዩ ብቻውን በላው። « አፈር ብላ !» አልኩት ሆዴን ተጠቅሜ ።

በጊሮ (ብይ) ጨዋታም ጠይሜን የሚስተካከለው አልነበረም ። ከርቀት የተቀመጠችውን ጊሮ እናቷን ቀንድሎ ሲሠብራት የጊሮዋ ባለቤት ደሞ « እናቷን !» ብሎ በመሠበሯ ጊሮዋን ይሠድባታል ። ሱቅ ሁለቱ ስሙኒ የሚሸጠውን ጊሮ እሱ ግን ሶስቱን ወይም አራቱን አንዳንዴም አምስቱን እየሸጠልን መልሶ ይበላናል ። ብዙ ገንዘብም ብዙ ጊሮም የሚያገኝ ሀብታም ማለት ጠይሜ ነው ።

ጋሽ በቂ ቧንቧ ሠርቶ ከሚያገኘው ብር ውጪ ሌላ ብር ጠይሜ ኪስ ውስጥ ካገኙ ገደሉት። በተለይ ቁማር ተጫውቶ ያገኘው ከሆነ ከተኛበት የሚቀሠቅሱት በዚያች በባለ ሁለት ምላስ የጠፍር መገረፊያው ዠልጠው ነው ። እሱም ይቼን ስለሚያውቅ ጊሮ ተጫውተን የበላንን ገንዘብ ሲምሽ አጥራቸው ሥር ቀብሮ ነው ወደ ቤታቸው የሚገባው ።

ብዙ ጊዜ ታድያ ገንዘብ ለመቅበር ሲሠናዳ ዙርያ ገባውን ይገላመጣል ። ማንም አለመኖሩንና አለመታየቱን ተረድቶ ለመቅበር ይሠናዳል ። አንዳንዴ ግን ጋሽ በቂ ጭብስ ብለው ቀድመውት ወደ ቤት ገብተው ካስጠሩት ያገኘበት ቦታ ይቀብረዋል ።

የዚያኔ እንከታተለውና እኔና ጠምበለል የቀበረውን ቆፍረን እናወጣበታለን ። ጠዋት መዘረፉን ሲያውቅ የሆነውን ይነግረናል ። እንደ አዲስ እንሠማዋለን ። ሌቦቹን ፈልገን እንደምንቀጠቅጣቸው



@BOOKALEM

ቃል እንገባለታለን ። ከዚያ መውሠድ አለመውሠዳችንን እንድናረጋግጥለት በገብርዔል ፣ በጊዮርጊስ ፣ በመድኃኒዓለም ፣በማርያም ፣ በሥላሴዎች ፣ በእናቶቻችን ፣ በአባቶቻችን ስም ያስምለናል ።

«ከትምህርቴ ገበታ ይነጥለኝ ! የልጅነት አበባዬን ይቅጨው !» እንልለታለን ። ያለ ጥርጥር እንምልለታለን ። ያምነናል ። ዘወር እንልና « ይቅር በለኝ ጌታዬ ! በሀሰት ነውና የማልኩት እናትና አባቴን አትንሳኝ ። የልጅነት አበባዬንም አትቅጨው ። ባይሆን ከጨከንክ ከትምህርቴ ገበታ ለየኝ !» እንለዋለን ሳናየው የምናምነውን አምላካችንን...እግዚአብሔርን እውነቱን ፣ ከጠይሜ የደበቅነውን ሐቅ ነግረን ይቅርታ እንጠይቀዋለን ። ለነገሩ ቶሎ ይሠሙናል ብለን የምናስበው ሠፈራችን ያሉትን ጊዮርጊስንና ገብርዔልን ነው ። እኛ ሠፈር ስለሆኑ በስም ሁሉ ለይተው እንደሚያውቁን እርግጠኞች ነን ። ሌሎቹ ቤተ ክርስትያናት ግን ከኛ ሠፈር በጣም ርቀው ስለሚገኙ አያውቁንም ።

ታድያ አምላካችንም በጠይሜ የምንበደለውን በደል ሥለሚያውቅ መሀላችንን አይቆጥርብንም ።

« የልጅነት አበባዬን ይቅጨው !» እያልኩ ብዙ ጊዜ በውሸት ምያለሁ ። አንዴም ግን ተቆ ጥሮብኝ አያውቅም ። እናቴ ሳትሞትብኝ እቤት እያለች « የእናቴ አጥንት እሾክ ሆኖ ይውጋኝ!» ብዬም እውቃለሁ ። እናቴ ግን እስካሁን በሕይወት አለችልኝ ። ረጅም ዕድሜ ለሷ ! ረጅም ዕድሜና ጤና ለእናቴ ! አምላክ በልጅነታችን የመሀላን ክብደት እንደማንረዳ ስላወቀ መሠለኝ ይቅር ያለኝ ፤ ይቅር ያለን ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ሁለት

## የጢቢኛ ፍቅር

ማለዳ ከእንቅልፉ ተነስቶ ፣ ዳገታማ ሥፍራ ላይ ቆሞ አቆልቁሎ የኛን ሠፈር የሚመለከት እንግዳ ሰው በሚያየው ነገር መደናገጡ አይቀርም ። ከአብዛኛዎቹ ቤቶች የሚወጣው ጭስ እየትጎለጎለ ወደ ሰማይ ሲንጠላጠል ያስገርማል ። ሠፈራችን የተቃጠለች ትመስላለች፤ መቃጠሏንም ነዋሪዎቿ በፀጋ ተቀብለን ፀጥ ያልን ጭምር ።

የእያንዳንዱ ቤት ጣርያ ዝገት የዕድሜ ብቻ ሳይሆን የየዕለት ጭስ ውጤትም ነው ። በእያንዳንዱ አሮጌ ቤት ውስጥ በአማካይ ሁለት አዳዲስ የልጅ ልጆች ሳይኖሩ አይቀርም ።እነ ልጅ በልጅነት ያሉት እኛ ሠፈር ነዋ።

የማለዳ ማለዳው ጭስ ተለመደና በኛ ሠፈር በመላው ኢትዮጵያ የሚታወቀውን የሕዳር ሲታጠን በዓል አስረሳ ። የኛ ሠፈር እንደ ሌሎቹ የሀገራችን አካባቢዎች በየዓመቱ ሕዳር ተጠብቆ ብቻ አትታጠንም ። የኛ ሠፈር ዓመቱን ሙሉ ያለ ማቋረጥ ትታጠናለች ። በኛ ሠፈር ዓመቱን ሙሉ «ሕዳር ሲታጠን» አለ ።

ከእያንዳንዱ ምጣድ ሥር የማይነድ ነገር የለም ። ሳጋቱራ ፣ የለውዝ ቅርፊት ፣ ኩበት ፣ የተቆራረጡ ጫማዎች ሁሉ ይነዳሉ ። ለአብዛኛዎቹ ምጣዶች ግለት ዋነኛው ግብዐት የጫት ገራባ ነው ። ጫት በኛ ሠፈር ተቅሞ ብቻም ሳይሆን ተፈልቶም ያመረቅናል ። በጫት ቅጠል ያፈላነውን ሻይ «ሃውዛ» እንለዋለን ። እናቶቻችን ከፍየልና በግ ተርፎ የደረቀውን የጫት ገራባ የምጣድ ቀለብ ያደርጉታል ።

የዚህ ሁሉ ጭስ ውጤት ደሞ ከብ ከብ የሆኑ ጢቢኛዎችን ወደ በላተኞች ያቀርባል ። እያንዳንዷ ጢቢኛ ጋጋሪ በቅርፅ ፣ በመጠንና በቀለም ጎረቤቷ ካለችው ጋጋሪ ጋር ትወዳደራለች። ይህ ብቻም ሳይሆን ቁንዶ በርበሬ የሌላት ጢቢኛ ጋጋሪ ገዢ እንደማይኖራት ማሰብ አለባት። ገበያዋ እንዲደራ የፈለገች ጢቢኛ ጋጋሪ ሥራዋን በጀመረች በመጀመርያው ቀን ለተወሠንነው ልጆች ትኩሱን ጢቢኛ በቁንዶ በርበሬ ማብላት አለባት ። እኛ በልተን ከጨረስን በኋላ ለጓደኞቻችንና ለቤተሰቦቻችን የአዲሱን ጢቢኛ ትልቀትና ጥፍጥና እናወራላታለን ። ከዚያማ ጠግበን እስከንጣላት ገበያውን ትቆጣጠረዋለች ።

አሁን አሁን እየገባኝ ያለው እውነት የማስታወቂያ ሥራን ሥራ መሆኑን ሳላውቅ የጀመርኩት በልጅነቴ እንደነበር ነው ። ገበያ ለማባረርም ሆነ ለመሳብ የኛ የልጅ የልጆቹ ዋጋ ከፍተኛ ነበር ።

እማማ ኮኮቤ የቆዩ ጢቢኛ ሻጭ ናቸው ። በዚህ ላይ ጴንጤ ። እኔና ጠይሜ ደሞ እሳቸው ቤት



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

አካባቢ በጎቻችንን እናግዳለን ። ልክ ከረፋዱ አራት ሰዓት ሲሆን ልጆቻቸውና ሌሎች ጓንጪዎች ተሰባስበው የሚፀልዩበት ጊዜ መሆኑን እናውቃለን ። ታድያ ሁሌም ያቺ ሰዓት እስከትደርስ እንቅበጠበጣለን ።

እሳቸው ለፀሎት ወደ ቤት ሲገቡ ሠፌዱን ብቻ አስቀርተን የጋገሩትን ጢቢኛ ልቅም አድርገን እንሠርቃቸዋለን ። ሠርቀን ከቤታቸው በስተጀርባ ካለ ጢሻ ውስጥ ተደብቀን እንበላለን። የተረፈንን ደሞ እንዳይነቃብን ለበጎቻችን እናጎርሳለን ። በጎቻችንም ታድያ የጢቢኛ ሱስ ይዟቸው ይመስለኛል ያቺ ሰዓት ሥትደርስ ተራ በተራ ይጮሃሉ ። ወደ ኩሽናው ስንኼድ ሊከተሉን ይሞክራሉ ።

እንደለመድነው አንድ ቀን ለፀሎት ሲገቡ ሠረቅናቸው ። ምጣዱ ላይ ካለው በቀር ምንም ሳናስቀር ወሠድንባቸው ። ከፀሎት መልስ ኩሽና ሲገቡ በረገጉ ። ከዚያ ከትልቁ ልጃቸው ከተፈራ ጋር ሆነው በጠፋው ጢቢኛ ዙርያ ማውራት ጀመሩ ።

« አይዞሽ እማዬ ውሻ በልቶት ሊሆን ይችላል ። የተረፈውን ከሸጥሽ ቀሪውን ኢየሱስ ይሞላዋል። ደሞም እንፀልይበታለን ።»

« ጌታ ይባረክ የኔ ልጅ ! እንኳንም ምጣዴ አልተሠበረ ። ጌታዬ ኢየሱስ በጎደለ ይሞላልኛል። አምስት ዓሳን ለአምስት ሺህሰዎች የመገበ ጌታ የኔን የሠፌድ ጢቢኛ ለመመለስ ምን ይሳነዋል?» አሉ ሁለቱን እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ቀስረው ።

ተደብቀን ከምናደምጥበት ጠይሜ ነካ ነካ አድርጎኝ

« ጭንቅሎ ሠማሃቸው ?» አለኝ

« ምኑን ?»

« ኢየሱስ ሠፌዴን በጢቢኛ ይሞላዋል አሉኮ ።»

« ወይኔ ! ምን ነበር የምጣዱን ጢቢኛ ባላስተረፍነው !» አልኩ ተናድጄ ።

«እኔም በማስተረፋችን የተቆጨኹት አሁን ነው ። ግን...ይኼ ኢየሱስ ዝም ብሎ ከሠጣቸው ለምን እሳቸው ይጋግራሉ ? ኡ ! እማማ ኮኮቤ ስግብግብ ናቸው ማለት ነው ። » አለ ጠይሜ

ከዚያ በሌላ ቀን ቅዳሜ ጠዋት እንደለመድነው እኔና ጠይሜ በጎቻችንንና ኩርቱ ፊስታላችንን ይዘን ወደተለመደው የእማማ ኮኮቤ ግቢ ገባን ። የዛሬው ጩኸትና ጭፈራ ሊላ ነው ። እንኳንስ ጢቢኛቸውን የተሰባሰቡበትን ቤት ጣራ ቆርቆሮ ነቅለን ብንወስድ የሚሠሙን አይመስሉም ። ከአማርኛ የተለየ የማናውቀው ቋንቋ ፤ እልልታ « አሜን ! አሜን ! » የሚሉ ቃላትን እንሠማለን ።

ተረኛው ሰራቂ እኔ ነበርኩና ጠይሜ ከግራ ወደ ቀኝ በግ የሚያግድ እየመሠለ ሰው ይጠብቅልኛል ። የኩሽናው በር ጋር ደርሼ ተመለስኩ ። ጠይሜ ተናደደና «ለምን ተመለስክ ?»



@BOOKALEM

አለኝ ።

« ኩሽናው ተቆልፏል ። »

ደነገጠ ።

« ግን ቁልፍ ማን ሠጣቸው ?» የሚገርም ጥያቄ ጠየቀኝ ።

« ኢየሱስ ይሆናላ ። ለእማማ ኮኮቤ ጢቢኛ ከምጨምርልዎትና ቁልፍ ከምገዛልዎት ብሎ አስ መርጦ ቁልፍ ሳይገዛላቸው አይቀርም ። »

« ሂድ አቦ ጅል ! ኢየሱስ ሱቅ አለው እንዴ ቁልፍ የሚሠጣቸው ? ብር እንኳን የለውም እሺ ። »

« ጠብሻም ነው እንዴ ? »

« ቀሽም ! እንደሱ አይባልም እሺ ! » ሠድቦ ገሠፀኝ ።

ከጠይሜ ጋር መግባባት አልቻልንም ። እኔ « ኢየሱስ ሀብታም ነው ። ብዙ ብር አለው » ሥለው እሱ ደሞ « ሀብታምማ አባባ ጉልላት ናቸው » ይለኛል ።

አባባ ጉልላት ሰባት የጭነት ማመላለስ ሥራ የሚሠሩ ወደል አህያዎች አሏቸው ። የልጅ ልጃቸው ፀሐይም ሁልጊዜ እቤታቸው ሰጋ ወጥ እንደሚሠራ ስለምትነግረን ሀብታምነታቸውን አረጋግጠንላቸዋል ።

ጠይሜ ወዲያው ፌስታሉን ነጠቀኝና « አንተ ሰው ጠብቅልኝ ። እኔ ግን ጢቢኛውን ይዤው ስመጣ ታያለህ !» ብሎኝ ወደ ኩሽናው ኼደ ።

በመጀመርያ እነ እማማ ኮኮቤ የሚፀልዩበትን የትልቁን ቤት በር ከውጭ ቀረቀረባቸው። ከዚያ ወደ ኩሽናው ገባና በቢጫ ፌስታል ተሸከሞ ወጣ ። ወደ ጢሻው ዘለን ገባን ። ልበላ ቋምጫለሁ ። በጎቹም የለመዱትን ለማግኘት ጮኹ ። የኩሽናውን በር እንዴት እንደከፈተው ጠየቅኩት ። ቁልፉ አላዩ ላይ ተንጠልጥሎ እንጂ ተቆልፎ እንዳልነበር ነገረኝ ። ጢሻው ውስጥ ገብተን ፌስታሉን ሲከፍተው ደነገጥኩ ። ፌስታሉ ውስጥ በማዳበርያ የተቋጠረ የስንዴ ዱቄት አለ ።

« ጢቢኛውስ ?» በመገረም ጠየቅኩት

« ጢቢኛ የለም !»

« እና ዱቄት ምን ያደርግልናል ? »

« እንሸጠዋለና !»



@BOOKALEM

« የት ? ለማን ?»

« ለእማማ ትሁኔ ! አረቂ ማውጫ ይሆናቸዋል ... ደብቀን በአምስት ብር እንሸጥላቸዋለን ::»

« ከየት አመጣችሁት ብንባልስ ? »

«ሲስተር ሳባ ሠጠችን እንላለና:: ቆይ ምን አስቦካህ? ኺደው አይጠይቋት ::»

በሲስተር ሳባ ተማመንን :: ሲስተሯ በካቶሊክ ቤተ ክርስትያን አገልጋይነቷና በዕርዳታ ሰጪነቷ ትታወቃለች :: በተለይ ለኛ ለልጆች የተለያዩ ጣፋጭ ብስኩቶችን ፣ የዱቄት ወተት፣ የስንዴና የፋፋ ዱቄት ፣ዘይትና ሌሎች አልሚ ምግቦችን ትሠጠናለች :: የሷን ስም ከጠራን ደሞ ማንም እንደሚያምነን ርግጠኞች ሆነን :: ዱቄቱን ተሸክመን ወደ እማማ ትሁኔ ቤት እየኼድን ሳለ ጠይሜን አንድ ጥያቄ ጠየቅኩት ::

« ዛሬስ ለእማማ ኮኮቤ ዱቄት ነው ጢቢኛ የሚሠጣቸው ?»

« ማ ?»

« ኢየሱስ !»

« አንተ ደሞ ሁሌ ጅል ትሆናለህ :: ዛሬ ኢየሱስ ከእማማ ኮኮቤ ይልቅ ለእማማ ትሁኔ ነው ዱቄት የሚሠጣቸው ::»

« እንዴት ?»

« ይኸው በርካሽ ልንሸጥላቸው አይደል ?»

« እ ! » አልኩት እንደገባኝ ሳረገግጥለት ::

እማማ ትሁኔ ቤት ስንደርስ አስደንጋጩ ነገር ተከሠተ :: የጠይሜ አባት ጋሽ በቂ ተቀምጠው ይጠጣሉ :: ያለ ወትሯቸው ከምሳም ከጫትም ሰዓት በፊት ሲጠጡ አገኘናቸው :: መለኪያቸውን ሲያስቀምጡት ለነገር መሆኑ ገባን ::

«እናንተ ዲቃሎች ! ደሞ ምናባታችሁ ልትሠሩ መጣችሁ ? መቼም ይኼ ሠፈር ደህና ልጅ አይበቅልበት :: እናንተም አረቂ ለመዳችሁልኝ ማለት ነው ? » ብለው ከዘራቻውን መሬት ተመተሙበት ::

« ኧረ አባዬ ! በዚህ ጋር ስናልፍ ውሃ ጠምቶን ነው ልንጠጣ ጎራ ያልነው :: » ጠይሜ ዋሻቸው ::

« ደሞ የማንን ዱቄት ነው የተሸከማችሁት ?»

« ሲስተር ሳባ ሠጥታን ነው !» የጠይሜ ድርቅና ገረመኝ ::



@BOOKALEM

« ለሁለት ተካፈሉ ብላ ?»

«አዎ ! ከረጢት ስታጣ ለሁለታችንም በአንድ ዕቃ ሰጠችን።»

መለኪያቸው ውስጥ ያለችውን አረቄ በአንድ ትንፋሽ ጨልጠው « ይህንን ዱቄት ይዘህ እቤቱ ስትገባ እንዳላይህ ። አንተ ለማኝ የለማኝ ዘር !» አሉት ጠይሜን

ውሃችንን ጨልጠን ስንኼድ መንገድ ላይ « አሮጌ ጫማ ፣ ብልቃጥ ፣ ግሪሲሊ የቅባት ጠርሙስ ያለው ?» እያለ የሚኼድ ሰው አግኝተን ዱቄቱን ሸጥንለት ። ቁራሌው ያገኘውን ነገር የሚገዛ የነጋዴ ዓይነት መሆኑ የገባኝ የዚያን ቀን ነው ።

***

ፍቅሩ ደሞ በሠፈራችን የሚታወቀው ባለበት የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ችግር ብቻ አይደለም። በጉልበት የሚበልጣቸውን ትናንሽ ልጆች ጠዋት ጠዋት እየጠበቀ ጢቢኛ በመንጠቅም ጭምር እንጂ ። አባቱ ከሰው ተግባቢ ፣ ተጫዋችና የተለኮሠ ሲጋራ እንደ ቀለበት ከጣቱ የማይለየው ሰው ነበር ። በሹፍርና ሥራ ቤተሰቡን የሚያስተዳድር ተፈናቃይ ወታደር ነበር የፍቅሩ አባት። እናትየው ደሞ በአንድ የመንግሥት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህርት ነበረች። እንዳለመታደል ሆኖ እናትና አባቱ በማይድን በሽታ ተይዘው ሞተውበታል ።

የእናቱን እናትና ታናሽ እህቱን የማስተዳደሩ ኃላፊነት በፍቅሩ ላይ ወደቀ ። ታላቅየው ወታደርነት ተቀጥሮ ኼዷል ። የት እንዳለም አይታወቅ ። ለቤተሰቡ ሁለተኛ ልጅ የሆነው ፍቅሩ ታናሽ እህቱን በጣም ይወዳታል ። የበለጠ የሚያዝነውም የሚንከባከበውም ግን ደካማዋንና ማየት የተሳናቸውን ሴት አያቱን ነው ።

አንዳንዴ የሸክም ሥራ ይሠራል ። ሠርቶ ያገኛትን ወስዶ ለአያቱ ይሠጣል ። እሳቸውም ደሞ ያቺኑ ለሆዳቸውም ለሱሳቸም ያቋድሷታል ። ሳይከደኑ በማያዩት ዓይኖቻቸው ወደ ሰማይ አንጋጠው ለፍቅሩ ፣ አድራሻው ለማይታወቀው ወንድሙና ለእህቱ ረጅም ዕድሜና ጤናን ፣ ለሟቿ ልጃቸው ከነ ባለቤቷ ደሞ መንግሥተ ሰማያትን ይማፀናሉ ።

ፍቅሩን ከሚፈሩት የመንደራችን ልጆች ውስጥ ረድዔትና ትንሳዔን የሚያክላቸው የለም። የአጎቴ ልጆች ናቸው ። ለዘወትር ማለዳ ቁርስ የተመደበላቸው ሃምሳ ሃምሳ ሳንቲም ነው። ሁለት ሁለት ጢቢኛ መግዣ ። ታድያ ጢቢኛ ለመግዛት በሚኼዱበት መንገድ ላይ አድፍጦ የሚጠብቃቸው አንድ ቀማኛ አለ - ፍቅሩ ሸዋረጋ ።

ሊገዙ ሲኼዱ አይናገራቸውም ። እንዳላያቸው አስመስሎ ያሳልፋቸዋል ። ገዝተው ሲመለሱ ወደ ኋላ እንዳያፈገፍጉ አድርጎ ያስቆምና አንድ አንድ ይቀበላቸዋል ። የገዙት አንድ አንድ ሲበሉ እሱ ግን ሁለት ያሻምዳል ።

ፍቅሩ ጢቢኛቸውን እንደቀማቸው ለቤተሰብ ቢናገሩ እንደሚመታቸው ስላስጠነቀቃቸው



@BOOKALEM

«ተቀማን» ብለው አይናገሩም ። ሁለት ሁለት ሊገዙ ወጥተው አንድ አንድ ይዘው ሲመለሱ መንገድ ላይ በልተውት እንደሆነ ስለሚናገሩ ማንም «ተቀምተው ነው» ብሎ የሚጠረጥር የለም ።

ከፍቅሩ ባህርይ ሌላው በጣም የሚያስገርመኝ ንጹሕ ልብስ የለበሠ ሰው አለመውደዱ። በተለይ እናቶች ያገር ባህል ቀሚስ ለብሠው ፣ አፍንጫን በሚማርክ ሽቷቸው ታጥነው አላፊ አግዳሚውን እያጠኑ ሲኼዱ ከገጠመው ቀስ ብሎ ከኋላ ይከተልና ጭቃ ይለቀልቃቸዋል ። ለአፈር ማራሻ ውሃ ቢያገኝ እንኳን በሽንቱ ያቦካዋል ። አቡክቶም ይለጥፍባቸዋል ።

« ነጭ ነገር ሲመለከት ዓይኑን ስለሚያጭበረብረው ነው እንዲህ የሚያደርገው ። ነጭ ነገር ሲያይ ሠይጣኑ ይነሳበታል !» ይባልለታል ።

ፍቅሩ ከነገሩ ሁሉ ትልቁ እንትኑ ነው ። እንትኑ በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ የብዙዎቻችን ትኩረት ለእንትኑ መሆኑ ይገርመኛል ። እንኳን ወንድ ወንዶቹና አብረውን ኳስ የሚጫወቱት ሔለንና ሠላምም « ፍቅሩ አሳየና » እያሉ ይለምኑት ነበር ።

ያለ ፍርሀት ዚፕሩን ተርትሮ መኾረጥ አድርጎ ሲያወጣባቸውና ወደነሱ ጨብጦት ሲጠጋቸው « ዋይ !» እያሉ ይሮጣሉ ። እኛም ታድያ ያለ ስስት እንትኑን እያየን እንዝናናበት ፤ እንቀናበትም ነበር ። ምን አብልቶ እንዳሳደገውም እንጠይቀዋለን ።

የንግግር ችሎታው ደካማነትም ለሳቃችን መሠረታዊ ምንጭ ነበር ። የተለያዩ ቃላትን እንልለትና ደግሞ እንዲልልን እናደርገዋለን ።

ለምሳሌ « ቴሌኮምዩኒኬሽን » የምትለዋን ቃል እስከ ዛሬ በትክክል ሊላት አልቻለም። «ቶሎ ቶሎ መኬሽን ፣ ቶሎ ቶሎ ኬሽን ፣ቶሎ ቶሎ እንኬሽን » ይላል ። « ሽሪሚሪ » በልልን ስንለው « ውሽሊሊ ! » ይልልናል ። ቢሞከርም የማይሳኩለት በርካታ ቃላት አሉ ። ለሱ ድካም ለኛ ሳቅን የሚያተርፉ ቃላት ።

ሲያኮርፍ አያምርበትም ። ለምቦጩን ብቻ ሳይሆን ንፍጥና ለሀጩንም ነው የሚያዝረበርበው። ሲያኮርፍ ሁሉ ነገሩ ይበለሻሻል ። ፊቱን ቶሎ ቶሎ በጥፊ መጠፍጠፍ ይወዳል ። ዝንብን በጥፊ መትቶ ከጣለ በኋላ በጥርሱ ቅርጭጭ አድርጎ ቆርጦ ይተፋታል ። ሌላው ቀርቶ ሌላ ሰው ላይ ያለች ዝንብም ብትሆን አጥምዶ ይነክሳታል ። መንከስና ቦድሶ መጣል እንጂ በፍጹም ስጋዋን ወደ ሆዱ አያስገባም ።

አንድ ጊዜ እግር ኳስ ተመራርጠን ስንጫወት እንቅፋት መታኝ ። የእግሬ አውራ ጣት ላይ ኃይለኛ የሞቀሞቀ ቁስል መኖርያውን ሠራ ። ለቁስሌ ማሞቅሞቅ ትልቁን አስተዋፅዖ ያበረከተችው ሲትነቷን በባዶ ሜዳ በማስካካት እንጂ እንቁላል በመጣል ማረጋገጥ የተሳናት ዶሯችን ናት ። እቤት ውስጥ ተቀምጬ ከእማዬ ጋር ድፍድፍ እየላስኩ እሷ ትዟዟራለች ። ድንገት ወደ እግሬ ትጠጋና በማንቁሯ ቁስሌን ንቁር ታደርገኛለች ። በርግጥ ንቁሪያዋ እኔን ለመጉዳት አስባ ሳይሆን ቁስሌ ላይ ያረፈችውን ዝንብ ፈልጋ ነበር ። ልትበላት ።



@BOOKALEM

እግሬን ይገፎ « እሪ !» አልኩ ። አውራ ጣቴ ደም በደም ሆነ ። ከዓይኖቼ ብቻም ሳይሆን ከጣቴም እንባ ፈሰሰ ያውም የደም እንባ ። አባቴ አዘነልኝ ። ጭንቅላቴን እየደባበሡ አባበለኝ። ከዚያ ወደ ኩሽና ኼደ ። የእናቴን የምጣድ ማሰሻ ጨርቅ በረመጡ ጠብሶ አምጥቶ እንጀቴ የተንሠፈሠፈበት ቁስሌ ላይ አስቀመጠው ። እሪታዬ ጎረቤቶቻችንን ጠራ ። አጥር የሌላት ግቢያችንን የሠፈር ሰዎች ወረሯት ።

ጩኸቴን ተከትለው ውሻችንና ሌሎቹ ዶሮዎቻችን ተራኮቱ ። ከዚያም የጩኸቴን ምክንያት አባቴ ለመጡት ሰዎች ሲነግራቸው እየተሳሳቁ ወደየቤታቸው ተመለሱ ። ከዚያ ጊዜም ወዲህ የዶሮ ፍቅር ከውስጤ ወጣልኝ ። ዶሮን እንኳን በቁሟ ታርዳም ጠላኋት ። ፀቤን ተንተርሺ ስጋዋን አልበላም ፤ እንቁላሏንም አልጠጣም ።

ፍቅሩ ከፊት ለፊቴ የቀኝ መዳፉን አጠፍ አድርጎ ለአደን ተዘጋጅቷል ። እኔ ደሞ ለአደን ሲዘጋጅ ወሬ እንደማይፈልግ ስለማውቅ ድርጊቱን በጥሞና መከታተል ጀመርኩ ። ተንደርድሮ ብቻ ቁስል አቅም የነሳት አውራ ጣቴ ላይ ሲከመርብኝ ተንገበገብኩ ። ሕመሙ አንጀቴ ገባ ። ለካንስ እሱ ቁስሌን ከብብ አድርገው የሚቦጠቡጡኝን ዝንቦች ሊበቀልልኝ ኖሯል ። ከዚያም እጁ በደሜ ተጨማለቀ ። እዬዬን ሳስነካው ያባብለኝ ጀመር ። ሲያባብለኝ ቢያሳዝነኝም ሕመሙን ስላልቻልኩት ግን ማልቀሴን አልተውኩም ። ዝም አልል ስለው ዝም ሊያስብለኝ አብሮኝ አለቀሠ ።

« ሁለተኛ እንዳታናግረኝ ። ቤታችንም እንዳትመጣ !» ብዬው እያነከስኩ ወደ ቤቴ ኼድኩ ።

ከሰዓት በኋላ በሹራቡ ውስጥ የሆነ ነገር ሸጉጦ እኛ ቤት መጣና በጣፋጭ ኮልታፋ አንደበቱ ጠራኝ ።

« ኺድ ጥፋ ከዚህ ! ሁለተኛ አላናግርህም ። » በሌባ ጣቴ የታችኛውን ከንፈሬን እያፈናጠ ርኩ እንዳኮረፍኩት በምንግባባበት ምልክት ገለፅኩለት ።

« ይጥልታ ! ይጥልታ አልቱህ አይደል እንዴ ጭንጥሎ ?» አለኝ ጭንቅላቱን እየሠበቀ ።

« ያንተን ይቅርታ አልፈልግም !»

« ጦይ ምን አደለቱህ ጭንጥሎ ?»

« ምን አደረግኩህ ትለኛለህ እንዴ? አውቀህ አይደል ቁስሌን ያደማህብኝ ?»

« እዝዳቤልን ! ጭንጥሎ አውጤ አይደለም ። ስንቦቹ ጡስልህን ሲበሉብህ አናደውኝ ነው የደ ደልቱልህ ። »

« ኺድ ውሸታም ! »

« እሲ ! ይጥልታ ጭንጥሎዬ ! »



@BOOKALEM

« አልፈልግም ! ያንተን ይቅርታ ቀቅለህ ብላው እሺ ::»

« ተው ጭንጥሎ ይጥልታ አልድልኝ ?»

«አልፈልግም :: በቃ ኺዳ ከሰው ቤት :: ቀላዋጭ !» ስላናደደኝ ሰደብኩት ::

« ተይዋ ! እኔ ድን ይቺን አምትቼል ስ ነበል :: » አለና ከሹራቡ ሥር የደበቃትን ጢቢኛ አሳየኝ ::

መጨከን አልቻልኩም :: እግርና አንገቴን ወደ ፍቅሩ አቅጣጫ አዙሬ ተመለስኩ :: ለሱ ምንም ሳይበላ እየቀረሰ እያጎረሰኝ አንዷን ጢቢኛ አስጨረሠኝ :: ከዚያም «እወድሳለሁ እሲ ጭንጥሎ !» ብሎ ጉንጬን ሳመኝ :: ታረቅኩት ::

***

ጢቢኛ በመንጠቅ ከሚታወቁት የመንደራችን ጎረምሶች አንዱ ደሞ ዳንኤል ባርያው ነው :: ጥቁር ነው :: ሚካኤል የረገጠውን ሠይጣን ለመምሠል ከሚካኤል ሥር መውደቅ የቀረው ርኩስ:: ሴት ወንድ አይል ሲሳደብ ለአፉ ለከት የለውም :: ወጣት አይል ሽማግሌ ያገኘውን ሲዘልፍ ስቅጥጥ አይለውም ::

በተለይ የኔ ሴት አያትማ መጫወቻ ጠጠሩ ነበሩ :: ከቤተ ክርስትያን ሲመለሱ ይጠብቅና ጢሻ ውስጥ ጭር ካለው ሥፍራ ሲደርሱ «እማማ ስንቄ» ብሎ ይጠራቸዋል ::

« አቤት ! » ብለው ዘወር ሲሉ ይደበቃል ::

አውራ ጣታቸውን አሹለውና ቀሪ አራት ጣቶቻቸውን ጨብጠው ያማትባሉ :: «ምረሽ ! የማርያም ብቅል እየፈጨሁ ነው :: » እያሉ ሲኼዱ በቀኝ ከነበረ በግራ ፣ በግራ ከነበረ በቀኝ አቅጣጫውን እየቀያየረ ፣እየሸወደ ፣ እየተከተለ « ኧረ እማማ ስንቄ አይዋሹ ! ማርያም ጠላ አትሸጥ ብቅል ምን ያደርግላታል !» ይላቸዋል :: አያቴ ግራ ይጋባሉ :: የሚያመልጡበት አቅጣጫ ይጠፋቸዋል :: ይሸሸጉበት ጥግ ያጣሉ ::

« ኧረ ! የዛሬውስ ሠይጣን አንቆ ሊደፋኝ መሠለኝ :: ቅዱስ ጊዮርጊስ ምን አደረግኩህ ? ደጅህን ረግጬ ፣ ማደርያህን ስሜ በተመለስኩ ምኑን አዘዝከብኝ ?» እያሉ እያጉተመተሙ ሲኼዱ አስፈሪ የተለያየ አውሬ ድምፅ እያሰማ ይከተላቸዋል ::

የአያቴን ጋቢያቸውን ሰብስበው ፣ መቋሚያቸውን እንደ ጦር ጨብጠው መሮጥ ካላየ አይተዋቸውም :: ከዚያ በኋላ አያቴ ለተወሰኑ ቀናት መንገድ ይቀይራሉ :: በዚያች ጢሻማ መንገድ ለብቻቸው አይኼዱም ፤ አይመጡም ::

ዳኒ ባርያው አያቴ ከቤተ ክርስትያን ሲመለሱ እጃቸው ላይ የጠበል ኮዳና ፈስታል ካየ አይለከፋቸውም :: እንዲያውም ከመቋሚያቸውም በስተቀር የያዙትን ሁሉ ካልተሸከምኩ ብሎ አቤት ያደርሳል :: ማድረሱስ ባልከፋ ነበር :: ነገር ግን ለኛ የመጣልንን ጢቢኛ ይበላብናል እንጂ::



@BOOKALEM

አያቴን ከፊት ከፊት እያስቀደመ እሱ ከፌስታል ውስጥ ጢቢኛውንም ፣ ንፍሮውንም ፣ የድፎ ቁራሹንም ፣ ቆሎውንም ኪሱ ይጠቀጥቃል ። እቤት ደርሶም ከቀረቸው ይቃረጠናል ።

የሆያ ሆዬ ቡድናችን እኔን ፣ጠይሜን ፣ ጠምበለልን ፣ ኑረዲንን ፣ ሔለንንና ሰላምንም ይይዛል ። ብዙ ጊዜ ታድያ ሔለን ገንዘብ ያዥ ፣ ሠላም ደሞ ጢቢኛ ሰብሳቢ ሆነው በዳኒ ባርያው አስነጥቀውናል ።

ዛሬ የሆያ ሆዬ የመጨረሻ ቀን ስለሆነ ብዙ ጢቢኛና ብዙ ብር እንደምናገኝ እርግጠኞች ነን ። ስለዚህ « ጢቢኛ ያዥ ይቀየር » ተባለና ሃሳብ ቀረበ ።

« ያገኘነውን እዚያው እንብላው ! »የሚለው የጠይሜ ሃሳብ ተከተለ ።

«ምንም ነገር ካጣብን ደሞ ዳኒ ባርያው ከከራችሁት ነው ብሎ ይመታናል።» በማለት ሔለን ስጋቷን ገለፀች ።

ጠይሜ ደፋር ነው ። ምንም አይፈራም ። በጭለማ ውስጥ እንኳን ብቻውን ሲኼድ የሚፈራው ነገር የለም ። እናም ተጨማሪ ሃሳብ አዋጣ ።

« የዚህ የሆያ ሆዬ ባንድ አባላት ስድስት ነን አይደል ?»

« አዎ !» የባንዱ አባላት በጋራ ትክክለኛነቱን አረጋገጠለት ።

« ስለዚህ ስድስት ዱላ አለን ማለት ነው ።»

« እ...ሺ ! ባክህ !» ሰላም ግርምቷን ገለፀች ።

«ታድያ አንዱን ዳኒ ባርያውን ማንቁራጠጥ ያቅተናል ?»

ሁላችንም ደነገጥን ።

« እንዴ ! ለየብቻ ሲያገኘን ግን ጥሬ ስጋችንን ነው የሚበላው !» ሲል ኑረዲን ፍርሀቱን ሊያጋባብን ሞከረ ።

« በቃ ! ምን አንቦቀቦቀህ አንተ ! እሱ ለየብቻችን እየጠበቀ ሊመታን ከሞከረ የትም ስንኼድ የባንዱን ዱላ ይዘን መዞር !» ጠይሜ እንደተናደደ ያስታውቃል ።

« ትምህርት ቤት ስንኼድም ?» ቀጭኑን የሔለንን ድምፅ ገና አሁን ሰማሁት ።

« ባክህ ጠይሜ ይኼ የማያስኬድ ሃሳብ ነው ። ይልቅ እንደዚህ ብናደርግስ ምን ይመስላችኋል?» ጠምቤ አዲስ ሃሳብ ይዞ ከተቀመጠችበት ተነሳች ።

« ምን እናድርግ ? »

«እንዴት እናድርግ ?» ሁላችንም የየግል ጥያቄዎችን ሠነዘርን ።



@BOOKALEM

« የቁልቋል ቅጠል ከነ እሾኩ ቆርጠን በፌስታል እንያዝ ። ከዚያ ትክክለኛውን ጢቢኛ የሚይ ዘው ሰው መሀከላችን ይሆናል ። ቁልቋሉን የያዘው ደሞ ከሠልፉ መጨረሻ ለመነጠቅ ዝግጁ ሆኖ ይጓዛል ። ከዚያ ዳኒ አገኘሁ ብሎ ሲመነትፈን እሾኩ ይወጋውና ይሞታል ። እሱ ከሞተ በኋላ ደሞ ማን አባቱ ጢቢኛችንን ይነጥቀናል ? በነፃነት እየጨፈርን በነፃነት ጢቢኛችንን እን ገምጣለን ።»

ሁላችንም ዳኒን ከገደልን በኋላ በነፃነት ስለምንገምጣቸው የየቡሄዎቹ ጢቢኛዎች እያሰብን ዳኒን በእሾክ ለመግደል ተስማማን ።

ዳኒ ባርያው እንደለመደው በነ መስፍኔና ብርሃኑ ቤት መካከል ባለችው ሸለቋማ መንገድ ተደብቆ በፌስታል የያዝነውን ቁልቋል ነጥቆን ሲሮጥ አደናቅፎት ወደቀ ። እንደ ወደቀ ጮኸ ። ጎረምሳ እያነቀ ሲያሰጮህ እንጂ ሲጮህ ሰምተነው ስለማናውቅ ተደናገጥን ።

የወደቀው እሾኩ ላይ ስለነበር እሾኩ በደረቱና በሆዱ ተሠግሠገ ። ጢቢኛችንን ሲቃማን እንደምናለቅሰው እሱም ሲያለቅስ በማየታችን በየልባችን ተቋጥሮ የነበረው ደስታ ፈነዳ ። ሌሊቱ እስኪጋመስ የሆያ ሆዬ ጭፈራችንን ትተን መዘመር ጀመርን ።

« ኃይል የእግዚአብሔር ነው

ጥበብ የእግዚአብሔር

ማዳን የእግዚአብሔር ።

እንመካም በጉልበታችን

እግዚአብሔር ነው የኛ ኃይላችን ። »



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ሦስት

## ቆጬ

መንደራችንንና ቡድናችንን በቆጬ የምትመራው ስንታየሁ ናት ። «ቆጬ» ማለት የሆነ ዕቃ እንዲገዙ ሲላኩ ባለቤቱ ባልፈቀደበትና ባላወቀበት መልኩ ከገንዘቡ ቀንሶ ለራስ መጠቀም ነው። አሁን አሁን «ቅሸባ» ይባላል መሠለኝ ።

ስንታየሁ ቆጬ መንደራችንን ያስጠራች ፣ በቆጬ ዓመታቷም እስከ ዛሬ የዘለቀች ስመ ጥር ቆጪስት ነች ። «ቆጬ» ድርጊቱ ሲሆን «ቆጪስት» ደሞ ቆጬ መቺውን ግለሰብ ይወክላል ። ልክ «ስፔሻል» ብለን «ስፔሻሊስት» እንደምንለው ።

የአራተኛ ክፍል ተማሪ ሳለን ነበር ስንቴን ለመጀመርያ ጊዜ የተገረምኩባት ። የክፍል አለቃችን ነበረች ። የመማርያ ክፍላችንን ለመወልወል ጋዝ መግዛት ነበረብን ። ቀይ ጋዝ ናፍጣ ። ሁላችንም አስር አስር ሳንቲም አዋጣንና ሠጠናት ። ወደ ስድስት ብር ከሃያ ገደማ ሆኗል ። ሁለት ቀን ብቻ የወለወልንበትን ጋዝ ገዛችና ብሩ እንዳለቀ ነገረችን ።

ሁላችንም አጉረመረምን ። እንዴት እናድርግ ? ብሩን ብንተሳሰባትና ቆጬ መምታቷን ለአስተማሪ ብንናገርባት አለቃ ስለሆነች ሰበብ እየፈለገች ለጋሽ ንጉሴ ታስጠበጥበናለች ። ጋሽ ንጉሴ ጥቁር ጉማሬ ካልያዘ ወደ ክፍል አይገባም ። የአንድን ሰው ምክንያት እንኳን የሚጠይቀው በጉማሬው ከገሸለጠ በኋላ ነው ።

በየሰበቡ ላለመለጥለጥ ሰግተን የሆዳችንን በሆዳችን ይዘን አለፍናት ። እርስ በርስ ስንገናኝ ግን ስንቴን ከመቦጨቅ አንቦዝንም ። ሴብነቷን እያሰብን በሌለችበት እናብጠለጥላታለን ።

ታድያ አንድ ቀን ጋሽ ንጉሴ ስንቴን ኒያላ ሲጋራ እንድትገዛለት ይልካታል ። ከትምህርት ቤታችን አጠገብ ከምትገኘው « መገናኛ ሱቅ » ግስላ ሲጋራ ገዝታለት መጣች ። ኒያላ ሁለቱ ስሙኒ ሲሆን ግስላው ደሞ አንዱ አስር ነበር ። ጋሼ ያልታዘዘችውን በመግዛቷ ቢናደድም ይበልጥ የተናደደው ግን መልሱን ባለመስጠቷ ነበር ።

« እሺ መልሴን » አላት ።

« መልስ የለውም ። አራቱ ሽልንግ ገብቷል ።» ብለውኛል አለችው ።

ጋሼ ብግን ብሎ የተገዛለትን ሲጋራም ሳይለኩስ ገዋኑን እንደለበሠ ወደ ሱቅ ሄደ ። ስንቴ እጁ ላይ ይዛው የነበረውን ጠጠር ከረሜላ እንድይዝላት ሠጠችኝ ። ጠምበለል ደሞ «ካልበላነው» አለኝ ። በላነው ። ጋሼ ሲመጣ ጆሮዋን ጠምዝዞ ጥቁር ሠሌዳው ላይ እጇቿን ዘርግታ እንድትቆም



@BOOKALEM

አዘዛት ። ከዚያማ በዚያ እህል ውሃ በማያሠኝ ጉማሬው እየለጠለጠ

« በገንዘቤ የገዛሽው ከረሜላ የታል ?» ሲል አፈጠጠባት ።

ወደ እኔ ጠቆመች ። ሽምጥጥ አድርጌ ካድኩኝ ።

« እስቲ አፍህን ከፈት !» ቁንጮዬን ይዞ ወደ ኋላ መዘዘኝ ።

ምላሴን ወደ ላንቃዬ አጥፌ ከፈትኩለት ። አልተመቸውም ። ምላሴን ዘርግቼ አፌን እንድከፍት እንደ ጨረር በሚያቃጥል ዓይኑ እያየ አዘዘኝ ። አደረግኩት ። ወደ ውጭ ያወጣሁትን ምላሴን ሳልሰበስብ በጉማሬው ቂጤን አላሠኝ። ከረሜላዬ ጩኸቴን ቀድማ መሬት አረፈች ።

ጠምበለልን ጠቆምኩ ። ተለጠለጠ ። እንባ በእንባ ሆንን ።

ስንታየሁ ቆጮ መሀላችን እንድትቆም ታዘዘች ። ከዚያም እጃችንን እንድንያያዝ ተነገረን ። አደረግነው ። ከጋሼ የሚተላለፈውን የመሀላ ቃል ደግመን እንል ጀመር ።

«...ከዛሬ ጀምሮ ቆጮ መትተን ከተገኘን በተማሪዎች ፊት አርባ እንገረፍ !» ብለን ማልን። የዛሬውንም ስላልቆጠርኩት ይሆናል እንጂ ዱላውስ ከአርባ አምስትም ሳያልፍ አይቀርም ። በጓደኞቻችን ዘንድም « የቆጮ ኅብረት ሥራ ማኅበር አባላት » የሚል ቅፅል ስም ለሦስታችንም ፀደቀልን ።

ስንቴ በቆጮ ረገድ ምሩቅ ነች ። ያለ ቆጮ የተገዛ ነገር የሚበረከት ሁሉ አይመስላትም ። የምትገዛውን ዕቃ የምትባርከው በቆጮዋ ነው ። እድገን እንኳን ስሟ አልቀረላትም ።

የአስር ሳንቲም የማሽላ ፈንዲሻ ለቡና ቁርስ እንድትገዛ ተልካ አምስቷን ሳንቲም ቆጮ የምትመታ ጨካኝ ነች ። ለነገሩ የቆጮ ነገር ከተነቃ ብቻ ነው የሚደብረው ። በተረፈ ካልተነቃ አሪፍ የገቢ ምንጭ መሆኑን አልከድም ። የቆጮ ማኅበራችን ተደራጀና አባላቱን በፆታም፣ በቁጥርም ፣በቴክኒክም አጎለበተ ።

መሪያችን ስንቴ ነች። እሷን መሪ ያደረግንበት ዐቢይ ምክንያት ድፍረቷን ተማምነን ነው። እንዴ! ለአስፈሪው ለጋሽ ንጉሴ ጉማሬ እንኳን እኮ አልተርበተበተችም ። የተለያዩ የቆጮ አመታት ዘዴዎችን ታሠለጥነናለች ። ሰዎች ለምነውን ወይም በግድ ለምነናቸው ካልተላከንላቸው ቆጮ ሊገኝ እንደማይችል ትነግረናለች ። ትሁት ፣ ታማኝ ፣ታዛዥ መስለን እየቀረብን ከተላክነው ላይ መቀነጫጨብ የግድ መሆኑ ተነግሮናል ። ችግሩ ግን ቆጮ መትተን ካሰባሰብነው ብር ላይ መልሳ ስንቴ ቆጮ ትመታናለች ። በናታችሁ የቆጮ ቆጮ ግፍ አይደለም በማርያም ።

አንድ ጊዜ የሆነ ወርቃማ ዕድል ገጠመኝ ። ሙሉነህና ኪድር የሚባሉ ወንደ ላጤዎች አጎቴ ቤት ተከራይተው ይኖሩ ነበር ። ምን እንደሚሠሩ ባላውቅም ውለው የሚገቡበት ሥራ እንዳላቸው ግን አውቃለሁ ። ብዙ ቀን የተለያዩ ሴቶችን እያመጡ በር ዘግተው ከውስጥ ሲቀመጡ አይቻለሁ ። ሲያስሙኗቸውም ሰምቻለሁ ። እንዲያውም አንድ ቀን ጢይሜ «እስቲ



@BOOKALEM

በር ዘግተው ምን እንደሚሠሩ እናዳምጥ» ብሉኝ እኔ ከበሩ እሱ ደሞ ከመስኮቱ ላይ ጆሯችንን ለጥፈን ስናዳምጥ አጎቴ አግኝቶ ለጥልጦናል ።

ታድያ የሆነ ቀን ሙሉነህና ከድር እቤታቸው ጠሩኝ ። ዳቦ በሙዝ ሠጡኝና በላሁ ። በጣም ጥሞኛል ። ደሞ እንደዚህ በልቼ አላውቅም ነበር ። በአንድ ጊዜ ወይ ዳቦ ወይ ሙዝ ነው በልቼ የማውቀው ። ሁለቱንም በአንዴ ግን ገና የዚያን ቀን ነበር የበላሁት ።

በልቼ እንደጨረስኩ ገበያ ሲልኩኝ እንደሆነ ነገሩኝ ። ተደሠትኩ ። « ቆጬ ተገኘ » አልኩት እራሴን ።

« በርበሬና ሽሮ ገዝተህልን ና !» አለኝ ሙሉነህ ከኪሱ ሃያ አንድ ብር አውጥቶ ።

« ስንት ስንት ነው የሚሸጠው ?» እዛገቶን ሙሉነህን ጠየቅኩት

«በርበሬው በጣሳ አስራ ሁለት ብር ፣ሽሮ ደሞ ስምንት ብር ።»

እሺ ! አስራ ሁለትና ስምንት ሃያ መሆኑን ጣቴን ቆጥሬ ከደረስኩበት በኋላ « እቺስ አንድ ብሯ ?» ሉብቻዋ አንጠልጥዬ እያሳየሁ ጠየቅኩት ።

« እሷማ የተላከባት ያንተ ነቻ ... ሳምቡሳ መብያህ !»

ባልተለመደ መልኩ ለጥ ብዬ እጅ ነሳሁ ። ፌስታልና ብሬን ይገ፤ እማማ ቆርቆምቤ ጋር ሄድኩኝ። የማይሸጡት ነገር የለም ። የእንጀራና የዳቦ ድርቆሽ ፣ ሽሮ ፣ በርበሬ ፣ ሚጥሚጣ ፣ በሶ፣ ጨው ፣ ቁጢ (የቡና ቅጠል)፣ የወይራ እንጨት...ብቻ ነፍ ነገር ነው የሚሸጡት ። ከጎናቸውም ብዙ የሽሮና በርበሬ ሻጮች አሉ ። ሁሉም ጋር ያለው ሽሮና በርበሬ የተለያየ መጠን ባላቸው ጣሳዎች እየተሞላ ተቀምጧል ። መምረጥ አቃተኝ ።

የሁሉንም ዋጋ ጠየቅኩ ። ትልቁ ጣሳ በርበሬ አስር ብር ፣ ሽሮ ደሞ ስድስት ብር ነው ። እነ ሙሉነህ ከገመቱልኝ አራት ብር ትርፍ አገኘሁ ። ግን ያረካኝ አልመሠለኝም ። ከዚያ የስምንት ብር በርበሬና የአምስት ብር ሽሮ ይገፄላቸው ሄድኩ ። ሥራ ሄደው ስለነበር በራቸው ላይ ፌስታሉን አስቀምጬ ወደ ቤቴ ተመለስኩ ።

የያዝኩትን የቆጬ ብር ፈራሁት ። በሕይወቴ የራሴ የሆነ ስምንት ብር ይገ፤ አላውቅም ። ምን ምን እንደምገዛበት ሁሉ አልገባኝም ። ለቆጬ ማኅበራችንም ስንቱን ገቢ ማድረግ እንዳለብኝ አልወሠንኩም ። ግን ከቆጬ ማኅበራችን ቆጬ መምታት እንዳለብኝ እራሴን አሳምኜዋለሁ። ሁሉንም ገቢ ካደረግኩ በማኅበራችን ከፍተኛ ብር ያስገባሁ ብቸኛ ሰው እንደምሆን አውቀዋለሁ። ግን ማንም ያገኘውን በሙሉ ስለማያስገባ እኔስ ለማን ደስ ይበለው ብዬ ባዶዬን ልቅር ።

ምሽት ላይ የአጎቴ ልጅ ፍላጎት መጥታ እነ ሙሉነህ እንደሚፈልጉኝ ነገረችኝ ። « ከተነቃ አልገደድም !» ብዬ እራሴን አሳምኜ በድፍረት ሄድኩ ። በራቸው ላይ ያስቀመጥኩላቸው ሽሮና በርበሬ አልደረሳቸውም። ጠፍቷል ።



@BOOKALEM

« አስቀምጬው ነበር !» ብዬ ተናገርኩ ። ሁለቱም አላመኑኝም ። ከድር የራስ ቅሌ እስኪያብጥ ዘነዘና በሚያክል ሻካራ እጁ ኮረኮመኝ ። አለቀስኩ ። አንቴም ዕዳውን ከፈለ ።

የቆጮ ማኅበራችን ተሰባስቦ በዕለቱ ገቢው ላይ ሲወያይ ጠይሜ ዛሬ እኔ አንት ግቢ ውስጥ የሠራውን ጀብድ ተናገረ ። እኔን ፍለጋ ሄዶ ተከራዮቹ እነ ሙሉነህ በር ላይ ሽሮና በርበሬ ተቋጥሮ አግኝቶ ለእማማ ትሁኔ በአራት ብር እንደሸጠው አወጀ ። አናደደኝ ። የማኅበራችን አባላት ሲሳሳቁ እኔ ግን የከድርን ኩርኩም አስታውሼ ጭንቅላቴን አሻሸሁ ።

***

የጠምበለል እናት ጉልት ሽንኩርት ፣ ድንች ፣ ከሠል ምናምን ይሸጣሉ ። ካሏቸው ሦስት ልጆች ውስጥ በጣም የሚያምኑት ጠምቤን ነው ። ጠምቤ ፍጹም ታማኝ መሆኑን ይመሠክሩለታል። ማታ ጉልት አምሽተው ሲመለሱ ቀኑን ሙሉ የሠሩበትን ገንዘብ የመቁጠር ኃላፊነቱን ለሱ ይሠጡታል ።

እሳቸው ቡናቸውን እያፈሉ የባቄላ አሹቅ እያጎረሱት ብራቸውን ይቆጥርላቸዋል ። ሲቆጥር ግን ብር ብሮቹን አልፎ ፣ አልፎ እየደረበ ይቆጥራል ። ደርቦ ያሳለፋቸውን ብሮች ቁጥር ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ወደ ሙዳያቸው ሊያስገባ ሲኼድ ቀንሶ ወደ ምስጢር ኪሱ ይጨምራል ። ሳንቲሞች ከሆኑ ደሞ በእግር ጣቶቹ መሀል ቆንጥጦ ይይዛቸዋል ። ጉንጩም የገንዘብ መደበቂያው ነው ።

ከማኅበራችን መሪ ከሰንታየሁ ቆጮ በተላለፈልን ጥብቅ ትዕዛዝ መሠረት በቆጮ የተገኘ ገንዘብ በምንም ዓይነት ሁኔታ ኪስ ውስጥ አያድርም ። የተለየ የማጠራቀሚያ ሥፍራ አለው ። የሱሪያችንን ወገብ ቀብቶ የምንታጠቅበትን ከፍል ለቆጮ ማከማቻ እንጠቀምበታለን ። ድርብ ነው ። ሥለዚህም ከመቀለፊያው የመጀመርያ ጫፍ ላይ እንበሳውና ያገኘነውን እንከከርበታለን ። ያቺን ቦታ ማንም ጠርጣሪ ነኝ ባይ ሊደርስባት የማይችል የምስጢር ባንካችን ናት ።

አንድ ቀን ጠይሜ በቆጮ ያጠራቀመውን ገንዘብ የምስጢር ኪሱ ውስጥ እንዳስቀመጠ እናቱ ልብሱን ልታጥብ ታነሳበታለች ። ይደነግጣል ። ከዚያ ከእናቱ ጋር ግብግብ ይገጥማል ።

« ይታጠብልህ ! እንዲህ አመድ መስለህ እየሄድክ አታሠድበን ።»

« ሳይቆሽሽ አይታጠብማ ። ልብሴን ልትጨርሺብኝ ነው እንዴ?»

« ቆይ አንተ እዚህ ልብስ ላይ ቆርበሃል ?» ብላ ሱሪውን መነጨቀችው ።

ማላዘን ጀመረ ።

«እኔምን አገባኝ ። አመድ ላይ ሲንደባለል የዋለ ገጣባ አህያ የምትመስል ...የምትሠደበው አንች! አመዳም!» አፍንጫው ላይ ወረወረችለት ።

ከዚያ ቀስ ብሎ አዲስ የሚቀይረው ልብስ ውስጥ ብሩን ከኮ/ረ በኋላ « እኔ ግን እንዳንቺ



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

አይደለሁም እሺ ! ያው እጠቢ !» ብሎ ወረወረላት ::

« አመዳም የአመዳም ዘር ! አሽከርህ መሠልኩህ እንዴ ? እናትህኮ ነኝ አንተ ቡቱቷም :: ሰው ላስመስልህ ፤ ያለህን አጥቤ አልብሼ ከጓደኞችህ ላቀራርብህ ብዬ ነው እንጂ...» ንግግሯን ሳትጨርሠው ሱሪውን ውሃው ውስጥ ነከረችው ::

***

በተለየ የቆጮ አመታቱ የሚታወቀው መሠለ ነው :: መሴ ለቤተሰቦቹ የማይታዘዝ ሲሆን የውጭ ሰዎች ግን ትህትናውን አብዝተው ይመሠክሩለታል :: ትምህርቱን ገና ከሦስተኛ ክፍል ነበር ያቋረጠው :: አባቱን እኛም እሱም አናውቃቸውም :: ታናናሽ እህትና ወንድሞች አሉት:: እናቱ ሰው ቤት እየተዟዟረች ልብስ በማጠብ ፤ እንጀራ በመጋገር ፤ የጠላ አሻሮና እንኩሮ በማዘጋጀት ነው ቤተሰቧን የምታስተዳድረው ::

እነ አቤል ቤት ተቀምጠን እንጫወታለን :: ከፊት ለፊታችን በሳፋ የተሞላ ዘይቱና ተቀምጧል:: ወደ ገበያ ተወስዶ ከሚሸጠው በተጨማሪ ቤት ድረስ እየመጡ የሚሸምቱት ልጆች ይበዛሉ :: እኔም ፤ መሴም ጠይሜም በዘይቱናው ቋምጠናል :: መግገ ገንዘብ ስለሌለን በሳፋ የተሞላውን ዘይቱና በማየት ብቻ ለመርካት ሳንነጋገር በየልቦናችን ወስነናል ::

መሴ ከዘይቱናው በቅርብ ርቀት ተቀምጧል :: ደጃፍ ላይ ያለችውን መሬት የምትጭር ዶሮ አሳየን :: እኔም ፤ ጠይሜም ፤ አቤልም ፊታችንንና ቀልባችንን ወደ ዶሮዋ አደረግን :: የየራሳችንን ሃሳብ ለመስጠት ወደ መሴ ዞወር ስንል በግንባሩ ተደፍቶ ፀሎተኛ መስሏል ::

« መሴ ! ምን ሆንክ ?» ጠይሜ ደንግጦ ጠየቀው ::

« ፀሎት ላይ ነኝ አትረብሸኝ ! » አለ

ድምፁ ወፈር ብሏል ::

ፀሎቱን ጨርሶ ቀና ሲል ሦስታችንም ባየነው ነገር ተሳሳቅን :: እሱ ግን አማተበ :: አገጩና ከንፈሩ ላይ ሁለት ሁለት ቀያይ የዘይቱና ፍሬዎች ተለጥፈዋል ::

መሴ አቤልን ሁሌም እንዲህ ነው የሚሸውደው :: በጉልበቱ እየተንበረከከ ፤ በግንባሩ እየተደፋ ፤ ፀሎተኛ እየመሠለ ዘይቱናቸውን ይሠለቅጣል ::

@BOOKALEM

# ምዕራፍ አራት

## ዲናሬ

ከልጅነቴ የጀመረውን ምስጢር ጠባቂነቴን ውስጤ የዘራችው እህቴ ነች ። ለነገሩ « ምስጢር ጠባቂነት » ከምለው « ዋሾነት » ማለቱ ሳይሻል አይቀርም መሠለኝ ። ነፍ «ቦይ ፍሬንዶች» እንደነበራት የገባኝ ካደግኩ በኋላ ነው ። ወደ ወንዶቿ ስትሄድ ለምን እኔን እንደ ዘንቢል እንደምታንጠለጥለኝ አሁን አሁን አይገባኝም ። ድሮ ግን ጥላኝ ስትሄድ ነበር የሚከፋኝ ።

መሳይ ታላቂ ናት ። ስትዘፍን ድምጿ ደስ ይላል ። ስትደንስም ይዋጣላታል። ቂጧን እየነቀነቀች ሥትውረገረግ ትገርማለች ። ጥቁር ሆና ቆንጆም ናት ። በቀበሌ ኪነት ውስጥ ተሳትፋ ሕዝቡን ታነቃንቀው ነበር ። ለእናት ሀገር ጥሪ ትዘፍናለች ። ለእናት ሀገር ጥሪ ሥትዘፍን ከሀገሪቱ ይልቅ ጥሪዋን የሚሠሙት ወንዶቿ ናቸው ።

ከመድረከ እንደ ወረደች እቤታቸው ያሰናዱትን አንሶላ የለበሰ መድረከ አብራቸው እንደ ልቧ ትሆንበት ዘንድ ይፈቅዱላታል ። እኔም በአስር ሳንቲም ጠጠር ከረሜላ እየተሸረደድኩ እስከ መድረኳ እሸኛታለሁ ።

እስጢፋኖስ ወታደር ነው ። ምያተኛ ወታደር ። የመኪና ሀኪምና ሹፌርም ጭምር ። አዲስ አበባ ተወልዶ አድጎ በእንጀራው ገመድ ተጎትቶ ወደ ሐረር መጣ ። መጥቶም እኛ ሠፈር ከአጎቴ ቤት ጀርባ ያለውን የቀበሌ ቤት ከግለሰብ ተከራየ ። አንድ ከፍል ቤቱ ውስጥ ብቻውን በወንደላጤነት ይኖራል ።

መሳይን ሁልጊዜ እቤቱ ያስገባና በሩን ከውስጥ ይቆልፋሉ ። እኔን «ሜዳ ከልጆቹ ጋር ኳስ ተጫወት » ይሉኝና ዲናሬ ሠጥተው ይሸኙኛል ። ብዙ ቀን ነው እንደዚህ የሚያደርጉት ። እኛ ቤት ግን ቀን ቀን በር ከውስጥ ተቆልፎ መቀመጥ አይቻልም ። ማታ ልንተኛ ከሆነ ብቻ ነው በራችን ከውስጥ የሚቆለፈው ።

የሆነ ቀን እስጢፋኖስ ዲናሬ (አስር ሳንቲም) ሠጠኝና ሜዳ ከልጆቹ ጋር እንድጫወት ነገረኝ ። በተሠጠኝ ዲናሬ አስር ጠጠር ከረሜላዎን ገዝቼ ስጫወት የአጎቴ ሠፈር ልጆች ከረሜላ እንድሠጣቸው ለመኑኝ ። አልሠጣችሁም ብዬ ግግም አልኩ ። ሲመካከሩ ጊዜ በኪሴ የከተትኩትን ከረሜላ በሙሉ አውጥቼ አፌ ጨመርኩት ። ጉንጬን በጣታቸው ፈልቅቀው ከአፌ ውስጥ ነጠቁኝ ። ከረሜላዎቹ የተለወሱበትን ምራቄን እየጠራረጉ በሏቸው ። በራሴ ከረሜላ እያቁለጨለጩኝ ሮጡ ። እርር ብዬ አለቀስኩ ።

እንባዬን እያዘራሁ ወደ እህቴ መጣሁ ። በሩ እንደተቆለፈ ነው ። አንኳኳሁ ፣ አንኳኳሁ ። አልከፍት አሉኝ ። ቀስ ብዬ ጆሮዬን ወደ ውስጥ ጣል ሳደርግ የእህቴን የሲቃ ድምፅ ሰማሁ ። ጆሮዬ እንደ ውሻ ጆሮ ወሬ ለመሰብሰብ እጥፍ ዘርጋ ሲል ተሰማኝ ።



@BOOKALEM

« አ ! አ ! አ ! እስጢፍዬ በናትህ ! በናትህ ! አ ! ቀስ ! ቀስ !» ትላለች ።

ደነገጥኩ ። እስጢፋኖስ እህቴን እያደበደባት እንደሆነ ገባኝ ። በሩን በድንጋይ አንጓጓሁለት። በፍጥነት በሩን ከውስጥ ከፈተና ማጅራቴን ጨምድዶ ጎትቶ አስገባኝና በሩን ወርውሮ ዘጋው። ከወገቡ በላይ ልብስ አልለበሰም ። ከደረቱ እስከ ሆዱ በፀጉር ተሸፍኗል ። አውሬ መሠለኝ ። ቅድም በር ከመዝጋታቸው በፊት ሱሪ ለብሶ ነበር ። አሁን ደሞ ቁምጣ ። መሳይ አልጋው ውስጥ ተኝታለች ።

« ምን አባክ ሆነህ ነው በር የምትደበድበው ?» አለችኝ

« ስታለቅሺ ሰምቼ ላስጥልሽ ነዋ !»

የለበሰችውን አንሶላ ገለጥ ሳደርገው እቤት ገላዋን ስትታጠብ እንደምታደርገው ናት ። ራቁቷን። ፀጉሯ ተበታትኗል ።

« ገላሽን ታጥበሽ ነው እንዴ ?»

« ጭንቅሎ በጠበጥከን እኮ ! ገላችንን እየታጠብን አንተ በሩን ስትደበድብ ሳሙናው ዓይኗ ውስጥ ገብቶባት'ኮ ነው ያለቀሠችው ።» አለኝ እስጢፋኖስ

« አንተም ታጥበህል እንዴ ?»

« እዎና !»

« ታድያ ከነ ልብስህ ነው እንዴ የታጠብከው ? ለምን እንደሷ ራቁትህን አልሆንክም ?»

ደነገጠ ።

« ቆይ ግን ጭንቅሎ ሳትጠራ እንዳትመጣ አላልኩህም ነበር ? ደሞስ ምን ሆነህ ነው ያለቀስ ከው ?» አለችኝ መሳይ

« ከረሜላዬን ነጥቀውኝ ነዋ !»

« እነ ማን አባታቸው ?»

« የዚህ የታች ሠፈር ልጆች ናቸዋ ። ቆይ ነገ ከጠይሜና ጠምበለል ጋር ሆነን ውግር ባናደርጋቸው ሞቼያለሁ ።» በቀኝ እጄ የተጨበጠ ቡጢ የግራ መዳፌን ቦቀስኩት ።

« በቃ አሁንም ሂድና ሜዳ ተጫወት ። ስንጠራህ ብቻ ነው እሺ የምትመጣው ።»

ደረቁ የመሳይ አሸኛኘት አልተመቸኝም ። መጫወት እንደማልፈልግ ነገርኳት ። ርስ በርስ ተያዩና ተጠቃቀሱ ። ለመኑኝ ። በእምቢታዬ ፀናሁ ። እስጢፋኖስም ለመነኝ ። አልሄድም ብዬ ግግም አልኩኝ ። ከተሰቀለው ኮቱ ኪስ ዲናሬ ሲያወጣ ፈገግታ ጨመርኩ ። ሌላ አስር ጠጠር



@BOOKALEM

ከረሜላ ልበላ መሆኑ ሲገባኝ ምራቄን ዋጥኩ ። ከረሜላውን ከገዛሁ በኋላ ለማንም ሳላሳይ ቁጭ ብዬ ብቻዬን ጭፍጭፍ ሳደርገው ታየኝ ። ጎመዠሁ ።

« ሱቅ ልላክሃ ጭንቅሎ ?» አለኝ እስጢፋኖስ

ደስ አለኝ ። ደግ እንደሆነ አውቃለሁ ። ሁሌም ከእህቴ ጋር በር ዘግተው ሲቀመጡ « እደጅ ተጫወት » እያለ ዲናሬ ይሠጠኛል ። አሁንም ዲናሬዋን በእጄ አስጨበጠኝ ።

« ቶሎ ብለህ ሠንደል ገዝተህልኝ ተመለሥ !»

« እ !» በትዕዛዙ ያልተጠበቀ መሆን ደንግጫለሁ ።

ሳቁን ለቀቀው ። መደንገጤ ሳያስደነግጠው አልቀረም ። ፍላጎቴን የተቃረነ መልዕክት እንደላከኝም ገብቶታል መሰለኝ ። መሳይም ተከትላው ሳቀች ።

« ኣ ኣይ ! እኔ ሱቅ አልሄድም ።» አልኩና አልጋው ላይ ተቀመጥኩ ። እግሬን እያወዛወዝኩ ከአየሩ ጋር መጫወት ጀመርኩ ።

« ለምንድን ነው ሱቅ የማትሄደው ?» አለችኝ መሳይ

« ልጆቹ ይመቱኛላ ።»

« የትኞቹ ልጆች ?»

« የታች ሠፈሮቹ ።»

« ትፈራቸዋለህ እንዴ ! የኔ ወንድም ሆነህ ?»

« ኸረ እናታቸውን...አልፈራቸውም !»

« እና ካልፈራሃቸው የተላከውን ገዝተህ አምጣልና !»

ትከሻዬን ሠብቄ እምቢታዬን ገለፅኩ ።

« እሺ በቃ ! እኔ ሠንደል ግዛልኝ ያልኩህ የቀልዴን ነው ። እቺ ዲናሬ ያንተ ነች ። የከረሜላ መግዣህ እሺ ጭንቅሎ ! » አለኝ እስጢፋኖስ ።

ዘልዬ ጉንጩን ሳምኩት ። ጉንጩ ላይ የቀባሁትን ለሀጬን በእጁ ጠራረገ ። በሩን ከፍቼ ልወጣ ስል እስጢፋኖስ አስቆመኝ ።

« ከረሜላውን ከገዛህ በኋላ የት ነው የምትሆነው ?»

« ሜዳ !»

« እኛ ጋር አትመጣም ?»



@BOOKALEM

« ሽረ ! አልመጣም ::»

« ለምን ?»

« መጫወት እፈልጋለሁኛ !»

« ብራቮ ጭንቅሎ ! ቤቃ አሁንም እንደ ቅድሙ መጥተህ በር ካላንኳኳህ ወደ ቤት ስትሄዱ ሌሎች ሁለት ዲናሬዎችን እሠጥሃለሁ ::»

ቃል ገባልኝ :: ተስማምቼ ወደ ሜዳ ሄድኩ :: ሌሎች አስር ወይም ሃያ ጠጠር ከረሜላዎችን እየበላሁ ወደ ቤቴ እንደምሄድ ለትንሿ ነብሴ ስነግራት ፈነደቀች :: የዲናሬዎቼ ሁሉ ምንጭ መሳይ በመሆኗም ወደድኳት :: እህቴ በመሆኗም ኮራሁባት ::

ወደ ቤታችን ስንመለስ በእህቴ አሠልጣኝነት ብዙ ውሸቶችን ተማርኩ :: ለወላጆቻችን የ«የት የት ውላችሁ መጣችሁ ? ምን ምን ስትሠሩ ቆያችሁ ?» ጥያቄዎች የምሠጣቸውን የውሸት መልሶች አጠናሁ ::

መሳይ የፅሕፈት መኪና ስልጠና ትወስድ ነበር :: ወደ እስጢፋኖስ ቤት የሄድነውም « ታይፕ ቤት ልንኬድ ነው » ብላ እናታችንን አስፈቅዳልኝ ነበር :: ስለዚህም ውሸቴ ሁሉ በ'ታይፕ ' ላይ አጠነጠነ ::

የዚያኔ የፅሕፈት መኪና ምን እንደሚመስል እንኳን ዕውቀቱ አልነበረኝም :: ዳስሼው ቀርቶ አይቼውም አላውቅም :: ስዋሽ ግን ብዙ ጽሑፍ ስጽፍ እንደዋልኩ ተናገርኩ ::

«ለመሆኑ ይኼ ታይብ የምትሉት ነገርዬ እንዲያው ምን ያክላል? ትንሽ ትልቁ ሲደብድበው እየዋለ የማይሠበረው እንዴት ያለ ግዙፍ ቢሆን ነው?»

« ት...ልቅ ነው :: ግ...ብዳ !» ያላየሁትን ያየሁ መስዬ ተናገርኩ ::

« ምጣድ ያክላል ?»

እናቴ ለኛ ከምግብ ማብሠል የዘለለ ሥራ ሥለሌላት ለሷ ትልቁ ነገሯ ምጣዷ ነው :: እማዬ «ዓለም ምን ታክላለች?» ተብላ ብትጠየቅ «ምጣዴን!» ማለቷ አይቀርም :: ምጣድ በኛ ቤተሰብ ውስጥ ትልቅ ቦታና ክብር አለው :: የጉሮሯችን ምንጭ መፍለቂያው ምጣዳችን ላይ ተቀብሯል ::

እኔና እህቴ በእናታችን ጤባነት ተይተን ተሳሳቅን :: በዚህ መሀል አባታችን መጣ :: ሁሌም እንደምናደርገው ከመቀመጫችን ብድግ ብለን ተቀበልነው :: የሆነ የተከፋበት ነገር በሆዱ እንደያዘ ፊቱ ያሳብቅበት ነበር :: ሲናደድ የደም ስሮቹ ተገታትረው ፣ አረንጓዴ ደም ቋጥረው ፣ ግንባሩን አፈሩ ከድቶት ሥሩ ያገጠጠ የጠወለገ ዋንዛ ያስመስሉታል ::

« ጭንቅሎ ! ና ወደዚህ ! የት አባክ ነው የዋልከው ዛሬ ?» አፈጠጠብኝ ::



@BOOKALEM

« የትም !»

« አኮ የትምማ እንደዋልክ ሠምቼ ነው የምጠይቅህ ። ምን ልታደርግ ነው አጎትህ ሠፈር እያ ለቀስክ የሰው በር ስትደበድብ የዋልከው ?»

እኔም መሳይም ደነገጥን ።

« ኧረ ! ውሸት ነው ። እሱ ከኔ ጋር ‹ታይፐ› ቤት ነው የዋለው ።» አለችው፡፡ አስማላት ።

ማለችለት ።

አመነን ።

አባቴ ከመሳይ ጋር በተያያዘ የፈለገ ከባድ ነገር ቢገጥመው ዱላ አያነሳባትም ። ያስምላትና ያምናታል ። ስትናደድ ሠይጣኗ ያስጮሃታል ። እንደታረደ ዶሮ ያንደፋድፋታል ። እንደሞተ ፀጥ ያደርጋታል ። አትንቀሳቀስም ። ፀበል ይረጭባታል ። ለሁለት ለሶስት ቀን ታኮርፈዋለች ። ለምኖ፣ ስልቫጅ ገዝቶላት ይታረቃታል ።

***

ጌትነትም በቀበሌ ቤት ውስጥ የሚኖር ወንደ ላጤ እንደነበር ትዝ ይለኛል ። ቤቱ በጣም ታምራለች ። በጣም ትልቅ «ቴፐ ሪኮርደር» አልጋው አጠገብ ከምትገኘው ኮመዲኖው ላይ አስቀምጦ የአፍሪካ ሙዚቃ ይለቅበታል ። ብልጭ ድርግም የሚል መብራት እንደ ሐረግ ግድግዳው ላይ ተንጠልጥሎ ቤቱን ያደምቅለታል ። የሚያጫጭሠው ሠንደል ከቤቱ ውጡ ውጡ አያሠኝም ።

ልክ ጌትሽ ቤት እንደደረስን መጀመርያ ምግብ ይቀርብልናል ። በተለይ ማካሮኒውን እየከካ የሚሠራው ቂንጬ እጅ ያስቆረጥማል ። እንዲያውም አንድ ቀን እኛ ቤት ለአራት ማካሮኒ ተገዛ። እናቴ በትልቅ ድስት ውሃ ሞልታ ምድጃው ላይ ስትጥድ

« ለምን የማካሮኒ ቂንጬ አትሠሪም እማ ?» አልኳት ።

«እንዴት ነው እሱ ደሞ የመኮረኒ ቂንጬ የኔ ሴታ ሴት ?» አለችኝ ማገዶውን እየቆሰቆሰች ።

« መጀመርያ ሽንኩርት ትልጪያለሽ !»

« እሺ !»

« ከዚያ ትከትፊዋለሽ ።»

« እና ድንች አረግከው ሳይከተፍ የሚቀቀል ? ጅል !»

« እሺ ! በቃ ባጭሩ ልንገርሽ ።»



@BOOKALEM

« ቀጥላ ! አዘበዝባለሁ ብትል ግን ወዮልህ !»

«በቀላሉ አረፍ ፤ የሚጣፍጥ ቁሌት በእርድ ትሠሪና ውሃ ትጨምሪበታለሽ ::»

« ከዚያስ ወይዘሮ ጭንቅሎ ?»

« ከዚያማ ውሃው ሲፈላ ማካሮኒውን ጨምረሽ ማንፈቅፈቅ ነዋ ! ሲበስል ታወጪውና እንነፋዋለና !» አልኳት በእጄ ቶሎ ቶሎ አከታትሎ የመጉረስ ምልክት እያሳየኋት ::

« የሚነፋ ይንፋህና ! ሂድልኝ ወዲያ ! ለመሆኑ ይህን ምግብ የት በልተኸው ነው እንዲህ ሳይሠራ ባየር ላይ አጣፍጠህ ምራቅህን የዋጥከው ?»

« እ...እዛ ! እ...እንትና...»

መሳይ በዓይኗ « ገደልኩህ ትነግራትና » አለችኝ ::

« እኮ ! ማን ጋ አንተ ለቃቃሚ !» እማዬ ተሳደበች ::

« ኧረ ! ማንም ጋ አልበላኹም ::»

« እና የት አባክ ሲሠራ አየህ ? በምን አባክ አወቅክ ?»

« ፈጥሬው ነው ::»

በእጇ የያዘችውን የመቆስቆሻ ብረት ለመማታት አወናጨፈችብኝ ::

« ደሞኮ ሥራዬን ትቼ አንተን ሰው ብዬ ማድመጤ » አለችና ከድስቱ ሥር ያለውን እንጨት ቆስቆስ አድርጋ በሸንበቆው ማንደድ ጀመረች ::

ቆይ ስለ ሸንበቆው ልንገራችሁ :: አራት ረጃጅም አንጓዎች አሉት :: ውስጥ ለውስጥ አንጓዎቹን የሚያስተሳስረው የሸንበቆ ክፍል ተወግዶለታል :: በአንደኛው ጫፍ በኩል አፍ ላይ አስቀምጠው ትንፋሽ ሲሠጡት በወዲያኛው ቀዳዳ ንፋስ ያወጣል :: ያ ንፋስ ደሞ በቀላሉ አልቀጣጠል ያለውን እሳት ያንበለብለዋል :: እና እማዬ በሱ ነገር ነው እሳቱን ማንደድ የያዘችው ::

ጌትነት ምግባችንን ካበላን በኋላ «ዕረፍት ያስፈልገናል » ይልና አልጋ ላይ እንወጣለን :: ከዚያ በግድግዳው በኩል ፤ መሳይን ፊት ለፊቷ ሆኖ ይደባብሳታል :: እሷ ደሞ እጇን ወደ ኋላ ሠድዳ ፀጉሬን ታሻሽኛለች :: እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ ይላል :: ሁሌም ታድያ ከእንቅልፌ ስነቃ እነሱን ካልጋው ወርደው ፍራሽ ላይ አንሶላ ለብሠው ተኝተው አገኛቸዋለሁ :: ገላቸውን ታጥበው ራቁታቸውን አንሶላ ብቻ ጣል አድርገው ተጋድመው እነቃለሁ :: ጌትሽ ግን እንደ እስጢፋኖስ ገላውን ሲታጠብ ቁምጣ አይለብስም ::

እዚህም ቤት « ራቁታችንን የሆንነው ገላችንን ታጥበን ነው » ይሉኛል እንጂ እንደኛ ቤት ገላቸውን ከታጠቡ በኋላ በሳፋ ውሃ መገኘት ሲገባው አግኝቼ አላውቅም :: መሬትም



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

አይበሰብሰም ። ምናልባት ከእንቅልፏ ሳልነቃ ደፍተውት ይሆናል ። ውሃም ሳሙም በቤቱ የለም። እህቴ ከጌትሽና እስጢፍ ጋር ገላዋን ስትታጠብ ለምን « ኧ ! አ ! ቀስ ! ቀስ !» እንደምትል አይገባኝም ። እቤታችንኮ ዝም ብላ ነው የምትታጠበው ። ውሃው ቀዝቃዛ ከሆነባት ግን « እችክ! እችክ !» ትላለች ።

ገላዬን ስታጥበኝ ወሸላዬን እየነካካች « አደገችልሽ አይደል ?» ትለኛለች ። አውቄ ትኩስ ሽንቴን እጇ ላይ ልትቅ ፈሰን ዘረኖ አደርግባታለሁ ። ውሃ ያራሠውን ጭኔን ስትቶነጠጥኝ እሪ እላለሁ ።

ጌትሽ ሁልጊዜም ከእንቅልፌ ከነቃሁ በኋላ ምግብ ያበላኝና ዲናሬ ሠጥቶ ጎረቤት ያሉት ቪዲዮ ቤቶች ፊልም እንዳይ ያደርገኛል ።

በርካታ ዲናሬዎችን ከመሳይ ጋር እየዞርኩ የማገኝበትን መንገድ ለጠይሜ ነገርኩት ። በጣም ሳቀብኝ ። ጅልነቴን እየጠቀሠ አለመጠብኝ ። ከዚህ በኋላ በምንም መልኩ መሸወድ እንደሌለብኝና ማድረግ የሚገባኝን ነገረኝ ። መሳይና ወንዶቿ በር እየዘጉ ራቁታቸውን የሚተኙት ገላቸውን ታጥበው ሳይሆን « ባለጌ ነገር አድርገው » እንደሆን ገለፀልኝ ። አፈርኩ ። በሁለቱ ትናንሽ መዳፎቼ አፌን በድንጋጤ ያዝኩ ።

ከጌትሽና እስጢፍ ጋር « ባለጌ ነገር » ማድረጓን ለወላጆቻችን ብንናገርባት ለሷ መጥፎ ነው ። ስለዚህም ሁሌም « ባለጌ ነገር ያደረግሽውን እናገርብሻለሁ » እያልኩ እያስፈራራሁ ብዙ ዲናሬዎችን እንድቀበላት መከረኝ ። የጠይሜ ሃሳብ ተመቸኝ ። ምክሩን ተግባራዊ ላደርገው ወሠንኩ ።

በሌሊት ከእንቅልፌ ነቃሁ ። ገና ወፎች መንጫጫት አልጀመሩም ። እኔና እርሷ አብረን ነው የምንተኛው ። አባትና እናታችን ደሞ ከኛ ትይዩ ባለው ሠፊ የሽቦ አልጋቸው ላይ ጓዳ ውስጥ ተኝተዋል ። የተወጠረ የሚመስለው አልጋ ሰው ሲያርፍበት መሬት ይሰማል ። እማዬና አባዬን ጠቅልሎ ሳይወዱ በግዳቸው ያስተቃቅፋቸዋል ።

« ዲናሬ ስጪኝ !» አልኳት መሳይን በሹክሹክታ ወደ ጆሮዋ ተጠግቼ ።

« የምን አባክ ዲናሬ ነው የምሠጠህ ? ቅማላም ! አርፈህ ተኛ ።»

« ዲናሬ ነዋ ! ከረሜላ የምገዛበት ።»

« ለአባዬ ልንገረው ጭንቅሎ ? ገንዘብ ይዘህ እንዳላይህ አላለሁም ? »

« ንገሪዋ ! የምፈራው መሰለሽ ነው ? አንቺ ከተናገርሽ ደሞ እኔም እናገርልሻለሁ ።»

« ምንድን ነው የምትናገ ረው ?»

« ትሠጪኛለሽ አትሠጪኝም ?»



@BOOKALEM

« አልሠጥህም ! ታስፈራራኛለህ እንዴ ? ገንቦ ራስ !» ብላ ተሳደበችና እጇን ወደ ጭኔ ላከች ::

« ተይ መሳይ...ከተናገርኩ በኋላ ግን ይቆጭሻል !»

« ምንድን ነው የምትናገረው ?»

« ሰው ቤት እየሄድሽ ገላሽን የምትታጠቢውን ነዋ !»

« እና ገላዬን ብታጠብ ምን ችግር አለው ?»

« ምንም !»

« እና ገላዋን ታጠበች ብለህ ብትናገር የሚቆጡኝ መሠለህ ? ገላ መታጠብ'ኮ ንፅሕናን መጠበቅ ነው :: እንዳንተ ለሰባት ግድግዳ የሚበቃ ጭቃ በገላዬ ተሸክሜ እንድዞርልህ ትፈል ጋለህ ? ጭቅቅታም !»

« ባክሽ ልትሸውጂኝ አትሞክሪ :: ጠይሜ ያልነገረኝ መሠለሽ ?»

« ምኑን ነው ጠይሜ የነገረህ ? ከሱ ልጅ ጋር አትግጠም ብትባል አልሠማም አልክ አይደል? እኔን አያርገኝ ጭንቅሎ ... አባዬ ከእንቅልፉ እንደተነሳ ባልነግርልህ !»

« ወንድ ነሽ ንገሪውና ሞክሪኝ !»

« ምን ታመጣለህ ?»

« ምን እንደማመጣማ ላሳይሽ ነው'ኮ :: ልብ ካለሽ አንቺም ንገሪው እኔም ንግር አደርግልሻለሁ:: ከፈለግሽ አሁኑኑ ቀስቅሺ እንዳልነግረው ::»

« ታስቦካኛለህ እንዴ ? ምኑን ነው የምትነግርብኝ ? ገንቦ ራስ !»

ልትቆነጥጠኝ ስትል ተከላከልኳት ::

« ብትቆነጥጪኝ ከጌትሽና አስጢፍ ጋር ባለጌ ነገር ማድረግሽን እናገርብሻለሁ ::»

እጇን ሠበሠበች:: ወደ ደረቷ አስጠግታ አቀፈችኝ:: በጡቶቿ አፈነችኝ :: ግንባሬን ፣ ጉንጬን ፣ ከንፈሬን ፣ አንገቴን ፣ ሆዴን ፣ ደረቴን ፣ መዳፌን ፣ ደጋግማ ሳመች :: ለመነችኝ ::

ጠይሜ ባለጌ ልጅ እንደሆነና እሱ እንዳለው ባለጌ ነገር እንዳላደረገች ነገረችኝ :: ዲናሪውን ግን ሁልጊዜ እንደምትሠጠኝ ፣ እንዲያውም ስሙኒ ስሙኒ እንደምታደርግልኝ ቃል ገባችልኝ ::

« ግን አንተ ... ለማንም እንዳትናገር እያልኩህ ለአገሩ ሁሉ ያወራኸው ምን ሆነህ ነው ጭንቅሎ ?» አለችኝ በተሸናፊነት ተሸብባ ፀጉሬን እየደባበሠች ::

« ኸረ ! እኔ ለአገሩ ሁሉ አላወራሁም :: »



@BOOKALEM

« እና ለነ ማን ነው ያወራኸው ?»

« ያወራኹት ለጠይሜ ፣ ለጠምበለል ፣ ለኑረዲን ፣ ለሠላምና ለሔለን ብቻ ነው ።»

« ብ ... ቻ ¡ » ሸሙጧ አልገባኝም ።

« አዎ ለነሱ ብቻ ።»

« አታፍርም ደሞ ስማቸውን ስትዘረዝርልኝ ! ዋና ዋናዎቹ ወሬ አቀባባዮች ፣ እነሱ አይደሉ እንዴ ! ለአገር የሚተርፉ የወሬ ወንፊቶች !»

ዝም አልኩ ። በስተመጨረሻ እነ ጠይሜ መሳይን መንገድ እየጠበቁ « ዲናሬ ካልሠጠሽን ለእናትና አባትሽ ከወታደሮች ጋር ባለጌ ነገር ያደረግሽውን እንናገርብሻለን » እያሉ ገንዘብ ይቀበሏት ጀመር ። ከቤታችንም መስረቅ ጀመረች ። ሥርቃ ለኔና ለጓደኞቼ ትሠጠናለች ። ሲያልቅ እያምር ሆነና « መሳይ ዲናሬ » መጠርያዋ ሆነ ። ቅፅል ስሟ ዕድሜ ለታናሽ ወንድሟ ለኔ ።

***

ዲናሬዎችን ከምንሰበስብባቸው ሠፈሮች ዋና ዋናዎቹ ቦቴ እና አንደኛ መንገድ ናቸው ። ሁለቱም ሠፈሮች ውስጥ ቡና ቤቶችና ሴተኛ አዳሪዎች ይበዛሉ ። ሴትኛ አዳሪዎች በግላጭ ለገበያ ሲወጡ ወንድኛ አዳሪዎቹ ግን ለኛ ለጩጬዎቹ ዲናሬዎችን እየሠጡ ይልኩናል ። መርጠን ፣ በዋጋ ተስማምተን ሴቶቹን ከያሉበት እናመጣላቸዋለን ።

ሴቶቹ እኔን ጠይሜንና ጠምቤን በደንብ ስለሚያውቁን በጣም ያቀርቡናል ። ተሰባስበው እየዋሉ ጫት ከሚቅሙበት እያስገቡ የበቆሎ ፈንዲሻ ፣ ብርቱካንና ፣ሳምቡሳ ያበሉናል። ያስተረፉትን ምግብ ይሠጡናል ። ሁልጊዜ ስጋ ወጥ ስለሚበሉ እንቀናባቸዋለን ።

ማርታ ሁሌም ገበያዋን ስለማመጣላት ትወደኛለች ። የሚልከኝ ሰውዬ ከሚሰጠኝ ዲናሬ ሌላ ሁለት ወይም ሦስት ዲናሬዎችን ትጨምርልኛለች ።

እቤቷ ስንሄድ እጥብጥብ አድርጋ «ሰው» ታስመስለኛለች ። የምበላው ትሠጠኛለች ። ቦቴ ውስጥ ካሉት ሸሌዎች ዝንጥ የምትለውም እሷው ናት ። ለሰው ታዝናለች ። የምትጎርሠውን ከአፏ ነጥቃ ታጎርሰኛለች ።

« ጭንቅሎ ! አንተ'ኮ አሪፍ ልጅ ነህ ። ገበያዬን የምታመጣልኝን አንተን ያልተንከባከ ብኩ ማንን ልንከባከብ ?» ትለኛለች ለከንፈሮቿ በቀረብኩ ቁጥር ጉንጭና ግንባሬን እየሳመች ።

የሆነ ቅዳሜ ቀን ከሰዓት በኋላ ጓደኞቿ ባሉበት እኔ ፣ ጠይሜና ጠምቤም ተቀምጠናል። ጫታቸውን እየቃሙ ጋያውን ሲያንደቀድቁት ብርቱካናችንን እየበላን ወሬያቸውን እናዳምጣለን ።

ማርታ እኔን ፣ ማህደር ጠይሜን ፣ ኤልሳም ጠምበለልን አቅፈው እየመከሩን ነው ። ገበያውን



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ወደነሱ ብቻ ይዘን እንድናመጣ እየጀነጀኑን ።

ሙዚቃው ተከፈተና መደነስ ጀመርን ። ጠይሜ ዳንሱ በጣም ያስቃል ። እግሩን ሠበር ሠበር ፣ ወልከፍ ወልከፍ ያደርግና አልፎ አልፎ እግሩ እየተማታበት መደነሱን ያቆማል። እየደነሠ መሆኑንም ይረሳውና ይቆማል ። ጠምቤ ግን ኃይለኛ ነች ። አጭር ወፍራም ሆና ስትደንስ ታስቀናለች ። በጣም ዳንስ ትችላለች ። የቄስ ዘርነቷን እስከጠራጠር በዳንሷ ተመልካቿን ታሳብዳለች ። ኤልሳም ጎንበስ ብላ አዳነሠችውና ጉንጩን ደጋግማ ሳመችው ።

« ያዝ ጭንቅሎ ! ያዝ ! ያዝ !» አለችኝ ማርታ እሷ እንደምትደንሠው እንድደንስላት እያሳየችኝ ። አቅሜን አሚጥጬ የምችለውን ያክል ሰብርብር እያልኩ ደነስኩላት ።

« ጭንቁ ! ራጋ ውረጅ ! ራጋ ! ወረድ ... ወረድ ... አዎ ! ወረድ ... ወረድ ወደ ኋላ ! ብራቮ ጭንቅሎ !» አለኝ ጠይሜ አውራ ጣቱን ከመሀል ጣቱ ጋር አጋጭቶ እያጨበጨበልኝ ።

በሞራል ወደ ኋላዬ ሄድኩ ። አልተመለስኩም ። በጀርባዬ ተንጋልዬ የነሱን ሳቅ አዳመጥኩ። ማርታ መጥታ አነሳችኝ ። ግንባርና ከንፈሬን ሳመችኝ ። የግንባሬ ምንም አልመሠለኝም ነበር ። ከንፈሬን ስትስመኝ ግን ለምን እንደሆነ እንጃ እንጂ ደነገጥኩ ። ሰውነቴን ውርር አረገኝ ። እቅፍ አድርጋኝ ፍራሹ ላይ ተቀመጠች ።

«ጭንቅሎዬ የኔ ቦምብ ራስ !» አለችኝ ማርታ የወደቅኩበትን ጭንቅላቴን እያሻሸች።

« እ !»

« ቀምሠሽ ታውቂያለሽ ?»

« ምን ?»

ሴቶቹ ተሳሳቁ ። ጠይሜና ጠምቤም ገብቷቸው ይሁን ሳይገባቸው ከነሱ ጋር ሳቁ ።

« ወይኔ ጭንቅሎዬ ... ትልቅ ብትሆኚልኝ እኮ አቀምስሽ ነበር ያውም አምስት ሳንቲም ሳላስከፍልሽ በነፃ !» ግንባሬን ሳመችኝ ።

« ምን ?»

« እስቲ ጭንቅሎ እውነቱን ንገሪኝ ! ቀምሠሽ አታውቂም ?»

« እኮ ምን ? እኔ እዚህ ምድር ላይ ያልቀመስኩት ነገር የለም ። ከሚጠጣ ማላታይን ከሚበላ ቅል ብቻ ነው ያልሞከርኩት !» ሲባል ሠምቼ እንጂ ማላታይን ምን እንደሆነ እንኳን አላውቅም ።

« ኧረ አንቺ በፈጠረሽ አፈሪ !» ማህደር ማርታን እየሳቀች ተቆጣቻት ።

«እንዴ ምን አገባችሁ ! እኔ በጣም ስለምወደው አቀምሰዋለሁ ። አቀምስሃለሁ እሺ ጭንቅሎዬ!»



@BOOKALEM

አለችኝ አገጬን በሦስት የቀኝ እጅ ጣቶቿ ቀና አድርጋ እያየችኝ ።

« እሺ መቼ ነው የምታቀምሺኝ ? » ለመቅመስ ያለኝን ጉጉት ገለፅኩላት ።

ማህደርና ኢልሳ አንባ እስኪወጣቸው ይስቃሉ ።

« አሁኑኑ መቅመስ ትፈልጋለህ ?»

« አዎ ! »

« እሺ ሱሪህን አውልቅ ! »

ደነገጥኩ ።

« ሙታንቲ አርጎ አያውቅም እንዴ !»

በጠይሟ ንግግር ሁሉም ከትከት ብለው ሳቁ ። አናደዱኝ ።

« አድርጌያለሁ !» ብዬ ሱሪዬን ዝቅ ሳደርገው የዱሮዋ ያለቀች ሱሪዬ ቁምጣ ሆና ታየች ።

« የአባቱ ሱሪ ነበር ሙታንቲ አይደለም ።» አለ ጠይሟ

ጠይሟ ድጋሚ አናደደኝ ። ምን አባቱ እንዳስቀናው እንጃለት የማያውቀውን ይዘላብዳል ።

« ይኼ ምንድን ነው ጭንቅሎ ? » አለችኝ ማርታ ያልተገረዘች ወሸላዬን በቁምጣዬ ላይ እየነካካች ።

አፈርኩ ።

« እሺ ይሄኛውስ ?» የራሷን እያሳየች ጠየቀችኝ ።

እንደማፈር ብዬ በሳቅ ፈቅፈቅ አልኩ ።

« ዛሬ የማቀምስህ የኔን ነው እሺ !»

« ያንቺን ምን ?»

« ይሄን ነዋ ! » ድጋሚ በእጇ ወደ ቅድሙ ቦታ ጠቆመችኝ ።

« እሺ እምቢየው ።»

« ለምን ጭንቅሎዬ ?»

« እቤት ይቆጡኛላ !»

በኀብረት ሳቁብኝ ።



@BOOKALEM

ጠይሜ ግን « ወይኔ ! እኔን ባለችኝ ኖሮ ! እንደ ሔለንና ሰላም ጡቷን ጭምቅ አድርጌ አስጮሃት ነበር ::» አለኝ ከወጣን በኋላ

« እንዴ ! እንዴ !» አልነው ጭንቅላታችንን ይዘን የነ ሔለንን ስም በብልግና ሲጠራ ::

« በሕልሜ ነው !» አለ ደንግጦ ::

ከነ ማርታ ጋር የተግባባነው በዋዛ አልነበረም :: አንድ ቀን የሆነ ሰውዬ ጠራኝና « ሂድና ከነኒያ ከተኮለኮሉት ሴቶች በአስር ብር እሄዳለሁ የምትለዋን ፣ዋጋ ጠይቀህ ተደራድረህ አምጣልኝ :: አሪፏን ካመጣህልኝ ሶስት ዲናሬዎችን እሠጥሃለሁ » ይለኛል ::

« ስንት ነሽ ?» አልኳት ማርታን የተኮለኮሉበት ቦታ ሄጄ ::

« ና ! በጆሮህ ልንገርህ ! » አለችና ሹራቤን ጨምድዳ ፣ አንገቴን አንቃ « የአያትህን ፈረስ ልትገዛ የመጣህ መሠለህ ስንት ነሽ የምትለኝ ?» ብላ እሽት አደረገችኝ ::

በአሁኑ ወቅት ታላላቅ ስልጣን የያዙ ሰዎችን ከበረሃ እንደመጡ የዓመታት ጥማቸውን የቆረጥንላቸው እኛ ትናንሾቹ ደላሎች ነበርን :: ጥርስ የሚሠብረውን ብስኩትና የታሸገ ዚግኒ እየሠጡን እነ ማርቲን የመሳሰሉ ሽንኩርቶችን እናቀርብላቸው ነበር ::

« ናኣማ ! ኢታ ማንጁስ ! ... እኔ ሾርምጣ እንጂ የደርግ ሲፓርታ አምጣ አልኩህ እንዴ ? ቱንበርከከ !» አለኝ ጎራሬያሙ ሻምበል ::

አንድ ሌሊት ማርታ ሻምበሉ መስመር ሲለቅባት በቃርያ ጥፊ ገባችለት :: ማርታ «በማርሻል አርት» የሰማያዊ ቀበቶ ባለቤት ነበረች :: ሽጉጥ ታጥቆ ብዙ ምሽት ፈሊጋት :: አጣትም :: በመጨረሻ ሻምበሉ ወደ ጅጅጋ ሲቀየር ነው ተረጋግታ መስራት የጀመረችው :: እንኳንም ተቀየረ:: ሻምበሉ በእንጀራችን ገብቶ እየበጠበጠን ነበርና መኬዱን ወደድነው ::



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ አምስት

## አወይ ቀላድ አምባ

« አወይ ቀላድ አምባ ካቦከር በታች

ፍየሏን ያርዱና ይላሉ ሞቶች ።»

( የመንደሬው ግጥም )

መንደሩ የተመሠረተው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስትያን ጋራን ከራስጌው አድርጎ ነው። ጊዮርጊስና አሮጌው ሥላሴ አብያተ ክርስትያናት ከእግራቸው ሥር የከተመውን መንደር ከተፈጥሮ ጥቃት ይጠብቃሉ ። ከጋራው የሚንደረደር ጎርፍ የአልፎ አልፎ ክስተት ቢሆንም በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት አድርሶ አያውቅም ። የቀላድ አምባ ሰው ክርስትናውንም ቀብሩንም የሚያስፈፅመው በዕድሜ ጠገብ ነጭ ባህር ዛፎችና ጥዶች በተከበበው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስትያን ነው ።

ቀላድ አምባ እንደ ስም አንድ ይሁን እንጂ አራት ቀበሌዎችን አስጠልሏል ። ቀበሌ አስራ አንድ፣ አስራ ሁለት ፣ አስራ ሦስትና ከፊል አስራ ስምንት የቀላድ አምባ የወሠን ክልሎች ናቸው። ቀላድ አምባ አባት ሆኖ የሚያስተዳድራቸው ትናንሽ መንደሮችም በውስጡ አሉ ።

ከሚጠቀሱት መካከልም ጣሳ ሠፈር ፣ አከምባሎ ሠፈር ፣ ጉልት ፣ ግሪካን ግቢ ፣ ቲ ቲ አይ፣ እስላም መቃብር ፣ ከብሪት አምባ ፣ ፈረሠኛ ፣ አሜድላ ፣ መብራት ኃይል ፣ አጋዴን አንበሳ፣ ድድ ማስጫ ፣ አራምዴ ፣ አዘረፈኝ ፣ ዳቦ ቤት ፣ ሞት ባይኖር ... ቀላድ አምባ በአባትነት የሚጠራባቸው መንደሮች ናቸው ።

ስምንት ያክል የጦር ካምፖች በዚህ መንደር ይገኛሉ ። ለመንደሩ ዕድገት ኋላ ቀርነት፣ ቀርፋፋነትና መበስበስ ትልቁ እንቅፋት የጦር ካምፖቹ በዚያ መገኘት ዓይነተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል ። በሐረር ከተማ ከሚገኙት አስራ ሁለት ያክል የጦር ካምፖች ስምንቱ እኛ ሠፈር ውስጥ ናቸው ። ስለዚህም የወታደር ልጆች ብንበዛ አይፈረድብንም ። ደግሞስ የወታደር ልጅ መሆን የጀግና ልጅ መሆን አይደል እንዴ ? ቀላድ አምባ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን በጉርምስናው ተቀብላ እስኪጎለምስ ያስተናገደችው መንደር ናት ።

አብዛኛዎቹ ደሀ የኅብረተሰቡ ክፍሎች የተሠባሰብነው እኛ ሠፈር ነው ። የመንደራችን ስያሜ እራሱ ያስገርማል ። ጥንት የኛ ሠፈር የአፄ ኃይለ ሥላሴ አባት የልዑል ራስ መኮንን ርስት እንደነበረ ይነገራል ። ሰዎቹ በመሬቱ ላይ ሠፍረው ለመኖር ሲሠነዳዱ ልዑሉ መሬቱን ለፈላጊዎች እየሸነሸኑ ሠጡ፡፡ በነፃ ይሁን በገንዘብ ግን እንጃ ።

« ቀላድ » እየተሸነሸነ ፣ እየተከፋፈለ የሚሸጥ መሬት ማለት እንደሆነ አባቴም ነግሮኛል ።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

እውነቱን ይሁን ሲፎግረኝ እንጃ እንጂ ። ልክ አሁን « ባንከ ሠፈር » ይባል የለ ! በባንከ ብድር የተሠሩ ቤቶች የበዙበት ቦታ ! እንዲያ መሆኑ መሠለኝ «ቀላድ አምባም » ።

በኛ ሠፈር የሌለ ብሔረሰብም የለም ። ብዙዎች እንደ አንድ ተስማምተውና ተፈቃቅደው የሚኖሩበት መንደር ነው ። የየግል ኃይማኖት ይዞ በማኅበራዊ ነገሮች ላይ ቢጋራ መሳተፍ የመንደሬው የጋራ ባህርይ መሆኑ ይታወቃል ። ለቅሶም ፣ሠርግም ፣ ምርቃት ፣ ልደትም በቀላድ አምባ ብዙ አጃቢ አላቸው ። ሟቹ ዕድር ኖረው ፣አልኖረው ፣ ለሠፈሩ አዲስ ይሁን ነባር ፣ ብቻ ሟቹ ፈልጎም ይሁን ሳይፈልግ ይሙት እንጂ ሞቱ አዛኝ ፣ ቀብሩ አልቃሽ ፣ ድንኳኑ ተቀማጭ አያጣም ። ይኼ ነው እንግዲህ የቀላድ አምባ ሰው ። ይኼ ነው ሠፈራችን ።

የግንብ አጥር አይታሠብም ። የጡብ ቤት ለመስራት ቢፈለግም መሬቱ የሚቀበል አይመስልም ይባላል እንደ አሉባልተኞች ገለፃ። አንዲት ፎቅ እንደ ብጉር በመንግስት ብትተከልልን ትረባ ወዳድ ነንና « አስቤሽ አላውቅም !» ብለናታል ። ድንገት ነበራ መንግሥት ካድሬዎቹን ማከማቻ የገነባልን ። የመንደር ውስጥ ለውስጥ የመኪና መንገድም አይታሠብም ። እሱን የምንላቸው ውስን ጥርጊያ መንገዶች ለግለሰብ ሳይሆን ለመንግሥት ፣ ለግል ድርጅትና ባለቤት ለማያሽከረክራቸው መኪኖች ብቻ የተመቹ ናቸው። እነ አራል ፣ ካማዝ ፣ዚል ፣ ዋዝ ፣ጂፕ ፣ ኤኔትሬ ፣ አይፋ … እነዚህ መኪኖች ብቻ ናቸው መንደራችንን የሚደፍሩት ። ባለቤት የሚያሽከረክራቸው መኪኖች የኛን ሠፈር መንገድ አያስቡትም ። ምክንያታቸውን አላውቅም ። እንዲህ ሲሉ ግን ሠምቻቸው አውቃለሁ ።

« ከመንገዱ የባሠ ልጅ አዋቂው ተንኮል ይወዳል ። የሚሰርቁት ቢያጡ ጎማ ያስተነፍሳሉ ።»

ለነገሩ ጎማ በማፈንዳት እኔን ፣ ጠይሜንና ጠምቤን የሚያከል አንድም የቀላድ አምባ ልጅ የለም ። በተለይ የማይረሳኝ የግብርናን መኪና ይነዳ የነበረው ፊይሠል ነው ።

አንድ ቀን « ሬንጅ ሮቨሯን » የግብርና መኪና አምጥቶ ኳስ የምንጫወትበት ሜዳ ላይ ገተራት ። እንዲያነሳልን ብንለምነው አልሠማ አለን ። ጭራሽ ሠደበን ። ሦስታችንም ተናደድን። የሞቀው ስሜታችን ላይ ሲረማመድብት በገንን ። ከዚያ ዘዴኛው ጠይሜ አቀፈንና ፊይሠልን የምናበግንበትን መላ ነገረን ። ተስማማን ።

በዝርግ ጣውላ ላይ ምስማሮች መታንበትና ሁለቱ የኋላ ጎማዎቹ ሥር አሸዋ አልብሠን አጠመድንለት ። ምሳውን በልቶ ጨረሰና መኪናውን አስነስቶ ወደ ፊት ሲኼድ ምስማሩን ረገጠና ጎማው ፈነዳ ። መኪናዋ ወደ ኋላ ተንበረከከች ። የፊት እግሮቹን ዘርግቶ በቂጡ ቁጢጥ ያለ ውሻ መሠለች ። የፍንዳታውን ድምፅ ተከትለው ብዙ ሰዎች መጡ ። መኪናዋን ከበቧት ።

« እነዚህ ርኩሶች ! » ይላሉ አንዳንዶች

« አባት የሌለው የሴት ልጅ ተሠብስቦ ድሮስ ምን ጤና ይገኛል ?» ትላለች የፊይሠል ሚስት ዘሀራ



@BOOKALEM

« ለመኾኑ እነማን ናቸው እንዲህ ያደረጉት ? ታውቀዋል ?» ይጠይቃሉ ሌሎች

እኛም ምንም እንዳላየን ፣ እንዳልሠማን ከተሠበሰበው ሰው ጋር ተቀላቅለን ሥራችንን በየልባችን እናደንቃለን ። ፈይሠል ግንባሩን የመኪናው መስኮት ላይ አስደግፎ ስቅስቅ ብሎ ያለቅሳል ።

« ዕድሜ ዘላለሜን ከፍዬም አዳውን አልጨርሠውም'ኮ ፣ በወር ደመወዜ ፈርጁ እንኳን ሥራዬን ልቀጥል ብል ቤተሰቤን ምን እመግባለሁ ?» ይላል ።

ዘሀራ አብራው ታለቅሳለች ። የኛ ሦስቱ ትንንሽ ነፍሶች በተንኮላቸው ተደስተው ይስቃሉ ። ፈይሠል እንዳቃጠለን ስላቃጠልነው ረክተናል ።

ወዲያው ትብብር ተጀመረ ። መንደሬው አቅሙን ተጠቅሞ የፈቀደውን በፍላጎቱ አዋጣ። ሠፈድ ፣ የመሶብ ከዳን ፣ ፌስታል ፣ ጃንጥላ ፣ እየተያዘ በየቤቱ ተዞረ ። እያንዳንዱ ሰው በሠጠው፣ በመፀወተው ልክ እየተመዘገበ ፈይሠልን ከኪሳራ ለማዳን ታገለ ። ድህነት ፣ ፍቅርና መተሳሰብ እኩል የነገሡበት መንደር ቀላድ አምባ ።

የሆነ ጊዜ ደሞ መላኩ ዱባለ የሚባል ልጅ አስቸገረን ። ታላቃችን ነው ። ወፍጮ ቤት ይሠራል ። የመዛኙ የኃይለ መስቀል ረዳት ነው ። ሽሮና በርበሬ የሚፈጨው እሱ በመሆኑ ከሱ ጋር መጫወት ይከብዳል ። ከነፈጨበት ቱታው ስለሚጫወት ስንጋጨው በርበሬው ከላዩ እየቦነነ ያስነጥሠናል ። ዓይናችንን ይለበልበናል ። በቆዳ ጫማ ቢጠረብ እንኳን አያመውም ። እሱ ግን በባዶ እግሩ ሲጣረብ በብረት የመታን ያክል ያሳምመናል ።

አንድ ቅዳሜ ታድያ ኃይለኛ የእኩያሞች ግጥሚያ ነበረብን ። በጨዋታው ላይ መሳተፍ የነበረብንም እኩያሞቹ ተጋጣሚ ቡድኖች ብቻ ። እሱ ግን ካልተጫወትኩ ብሎ ግግም አለብን። ብንለምነው ፣ ብንለማመጠው በእምቢታው ፀና ። ተጋጣሚዎቻችን የነበሩት ልጆች ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ ። ተናደድን ። ከዚያ ሦስቱ ጓደኞሞች ተመካከርን ። ጨዋታውን ላለማካሄድ የወሠንን መስለን ወደ ሳህሌ እርሻ ሄድን ። የቲኒ (ቁልቋል) ቅጠል ከነ እሾኩ ቆርጠን አመጣን። ጠይሜ መላኩን በወሬ ጠምዶ ሲይዝልን እኔና ጠምቤ እሾኩን አፈር አልብሠን የመጫወቻ ሜዳችን ላይ ቀበርነው ።

መላኩ ገግሟል ። ካላጫወትነው ሜዳውን እንደማይለቅልን ፣ እንዲያውም ኳሳችንን እንደሚወስድብን አስፈራራን ። የሠራነውንና ያቀድንለትን ስለምናውቅ ገብቶ እንዲጫወት ፈቀድንለት ።

ተመራረጥን ።

ጠይሜና መላኩ እኔና ጠምቤ ።

ጀማሪዎቹ እነ ጠይሜ ሆኑ ። እኛ ደሞ ነጣቂዎች ። ጠይሜ ሆን ብሎ አፈር ለብሶ ወደ



@BOOKALEM

ተቀበረው እሾከ ኳሷን ለጋት ። መላኩ ኳሷን ተከትሎ ሮጠ ። እኔ ደሞ እሱን ። ኳሷ ላይ ሳይደርስባት የቀኝ እግሩን በሁለት እጆቹ ጨብጦ ተንጋለለ ። ኡኡታውን አቀለጠው ። ቲኒው እንደ ጫማ እግሩ ላይ ተጣበቀ ። እንደ ፌይሣል መኪና ጎማ የመላኩ ዱባለን እግር በእሾከ አስተነፈሰንለት ። አርፎ በሰላም በርበሬውን እንዳይፈጭ መንቀሳቀሻውን አገትነው ። ያን መጅ የሚያከል እግሩን አስተንፍሦን « ቁልቋል » የተሠኘ አዲስ ጫማ በልኩ ገጠምንለት ።

ከረምት ሲመጣ ደሞ የጭቃ ጨዋታችንን እንጀምራለን ። ጭቃ እያድቦለቦልን የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን እንሠራለን ። እንረጫጫለን ፤ እ ... በወፈረው እንለጣጠፋለን ። ጭቃ ሰብስበን እንከምርና ላስቲክ አልብሠን ከሌላ ቦታ ደረቅ አፈር አምጥተን እንነሰንስበታለን ። መንገደኞች ደረቅ መስሏቸው እንደረገጡት ወይ ሲያሠምጣቸው አልያም ሲያዳልጣቸውና ሲወድቁ ተደብቀን እያየን እንስታለን-የምር ሳቅ ። በልብሳችን አፉችንን ከድነን ቢድብቅ የምንስቀው የምር ሳቅ ።

ጠይሜ የጭቃ ኳሷን ወደ አየር ከፍ አድርጎ አቀበለኝ ። ያለ የሌለ ኃይሌን ተጠቅሜ ኳሷን መታሁ ። ፈገግታዬ አየር ላይ ቀረ ። ለቅሶዬ ሳቁን አጨናገፈው ። በሁለት እጆቼ እግሬን ይዤ በአራት መዐዘን አነባሁ ። ጠምቤ በርህራሔ አባበለችኝ ። ጠይሜ በሳቅ ይንከተከታል ። ጭቃ ውስጥ ሆን ተብሎ በጠይሜ በተደበቀ ጥቁር ድቡልቡል ድንጋይ እግሬን ተሠበርኩ ። ያሳዝናል ! ጠይሜ የሚባለው «ድንጋይ» ለቀልድ የሸጎጠው ድንጋይ የሦስት ቀን አንካሳ አደረገኝ ።

ለነገሩ እግር ለመስበር ጠይሜ አዲስ አይደለም ። አንድ ቀንም በካልሲ ውስጥ ተጠቅልሎ ሞላላ ኳስ በመሠለ ድንጋይ ጠምቤን ሠብሯታል ። ግን ደሞ እንዲህ እየሠበረን ለምን ከስሩ እንደማንርቅ አይገባኝም ። እግራችን ተሠብሮ ወይም የሆነ ጉዳት በጠይሜ ደርሶብን ወደየቤታችን ስንገባ ከሱ እንድንርቅ ይነገረናል ። እኛ ግን እንዳናገኘው ስንከለከል ፍቅራችን ይብስ ይጨምርብናል ።

የጠይሜ የአክስቱ ልጅ ፍሠሀ ከመቀሌ ከቤተሰቦቹ ጋር ከመጣ ሦስት ቀን ሆኖታል ። እኔና ጠምቤንም ተዋውቆ አብሮን መጫወት ጀምሯል ። ብዙም አማርኛ ስለማይችል በአነጋገሩ እየተሳሳቅንበት አብረነው እንውላለን ። ቢያንስ በአንድ ተጨማሪ ቋንቋ በልጠን እያለ ሁለተኛው ላይ ሲኮለታተፍ እንስቅበታለን ። የሚያውቃቸውን አርባ አምስት የሚጠጉ የአማርኛ ቃላት እያገጣጠመ ቀልድ ሲፈጥር ይገርመኛል ፤ ያስቀኛልም ።

ፍሠሀን « ዓይናችንን በጨርቅ አስረን አባ ያዕቆብ የተሠኘውን ጨዋታ እንጫወት » ይለዋል ጠይሜ ። ስለ ጨዋታው ገለፃ የተደረገለት ፍሠሀ ለመጫወት ተስማምቶ ዓይኖቹን በጨርቅ ይታሠራል ። ጠይሜ ሆን ብሎ ዓይኖቹ ታስረው ለጊዜው የማያዩትን ልጅ በሠንሠለት ወደ ታሠረው ኃይለኛ ውሻቸው አቅጣጫ ይመራዋል ። ጋሽ በቂ ብርቅ ሆኖባቸው ለፍሠሀ በየቀኑ ብስኩት ስለሚገዙለት ጠይሜ አንጀቱ አርሮ ብሷል ። ቂሙን የሚወጣበትን ቀን ጠብቆም ዛሬ ላይ ደረሠ ።

ውሻው ከአሳዳሪዎቹ ውጪ ሠንሠለቱን ጨምሮ ያገኘውን በመንከስ ታላቅ ዝና አለው ።



@BOOKALEM

ቀኑን ሙሉ ታስሮ እየዋለ ምሽት ከአምስት ሰዓት በኋላ ነው ሠንሠሉ ከአንገቱ የሚወልቅለት ። የሚመገበው ከቄራ እየታፈሰ የሚመጣለትን የከብቶች ደም ።

ፍሠሀ ዓይኖቹ እንደታሰሩ ድምጹን አጥፍቶ ወዳደፈጠው ተናካሽ ውሻ ተጠጋ ። ጠይሜ ሆን ብሎ እሱን ከማይነከሠው ውሻ ኋላ ቆሞ ለፍሠሀ ድምፅ ያሰማዋል ። ፊሽ ወደ ፊት ፣ ድምጹን ወደ ሰማበት አቅጣጫ እጁን ዘረጋ ። ጠይሜን ለመጨበጥ የተዘረጋ እጁን ውሻው ተቀበለው ። በከስተቱ ተደናግጦ ሲደናበር ወደቀ ። ውሻው አልራራለትም ። የጠይሜ አከሰት ልጅ የአሳዳሪዎቹ ዘመድ መሆኑን ውሻው አልተረዳም ። ፊሽ እየጮኸ ቂጡን ለውሻው ሠጠ ። የልጇን በደም መጨመላለቅ ባለማመን ያየችው እናት « አወይ ! አነ ትርሀስ ! አወይ ! ፍሠሃየ !» እያለች ከልጇ ጋር አለቀሰች ።

ጠይሜ በጋሽ በቂ ዱላ ሰብርብር ተደረገች ። ውሻውም በፌሮ ብረት ጭንቅላቱን ተመትቶ ተገደለ ። በውሻው ሞት ጋሽ በቂ ከሚስታቸው ተጣሉ ። በሚስታቸው ንግግር እራሳቸውን መቆጣጠር ያልቻሉት ሰው ውሻቸውን የገደሉበትን ዱላ ሠነዘሩ ። የጠይሜ እናት ተዘረሩ ። እየሆነ ያለውን ቆመው መመልከት ያልቻሉት የፍሠሀ ቤተሰቦች ጋሽ በቂን ተጋግዘው ወገሯቸው። ቤቱ ተረበሸ ። የፊሽ እናትና አባት በማግስቱ ለአንድ ወር የመጡበትን የቆይታ ጊዜ ሠርዘው ወደ መቀሌ ተመለሱ ።

***

ከማርፈጃው እስከ ቀትር በተለያዩ ድምፆች ውከቢያ የሚታጀበው መንደራችን ከሰዓት በኋላ ሰው የሚኖርበት አይመስልም ። ፀጥ ፣ረጭ ይላል ። ሩጫና ፍጥጫ ከሰዓት በኋላ ሰዓት እላፊ ተጥሎባቸዋል ። እንኳንስ ትላልቅ ሰዎችና ትናንሾቹም ለጨዋታ የምንመርጠው የጠዋትና አመሻሽ ከፍለ ጊዜውን ነው ።

ማርፈጃውን ተጣልተው ፣ ተናቁረውና ተባልተው ያመጡትን ብር ይዘው ወደ ጫት ተራ ይሄዳሉ ። ብዙዎች እራሳቸው የሚፈልጉትን የጫት ዓይነት ለራሳቸው መርጠው ይገዛሉ ። በዋጋ መከራከር ፣ ጫት መግዛታቸውን ሌሎች እንዳያውቁባቸው የሚፈልጉ ፣ በታዘዝነው መሠረት ወይ በግላጭ አልያም በድብቅ እንደ መልዕክቱ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እናደርሳለን ።

ጠዋት ተጣልተው ሲሠዳደቡ ፣ ሲደባደቡና ለገላጋይ ሲያስቸግሩ ያረፈዱ ሰዎች ጫት መቃም ከጀመሩ በኋላ ፀብ የለም ። ያለ ሽማግሌ ይታረቃሉ ።« አቦ !በኢማን እንታምበታ!» ተባብለው በጉንጫቸው ልከ እየጎረሱ ፣በመንጋጋቸው አቅም እያኘኩ ጫትና ጊዜያቸውን እኩል ይበላሉ ።

ከየቤቱ ሞቅ ብሎ ይሰማ የነበረው ሙዚቃና የተሰባሰቦ ቃሚዎች ድምፅ በምርቃና ሰዓት አይታሰብም ። ሁሉም ለየራሱ የሀሳብ ፈረስ ገዝቶ ይሳፈራል ። በሀሳብ ፈረሱ ላይ ተቀምጦ ዓለምን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ሲገዛ ያመሻል ። በሀሳቡ በፈጠረው ፣ ገንብቶ ቀለም በቀባው ቪላ ውስጥ እየተንደላቀቀ ፣ በመኪናው እየተንሸራሸረ ፣ ጠላቶቹን እያጠፋ ፣ ወዳጆቹን እያባዛ



@BOOKALEM

ከፍራሹ ሳይነሳ በሀሳብ ይባዝናል ።

በዚያች መንደር ከልጆች ተሸሽጎ የሚደረግ ምንም ነገር የለም ። ሰስ አስያዥ ነገሮች በየሜዳው ሲቸበቸቡ ፣ ተጠቃሚዎቹም እንደልባቸው ለልጆች መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ ሳያደርጉ እየቃሙ ፣ እያጨሱ ፣ እየሰከሩ ፣ እየፈነከቱ ፣ እያጭበረበሩ መጥፎ አርዓያነታቸውን ያወርሱናል ።

ጋሽ በቄ እኔንና ጠይሜን ጫት እንድንገዛላቸው ወደ ደንበኞቻቸው ሀሊማ ዘንድ የሚልኩን ምራቃቸውን መሬት ላይ ተፍተው ነው ።

« እንትፍ ! እስከትመለሱ ይቺ ምራቅ ከደረቀች ወዮላችሁ !» ይሉናል አረንጓዴ ምራቃቸውን መሬት ለድፈው ። ያለንን የመጨረሻ የፍጥነት ወሰን ተጠቅመን ወደ ጫት ተራ እንሮጣለን ። የተባልነውን የጫት ዓይነት በተሠጠን ዋጋ ልከ ገዝተን ስንከንፍ እንመለሳለን ።

እሳቸው ሲቅሙ ጠይሜ ውሃ በቅል ያቀራርባል ። ዕጣንና ሉባንጃ ያጫጭሳል ። እኔ ሻይ አፈላለሁ ። ስኳርና ጨው ቀላቅዬ ያፈላሁትን ሻይ ለጋሽ በቄ አቀራርባለሁ ። ሦስት ብርጭቆ ሻይ አከታትለው ከጠጡ በኋላ ከተረፈ እኛ እንጠጣለን ። ካልተረፈ ግን «ጭንቅሎ ! ባትጠጣም ምያ ከተለማመድክ ይበቃሀል ! » ይሉኛል ።

ብዙ ጊዜ ጠይሜም በአቅሟ እኔ ላይ ጉልቤ ስለምትሆን ያፈላሁትን ሻይ የመጠጣት ቀርቶ የመቅመስ ዕድል አይገጥመኝም ። ጭራሮ ከግቢ ውስጥ ለቃቅሜ ፣ በጭስ ዓይኖቼ እስኪጠፉ ተሠቃይቼ ያፈላሁትን ሻይ ጋሽ በቄ ፊት ካልሆነ የማልጠጣበት አጋጣሚ ይበዛል ።

ጋሽ በቄ አንደኛ ጉልቤ ፣ ጠይሜ ሁለተኛ ፣ እኔ ደሞ የመጨረሻው ነኝ ። ጠምቤ ካለች ግን በጉልበት የምበልጠው አንድ ሰው ይኖረኛል ።

ሁሌም ጋሽ በቄ ከጫት ጋር ብዙ ስኳር ስለሚቅሙ ፣ ብዙ ለውዝ ስለሚበሉ እንቀናባቸዋለን። የኔና የጠይሜም የወደፊት ራዕይ እንደሳቸው ለመሆን ሆነ ። ከጠይሜ ጋር ተመካከርን ። ዕቅዳችንን ዕውን ለማድረግ ካሰብን ለማሳካት ገንዘብ እንደማንቸገር ርግጠኞች ስንሆን የት ተቀምጠን እንደምንቅም ወሰንን ።

በጎቻችንን ይዘን ወደ ጋራ ወጣን ። ቀን ላይ ለጋሽ በቄ ስንገዛ አብረን በሌላ በፌስታል የከከርነውን ጫት ደብቀን ይዘናል ። በጎቹን ለቀቅናቸውና የድግጣ ቅጠል ቆርጠን አባባ ኪዳኔ እርሻ ውስጥ ከአንድ ዛፍ ሥር ጎዘጎዝነው ። ሹራባችንን አወለቅንና በትላልቅ ድንጋዮች ጠቅልለን ቆርቋሪ ትራስ አበጀን። በአካባቢያችን ማንም ሰው አለመኖሩን ተመለከትንና ሁለታችንም ጫቱን መሀከላችን አድርገን በግራ በግራ ከንዳችን የድንጋይ መከዳችንን ተንተራስን ።

« አቀማመጥ ያምርብሀል ! » አለኝ

ተደሰትኩ ። ምኑንም አይንቀልኝ ስለማያውቅ ድንገተኛው አድናቆቱ ጮቢ አስረገጠኝ ።



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

የመጀመርያዋን ሜት አነሳሁ ። እንደ ጋሽ በቂ የመሀል ጣቴን በአውራ ጣቴ አፋትጌ እያፈናጠርኩ ቀንበጧን ቀንጥሼ አፌ በማስገባት ከሜት ጋር የተያያዘ የመጀመርያ ታሪኬን ምላሴ ላይ ጻፍኩ ።

ጠይሜ በጉንጩ የያዘውን ሜት በስኳርና ለውዝ እያዋሃደ ዋጠው ።

« ኢታታም ያምርብሀል ! » ሲላ አድናቆት ጨመረብኝ ።

መልስ አልሠጠሁትም ። ፍጥነት ይቀርሀል የተባልኩ ይመስል እየተሻማሁ ቀረጣጠፍኩት። ለጥርሴ የጠነከረውን ግንድ ብቻ እየተውኩ በፍጥነት ጎረስኩት ። የጎረስኩትን አኘክ ፣ ድቅቅ አደረግኩት ። አኘኬ ያደቀቅኩትን በለውዝና በስኳር ለውሼ ዋጥኩት ። በኮዳ ከያዝኩት ውሃ ተጎነጨሁ ። በተጎነጨሁት ውሃ አፌን ተጉሞጠሞጥኩ ። ሙቀት ውስጤ ነገሠ ። ውስጤ ቀልጦ ውሃ ሆኖ በገላዬ ፈሠሠ ።

ጠይሜ ከነ ሥሩ ተነቅሎ ፊት ለፊታችን ወደተከመረው የወፍ ቆሎ ግንድ አመራ ። የደረቀውን ሥር ሠብስቦ አመጣ ። ያመጣውን ከፌስታሉ ላይ አኖረው ።

« ምን ያደርግልሃል ?» አልኩት ።

« ለኔ ብቻ አይደለም ላንተም ነው እሺ !»

« ምኑ ? »

« ሥሩም ቅጠሉም ። »

« እኮ ! ምን እና ምን እናደርገዋለን ? »

«አሳይሃለሁ፡፡ ትዕግስት ይኑርህ !»

እጁን ወደ ኪሱ ሰድዶ ክብሪት አወጣ ። የክብሪት ዘንጎቹ በወረቀት ተጠቅልለዋል ። ፓኮ የላቸውም ። ከሌላኛው የሱሪው ኪስ ደሞ የተበተነ የክብሪት ፓኮ አወጣ ። ከተከመረው ሥር አንዱን መዘዘ ። በእስከርቢቶ ቁመት ቆረጠው ። የተቆረጠውን በጥርሱ ነከሶ በከናፍሮቹ አቀፈው። ክብሪቱን ጭሮ በአፉ ወደያዘው ሥር አስጠጋው ። ነበልባሉን ሥሩ ላይ ለጥፎ በቀዳዳው አየር ወደ ውስጥ ሳበ ። ሲምገው ሥሩ ተቀጣጠለ ። ከአፉ ነጭ ጭስ እየተትጎለጎለ ወጣ። ደነገጥኩ። የጠይሜን ጥበብም ተገረምኩበት ። አከታትሎ እየማገ አከታትሎ ጭሱን ቡልቅ፣ ቡልቅ አደረገው ።

ቀናሁበት ። በጠይሜ የሥር ሲጋራ አጫጫስ ተመሠጥኩ ። ከአፉ ላይ ነጥቄው ወደ አፌ አደረግኩት ። ገና ስምገው ጭሱ ውስጤ ተበታትኖ ሳል ለቀቀብኝ ። ጠይሜ ሁኔታዬን እያየ በሳቅ ፍርፍር አለ ።

« ድገምበት ይተውሃል !» አለኝ ።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ደግሜ ሳብኩ ። ሳሉ ባሰብኝ ። እንባ ከዓይኖቼ እስኪፈስ ሳልኩ ። በጠይሜ አሠልጣኝነት እንዴት ሳላስል ማጨስ እንዳለብኝ ተማርኩ ። « ቆይ ጭንቅሎ ...ሌላ ዓይነት አጫጫስ ደሞ ላሳይሽ » አለኝና ሥሩን ምን ጭሱን ባፍንጫው አወጣው ።

ደነቀኝ ። ለመሮካከር ወሰንኩ ። « ማን ከማን ያንሳል !» አልኩ አፌን ሞልቼ ። እንደሱ ማድረግ እንደማያቅተኝ አመንኩ ። በአፍንጫዬ ለማውጣት የሞከርኩት ጭስ ጠፍጣፋዋን አፍንጫዬን የበጠረቃት መሠለኝ ። ንጥሻና ሳል በዛብኝ ። በሂደትም ደረቁን ቅጠል በወረቀት እየጠቀለለ እንደ ሲጋራ እናጨሠው ጀመር።

ጠይሜ በወረቀት የተጠቀለሉ ማጣርያ የሌላቸው የሲጋራ ቁሬዎችን ከኪሱ አወጣ ። በከብሪት እየለኮሰን አጨስናቸው ። ከንፈራችን እስኪጠበስ ቁሬዎቹን መገመግን ።

« ስጠኝ ?» አልኩት

« ስጠኝ አይባልም ?» አነጋገሬን ሊያርም ሞከረ ።

« እና ምንድን ነው የሚባለው ? »

« አስወጋኝ !»

የምንተፋ ፣ የቅሚያ ያከል ተቻኩዩ ቁሬውን መገመግኩት ።

አፍንጫዬ ረዘመብኝ ። ከፊት ለፊቴ የሚታየኝን ማንኛውንም ነገር የሚበልጥ ት...ልቅ አፍንጫ ፊቴ ላይ ተለጥፏል ። ስራመድ አፍንጫዬ መሬቱን እንዳይነካብኝ እየተጠንቀቅኩ ፣ ወደ ላይ ቀና እያደረግኩ አፍንጫዬን ከአደጋ ለመጠበቅ ሞከርኩ ። እየዞረብኝ ነው ። ጠይሜ እዚያችው የድግጣ ቅጠል ላይ በደረቱ ተጋደመ ። እኔም በደረቴ ለመተኛት ስላልቻልኩ ጀርባዬን ተጠቀምኩበት ። ተጋድሜ ወደ ሰማይ ስመለከት አንዲት አውሮፕላን መጣች ። አፍንጫዬን እንዳትገጭብኝ ወደ ታች ተጭኜ ይገዤ ተሳቅቄ አሳለፍኳት ። ብዙም ሳልቆይ እንቅልፍ ወሠደኝ ።

ቀድሞኝ ከእንቅልፉ የነቃው ጠይሜ ቀሠቀሠኝ ። ለዓይን ያዝ እያደረገ ነው ። ርቦኛል ።

« በጎቹስ ? »

ትከሻውን በ«እኔ እንጃ !» ስሜት ሰብቆ የት እንዳሉ አለማወቁን ገለፀልኝ ።

ተነስተን ፈለግናቸው ። የሉም ። ከቅርብ ርቀት ላይ እሳት ሲነድ ተመለከትን ። ተጠጋን። እሳቱን የከበቡትን ጎረምሳዎች እናውቃቸዋለን ። በመንደራችን የታወቁ አጣቢዎች ናቸው ። ከምላስ ላይ ምራቅ ሲሠርቁ የማይነቃባቸው ሞጭላፎች ።

« ኑ ብሉ ! » አሉን ።

ከሚጠብሱት ስጋ እየቦጨቅን በላን ። « ሚዳቋ ገድለን ነው። ስጋዋ አይጣፍጥም ?» ጠየቀን



@BOOKALEM

ከበላተኞቹ አንዱ ። መጋጥና ማኘክ ሳናቆም የሲጋውን ጥፍጥና ጭንቅላታችንን ነቅንቀን አረጋ ገጥንለት ።

በልተን ስንጨርስ የሚዳቋ ያሉትን ቆዳና ጭንቅላት አየነው ። የጠፉችው የጠይሚ በግ ናት ። ጣፍጣን የበላናት ፣ሲጋዋን አኝከን አጥንቷን የቆረጣጠምንላት ። ጠይሚ አለቀሰ ። በፈላጊዎቻችን ታጅበን ወደ ቤት አምሽተን ገባን ። የበጓን በቀበሮ ተበልታ መሞት ተናገርን ።

« አወይ ቀላድ አምባ ከአቦከር በታች

ፍየሏን ያርዱና ይላሉ ሞተች ! » እንዲል መንደርተኛው ።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ ስድስት

## ድብቅ

« ድብቅ » ይባላል የመዋኛ ስፍራችን ። ድብቅ የተባለበት ምክንያቱ ብዙ ነው ። ቀዳሚው ምክንያት ጥቅጥቅ ካለው ጫካ መሃል መገኘቱ ። ሁለተኛው ከውሃው ዳርቻ ከፍተኛ ዲብና ቁጥቋጦ ኖሮ ቦታው በሁሉም ሰው ታዋቂ አለመሆኑ ። የውሃው ጎርፋማ ቀለም ካረፈበት መሬት ጋር መመሳሰሉ እና ለመዋኘት ወደ ውሃው የምንሄድ ልጆች ከቤተሰባችን ተደብቀን በመኾኑ ነው ።

የምንዋኘው ከረምትን ተንተርሶ እየጎረፈ ከሚጠራቀመው የኩሬ ውሃ ውስጥ ነው ። በውሃው ውስጥ የሰው ብቻም ሳንሆን የእንቁራሪት ልጆችም ይዋኙበታል ። የእንቁራሪት ልጆችን «የውሃ እናት» እንላቸዋለን ። ሲዋኙ ያስቀናሉ ። ረጅሙን ጭራቸውን እያወዛወዙ በውሃው ውስጥ እንደልባቸው ሲሯሯጡ ከነሱ ለመስተካከል በደረታችን ዘፍ እንልበታለን ። ከብደታችንን ውስጥ እንደልባቸው... መሽከም ተስኖት ውሃው ከስሩ ያስተኛናል ። ውሃው በአፍና በአፍንጫችን ይገባል። ተፍተን፣ ተናፍጠን ስናበቃ በጭቃ የተለወሠ ገላችንን ለመጨቅየታችን ምክንያት በኾነው ውሃ እንለቀለቃለን ።

መልሠን ከውሃው እንገባለን። እንደ የውሃ እናቶቹ በቅልጥፍና ለመዋኘት እንጣጣራለን ። ለጊዜው የውሃ እናት መኾንን እየተመኘን እንንቦራጨቃለን ። የውሃ እናቶቹ የተካኑትን የዋና ጥበብ ለመኮረጅ ከውሃው ጨልፈን እናወጣቸዋለን ። መዳፋችን ላይ አስቀምጠን ጥቂት ውሃ እንሠጣቸዋለን ። ጭራቸውን እየቆሉ በዋና ባዕድ ከሆነባቸው መዳፋችን ለማምለጥ ይታገላሉ። የዚህን ጊዜ የማገቻ ጥበባችንን እንጠቀማለን ። የእጃችንን ጣቶች ከፊት በማድረግ ውሃውን አፍሰሠን እነሱን አጠንፍፈን እናቆያቸዋለን ። ጥቂት ይንፈራገጡና ፀጥ ይላሉ ፤ ምናልባትም እስከወዲያኛው ።

ጡታችን እንዲያድግልን የውሃ እናቶቹን እናስጠባቸዋለን ። ጡቶቻችንን ሲጠቡልን ደስ በሚል ስሜት እንሞላለን ። «ነከሡችኝ ፣ነዘረኝ ፣ኮረኮረችኝ» እያልንም ማስጠባታችንን አንተውም። በተለይ ተለቅ ተለቅ የሚሉት የውሃ እናቶች ጡት ሲጠቡ ደስ ይላሉ ።

ጭራቸውን ደብቀው እጅና እግር ሲያወጡ እንደነግጣለን ። ዕድገታቸው ያስፈራናል ። እንኳንስ እንደ ድሮው እጃችን ላይ ልንይዛቸው ፣ ጡታችንን ልናስጠባቸው ይቅርና ፍንጥር፣ ፍንጥር ሲሉ እንሸሻቸዋለን ። ፍቅራችን ባይቀንስም በፍርሀት እንደታጀበ ግን ውስጣችን ይኖራል። በፍርሀት የታጀበ ፍቅር ደሞ ደስ ይላል ።

እኔ ፣ ጠይሜና ጠምቢ ወደ ድብቅ ስንሄድ ከቤተሰባችን እንደበቃለን ። ወደ ጫካ ሄደን



@BOOKALEM

ኩሬ ውስጥ ስንንቦራጨቅ መዋላችንን ቢሠሙ ይገድሉናል ። ወደ ድብቅ እንዳንሄድ ብዙ ጊዜ ብዙ ማስጠንቀቂያዎች ተሠጥተውናል ። ማስፈራሪያ የሚጨመርበት ጊዜ ይበዛል ። በተለይ ስለ ጭራቅ የሚነገረንንማ እያለቀስን ነበር የምናዳምጠው ።

ጭራቅ ማለት ሰባት ቀንዳም ጭንቅላቶች ፣ አስራ አራት ምላሶች ፣ ብዙ ሺህ ጥርሶች ፣ ረጅም ሠንሠለትና ልጅ የሚያርድበት ት...ልቅ ቢላዋ ይዞ የሚዞር መጥፎ ፍጥረት መሆኑ ይነገረናል። ባለጌ ልጅ ሠርቆ ይወስድና እ...ርድ አድርጎ በማሰሮ ቀቅሎ ይበላዋል ። የባለጌውን ልጅ ደም ጥጥት ፣ ስጋውን ብልት ያደርጋል ። የቤተሰቡን ምክር የማይሠማ በቤተሰቦቹ ፍላጎት ለጭራቅ የሚበረከት ልጅ እንደሚኖርም ይነገረናል ። በቃ ይህ ታሪክ የሚነገረን ማታ ፣ ማታ ስለሆነ አዳራችን የተመሠቃቀለ ፣ በቅገርት ፣ በብንኛና ጩኸት የተሞላ ይሆናል ።

ሲነጋ...በተለይ ሦስቱ ጓደኛሞች ከተገናኘን ይህን የጭራቅ ታሪክ እንረሳዋለን ። ዕድሜ ለጠይሜ ጭራቅ የሚኖረው ሩቅ ሀገር እንጂ ድብቅ ውስጥ አለመሆኑን ወደ ዋና የሄድንባቸውን ተደጋጋሚ ቀናት እያስታወሰ ፍርሀታችንን ያስወግድልናል ።

የምንዋኝበትን የዋና ዓይነት በአብዛኛው የመወሡኑ ስልጣን የጠይሜ ነው ። « ጭልምታ ግቡ» ካለ ቻልንም አልቻልንም ከዲቡ ላይ ተወርውረን ጭልምታ እንገባለን ። ጭልምታ ሲገባ ውሃው ውስጥ ጥቂት መቆየት ግድ ይላል ። ውሃ በጆሮና አፍንጫችን እንዳይገባ መጠንቀቅ ሥላለብን የተለያዩ ሙከራዎችን እናደርጋለን ። በጥጥ ቀዳዳዎችን ጠቅጥቆ መግባትን ሳይቀር ሞክረነዋል ።

አምስት ፣ አምስት ደቂቃዎችን ውሃ ውስጥ በመቆየት ተስማማን ። ጠይሜ ቀድሞን ገባ ። አስር ሠኮንድ እንኳን ሳይቆይ ወጣና « ሰባት ደቂቃ ቆይቻለሁ » አለ ። ብንከራከረውም « ሰባት ብያለሁ ሰባት» ብሎ ድርቅ ከችች አለብን ። አምባገነን ነው ።

ቀጥሎ ጠምቤ ገባችና ሳል በሳል ሆና ወጣች ። አስታወከት ። እኔና ጠይሜ በቅሽምናዋ ሳቅንባት ። ሁለቱንም በዋና እንደምበልጣቸው ርግጠኛ ሆኜ ዲቡ ላይ ወጣሁ ።

« አፍንጫና ጆሮህን በጣትህ ዘግተህ ግባ » አለኝ ጠይሜ

« እንዴት ?»

« እንዲህ ነዋ ! » ይዞ አሳየኝ

በሁለቱ አውራ ጣቶቼ ጆሮዎቼን ፣ በሁለቱ የመሀል ጣቶቼ ደግሞ የአፍንጫዬን ቀዳዳዎች ደፈንኩ ።

« አንድ... ሁለት... ሶስት! » ብለው ለሁለት ቆጠሩልኝ ።

ዘለዬ ገባሁ ። በግንባሬ ተተከልኩ ። ዞረብኝ ። እጄን ከጆሮና አፍንጫዬ አላቅቄ በአሸዋማ ጭቃ የተጋጠውን ግንባሬን እያሻሸሁ ከውሃው ብቅ አልኩ ። ጠይሜና ጠምቤ ተራቸውን ሳቁብኝ ።



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ለነገሩ ግንባሬ አብጦ ኖሯል።

ግንባሬ በጣም እያበጠ ሲመጣ ሁለቱም ደነገጡ ። እያመመኝ አሹልኝ ። በተለይ ጠይሜ ሲያሽ በጣም ያሳምማል ። ሆን ብሎ ለማሳመም እንጂ እብጠቱን ለመቀነስ አይደለም ። ጠምቢ ግን እያባበለችኝ ለስሀን አሰተሻሸቷ ተመችቶኛል ።

« ወይ ጭንቅሎ...ድፍረትህ ይገርማል ። ማሰሮ የሚያክል ጭንቅላት አንገትህ ላይ አስቀምጠህ ጭልምታ ለትግብ አታፍርም? እናቱ ትሙት ደፋር ነህ እሺ !»

የጠይሜ ንግግር አበሳጨኝ ።

« ጠይሜን ወግር ባደርገውስ ? ምን አባቱ ያመጣል ? » አልኩ ለራሴ ። ግን ደሞ ከሱ ጋ ለመ ደባደብ መሞከር እንደማያዋጣኝ ሲገባኝ ተውኩት ።

« ጭንቅሎ...ቤተሰቦችህ ያበጠውን ግንባርህን ሲያዩ ምን ይሉሃል ?» አለችኝ ጠምቤ

« ምን ይሉታል ?»

« እንዴት ምንም አይሉኝም ?» ጠይሜ ላይ አፈጠጥኩበት ።

« እህ ...ያንተ ጭንቅላት እኮ በየቀኑ ስለሚያድግ ማበጡ አያስፎግርም ብዬ ነው ። አይደል እንዴ ጠምቢ ?»

« አዎ ! » ጠምቢ ፈርታው ይሁን ንግግሩ አሳምኗት የጭንቅላቴን በየቀኑ ማደግ በእምነት አረጋገጠችለት ።

ተናደድኩ ። ጠምቤን ገፍትሬ ውሃው ውስጥ ጨመርኳት ። ጠይሜ እንድገፈትረው ፈልጓል። ውሃ ውስጥ መደፋፈቅ ስለምንጨዋወት በዚያው ሊያረሳሳኝ ሞከረ ።

« እስቲ ልብ ካለህ እኔን ገፍትረኝ ? ፈሪ !» አለኝ ጠይሜ

እልህ ያዘኝ ። ጠይሜ እየደጋገመ በማስፈራራት ሠበብ እንድገፈትረው ይትተትኛል ። የተቀመጥንበት ዲብ ከውሃው ከፍ ይላል ። ሲብስብኝ ቢመታኝም ይምታኝ ብዬ ገፈተርኩት ። እጄን ይዞ ወረደ ። ሁለታችንም ውሃ ውስጥ ወደቅን ። ጠምቤም ተጠጋችኝና ውሃ በመረጫጨት ተጫወትን ። ሁሉንም ረሳነው ።

ወደ ቤት ከመሄዳችን በፊት ከርቀት የሌሎች ልጆችን ድምፅ ሠማን ። ሲዋኙ የሚመጡ የአከምባሎ ሠፈር ልጆች ናቸው ።

« በዋናማ አንደኛ እኔ ነኝ ! የለም እኔ ነኝ !» መባባላቸውን የጠይሜ ጆሮ አረጋገጠ ። ሁሌ እን ደምናደርገው ሽንታችንንም አራችንንም ውሃው ውስጥ ደበቅነው ። ትኩስ ሽንትና ትኩስ እር ውስጥ ሲዋኙ እያየን ለመሳቅ ተደበቅን ።



@BOOKALEM

« ና ! እስቲ ጭንቅሎ ! » አለኝ አባቴ እቤት እንደገባሁ ።

ተጠጋሁት ። አተኩሮ ግንባሬን ተመለከተው ። ለመማታት ሲፈልግ ነገሮችን በአንክሮ ማየት እንደሚወድ አውቃለሁ ። የሸሚዜን ቁልፍ ፈታና አመዳም ገላዬን ተመለከተው ። ወደ አፍንጫው አስጠግቶ ጠረኔን ማገ ።

« ከሞተ ዓሳ ጋ ተኝተህ ነበር እንዴ ? » ብሎ ገፈተረኝ ።

ተንገዳግጄ ቆምኩ ።

« የት ነው የዋልከው ? » አፈጠጠብኝ ።

ዝም ።

መልስ አጥቼ አይደለም ። የዋልኩበትን ከነገርኩት በበርበሬ ያጥነኛል ። እሳት ላይ በርበሬ አጭሶ ብዙ ቀን ንፍጥ በንፍጥ አድርጎኛል ። ዛሬም ንፍጥ በንፍጥ ስሆንለት እያየ እንጀቱ ቅቤ እንዳይጠጣ ፈለግኩ ። እኔ በበርበሬ ጢስ ታፍኜ እየተቃጠልኩ ሳለቅስ ፤ ሳስነጥስና ሳስል አንጀቴን ለማሳረር ሲስቅብኝ ማየት ከምንም በላይ ያመኛል ።

«እየጠየቅኩህ ነው ? » ግድግዳ ላይ ወደ ተሠቀለችው አለንጋ ተመለከተ ።

ሽንቴ መጣብኝ ። ከያዘ እንደማይለቀኝ ስለማውቅ ተንቀጠቀጥኩ ። ሮጬ አምልጬ ከቤት መጥፋትም አማረኝ ።

« የትም አልሄድኩም !» አልኩትኝ በግግምና ።

«ቀጣፊ ! የትምማ ሄደሃል እንጂ ። እንዲህ በአመድ ያጠቡት ጥቁር አሻንጉሊት መስለህ የመጣኸው የትም ሳትሄድ ነው ?» አለንጋዋ እላዬ ላይ አረፈች ።

« ሄጃለሁ ! ሄጃለሁ ! ከነ ጠይሜ ጋር ሄጃለሁ ! » ለፈለፍኩ ።

« እኮ! ሄደህማ እንደነበር ሳትነግረኝ አውቄያለሁ ። ግን የት አባክ ነበር የሄድከው ?» ሁለተኛዋን ደገመኝ ።

« ድብቅ !»

« አትሂድ ብዬህ ነበር አይደል ?» ሦስተኛዋን ቀመስኩ።

« ብለኸኝ ነበር አባይዬ ! እነ ጠይሜ ናቸው'ኮ...»

« ከኔና ከነ ጠይሜ የማን ቃል ነው መደመጥ ያለበት ?»

አራት ።



@BOOKALEM

« ያንተ ! ያንተ ! ያንተ ነው መደመጥ ያለበት !»

« እኮ ! መቼ ቀን ሠምተኸኝ ፣ መቼ ቀን አድምጠኸኝ ታውቅና አንተ ቀጣሬ ! »

አምስተኛዋን ተወጋሁ ።

« ካሁን በኋላ እሠማለሁ ። አይለመደኝም ። ሁለተኛ ...ሁለተኛ አይለመደኝም ። አባይዬ _ የዛሬን ማረኝ ! በጊዮርጊስ የዛሬን ብቻ ማረኝ ! የዛሬን ብቻ ! »

እግሩ ላይ ተጠቀለልኩበት ። ተንገዳገደ ። ይገድለኛል እንጂ አንስቼ ባፈርጠው ምንኛ በተደሠትኩ ።

« ሁለተኛ ወደ ድብቅ ትሄዳለህ ?»

« ኧረ ምን በወጣኝ አባይዬ !»

እናቴ እየሳቀቀችብኝ መሠናበቻዬን ከአባቴ እጅ ተረከብኩ ። ደግሜ ወደ ድብቅ እንደማልሄድ በመሃላ አረጋገጥኩለት ።

አባቴ ፀጉሬን እየደባበሠ ሲገርፈኝ በሰውነቴ ላይ ያስቀረውን ማህተም አሻሸልኝ ። ሁሌም ከመታኝ በኋላ አቅፎ ይደባብሠኛል ። ዓይኖቹ እንባ እያቀረሩ ፣ ሠንበሮቹን በጣቶቹ ሲያጠፋልኝ ይሞክራል ። እኔ ግን መመታቴም ጎልቶ የሚሠማኝ የዚያኔ ነው ። በእጁ ሠንበሮቼን ሲደባብሳቸው የልፋት ውጤቱን እየገመገመ « ለነገ የቱ ጋ ብመታው ውጤታማ እሆናለሁ ። የት ጋ ብመታው ተለቅ ያለ ሠንበር ሊያወጣ ይችላል ?» እያለ ከራሱ ጋር በኔ ገላ የሚማከር ይመስለኛል ።

***

የክፍላችን ተማሪዎች ወንዶቹ በእንዳልካቸው ፣ ሴቶቹ ደሞ በሰንታየሁ ቆጮ እየተመሩን ድብቅ ደረስን ። ቅዳሜ በጠዋት ከየቤታችን የወጣነው «ትምህርት ቤት ተጠርተናል» የሚል ሰበብ ፈጥረን ነበር ። ለሰበብ የተመረጠው ደሞ የሳይንስ አስተማርያችን ጋሽ ተፈራ የኋላእሸት ።

ጋሽ ተፈራን ለሰበብነት ያስመረጠው የቀደመ ትዕዛዙ ነበር ።

«... በሰው ሠራሽ መንገድ ትምህርት ቤታችን ውስጥ ዓሳዎች እናረባለን ። ለዚህም ታስበው የተዘጋጁ ሁለት ገንዳዎች አሉ ። በአንደኛው ገንዳ ውስጥ ቅድሚያ የውሃ ውስጥ ዕፅዋትን እንተክላለን ። በቀላሉ ዓሳዎቹ እየተመገቡት እንዲያድጉ እናደርጋለን ።

«...በሌላኛው ገንዳ ውስጥ ደሞ ዓሳዎችን እንጨምርና ዳቦ ፣ ጉበት ፣የተለያዩ ትላትሎችን እየሠጠን እንመግባቸዋለን ። ከዚያ በየትኛው ገንዳ ውስጥ ያሉት ዓሳዎች ተስማምቷቸው እንደሚራቡ እናጠናለን ። ለዚህም የተግባር ሙከራ ዓሳዎችን ማቅረብ የናንተ ግዴታ ነው ። —» ብሎናል ።



@BOOKALEM

የጋሼን ግዴታ ተከትለን ሰበብ ፈጠርን ። ተያይዘን ፣ ተጠራርተን ወደ ድብቅ ሄድን ። ዝናብ በዘነበ ቁጥር ብቻ እየተጠራቀመ ለዋና በምንጠቀምበት ኩሬ ውስጥ ዓሳ እንደሌለ በተለይ ወንድ ወንዶቹ በደንብ እናውቃለን ። ውኃቿን እዛው ነዋ ። ከቤት ጠፍተን ድብቅ ፣ ከትምህርት ቤት ፎርፈን ድብቅ ነዋ ምሽጋችን ። ድብቅ ውስጥ እንቁራሪት እንጂ ዓሳ የለም ። ኖሮም አያውቅም ።

በርግጥ ድብቅ ከመድረሳችን በፊት በሚሊቴሪ ፖሊስ ጫካ ውስጥ አቋርጦ የሚሄደውን አነስተኛ ጅረት ፈትሸነዋል ። ውሃው ዓሳ ቀርቶ የውሃ እናት የመያዝ አቅምና ፍላጎት የለውም ። እኛ የዘወትር አንበራሜቂዎቹ እያለን ሰላም የለውምና ዓሳን አዚያች ውሃ ውስጥ ማሰብ ጅልነት ነው ። የማይካደው ከድብቅ በተሻለ ኩልል ያለ ንፁህ ውሃ አለው ።

ለወራጁ ውሃ መገኘት ምክንያቶቹ «ማመላለሻ» እና «ጥገና» የሚባሉት የወታደር መሥርያ ቤቶች ናቸው ። ሁለቱም ጋ የመኪና እጥበት ይካሄዳል ። ለሃያ አራት ሰዓታት የአስፋልቱን ዳርቻ የውሃ መውረጃ ቦይ ተከትሎ ሲፈስ ይውላል ፤ ያመሻል ። የተቃጠለ የመኪና ሞተር ዘይት ( «ኦሊዮ» እንለዋለን ) በውሃው ላይ ሲንሳፈፍ ፣ ከተንሳፈፈው ዘይት ሥር ውሃው እየተሽሎከሎከ ሲወጣ ያስደምማል ።

በውሃው ላይ የቀስተ ደመናን ቀለም ተዘበራርቆ ስናየው እንረካለን ። ሰማይ ላይ ተመልከተን « አረንጓዴ ፣ ቢጫ ፣ ቀይ የማርያም መቀነት የኔ !» የምንለው ጨዋታ ውሃ ጠብ ካለበት ይለወጣል። የኔነቱን ለማረጋገጥ እተቀመጠበት ደርሠን በእጃችን እንነካዋለን ። በቀለማት አሸብርቆ ፣ አጓጉቶን፣ ስሜትና ቀልባችንን ገዝቶ ተስገብግበን በእጃችን የዘገንነውን ከውሃው ካነሳነው በኋላ እጃችን ላይ እናጣዋለን ። ሌላ ግርምት የሚፈጥር ተዓምር !

ለነገሩ በ«ኦሊዮ» ክፍላችን ውስጥ ያላፈረጥነው አስተማሪም የለም ማለት ይቻላል ። ከፍላችንን አፅድተን ስንጨርስ «ኦሊዮ» አርከፍክፈን እንወለውለዋለን ። በደንብ ያፀዳ ክፍል የሰንደቅ ዓላማ ሠልፍ ላይ ከፍተኛ ሞራል በሌሎች ክፍሎች ተማሪዎች እንዲሠጠው ይደረጋል ። ታድያ ከአስተማሪ ጋር ስንጣላ ሠሌዳው አካባቢ በዛ ኦድርገን እንደፋዋለን ። «ቲቸር » ሆዬ አገር አማን ብሎ ሠከም ፣ ሠከም ሲል አንድ እግሩን ሠቅሎ በጀርባው ይፈርጣል ። ከዚያ ምድረ ተሜ ውስጥ ለውስጥ እየተጎነታተለ በሳቅ መንፈቅፈቅ ነው ።

ሴቶቹ ዳቡ ላይ ተቀምጠው ሞራል ይሠጡናል ። ወንዶቹ ደሞ ውሃው ውስጥ በመዳፋችን አቅም ውሃ እየዘገንን እንረጫጫለን ። እንንቦረጫጨቃለን ። ሴቶቹ የከፍል ጓደኞቻችን ስላሉ እኔና ጠምቤም ያለ ልምዳችን ከነ ቁምጣችን ገብተናል ። ድብቅ ገላዬን እንጂ ቁምጣዬን አበስብሷት አያውቅም ነበር ። ዛሬ ግን ዕድሜ ለከፍሌ ሴቶች እየተመኘ አበሠበሳት ። ከሚስቁት ልጆች መሃል ትበልጪን አየኋት ።

«ብራቮ ! ጭንቅሎ !» አለችኝ በምልከት የቀኝ እጅ አውራ ጣቷን ወደ ኋላ አጥፋ።

ሞራሌ ጢም አለ ። በደረቴ ውሃው ላይ ተኛሁ ። ውሃው እንደማንሳፈፍ አድርጎ እግሬን ወደ ሰማይ ፣ ጭንቅላቴን ወደ ወለሉ ወሠደው ።



@BOOKALEM

« ብራቮ ! ጭንቅሎ ! ጭንቅሎ ጭልምታ ገባ !» ጭብጨባ ፣ ፉጨትና የሴቶቹ እሪታ ይሠማኛል ።

ወደ ጎን ዘርግቼ እንደ ዋናተኛ ልቀዝፍባቸው የምከርኩባቸውን እጆቼን ወደ ወለሉ ሠደድኩ። እግሬን ወለሉ ላይ አሳረፍኩት ። እንገቴን ብቅ ኢደረግኩ ፡፡ ነፍሴ መለስ አለች ።

« ብራቮ ! ብራቮ ጭንቅሎ !» ወንዶቹ አድናቆታቸውን ገለፁልኝ ።

በልበ ሙሉነት በሁለት እግሬ ውሃው ውስጥ ቆምኩኝ ። ወንዶቹ ከትከት ብለው ሳቁብኝ ። ገሚሶቹ ሴቶች እኔን ላለማየት ፊታቸውን አዞሩ ። አንዳንዶቹ ደሞ ዓይኖቻቸውን በመዳፎቻቸው ሸፈኑ ።

« ኧረ ጭንቅሎ እፈር ! » አለኝ ጠምቤ ከርቀት ሆኖ ።

እጄን ወደ ጠቆመበት አቅጣጫ ዓይኖቼን መለስኩ ። ቁምጣዬ እላዬ ላይ የለችም ። ራቁቴን ነኝ ። ሁሉም ነገር ገባኝ ። የወንዶቹ ሆታና የሴቶቹ እሪታ መንስዔ የዋና ጥበቤ ሳይሆን ቁምጣዋ ጠፍቶባት በእፍረት የተኮማተረችው ወሸላዬ ነበረች ። ሳያት ለራሴም አሳቀችኝ ። ቁምጣዬ ምኔ ከላዬ እንደወለቀች እንጃ ። ውሃው ውስጥ እጄን አልብሼ አስቀመጥኳት ወሸላዬን ።

በእንዳልካቸው መሪነት ወደ ሌላ ከመንደራችንም ፣ ከትምህርት ቤታችንም ወደ ራቀ የዋና ሥፍራ ሄድን ። ቦታው በተለምዶ «የመሀመድ እርሻ» ይባላል ። አካባቢው ከማማሩ በተጨማሪ ፍራፍሬው ያስጎመጃል ። ዘይቱናውን ፣ ማንጎውን ፣ ጊሽጣውን ፣ ሙዙን ፣ብርቱካኑን፣ ኮኩን ፣ፓፓያውን ፣ሸንኮራ አገዳውን ገና ስናያቸው ቋምጠንባቸዋል ። ዋኝተን ስንመለስ እንደምንሠርቅም ተነጋግረናል ።

ውሃው በጣም ደስ ይላል ። ስፋቱ ያስገርማል ። ጥልቀቱ ምን ያክል እንደሆነ ግን ከእንዳልካቸው በስተቀር የሚያውቅ የለም ። ወንዶቹ ልብሶቻችንን አወላለቅን ። እንዳልከ ከዳር እስከ ዳር በውሃው ውስጥ በእግሩ እየተጓዘ እንደማያሠምጥ አሳየን ። እየዘለልን ገባንበት ። መንቦራጨቅ ፣ መረጫጨት ጀመርን ። ጫጫታችን የአካባቢውን ፀጥታ ጠረመሠው ።

በስንታየሁ ቆጬ ቀዳሽነት የተጀመረው የሴት ዋናተኞች ቁጥር ቀስ በቀስ ጨመረ ። ሴት ወንድ ሳንል ተቀላቅለን ውሃው ውስጥ ተከተትን ። በደረት ተኝተው ለመዋኘት ከሚሞክሩት በተለየ እንደ እንቁራሪት እንጣጥ ፣ እንጣጥ የሚሉት ያስቃሉ ። ዋና ባንችልም በማይችሉት መሳቃችን አልቀረም ። በተለይ አይቸውና አቤልማ የሚዋኙ ሳይሆን የሚያሽበሽቡ ነው የሚመስሉት ።

እኔና ጠምቤ ከሴቶች ጋር ተቀላቅለን ዋኝተን አናውቅም ። መዋኘቴን አቁሜ ትብልጨን ማድነቅ ጀመርኩ ። ፀጉሯ በውሃው ርሶ ፣ አንገትና ትከሻዋ ላይ ተለጥፎ እንደራበው ውሻ ተኮራምቷል ። የጡቶቿ ጫፎች አበጥ ፣ አበጥና ሾል ፣ ሾል ብለዋል ። ጡቶቿ ያደጉላት በውሃ እናት አስጠብታ እንደሆነ አመንኩ ። ጓደኞቻችን ባይኖሩ ጡቶቿን ጨምቄ ምን እንደሚወጣው እመለከት ነበር ።



@BOOKALEM

ትበልጪ አንድ እግሯን ከመሬቱ ሳትነቅል በሁለት እጇቿ ውሃውን ሸብረክ ብላ እየቀዘፈች መሬት ያልረገጠውን እግሯን ቀና ታደርጋለች ። ወደ ውሃው ሳትገባ በፊት ነጭ የነበረው ሙታንቲዋ በምንዋኝበት ውሃ ቆሸሸባታል ። ገዢታው ሳይሆን ከውሃው ውስጥ አግኝታ ያጠለቀችው ይመስላል ። እቤት ስትገባ እንዳይገርፏት ሠጋሁላት ። እንደኔ በአለንጋ እየተሰጠለጠች በበርበሬ እንዳትታጠን ፈራሁላት ። በባለ ሁለት ምላስ አለንጋ ላጥ ላጥ ሥትደረግ ያበጡት ጡቶቿ እንዳይፈርጡ ፈራሁላት ። ወይ ደሞ ጡቶቿ ሲፈርጡ ከውስጣቸው የሚወጣውን ነገር ለማየት እንድታደል እነሱ ቤት በሆንኩ ወይም እኛ ቤት አብረን በተገረፍን ስል ተመኘሁ ።

« ምን ሆነህ ነው ጭንቅሎ የምታለቅሰው ?» አለኝ አቤል ተጠግቶ

« ምንም !»

« ታድያ ዓይንህ ውስጥ ትንኝ ገብቶብህ ነው ያስለቀሰህ ? »

« ኧረ ! አላለቀስኩም ። »

« ይኸው እያለቀስክ አይደል እንዴ ?»

« ኧረ ! እኔ አላለቀስኩም ።»

« ካላመንከኝ ጎንበስ በልና በውሃው ውስጥ ፊትህን እየው ። »

አፈርኩ ። ሳይታወቀኝ ስለ ትበልጪ እያሰብኩ እያለቀስኩኝ ነበር ። ከውሃው ዘግኜ ፊቴን ታጠብኩት ። እንዳልከ ከምንዋኝበት ግድብ ወጣ ። ራቁቱን ወደ እርሻው ውስጥ ገባና የሆነ ትልቅ ብረት ይዞ መጣ ። ያረጀ ማረሻ መሠለኝ ። የግድቡን ውሃ ለማፍሠስ ግድግዳውን ቆፈረው። ወንዶቹ በጉልበት አገዘነው ። ውሃው መሹለኪያ ቀዳዳ ሲያገኝ ግድግዳውን በደሠው። አቤልና ትበልጪን እያንደባለለ ይዟቸው መጥቶ ከግድግዳው ጋር አላተማቸው ። ውሃው ያልተጠነቀቅነውን በሙሉ ከእግራችን እየሰቀሰቀ ፤ እያጋደመ እንደባለለን። እንዳልከ ግን እየሆነ ባለው ነገር ተደስቶ ይስቃል።

ውሃው ፈሰሶ እርሻውን አጥለቀለቀው ። ለውዝና ስኳር ድንቹ በውሃው ተዋጡ ። ልብሳችንን ለብሰን ከአካባቢው መጥፋት ፈለግን ። የአንዳችንም ልብስ የለም ። ፈልገን ፤ፈልገን አጣነው። ሴቶቹ ማልቀስ ጀመሩ ። የኔም ሱሪ የለችም ። « አውልቀው ለዐመት በዓል ይታጠብልህ » ስባል እምቢ ብዬ ነበር የመጣሁት ። አልቅሼ እለብሳለሁ ብዬ የገገምኩበትን ሱሪዬን ጥዬ ስገባ የምገረፈውን ሳስብ ተንቀጠቀጥኩ ።

የእርሻውና የግድቡ ባለቤት መሀዲ ሜንጫና ረጃጅም ርጥብ የባህር ዛፍ ግንጣይ አርጬሜዎችን ይዞ መጣ ። ፈራነው ። ውሃውን ለቅቀን እርሻውን ያበላሸንበትን ምክንያት ጠየቀን ። መልስ ሲያጣ በቅርበት ፊት ለፊቱ ተገትሮ ያገኘውን ጠምበለልን በአርጬሜው ገርጥ አደረገው ።



@BOOKALEM

ጠምቢ ሮኸች ። በውሃ የራሠ ገላዋን አርጬሜ ሲነካባት አበደች ። መሀዲን ሁላችንም ፈራነው። ትበልጪማ ስትርገፈገፍ ላያት አጣዳፊ ወባ የያዛት ትመስል ነበር ። መሀዲ ከሚፈራቸው ነገሮች አንደኛው ወታደር እንደሆነ መጀመርያውኑ እንዳልኩ ነግሮናል ።

አርጬሜውን ለተረኛ ተገራፊ እያሰናዳ የወላጆቻችንን ሥራ ጠየቀን ። ሁላችንም የወታደር ልጆች መሆናችንን ገለፅንለት ። የውሸታቸውን የወታደር ልጆች ነን ያሉም ነበሩ ። አርጬሜውን በቅፅበት ወረወረው ። እኛን ከገረፈን የሚከተለውን ገምቶ ስለፈራን ደስ አለን ። አጠገባችን የሌሉትን ወታደሮቹን አባቶቻችንን እያሰብን ተጀነንን ። ተጠቃቅሠን ሳቅንበት ። አንዳንዶቹ ሴቶች አለቃቀሱ ። እጆቻቸውን ዳቦዎቻቸው ላይ ጭነው የመጡበትን ሁኔታ ረገሙ ።

ከወንዶቹ ጋር ተቀላቅላን የምትስቀው ሰንታየሁ ቆጬ ብቻ ናት ። የትበልጪን እንባ ማየት ከበደኝ ። የትበልጪ እንባ የኔን እንባ ተጣራ ። ሰሰሷ ... ስለትበልጪ አለቀስኩ ።

እንድንንበረከክ ታዘዝን ። ተንበርከከን ጎን ለጎን ተንሾካሾከን ። የምናመልጥበትን ዘዴ ፍለጋ ተመካከርን ።

« እንሩጥ ! » አለኝ ጠምቤ

« እሺ ! »

« ግን ሮጦ ቢይዘንስ ? » ጠምቤ ራሷ ሃሳቡን አምጥታ ራሷ ፈራች ።

«ሳያየን ነዋ የምንሸውደው !» ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብዬ ነገርኳት ።

« እሺ ተዘጋጅ ።»

« ልቁጠር ?»

« ምንድን ነው የምትቆጥረው ? »

« አንድ ፣ሁለት ፣ሦስት ልል ነዋ ! »

« ጭንቅሎ ደሞ...ቢያንስ ለችግር ቀን እንኳን ብልጥ አትሆንም እንዴ ?»

ተናደደብኝ ። እንደተንበረከከን ወደ ኋላ መንፏቀቅ ጀመርን ።

« እንዳታስፎግር ! » አስጠነቀቀኝ ።

ጢሻ መሠሉን የወፍ ቆሎ ከእጋቻችን ዓይኖች ተከለልንበት ። መሀዲ ከተንበረከኩት ጓደኞቻችን ፊት ለፊት ሽርጡን ሲበሶ የፍየል ቆዳ አንጥፎ ጫቱን ይቅማል ። ስላላየን ፣ ስለሸወድነው ደስ አለን ።

«በል ከዚህ በኋላ እንሩጥ !» ጠምቢ እንንቡሳ ቁልቁል ሮጠች።



@BOOKALEM

ተከተልኳት ። ቁልቁለቱ እንደርድሮ እንከባለለኝ ። ሰውነቴ ተጋጋጠ ። ደሜ ከውስጤ እገር ሆኖ በቆዳዬ መፍለቅ ጀመረ ። በእንቅፋትም ፤ በግጭትም ቀድሞ አደጋ የማያጣው ትልቁ ጭንቅላቴ አብጧል ። ጠምቤም የቆንጥር እሾህ በጫጭቃት ታለቅሳለች ።

ራቁታችንን መሆናችንን ስናይ ደነገጥን ። መጥፋታችን ትክክል እንዳልነበር ተማመንን ። ያለ ልብስ ወዴትም መኼድ እንደማይቻል ሲገባን ወደ ኋላ ለመመለስ ተስማማን ።

መሀዲ መጥፋታችንን አውቋል ። ይህንን ያወቀውም በስም ወይም በመልክ ለይቶን ሳይሆን በልብሳችን ነበር ። የጓደኞቻችንን ልብስ ሲሠጥ የኔና የጠምቤ ተረፈው ።

እንዳልካቸው ተንበርክኳል ። ራቁቱን ነው ። በአራት መዐዘን ያለቅሳል ። ጀርባው ሠንበር በሠንበር ሆኗል ። ጥቁር ቆዳው ቀያይ ሠንበር ተሸከሟል ። የተቀጣው በኛ ምክንያት ነበር ። መጥፋታችንን ሲያረጋግጥ እንዳንፎገር እስቦ « የኔ ሱሪዎች ናቸው ። ከቤት ስወጣ ደራርቤ ለብሻቸው ነው ። » ብሎ ሊሸውደው ሞከረ ። መሀዲ የእንዳልከን መዋሸት ሲያውቅ ተናዶ ገረፈው ። እንበረከከውም ።

ወደ ጓደኞቻችን ስንመለስ ሴቶቹ ጮኹ ። መሀዲ ደንገጥ ብሎ ተመለከተን ። ተጠጋነውና ለይቅርታ እግሩ ሥር ተንበረከክንለት ።

« የት ነበራችሁ ? » አርጩሜውን ጨብጦ አፈጠጠብን ።

« ሸንታችንን ልንሸና ሄደን ነው ። »

« ሸንታችሁን ብቻ ? »

« ኧረ ! አራችንንም አርተናል ። » አልኩት ፈጥኜ ።

« የት ? »

« እ...ዚያ የወፍ ቆሎው ሥር ።»

« እርሻዬ ውስጥ እንድታሩ ማን ፈቀደላችሁ ? »

« ወጥሮን ነው ። ይቅርታ አድርግልን ።» ጠምቤ ለመነችው ።

እንዳልከን ከተንበረከከበት አስነሳውና እንዲገርፈን አዘዘው ።

« እኔ አልማታም ። ከፈለግክ አንተ ምታቸው ። »

« ያዘዝኩህን ፈፅም ! ያለበለዚያ አንተን ነው የምመታህ ! »

« እንደፈለግክ ምታኝ እንጂ ጓደኞቼን አልመታም ። »

« ሦስታችሁም ፊት ለፊቱ ሸንታችሁን ሽኑ ! »



@BOOKALEM

ፈራንም ፤አፈርንም ።

« አፍጥኑት ! » መሀዲ በቅል ከያዘው ወተት እየተጎነጨ አዘዘን ።

ሦስታችንም ተያየን ። የጓደኞቻችን ዓይኖች ጠቅላላ ወደኛ አነጣጥረዋል ።

« አውጡት !» መሀዲ ፊት ላይ የደበዘዘ ፈገግታ ብቻ ይታያል።

ዝም አልነው ።

እጆቻችንን በቁምጣችን በኩል አሾልከን መሽኛዎቻችንን ጨብጠናል ። ለመሳቅ ያቆበቆቡት ጓደኞቻችን እንገታቸውን እሠገጉ ።

መሀዲ በያዘው አርጩሜ ቂጥ ቂጣችንን ሲልጠን አውጥተን አንፎለፎልነው ። ጓደኞቻችን አስካኩ ። ጭራሽ ሞራል ይሠጡን ጀመር ።

« ብራቮ ! ጠምቤ ብራቮ !»

« ራስ በዛብህ ተቀደምክ !» በጭንቅላቴ ትልቀት ሲቀልዱ እንዲህ ነው የሚሉኝ ።

« እንዳልከ ብራቮ ! »

እየተሳቀቅን ስንሸና መሀዲ መሽናት እንድናቆም አስጠነቀቀን ። ደንግጠን ቁምጣችን ላይ ጭርቅ ፣ ጭርቅ አደረግነው ።

« እርሻዬ ላይ ለምን ሸናችሁ ?» መሀዲ ግራ የተጋባንበትን ጥያቄ ሠነዘረ ።

« እራስህ ሽኑ ብለኸን አይደል እንዴ ?» እንዳልከ ጥያቄውን በጥያቄ መለሠበት ።

« አንተ ጥጋበኛ እንዳልጨምርልህ እሺ ! ሽኑ እንጂ እርሻዬ ላይ ሽኑ አላልኩም ። ስለዚህ ሽንታችሁን ከእርሻዬ ላይ አንሱልኝ ። »

« እንዴት እድርገን ? » ጠምቤ በእጇ ለማፈስ ተዘጋጅታ ጠየቀችው ።

« እኔ ምን አውቃለሁ ። ብትፈልጉ ምጠጡት ፣ ባትፈልጉ እፈሱት ብቻ እኔ የምፈልገው ሽንታችሁን ከእርሻዬ ላይ እንድታነሱልኝ ነው ። ያለበለዚያ ውሻ ነው የምለቅባችሁ ። » ተቆጣ።

ሦስታችንም የረጠበውን አሸዋማ አፈር በእጃችን ሰበሰብነው ።

« አፈሩን ቁጭ አድርጓት ። ይኼንግማታም ሽንታችሁን እንጂ አፈሩን አፈሱልኝ አላልኳችሁም ።»

መላ ቅጣችንን አሳጣን ። መሀዲ አሠቃየን ። እጅ በጀሮ፣ ቁጭ ብድግ አሠራን። እግራችን ተብረከረከ ። ጓደኞቻችን በሙሉ እኛን ተከትለው አለቀሱ ። ጫካው በኛ ለቅሶ ተዋጠ ።



@BOOKALEM

የሚሊቴሪ ፖሊስ ጫካ ዘበኞች ጋሽ ጴጥሮስና ጋሽ አማረ ደረሱልን ። ጋሽ ጴጥሮስ የእንዳልከ የከርስትና አባት ናቸው ። የልጃቸውን ሠምበር በሠምበር መሆን ሲመለከቱ ተናደዱ። መሣርያቸውን አቀባበሉ ። በሠደፉ መሀዲን ወገቡን አቀመሱት ። በደረቱ ተደፋ ። የእንዳልከ እንባ የከርስትና አባቱን መምጣት ተከትሎ የፍሰት መጠኑን ጨመረ ።

መሀዲን ልብሱን አስወለቁት ።እሱ እኛን ራቁታችንን አድርጎ እንዳሳቀብን ተሰብስበን ሳቅንበት። በደንብ ተገረፈ ። እንዳስለቀሠን በተራው አለቀሠ ። ይቅርታ ጠይቆ ምህረት ተደረገለት።

መሀዲ ከእርሻው ውስጥ ዘይቱና ፣ ማንጎና ፓፓያ ቆርጦ አደለን ። ለነ ጋሽ ጴጥሮስም ጫት ቆረጠላቸው ። ከመሀዲ ጋር ይቅርታ ጠይቀን ታረቅን ። የገደበውን ውሃ ለቅቀን ያጠፋንበትን ለውዝና ሚጣጢስ (ስኳር ድንች) አሳያቸው ። ሁለቱም ዘበኞች በጥፋታችን አዘኑ ። እኛም ውሃውን የለቀቅነው ፈሰሶ ካለቀ በኋላ ከሥር የምናገኛቸውን ዓሳዎች ለመውሠድ ፈልገን እንደነበር ተናገርን ።

« ልጆቹ አላጠፉም ፣ ጥሩ ሥራ ሠርተዋል ብለንም አይደለም የመታንህ ። ግን እንዴት ልጅ ራቁቱን ይገረፋል ? የልጅ ገላኮ ስስ ነው መሀዲ። እንኳንስ ውሃ ነኩቶትና እንዲሁም ዱላ ሲያርፍበት ይለበልበዋል ። ልጆቹ ላጠፉት ጥፋት ይቅርታ እንጠይቅሀለን ።» አሉት ጋሽ ጴጥሮስ የጋሽ አማረንም ውክልና ወስደው ።

***

ጋሽ ጴጥሮስ በጨካኝነታቸው ዝነኛ ናቸው ። የባህር ዛፍ ቀበኞች ቅልጥም በጥይት በመስበር ይታወቃሉ ። እሳቸው ተረኛ ከሆኑ የሚሠረቅ ዛፍ የለም ። ለጫት ሲያጡ ወደ ሚሊቴሪ ፖሊስ ጫካ ገባ ብለው አጣና ገንጠል አድርገው ሸጠው የሚመረቅኑ ጎረምሶች በጋሽ ጴጥሮስ ተራ ሲያዛጉ ይውሏታል እንጂ ጎራ አይሉም ። ከመሞት መሠንበትን እየመረጡ ።

ጋሽ ጴጥሮስ እንኳን ለዛፍ ቆራጭ ለቅጠል ለቃሚም አይመቹም ። ከዛፉ ላይ ጠውልጎና ደርቆ የረገፈውን ቅጠል ከለቃሚ ይከላከላሉ ። ምክንያታቸው ደሞ «ሰዎቹ የረገፈ ቅጠል ሲያጡ ርጥቡን እየሸመጠጡ ዶንያቸውን ይሞላሉ» የሚል ነው ።

ሚሊቴሪ ፖሊስ ጫካ ውስጥ እንደልቧ በፈቀደችው ሰዓት እየገባች ቅጠል የመልቀም ያልተፃፈ ሥልጣን ያላት የሺ ናት ። የሺ

« የሺ ድንጋይ ላይ ፍሺ

ጴጥሮስ ሲመጣ ቆመሽ ደንሺ፡፡» እያልን የምናበሽቃት እንጀራ ጋጋሪ ናት ።

ሚሊቴሪ ፖሊስ ጫካ ውስጥ « የጡንች ዋሻ » የሚባል ቦታ አለ ። ጡንች ሠካራም ፣ሀማል ነው ። ገንዘብ እየተቀበለ የሰዎችን ሸከም የሚያቃልል ወዛደር ። ዋሻው ጨለማ ነው፤ ያውም ጥቅጥቅ ዕልመት የዋጠው ዋሻ ። ብዙ ጊዜ ወንድና ሴት ተቃቅፈው እየገቡበት ቆይተው ፣ቆይተው



@BOOKALEM

ሱሪና ቀሚሳቸውን እያራገፉና እያስተካከሉ ይወጣሉ ። ጋሽ ጴጥሮስና የሺም ብዙ ጊዜ የባህር ዛፍ ቅጠል ይዘው ወደ ዋሻው ይገባሉ ።

የሺን እየኮረኮሩ እያሳሳቋት ወደ ዋሻው ይዘዋት ይገቡና ቆይተው ፣ቆይተው ይወጣሉ ። እነሱ ከወጡ በኋላ ወደ ዋሻው ገብተን የተጎዘጎዘው የባህር ዛፍ ቅጠል ላይ እንንደባለላለን ፤ እንገለባበጣለን። ጋሽ ጴጥሮስ ከመጡ ግን ገደሉን ። ለነገሩ ዋሻው ሁለት በር ስላለው በአንዱ ሲመጡ በሌላኛው እንሸውዳቸዋለን ። አንዳንዴም እዚያችው ዋሻ ውስጥ ተቀምጠን ባጠገባችን ሮጠው ያልፋሉ ። ደጁ ጠራራ ፀሐይ ቢሆንም ውስጥ ግን ያለ ባትሪ እርዳታ መጓዝ ይከብዳል ።

የሺ በዋናነት የጋሽ ኢብራሂም ሚስት ናት ። ጴጥሮስና ኢብራሂም ደሞ አበልጃሞች ናቸው ። ልጅ እግር ወጣት ነገር ናት ። የኘያ የሸማግሌው ሚስት አትመስልም ። ሚስት መሆኗን ያወቅነው ከቤተሰባችን የቡና ወሬ ነበር ። ልጃቸው እንጂ በምንም ተዓምር ሚስታቸው አትመስልም። ከገጠር አስመጥተው አገቧት - ከወሎ ። አንገትና ጉንጯ ላይ የመስቀል ፣ የሠንሠለትና የነጠብጣብ ቅርፅ ያለው ንቅሳት አለባት ።

እነጋገሯ የኛ ማልመጫ አድርጓታል ። የማይመለከተንን ርዕስ እያነሳን እናዋራታለን። ስታወራልን እንስቅባታለን ። ስንስቅባት ትናደዳለች ። ስትናደድ « ዴንጌሳም ! የዴንጌሳም ልጅ!» ብላ ትሠድበናለች ። ድንጋይ አንስታ ታባርረናለች ። ሥታባርረን ደስ ይለናል ። የሺ እኛን እንደምታባርረው ጋሽ ጴጥሮስም እሷን እያባረሩ ወደ ጡንች ዋሻ ያስገቧታል ።

ቆይተው ፣ ቆይተው ከዋሻ ሲወጡ ተደብቀን እናያቸዋለን ። የሺ ቀሚሷን እያራገፈች ግራ ቀኙን ተመልከታ ትወጣለች ። ፀጉሯን ደሞ ጋሽ ጴጥሮስ ያራግፉላታል ። ፀጉሯን አራግፈው ሲያበቁ ቂጧን በጥፊ ይመቱታል ። ጥፊ የቀመሠውን ቂጧን እያሻሸች እየሮጠች ወደ ጢሻው ትገባለች ። ይከተሏታል ። ከጉቶው ጎን ላይ ተለጥፎ ያደገውን ሊጋ ባህር ዛፍ እየገነጠሉ ፣ እየሠባበሩ ጆንያዋ ውስጥ ይጨምሩላታል ።

ከጫካው እስከ ዋናው መንገድ ማገዶዋን ተሸክመው ያወጡላታል ። ጠብመንጃቸውን አንግታ ሮጥ ሮጥ እያለች ትከተላቸዋለች ። ሲደከማቸው ሽከማቸውን ያራግፋሉ ። የሺ በርከክ ትልላቸዋለች ። ጆንያውን አንስተው ወገቧ ላይ ይጭኑላታል ። ጆንያው ወገቧን ሲንተራስ ጎንበስ ብላ በሁለት እጆቿ መሬቱን ትደገፋለች ። ከቂጧ ፈንደድ እንዳለች ጋሽ ጴጥሮስ የማዘያ ገመዱን ያጠላልፋሉ ። ጆንያውን ከትከሻዋ ጋር ለማስተሳሠር ይታገላሉ ።

ጥብቅ አድርገው ያስሩላታል ። ገመድ የሚያጠላልፉ እያስመሠሉ ጡቶቿን ይጎነታትላሉ። በእጇ እጃቸውን መታ ታደርጋቸዋለች ። ፊቷ ላይ ግን ብስጭት አይታይም ። እሷ ተሸከማ እንዳጎነበሠች ከጡትና ቂጧ ጋር ድብብቆሽ ይጫወታሉ ። ሲደከማት ለመነሳት ትሞክራለች ። ጆንያው በርጥብ እንጨት ስለተሞላ ባይከብዳት ነው የሚገርመው ። ተነስታ መሬትን በሁለት እግሮቿ እስከትረግጥ ትቸገራለች ።



@BOOKALEM

ጋሽ ጴጥሮስ ከኋላዋ ሆነው እጃቸውን ወደ ደረቷ ይልካሉ ። በላይ በትከሻዋ በኩል የሠደዱት እጃቸው ለጡቶቿ ይርቅባቸዋል ። ከነ ሸከሟ ለማንሳት ይቸገራሉ ። የድጋሚ ሙከራቸውን በጀንያው አልፈው በብብቷ በኩል ያደርጋሉ ። በብብቷ በኩል አልፈው ሁለቱን ጡቶቿን አቅፈው የሞት ሞታቸውን ያነሷታል ። ነፍስ ትዘራለች ። ጉልበቷ ሙሉ ይሆናል ። ዳገቱን እያማጠች ስትወጣ ከዓይኖቻቸው እስከትሠወር ቆመው ያይዋታል ። ዓይኖቻቸው ከየሺ ምስል ሲርቁ ተመልሠው ወደ ጫካው ይገባሉ ። የጫካው ጠባቂ መሆናቸው ትዝ የሚላቸው የሺን ከሸኙ በኋላ ነው ።

ወደ ቀጭኗ ወራጅ ውሃ እያንገራገሩ ይጠጋሉ ። ዙርያ ገባውን ከቃኙ በኋላ መጀመርያ ከላሻቸውን ያስቀምጣሉ ። ኮፍያቸውን ፣ የወታደር ፊልድ ጃኬታቸውን ፣ ሹራባቸውን ፣ ሸሚዛቸውን፣ ካናቴራቸውን ፣ ከስከስ ጫማቸውን ፣ ተረከዘ ቡድስ ካልሲያቸውን ፣ ሱሪያቸውን በመጨረሻም ቡራቡሬ ሙታንቲያቸውን ያወልቃሉ ። ትንሽዬ ባለ ቀለበት ወርቃማ ቻርኔላ የሚታይበት ኪስ ያለው ጀምስ ፓንት ። የጥቁር ተፈጥሯዊ ቆዳ ባለቤት የሆኑትን ጋሽ ጴጥሮስን ያለ ልብስ ስናያቸው ትንንሽ ልቦቻችን «ድው ! ድው !» ይላሉ ።

ዓይኖቻችን ጭንና ጭናቸው መሀል ተንጠልጥሎ በሚወዛወዘው ጥቁር ጭንቅላታም ሙዛቸው ላይ ይወረወራሉ ። ከወራጁ ውሃ በእጃቸው ጨልፈው ቅድሚያ ሙዛቸውን ያጥቡታል ። በውሃ እያንቸፈቸፉት ያዋሩታል ። ምን እንደሚሉት አይሠማንም እንጂ ያዋሩታል። ያሻሹታል ። ሳሙና እየቀቡ ደጋግመው ያጥቡታል ። ጭንቅላቱን ደፍቶ የነበረው ሙዛቸው ቀና፣ ቀና ይላል እንደተዘረጋ እግር ። ልክ የኔ ጠዋት ፣ ጠዋት ከእንቅልፌ ስነሳ ሸንቴን ሲወጥረኝ እንደሚሆነው፣ ልክ እንደዚያ ።

« ጴጥሮስ አይቼሃለሁ !» ይላል ጠይሜ ድምፁን አቅጥኖ

« ሞረሽ ! የማርያም ብቅል እየፈጨሁ ነው ። » ይላሉ እያማተቡ ።

« አቤት ውሸት ! » ጠይሜ ድምፁን ሲያቀጥን የምር ሴት ነው የሚመስለው

« ጴጥሮስ የየሺ ባል ! ጡንች ዋሻ ውስጥ ባለጌ ነገር አርጋችሁ ነው አይደል ?» ጠምቤ ይከተላል ገላቸውን ሳሙና መለቅለቃቸውን ጠብቆ ።

« ለጋሽ ኢብሮ እንናገራለን ! » እላለሁ ።

በንዴት ብው ይላሉ ። ወደ ድምፃችን አቅጣጫ ተቃንተው ለማየት ይሞክራሉ ። ፊታቸውን ያዳረሠውን ሳሙና በውሃ ተለቃልቀው ጥይታቸውን ሲያነሱ የልባችንን ድው ድውታ ተከትለን እንፈረጥጣለን ።

« ያዘው ! የታባቱ ይኺ ዲቃላ ውላጅ ! » በሩጫ ሳይከተሉን በድምፅ ብቻ ያሳድዱናል ። በቃ እንዲህ ናቸው ብዙ ጊዜ ጋሽ ጴጥሮስ ።



@BOOKALEM

***

ከናትናዔል ነጋሽ በስተቀር ሁሉም የአምስተኛ «ቢ» ክፍል ተማሪዎች ታመምን ። የሁላችንም ሕመምና ሁኔታ ተመሳሠለ ። ሁላችንም ቂጣችን ያለማቋረጥ አፈሠሠ ። የበላነው ሆዳችን ውስጥ አልቀመጥ አለ ። የሚያስጮህ የሆድ ቁርጠትና የሚያንቀጠቅጥ የወገብ ሕመም ቀፈደደን ።

ከትበልጪ ዘርዓይ ፣ ዮርዳኖስ ይሳቅ ፣ወንድምና እህቶቹ ፍሬ ዓለምና ምዕራብ አበበ በስተቀር ጦር ሠራዊት ሆስፒታል በወላጆቻችን ተደግፈን ታከምን ። የወታደር ልጆች ስለሆንን ወታደራዊ ሆስፒታል ውስጥ የመታከም መብት አለን ።

እነ ትበልጪ ግን ሕይወት ፋና ሆስፒታል ነበር የታከሙት ። የሲቪል ልጆች ናቸው ። ናትናኤል ነጋሽ ወደ ዋና አብሮን ስላልኺደ ከበሽታው ነፃ ሆነ ። ትምህርት ቤታችን ምስጢራችንን ሳያውቅ « ተላላፊ የልጆች በሽታ ስለገባ » ተብሎ ለአንድ ሳምንት ተዘጋ ። ድብቅ የመዋኛ ሥፍራ፣ ድብቅ ምስጢር፣ ድብቅ በሽታ ።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ ሰባት

## የድድ ማስጫ ልጆች

ድድ ማስጫ ላይ የሌለ ነገር ፣ የማይቆም መኪናና ሰው የለም ። ከወታደራዊ እስከ ንግድ መኪናዎች የጎዳናውን ግራና ቀኝ ጠርዝ እየጠበቁ ይኮለኮላሉ ። መኪናዎቹ በጎዳና ላይ እፐብት ፅዳት ናፍቀው ወረፋ ይይዛሉ ። መንገደኞች ታክሲ ለመሳፈር ይጠባበቃሉ ። ፔጆ ታክሲዎች ከአራት ሰው በላይ መጫን አይፈቀድላቸውም ። ሹፌሩ ከኋላው ሦስትና አጠገቡ አንድ ሰው ብቻ ጭኖ እንዲሄድ ከትራፊክ ፖሊስ ፍቃድ አለው ። እኔ ግን ሁሌም ታክሲዎቹ ያሳዝኑኝ ነበር ። አራት አራት ጎማ ኖሯቸው አምስት አምስት ሰው ከነኮተቱ መጫናቸው ከአቅም በላይ እንዲሠሩ የተገደዱ ያህል ይሠማኛል ።

በአስፋልቱ ግራና ቀኝ የወታደር ካምፖች አሉ ። ማመላለሻ ከነዳጅ ማደያ እስከ የከባባድ መኪና ማቆሚያ ሀንጋር አለው ። የሀንጋሩ ከፍታ ይገርማል ። የፎቅን ያህል ይገዝፋል ። ቁልቁል ወደ ሸዋ በር ሲወርዱ በስተቀኝ የተቀመጠው ማመላለሻ ሠፊውን የመግቢያ በሩን የየወቅቱን ወታደራዊ መለያ በለበሱ ወታደሮች ያስጠብቃል ። የደከመና የወዳደቀ የቆርቆሮ አጥሩን ሌቦች አብዝተው ከሞት ይታደጉለታል ። ቆርቆሮውን እየነቀሉ ፣ እሾሃማ ሽቦውን እየፈቱ ለቆራሊዮ ይቸበችቡለታል ። አንድ መለስተኛ መንደር ሊመሠርት የሚችል መሬት የያዘው ማመላለሻ ሁለት በሮች አሉት ። ጠባቂ የማያጡ የሰሜንና የደቡብ በሮች ። ድድ ማስጫን ፊት ለፊቱ የሚመለከተው የሰሜኑ በር ነው ።

ማንኛውም መንገደኛ ቀኙን ይዞ ወደ ኮምቦልቻና የአፄ ኃይለ ሦላሴ የትውልድ ሥፍራ የሆነችው ጃርሶ የገጠር ከተማ ለመሄድ ድድ ማስጫን መሳለም ግድ ይለዋል ። ከማመላለሻ ጋር መንገድ የለያቸውን የጦር ሠራዊት ሆስፒታልንና ሥንቅና ትጥቅ መሥርያ ቤቶችን እግረ መንገዱን ይሳለማል ። ከቡን አደባባይ ተሠናብቶ መንገዱን ይጀምራል ።

የኮምቦልቻ ላንድ ሮቨሮች ፣ ዳይናዎች ፣ ቼንቶዎች ፣ ፋይፈሌዎች ፣ ስታውቶች ፣ ሃይሉክሰችና የዕርዳታ እህል የሚጭኑ ረጃጅም ባለተሳቢ መርቸዲሶች ማርሻቸውን የሚለውጡት አደባባዩ ላይ ሲደርሱ ነው ። የከተማው አስፋልት አብቅቶ ወደ ፒስታው መንገድ ሲቀላቀሉ ማርሽ መቀየር፣ በእግራቸው የተጫኑትን ነዳጅ መስጫ ለቀቅ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ። ከኮምቦልቻ ትርፍ ሆነው ተጭነው የሚመጡ ሰዎችም ከነኮተታቸው የሚራገፉት ድድ ማስጫ ላይ ነው ። የትራፊክ ፖሊስ ባዘቦት ቀን ድድ ማስጫን አያውቃትም ። ዓመት በዓል ካልደረሠ የትራፊክ ፖሊስ ድድ ማስጫን አይረግጣትም ። ለትራፊክ ፖሊሶች እግር ባዘቦት ቀን የምትቀፍ መንደር ናት ድድ ማስጫ ።

በማመላለሻ ፣ ሕክምናና ሥራ መሐንዲስ በተሠኙ የወታደር ሀብቶች የተከበበችው ድድ



@BOOKALEM

ማስጫ ለብዙዎች የአለት ጉርስ ሸፋኝ የአንጀራቸው መሶብ ናት ። ያመት ልብስም ጭምር ። መኪና አጥበው ፣ ጓዝ ተሸክመው ፣ የጉልበት ሥራ ሠርተው ፣ ደልለው ፣ ቀፍለው ፣ ቁማር ተጫውተው ሕይወትን የሚታገሉ ብዙ ሰዎች ይውሉባታል ። ድድ ማስጫ ቀን ቀን እንጂ ለዓይን ያዝ አድርጎ የመንገድ መብራት ከበራባት በኋላ ወዳጅ አታውቅም ። ሠርከ ቢነጋ ቢመሽ፣ ቢዳምን ቢፈካ ከሥራ የማይሸሽው መሄጃና ተንከባካቢ ያጣው አደባባይዋ ብቻ ነው ። ድድ ማስጫ የቀን አድማቂዎቿን ሲመሽ ነጣቂዎቿ ይበዛሉ ።

ቀኑን ሙሉ ንቅት ብላ እንግዶቿን ስታስተናግድ ትውልና ሲመሽ ትተከዛለች ። ፍዝዝ፣ ድብዝዝ ትላለች ። ማንም ፣ ምንም ፣ መቼም ፣ ሰው ረግጧት የማያውቅ ያም አዳሪ መሬት ትመስላለች ። የመንደር ውስጥ ጨለማ የሚደብራቸውና እራሳቸውን ከጅብ አደና ለማስጣል በሚጥሩ አሳዳሪ አልባ ውሾች ትታጀባለች ። አደባባይዋ ውስጥ « እሹሩሩ » ብላ እያባበለች ምስኪኖቹን ውሾች ታስተኛለች ። ቀን ለሰው ልጆች ሌሊት ለውሾች መከታ ናት-ድድ ማስጫ ።

ድድ ማስጫ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው መለያ ጠባይ ያላቸው ሀማሎች አሏት ። «ሀማሎች» የምንላቸው የደከሙ የሰፈሩ መንገደኞችን እቃዎችና ጓዞች በከፍያ የሚሸከሙትን ወዛደሮቿን ነው። « ሀማል ! ሀማል ! » ተብለው ሲጠሩ ወደ ጠሪያቸው ተሯሩጠው ይጠጋሉ ። በዋጋ ተሰ ማምተው ዕቃውን ያደርሳሉ ።

« ሀማል ሀማል

ቂጡ ይገማል።»

እንላቸዋለን ልጅ ልጆቹ ስናበሽቃቸው ። ያሯሩጡናል ። እየሳቅን ስንሮጥ እየበሸቁ ይከተሉናል ።

በሕይወቴ ውስጥ ከማይረሱኝ የድድ ማስጫ ሀማሎች አየለ ቅጫም ዋነኛው ነው ። ቀጫጫ፣ ጥቁር ፣ ፊቱ የማይፈታ ፣ ቂጡ የተቦጨቀ ቅጠልያ የወታደር ሱሪ የሚያደርግ ለወላጆቻችን እኛን ማስፈራርያ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን አስታውሳለሁ ። ማስፈራሪያነቱ እንደ ጭራቅ በርቀት እየኖረ ሳይሆን ከነ ጠባይና ተክለ ሰውነቱ እያወቅነው ።

ደማቅ ጥቁር ሉጫ ፀጉር አለው ። ወታደሮች ካልሆኑ በስተቀር ማንም ሰው « አየለ ቅጫም» ብሎ አይጠራውም ። ተሳስተው ከጠሩት እንኳን ወይ በቡጢ አልያም በዱላ ይዘርራቸዋል። ጉልቤ ነው እንደ ጠይሜ ። እሱ ካልፈቀደላቸው በስተቀር ሌሎቹ ሀማሎች እሱ እያለ አይሸከሙም ። ድድ ማስጫን ቁልቁል እያየች የምትጣራው የአባባ አዘረፈኝ ጠጅ ቤት ቤቱ ነች። እየጠጣ የሚደባደብባት-የቦከሰ ሪንጉ ።

ኩንታል ሙሉ እህል ተሸክሞ ያለ ዕረፍት ከተባለበት ርቀት ያደርሳል ። አሸካሚ ካገኘ አውራጅ አይፈልግም ። ሸከሙን አራግፎ ሲመለስ ነዳጅ ይሞላል ። በብርሌ ያስሞላትን ቢጫ ነዳጅ ሳብ ሳብ አድርጎ ሲያበቃ ወደ ሥራው ይመለሳል ። የጋሽ አዘረፈኝ ጠጅ የአየለ ቅጫም ነዳጅ ናት ።



@BOOKALEM

« አየለ ቅጫም

ገባ ቢሲዲሞ ፡፡ »

አልነው አንድ ቀን እኔ ፣ ጠይሜና ጠምቤ (ቢሲዲሞ የስጋ ደዌ ሕሙማን መታከሚያ ሆስፒታል ነው፡፡)

« እናታችሁን ቢሲዲሞ አልጋ ላይ አስተኝቼ ልሳምላችሁ እሺ !» ብሎ ድንጋይ አንስቶ ተከተለን ፡፡

ሮጠን የማመላለሻ ዘበኞች ሥር ተወሸቅን ፡፡ ቆመ ፡፡ ምንም ሳናደርገው ሊመታን እንደሚያሳድደን ነገርናቸው - ውሸት ፈጥረን ፡፡ አንደኛው ወታደር ጠራውና አስጠነቀቀው ፡፡ ልጆችን የሚማታ ከሆነ ከድድ ማስሚ እንደሚያባርረው ነገረው ፡፡

« ሰድበውኝኮ ነው ጌታው ! » አለ በተሸናፊነት ድምፁን አስልሎ ፡፡

« ምን ብለው ሰደቡህ ? » ጠየቀው ወታደሩ

« ኧረገኝ...አየለ ቅጫም

ገባህ ቢሲዲሞ ... የሚሉት የት አባታቸው አይተውኝ ነው ?»

« እና ቢሉህ ምን ችግር አለው ? »

« ኧረግ ! ጌታው ምን ነካህ ? በዘሬም በሌለብኝ ቁምጥና በምን ዕዳዬ ልጠርጠር ?» ዓይኖቹ እንባ አቀረሩ ፡፡

ወታደሩ አየለ ቅጫም አሳዘነው መሠለኝ ውሃ የሚያስጠማ ኩርኩምና ካልቾ አቅሞሶ ለቀቀን፡፡ ጭንቅላታችንን እያሻሸን ስንሄድ ሙኪኬን አገኘናት ፡፡

« ሙኪኬ ! » አላት ጠይሜ

ድንጋይ አነሳች ፡፡ ሮጥን ፡፡የወረወረችው ድንጋይ አየለ ቅጫምን ሳተው፡፡ አየለ ተንደርድሮ መጣና በግራ እጁ አንገቷን አንቆ በቀኙ በተጨበጠ ቡጢ አገጯን አኅናት ፡፡ ተዝለፈለፈች ፡፡ ጎንበስ ብሎ እግሮቿን አቅፎ ትከሻው ላይ አሳረፋትና ወደ ኋላው ባፍጢሟ ለቀቃት ፡፡

አካባቢው በጩኸት ተተራመሠ ፡፡

« ወይኔ ! ሙኪኬን ገደላት ፡፡ » አለ ጠይሜ ደንግጦ

« ሙኪኬ ከሞተች ማንን እናበሽቃለን ? » ጠየቀ ጠምቤ

« ያቺ ሸፋፋ አሮጊት እናትህ ትሙትልህ እሺ...ለአንቴ ሞት ትመኛለህ? ቀሽም !» ጠይሜ ተናደደ ፡፡



@BOOKALEM

« ሙከኬ እኅትህ ናት እንዴ ? » ገርሞኝ ጠየቅኩት ።

« እና ... የአባዬ ታናሽ ወንድም አይደለች እንዴ ? ምን እንደማታውቁ ትሆናላችሁ ። » ጠይሜ አኮረፈ ።

« እና የጋሽ በቄ ወንድም ሆና ለምን ሀማል ሆነች ? » ጠምቤ ገርሟ ታል

« እኔ ምን አውቃለሁ ? እንዴ ! እንዴ ! » አለና ጠይሜ ወደ ትርምሱ መሀል ሮጠ ።

ጋሽ በቄ አየለ ቅሜምን በከዘራቸው ያንቆራጥጡታል ። ገላጋይ መሀል ገብቶ ይታገላል። ጋሽ በቄ ለገላጋይ አስቸገሩ ። ጠይሜ የወረወረው ድንጋይ የአየለን እግር አገኘ ። አየለ እግሩ ጋሽ በቄ ለገላጋይ አስቸገሩ ። ጠይሜ የወረወረው ድንጋይ የአየለን እግር አገኘ ። አየለ እግሩ የተመታበትን ድንጋይ በእጁ አስገባ ። ከወገቡ ቀና ብሎ ፤ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ድንጋዩን ወደ ጋሽ በቄ ግንባር ላከው ።

ወደቁ ።

ከዘራቸውን ሲያነሳ የአንድ ወታደር ቃርያ ጥፊ መጣጣ ፊቱ ላይ አረፈ ። ከዘራቸውንም እራሱንም ወደ መሬት ጣለ ። ተልፈሠፈሠ ። እንደ አባብ ተጠቀለለ ። ጅማት የነበረው ሰው ፓስታ ሆነ ያውም ፍል ውሃ የነካው ፓስታ ።

ሙከኬ ስም የወጣለት ከአጠጣጡ ነው ። ሲጠጣ ቀይ ፊቱ እንጆሪ ይመስላል ። እንደ ጨርቅ ጥምልል ፤ እንደ ንፍሮ ሙከከ ይላል ። ሲጠጣ የሚቆም አካል የለውም ። ምላሱም ቢሆን ይንዘላዘል ይሆናል እንጂ ቀጥ ብሎ አይዘረጋለትም ። ስርቅታውን ተከትሎ ለሀጩ ፀሐይ እንደወቀረው ውሻ ይዝረበረባል ።

በአየለ ቅሜም በደረሠበት ወገራ ምክንያት እነ ጠይሜ ቤት የተኛው ሙከኬ በልቡ ቂም ቋጥሯል ። ሠበብ እየፈለገብን ቆይቶ አንድ ቀን ሦስታችንንም በር ዘግቶ ቀጠቀጠን ። እኛም ተመካከርንበት ። ልናሳሸው ወሠንን ።

ግርግር የሚባለውን ሀማል አገኘነው ። ግርግር ልጅ ይወዳል ። ተሸከሞ ባገኘው ገንዘብ ከረሜላ ፤ ብስኩት ፤ ዘይቱና ፤ ማንጎና ጀላቲ ይገዛልናል ። እጥር ፤ ውፍር ያለው እቋሙ ደስ ይላል። ትክክለኛ ስሙን አናውቀውም ። ራስ በራ ከመሆኑ በተጨማሪ የራስ ቅሉ ላይ ያሉት ፀጉሮችም ተለቅመው ይቆጠራሉ ። ግንባሩ ላይ አውራ ጣት የሚያስገባ ቀዳዳ አለ ። ሲያጫውተን፤ ተዓምር ሊያሳየን ሲፈልግ ቀዳዳው ውስጥ የተለኮሠ ሲጋራ ያስቀምጥበታል ። ካሁን አሁን ተቃጠለ እያልን ስንሰጋ ጎንበስ ብሎ ሲጋራውን ወደ መሬት ይጥልና አንስቶ ሳብ ሳብ ፤ ጭሱን ቡልቅ ቡልቅ ያደርገዋል ። ቁሬውን እንደ ማስቲካ ያኘከዋል ።

ወታደር እንደነበር ይወራለታል ። ልዩ ስድስተኛ መንጃ ፍቃድ ቢኖረውም ስለቀወሰ መንዳት እንደተከለከለ ሁሉም የመንደራችን ሰው ያምናል ። ስድስተኛ መንጃ ፍቃድ ሲደተኛ ያደረገው ሰው ግርግር ነው ።



@BOOKALEM

ሙከኪ ልትመታው እንደምትፈልግ ነገርነው ። ተናደደ ።

« እደፋታለሁ ! » አለ

ደስ አለን ። ሙከኪ እንደወገረችን ልናስወግራት ተዘጋጀን ። በኪሳችን ደብቀን ሀሳቡን ከተረዳን በኋላ ልንሠጠው የተስማማንበትን ሦስት ሲጋራ ጠይሚ አቀበለው ። ክብሪት ለኩሶ ጭሱን አብለቀለቀው ። ፊቱ ሲለዋወጥ አየነው ። ቅጥቅጥ እንደሚያደርግልን አመንን ።

ሙከኪ እንደለመደችው ሙከከ ብላ ሠክራ በመንገዷ ያገኘችውን ሁሉ እየሠደበች መጣች። ለግርግር አሳየነውና ሮጠን ከሥሩ ጠፋን ። በአንድ ቦክስ ገለበጣት ።

« ግርግር ተነሳበት ! » ተባለ

ሁሌም ሰው ከተማታ እንዲህ ነው የሚባልለት ። « አዲስ ጨረቃ ስትወለድ ያመዋል ፤ እብደቱ ይነሳበታል !» ይባላል ።

«ግርግር ያበደው የሌሊት ወፍ ሸንታበት ነው ። » ስለሚባል ማታ ማታ እራሳችንን ከሌሊት ወፍ ሽንት እንጠብቃለን ።

« የሌሊት ወፍ ማታ ማታ ብቻ የምትዞረው ዱርዬ ፤ እደጅ የሚያመሽ ልጅ ላይ ሽንቷን ሸንታ ለማሳበድ ነው ።» ስለምንባል ላለማበድ በጊዜ ወደ ቤት እንገባለን ።

ሳሙኤል ግርግርን ተሸክሞ አደባባዩ ውስጥ ወረወረው ። ሳሚ የድድ ማስጫ ጉልቤ ነው ። እኛ ሠፈር ከኔ በቀር በሳሚ ያልተመታ የለም ። እኔን የማይነካኝ ስለሚወደኝ አይደለም ። እኛ ቤት ሲመጣ እንጀራ እንዳይከለከል እንጂ ።

እናቱ የእናቴ የቅርብ ጓደኛ ነች - አብሮ አደግ ። ዝዋይ ሕፃናት አምባ ነበር ከታናሽ ወንድሙ ጋር ያደገው ። ኢሕአዴግ በአምባው የነበሩትን ተማሪዎች ሲበትን ወደ እናቱ መጣ ። የመጣው እናቱ የማታውቀውን ፤ ለመንግሥት ያላስረከበችውን ሳሙኤልን ሆኖ ነበር ።

ሲጋራ ፤ ጫት ፤ መጠጥና ሴት ያለ ዕረፍትና ያለ ዕፍረት በየአውራ ጎዳናው የሚጠቀም የባከነ ልጅ ። እናቱ የተለየ ፤ ለድሎት ቀርቶ ለእለት ጉርስ የማያሳቅቅ የገቢ ምንጭ ስላልነበራት እንደ ሌሎቹ ልጆቿ ዕድልና ጉልበቱ የፈቀዱለትን እየሠራ እንዲኖር ሞከረች ። አልተሳካላትም ። ሰው መደብደብ ፤ በጩቤ መውጋት ፤ መንጠቅ የሠርክ ተግባራቱ ሆኑ ። ለወደደው ሟች ለጠላው ገዳይነቱን በተግባር አረጋገጠ ። ምርር ሲላት ከቤት አባረረችው ። ምግቡን የትም በልቶ አዳሩ ብቻ ከሷ ጋር ይሆን ዘንድ በእናቴ ልመና ፈቀደችለት ።

ጉልቤው ባለበት ሴትና ወንድ ተቃቅፈው እንደልባቸው እያወሩ ፤ እየተላፉ መሄድ አይችሉም ። ወንድየው ንብረቱን ብቻ ሳይሆን ሴቲቱንም ያስረክባል ። እያለቀሠ በሳሚ ፊት ተሸናፊነቱን ካላረጋገጠ ጉንጩ ላይ የቡጢውን አሻራ ያስቀምጥለታል ። በጭካኔው ስለሚታወቅ እንኳን ሠፈርተኛው መሣርያ የታጠቁት ፖሊሶችም ይፈሩታል ። ሳሚ የሠፈራችን ጀግና ነው ።



@BOOKALEM

ግርግር በጀርባው እንደተኛ የሳሚን ቡጢ ያለ አፀፋ እየተቀበለ እንዲተወው ይለምነዋል። መንገደኞች ስለ ጉልበቱ ይማፀኑታል ። የማመላለሻ ጠባቂ ወታደሮች ይስቃሉ ። የነፃ ትግል በቴሌቪዥን የሚከታተሉ እየመሠላቸው ይዝናናሉ ።

ሆዱ ላይ ተቀምጦ የሚቀጠቅጠውን ሳሚን ሰው ሁሉ በቃሉ እንጂ መሀል ገብቶ ለመገላገል የፈራ ይመስላል ። ግርግር ያለቅሳል ። ትልቅ ሰው ሲያለቅስ ያሳዝናል ። ትልቅ ሆኖ ማልቀስ እንደሚቻል ያወቅኩትም በግርግር አንባ ነበር ።

ከሥር ሆኖ ያለ አፀፋ በሳሚ መደብደብ ታከተው ። ፊቱ ተለዋወጠ ። ዓይኖቹ ተገለባብጠው ጥቁሩ ወደ ውስጥ ነጩ ወደ ላይ ሆነ ። በጥልቀት ተነፈሠ ። ሰዉ ተበታተነ ።

« ሞተ ! ገደለው ! ግርግርን ገደለው ! » አሉ አንዱ ሰውዬ

ግርግር ሳሚን ገለበጠው ። ተሸከሞ አንስቶ እንደ ንፍጥ አፈረጠው ። ተረኛ ሆነና እያከታተለ ጥርስ ፣ ጥርሱን በቦክስ በቴስታ ረመረመው ። ሳሚ ደም በደም ሆነ ። የፊት ጥርሶቹ እያየናቸው ረገፉ ። እጆቹ ተዝለፈለፉ ። አፍና አፍንጫው ከትንፋሽ ይልቅ ደም ማጉረፍ ቀለላቸው ።

ሲስቁ የነበሩት ወታደሮች ግርግርን በሠደፍ መቱት ። አንዱን ወታደር ጉሮሮውን አነቀው። የምር ተነስቶበታል ። እብደቱ ጉልበት ሆኖታል ። ሰው ሁሉ እየሆነ ያለውን በርቀት ነው የሚከታተለው ።

ሌላኛው ወታደር ግርግርን ጭንቅላቱ ላይ በሠደፍ መታው ። ደም ከጭንቅላቱ ጎረፈ ። ሌላ ቀዳዳ ከጭንቅላቱ የኋለኛው ከፍል ሊፈጠር እንደሚችል ገመትኩ ። ሌላ የሲጋራ መተርኮሻ...ሌላ ተዓምር ማሳያ ቀዳዳ ።

ግርግር ወደ ኋላው ተዘረረ ። ራሱን ሳተ ። ራሱን ስቶም በሕይወት ያሉት ወታደሮች በድኑን ገረፉት ። በከስከስ ጫማቸው እንደ እባብ ጭንቅል ጭንቅላቱን ረጋገጡት ። « የነፃ ትግሉ» ተመልካች የነበሩት ወታደሮች በሠፈሩበት ተሠፍረው ተመልካች አገኙ ። « ተዉ !» የማይል በፍርሀት የተሸበበ ተመልካች ።

በርካታ ከናፍሮች ለዚያ ምስኪን ሀሜል ተመጠጡ ። ከንፈር ከመጠጡለት ሰዎች ውስጥ ለዚህ ሁሉ ነገር ምክንያቶቹ የሆንነው እኔ ፣ ጠይሜና ጠምቤ እንገኝበታለን ። ታሞ እዚያችው አደባባይ ውስጥ በተኛበት አጋጣሚም ከቁርስና ምሳችን እየቀነሥን አብልተነዋል ። ከየወታደር ካምፖቹ ኡፋ እየለመንን ቁስሉ ያጠግግለት ዘንድ የአቅማችንን አበርክተንለታል ። ስናገኝ ድፍን እየገዛን ስናጣም ቁሬ እየለቃቀምን ሱሱ ሌላ ሕመም እንዳይጨምርበት ተንከባክበነዋል ። እማማ ትሁኔን ኩሽናቸው ውስጥ ቆልፈንባቸው ከቤታቸው አረቄያቸውን ሠርቀን አጠጥተነዋል ።

***

በአካል ሳናውቃት የወደድናት ሀገር ጅቡቲ ናት ። ጅቡቲ በኛና በድድ ማስጫ ልጆች



@BOOKALEM

ለመወደዱ ምክንያቱ ደም በከሬ ነበር ። በከር አብደላ ነው ሙሉ ስሙ ። በከሬ አማርኛን አቀላጥፈው ከማይናገሩ የድድ ማስጫ ሀማሎች ጎልቶ ይታወቃል ። ለመታወቁ መንስዔዎቹ ደም የሚሸከመው በዝቅተኛ ሒሳብ በመሆኑና መንደርተኛው ላይ በሚደርስ ማንኛውም ዓይነት ችግር ከአምቡላንስ ቀድሞ ደራሽነቱ ነበር ።

አወቀውም አላወቀውም ለሞተ ሁሉ ያለቅሳል ። ድንኳን በተጣለበት ሁሉ በከሬ አለ ። ከአንባው እስከ ጉልበቱ ለሀዘነተኞቹ መፅናኛ ያውላል ። ሟቿ ሴት ከሆነች « አባዬ ! አባዬ !» ወንድ ከሆነም « ጋሺዬ ! ጋሺዬ ! » እያለ ያለ ገደብ ያለቅሳል ። እንጨት ፈልጦ ፣ ውሃ ቀድቶ ፣ ከገበያ የሚገዛዙ ነገሮችን ተሸክሞ በነፃ ያገለግላል ። እነኚህ ተግባራቱ ናቸው በእናትና አባቶቻችን ዘንድ ያስወደዱት ።

በከሬ ለኛ የሳቅ ምንጫችንም ነው ። እንደልባችን እንደ ልጅ እየሸወድን የምንጫወትበት አሻንጉሊታችን ። አንድ ቀን እኔ ፣ ጠይሜና ጠምቤ ቁማር በልብስ አዝራር እየተጫወትን ሳለ በከሬ መጣ ። ከኛ ቤት ጀርባ ያሉት እማማ መሠሉ የልጅ ልጃቸውን ክርስትና ለመደገስ ድንኳን ጥለዋል ። ጠራነውና እማማ መሠሉ መኪና ገጭቷቸው እንደሞቱ ነገርነው ።

ደነገጠ ። የሚሆነው ጠፋው ። ጠይሜ የውሸቱን ሲናገርም አይስቅም ። ደግመን ደጋግመን የእማማ መሠሉን ሞት አሳዛኝነት አልቃሽ መስለን አረዳነው ። ይህንን ያደረግነው በጣም እንደሚወዳቸው ሥለምናውቅ ነበር ። ከው ፣ ድርቅ ፣ ቡዝዝ ብሎ አመድ መሠለ ።

« ወዮ ! ወዮ ! ወዮ !... ወዮ ! አባዬ ! ኢናቴ ! ኢናቴ ! አጉራሼ ... ወዮ ! ወዮ ! ወዮ ! አባዬ ሚን ዓይነት ሹፌራ ነው የገደለሽ ... አባዬ ...ወዮ አባዬ ! ወዮ አባዬ ! » እያለ ወደ ድንኳኑ ሲገባ በድንኳኑ የተገኙት ሁሉ ደንግጠው ፀጥ አሉ ። የነበረው ጨዋታና ሳቅ ቀዘቀዘ ።

ለቅሶውን ያዩ ሁሉ ደነገጡ ። እኛም በድንኳኑ ሸራ ተሸፍነን በቀዳዳ እያየነው እንስቅበታለን ።

« ማነው የሞተው በከሬ ? » የኔ እናት ጠየቀችው

« አባዬ ሞተቺኮ ! ወዮ ! » አለ አንገቱን ጉልበቱ ላይ ደፍቶ እያለቀሠ

« የቷ አባዬ ? »

« አባይ መሠሉ ሞተች ። መኪና ገጪት አሉ 'ኮ ... ወዮ ! »

«ኧረ የሠይጣን ጆሮ ይደፈን በል በከሬ ። ጎንጨት ብለህ ነው እንዴ የመጣኸው ? ይችትናልህ'ኮ አባይ መሠሉ ። »

ቀና አለ ። እማማ መሠሉን ሲያያቸው ደነገጠ ።

« ወዮ ! ... አባዬ አለሽ ? » አላቸው በሁለት መዳፎቹ ጉንጮቹን ተጭኖ

« አለሁልህ በከርዬ የኔ አዛኝ ! አለሁልህ ። ኧረ ለመሆኑ ማነው ሞታለች ብሎ ያስደነገጠህ ?»



@BOOKALEM

አሉና በነጠላቸው ጫፍ እንባውን አበሱለት ።

« ወዮ! ነይ አባዬ ... ሊጆቹን ላሳዩሽ ! » ብሎ እጃቸውን እየጎተተ ኪድንኳን ሲወጣ እንዳንታይ ተደብቀን ፈረጠጥን ።

በሌላ ቀን ደሞ አራምባውን ሰቦ እየተንገዳገደ ሲመጣ አገኘነው ። የአባባ ሺበሺን ቤት አሳየነው ። ግቢያቸው ውስጥ ድንኳን ተጥሏል ። የሚችች ልጃቸው የአርባ ቀን መታሰቢያና የሀውልት ምርቃት ነገ ይካሄዳል ።

ለድግሱ ወጥ እየተሠራ ፣ እንጀራ እየተጋገረ ፣ የጠላ መጠጫ ጠርሙሶች በጠላ እየተሞሉ ፣ መመገቢያ ሳህኖች እየታጠቡ የአባባ ሺበሺ ግቢ በሠራተኛ ሰዎች ተሞልቷል ። ለበከሬ ነገ የአባባ ሺበሺ ልጅ ብርሃኔ ዶክተር እንደምታገባ ነገርነው ። ደስ አለው ።

« አለ ገና አለ ገና

አለ ገና አለ ገና

የጋሽዬም አለ ገና ...» እያለ ሲዘፍን በተለያየ ሥራ ተጠምደው የነበሩ ሰዎች ደነገጡ ።

ትልቁ የአባባ ሺበሺ ልጅ መሳፍንት በከሬን በፍልጥ አገላበጠው ። በሰዎች ገላጋይነት ከመሞት የተረፈው በከሬ እያነከሠ ወዳላወቅነው ቦታ ሄደ ።

አባቱ ታመው ተኝተው ስለነበረ መሠለኝ መሳፍንት በከሬን የወገረው። ጠይሜ ግን መሳፍንት በከሬን የደበደበው ሥለዘፈነ ሳይሆን ድሀ ስለማይወድ ነው አለን ። አመንነው ። «እናንተ የዝቅተኛ ቤተሰብ ልጆች...ዘንድሮም በጨርቅ ኳስ ነው የምትጫወቱት ? አመዳሞች !»ይለናል ሁሌ ነገር ሲፈልገን ።

በከሬ ለረጅም ጊዜ ከሠፈራችን ጠፋ ። የናፈቅነው ልናገኘው አልቻልንም። መጫወቻ አጣን። ሳቅ ናፈቀን ። የሆነ ቀን ግን እኛ ቤት የጎረቤት ሰዎች ተሰብስበው ቡና ሲጠጡ የበከሬን ነገር አነሱ ።

የጠፋበት ዋና ምክንያት ዘመዶቹ ከጅቡቲ መጥተው ፣ አዲስ ልብስና ጫማ ገዝተውለት እያዝናኑት እንደሆነ ሠማሁ ። ለነ ጠይሜ የማወራላቸው አንድ እንቁላል የሆነ ወሬ እንዳገኘሁ ገባኝ ።

« በከሬ ግን ዕድለኛ ነው ! » አለች ጠምቤ

« እንዴት ? » እኔና ጠይሜ ዕድለኝነቱ እንዲብራራልን ጠየቅን ።

« ጅቡቲ ከገባ በኋላ እንግሊዝኛ በደንብ ይችላላ ። »

« አይችልም ! » ጠይሜ ተቆጣ



@BOOKALEM

« ለምን ? » ጅቡቲ ፈረንጅ ስለሚኖር ፈረንጅኛ ሊያውቅ እንደሚችል ገምቼ ጠይሜን ተከራ ከርኩት

« ጅቡቲ'ኮ እዚህ ከድሬዳዋ ቀጥላ የምትገኝ ሀገር ናት ። ፈረንጅ የሚኖረው ደሞ እ ...ዛ ! ሩ...ቅ! አሜሪካ ነው ። የጣሳ ዘይትና ነጩ ስንዴ ከሚመጣበት ሀገር ። ጤባ ናችሁ እንዴ ! » ጠይሜ ባለማወቃችን አለመጠብን ።

« ቆይ ግን አሁን በከሬ ጅቡቲ ከገባ በኋላ ሀማልነት ሠርቶ ዕቃውን እቤታቸው አደረሠላ ቸው እንበል ። እንዴት አድርጎ ነው ሳቢውን የሚጠይቃቸው ? » ጠምቤ ጠይሜን ጠየቀችው

« እኔ እንጃ ! »

« ቆይ ሳቢ ምንድን ነው ?»

ሁለቱም በጥያቄዬ ሳቁብኝ ። የጠምቤማ አሳሳቅ ያናድዳል ።

«ምን ያስቃችኋል ?» ስላናደዱኝ ኮስተር አልኩ

«እረ ጭንቅሎ...አታፍርም እንዴ ? ይህንን የሚያክል የእማማ ትሁኔን እረቁ ማውጫ ማሰሮ የሚበልጥ ጭንቅላት ተሸክመህ እስከዛሬ ሳቢ ምን እንደሆነ አታውቅም ? ሒሳብ ማለት ነዋ ። ምን ዓይነት ጤባ ነው በናትህ !» አለው ለጠምቤ

« ቅልጥ ያለ የገበሬ ማኅበር ጤባ እንጂ ! »

« ይቼ እንዲያውም ከአራዳ ማኅበር ይሠረዝ ! »

« ይሠረዝ ! »

ጠምቤ በአቅሟ ይሠረዝ ብላ ስትወስንብኝ ብልጭ አለብኝ ። በእጄ ጨብጬው የነበረውን አሸዋ ዓይኖቿ ውስጥ ሞጀርኩባት ። እርር ብላ አለቀሠች ። ጠይሜ እንዳሳረረኝ ጠምቤን እርር አደረግኳት ።

ጠይሜ ተደርቦ ሊመታኝ ሲል ሸሸሁት ። ተናድጄ ስለነበር ሳላውቅ ዓይኖቿ ውስጥ እንደበተንኩባት የውሸቴን ተናግሬ ይቅርታ ጠየቅኳት ። ጠምቤ ዓይኖቿ ሞጭሙጨው ከጠይሜ ጋ ብቻ ትጫወታለች ። እኔን አገለሉኝ። የሆነ ወሬ ሲያወሩ በመሀል እየገባሁ መልስ ሰሠጥ ፀጥ ይሉኛል።

« አንተ ከአራዶች ማኅበር ተሠርዘሀል ! ወጥተሀበታል ። ሂድና የጤባ ማኅበር አቋቁም ! » ይሉኛል ።

ርጥብ ፣ ጤባ መሆኔን አምኜ ተቀበልኩ ። እስከ ዛሬ ድረስ አራዳ ነኝ እያልኩ ከነሱ ጋር በመዘሬ ይቅርታ እንድጠይቃቸውና ካሁን በኋላ አጠገባቸው እንዳልደርስ አስጠነቀቁኝ ።



@BOOKALEM

ለብቻዬ ተቀመጥኩ ::

ብቻዬን ጎርፍ ባመጣው ደለል አፈር ስጫወት ተመካከረው እየመጡ የሠራሁትን ቤት ያፈርሱብኛል :: የአስከዛሬው የአራድነት ጉዞዬ የውሸት እንደነበር ሳላናግራቸው ይነግሩኛል ::

« ዱባ ራስ ! ቅል ራስ ! ራስ ከምር ! » የማይሉኝ ፤ የማይሠድቡኝ ስድብ የለም ::

እያለቀስኩ ወደ ቤቴ ሄጄ ለእናቴ ያደረጉኝን ነገርኳት :: ለሁለት ውግር እንድናደርጋቸው ተማፀንኳት :: ጠይሜን እንጂ ጠምቤን እንኳን አንቄ እንደምደፋት ገለፅኩላት :: ሁሉንም ካዳመጠችኝ በኋላ ግን « ... አንተ ነገ ጠዋት ዞረህ ለምትገጥመው እኔ የሰው ልጅ የምደበድብበት ምክንያት የለም » አለችና አባረረችኝ :: አናደደችኝ :: ለአባቴ ደሞ እንደዚህ ያለ ነገር አይነገረውም ::

« ፎሽፏፃ ! ሴታ ሴት ! አንተ ለነዚያ የማግማሳያ ሰባሪ ለሚያካክሉ ልጆች አንሥህ ነው ? ይኼኔ እህል ቢሆን አግዞኝ አትልም :: አንተ ወትሮስ ቢሆን ትሪ ላይ የተዘረረን እንጀራ ካልሆን መች ሌላ ነገር ታሸንፍና ! ሄድልኝ ከፊቴ ! እንኩሮ ! » ብሎ እንደሚያባርረኝ አውቃለሁ :: የአባቴ ትልቁ ስድብ « እንኩሮ !» ነው ::

እማዬ ለቡና ቁርስ ያዘጋጀችውን የባቄላ አሹቅ በሁለቱ የሱሪ ኪሶቼ ያዝኩ :: በብረት ምጣድ ተጋግሮ ፤ በእማዬ የጣት አሻራ አሸብርቆ ዘይትና በርበሬ የተለወሠውን ጠይም የማሽላ ቂጣ በትንሽ በትንሹ እየገመጥኩ ወደነ ጠምቤ ሄድኩ :: እያስቀናኋቸው ፊታቸው በልቼ እንደምጨርሠው ለራሴ ነገርኩት ::

ቁጭ ብለው ይጫወታሉ :: ቂጣዬን ወደ ኋላ ደብቄ ያዝኳት ::

« ጤባው ! ምን ልታደርግ መጣህ ? ከማኅበራችን እኮ ተወግደሃል :: » አለኝ ጠይሜ

« ጭንቅሎ ! ከኛ ከአራዶቹ ጋር ልትሆን ያምርሃል እንዴ ?» ጠምቤ ደረቷን በሌባ ጣቷ እየጠነቆለች አሳገጠችብኝ ::

ምንም ሳልናገር የከከርኳትን ቂጣ ወጣ አድርጌ በቁንጥ ገመጥ አደረግኩላት :: አሹቁንም ከኪሴ ቆንጥሬ ቃም ::

«ኧረ ጭንቅሎ ! » አለ ጠይሜ እጁ ላይ ያለውን አፈር እያራገፈ

« ኧረ ዲታው ጭንቅሎ ... ቂጣ ቆሎ ... እንዲ ...» ጠምቤ መገረሟን አበሠረችኝ

እንዳቁለጨለጭኳቸው ሳውቅ ተመቸኝ :: እጃቸውን እያራገፉና ልብሳቸው ላይ አፈሩን እየጠረጉ ተጠጉኝ :: በጉልቤ ሲነጥቁኝ ከምከፉ በጥርሴ ዝልገዝል እንደማደርጋቸው በልቤ አሰቤያለሁ ::

« ወደ አራዶች ማኅበር በክብር ለመመለስ ከፈልግክ ብጌ ! » አለኝ ጠይሜ እጄን ለልመና



@BOOKALEM

ዘርግቶ

« ባትጋራኝ ! » አልኩት

« ቀድሜ ብገ ብዬሃለሁ ! »

« አትሠማም እንዴ ... ባትጌ አልኩሆኮ ! »

በጣም ሰመኑኝ። ታረቅን። ትንንሾቹን የማርያም ጣቶቻችንን እያቆላለፍን አውራ ጣቶቻችንን ሳምን። ቂጣዬንም አሹቂንም ተካፍለን በላን።

***

በከሬን ፊት ለፊታችን እያነከሠ ሲመጣ አየነው ። ከጅቡቲ መመለሱን አመንኩ ። ጠምቤም «ከጅቡቲ በእግሩ ተመልሶ ሲመጣ እግሩ ተልጦ እያነከሠ ይሆናል» ብላ ይሆናኗን አስቀመጠች ። ጠይሜ ግን የአባባ ሺበሺ ልጅ መሳፍንት በፍልጥ የመታው እግሩ እንደተሠበረ ነገረን ። ከልባችን አዘንለት ።

አጠገባችን ሲደርስ የበከሬን እግር አይተን በረገግን ። ሁለቱም እግሮቹ አብጠዋል ። በቁስል ንፍርቅ ብለዋል ። የታሠሩበት ጨርቅ ከቁስሉ በሚወጣው ፈሳሽ ረስርሷል ። ያ ፈጣን ተራማጅ የነበረው ሰው ሁለቱን የእግር መረገጫዎቹን አንፈርክኮ በዱላ ተደግፎ ተጓዥ ሆኗል ። ያውም እንደ ዔሊ በዝግታ ።

ጅቡቲ ሲገባ ነው እየተባለ ዕድለኝነቱ የወላጆቻችን ቡና ማዳመቂያ ተደርጎ የነበረው ሰው የስጋ ደዌ ሕመም ተጠቂ ሆኖ ቢሲዲሞ ከርሞ መውጣቱን በኮልታፋ አማርኛው ነገረን ። በፈርጣማው ጉልበቱ ተሸክሞ በበላባት ፣ የበርካቶችን ድካም ባቃለለባት ድድ ማስጫ ጨርቅ አንጥፎ ተመፅዋች ሆነ ። የጅቡቲው መንገደኛ የሰው እጅ ጠባቂነቱ ፣ ለምኖ አዳሪነቱ እስከ ሕይወቱ ፍፃሜ ቀጠለ ።

በከሬ ከእጁ እርጥብ የባህር ዛፍ ቅጠል የማይለየው ሰው ሆነ ። ያለ ዕረፍት ቁስሉን የሚመጠምጡበትን ዝንቦች ያባርራል ። ሰዎች ዳቦ የማይገዛ ሳንቲም ሲወረውሩለት እንኳን ፊታቸውን አዙረው ነበር ተጠይፈውት ፣ ቁስሉን ማየት ቅፍፍ ብሏቸው ። እኛም « ኢሺሼ!» እያልን ሌላ ሕመም ሆንበት ። የሳቅ ምንጫችንን ፣ አውርቶ አሳሳቂያችንን ፣ መጫወቻችንን በከሬን የስጋ ደዌ በሽታ ነጠቀን ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ስምንት

## ለከፋ

« ብሪቱ የሳሙና ሴባ !» ሲሏት አትወድም ። እሷ ግን ማንንም ቢሆን የምትሳደበው « አትሄድም ከዚህ አንት የሳሙና ሴባ !» እያለች ነው ። ከሳሙና ሌላ ሌላ የሚሠረቅ ነገር ያለ አይመስላትም መሠለኝ ። ወይም ደሞ የምታውቀው ሁሉም ነገር ሳሙናና ሳሙና ብቻ መሆን አለበት ። ለዚያም ይመስለኛል «ሳሙኔ!» የሚለውን ቅጥያ መጠርያዋን መንደራችን የሠጣት ።

ብሪቱ እብድ ናት ። በመንገድ ሁሉ ያያት የሚፈራት ፣ ፈርቶም መንገድ የሚለቅላት አደገኛ እብድ ። አፏ ዝምታን አያውቅም ። ተቀምጣም እየሄደችም ትለፈልፋለች ። ሰው አጠገቧ ኖረም አልኖረም ከመለፍለፍ አትታቀብም ።

በጀርባዋ የምታዝለው ኮተት ብዛት ይገርማል ። « ምነው ይቺ ሴትዮ ይህን ያክል ኮተት ቀኑን ሙሉ ተሸክማ መዋል ከቻለች ሸክሟን በገንዘብ ብትቀይረውስ ?» እያለች እናቴ ብዙ ጊዜ ብሪቱን ስታማት እሠማታለሁ ። በርግጥ እናቴ እብዷን የምትቦጭቃት ከቡና አጣጪ ከአማማ ዘርትሁን ጋር ሆና ነው ። ግን ያው መስማት ስለማልከለከል የሚሏትን ሠማሁ ።

እብዷ ብሪቱ የጎረቤታችን እህት ናት ። ያውም ታላቅ እህት ። እህትየው አግብተው ይኖራሉ ። ልጅ የላቸውም ። ተፈጥሮ ማዕቀብ ጥላባቸው መውለድ ስለማይችሉ « ልጄ » ብለው የሚያሳድጉት የእብዷን የብሪቱን ልጅ ተመስገንን ነው ። ፈቅዳ ሠጥታቸው ሳይሆን ለዱርዬዎች ገንዘብ ከፍለው ጨቅላዋን አሰሠርቀዋት ። ተሜ በትምህርቱ ጎበዝ ስለሆነ ብዙ ጊዜ እንዲያስኮርጀን እንጠይቀዋለን ። ግግም ካለ ሙጫ ነው ።

« አስኮርጀን ከምትሉኝ አታጠኑም ?» ይለናል ።

እንናደዳለን ። አጥኑ የሚለንን ሰው እንዴት እንደምንጠላው ባወቀ ። ልናበሽቀው ስንፈልግ « የሳሙኔ ልጅ !» እንለዋለን ። ይንጨረጨራል ። ድንጋይ አንስቶ እስከ ቤት ቤታችን ያሳድደናል። ሲናደድ ከእብዷ እናቱ በላይ ያስፈራል ።

ከሠፈራችን ልጆች ሳሙኔ የተሜ እናት መሆኗን በመጀመርያ ያወቅኩት እኔ ነኝ ። እኛ ቤት አከስቱ ከእናቴ ጋር ቡና ሲጠጡ የሚያወሩትን ተደብቄ ሠማኋቸው ። አልጋዬ ላይ ተጋድሜ ፣ በብርድ ልብሴ ተሸፍኜ ፣ የተኛሁ መስዬ ምስጢራቸውን ልቅምቅም አደረግኩ ።

« ግን ብሪቱን ያስወለዳት ይታወቃል እንዴ እትዬ ?» አለቻቸው እናቴ የተሜን አክስት

« እንዴታ ! ይታወቃል እንጂ ! »

« ታድያ ... እንዲያው ልጄ የት ደረሰ ብሎም አይመጣም ? እሷንስ የት ወደቅሽ ብሎም የማያ



@BOOKALEM

ያት ምን ሆኖ ይሆን ?»

« ኸረ ምን በወጣው እቴ ! »

« እንዴት እትዬ ... ምንም ብትሆን ሚስቱ ተሚስ ቢሆን ልጅ አይደል እንዴ ?»

« ለማበዷስ ምክንያቱ ማን መሆኑ ቀረና መጥቶ ይጠይቅ ? ለራሱ ጠያቂ የሚያሻው እብድ !» የተሚ አከሰት በስጨት ያሉ መሠለኝ ።

« በባሏ ምክንያት ነው ያበደችው እንዳይሉኝና እንዳላብድ ብቻ !»

« አልኩሽ እንጂ ወዳጄ !»

« አፈር ይብላ ! ዱሮስ የዘንድሮ ወንድ መች ፍቅር ያውቃል ። ይኼኒኮ በየጠንቋይና ደብተራው ቤት እየዞረ አስተብትቦባት ይሆናል ።»

ጆሮዬ የተሚን ምስጢር ለማዳመጥ ከመቼውም በላይ ቆመች ። ትንፋሼን ዋጥ አድርጌ ምስጢራቸውን በአንገሌ ከረጢት ጠቀጠቅኩ ።

« የተሚ አባትም እብድ ነው ። አህመድ ይባላል ። ብራቱ በመንደሯ በዘናጭነቷና ቀብራራነቷ ታዋቂ ወይዘሪት ነበረች ። ትምህርቷን ባትጨርስም በመንግሥት መሥርያ ቤት ተቀጥራ እንጀራ የሚያስቆርስ ገቢ ነበራት ። ድንገት አህመድ አንቆ እስኪያበላሻት ድረስ ክብረ ንፅህናዋን የጠበቀች ሴት ጉድ ሆነች ።»

« ተደፍራ ነው እንዳይሉኝ ብቻ ያበደችው ?»

« ነው እንጂ ! ይኼ ቡዳ አህቴን በላብኝ ። ወደ ሥራዋ እየኼደች መንገድ አገኛት ። ከአደሬ ጢቆ ድልድይ ቁልቁል ገፈተራት ። አለቱ ላይ ተፈጠፈጠች ። ከገባችበት ሰመመን ሳትነቃ ሰው ተሰብስቦ እያየ ደፈራት ። ክብሯንና ንፅህናዋን በጉልበቱ ነጠቃት ።»

ይኼ...ክብረ ንፅሕና የሚባለው ነገርዬ ምን ዓይነት ዕቃ ቢሆን ነው በጉልበቱ የወሠደባት ? ግራ ገባኝ ። «ቀለበት ፣ ሀብል ፣ ኮፍያ ፣ ፎጣ ፣ ደብተር ተነጠቁ !» እንጂ «ክብረ ንፅሕና ተነጠቁ !» ሲባል ሠምቼ አላውቅም ። እናቴን እሷም ክብረ ንፅሕና እንዳላትና እንደሌላት ፣ እንደተነጠቀችና እንዳልተነጠቀች ወሬያቸውን ሲጨርሱ እንደምጠይቃት ተማምኜ ማድመጤን ቀጠልኩ ።

« ሰው እያለ ፣ ተሰብስቦ እያየ ፣ በጠራራ ፀሐይ በእብድ ስትደፈር ሰዉ እንዴት ዝም ብሎ ቆሞ እንደ ቀበሌ ኪነት ያያል !»

« አዬ ! ሰዉ ምን ያድርግ ! ወዲህ እብድ ነው ፣ እዚያ ስሜት ላይ እያለ ተው ቢሉት አሳድዶ አይገድላቸውም እንዴ ?»

« ኧረ ! ምን አባቱ ያመጣል ይኼ ጉፋያ !»



@BOOKALEM

« ኤድያ ! አንቺ ደሞ አበዛሽው ። ብትኖሪ የማታደርጊውን አትፎክሪ ። ሰው ሁሉ ያለ ዕድሜው የሚቀጨው በእምስ ዳፋ መስሎኝ ።» እትዬ ሳይበሳጩ አልቀረም ።

አፌን ይገኘ ሳቅኩ ። ለካ ትልቅ ሰውም ባለጌ ነገር ይናገራል ! የተሜ አክስት ... እትዬ ባለጌ ናቸው ። ወይም ደሞ ጆሮዬ እትዬ ያላሉትን ሠምቷል ። እንደዚህ ከሆነ ደሞ ባለጌው የኔ ጆሮ ይሆናል ።

እናቴ ቡናውን ስትቀዳ ይሠማኛል ። በመዐዛው ብርድ ልብሴን ጥሶ አፍንጫዬን ያነቃነቀውን ሉባንጃ የእጣን ማጨሻው ላይ ካለው እሳት ጨመረች ። እየተንጫጫ ጨሰ ። ሽታው ብቻም ሳይሆን ጫጫታው ተመቸኝ ። ቸ ቸ ቸ ቸ ... አቤት ሉባንጃ እወዳለሁ ። እቤት ውስጥ ከርቤ ከሚያጨሱ አፍንጫዬ ውስጥ ሉባንጃ ቢያጨሱ እመርጣለሁ ።

« እንዲህ እንደሉባንጃው ያባቴ አምላክ በገሃነመ እሳቱ ያንጨርጭረው ። በጠራራ ፀሐይ እንደደፈራት በጠራራ ፀሐይ ይሠርረው !» አለች እናቴ

« ይቅር ይበልሽ ወዳጄ ! ለመሆኑ ያልሽውን ታውቂዋለሽ ?»

« እንዴታ! የምለውንማ አውቃለሁ እንጂ !» እናቴ እርግጠኝነቷን ተናገረች።

« ተይ ! ተይ ! ...ያልሽውንማ አታውቂውም !»

« አውቃለሁ እንጂ እትዬ...ምን ማለትሁ ነው ?»

« ኤድያ ! ‹አውቃለሁ ፣ አውቃለሁ› አትበይኝ አ! የምትናገሪውን ብታውቂውማ ‹በጠራራ ፀሐይ ይሠርረው› አትይም ነበር ። እሱ ይቅር ይበልሽ ! መቼም መሀሪነቱ የበዛ ነውና የአፍሽን አይቆጠርብሽ !»

«ኧረ የታባቱ ! ... ይኼ ብስብስ ! አሁንም በጠራራ ፀሐይ ይሠርረው !»

«እኮ ማ ማንን ? »

«ሠይጣን ነዋ !ዲያቢሎስ...የቀትሩ ጋኔል ነዋ አህመድን የሚሠርርልኝ ።»

« ነው እንዴ ? አሂሂ ...» የተሜ አክስት ብቻቸውን ሳቁ ።

« ማን መስሎዎት ነው ታድያ ?»

« ኧረ ተይው እቴ... እኔው ነኝ ባከሽ የዞረብኝ...ይቅር በለኝ !» አሉ

« ለመሆኑ...ይኼ ምስኪን ተመስገን ታሪኩን ያውቀዋል ?»

« ማን ነግሮት ? ብሪቱም ብትሆን እንኳን እናቱ ዘሩ አትመስለውም ።»

« አይንገሩት ! እንዲያው ትንሽ ከፍ ሳይል እንዳይነግሩት ። ለመሆኑ መንደርተኛውስ ይኼን



@BOOKALEM

ታሪክ ያውቀዋል ?»

ማንም ሰው የተሜን ታሪክ እንደማያውቅ አረጋገጡላት ። የተሜን ምስጢር ከእናቱ ቀጥሎ በእንጎሌ ካስት ቀርጮ የያዝኩት ብቸኛው ሰው በመሆኔ ኩራት ተሠማኝ ። ጠይሜ ቢሆን ይኼን ከባድ ምስጢር አሪፍ የገቢ ምንጭ ያደርገው ነበር ።

እኔ ግን እነ ጠምቢን እያስማልኩ ብቻ ለሌላ ሰው እንዳይነግሩ እያስጠነቀቅኩ የተሜን ታሪክ ነገርኳቸው ። ደነገጡ ። ሳሙኔ የተሜ እናት መሆኗን ሲሠሙ ክው አሉ ። በየፊናቸው ሳሙኔ የተሜ እናት መሆኗን ለሠፈር ልጆች እያስማሉ ነገሩ ። የሠፈር ልጆችም ለሌሎች ምስጢሩን ላልሠሙ የትምህርት ቤት ጓደኞቻችን እያስማሉ ተናገሩ ።

በየብሽሽቁ ተሜን «የሳሙኔ ልጅ » ስንለው ከአቅሙ በላይ ለሆነት ያለቅሳል ። ሊግደረደራቸው የሚችለውን በድንጋይ ያሯሩጣል ። እንደ ዘበኛ ጥይት ከጉልበት ይቀለጥማል። እናቱና የተሜ አክስት ተረጋግመው ተለያዩ ። እናቱ እትዬ የነገሯትን ምስጢር ለራሷ እንኳን ደግማ እንዳልተናገረች ምላ አረጋገጠችላቸው ። አላመኗትም ። የብራቱን ጦስ ትወስድ ዘንድ ፈሪሳ አሉባት ። እናቱ በኔ ምክንያት ወሬኛ ተባለች ። በመንደርተኛው ተጠላች ።

የሳሙኔን ከአካባቢው መሠወር ተከትላ በመንደራችን ገናና የናኘው እብድ «ዘርፈሽዋል» ትባላለች። ስናቆላምጣት ደግሞ ዘርፌ ። ታጨሳለች ። ገንዘብ ካላት ገዝታ ከሌላትም ቁሬ እየለቃቀመች ፣ ሱቅ ውስጥ የተሠባበረ ፣ በዘይትና ጋዝ የተበላሸ ሲጋራ እየለመነች ታቦናለች ። አንድ ወቅት ላይ « የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበት ሲጋራ አጭሳ ነው » ተብሎ ከሞት በመከራ ተመልሳለች ። ስታጨስ ማንም እንዲያያት አትፈልግም ። በተለይ ትልልቅ ሰዎች ከመጡባት የያዘችውን ሲጋራ ትደብቀዋለች። ከነ እሳቱ ወደ ብብቷ ትከተዋለች ። እንዴት እንደማያቃጥላት ፈጣሪዋ ይወቅላት ።

ጫማ አትወድም።እንኳንስ በእግሯ ልታደርገው ይቅርና የጫማ ጥቅሙም የገባት አይመስለኝም። ጉልበት ላይ የሚቀር እጀ ጉርድ ባለ አበባ ሽንሽን ቀሚስ ታደርጋለች ። ዘወትር መኝታዋን አዝላ ትዞራለች ። ቀኑን ሙሉ አዝላው ትውልና መሽቶ ወደ ማደርያዋ ስትገባ አንጥፋ ትተኛበታለች።

የዘርፌ ቤት ለአማማ በቀሉ ኩሽና ነው ። ምግብ ማብሰያቸው ፣ ጠላ መጥመቂያቸው ፣ አረቂ ማውጫቸው ። ኩሽናው ሠፊ በመሆኑ ምጣዳቸውን ወደ አንድ ጥግ ጥደው ፣ አጠገቡ የብረት ጉልቻ አስቀምጠው ቀሪውን እንድትተኛበት ፈቅደውላታል ። እሳቸው ቤተ ክርስትያን ሳሚ ፣ ጿሚ ፣ ፀላይ ናቸው ። የራበው ማየት ያስከፋቸዋል ። የታረዘን ማልበስ ይቀናቸዋል። ለዚያም ነው ዘርፌን ማዕድ ቤታቸው ውስጥ እንድታድር የፈቀዱላት ። ለፅድት ትሆነኛለች ብለው ያስጠጓት።

የኩሽናውን ፅዳት ትጠብቃለች ። ለዘርፌ ሴቶች ሁሉ እትየ አበቡ ሁሉም ወንዶች ጋሽ አበቡ ናቸው ። በዘርፌ ዓለም ውስጥ ሁለት ስሞች ብቻ አሉ ። የራሷ መጠርያ የሆነው «ዘርፌ» እና ፆታ ሳትለይ ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች ያለ ስስት የምትጠቀምበት «አበቡ» ። የቡና ጀበናዋንና ስኒዋን



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ከሠረቁባት ጊዜ ጀምሮ ቡና የምታፈላው ከእማማ በቀሉ እየተዋሠች ነው ። እብድ ናትና ምጣዱን ትሠብራለች አሳሉም ።

ጀበና ፣ ስኒ ፣ ጊርጊራና ማንደጃ ትዋሳለች ። በራሷ ብረት ምጣድ ቡናውን ትቆላና ጎረቤቶቿን ውቀጡልኝ ትላለች ። የፈለገ ነገር ቢመጣ ቡና ለመውቀጥ ዘነዘና አታነሳም ። « እጄን ይቀረጥፈኛል...ውቀጡልኝ !» ብላ በቅርቧ ያገኘችውን ትለማመጣለች ። አንዳንዴ ደሞ ጠይሜና እኔ እንወቅጥላትና የጠጠር ከረሜላ መግዣ ሳንቲም እንቀበላታለን ። ገንዘብ ስታገኝ እንደምትሠጠን ቃል እየገባችልን በዱቤ የምንወቅጥበት ጊዜም አለ።

አንዳንድ ቀን ደሞ ጉልቤ ትሆንብናለች ። ቡናዋን አስወቅጣን ስታበቃ « የምን አባታችሁ ገንዘብ ነው የምሠጣችሁ ! ሂዱልኝ ከዚህ ሌቦች !» ብላ በቡና መቁያ ብረት እያስፈራራች ታባርረናለች ። ድንጋይ ስናነሳባት ትፈራለች ። ያልወረወርንባት ድንጋይ ፊቷን እንዳይመታት በእጇ እየተከላከለች « ኡ ! ኡ ! » ትላለች ። ጎረቤቶቿ ይወጣሉ ። እኛ እንደበቃለን ። ተደብቀን እያየናቸው ሳያዩን ይረግሙናል ። የገዛ ወላጆቻችንም በተራጋሚነት ተሠልፈው « ይድፋቸው ! በአጭር ያስቀራቸው ! የሷን ዕድል ለነሱ ያርግላቸው !» ይሉናል ።

ዘርፌ ቡና አፍልታ ጎረቤቶቿን ትጠራለች ። የማያሳፍሯት ጎረቤቶቿ እብዷ ዘርፌ ቤት ቡና ሲጠጡ ጥሪዋን ተከትለው ይመጣሉ ። እንግዶቿን አስቀምጣ በአንደኛው ስኒ ብቻ ደጋግማ እየቀዳች ደጋግማ ብቻዋን ትጠጣለች ። ለራሷ ብቻ እየቀዳች በእንግዶቿ ፊት ትጨልጣለች ። እንግዶቿም ይህን ባህርይዋን ያውቃሉ ። አንድ አራት ስኒ ከጠጣችና ከጠገበች በኋላ ከተረፋት ለእንግዶቿ ትሠጣለች ። ያለበለዚያ ስትጠጣ አይተዋት መመለስ ግድ ይላቸዋል ።

« ምነው ዘርፌ...ቡናውን ለኛም ሥጪን እንጂ ?» አሏት እማማ በቀሉ

« ቆዩ ! እንጂ እትየ አበቡ...እኔ ገና መች ጠጣሁና !» ሦኒዋን እንደጠጣች እኔም ፣ ጠይሜም፣ ጠምቤም በኩሽናው ቀዳዳ አይተናታል ።

«ይኸው ! እኛን ቁጭ አርገሽ ጠጣሽ አይደል እንዴ ዘርፍዬ ?»

« ማ እኔ ? ኧረ አልጠጣሁም ። እሙብርሃንን እትየ አበቡ ገናኮ አልጠጣሁም ።»

«ተይው በቃ ! እሙብርሃን መህላሽን አትቅቁጠርብሽ ።»

« ኧረ ትቁጠርብኝ ...እሙብርሃንን ስልሽ እትየ አበቡ ።» ዘርፌ አራተኛ ስኒዋን ለራሷ ቀዳች።

« ለመሆኑ ስንት ስኒ ጠጣሽ ? አራተኛሽ መሆኑም አይደል ?»

« እሙብርሃንን ! ብዬሽ እትየ አበቡ...እኔ ገና ሰባት ነው የጠጣሁት ። አራትማ አልጠጣሁም ።»

« ወይ ጉድ ! ከአራትና ከሰባት የቱ ይበልጣል ዘርፍዬ ?» አሏት ስህነ

« እኔ ነኛ...እኔ ነኛ ታላቅ !»



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

በዘርፌ መልስ ሁሉም ቡና ጠጪዎች ሳቁ ። እኛም እየሳቅን ሮጥን ።

« ቆይ ጠብቅ አንተ ጭንቅሎ...ለአባትህ ባልነግርልህ እኔ በቀለች አይደለሁም ። አሃ ! ተገረመሣና ብለህ ብለህ ኩሽና ስርሰራ ጀመርካ ! ድሮስ ማንን አይተህ ታድግ !»

ዘርፌ የግል ንፅሕናዋን ለመጠበቅ የምታደርገው ጥረት ይገርመኛል ። ወግ ወጉን ይዛዋለች። ገላዋን ለመታጠብ ልብሷን ሰው ፊት ማውለቅ አያሳፍራትም ። በሯ ላይ ነው የምትታጠበው። ያወላለቀችውን ልብሷን ሰብስባ ቤቷ ታስገባና በሯን ከውጭ ትቀረቅራለች ። ከዚያ በባለ አንድ ሊትር የፕላስቲክ ጠርሙስ ይዛ ያመጣችውን ውሃ ፀጉሯ ላይ ትጨምራለች ። « እችክ ! እችክ! ...» ትላለች ገና ውሃው ገላዋን ሳይዳስስ ። ከፀጉሯ ሾልኮ ያመለጠው ውሃ ተንኳሎ እግሯ ይደርሳል። በቃ ውሃው እግሯ ጋር ሲደርስ የዘርፌ ገላ እጥበት ያበቃል ። ከአንድ ሊትር ውሃ ላይ ቢያንስ ሩቡን ታስተርፋለች ። ሁሌም ገላ መታጠብ ለዘርፌ እንዲህ ነው ።

ዘርፌ ወገቧን በመቀነት ታስራለች ። በጀርባዋ ከምትሸከመው በተጨማሪ በሆዷ በኩልም የማትጠቀጥቀውና የማትይዘው ኮተት የለም ። የጀርባዋ መሻታዋ የሆዷ ደሞ ገንዘብ እንደሆነ ይታመናል ። እናም አንድ ምሽት ወደ ቤቷ ስትገባ ጨለማ ውስጥ ዱርዬዎች ጠበቋት ።

ጨለማውን ተገን አድርገው ሲዘርፏት አሥፈሥፉ ። አጠገባቸው ስትደርስ በዱላ መቷት። ስትጮህ ድምጿን የሠሙ ደረሱላት ። ዱርዬዎቹ በታዳጊዎቿ ላለመታየት ሸሹ ። ሽሽታቸው ብዙ አላስኬዳቸውም ። ቀን በብርሃን ያላዩት ፣ይኖራል ብለው ያልጠረጠሩት መሥናክል ለስልክ መስመር ዝርጋታ የተቆፈረ ቦይ ውስጥ ከነ ነጠቋት ኮተት ተሠባብረው ተገኙ ። በድርጊታቸው እየኮነኑ ዱርዬዎቹን ለፖሊስ አሳልፈው ሠጧቸው።

ዱርዬዎቹ እኔና ጠይሜን ቢጠይቁን ኖሮ ስለ ዘርፌ በደንብ እንነግራቸው ነበር ። በሆዷ በኩል እየጠቀጠቀች እርጉዝ የምትመስልበት ኮተት እየለመነች የምትሠበስበውን ቡና፣ አተር፣ ፈንዲሻ፣ ሽምብራ ፣ ከሠል ፣ ባቄላ ፣ ሽንኩርት ፣ ቲማቲም ፣ ቃርያ ምናምን መሆኑን እናውቃለን። የገንዘቧ ማስቀመጫ ቋሚ ሥፍራ የለውም ። ሲያሠኛት መቀነቷን ፣ በይ ሲላትም ሻሿን ፣ አንዳንዴም ከረጢት አንገቷ ላይ አንጠልጥላ ትይዛለች ።

በምንም ተዓምር ቀን ቀን እየለመነች የሰበሰበችውን ገንዘብ ወደ ቤት አታመጣም ። ባገኘችው ልክ ጠጥታበት ትገባለች እንጂ ። ሥከር ካለች ትሳደባለች ።በተለይ ልጅ ልጆቹን በስድብ ሙልጭ ማድረግ ያስደስታታል ።

እኔና ጠይሜ ከቤት ሥትወጣ እንጠብቃትና እንለከፋታለን ። «ዘርፌ የሠጤ ሚስት» እንላታለን ። ደስ ይላታል ። ሠጤን ትወደዋለች ። በአህያ ትከሻ እየጫነ በሚያመላልሠው አሸዋ የብዙዎቻችን ቤት ተገንብቷል ። ሥራ ብቻም ሳይሆን ጨዋታም ያውቃል ።

« ሠጤ ባለጌ !» ስንለው

« እናትክን ነፋሁልህ እንደዚህ አድርጌ !» ይለናል ቂጡን አፈንድዶ ።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

እንስቃለን ። እናቶቻችንን በሌሉበት እያሠደብን እንፍለቀለቃለን ። በጥቁር ፊቱ ላይ ነጭ ጢም ያበቀለ ፣ የሚለብሠው ሱሪና ጃኬት ሠፋፊ የሆነ ፣ መቆምና ቅርፅ መያዝ በተሳናት ወዘ ቢስ ኮፍያ ጭንቅላቱን የሚሸፍን ፣ ለአህያዎቹ መግረፊያ ዱላ ከእጁ የማያጣ ሰው ነው ሠጤ ። አንዳንዴም በዱላዋ ገርጥ ያደርገናል ።

« ሠጤ ...የአህያዋ ቂጥ እንዴት ይላል ?» ስንለው ከናፍሮቹን አጥብቦ ፣ ምላሱን አሾልኮ ብቅ ጥልቅ እያደረገ ያሳስቀናል ። ከናፍሮቹን እያርገበገበ የንዝረት ዓይነት ድምፅ እያወጣ ምራቁን አውቆ ፊታችን ላይ ይረጭብናል ። ፊታችንን ከምራቁ እያፀዳን እንስቃለን ።

ታላላቆቻችን ተሠብስበው « ሠጤ ከአህዮቹ አንዷ ሚስቱ ነች !» ሲሉ ሰምተናቸው እናውቃለን። ስለዚህ ጉዳይ ጠይቀነው ግን አናውቅም ።

« ዘርፌ ባልሽ ማነው ?» ተብላ ስትጠየቅ ባለ አህያው ጋሽ አበቡ መሆኑን ትናገራለች ። ለዚያም ነው የሠጤን ስም ስናነሳባት ደስ የሚላት ።

እሱ ግን ይናደዳል ። ዘርፌ ሚስቱ መሆኗን ስለነቃንበት በሽቋል ።

« ልጆችዬ ! የሷን ወሬ አትስሙ ። እሷኮ አብድ ነች ። ነገ ጠዋት የናንተንም አባት ባሌ ነው ልትል ትችላለች !» ይለናል ሲያስቀይሰ ።

እናምነውም ።

እኔ ጠይሜና ጠምቤ ጀርመን ሜዳ ኳስ እንጫወታለን ። ሠጤ አህያዎቹን እየነዳ ወደ ወንዝ አሸዋ ሊጭን ይወርዳል ። ዘርፌም ተከተለችው ። ተጠቃቀስንና ወደ ጫካው ሲገቡ አድፍጠን በቆረጣ ተከትለናቸው ። ወደ ፊት ወደ ኋላ ፣ ወደ ቀኝ ወደ ግራ ተዘዋውሮ አካባቢውን ተመለከተና ወደ ጢሻው ይዟት ገባ ። ቀሚሷን ገልቦ አስተኛት ። ሱሪውን አውልቆ ሊቀመጥባት ሲል ጠይሜ ተንኮል አሰበ ።

አህዮቹን ነድተን የበቆሎ ማሳ ውስጥ ጨመርናቸው ። ሲድስቱም አህዮች በቆሎውን ከወገብ ከወገቡ እየገነደሱ ተጫወቱበት ። ሠጤ ያየውን ነገር ማመን አልቻለም ። በፍጥነት ከእርሻው ውስጥ አህዮቹን አስወጥቶ ሊሄድ ሲል የእርሻው ባለቤት መጣበት ። ተናደደ ። ሠጤን በቦክስ ነቀለው ። እንደ እሎሎ ወርዋሪ ተንገዳግዶ ፣ ተሽከርክሮ ተዘረረ ።

«Knock Out !»

« ወይኔ ! ለካ ሠጤ አቅም የላትም ?» ጠምቤ የጠይሜን እንግሊዝኛ ተከትላ ሃሳብ ሠጠች ።

ዘርፌ ራቁቷን የተዘረረው ሠጤ ላይ ተደፋችበት ።

« ባሌን ገደልከብኝ ጋሽ አበቡ !» አለችው ባለ እርሻውን

« አንቺንም እንዳልገድልሽ ! ጥፊ ከዚህ...ደሞ ለምንድን ነው ልብስሽን ያወለቅሽው ?» ተቆጣት



@BOOKALEM

« ባለ አህያው ጋሽ አበበ እቅፍ አድርጎኝ ተኝቶ ነበራ ። አንተ ባትገድለው ኖሮ እስካሁን ያቅፈኝ ነበርኮ ። በቃ እሱ ከሞተ ና አንተ እቀፈኝ !» አለችው እየተጠጋች ።

ሸሻት ።

ተጠጋችው ።

ሲሸሻት ስትጠጋው በመጨረሻ ፈርቷት ሮጠ ። ተከተለችው ። ኡኡታዋን አቀለጠችው ።

መሮጡን አቆመ ። ራቁቷን እላዩ ላይ ተጠመጠመችበት ። አንገቱን አቅፋ በሁለት እግሮቿ ወገቡን ቆልፋ ተለጠፈችበት ። ሊቋቋማት አልቻልም ። ሸሚዙን በጉልበቷ ቀዳደደችበት ። በጉልበቷ ሱሪውን አወለቀችበት ። በጀርባው ወደቀ ። ተመቻት ። « ዘርፌ በናትሽ !» ይለምናታል። አፏን ወደ ሽንት መሽኛው አስጠጋች ።

« ወይኔ ! ወሸላውን ልትበላበት ነው !» አለ ጠይሜ

« ወሸላው ከተበላበት እንዴት ይሸናል ?» ጠምቤ ጠየቀች

« እንደ ሴት ባለ ዳቦ ይሆናላ !» አልኩኝ

ማንም አልሳቀልኝም ።

« ኧረ ! በናታችሁ ይኼን ሰውዬ እናስጥለው ።» አለ ጠይሜ

ከባህር ዛፉ ቀጠን ፤ ቀጠን ያለውን ገንጥለን ይዘን ወደነ ዘርፌ ሮጥን ። ሆስታችንም ዱላችንን አሳረፍንባት ። ተነስታ ሮጠች ። ልብስ ኮተቷን ጥላ ተፈተለከች ።

ዘርፌ በጣም ከምትፈራቸው እብዶች ውስጥ ዋነኛዋ ቀሽቲ ነች ። ለነገሩ ቀሽቲን የማይፈራ ማን ጤነኛስ አለና ።

ቀሽቲ ከፀጉሯ እስከ አለባበሷ ቁጥርጥር ነው ። በፍፁም አማርኛ አታወራም ። አፍ የመፍቻ ቋንቋዋን ትጠቀማለች ። ለሚለከፏት ካልሆነ ለልጆች ፍቅር ነች ። የምታሳድጋት የውሻ ቡችላ አለቻት ። የምትኖርበት ቤት የላትም ። የምታድረው የወታደር ካምፕ አጥርን ተደግፋ አልያም ፖሊስ ጣቢያን ተጠግታ ነው ። ውሻዋን ይዛ ትተኛለች ። ለማንም መንገደኛ በምሽት በዝግታ መራመድ የሚከለከለው ካምፕ አጥር ለቀሽቲ ግን የመዋልም የማደርም ሙብት መስጠቱ ይገርመኛል ። « ፎቶ ግራፍ ማንሳት ከልከል ነው !» የሚል ፅሁፍ ያለበትን አጥር በከፉ ዓይን እንኳን ማየት እንሚያስቀጣ አውቃለሁ ። እንዲያውም አንድ ጊዜ እንዲህ ሆኛለሁ ።

የስድስተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከመውሠዳችን በፊት ጋሽ ተፈራ ፎቶ አነሳን ። በተነሳን በሳምንቱ ሁለት ሁለት ፎቶ ግራፎች ትርፍ ናቸው ተብለው ተመለሱልን ። በሕይወቴ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ፎቶ መነሳቴ ነበር ። የመጀመርያው ለሕክምና ካርድ ማውጫ ከቤተሰቦቼ ጋር የተነሳሁት ሲሆን ሁለተኛው ይህኛው የሚኒስትሪው ነው ። ትዝ የሚለኝ አንደኛ ክፍል ስመዘገብ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ለትምህርት ቤት የተሠጠው ፎቶዬ አባቴ ጡረታ ስለወጣ ከሕክምና ካርዱ ላይ የኔ ለብቻው ተቀርድዶ ነበር ። እና ሁለቱን ፎቶዎቼን በደብተሬ ከትቼ ወደ ቤቴ ስሄድ « ፎቶ ግራፍ ማንሳት ክልክል ነው !» የሚለው ቦታ ጋ ስደርስ ደብተሬ ከእጄ ወደቀ ። ፎቶ ግራፎቼም ተበታትነው ወደቁ ። በሩን የሚጠብቀው ወታደር ፍጥጥ ብሎ ሲያየኝ ደብተሬን ብቻ አነሳሁና ፎቶዎቼን እዚያው ተውኳቸው ። ከዚያም ፈረጠጥኩ ።

« ማሙሽ ! ማሙሽ ! ፎቶ ጥለሃል አንሳ !» አለኝ ወታደሩ

« ኧረ ብልጡ ! እ...ልትመታኝ !»

« እንዴ ለምን እመታሃለሁ ?»

« ማንበብ የማልችል መሠለህ ! ግድግዳችሁ ላይ 'ግድግዳችሁ ላይ ፎቶ ግራፍ ማንሳት ክልክል ነው' ብላችሁ ለጥፋችሁ የለ ?» አልኩት ወታደሩ ሳቀ ።

እቤት ስገባ ጠምቤ ፎቶዎቼን ይዛልኝ መጣች ።

ቀሽቲ ግን እንደ ልቧ ናት ። እንኳን አጥሩ ሥር ለማደርና ግቢው ውስጥ እየገባች እንዳሻት እየተሽከረከረች ትውልበታለች ። ያለ ክልካይ ትፈነጭበታለች ። በጉልበቷ ገብታ ተለምና ትወጣለች ። የበሩን መከለያ ትልቅ አግዳሚ እንጨት በብረት መዝጊያ ካልቀየሩላቸው ቀሽቲን ወደ ግቢው ከመግባት ሊከለክሏት እንደማይችሉ ወታደሮቹ ይናገራሉ ።

እሷን መምታት የማይታሰብ ነው ። እንኳንስ የሚመታትን በክፉ ዓይኑ የሚያያትን ድንጋይ ለቃቅማ ታሳድደዋለች ።

«ዴሚ ኑራ ! ኢልመ ሸርሙጣ ! ማሊፍ አከና ነላልታ ? ነኛቹ ፌታ...አዉ !» (ኺድ ከዚህ ! የሸርሙጣ ልጅ ! ለምን እንደዚህ ታየኛለህ ? ልትበላኝ ፈለግክ እንዴ...አዉ !) ብላ እንደ ጅብ ትጮህበታለች ። ይኼኔ መቆም አይታሠብም መፈርጠጥ እንጂ ።

እንደ ሌሎቹ እብዶች መንደር ለመንደር አትንከራተትም ። ምግቧን ፍለጋ ካምፕን ትመርጣለች። የወታደር ትርፍራፊ ካልሆነ አትበላም ። ከጦር ሠራዊት ሆስፒታል በስተቀር ሁሉንም ካምፖች እንደ ልቧ እየገባች ትወጣባቸዋለች ። ሆስፒታል ያሉት ወታደሮች ወደ ግቢያቸው የማያስገቧት በሽተኞችን ትረብሻለች ብለው መሠለኝ ።

ዘርፌ ቀሽቲን ካየች አትቆምም ። ትሮጣለች ። « ታርደኛለች ። እብዷ አበቡ በሽጉጥ ትገድለኛለች...ኡ ! ኡ !» እያለች ትሸሻለች ።

አንዳንዴ ልናስፈራራት ከፈለግን የቀሽቲን ስም እንጠራባታለን ። ትበረግጋለች ። የምትገባበት ታጣለች ። እንስቃለን ።

« ዘርፌ...ቆይ ለምንድን ነው ቀሽቲን የምትፈርያት ? » አላት ጠይሜ አንድ ቀን



@BOOKALEM

ቡና እየወቀጥንላት

« እንዳትጠጓት ! ታርዳችኋለች ! እብዷ አበቡ በሽጉጥ ትገድላችኋለች ። በቢላዋ ትዘለዝላችኋለች ! በጥርሷ ትበላችኋለች !»

ስታስጠነቅቀን ፍርሃቷ ዓይኖቿ ውስጥ ይነበብ ነበር ። ወደ ቤቷ ገብታ ፣ በሯን ገርበብ አርጋ፣ አንገቷን አውጥታ ነበር የምታስጠነቅቀን ።

« አንቺ ፍሪያት እንጂ እኛ ግን አንፈራትም ። ስትመጣብሽ ለኛ ንገሪን እሺ ! በተለይ እኔ ጥርሷን ፣ ድዷን ፣ ልቧን በቦክስ መትቼ እገድልልሻለሁ እሺ !» ጠይሜ ጉልቤው ለዘርፌ መከታ ሊሆናት ቃል ገባላት ።

«ኸረ ተው ትበላሃለች ! ታርድሃለች ! ትሰድብሃለች !»

« አማርኛኮ አትችልም ።»

« ትችላለች ። »

« እርግጠኛ ነሽ ?»

« አይደለሁም ።»

« እና ?»

« ዘርፌ ነኛ !»

ሳቅንባትና ለቡና ቁርስ የቆላችውን ፈንዲሻና ሽምብራ ሠርቀናት ሄድን ። ቆሎውን እየነፋን ሳለ ዘርፌ ልትመታን ትልቅ ድንጋይ ይዛብን መጣች ። ደነገጥኩ ። ጠምቤ ድንጋይ አነሳች ።

« ቀሽቲ ! ቀሽቲ ! ዘርፌ ይችትልሽ !» አለ ጠይሜ የውሽቱን ።

ዘርፌ ወደ ኋላዋ ሮጠች ። እየተገላመጠች ስትሮጥ ወደቀች ።

***

«ሳንፊል» ይሉታል ትልቁን የራዲዮ ማሠራጫ ጣቢያ አንቴናና የሳተላይት መቀበያ ጎድጓዳ ሳህን የተሸከመ ቁመታም ብረት ። ርዝመቱ ያስፈራል ። ዘጠና ስምንት ሜትር ከፍታ እንዳለው ጋሽ ዳዲ ሲያወሩ ሠምቻለሁ ። ጋሽ ዳዲ ለፍሬው አባት ፣ ለኔ ጎረቤት ፣ ለሳንፊል ደሞ ጠባቂው ናቸው ። ከሲቪል ጠባቂዎች አንዱ ።

ሳንፊልን አቋርጠን ወደ ካባ እንሄዳለን ። ሐረር ቢራ ፋብሪካ የተሠባበሩትን ጠርሙሶቹን የሚደፋው «ካባ» ከሚባለው ቦታ ላይ ነው ። እሱ የደፋውን ስብርባሪ ጠርሙስ አጥራቸውን የገነቡ ሀብታሞች ተሻምተው ይወስዱታል ። እኛም ቆርኪ ለመልቀም ቢያንስ በሳምንት አንዴ



@BOOKALEM

ካባን እናያታለን ። የድንጋይ ፈላጭ ወጠምሻ ጎረምሶችን ኩርኩም ሠርከ ብንቀምስም ከካባ ቆርተን አናውቅም ። ድንጊስቶች ኩርኩማቸው ፀጉር ይነቅላል ። እንኳን ዱላቸው ቁጣቸው ያማል ።

ወደ ካባ ስንሄድ ቀሽቲን መጀመርያ ያያት ጠምቤ ነበር ። ሲጠቁመን ያየነውን ማመን አልቻልንም ። ትልቁ ዋርካ ላይ ወጥታ እዳሪዋን ወደ መሬት ታንጠባጥባለች ። እንዳትሠማን አፋችንን ይዘን ሳቅን ። እንዳላየችን ርግጠኞች ስንሆን ተደብቀን ልናስደነግጣት ወሠንን ። ሦስታችንም ድንጋይ አነሳን ። ጠይሜ በእጁ ምልክት እንዳንወረውርባት ከለከለን ። ዘወር ዘወር ብላ አካባቢዋን ቃኘች ። ሴትነቷን አምነን ተቀብለን የነበርን ሁሉ ተሸውደናል ። የሽንት መሽኛዋ ተንጠልጥሎ ሲወዛወዝ አየነው ። ቢድንጋጤ አፎቻችንን ያዝን ። እጇን ወደ ደረቷ ሠደደችና የሬዲዮ መገናኛ አወጣች ።

« እንዴ ?» አለ ጠይሜ

« ሠርቃ ይሆናል ይኼኔ !» ጠምቤ ግምቷን አቀረበች

« ለፖሊስ እናሲዛት !» ስል ጠይሜ የዝም በሉ ምልክት ጣቱን ከናፍሮቹ ላይ በመጫን አሳየን ።

በራዲዮ መገናኛው ማውራት ጀመረች ። በኦሮምኛ ስትናገር ድምጿ የማናውቀው ሆነብን። እንግሊዝኛ ነገር ትቀይጣለች ። እያወራች አካባቢዋን ትገለማመጣለች ። እንደ ሌባ ዓይኖቿ ብቻቸውን ይሯሯጣሉ ። የምታወራው በኦሮምኛ ቢሆንም ጠይሜ እየተረጎመ ይነግረናል ። የሚተረጉመው የእውነቱን ይሁን የውሸቱን እራሱ ብቻ ነው የሚያውቀው ። ጠይሜ ጉልቤ ስለሆነች ውሸትሽን ነው ብሎ መቃወም አይፈቀድልንም ።

« እንልከፋት !» አለ ጠይሜ

« እሺ !»

« ምን እንበላት ?» ጠምቤ ጠየቀ

« ያልሽውን ሁሉ ሰምተንሻል ! ለፖሊስ እንናገርብሻለን ነዋ !»

«አሯሩጣ ይዛ ብትገድለንስ? ቀሽቲ'ኮ ወንድ ነች። በሩጫ አናመልጣትም ።» ደንግጬ ሃሳባቸውን ተቃወምኩ ።

ለመሮጥ ተዘጋጀን ። ከተናገርናት በኋላ መቆም የለም ። ቢያንስ የሬዲዮ ማሠራጫ ጣቢያውን ከሚጠብቁት ወታደሮች ሌላ በቅርበት ሊያስጥለን የሚችል አለመኖሩን ርግጠኞች ነን ።

« ቀሽቲ ወንዱ !» ጠይሜ ተጣራ

« ያልሽውን ሰምተንሻል !» አልኳት



@BOOKALEM

«ለፖሊስ እንና...» ብሎ ጠምቤ ሃሳቡን ሳይጨርስ የራዲዮ መገናኛዋን እንደያዘች ሽጉጥ አውጥታ ከዛፉ ላይ ተገልብጣ ወረደች ።

ሮጥን ።

« እናንተ ዲቃሎች ! እናንተን ካልገደልኩ ተልዕኮዬ ይበላሻል ። እናንት የወያኔ ቡችሎች !»

«አማርኛ እንደምትችል ዘርፌ ነግራን ነበር ፣ ሽጉጡንም ፣ በቃ ትልቁ ቢላዋም አላት ማለት ነው።» የጠይሜ ንግግር የሩጫ ፍጥነታችንን አስጨመረን ።

ተከታታይ የተኩስ ድምፅ አምባረቀ ። ጠይሜ በደረቱ ወደቀ ። ጠምቤ ፊት ለፊቱ ካለ ግንድ ጋር ተላትሞ በጀርባው ተዘረረ ። የሞት መስዬ ጠይሜ አጠገብ በደረቴ ወደቅኩ ።

« ልጆች አይዟችሁ ደርሠንላችኋል!» የሚል በርከት ያለ ድምፅ ሠማን። ወታደሮች ነበሩ። አምስቱ ክላሽ ይዘዋል ። አንደኛው የርቀት መመልከቻ መነፅርና ሽጉጥ ፣ ሌላኛው የቪዲዮ ካሜራ...ቀሽቲ ተነቃባት ። «ኡበድ» መባሏ ቀረና ካቴና እንደ አጅ አምባር አጠለቁላት ። እኛንም በየወደቅንበት በቪዲዮ ቀረፁን ። የሆነውን ጠየቁን መለስንላቸው ። ቀሽቲ የኦነግ ሰላይ ፣ የኦነግ የመረጃ ክፍል ቁልፍ ሰው መሆኗ ታወቀ ። ፆታዋ ለውጥ እንዳለው ቢታወቅም «አንቺ»ነት በታሪክ ውስጥ ሁሉ መታወሻዋ ሆነ ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ምኞት

የክፍል ተጠሪ መምህራችን ጋሽ ታደሠ ይባላል ። ሲማታ ያስፈራል ። ኧረ ምን ሲማታ ብቻ ገልመጥ ሲያደርግም ያንቀጠቅጣል እንጂ ። «ብጥላት ትጣለኝ» ብሎ የማለባት ጉማሬ አለችው። በሷ መማታት ከጀመረ «ሁለተኛ አይለመደኝም !» የሚለውን መሀላችንን በለቅሷችን ታጅቦ ደጋግሞ ካልሰማ አይተወንም ። እኛም ጋሼ በማያውቀው መልኩ ለዱላዋ ስም አውጥተንላታል «አይለመደኝም !»።

ከማስተማር ይልቅ ለመማታት ፍቅሩ ከፍ ይላል ። ከልጅ ይልቅ «አይለመደኝም»ን ማቀፍ ይቀለዋል ። የተመረቀው በመማታት እንጂ በማስተማር አይመስልም ። ጠየም በሚለው ገፁ ላይ «አይለመደኝም» ስትጋደምበት አባብ በትከሻው የተሸከመ ይመስላል ። የጋሼ አባብ ግን «አይለመደኝም» ነች ።

ጋሼ ፀባዩ እንጂ መልኩ ያምራል ። የፀጉሩ ሉጫነት ያስቀናል ። ወደ ኋላ ልጎ አስተኝቶት ወደ ክፍላችን ሲገባ ሁላችንም በቅናት ፀጉራችንን እንደባብሳለን ። በሀበሻ የራስ ቅል ላይ የህንድ ፀጉር የተሸከመ ብቸኛው ሰው ጋሽ ታዴ ። ሲያስተምርም ደስ ይላል ። እንግሊዝኛውን ሲያንጸረጽረው ይገርማል ። አንዳንዴ አንድም አማርኛ ሳይቀላቅል በእንግሊዝኛ ብቻ ሲያወራ ግራ ያጋባናል ። የሀበሻ ልጆችን ሰብስቦ እንደሚያስተምር አልገባውም ። ወይም ጋሼ ሀበሻነታችንን ረስቶታል ። አውርቶ አውርቶ ሲጨርስ እንደገባንና እንዳልገባን ለማረጋገጥ

« Is it clear ?» ይለናል ።

« Yes !» እንመልሳለን ። በቃ በኛ ቤት እንግሊዝኛ ጨቅ ነን ።

«ሙሉ መልስ ስጡኝ ። ደደብ ሁላ! Yes , it is . በሉ !» ይጮህብናል ።

« Yes , is is .»

ይናደዳል ።

« Is is ያርጋችሁ እሺ ያባቴ አምላክ ! Yes , it is. በሉ ! » ይልና አይለመደኝምን ያወዛውዛታል። «Yes , it is !» ሁላችንም በትክክል እንልለታለን ።

ሲያድግ ጋሼን ለመሆን የማይመኝ ተማሪ አይገኝም ። እንግሊዝኛን እንደ ጋሼ ለማንደቅደቅ የማይቋምጥ የለም ። ጋሼ በርግጠኝነት ሁለት የማይኮረጁ ነገሮች አሉት ። ደርቀው የጠቆሩት ከናፍሮቹና አስጠሊታ ትንፋሹ ።



@BOOKALEM

ጥሉበት አይወደኝም ። የማይወደኝ ደሞ በእህቴ በመሳይ የተነሳ ነው ። አንድ ቀን ወላጅ እንዳመጣ አዘዘኝ ። መሳይ ወላጅ ሆና መጣችልኝ ። ሲያያት ደነገጠ ። ተማሪዎቹ እሱን ስናይ እንደምንንቀጠቀጠው መሳይን ሲያያት ተንቀጠቀጠ ። እኛ ላይ የሚያጠቁረውን ፊቱን ለመሲ በፈገግታ ሞላላት ። ጥፋት ያለውን ነገራት ። ለነገሩ እሱ ጥፋት መሠለው እንጂ ወላጅ እንዳመጣ ያዘዘኝ ትበልጪን ጡትሽን አሳዪኝ ብያት ስታሳየኝ ነበር ። ቆይ እስቲ አዲስ የበቀለን ጡት ማየት ጥፋት ይባላል በናታችሁ ? ደሞኮ...ጠይሜ የሔለንን በጉልቤ እንዳየባት አላየሁባትም ፤ እንደነካባት አልነካካሁባትም ።

« አሳዪኝ » ብዬ ጠየቅኋት ። ወድዳ ፤ ፈቅዳ ፤ ደስ ብሏት እጄን እየጎተተች ሽንት ቤት ወሠደችኝ ። ደረቷ ላይ የበቀሉትን ሁለት ትንንሽ ጡቶች በዓይኔ እያየሁ ስገረም እንድነካካቸው ፈቀደችልኝ ። ስነካካቸው « አታሳምመኝ ፤ ቀስ ቀስ እያልክ ነካካቸው ። በቀስታ ሲነኩ ደስ ይለኛል። እከከ እከክ አድርጋቸው !» አለችኝ ። ትዕዛዝ ነው ነካካሁላት ። አከከኩላት ። « እሠይ ! እሠይ !» አለች ደስ ብሏት ። ጋሼ ከየት እንደመጣ ሳናውቅ በጉማሬው ጠበጠበን ። ቆይ እኔ ምን አጠፋሁ ? እኔ ልያቸው እንጂ ልንካቸው አላልኳት ። ጋሼ ግን ይቺን ጥፋት ብሎ ወላጅ አስጠራኝ። ትበልጪ ግን « ወላጅ ፌስታል መሠለው እንዴ !» ብላ የጋሼን ትዕዛዝ ሳትፈፅም ቀረች ።

ጋሼ እኔና መሳይን ወደ ቢሮ ይዞን ገባ ። ስለኔ ማውራቱን ትቶ ስሟንና የት እንደምትማር ጠየቃት ።

« አንቺ ቆንጆ ነሽ! የዚህ የጭንቅሎ እህትማ ልትሆኚ አይገባሽም !» አላት ።

ንግግሩ አናደደኝ ። እሱቲ ምን አገባው ? እሱ እግዛቤር አይደል ! የሷ ወንድም ከመሆን የሚከለክለኝ ።

« እንዴት ! ጭንቅሎ ቆንጆ አይደለም እንዴ ?» አለችው ፀጉሬን እየደባበሠች ።

«ኧረ ! ቆንጆ ነው...ሆ ! ወንዱ ሞናሊዛ ። ታቦት የተሸከመ ሚጢጢ ቄስ አይደል እንዴ የሚመስለው ። እኔ'ኮ አንዳንዴ ትኩር ብዬ ሳየው ይገርመኛል ። »

መሳይ ዝም አለችው ። ስትዘጋው ደስ አለኝ ።

« ምን ያስገርምሃል አትይኝም እንዴ ቆንጂት !» አላት

ሳቅ አለችለት ።

« አንቺ ብትጠይቂኝም ባትጠይቂኝም እኔ ግን የሚያስገርመኝን ነገር ሳልደብቅ እነግርሻለሁ ።»

ቀና ብላ አየችው ። አንገቱን ቅብር አደረገ ።

« ሁልጊዜ ጭንቅሎን ሳየው ታቦት የተሸከመ ይመስለኛል ። እናም... ይኼን ልጅ እግዚአብሔር ታቦት ካሸከመው ጭንቅላቱን የት አደረገው ? ጭንቅላት ብሎ ከሆነ ደሞ ይኼን የሠራለት ለምን



@BOOKALEM

የሰው ጭንቅላት ቅርፅ ነሳው ? አላለሁ ። እንዴ ግንባሩ እንደ ኮፍያ ከመሸሉ የተነሳ ዝናብና ፀሐይ ዓይንና አፍንጫው ላይ አያርፉም። በተፈጥሮ ኀንጥላ የተገጠመለት ዕድለኛ ልጅ !»

መሳይ ተንከትከታ ሳቀችለት ። አናደደችኝ ። አፍንጫዬን ነፍቼ ቆምኩ ።

« ግን ማነው ጭንቅሎ ብሎ ስም ያወጣለት ?»

« አባታችን ነው ። »

« አድናቂያቸው ነኝ...» አለና ወደ ክፍሌ እንድገባ አዘዘኝ ።

መሳይ ጉንጩን ሳመችና ሸኘችኝ ። እኔ ግን ወደ ክፍሌ የምሄድ አስመስዬ ምን እንደሚላት ለማዳመጥ ወደ ጋሼ ቢሮ ጓሮ ዞሬ መስኮቱ ሥር ተለጠፍኩ ። ጓሮው በትላልቅ የሠንበሌጥ ሳር ተውጧል ። ተመቸኝ ። ወሬያቸው በደንብ ይሠማኛል ። ሳይነቁብኝ ወሬያቸውን ልቅም ።

ጋሼ ከትበልጪ ጋር ያደረግነውን ለመሳይ ነገራት ። አፏን ያዘች ።

« ሌላ ነገር አርገዋል ?» አለችው

« አላየሁም...ጡቷን ሲደባብስና ልጅቷ ስሜት ውስጥ ገብታ ስታለከልክ ነው የደረስኩባቸው ።»

« ጂሰስ ! ልጅቷ ማንን ታክላለች ?»

« እኩያው ናት ።»

«አንድ ክፍል ናቸው ?»

« አዎ !»

መሳይ ተከዘች ።

« አይዞሽ ! ቀለል አርገሽ አስቢው ።»

« እንዴት ነው ይህን ያክል ከባድ ነገር አቅልዬ የማስበው መምህር ? ገና አስራ ሁለት አመት እንኳን አልሞላውም እኮ !»

ግራ ገባኝ ። ምን ወንጀል ሠራሁ ? ምን አጠፋሁ ? ጡቷን ነካካሁ እንጂ አልፈነከትኳት፣ አልቧጨርኳት ፣ አልነከስኳት ፣ አላደማኋት ፣ ጡቷ ውስጥ ያለውን ወተት አልጠባሁባት...እንዴ ምን አደረግኩ ?»

« ማን ነበር ስምሽን ያልሽኝ ?» አላት ጋሼ የመሳይን ቀኝ እጅ በሁለት እጆቹ ይዞ ኢያሻሸ ።

« መሳይ !»

«ስምሽ ያምራል። ግን...ማንን መስለሽ ነው ይህን የሚያክል ስም ለብቻሽ የሰጡሽ ?»



@BOOKALEM

« አራሴን !»

« በጣም አሪፍ ። ለማንኛውም በደንብ ብንተዋወቅ ደስ ይለኛል ። ታደሠ ወዳጆ እባላለሁ ። ታዴ ልትይኝ ትችያለሽ ።»

እጇን ጨመቅ ሲያደርጋት አየሁት ። በአይለመደኝም ሊያቀምሳት መስሎኝ ፈራሁ ። ብዙ ጊዜ ሊግታ ሲል የሚያመልጠው መስሎ የታየውን ሰው እጁን ጨምቆ ይዞ ነው የሚለጠልጠው ።

« የጠዋት ወይስ የከሰዓት ?» እጇን ሳይለቅ ጠየቃት

የጠዋት ፈረቃ ተማሪ መሆኗን ነገረችው ።

« አንዳንዴ እየተገናኘን ብንጨዋወት ምን ይመስልሻል ?»

« ችግር የለውም ።» ትከሻዋን ሰበቅ ፣ የዓይኖቿን ቆቦች በልጠጥ አደረገችለት ።

« አመሠግናለሁ ! ስልክ ብትሠጪኝ !»

እኛ ቤት ስልክ የለም ። ዘመዶቻችን ሲደውሉልን የምናወራው በነ አባባ ዘነበ ስልክ ነው ። ያውም እቤታቸው እንዳንገባና ምንጣፋቸውን ረግጠን እንዳናቆሽሽባቸው በበረንዳው በኩል በመስኮት መነጋገርያውን እያቀበሉን ።

« እንደሱ ዓይነት አማራጭ እንኳን የለኝም ።» አለችው

« ማለት ?»

« ስልክ የለኝም ።»

« እና እንዴት ላገኝሽ ታድያ ?»

« መልዕክት ሲኖርህ በጭንቅሎ ላከብኝ ።»

« እንዴት አድርጌ ?»

« ወረቀት ፃፍና ስጠው ።»

« ለቤተሰብ ቢሠጥስ ? ልጁ እኮ ገና አልበሠለም ባባትሽ ። የኔና ያንቺን ግንኙነት ደሞ ከኔና ካንቺ ውጪ ማንም ባያውቀው ደስ ይለኛል ።»

« ቀላል እኮ ነው ። ፅፈህ ደብተሩ ውስጥ ከተተው እኔ አወጣዋለሁ ።»

«እሺ! እንደዚህ እናርግ...የእንግሊዝኛ ደብተሩ ውስጥ አስቀምጥልሻለሁ ። ሽፋኑን እየገለጥሽ አውጪ ።»



@BOOKALEM

ተስማሙ ። ጉንጯን ስሞ ሸኛት ።

ይህንን የጋሼንና የመሳይን ምስጢር ለጠይሜና ጠምቤ ነገርኳቸው ። ጋሼም ሁሌ የኔን ደብተር እየተዋሠ ወደ ቢሮ ይዞ ይኼድና አድንቆ ፣ ጎበዝ መሆኔን ገልጾ ይመልስልኛል ። የከፍላችን ልጆች ምንም አልባነኑም ። እኔ ፣ ጠይሜና ጠምቤ ግን ጋሼ ለመሳይ የሚፅፈውን ደብዳቤ እያወጣን እናነብና መልሠን እዛው እናስቀምጥላታለን ።

መሳይም « እስቲ ዛሬ ምን ተማርክ ?» እያለች ሁሌ የእንግሊዝኛ ደብተሬን ብቻ ትገልጣለች። ከዚያ ወረቀቱን ማውጣት ሳይመቻት ሲቀር ወደ ጓዳ ትልከኛለች ። ውሃ አምጣ ፣ ብርጭቆ አቀብለኝ ፣ ማማሳያውን ፈልግልኝ ፣ ሳሙና ሥጠኝ...ነፍ የማያስፈልጉ ሠበቦችን ትደረድራለች። ጓዳ ገብቼ በመጋረጃው ቀዳዳ ስመለከታት የደብተሬን ሽፋን ገልጣ የጋሼን ደብዳቤ አውጥታ ኪሷ ትከታለች ። ወረቀቱን ኪሷ ከከተተች በኋላ ያዘዘችኝን መልዕክት እንድተወው ትነግረኛለች። አልናደድም ። በሷ ቤት እኔን መሸወዷ'ኮ ነው - የድሮ ብልጥ ።

«... መሲ የኔ ቆንጆ ! ትላንትና የሳምኩት ከንፈርሽ መዐዛ ዛሬም ከከናፍሮቼ ላይ ታትሞ ተቀምጦልሻል ። መቼ ይሆን የምትደግሚው ?...»

«...መሲ የኔ ማር እወድሻለሁ ! ባይገርምሽ እንደ ትላንትና ዓይነት የሚገርም ቀን ገጥሞኝ አያውቅም ። የውስጥ ሱሪዎቻችንን መለዋወጣችንን ያወቅኩት አንቺን ሸኝቼ ከተመለስኩ በኋላ ገላዬን ስታጠብ ነበር ።...»

«...መሲ የኔ ውብ ከረሜላ ! ' ሳላረግዝ አልቀረሁምና ለመመርመርያ የሚሆን ገንዘብ ፈልግልኝ' ብለሽኝ ነበር ። እባክሽ እኔ ፈልጌ ማግኘት አልቻልኩም ። ወር ላይ ደመወዝ ሲደርስ እሠጥሻለሁ ። ብድር ፈላልጊና ተመርመሪ ። ፀንሰሽ ከሆነም መላ በይው ።...»

«...የኔ ፍቅር ! ጭንቅሎ የኔና ያንቺን ግንኙነት ያውቃል እንዴ ? ከፍል ውስጥ ስገባ እስተያየቱ ደስ አላለኝም ። የሆነ የነቃው ወይም ያነቃው ነገር ሳይኖር አይቀርም ። እንደ ድሮው አይፈራኝም ። ሲያየኝ ይኮሳተርብኛል ። ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ ይጠቋቆምብኛል ። በናትሽ እውነቱን ካንቺ ልስማው ። ...»

እነኚህ ሁላ እየሠረቅን ያነበብናቸው የጋሼ መልዕክቶች ናቸው ። እረሳኋቸው እንጂ ብዙ መልዕክቶችን ሠርቀን አንብበናል ። ታድያ መሳይ በጣም ታማ ደም እየሸናች አልጋችን ሲበላሽ ፣ መናገር አቅቷት ለመሞት ስታጣጥር ሕመሟን ጋሼ ሊያውቅ ሥለሚችል እንዲጠይቀው አባቴን ለመንኩት ።

አባቴ ደሞ ፍትር አድርጎ ያዘኝ ። እኔ ብቻ ሳልሆን እነ ጠይሜም ምስጢሩን እንደሚያውቁና የደብዳቢዎቹን ይዘት ዘከዘከኩለት ። እስኪነጋ ድረስ አባቴ ቁና ቁና ሲተነፍስ አደረ ። መሳይን እውነቱን ብቻ እንድትነግረው ሲጠይቃት ሽምጥጥ አድርጋ ካደችው ።

ጠዋት እኔን ይዞ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ ። ጋሼን ጠራውና በጣም ፈልጎት እንደመጣ ነገረው ።



@BOOKALEM

«እኔም መቼ አግኝቼ ባወራሁዎት ስል ነበር ። እንኳን ደህና መጡ ! ይቀመጡ !» አለው አባቴን ወንበሩን እየጠቆመው ።

« የመጣሁት በደህናም ልቀመጥም አይደለም ።»

« ትክክል...ደህና ላይሆኑ ይችላሉ ። ጭንቅሎ እያለ ምኑን ደህና ይሆናሉ ። እዚህም እያስቸገረን ነው ። በርግጥ አሁን አሁን እንኳን እየተስተካከለ ይመስለኛል ። አይደል ጭንቅሎ ?»

« መምህር...የመጣሁት ስለ ጭንቅሎ ልጠይቅህ አይደለም ።»

« እና ታድያ...እሺ ምን ልታዘዝ ?»

« ስለ ልጄ...ስለ ሴቷ ልጄ...ስላበላሸህብኝ ስለ መሳይ ጉዳይ ምንም ሳትደብቅ በግልፅ እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ ።»

« መሳይ ማን ናት ?» ጋሼ ዋሸ ።

«መሳይን አላውቃትም ሲል ነው እንዴ? አስተማሪም ይዋሻል ማለት ነው ?» አልኩ በልቤ ።

« መምህር አሁን መወሻሸቱ ምንም አይጠቅመንም ። አስራ ስምንት አመት ያልሞላትን ልጄን ከብሯን ገፍፈህ አስረግዘህ ስታበቃ ፅንሱን አስወርጃው አልካት አይደል ?»

« ኧረ ! እባክዎት እርስዎ ሰውዬ ስለ እግዚአብሔር ይሁንብዎት ! ስለምን እንደሚያወሩ ይወቁ እንጂ ። እኔ ከርስዎ ልጆች የማውቀው ገና በዚህ ዕድሜው ሴት ማማገጥ የጀመረውን ጭንቅሎን ነው ።»

ማማገጥ ምንድን ነው ? ግራ ገባኝ ። መግመጥ ማለት እንዳልሆነ ግን ተረድቼዋለሁ ። ምክንያቱም ሴት ዳቦ አይደለች የምትገመጥ ።

« ወዬት ! ወዬት ! ... ለመሆኑ ያልከውን ታውቀዋለህ አንተ ራስህ ? ራስህ ይውለቅና ።» አባቴ በንዴት ብው ብሏል ።

« እኔ እንኳን መጡ ያልኩዎት ልጅዎ በዚህ ዕድሜው ሽንት ቤት ውስጥ ዕኩያው የሆነች ተማሪን አስገድዶ ሊድፍር ሲል ተይዞ ...»

« ዝም በል ወሸካታ ! እንዳንተ ዓይነት ቀጣፊ ልጄን የማስተማር የሞራል ብቃት የለውም ።»

« እውነቱን ነው የምልዎት ። እርስዎ የሚሏትን ልጅ እኔ አላውቃትም ። ይመኑኝ የጭንቅሎ አባት !»

ጋሼ ድጋሚ ሽምጥጥ አድርጎ ሲከድ ገረመኝ ። ለሌላ ጊዜ መዋሸት ምንም ችግር እንደሌለው ተረዳሁ ። ጋሼን ግን ታዘብኩት ። አንድ ቀን እኔና ጠምቤንኮ ለምን ውሸት ተናገራችሁ ብሎ ቀጥቅጦን ያውቃል ።



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

« አታውቃትም ?» አለው አባቴ ጋሼ ላይ አፍጥጦበት ።

« ጌታ ምስክሬ ነው...አላውቃትም !»

« አቤት ውሸት !» አልኩት ጭንቅላቴን ይገና ።

ያባቴ በርበሬ የሆነች ጥፊ ንግግሬን ተከትላ ፊቴ ላይ አረፈች ። አባቴ ጋሼን ፈርቶ እኔን መታኝ ። የጋሼን እልህ እኔ ላይ ተወጣብኝ ። አስተማሪ ቢዋሽም ዋሸተሃል እንደማይባል በዱላ ገባኝ ። አባቴም በሕግ እንደሚጠይቀው ዝቶበት እኔን ይዞኝ ሊወጣ ሲል በሩ ላይ ኘው ብሎ በደረቱ ወደቀ ። የደም ግፊት በሽታው ተነሳበት ። እሪ አልኩ ። በቀይ መስቀል አምቡላንስ ጋሼና የቀይ መስቀል ወጣቶች አባቴን በቅርበት ወደሚገኘው የጦር ሠራዊት ሆስፒታል ወሠዱት ። አጋጣሚዋን ተጠቅሞ ጋሼ ከሐኪሞች ጋር ተባብሮ አዳነውና ከአባቴ ታረቀ ። እኔን ግን ለዓይኑ ጠላኝ ።

ጋሼ ሲያስተምር ደስ ይለኛል ። በትምህርቱ መሀል የሚፈጥራቸው ቀልዶች ይመቹኛል ። ጥያቄ ይጠይቀንና መልስ ስንሠጠው በመልሳችን ተንተርሶ ቀልድ ፈጥሮ ያስቅብናል ።

አንድ ቀን በእንግሊዝኛ « What do you want to be when you get older ?» ( ስታድጉ ምን መሆን ትፈልጋላችሁ ?) የሚል ርዕስ ይዞ መጣ ። የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ከመጀመሩ በፊት መዝሙር አስዘመረን ። ከዚያ ርዕሱን በቀይ ጠመኔ ጥቁር ሠሌዳው ላይ ፃፈና ተራ በተራ እያስነሳ መጠየቅ ጀመረ ። ማንም ሰው በእንግሊዝኛ አልመልስ ሲለው ጥያቄውን በአማርኛ አደረገው ። ማለት እንግሊዝኛ በአማርኛ ተማርን ።

« ጭንቅሎ ተነስ !» አለኝ

ተነሳሁ ።

« ወደ ፊት ስታድግ ምን መሆን ነው የምትፈልገው ?»

« ምንም !»

ጋሼ ደነገጠ ። ተማሪዎቹ ሳቁ ።

« ጥያቄዬን ሰምተኸኛል ጭንቅሎ ? ተምረህ ትልቅ ልጅ ስትሆን ምን መሆን ትፈልጋለህ ነው ያልኩህ ። አሁንስ ገባህ ?» ጥያቄውን አብራራልኝ ።

« አዎ !»

« እሺ ! ስታድግ ምን መሆን እንደምትፈልግ ንገረና !»

« ምንም ! »

«ሂድ አንተ ! ቤተሰብ ነው ፈጣሪ ይኼን የሚያክል ጭንቅላት ያለምንም ባዶውን የሜነልህ?



@BOOKALEM

ምንም ይለኛል እንዴ ! ለመሆኑ ጭንቅላትህ ውስጥ ምንድን ነው ያለው ?» አፈጠጠብኝ ።

« ምንም !»

ጋሼ ተንከትክቶ ሳቀብኝ ። ተማሪዎቹም ሳቁን በሳቃቸው አገዙት ። ስቆ ሲጨርስ « እውነትክን ነው ! ውስጡ ምናምን ቢኖረው መች እንደዚያ ጉድ ትሠራኝ ነበር !» አለ ።

ጠምቤ ጋሼ እንደዚህ ያለኝ ከመሳይ ጋር የነበረውን ግንኙነት ለአባቴ ስለነገርኩበት ተበሳጭቶ መሆኑን በሹክሹክታ ነገረኝ ።

ጋሼ አንዳንዴ የሕንድ ፊልም ላይ እንዳሉት ሙጅሪሞች ያደርገዋል ። በሆነ ነገር ከትከት ብሎ ይስቅና አብረነው መሳቅ ስንጀምር ድንገት ፀጥ ፣ ኩስተር ይላል ። እሱ ከተኮሳተረ በኋላ የሳቀ አለቀለት ። « ምን አባክ ያስገለፍጥሃል ... ድዳም አህያ !» የሚል ሰድብ ይከተለዋል ።

ሁለተኛዋ ምኞቷን ተጠያቂ ደሞ ሞኛ ሞኟ ጫልቱ ነበረች ።

« ጫልቱ ! አንቺስ ስታድጊ ምን መሆን ነው የምትፈልጊው ?» ሲል ጠየቃት ።

« እኔ ሳድግ መሆን የምፈልገው ?»

« አዎ !»

« እኔ ሳድግ መሆን የምፈልገው የጎዴ ሆቴል ሸሌ ነው ።»

ጋሼ ደነገጠ ። እኛ ሳቅን ።

« ለምን ጫልቱ ?» አላት ዓይኖቹን አጥብቦ

« ሁል ጊዜ ስጋ እንድበላ ነዋ !»

« የጎዴ ሆቴል እንትኖች ሁሌ ስጋ ነው እንዴ የሚበሉት ?»

« አዎና !»

« የት አየሻቸው ?»

« ጎዴ ሆቴል እኮ እነሱ ሠፈር ነው ።» አለ እንዳልካቸው

« እና ልጆች...ይኼ አሁን ጥሩ ምኞት ነው ባባታችሁ ?» ጋሼ ከመቼውም በላይ ትህትናው ጨምሯል ።

« በይ ጫልቱ ነገ ወላጅ እንድታመጪ !»

« እንዴ ! ምን አጠፋሁ ጋሼ ?» እንባ አቀረረች ።



@BOOKALEM

« ምንም አላጠፋሽም ። ቤተሰቦችሽ ሁልጊዜ ስጋ እንዲሠሩልሽ ልነግርልሽ ነው ። አንቺ ዝም ብለሽ ኑ ተብላችኋል ብቻ በያቸው እሺ !»

« እሺ ! ናሆም ተነስ እስቲ !»

ናሆም ቀልድ መፍጠር የራሱ ነው ። ከጋሼ የባሰ ቀልደኛ ፍጥረት ።

« እሺ ! አንተስ ስታድግ ምን መሆን ነው የምትፈልገው ?»

« ኢ...እኔ እንኳን ሳድግ መሆን የምፈልገው አንትን ነው ።»

« ምን ?» ሁላችንም የናሆምን ምኞት ለመስማት ጓጉተን ጠየቅነው ።

« ሀማል...ማለቴ ወዛደር መሆን ነው የምፈልገው ።»

ሁላችንም ስንስቅ ጋሼ ፀጥ አለ ።

« ምን መሆን አልክ ናሆም ?»

« ኢ... ወዛደር !»

ሳቅን ። ጋሼ አረረ ። «ዳስተር» ወርውሮ ሳተው ። ናሆምን የሳተው ዳስተር ግድግዳውን ጫረው ።

« ይህን ያክል የምለፋው ወዛደር ለማፍራት ነው እንዴ ?»

« አይደለም ጋሼ ! እኔኮ በቀደም አውቶቡስ ተራ ሂጄ ያየሁት ነገር አስገርሞኝ ነው ወዛደር መሆን የፈለግኩት ።»

« ምን አይተህ ምን አስገረመህ ?»

« የሆነ ፈረንጅ ሻንጣውን ተሸክመው ካመጡት ወዛደሮች ጋር በሒሳብ ሲጣላ አየሁት። ሁለቱም ወገኖች በቋንቋ አልተግባቡም ። ወዛደሮቹ እንግሊዝኛ ቢያውቁ አይጣሉም ብዬ አሰብኩ ። ደሞኮ 'ዴች ዴች' ጠብቀው 'ካሩ ካሩ' ብቻ ነበር የሠጣቸው ።»

«ዴች ፤ ካሩ ምንድን ናቸው ?»

«ዴችማ አስር ብር ነዋ !»

«ካሩስ ምንድን ነው ?»

« አይ ! ጋሼ ያራዳ ቋንቋ አትችይም እንዴ ? ብር ብር ነዋ !»

ከጋሼ ጋር አብረን ሳቅን ።



@BOOKALEM

« ሃሳብህ መልካም ነበር ናሆሜ ። ግን ቢያንስ ለምን አንተ እንግሊዝኛ ተምረህ ወዛደር ከምትሆን እሱን አማርኛ አስተምረህ ወዛደር አታደርገውም ? ሀገራቸውም ሄደን ሀገራችንም መጥተው የነሱ አሽከር ሆነን መኖር ቢያንስ በናንተ ትውልድ እንኳን አይበቃም ልጆች ? ወይኔ ታደሠ ወንዱ !» ጋሼ ተከዝ አለ ።

ትብልጪ ለጋሼ እንዳዘነችለት ያስታውቃል ። ትከዝ ብላለች ። መጀመርያ ጋሼ እኔን ሲሠድበኝና ተማሪ ሁሉ ሲስቅብኝ እሷና እኔ ብቻ ነን በኔ ላይ ያልሳቅነው ።

« ትብልጪ ! ተነሽ እስቲ ያንቺንም ዕቅድ  ልስማው ።»

ተነሳች ። ለመናገር ጉሮሮዋን ጠረግረግ አደረገች ።

« በያ ንገሪን !»

« ምኑን ?»

« ስታድጊ መሆን የምትፈልጊውን ።»

«እ ... እኔ እንኳን ሳድግ መሆን የምፈልገው ...»

«ቆይ ቆይ! ከዚያ በፊት የምጠይቅሽን መልሺልኝ። የየት ሠፈር ልጅ ነሽ?»

« የቀላድ አምባ !»

« እ...እነ ጋሽ ጭንቅሎ ሠፈር ?»

ተማሪዎቹ የጋሼን ፌዝ ተከትለው ሳቁብኝ ።

« ጎረቤት እኮ ናቸው ።» አለ እንዳልካቸው

ጋሼ እንዳልካቸውን በኩርኩም አነደደው ። ከዚህ በፊትም ሳይጠየቅ እንዳያወራ ተነግሮት ነበር ። እሱ ግን ይንቀዠቀዣል ።

«ትብልጪ ! ቤተሰቦችሽ ሥራቸው ምንድን ነው ?»

«አባቴ ትምህርት ቢሮ ነው የሚሠራው ። እናቴ ሐኪም ናት ።»

« አሃ ! የምሁር ልጅ ነሻ ?»

« እንከት !» አለችው ።

ሳቅንባት ። አፈረች ።

«ለመሆኑ ወደ ፊት ስታድጊ ምን መሆን ነው የምትፈልጊው ?»



@BOOKALEM

« ዶክተር !»

« አጨብጭቡላት !» አለን

አጨበጨብንላት ። እጃችን እስኪቃጠል ብናጨበጭብም አልረካም ። ቆመን እንድናጨበጭብ አዘዘን ። ብዙ አሞጋገሳት ፣ ካባት ። ፊቱ በደማቅ ፈገግታ ተሞላ ። አርዓያችን መሆን የምትችለው እሷ ብቻ መሆኗን አከክ እስኪለን ደጋግሞ ነገረን ።

« ትበልጢ !»

« አቤት ጋሼ !»

« ለመሆኑ የምን ዶክተር ነው መሆን የምትፈልጊው ? ማለቴ እ...ለምሳሌ የሕፃናት ዶክተር ፣ የልብ ፣ የዓይን ፣ የጥርስ ዶክተር አለ ። አንቺ የየትኛውን ነው መሆን የምትፈልጊው ?»

« የከብር !»

ጋሼ ብቻውን ሳቀ ። እኛ «የከብር» የሚለው አገላለጿ ትርጉሙ ስላልገባን የውሸታችንን ድዳችንን ብቻ አዋስነው ።

« እውነትም የምሁር ልጅ ! ቁጭ በይ ወደዛ !» ተቆጣት ። ጋሼና ዶክተር ትበልጢ ተጣሉ ።

ትበልጢ አኮረፈች ። ልጆቹ ሳቁባት ። እኔ ትበልጢን ተከትዬ አኮረፍኩ ። ብዙዎቹ እየተነሱ « ዶክተር ፣ ነርስ ፣ ኢንጂነር ...» መሆን እንፈልጋለን አሉት ።

ቀጥላ የተጠየቀችው ቤቲ ነበረች ። ቤቲ ምን መሆን እንደምትፈልግ ለማስማት ሁላችንም ጓጉተናል ።

« እሺ ተረፒት...አንቺስ ምን መሆን ነው የምትፈልጊው ?» አላት ጋሼ በተሸነፈ ድምፅ ።

« በሽተኛ !»

« ምን ?»

ቤቲ ሳቋን ለቀቀችው ። ተከትለናት ሳቅን ። ጋሼ አይለመደኝምን ፈለጋት ። የለችም ። እንዳልካቸው በመስኮት ወርውሯታል ።

« ምን መሆን ነው የምፈልገው አልሽኝ ቤቲዬ ?» አለ ጋሼ ሳያስነቃ አይለመደኝምን በዓይኖቹ እየፈለጋት ።

« በሽተኛ !»

« ምን ዓይነት በሽተኛ ?» ጋሼ ጠየቃት



@BOOKALEM

« የቀብር !» እንዳልካቸው አሁንም ሳይጠየቅና ሳይፈቀድለት ተናገረ ።

ጋሼ ጨሠ ። እንዳልካቸውን ከዴስኩ ጋር አጋጨው ። የሚሆነውን አጣው ። እጁን ወደ ኪሱ ሠደደና ሲጋራና ከብሪት አወጣ ። ፊት ለፊታችን ቆሞ ለኮሠው ። ከከንፈሩ ሳይነቅል አቡለቀለቀው ። ገዋኑን አውልቆ ወደ መሬት ወረወረው ። ወደ መስኮቱ ተጠግቶ አሻግሮ ወደ ውጭ ተመለከተ ። አይለመደኝምን ተመለከታት ። መስኮቱን ከፍቶ ዘለለ ። ለዝላዩ ጮህንለት ። አይለመደኝምን ከወደቀችበት አነሳት ።

አየሮጠ ሊቀጠቅጠን ሲመጣ መስኮቱን ቀረቀርንበት ። በሩንም ዘጋንበት ። ከውስጥ ሆነን ሁላችንም በአንድ ድምፅ እሪ ብለን ጮህን ።

« ልጆች !» ጋሼ ደንግጦ በሩን እንድንከፍትለት እየደበደበ ይጣራል ።

« አቤት !» በአንድ ድምፅ

« አባካችሁ ልጆችዬ ክፈቱልኝና የኔንም የወደፊት ምኞት ልንገራችሁ ።»

« እንከፍትልሀም ! ልትመታን ነው ። ደሞ አንተ ት...ልቅ ስለሆንክ የወደፊት ዕቅድ አይኖርህም !» መለስንለት በእንዳልካቸው መሪነት ።

« እመኑኝ ! ጫፋችሁን አልነካችሁም ።»

አምነን ከፈትንለት ። ሁላችንም በፀጥታ በየመቀመጫችን ሳንታዘዝ እጅ በደረት አጣምረን ተቀመጥን ። ጋሼም ጠረጴዛው ላይ ተደፍቶ አለቀሠ ። ተንሠቀሠቀ ። አሳዘነን ። አብረን አላቀስነው ።

ጋሼ በኛ የወደፊት ተስፋ ቢስ ምኞት እኛ በሱ ለቅሶ አለቀስን ። « የጋሼ የወደፊት ምኞት ማልቀስ ነው !» አለኝ እንዳልካቸው ወደ ጆሮዬ ቀርቦ ። አልሳቅኩለትም ። በጋሼ ለቅሶ ሰቁ በኔ ደስታ እንዳላለቅስ ፈራሁ ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ አስር

## ፈረንሳይ ካራቴ

ቪዲዮ የምናይባቸውን ቤቶች ከጥቅም አንፃር እንመርጣቸዋለን ። የሁሉም ቪዲዮ ቤቶች የመግቢያ ዋጋ ይቀራረባል ። ሁለት የአሜሪካና አንድ የሕንድ ፊልም በሽልንግ ጥግብ እስክንል እናያለን ። በርግጥ አንዳንድ ገና ገበያ ያልተላመደላቸው ቤቶች አንድ ፊልም በዲናሬ ያሳዩናል ።

የደራ ገበያ ካላቸው ቪዲዮ ቤቶች የነ መዐዛን ቤት የሚያክል ባለ ትልቅ ገቢ ቪዲዮ ቤት የለም ። ሁሌም ቤቱ በተመልካች ይሞላል ። የመዐዛ ቤተሰቦች ለነ ጠይሜ አበልጆች ናቸው ። የጠይሜ ክርስትና አባት ለመዓዛ ወላጅ አባት መሆናቸውን እናውቃለን ።

ቤታቸው ወደ ጎን መደዳውን ቀጥ ተደርጎ የተሠራ ባለ አራት ክፍል ነው ። አጥር የለውም። የመጀመርያዋ የቤቱ ጫፍ ቁናሳም ሽንት ቤትን የተጎራበተች ሱቅ ናት ። ቀጥሎ ያለው የመዐዛ እናትና አባት ድካም ማቃለያና ዘር መፍጠርያ አልጋ ተዘርግቶበታል ። የተወሠኑ ጠረጴዛና ወንበሮችም አሉበት ። ሦስትና አራተኛው ክፍሎች ግን ቪዲዮ ቤቶች ናቸው ። በርግጥ ሦስተኛው ክፍል ውስጥ ቀለሙ የተፋፋቀ አሮጌ ቁም ሳጥንና የመዐዛና ወንድሟ መኝታ እንደተነጠፈ ይውልበታል ። አራተኛው ደሞ በጆንያ የተሞላ ያልተፈለፈለ ለውዝና በበርሜል የተሞላ አረቄ ይቆለልበታል።

አብዛኛው ቪዲዮ ለመመልከት የሚገባ ልጅ አራተኛው ክፍል ውስጥ ከተነጠፈው ሠሌን ላይ መቀመጥ ይጠበቅበታል ። ሦስተኛው ክፍል አረቄ እየጠጡ በሥበቡ ቪዲዮ ለሚያዩ ብቻ የተፈቀደ ነው ። በተለይ የከሰዓት በኋላው ፊልም ሲታይ መከራው ይበዛል ። ፊልሙ እስኪጀምር የተከፈተው በርና መስኮት ይዘጋጋል ። ብርሃን አይታሰብም ። የተመልካች ቁጥር ገደብ ስለሌለው ተጠቅጥቀን እግራችን ላይ ሁሉ ሰው እናስቀምጣለን ።

በርና መስኮት ተዘግቶ ፊልሙ ሲጀምር ሙቀቱም ከፊልሙ የሚወጣ ይመስል በእንፋሎት እንቀቀላለን ። የትንፋሽ እንፋሎት እያነደደን የጫማ ሽታ ሲታከልበት የበላነው እስኪወጣ ያጥወለውለናል ። የአፍ መጥፎ ጠረን መከራችንን ያበላናል ። የፈስ ነገርማ አይጣል ። ማንም ይፍሳ ማን የሚሳበበው በድንቡሽ ነው ። ድንቡሽ እናቱ የባቄላና የአደንጓሬ ንፍሮ እንደዚሁም የተቀቀለ ሚጣጢስ (ስኳር ድንች) ስለሚሸጡ ከኪሱ ንፍሮ ከቂጡ ፈስ የማያጣ ሰሙጥር የሠፈራችን ፈሳም ነው ። ታድያ እኛም ሳናስፎግር ቱስ እናደርገውና ገና ሰዉ ሁሉ ሳይሸተው አፍንጫችንን እንይዛለን ።

እኔ ፣ ጠይሜና ጠምቤ ሁሌም ከኪሳችን ስሪንጅና ብልቃጥ አናጣም ። በጭለማው ውስጥ አረቄውን እንቀዳና እንሸጣለን ። አየር በአየር ነው የምንሸጠው ። እዚያው አብረውን ሠሌን ላይ ተቀምጠው ፊልም ለሚያዩ ጨባሽ ጎረምሶች በሳንቲም እንቸበችባለን ። ከባለቤቶቹ በስተቀር አብዛኛው ፊልም ተመልካች ይህንን ድርጊት ያውቃል ። እነርሱም በተራቸው እየቀዱ ይሸጣሉ።



@BOOKALEM

ጉልቤዎችም እያስቀዱ ይጠጣሉ ። ከጠጪዎቹ የሚጠበቀው የመጀመርያዋን በገንዘባቸው ከባለቤቶቹ ማዘዝ ብቻ ።

አረቄ ብቻም ሳይሆን ለውዝም እያወጣን እንበላለን ። ጆንያውን ቀስ እያልን እየዘረዘርን ቀዳዳ እያወጣን ጥሬውን ለውዝ እየሠረቅን እንነፋለን ። አንድ ቀን ግን ከኛ «ግሩፕ» ውጪ ያሉ ልጆች አስፎገሩን ።

የፕላስቲኩን በርሜል ከዳን ከፍተው አረቄውን እንቀዳለን ብለው ሲታገሉ የተደራረበው በርሜል ተንከባለለባቸው ። አርሬው ፊልም ሲያዩ የነበሩ ትንንሽ ልጆ ላይ ወደቀ ። የወደቀባቸው ጮኹ ። አረቄው ቤቱን በሽታና በጎርፍ አጥለቀለቀው ። የመዐዛ አባት ተናደዱ ። በአረቄ ጎርፍ የተጥለቀለቀውን ቤታቸውን ተመልክተው አበዱ ። ከዘራቸውን አንስተው «ምድረ ሌባ !... ውጡልኝ ከዚህ !» ብለው ወግረው አባረሩን ። ጠይሜ በኪሱ ከነሞላው ለውዝ ተያዘ ።

« እንዴት የገዛ አባትህን ቤት ከሌቦች ጋር ተባብረህ ትዘርፋለህ ?» ብለው እስኪበቃው ወቀጡት ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እዛ ቤት ቪዲዮ ማየት አቆምን ። እነሱም አከሳሪነቱን ዘግይተው የተረዱትን ቪዲዮ ቤታቸውን ዘጉት ።

ወደነ ፈጠነ ቪዲዮ ቤት መዋያችንን የቀየርነው ከነ መዐዛ ቤት ከተባረርን በኋላ ነበር ። የፈጤ አባት ሲበዛ ስግብግብ ናቸው ። ሱቃቸው ውስጥ ሲሸጡ በገንዘባችን የገዛናቸውን ዕቃ መዝነው ለመስጠት እጃቸው ይንቀጠቀጣል ። ስባሪ ሳንቲም አያልፉም ። ሒሳብ ስለማይችሉ ግን ብዙ ጊዜ እንሸውዳቸዋለን ። አምስት ብር እንሰጣቸውና በወሬ እንጠምዳቸዋለን ። በተለይ ስለ ሰካራም ሲወራላቸው ደስ ይላቸዋል ። አዋርተናቸው ሲጠግቡ «መልስ ስጡን» እንላቸዋለን። «ስንት ነበር የሠጠኸኝ ?» ይሉናል ። ጨምረን እንነግራቸዋለን ። እየሳቁ ምንም እንዳልተሸወዱ ሆነው ይሠጡናል ። ይዘን ፈትለክ ።

የፈጤ አባት ሚስታቸውን ከቤት እንዳባረሯቸው ይወራባቸዋል ። ትላልቅ ጎረምሶች አፍርተዋል ። ሰድስቱም ልጆቻቸው ወንዶች ናቸው ። በቤታቸው ውስጥ በነዋሪነት የተመዘገቡት አንዲት ሴት እናትየው ነበሩ ። ግድግዳ ላይ ካሉት በርካታ ፎቶዎች መሀል ሁለቱ የሴት ናቸው ። ያውም አንደኛዋ በቤቱ ሰዎችና በሠፈርተኛው ፣ ሁለተኛዋ ደሞ በዓለም ሰዎች ዘንድ ታዋቂ የሆኑ ሴቶች ። እምዬ ማርያምና የፈጤ እናት ። በነ ፈጤ ዘር ውስጥ ሴት ልጅ ሜርኩሪ ናት በቀላሉ የማትገኝ ። አንዳንዶች ደሞ « ሴትየዋ ባላቸው አላስተኛ ብለው ስላማረሯቸው ሀገር ጥለው ገዳም ገብተው ቀርተዋል » እያሉ ያስወሩባቸዋል ።

ጠይሜ እናትና አባቱ ሲያወሩ ሰምቶ የነገረኝ ደሞ ይገርማል ። ሁልጊዜ በገቡ በወጡ ቁጥር «ካልሠጠሽኝ » እያሉ ስለሚጨቀጭቋቸው ተማረሩ ። ቀንም ማታም እያሯሯጡ የሚደበድቧቸው « መረረኝ አልሠጥህም !» በማለታቸው እንደሆነ ደጋግሞ አውርቶልኛል ። ሴትየዋ ለመስጠት የማይፈልጉትን ነገር ምንነት ስጠይቀው ግን « ጤባ !» እያለ መልስ አይሠጠኝም ።

የነ ፈጠነ ቪዲዮ ቤትም መኖርያቸው ነው። ሳሎኑ ውስጥ ያሉት ዕቃዎች ወደ አንድ ጎን



@BOOKALEM

ይደረጉና ፊልማችንን እንከሽከሻለን ። ብዙ ልጆች ተሽቀዳድመን ገብተን በስኳር ተሞልተው የሚከመሩት ጀንያዎች አጠገብ እንቀመጣለን ። ቀድመን ቦታችንን ከያዝን ቀጣዩ መብራት የሚጠፋበትን ሰዓት መናፈቅ ይሆናል ።

ብዙዎቻችን የስኳር ቀበኞች እንደሆንን ብናውቅም ከ«ግሩፕ» አባላታችን ውጪ ለማንም ምስጢራችንን አሳልፈን አንሠጥም ።

« ዛሬ›ኮ ‘ማዘር ኢንዲያ’ የሚለው የሕንድ ፊልም ነው እነ ፈጤ ቤት የሚታየው » አለ ጠምቤ ።

« አንድ ፊልም ብቻ ?» ጠይሜ ጠምቤን ጠየቀው ።

« ርዕሶቹን ረሳኋቸው እንጂ ቫንዳምና ሚስተር ቦንድ የሚሠሩባቸው ሁለት የአሜሪካ ፊልሞችም አሉ ።»

« እኔ›ኮ መግቢያ ሳንቲም የለኝም ።» እውነቱን ተናገርኩ ።

« እኔም የለኝም ። እቤቴ ሄጄ ግን የእማዬን ሙዳይ አስደነግጣለሁ ።» አለ ጠይሜ

« እንዴ ብትቀሰፍስ ?»

« ጭንቅሎ ደሞ ሲበዛ ፈሪ ነህ ። መቀሰፍ ብሎ ነገር የለም ። ደሞስ ከሙዳይ እንጂ ከእግዛቤር አልሠረቅኩ ። ሙዳይ ለራሷ ነብስ የላት ! አትበላ አታራ ! እንዲሁ ብቻ ቤታችንን በቅቤ እንዳገማች አብራን ትኖራለች ። አይ ጭንቅሎ ! በሳር የተሠፋች ሙዳይ እንጂ ፈጣሪን አረግካት እንዴ የምትቀሰፈኝ ?»

« ኧረ ጠይሜ እንደዚህ ዓይነት ድፍረት አታብዛ ። እማዬ›ኮ ሙዳይ ከከፈትክ ትቀሰፋለህ። ከሙዳይ ውስጥ ገንዘብ ከሠረቅክ ሙዳይዋን የነካህበት እጅህ ሸባ፣ ያየህበት ዓይንህ እውር ይሆናል ብላኛለች ።» አልኩት።

«.ሲያስቦኩሽ ነው ጭንቅሎ ! እኔ›ኮ ሁሌ ገንዘብ ሳጣ የእማዬን ሙዳይ እያስደነገጥኩ እዝናናበታለሁ ። አትፍራ ጭንቅሎ ! አላየኸውም እንዴ ...ውስጡ ጨሌ ብቻ›ኮ ነው ያለው ።» ጠይሜ እስከዛሬ በምስጢር ይዞት የነበረውን የገንዘብ ምንጩን ተናገረ ።

« ኧረ ! እኔም ሙዳይ አስደንግጬ አውቃለሁ ።» ጠምቤ ጣልቃ ገባች

« ማርያምን በይ እስቲ ?»

« ማርያምን ! »

«እስቲ ስንት ቀን አስደንግጠሻል ?»

« ነፍ ቀን ! ስቾስት ስቾስት እማዬ ሙዳይ ውስጥ ቻስ ነው ።»



@BOOKALEM

« ምንም አያስፈራም ? እ ... ምንም አልሆንሽም ?»

« ይኸው አያየኸኝ አይደል ... ምን ሆንኩ ? የመጀመርያ ቀን ስከፍተው ፈራሁ ። እግዛቤርና ማርያም ሙዳይ ውስጥ ያሉ መሰለኝ ተንቀጠቀጥኩ ። ሙዳዩ ውስጥ እግዛቤርና ማርያም ካሉ ሳያዩኝ ከድን አድርጌባቸው እንደምሮጥ አራሴን አሳምኜው ነበር ። ስከፍተው ግን ቅቤ በተለቀለቀ ጨሌ ፣ ድፍን ቡና ፣ አሪቲ ፣ ከሴ እና ነፍ ሳንቲሞች ተሞልቷል ።»

« ከዛስ ?» ጠይሜ በጉጉት ጠየቀው

« የሚበቃኝን ሳንቲም ወስጄ ሙዳይዋን እንደነበረች ከድኜ ሠንዱቃችን ውስጥ ዱቅ አድርጌ እፍ አልኳ ።»

« ማንም አልነቃብሽም ?»

« ኧረ ! ማንም አልነቃብኝም ። አሁንም ሲጠብሸኝ የምነበኘው የጨሌ ሙዳያችንን ነው ።»

ሦስታችንም ሳቅን ። ድፍረት በትንሿ ልቤ ውስጥ በፍጥነት በቀለ ። ለምንም ነገር ደንታ የማይኖረው ፣ ለምንም ግድ የሌለው ድፍረት ።

« ካሁን በኋላ ግን የቪዲዮ መግቢያ ሳንቲማችንን ለምን በቀላሉ አናጠራቅምም ?»

« እንዴት እናጠራቅመው ? ከየትስ አምጥተን ማጠራቀም እንችላለን ?» ጠምቤ የጠይሜን ጥያቄ በጥያቄ መለሠችበት ።

እነ ፈጤ ቤት ትልልቅ በሲሚንቶ ወረቀት የተሠሩ ኪሶችን ይዘን ገባን ። የተከመሩትን የስኳር ጆንያዎች ለሦስት ከበብናቸው ። ፊልሙ መታየት ሲጀምር ሙብራት ጠፋ ። ደብቀን የያዝነውን የአስከርቢቶ ቀፎ ጆንያውን ሠቅሠቅ አድርገን አስገባንለት ። የወረቀት ኪሳችንን ከእስክርቢቶው ቀፎ ጋር አገናኘነው ። ሿሿሿ ...ስኳር በቧንቧ መስሎ ወደ ወረቀት ኪሳችን ተንቆረቆረልን ። ሲሞላ ወገባችንን በገመድ ጥፍንግ አድርገን አሰረን ኪሱን በጉያችን ሸሸግነው ። ፊልሙ ሳያልቅ ተራ በተራ አቋርጠን ወጣን ።

ጢሻ ውስጥ ተከከረን ሦስታችንም የያዝነውን ስኳር በአንድ ፌስታል ገለብጥነው ። ሻይ ሻጯ አበሩ ጋር ሄድንና ሁሉንም በሁለት ብር ከሃምሳ ሸጥንላት ። ሌላም ካገኘን እንድናመጣላት ጋበዘችን ። አበሩ የተሠረቁ ነገሮችን በመግዛት ትታወቃለች ።

ወደ ቪዲዮ ቤቱ ተመልሠን ስንገባ የፈጤ አባት በረንዳ ላይ ተቀምጠው ጋዜጣ ያነባሉ ።

« ሽማግሌም ማንበብ ይችላል እንዴ ?» አልኩት ጠይሜን

« እና እንዳንተ እያት ከብት ሲያግዱ ያደጉ መሠለህ ?»

መልሱ አበሸቀኝ ። ጠምቤ እግሯን አንስታ ሳቀች ።



@BOOKALEM

«የኔ አያት ከብት ሲያግዱ ማደጋቸውን የት አየህ?» አልኩና አፈጠጥኩበት።

«ጭንቅሎ ደሞ መከራከር ትወዳለህ...ያስታውቁ የለ እንዴ !»

« እንዴት ?»

« ሁሌ ሲዘፍኑ የማልሠማቸው መሠለህ !»

« ምን እያሉ ሲዘፍኑ ሰማሃቸው ?» ስትል ጠየቀችው ጠምቤ

« እምቧ በይ ላሚቱ ...ላሚቱ

እምቧ በይ ላሚቱ

እምቧ በይ ላሚቱ ...ላሚቱ

ኮርማ ወላዲቱ ።»

አብሬያቸው ሳቅኩ ።

ወደ ነበርንበት ቦታ ሄደን ስንቀመጥ እኛ ቦታ ላይ ተቀምጠው የነበሩት ልጆች በሙሉ እጃቸው ፣ ከንፈራቸው ፣ አፍንጫቸው ስኳር በስኳር ሆኗል ። ወለሉ ላይ የተቆለለ ስኳር ይታያል። ጠምቤ የአስከርቢቶ ቀፎዋን እንደተከለችው ረስታላቸው ወጥታ ነበር የተንቆረቆረው ።

ሁለተኛው ፊልም ሊቀየር መብራት ሲበራ ነገሮች ሁሉ እንዳልነበር ሆኑ ። ጠይሜ ተንኮለኛው ለፈጤ ልጆቹ ስኳር ሠርቀው እየቃሙ እንደሆነ ቀስ ብሎ ነገረው ። ፈጤ የስኳር ነጥብ ያገኘባቸውን ልጆች በሙሉ በጥፊ ጆሮ ግንዳቸውን እያነደደ አባረራቸው ። እኛን ሦስታችንን ግን አልነካካንም ። እነዛን ልጆች አባረረና እኛን የስኳሩ ጠባቂዎች አደረገን ። አደራ ከተሰጠን በኋላ ሰኳር ለመስረቅ አልመቸ አለንና ከዛ ቤት ቀረን ።

***

ማሙሽት አልተማረም ። ማለቱ ከሁለተኛ ክፍል ነበር ትምህርቱን ያቋረጠው ። « የአርቲስት ልጅ ነኝ ። ትምህርት በቃኝ ፣ እንደ አባቴ አርቲስት መሆን ነው የምፈልገው !» ብሎ ነበር ከትምህርት ቤት የቀረው ።

እውነቱን ነው ። አባቱ በመንደራችን ጠጅ ቤቶች ውስጥ ታዋቂና ከፍተኛ ዝና ያላቸው ባለ ማሲንቆ ነበሩ ። ጋሽ አመራ ይባላሉ ። ረ...ጅም ናቸው ። የኤሌትሪክ ሽቦ አልተወጠረባቸውም እንጂ ስልክ እንጨት ነው የሚያክሉት ። ልጅ ይወዳሉም ይወልዳሉም ። በየእናቶቻቸው ዘንድ የሚያድጉ ብዙ ልጆች አሏቸው ። ልጆቻቸው ከሳቸው ያተረፉት ስማቸውን ብቻ መሆኑ ይገርመኛል ።

« እኔ ነኝ አመራ



@BOOKALEM

## እኔ ነኝ አመራ

በየ ጠጅ ቤቱ ሙብራት የማበራ ::» እያሉ ያስቁናል ጭብስ ብለው ከጠጅ ቤት ሲወጡ ::

ጨዋታቸው ደስ ስለሚለን ሁሌም እየጠበቅን በማሲንቋቸው እንዲጫወቱልን እንለምናቸዋለን:: ለሦስት ከብብ እናደርጋቸውና እናጨበጭብላቸዋለን :: የፈለገ ቢሠከሩ ማሲንቋቸውን መገዝገዝ አይሳናቸውም :: በተለይ ለኛ ለልጆች ጥሩ አጫዋች ነበሩ ::

« እሺ ልጆችዬ...ሙዚቃ እንድጫወትላችሁ ትፈልጋላችሁ ?» አሉን አንድ ቀን ውትውት ስና ደርጋቸው ::

« አዎ !»

« ልጫወት ?» ደግመው ጠየቁን

« አዎ !»

« እሺ በሉ ተዘጋጁ...በል መጀመርያ ጭንቅሎ ግጥም አምጣ !» አሉኝ ማሲንቋቸውን የሚሟ ቂያ ዜማ አስጀምረው ::

« ከየት ?»

ሳቁብኝ ::

« ከየት ነው ግጥሙን የማመጣው ጋሽ አመራ ?»

« አንተ ልጅ ኮንቴይነር ነው ጭንቅላት አንገትህ ላይ የሠኩልህ ?» አሉኝ በደጋኑ ወደ ጭንቅ ላቴ እየጠቆሙ ::

አንድ ቀን ጉድ ሠራናቸው :: ጭብስ ብለው የሚሆኑትን አያውቁም :: የሚሆኑትን ብቻ ሳይሆን የምናደርጋቸውንም አያስታውሱም :: ማሲንቋቸውን ሠረቅንና እነ አሊያ የሠንሠል አጥር ውስጥ ከከርነው :: ኤድረው ፣ ስካራቸው ጠፍቶ ወደ እራሳቸው ሲመለሱ ማሲንቋቸውን ፈለጓት:: ሊያገኟት ስላልቻሉ አርጅታ ጥለዋት የነበረችውን ጡረታ የወጣች ማሲንቆ ከኩሽና ግድግዳ ላይ አንስተው ጭስና የሸረሪት ድሩን አራግፈው ሥራ ጀመሩ ::

የደበቅነውን ማሲንቆ ቦታው ላይ ስላገኘነው ለሀሠን እንዲታየው አድርገን ግቢው ውስጥ ጣልንበት :: ሁሌ ሠከረው ሲያገኙት ስለሚሠድቡት አይወዳቸውም :: እሱም ባያቸው ቁጥር ምራቁን ይተፋል :: ሚስቱ አሊያ ማሲንቆውን አንስታ ወደ ቤቷ ስታስገባው አየናት :: በግቢው ውስጥ በርካታ ማር ሠጪ ንቦች በየቀፏቸው ይኖራሉ::

ጋሽ አመራን ጢጥ ብለው ጠጃቸውን ጠግበው ሲመጡ ጠበቅናቸውና ማሲንቋቸውን



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

የሠረቀው ሀሠን መሆኑን ነገርናቸው ። ከርካሳ የግቢ በሩን በርግደው ገብተው ከሀሠን ጋር ተጣሉ። ጭቅጭቃቸው ያስደነገጠው ህፃኑ አፈንዲ አለቀሠ ። ሲሠድባቸው ዱላ ሠነዘሩ ። በቦከስ ሰላቸው ከንቦቹ ቀፎ ጋር ተጋጩ ።

ቀፎው ሲወድቅ ንቦቹ ግልብጥ ብለው ቤታቸውን ጥለው ወጥተው ወደ ጊዜያዊ ቀፏቸው ወደ ጋሽ አመራ መውጊያቸውን ይዘው ተመሙ ። ሠፈሩባቸው ። የንቡ መንጋ ጋሽ አመራን ጊዜያዊ ቀፎ አድርጎ ተዝናናባቸው ። ግንድ የሚያከሉትን ሰውዬ የጥፍራቸውን ግማሽ የማያካክሉት ንቦች አስተኝተው እያንደባለሉ ፣ እያስጮሁ ፣ አሰለቀሏቸው ። ሀሠን ሮጦ ወደ ቤቱ ገብቶ በሩን ዘጋባቸው ። የመሞታቸውም መነሻ ንቦቹ ሆኑ ።

ማሙሽት በዚህ ዓይነት ሁኔታ አባቱ ከሞቱ በኋላ ኑሮው ተናጋበት ። እናቱ በየሆቴሉ ተቀጥረው በእንጀራ ጋጋሪነት ይሠራሉ ። ሥራቸውን አገባድደው ወደ ቤት ሲመጡ በትልቅ ፌስታል ኡፋ (ቡሌ) ይዘው ይመጣሉ ። አሪፍ ኡፋ ። ተሻምተን በፍቅር የምንበላው ኡፋ ያለው እነ ማሙሽት ቤት ነው ።

ኡፋውን እየበላን ድንገት ስጋ ካገኘን ከአፋችን እናወጣና በእጃችን እንይዘዋለን ። እንደዚህ የምናደርግበት ዋነኛ ምክንያት ስጋ ለማኘክ በምናጠፋው ጊዜ መሀል እንጀራ እንጀራው ተበልቶ እንዳያልቅብን በመስጋት ነው ። እንደ እሳት ያገኘውን ነገር በሙሉ ሳያኝክ የሚውጥ ፈርጣማው በድሉ ጅቦ ብቻ ነው ።

የነ ታገልን ቪዲዮ ቤት የሚቆጣጠረው ማሙሽት ሆነ ። እነ ታገል ትልልቅ ጎረምሶች ስለሆኑ « ከሙጫጭሬ ጋር ፊልም አናይም » እያሉ ፊልም የማሳየቱን ኃላፊነት ለማሙሽት ሠጡት ። ፊልም ከመጀመሩ በፊት የሚመጡ ሰዎችን የመግቢያ ሒሳብ የሚቀበለው እራሱ ታገል ነው ። ማሙሽት ሒሳብ አያውቅም ። ሒሳብ መቀበል የሚጀምረውም ታገል ወደ ጫቱ ሲሄድለት ነው ። እኛም የምንገባው የታገልን ጫት ይዞ መሄድ ተከትለን ።

ሒሳብ ተራራ እንደመሸከም ይከብደዋል ። የአንድ ሰው መግቢያ ሽልንግ ስለሆነች በቀላሉ ቆጥሮ ይቀበላል ። እኛ ግን ስናጭበረብረው የሦስታችንን ሒሳብ አምስት አምስት ሳንቲም ዘርዝረን አስራ አምስት አምስት ሳንቲሞች እንሠጠዋለን ። እያምታታን እንቆጥርለትና ያስገባናል። የሰበሰበውንም ሳንቲም « ቁጠሩልኝ » ብሎ ሲሠጠን እንቀንስበታለን ። በጣም የሚያምነን ነገር ግን ፍጹም ታማኝ ያልሆንን ሰዎቹ እኛ ነን ።

ማሙሽት ቪዲዮ ቤት የተመረጡ ጎረምሶች ብቻ ሲመሻሽ አንድ ፊልም በሽልንግ ያያሉ ። ማንኛውም ሙጫጭሬ መክፈል ቢችልም መግባት አይፈቀድለትም ። የፊልሙ ማስታወቂያ ብዙ ጊዜ እደጅ አይለጠፍም ። ፊልሙ ምስጢር ነው ። እኔና ጠምቤ አናውቅም ። ጠይሜ ግን የሆነ ጭምጭምታ ሳይሠማ አልቀረም ። ወንድሙ የማታ ማታውን ፊልም ማየት ስለሚፈቀድለት አውርቶለት ይሆናል ።

ተን ተን እከከ እስኪለን የምናየውን ፊልም ማታ ለማየት ቋመጥን ። የቀን ቀኑ ፊልም



@BOOKALEM

ተመልካች ቁጥር ቀነሠ ። አብዛኛው ወጣት የሚሠገሠገው ሲመሽ ሆነ ። የማስታወቂያ ሠሌዳው ላይ የማይለጠፍ ፣ ርዕሱ ቀድሞ የማይፃፍ በሁሉም ሰው ዘንድ የሚታወቅ የጋራ ርዕስ አለው «ፈረንሳይ ካራቴ !»

ለመጀመርያ ጊዜ ፈረንሳይ ካራቴን ያየሁት ከእህቴ ከመሳይ ጋር ነበር ። ታገል መሳይን ይገርት ከመጣሁ ሁሴ ፊልም በነፃ እንደሚያስገባኝ ቃል ገባልኝ ። ብቻዬን...እነ ጢይሚን ትቼ መግባት እንደማልፈልግ ነገርኩት ። ለሦስታችንም በነፃ ፈቀደልን ። መሳይን አስይዤ ጓደኞቼን ፊልም ጋበዝኩ ።

በቪዲዮ ቤቱ ውስጥ ያለችው ብቸኛ ሴት መሳይ ነበረች ። ወንዶች እንበዛለን ። ማምሻት ፊልሙን ሲከፍተው ታገል መብራቱን አጠፋውና ከመሳይ አጠገብ ተቀመጠ ። ቤቱ ከቴሌቪዥኑ በሚወጣው ብርሃን ብቻ እየታገዘ በቤቱ የነበረውን ረብሻ ገታው ። መሲ ከጭንቅላቴ ላይ ቅማሎቼን ስትገድልልኝ እንደምታደርገው ጭንና ጭኗ መሀል አስገብታ አቅፋኛለች ።

«ርዕሱ ምንድን ነው የሚለው?» አልኳት ጆሮዋ ሥር ተጠግቼ ።

« ሰቨንቲንገ !»

« ምን ማለት ነው ?»

« አስራ ሰባተኛ !»

« ከሽከሽ አለው ?»

« እኔ እንጃ !»

ዓይኖቼን ቲቪው ላይ ሠክቼ ቀረሁ ። አንዲት ወርቃማ ፀጉር ያላት ወፍራም ፈረንጅ ቀስ ተደርጎ በተከፈተ ሙዚቃ ቂጧን እያማሰለች ልብሷን አወለቀች ። እላይዋ ላይ ሙታንቲዋና ኮፍያዋ ብቻ ቀሩ ። ደነገጥኩ ። የሜዳ ቴኒስ መጫወቻ ራኬት የያዘ ጠብደል ጥቁር ወንድ መጣና አጠገቧ ቆመ ። ከንፈርና ከንፈራቸውን አጋጠሙ ። ራኬቱን ጥሎ በእጁ ጡቶቿን አሻሻቸው ። ካናቴራውን አወለቀችበት ። ቁምጣውን እራሱ አወለቀው ። እራቁቱን አጠገቧ ሲቆም አለማፈሩ ገረመኝ ። እሱ ቆሞ እሷን እንደ ፎቶ እንሺ አንበረከካት ።

«ተንበርከካ እንዳይመታት ልትለምነው ነው » ስል በአፏ ባለጌ ነገሩን ጎረሰችበት ። እንደ ጀላቲ ስትልስበት ጭንቅላቷን ይዞ ኢቃሰተ ። ተራ በተራ የተለያዩ ሴቶች እየመጡ ወንዱን ሲያሠቃዩት የሆነ ደባሪ ሽታ ሠነፈጠኝ ። የማወራውና ምራቄን ጢቅ የማደርገው እኔ ብቻ ነኝ ። ሁሉም በተመስጦ ፀጥ ብሏል ። መሳይ ጥብቅ አድርጋ ወደ ደረቷ አስጠግታ አቀፈችኝ ። እጇን ወደ ወሽላዬ ሠድዳ ስትነካካብኝ ቆነጠጥኳት ።

ደነገጠች ። ሴባ ጣቴን የምታክለው ወሽላዬ ቆማ ነበር ።



@BOOKALEM

« አንተ ... ምን አይታ ነው ወሸላህ የቆመችው ?» አለችኝ በጆሮዬ ::

« ሽንቴን ወጥሮኝ !» በድንጋጤ አፌ ላይ የመጣልኝን መለስኩላት ::

ሳቅ ብላ ጉንጬን ሳመችኝ ::

« በል ተነስ ! ከዚህ ቤት ቶሎ መውጣት አለብን ::»

« ሳንጨርሠው ?»

« ይኼ የባለጌ ፊልም ነው :: ሁለተኛ እዚህ ቤት መምጣትም የለብህም እሺ !» አስጠነቀቀችኝ ::

እነ ጠይሟ እዚያው ሲቀሩ እኔ ጋባዣቸው ግን ያለ ፍላጎቴ ወደ ቤት ሄድኩኝ :: ከዚያ ጊዜ ወዲህ ግን ያለ ፈረንሳይ ካራቴ የምንመርጠው ፊልም አልነበረም :: ፖሊስ የነ ታገልን ቲቪና ዴክ እስኪወስድባቸው ድረስ ::



@BOOKALEM

# ምዕራፍ አስራ አንድ

## ዓለም ገምታለች

ኩርት ፣ ዝንጥ ፣ ቅብርር ያለ ኑሮ የሚኖሩ ሰው ናቸው ። ረዝሞ የወረደ ቁመናቸውን በሙሉ ሱፍ ሲለብጡት ያምራሉ ። ልጅ ፣ ሚስት የሚባል ጣጣ አያውቁም ። አባቴን በገቢም የሚበልጡት ጋሽ ለማ አላገቡም ፤ አያገቡምም ። ትዳራቸው የቢራ ጠርሙስ ውስጥ የተደበቀ ይመስል ካልተነነጩ ውሎ ማደር የሚቻል አይመስላቸውም ።

ጠቆር ያለውን ፊታቸውን ለመለየት የግድ ጥቁር አንበሳ የሚያስመስላቸውን የጢም ጎፈር መላጨት አለባቸው ። ካልተላጩት ፊታቸውና አንገታቸው በጥቁር ፀጉር ይደፈናል ። አፍንጫቸው ውስጥ በቅለው ወደ ከናፍሮቻቸው የሚንጠራሩት ነጫጭ ፀጉሮች ያስፈራራሉ ። አፍንጫቸው በብዙ ፀጉር ተሞልቶ መተንፈስ አለመቸገራቸው ይገርመኛል ። በዚህ ላይ ፍንጭት ናቸው ። ከከንፈር ተርፎ የወጣ ፍንጭት ባለቤት ።

« በሰማይ የጸደቀ በምድር ያስታውቃል

ከከንፈሩ ተርፎ ጥርሱ ጻይ ይሞቃል ። » ተብሎ በአያቴ የተሾፈበት ጥርስ ።

ጋሽ ለማን ከርቀት ሆኖ ሲስቁ ለተመለከታቸው እየሳቁ ሳይሆን ማስቲካ እየነፉ ሊመስለው ይችላል ። በሽምግልና የፊንዱ የዘመናችን K-50 ። የውስጥ እጅና እግራቸውም ሳይቀር ጥቁረቱ ይገርማል ።

የሚታወቅ ቋሚ ሥራ የላቸውም ። አልፎ አልፎ የጥበቃ ሥራ ይሠራሉ እየተባለ ይወራላቸዋል ። እሳቸው ግን ከኛ የሚገናኙት ሁሌም ጨብሠው ነው ። ጥምብዝ ብለው ሠክረው፣ እየተንገዳገዱ፣ ዓይኖቻቸውን ጨፍነው ወደ ፊት ሲሄዱ ። እኛ የምናውቀው የጋሽ ለማ መደበኛ ሥራ መስከር መሆኑን ነው ። ጢጥ እስኪሉ እየጠጡ የሚንቦጃቦጁ ፣ ነገን የማያውቁ ፣ የልጅና ሚስት ሃሳብ የሌለባቸው ሽማግሌ ። ከዕድር ፣ ከማኅበር በፍቃዳቸው የተገለሉ ሰው ።

የማናውቃቸው ሁለት ወንድሞቻቸው ውጭ ሀገር ይኖራሉ ። በየጊዜው ገንዘብ ይላክላቸዋል። በጊዜና በፍጥነት ጠጥተውበት ይጨርሱታል ። ከባንክ ብር የተቀበሉ ምሽት እሳቸው በገቡበት መጠጥ ቤት የገባ ሁሉ ኪሱን አያስብም ። ጋሽ ለማ እጃቸውን ወደ ኪሳቸው ልከው የጠጣውን ያህል ይከፍሉለታል ። የሚያወሩለት ቢጥመውም ባይጥመውም ያለ ሃሳብ መጠጣት ከፈለገ ድዱን ማሳየት ይጠበቅበታል ። የውሸቱን እየገለፈጠ ሆድ ዕቃውን ለመጠጥ ማስፋት ። እያጨበጨበ ቀኟውን መጥራት ካማረው ለጋሽ ለማ የግድ መሳቅ ይገባዋል ።

የፈለገ ቢመጣ አያመሹም ። ገና አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ወደ ቤታቸው ለመግባት መንገድ



@BOOKALEM

የሚጠጡትን ቢራ ይይዛሉ ። ሐረር ቢራን ይጀምራሉ ። በኮታቸው ኪስ እቤታቸው ተኝተው የሚጠጡትን ቢራ ይይዛሉ ። ሐረር ቢራን ይመርጡታል ። መርጠው ይጨልጡታል ። እንደ አብዛኛዎቹ የሠፈራችን ሽማግሌዎች ለአረቄና ጠጅ እጅ አልሠጡም ። በጋሽ ለማ ፍልስፍና ውስጥ አረቄና ጠጅ የድሀ መጠጦች ናቸው ። ብርና ተስፋ የራቃቸው ሰዎች በባዶ ሆዳቸው እየተጎነጩ ግብዓተ መሬታቸውን የሚያፋጥኑባቸው እራስን የማጥፊያ ባህላዊ የጦር መሣሪያዎች ። እንደ ጥይት ጉብትን ብስት እንደ ፈንጂ ኩላሊትን ፍንድት ፣ ቡርቅስ የሚያደርጉ መጥፊያዎች ።

እጆቻቸው ከኪሶቻቸው አይለዩም ። የእጆቻቸው ከኪሶቻቸው በፍቅር መጣመር መንስዔዎቹ የሠፈራችን ጎረምሶች ናቸው ። መንገድ ላይ እየጠበቁ በኪሶቻቸው የያዟቸውን ቢራዎች ይመነትፏቸዋል ። ሮጠው መንታፊዎቻቸውን መያዝ አይችሉም ። ስለዚህም እደጋ ከመድረሱ በፊት ቀድሞ መከላከልን መረጡ እጅ በኪስ ።

ልብሶቻቸው በሙሉ ሱፍ ናቸው ። ያውም ምርጥ ምርጥ የውጭ ሀገራት ሱፍ ። ቁርጭምጭሚቱ ላይ ጡት ጡት ያለው ሽራ ጫማ ይጫማሉ ። ወንድሞቻቸው የሚልኩላቸውን የቆዳና የስኒከር ጫማዎች እየሸጡ ሽራ ጫማና ቢራ ይገዛሉ ። የፈረንጅ ጫማ እግሬን ያቆስለኛል ይላሉ ለመሸጥ ሠበብ ሲፈልጉ ።

የሠፈር ሰዎች እሳቸውን መጠጥ ለማስተው ያልሞከሩት ዘዴ የለም ። መጠጥ ሳይቀማምሱ በወዳጅነት መከረዋቸዋል ። ጧት እሺ ያሉትን ሲመሻሽ ያፈርሱታል ። እንዲያውም የተመከሩ ቀን ይብሰባቸዋል ።

የሆነ ቀን ገና ከቀኑ ስምንት ሰዓት አካባቢ ጥምብዝ ብለው ሠክረው መጡ ። የሠፈር ሰዎች ተመካከሩና ያዟቸው ። እጃቸውን ጠምዝዘው ኳስ የምንጫወትበት ሜዳችን መሀል ወደ ተተከለችው ባለ ድጋፍ ሰልክ እንጨት አመጧቸው ። ከእግራቸው እስከ ደረታቸው በተጠመጠመ ገመድ ከስልክ እንጨቱ ጋር ጠፈሯቸው ።

መውደቅም መንቀሳቀስም አልቻሉም ። ማንቀሳቀስ የሚችሉት የራስ ቅላቸውን የተሸከመውን አንገታቸውን ብቻ ነበር ። ያውም ወደ ቀኝና ግራ ትከሻቸው ብቻ ። አባቴ በውሃ የተበጠበጠውን ስኳር ፊታቸውን ቀባቸው ። ከንፈራቸው ላይ የደረሠውን አጣጣሙት ። ምላሳቸው ወደ ውጭ ተጎልጉሎ ወጥቶ የቻለውን ያህል ተጉዞ አፋቸው አካባቢ የተቀቡትን ጠራረገላቸው ። ዓይኖቻቸውን መግለጥ ተቸገሩ ።

ቀጥሎ ፊታቸው ላይ ያለውን ስኳር የመላስ ተራው የዝንቦች ሆነ ። የጋሽ ለማ ፊት የዝንቦች መናፈሻ መሠለ ። ዝንቦች ከያሉበት በፉጨት እየተጠራሩ ወደ አዲሱ መናፈሻቸው ጎረፉ ። ከጋሽ ለማ ፊት ላይ ያለ ከልካይ ስኳር ሲልሱ ተሰበሰቡ ። ስኳሩን እየላሱ የጠገቡ እየተፀዳዱ ተዝናኑባቸው ። ፀጉራቸው በስኳሩ ሙጫ ተጣበቀ ። ሰሚ ባያገኙም ገመዱ እንዲፈታላቸው አጥብቀው ለምነው ነበር ።



@BOOKALEM

አባቴና ጓደኞቹ ጋሽ ለማን የታሠሩበት ጥለዋቸው እኛ ቤት ገቡ ። እኔ ፣ ጠይሜና ጠምቤ ደሞ ድርጊታቸውን ተደብቀን አይተናል ። እንደታሠሩ ብቻቸውን መቅረታቸውን ካረጋገጥን በኋላ ተመካከርን ። በሲጋራ ፓኮ ውስጥ ጥቋቁሮቹን ትንኳሾችና ቀያዮቹን ዘመሚቶች ሰበሰብን ።

ቀስ ብለን ሳያዩን በኋላቸው በኩል ተጠጋናቸው ። በቁምጣቸው አንቅልፍ ወስዷቸዋል ። እንደ ፈረስ በቁማቸው ተኝተው ያንኮራፋሉ ። ጠይሜ ኪሳቸው ውስጥ እጁን ከተተና ያላቸውን አራት ብር አወጣው ። ብሩን በማግኘታችን ተደሠትን ። አንገታቸው ላይ ተንጠራርተንም መድረስ አቃተን ። ረጅም ስለሆኑ ጭንቅላታቸው ላይ ለመድረስ እንኮኮ መደራረግ ነበረብን ። ወይ መንሠላል መፈለግ ግን ጊዜ የለንም ።

ጠይሜን እንኮኮ አደረግኩት ። በፓኮ የያዛቸውን ትንኳሾች ኮሌታቸውን ከፊት አድርጎ ጨመረባቸው ። በትንኳሾቹ ንክሻ ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ሮጠን ተደበቅን ። ተቁነጠነጡ ። ጮኹ ። ሰዎች ሲሰበሰቡ እኛም ተቀላቀልን የሚሆነውን ማየት ጀመርን ። ኡኡታቸውን ሰምተው አባቴና ጓደኞቹ ተሯሩጠው መጡ ።

« ምን ሆንክ ለማ ?» አሏቸው አባቴ

« አባካችሁ ! ተቃጠልኩ...ፍቱልኝ ይኼን ገመድ ።»

« የምን ገመድ ?»

« ዓይንህ አያይም ? የታሠርኩበትን ነዋ !» ቆነጠጧቸው መሠለኝ አባቴ ላይ ጮኹበት

« ማነው ያሠረህ ?»

«ሌቦች ናቸው ! እኔን እዚህ አስረው ቤቴን ሊዘርፉ ሄደዋል።»

« አስረውህ የሄዱት ሌቦች መሆናቸውን በምን አወቅህ ?»

« ዘረፉኛ ! አቃጠሉኝ ! ቤንዚን አርከፍክፈው ክብሪት ጫሩብኝ ። ነደድኩ ! አባካችሁ ተቃጠልኩ ፍቱኝ ። ኧረ! አሲድ ነው መሠለኝ የደፉብኝ ።» ተፈራገጡ ።

« እሠይ ! ቅጥል ...ንድድ በል ! ገዝተህ የጠጣኸው አሲድ ነው የሚያነድህ ። ተው ስትባል የማ ትሠማ ደነዝ !» አባባ ታምራት ተሳደቡ ።

« ዛሬ ነው እንዴ መቃጠልህ የታወቀህ ?» እማማ ጀማነሽ ምላሽ ላያገኙ ጠየቁ

« ጀርባቸውን ከግንዱ ጋር እያፋተጉ ታገሉ ።»

« ይበቃዋል አንፍታው መሠለኝ ። መቼም ሰው ከሆነ ካሁን በኋላ ስካርን አይደግመውም ።» አለ አባቴ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

« አዎ ! ፍቱኝ እባካችሁ ! አሲዱ አነደደኝ ። በፈጠራችሁ ! ከነ ልብሴ ወስዳችሁ ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ዘፍዝፉኝ ። ኧረ ! መብረቅ ነው መሠለኝ የመታኝ...ወይኔ ! ወይኔ ! እባካችሁ ነደድኩ! ተቃጠልኩ ። ቆይ...እኔ ብሞት ምን ትጠቀማላችሁ ? ኧረ እባካችሁ በልጆቻችሁ ! ኧረ በሚስቶቻችሁ !» ለፈለፉ ።

« አዎ ! አንት ገልጃጃ አታግባና እንዲሁ ልጅና ሚስትን ለመማፀኛ እንደተጠቀምክ ዕድሜህን ጨርስ !» እማማ ጀማነሽ የተናደዱ ይመስላሉ ።

ጋሽ ለማ እማማ ጀማነሽን ገላመጧቸው ። ሰውነታቸውን ከታሠሩበት የስልክ እንጨት ግንድ ጋር እያስታከኩ ታገሉ ። ሲብሰባቸው እንባ አውጥተው አለቀሱ ። ማልቀሳቸው እግራቸውን አስፈታላቸው ። ተቁነጠነጡ ፤ ተፈራገጡ ።

ልጅ ልጆቹ ተንፈቅፍቀን ሳቅን ። ትልልቆቹም ገሚሶቹ መገለጫቸው በሆነው ሳል ታጅበው ሳቁ ። ከብዙ መሀላ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ከእስራት ነፃ ወጡ ። መሬት ረግጠው መቆም አልቻሉም። መሬት ላይ ተዘርፍጠው ልብሶቻቸውን ተራ በተራ እያወለቁ ጣሉ ። ልብሳቸው በትንኳሽና ዘመሚት ተወርሯል ። ተሠብስበው ሲስቁ የነበሩት ሁሉ ደነገጡ ። በተመለከቱት ነገር ደስተኛ ያልነበሩ ሰዎች በነ አባቴ ላይ አጉረመረሙ ።

የጋሽ ለማ ጥቁር ገላ አባብጧል ። ከእግር እስከ አንገታቸው በነፍሳቱ ንክሻ ድብድብ ብሏል ። ሰዎች ተራ በተራ ከልብሶቻቸው ላይ ትንኳሾቹን አራገፉላቸው ። ፀብ፣ ትርምስ ፣ሳቅ በምናፍስበት ሜዳችን ነገሰ ።« ጎሽ ! ደግ አደረጉ !» እያሉ እነ አባቴን ያሞገሷቸውም አልጠፉም ።

« ምን አገባቸው ? ባፉ ቀርቶ በቂጡ...እንደፈለገ ቢጠጣስ ? ገዝቶ እንጂ ሠርቆ አልጠጣ !» እቴነሽ ተቆጣች ።

« እነሱስ እነማን ሆኑና ሠካራምን የሚቀጡ...እግዚአ ጭካኔ ! እንዴት ታደርገኛለህ ?» አሉ የነፍስ አባታችን አባ ግርማ ወደ ሰማይ አንጋጠው ።

« ይኼስ የጭንቅሎ አባት...እሱን ብሎ ሠካራም ቀጪ ! ጠግቦ እየገባ አይደል እንዴ ልጁን በርበሬ የሚያጥን ፣ ምስኪን ሚስቱን በከዘራ የሚቀጠቅጥ...የለየለት አረቂያም ። እንደው እነሱን ነበር እንዲህ አስሮ በትንኳሽ ማስበላት !» አለች እቴነሽ ። አባቴ በእቴነሽ ሲሠድብ ተናደድኩ ። ቀስ ብዬ ተጠጋኋትና አንድ አምስት ትንኳሾችን በውሃ ርሶ በተራመደች ቁጥር እንደ ፈስ ጡጥ ጡጥ በሚለው ኮንጎ ጫማዋ ውስጥ አስገባሁላት ። ዘለለች ። ከስሯ ላጥ አልኳ ።

« እኔኮ የገረመኝ የጀማነሽ ማጨብጨብ...ሊያገባኝ ነው ብላ አስወርታበት ስትጠግብ አላገባሽም ስላላት በሠበብ ልታስገድለው ፈልጋ'ኮ ነው !» አለች አሽሙረኛዋ በለጡ ።

ጀማነሽና በለጡ በስድብ ተለጣለጡ ።

ውክቢያው ተዝቀዝ ያለው ጋሽ ለማ ወደኛ ቤት ሲወሠዱ ነበር ። አባቴ ገላቸውን አጥቦ



@BOOKALEM

አስተኛቸው ። አባቴና ጋሽ ለማ የአንድ አካባቢ ልጆች ስለሆኑ ይዋደዳሉ ።

ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ነገር መጣ ። «ኪሴ ውስጥ የነበረ ገንዘብ ጠፍቶብኛል መልሺ !» አሏት እናቴን ። እናቴ ተናደደች ። ባላደረገችው መጠርጠሯ አስከፋት ። ቀበሌ እንደሚከሷት ገለጹላት ።

« ቀበሌ ? ቀበሌ ያንተ ቢጤ አምቡላም እንጂ እግዚሀር የተቀመጠ መሠለህ እንዴ !» እናቴ ተና'ዳለች ።

አባቴ ጣልቃ ገባ ። ጋሽ ለማ ሊረጋጉ አልቻሉም ።

« ለመሆኑ ስንት ብር ነው የጠፋብህ ?» አላቸው አባቴ በርጋታ

« ሃያ አምስት ብር !»

« እውነትከን ነው ለማ ?»

« ምን ልጠቀም እዋሻለሁ ታድያ !»

« እርግጠኛ ነህ እንደዚያ ሠክረህ እንኳንስ የነበረህን ቀሪ ብርና እራስህንስ ታውቅ ነበር ?»

« እንዴት አላውቅም ? መጠጣት ለኔ ብርቄ ነው እንዴ ?»

« ለመሆኑ ስልክ እንጨቱ ላይ ያሠረህ ማን እንደነበር ታስታውሳለህ ?»

« ማንን ?»

« አንተኑ ነዋ !»

« መቼ ?»

« ይኼንንም አታስታውስም ?»

« ይልቅስ ብሬን ከሚስትህ ላይ ታስመልስ ከሆነ አስመልስልኝ ። ያበድኩ መሠለህ እንዴ ታስረህ ነበር የምትለኝ ። ያለዚያ...አታሠጠኝ እንደሁ ልሂድ !» መንገድ ጀመሩ ።

« ምን ታስፈራራኛለህ ? እከስሻለሁ ብለህ የለ እንዴ ?...ሂዳ ሩጥ አንካሳ ዶሮ ሳይቀድምህ ! እኔ የጭንቅሎ እናት እንኳንስ ከእንዳንተ ዓይነት አምቡላም ቀርቶ ከማንም አልሠርቅም ።» እናቴ እጇን እያወዛወዘች ተሳደበች ።

« እሺ ! ችግር የለም ። እኔ ብርህን እሠጥሃለሁ ። ብሩን ከመውሠድህ በፊት ግን እጅህን መፅሀፍ ቅዱስ ላይ ጭነህ ትምልልኛለህ?» አላቸው አባቴ መፅሀፍ ቅዱስ እያቀረበ ።

ሲምሉ ገረሙኝ ። አባቴ እጁን ወደ ኪሱ ልኮ የገንዘብ ቦርሳውን አውጥቶ ከፈተው ።«አንድ፣



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

ሁለት...» ብሎ ቆጥሮ ሃያ አምስቱን ብር አስረከባቸው ። ተናደድኩ ። ለዓመት በዓል ሰልባጅ የማስገዛበትን ብር ጋሽ ለማ ሲወስዱት ሳይ አረርኩ። ብሩን ይዘው ከቤት ሊወጡ ሲሉ በሩን ዘጋሁባቸው።

« ምነው ጭንቅሎ በሩን ልቀቅለት እንጂ ?» አለኝ አባቴ

« አልለቅም !»

« ለምን ?»

« ውሸታቸውን ነው ሃያ አምስት ብር አልነበራቸውም ።»

« ስንት ነበራቸው ታድያ ?»

« አራት ብር ብቻ !»

« እንዴት አወቅክ ?»

« እኛ ነና ከኪሳቸው ገብተን ብሩን ያወጣንባቸው ።»

« ኸ ! መቼ ?» አባቴ አፉን በእጁ ከደነ ።

« ታስረው የነበረ ጊዜ ።»

« ለመሆኑ አብረውህ እነማን ነበሩ ?»

« ጠይሜና ጠምቤ ።»

« እሺ ! አሁን ብሩ የታል ?»

«ይኸው ! እኔጋ ያለው ይኼ ነው !» አንድ ብር ከሰላሳ ሰጠኹት ።

« ሌላውስ ?»

« ጠይሜና ጠምቤ ጋር ።»

« ለምን ዘረዘራችሁት ?»

« ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ልንሠጣቸው ።»

« ነ...ው ? ከእንቅልፉ ሲነቃ ልትሠጡት ?»

« አዎ !»

የአባቴ ጥፊ ጆሮዬን አጠፈጠፈው ። የአሮጌ ቦቲ ጫማውን ቁጥር ሆዴ ላይ አተመው ። ሆዴ ወደ ውስጥ ተሠርጉዳ የገባች መሠለኝ ። ትንፋሽ አጠረኝ ። ወለሉን ተንደባለልኩበት ። እያከታተለ



@BOOKALEM

ቀቡቶውን ጀርባዬ ፣ ታፋዬ ፣ ቂጤ ...ብቻ እጁ የደረሰበት የአካል ክፍሌ ላይ ሁሉ አሳረፈው ::

የእናቴን ጣቶች ጭኖቼ መሀል አገኘኋቸው :: የተለመደ ሚጥሚጣ የሆነ ቁንጥጫዋን ያለ ፍላጎቴ ተቀበልኩ :: ማንን ልከላከል ? የማንን ቅጣት ልቋቋም ? ሁለቱም ነደዋልና የሚያበርድ የለም :: እናቴ ባልሠራችው መጠርጠሯ ፣ በኔ በከንቱ መመካቷ ፣ አባቴም ያልጠረጠረው ሆኖ ሲገኝ ድርጊቴ አንጀቱን አደበነው :: ለመናደዱ ምክንያት እኔ ነበርኩና እጁ እስኪዝል ወቀጠኝ ::

በእናትና አባቴ ላይ ቂም ቋጠርኩ :: ለሁለት ተባብረው ስለወገሩኝ ተናደድኩባቸው :: ሌላ ጊዜ «አትዋሽ ፣ አትካድ ! ከህደት ነው ኢየሱስን ያስገደለው !» እያሉ ይቀጠቅጡኝ ነበር :: ቃላቸውን ልጠብቅ እውነቱን ብናገር አሹኝ :: ቂሜን የምወጣበትን ዘዴ ሳሰላስል ቆየሁ :: ወደ ጓሮ ሄድኩና ከበጎቹ ቤት ጎን ያለውን ጠፍጣፋ ድንጋይ ገለበጥኩት :: ከድንጋዩ ሥር ያገኘኋቸውን ቀያይ ዘመሚቶችና ጥቋቁር ትንኳሾች በክብሪት ፓኮው ውስጥ ጠቀጠቅኳቸው :: ወደ ቤት ገባሁና የክብሪት ፓኮውን በወረቀት ጠቅልዬ በክር ጥፍንግ አደርጌ አሰርኩት ::

አድፍጬ የሚተኙበትን ሰዓት ጠበቅኩ :: እኔና መሳይ ተለያይተን ነበር የተኛነው :: የተለያየንበት ምክንያት ደሞ « ከሌባ ጋር አልተኛም :: እናትና አባቱን የሚያሰድብ ሌባ ወንድም የለኝም !» በማለቷ ነበር :: የሁሉንም በእንቅልፍ መወሠድ ካረጋገጥኩ በኋላ የክብሪት ፓኮዬን ይዤ ወደነ እማዬ አልጋ ተጠጋሁ :: ቢነቁብኝም የሌሊት ሽንት ማጠራቀሚያ ፖፖዋቸን አልጋቸው አጠገብ ስለሚቀመጥ ለሽንት መነሳቴን እናገራለሁ :: ከዚያ ቀስ ብዬ በጭለማው እየዳበስኩ በትራስጌያቸው በኩል ትንኳሽና ዘመሚቶቹን ነሥነስኳቸው ::

መኝታዬ ውስጥ ተጠቅልዬ ማዳመጥ ጀመርኩ :: ድምፅ ሲጠፋ መሬት ላይ የደፋኋቸው መሠለኝ :: መሬት ካረፉ ደሞ የተኛሁት መሬት ተነጥፎልኝ ነውና አለቀልኝ :: ባጠመድኩት ወጥመድ እንዳልጠመድ ፈራሁ ::

ጀሮዬ ከተሳከበት የነ እማዬ አልጋ መልዕክት ይዞ መጣ :: የመንፈራገጥ ድምፅ :: መንፈራገጡ ጨመረ :: መንፈራገጡ የእማዬ ድምፅ ተጨመረበት ::

« እማምላክ ድረሽ ! ደሞ ምን ልሁን ብለህ ነው በውድቅት ሌሊት ጭኔ ውስጥ ገብተህ የምትቆነጥጠኝ ?» አለችው እማዬ ከጣራ በላይ የሚያንከራፋውን አባቴን ::

በመሸወዷ ፈገግ አልኩ :: ሁለቱ የኔ ጠላቶች እርስ በርስ ሊጣሉልኝ ስለሆነ ደስ አለኝ :: መሳይም ከእንቅልፏ ነቃች ::

« ልተኛበት እንጂ ምን ትንፈራገጪብኛለሽ ?» ሲል የነበረው አባዬ መብራት አብርቶ መገለል ጀምሯል :: እማዬም ከአባዬ ላይ ትንኳሾቹን እየለቀመች የራሷ ሲመዘልጓት ትነጥራለች ::

« ያ አምቡላም ነው ቤቴ ውስጥ ዘርቷቸው የሄደው !» አለች እማዬ ጋሽ ለማን ሰበብ አድርጋ:: ተመሰገን ከመጠርጠር ዳንኩ ::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ሁለቱም ትንኳሽና ዘመሚቶቻቸውን ሲለቃቅሙ ፤ ሲዘልሉ እኔና መሳይ እንስቅባቸዋለን። «የትልቅ ሰው ጭፈራ » እየተባባልን እናለምጥባቸዋለን ። እንጀቴ ቅቤ ጥጥት ። ለሁለት ተጋግዘው እንደደበደቡኝ እኔም በትንኳሾቼ አስወገርኳቸው ። አባዬ እራቁቱን ቁምጣውን እንደለበሰ እደጅ ወጣ ። « ተው አንተ ሰውዬ ንፋስ ይመታሃል !» ስትል የነበረችው እማዬ ልብሷን አውልቃ ጊታሯን መምታት ጀምራለች ። ዕድሜ ለጓደኛዬ ለጠይሜ ይቺን ዘዴ ባይነግረኝ እንዴት አባቴ አድርጌ ቂሜን እወጣ ነበር ? ኡፍ ! አባዬን አስለቀስኩት...የታባቱ ! እሱስ ሳለቅስለት « የታባክ!» አይደል የሚለኝ ።

ጠይሜ ጋሽ በቂ ሲወግሩት ሲወግሩት እየጠበቀ በትንኳሽ ሲያስነክሳቸው ያድራል ። የሌሊት አዘላለላቸውን እያሳየን ሳቅ ይጋብዘናል ። እኔም ሲነጋ ለጓደኞቼ ጥቂት ውሸት ጨማምሬ የማወራላቸው አስቂኝ አዘላለል አገኘሁ ።

ጋሽ ለማ መስከር አይሰለቻቸውም ። መጠጣት አይደከማቸውም ። ኳስ መጫወቻ ሜዳችን ላይ ከገቡ በግድ ተገፍተው ካልሆነ አይወጡም ። እግራቸው ችሎ ኳስ ላይመቱበት እየሠነዘሩት እየወደቁ ይነሳሉ ። አውቀን ኳስ እናቀብላቸዋለን ። ኳስ ሊመቱበት የሠነዘሩት የቀኝ እግራቸው ቆሞ ጠባቂውን የግራ እግራቸውን ይመታባቸዋል ። በገዛ እግራቸው እግራቸውን ጠርበው ሲያበቁ ፊታቸው ኳስ ይዞ የተገኘውን ሰው « ለምን መታኸኝ ?» ብለው ያፈጡበታል ። ሲያንቁት ያሳድዱታል ።

አንድ ቀን የኛ ታላላቆች በሠፈር የእግር ኳስ ግጥሚያ ነበራቸው ። ሞቅ ደመቅ ብሎ ለየሠፈራችን ቡድኖች ድጋፋችንን በጭብጨባና ፉጨት እንገልፃለን ። እንዘምራለን ። ጠይሜ ግጥምና ዜማ ያወጣል ፤ እኛ እንቀበለዋለን ።

«እህህ እህህ

እህህ እህህ እህህ

የሽምብራ ገንፎ...እህ

የጤፍ አሹቅ የለም

የሽምብራ ገንፎ ...እህ

የጤፍ አሹቅ የለም

ምንም ብንዋደድ... እህ

በ'ግር ኳስ ቀልድ የለም ።

እህህ እህህ

እህህ እህህ እህህ !»



@BOOKALEM

ይህኛው ዘፈን ሲሰለቻው ደሞ ሌላ ይዘፍናል ።

« ኤያ...ቼቼ ባሬላ ባሬላ

ኤያ ...ቼቼ ባሬላ ባሬላ

የቀላድ ልጆች ...ባሬላ

አሚጭሮቹ ... ባሬላ

ጎል ለማስገባት ...ባሬላ

አቤት ሲመቹ ...ባሬላ

ኤያ ቼቼ ባሬላ ባሬላ ...»

ታድያ እንዲህ ሞቅ ደመቅ ያለውን ጨዋታችንን ጋሽ ለማ መጡና አደበዘዙት ። ቢለምኑ ፣ ቢለምኑ ከሜዳችን አልወጣ አሉን ። ጎረምሶቹ ተናደዱና ተሸከመው እቤታቸው አደረሷቸው ። ጨዋታው ቀጠለ ። የጠይሜም ዜማ ቢጫ ሜዳን በድጋሚ አቀለጣት ።

« ነይ ርግብ ነይ ርግብ

ነይ ርግብ ...አሞራ

ነይ ርግብ አሞራ ።

ጎሉን ከሚያስገባው

ነይ ርግብ ...አሞራ

ነይ ርግብ ...አሞራ

ከቀላድ ልጅ ጋራ

ነይ ርግብ ...አሞራ

ነይ ርግብ አሞራ ...»

ብዙም ሳይቆዩ ጋሽ ለማ ከዘራቸውን ይዘው እየተንገደገዱ መጡ ። ሁላችንም ስንሸሻቸው ጎረምሶቹ ከብብ አድርገው ለመኗቸው ። ልመናቸውን ከፍርሃት ቆጠሩባቸውና ለመማታት ሞከሩ። ሜዳችን ውስጥ ሽንታቸውን ሸኑ ። ከኪሳቸው ቢራ እያወጡ ሜዳ ውስጥ እያየናቸው፣ ሞራል እየሠጠናቸው ጠጡ ። ጠርሙሱን ሜዳው ውስጥ ሠባበሩት ። ጎረምሶቹ ተናደዱና ከዘራቸውን ነጥቀው ድጋሚ ያለ ወሳንሳ ተሸከመው ቤታቸው አደረሷቸው ። በተለይ ሁለት ለአንድ እየተመሩ የነበሩት የኛ ተቃራኒ ቡድኖች እርር አሉ ። ሰውዬውን መማታትም ቃጣቸው ።



@BOOKALEM

የጨዋታው መደበኛ ሰዓት በአቻ ውጤት ተጠናቆ በፍጹም ቅጣት ምት ለመለያየት ዳኛው የመጀመርያ መቺና ቀላቢዎችን ወደ ሜዳ ሲያስገባ ጋሽ ለማ ለሦስተኛ ጊዜ ተመልሰው መጡ ። ሌላ ረብሻ አነሱ ። የጎረምሶቹ ንዴት ጨመረ ። ጋሽ ለማን ተሸክመው ወደ ቤታቸው ወሠዷቸው። ከዚያ እርኩሱ ሰለሞን መንገድ ላይ ያገኘውን የሕፃን ልጅ አር በስንጥር ቆንጥሮ አፍንጫቸውን ለቀለቃቸው ። ሳቅን ። ከዚያ ቤታቸው አስገብተው በግድ አልጋቸው ላይ አስተኟቸውና በራቸውን ከውጭ ቀረቀረባቸው ። በሩን ደብድበው ፣ ደብድበው ከፋች ሲያጡ እንቅልፍ ወሠዳቸው ።

ምሽት አካባቢ ተሰባስበን ወደ ቤታቸው ሄድን ። ከእንቅልፋቸው ተነስተው በመስኮት በኩል እንገታቸውን ለማውጣት ሲታገሉ አገኘናቸው ። መስኮታቸው በጋቢዮን ሽቦ የተከለለ ነው ። ለማየት ካልሆነ ለመሹለክ አይመችም ።

« ልጆች !» አሉን እንዳዩን

« አቤት !» በጋራ ጥሪያቸውን ተቀበልን ።

« ኧረ ! ቤቴ ሳይበላሽ አይቀርም ።»

« ምን ሆኖ ?» ሰለሞን ጠየቃቸው

« እንጃ ! ብቻ ጥሩ ያልሆነ ሽታ ይሸተኛል ።»

« ምን ዓይነት ሽታ ?» እኛ ስንስቅ እሱ ኮስተር ብሎ ያዋራቸዋል ።

አፍንጫቸውን በላይኛው ከንፈራቸው እየደፈኑ ሽታውን ለመከላከል ይጥራሉ ። በሩን ሰለሞን ከፈተላቸው ። ቤታቸውን ከዳር እስከ ዳር አሠሡት ። ምንም አጡ ። ገብተን የሚሸተውን ነገር እንድንፈልግላቸው ጋበዙን ። ምንም እንደሌለ እያወቅን ፈለግንላቸው ።

« ልጆች ! ምንም አይሸታችሁም ?»

« ኧረ ! ምንም አይሸተንም !» በጋራ መለስንላቸው ።

« ና ! እስቲ ጭንቅሎ...መቼም ይኼን የመሠለ ጠፍጣፋ አፍንጫ ይዘህ ካልሸተተህ ጉድ ነው...እዚህ ጋ ምንም አይሸትህም ?»

« ኧረ ምንም አይሸትም !»

« እውነትከን ነው ጭንቅሎ ?»

« አባቴ ይሙት ! ምንም የሚሸት ነገር የለም ።»

«አዬ ! ይኼን የአያትከን ወጭት የሚያክል አፍንጫ ተሸክመህ የምትዞረው ያለ ስሜት ነዋ !» ሲሉ አለመጡብኝ ።



@BOOKALEM

ልጆቹ ሳቁብኝ ::

« እናንተስ ምንም አይሸታችሁም ?» ልጆቹን ጠየቁ

ሽተተኝ የሚል አጡ :: አልጋቸውን ገለጡት :: አንሶላቸውን ፤ ብርድ ልብሳቸውን ፤ ጫማዎቻቸውን ፤ የመመገቢያ ዕቃዎቻቸውን ፤ ልብሳቸውን ፤ የውሃ መጠጫ ብርጭቋቸውን ሁሉ አሸተቱ :: ሁሉንም ሲያሸቱ ግንባራቸውን አኮሳተሩ :: ያሸተቷቸውን ዕቃዎች በሙሉ ወደ ደጅ አውጥተው ወረወሩ :: ወደ ጓሮ ዞሩ :: ፈጠን ፈጠን እያሉ ተመለሱ :: ደግመው ደጋግመው ምራቃቸውን እየተፉ አፍንጫቸውን ያሻሹ ::

« ልጆች ምንም አይሸታችሁም ?»

« ይኸው ! ቤቴም ዕቃዬም ተበከሏል :: እኔ ቤቱ የተበላሸ መስሎኝ ነበር :: እደጅም ብወጣ ሽታው ተከትሎኛል ::»

« እርስዎ የሚሉት ሽታ እኮ እኛ ጋር የለም !» ጠይሜ ነበር ያናገራቸው

« ዝም በል ወዲያ...አፍንጫ ቢስ ! ይልቅስ አፍንጫዬ አይሠራም አትልም :: የግም ዓለም ግም ልጅ ...ድሮስ ግም ሆነህ መች ግማት ይሸትህና ! እናንተ የዚች ግም ዓለም ግም ልጆች አፍንጫችሁ ነገርን እንጂ መች ጠረንን ለመለየት ታደለና ! ጠይሜ እየሰማኸኝ ነው...ዓለም ገምታለች :: እነሆ ገምታ መሠለኝ መተኛ ማረፊያ የነሳችኝ :: እ...ፍ !»

ሁላችንም ሳቅን :: አፍንጫቸው ላይ የተቀቡትን እር ሳይጠርጉ « ዓለም ገምታለች » ሲሉ ገረመን ::

ሰለሞን ልብስ አጣቢዋን ሰብለን እንዲጠራላቸው አዘዙት :: እሱ ግን ብሩን ከከፈሉን በቤቱ ያለውን ልብስና ዕቃ በሙሉ ተጋግዘን እንደምናጥብላቸው ነገራቸው :: አስቀድሞ ገንዘብ ተቀበላቸው :: አምስት ብር ሠጡት :: ውሃና ሳሙና ይዞ ተጠጋቸውና « ዕቃ ማጠብ ከመጀመራችን በፊት ፊትዎን ይታጠቡ !» አላቸው ::

ታጠቡ ፤ ፀዱ :: የዓለም ግማት ጠፍቶ የሰለሞን ተንኮል መሆኑ ገባቸው :: አየሩን ሳብ ሳብ አደረጉት :: ድንጋይ አንስተው አራወጡን :: ከዚያ ወዲህ የፒያ የሠካራሙ ጋሽ ለማ ቅፅል ስም «ዓለም ገምታለች !» ሆነ :: እይ ጋሽ ለማ ተሸወዱ :: የዓለምን ግማት በአምስት ብር ከአፍንጫቸው ላይ አፀዳንላቸው ::



@BOOKALEM

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## ከእብደት በስተጀርባ

« መቶ አለቃ !»

ይህን ጥሪ አይወደውም ። እንዲህ ብሎ የጠራውን ሰው ከአፉ ስድብ ከእጁ ድንጋይ ያቀብለዋል ። ሰውዬው በቁም ነገር ቁጭ አድርገው ላወያዩት ቁም ነገረኛ ይመስላል ።

በሥርዓተ ደርግ ውስጥ የሺህ አልቅና ማዕረግ አግኝቶ እነደነበር ይወራል ። ማዕረጉን አግኝቶ የአንድ ወር ደመወዝ ሳይበላበት ኢህአዴግ ሀገሪቱን ተቆጣጠረ ። ኢህአዴግ ሀገርን ያክል ታላቅ ርስት ሲቆጣጠር እሱ ግን ሀገር ፈጣሪዋን አንዲቷን ሚስቱን መቆጣጠር ተሳነው። ደርግ ያሠለጠናቸው ወታደሮች በጠቅላላ ከየተሸሸጉበት እየተለቀሙ ሁርሶ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ ለተሀድሶ ሥልጠና በኢህአዴግ ሠራዊት ተግበስብሰው ተወሠዱ ። ለሁለት ወራት ያክል ማሠልጠኛው ውስጥ ከርመው ሲመለሱ በጣት ቀለበት የታሠረች ሚስቱ ማሠርያዋን ፈትታ ቆየቻው ።

የሚወድላትን የቀድሞ ፈገግታዋን ነሳችው ። « መሸቆጥቆጥ ያኔ ደርግ ሳለህ ቀረ !» አለችው። መታዘዝ ፣ ትህትና ፣ለባል መሠጠት የሚገባው ሰዋዊ ክብር ፣ ታማኝነት ከውስጧ ብን ብለው ሸሿት ። ትዕግስት አልባ ሆነች ። መኖርያ ቤቷን ያልተቀላቀለ ባል አግብታ ጠበቀችው ። እንደ ቅዱሳን በስም እንጂ በአካል ያልተገለፀ ባል ። የኢህአዴግ ደርግን ማሸነፍ ማዕረጉን ብቻ ሳይሆን የባልነት ድርሻና ክብሩንም ገፈፈው ።

በደሏ በዛበት ። መኝታዋን ለየች ። ለሷ አልጋ ለሱ መሬት አነጠፈች ። ለአንደበቱ ፍሬዎች ቅን መልስ መስጠት አቆመች ። ቤቱን ትቶ እንዲወጣላት የተለያዩ ዘዴዎችን ሞከረች ። የቀደመ መሽቆጥቆጥና መንቀጥቀጧን በንቀት ተካችለት ። በንቀት የተኮተኮተው አዲሱ አመሏ ስድብ አበቀለ ። የዕለት ተዕለት ስድቧ ሃሳብ በውስጡ እያብከነከነው መላ ቅጡን ያሳጣው ዘንድ መንገድ ጠረገለት ። በሷ ላይ የነበረው እምነትና ተስፋ ከአፍቃሪው ልቡ ብን እያለ እያደር ሲጠፋ ተሠማው ።

ምግብ ሠርታ አታቀምሰውም ። በጠዋት ተነስታ እያየውና እየሸተተው የሠራችውን ምግብ ምሳዋን በሠሀን ቋጥራ ፣ ቁርሷን ጠራርጋ በልታ የበላችበትን ሠሀንና የሠራችበትን ድስት እንዲያጣጥብ ትዕዛዝ ሠጥታው ትሄዳለች ። እሷን ለማለዘብ የታዘዘውን እየተራበ ይሠራል ። እየተሰደበ የቀድሞ ፍቅሩን ሊያስመልስ ይታገላል ።

ቁንጅናዋን ተማምና ቀንጆ ሥልጣን የነበረውን ባሏን ጠላችው ። አብሯት የሚሠራ አለቃዋ የሆነ ሌላ ጎረምሳ ባለሥልጣን መጥበሿ በሠፈሩ ተወራባት ። « ብዙ ባሎች አግብታ ታተረማም



@BOOKALEM

ሳቸዋለች !» ተብሎ ስሚ ለእናቶቻችን ቡና ማጣጫ ቁርስ ሆነ ። ወሬው ከዕለት ዕለት ዓይነ ቱን እየለዋወጠ ከጆሮው ይደርሳል ። በራሱ መንገድ ተጉዞ ነገሩን ማጣራት ጀመረ ። ወሬው እውነት ሆኖ አገኘው ። እውነታው ለሚስትየው ባል ፣ ለሱ ፣ ለተፈናቃዩ ሻለቃ ደሞ እብደ ትን ለገሰው ።

የመሥርያ ቤቱ ፀሐፊ ሆና ሳለ ከአለቃዋ ጋር ለመስከ ሥራ ኢያለች ሳምንት አስራ አምስት ቀን የትም ከርማ ትመለሳለች ። ለጎረምሳው አለቃዋ የሞያዋ ብቻ ሳይሆን የገላዋም አዛዥ መሆኑን አብራ በመከረም አረጋገጠችለት ። «እፍ ኪድን» የሚሉት ዓይነት ፍቅር ውስጥ የገባችው ሴት ሻለቃውን አሳፈረችው ። እንደ ቀልድ « ፈትቼሃለሁ !» አለችው ። ቤቷን ለቅቆ ወደፈለገበት ቢሄድላት እንደምትመርጥ ያለጥርጥር ነገረችው ። ጭቃ አቡኪቶ ፣ ውሃና አፈር ከቀን ሠራተኞች ጋር ተሸክሞ የሠራው ቤት በአፍታ ከ«የኛ»ነት ወደ «የኔ»ነት መለወጡ አስበረገገው ።

« አለኝ !» የሚለውን ትዳር በነበረበት ሲያጣው እንጎሉ ተቃወሠ ። አስተሳሰቡ ተዛባ ። በፍቅር ገንብቼዋለሁ ብሎ የተማመነበት ትዳሩን ካስቀመጠበት ፈልጎ አላገኘውም ። ሆን ብላ በበደሏ ገፋችበት ። ሌላ ባል ልታገባ መሆኑን በድፍረት ነገረችው ። ቤቷን ለቆ እንዲሄድላት አስ ጠነቀቀችው። እራሱን መቆጣጠር ሲሳነው ፊት ለፊቱ ባገኘው ጠርሙስ ከፉ ሃሳቧ በቅሎበታል ብሎ ያመነበትን ጭንቅላቷን ቦተረፈላት ።

ፖሊስ መበደሉን ፣ መገፋቱን ረስቶ አሰረው ። « ወንጀል በወንጀል አይታረምም !» አለው። ብዙም ሳይቆይ ከእስር ቤት ተለቀቀ ። የተለቀቀው ግን ጤናውን ተነጥቆ ነበር ። ብቻውን የሚያወራ ፣ ጫማ የማያደርግ ፣ ጢምና ፀጉሩን መከርከም የጠላ ፣ ሲያሰኘው ልብሱን አወላልቆ እንደተፈጠረ እየለፈለፈ ከተማውን በዙረት የሚያካልል ሰው ሆኖ ነበር ሻለቃ ተወልደ ብርሃን ።

ከዚህ ሁሉ ችግር በኋላ ማበዱን ብንሰማም ለከንፈራችን በሳቅ መገለጥ የራሱን አስተዋፅዖ ስለሚያበረክት ከማብሸቅ ወደ ኋላ አንልም ። ሠበብ ፣ ኢጋጣሚና ቦታ እየጠበቅን እንዲያሯሩጠን እንለከፈዋለን ። ካልነኩት የማይነካ ቂም የማይቋጥር ሰው ።

ከኛ ጋር እኩል መሬት ላይ ተረፍቆ ጎርፍ ባመጣው ደለል አፈር ይጫወታል ። እንደኛ እግሩ ላይ እርጥብ ደለል አሸዋ እየቆለለ ቤት ይሠራል የአፈር ፣ የዕቃ ዕቃ ቤት ። የሠራውን ቤት አተኩሮ ይመለከተዋል ። የአፈሩ ቤት ቀስ ቀስ እያለ ይፈራርሳል ። ይኼኔ እንባው ከዓይኖቹ ዱብ ዱብ ይላል ። ለቤቱ መፍረስ ምክንያቱ ሚስቱ እንደሆነች ሰሚው ለሆነው ለቤቱ ይነግረዋል ። የፈረሠውን መልሶ ለመገንባት እግሩን በደለል አፈር ይሸፍናል ።

« አይ የሰው ልጅ መጨረሻ ! በቃ ያንተ ነገር እንዲህ ሆኖ ቀረ ሻለቃ ?» አሉት ሻምበል ወንድሙ አለቃቸው ነበር ።

« ምን ሆንኩ ? ምን ስሆን እየኸኝ ?» ከተቀመጠበት ተነሳ ።

«ኧረ ! ምንም አልሆንክም ። እንዲያው መጨረሻህ ከልጆች ጋር በአፈር መጫወት መሆኑ ቢያስከፋኝ ነው አለቃዬ !»



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

« እንኳን ከፋህ...እንኳን ደስ አለኝ...እሰይ ደግ ! እኔን ያስደሰተኝ ነገር አንተን ቢያስከፋህ እኔ ምን ጨነቀኝ ! ምን አገባኝ !»

«ለመሆኑ ምሳህን በልተሃል?» እጃቸውን ወደ ኪሳቸው እየከተቱ ጠየቁት ::

« ሲጋራ የማጨስበት ገንዘብ የለኝም ::»

« እሱን ደሞ ማን አስለመደህ ?»

« እግዚሀር !»

« ምን አርገው ብሎ ?»

« ይጠቅምሀል አጭሠው ብሎ ነዋ ::»

« መሬት ወርዶ ነው አጭስ ያለህ ?»

« ቀድሞውኑስ ማን ሰማይ ሰቀለውና ! ምድር ላይ ሲዞር ይዘው‑ት አይደል እንዴ ዘመዶችህ ያንጠለጠሉት ::»

« አታመጣው ፣ አታወራው የለህ ...ደሞ ስለሱ መመራመር ጀመርክ ?»

« ሲጀመር ...ሲጋራ የሆነች ሚስት ማን ፍጠር አለው ?»

« የሷንስ ነገር ተወው ...ቆይ ግን ለምን አትረሳትም ?»

ዝም አለ ::

« እየጠየቅኩህ ምነው ዘጋኸኝ ሻለቃ ?»

« እርሳት አላልከኝም ?»

« ብዬሃለሁ ::»

« ስለዚህ እየረሳኋት ነዋ !»

« እሺ ! ና አሁን እንሂድና ምሳህን በልተህ ትመለሳለህ ::»

ዝም ብሎ መጫወት ጀመረ :: ጨቀጨቁት :: ሌባ ጣቱን አፉ ላይ ጭኖ ዝም እንዲሉ አሳሰባቸው ::

« ምነው...ምን መጣ ?» ከሹክሹክታ ከፍ ባላለ ድምፅ ጠየቁት ::

« ተኝታለች ! አትረብሻት ባክህ ዝም በል ::» ተቆጣቸው ::

«ማናት የተኛችው ?»



@BOOKALEM

« ሚስቴ !»

« የት ነው የተኛችው ?»

« ይኸው ...እዚህ ቤት ውስጥ ተኝታለች ። አትታይህም እንዴ እግሮቿን ዘረጋግታ በጀርባዋ ተኝታ ። ማንም ሰው ቢመጣ እንዳትቀሰቅሰኝ ብላኛለች ። ዝም በል አትለፍልፍ !» አላቸው ወደ ሥራው የአፈር ጎጆ እየጠቆመ ።

« እሺ ! እሷ ከእንቅልፏ እስከትነሳ ምሳ በልተህ ተመለስ ።»

« አልበላም !»

« ለምን አትበላም ?»

« ሚስትህን እርሳት አላልከኝም ?»

« ብዬሃለሁ ሻለቃ...ለውጥ ለሌለው ነገር ለምን እራስህን ትጎዳለህ እርሳት ። ምን ትጠቅምሃለች ?»

« እኮ ! አትጨቅጭቀኝ...ተወኝ ሚስቴን ልርሳበት ።»

« እኔኮ ምሳ እንብላ ነው ያልኩህ ።»

« አልበላማ ቢቃ !» ጮኸባቸው

« ለምን ?»

« ለምን ብሎ ጥያቄ ምንድን ነው ? ሚስቴን አልበላም ። ሚስቴን ከምበላ ዘላለም ተርቤ ልሙት ።»

« ሻለቃ ! ...እኔ ምሳህን እንጂ ሚስትህን ብላ አላልኩህም ?»

እነ ጠይሜ ሳቁ ። ሻምበሉ ገላመጧቸው ።

« ሚስቴ ምሳዬ ናት...እሷን ደሞ እንኳን እኔ አፈርም እንዲበላት አልፈቅድለትም ። ካሁን በኋላ ሚስቴን እንድበላት አታስገድደኝ ። ትወደኛለች ። ስትሞት እንኳን በኔ ተጠቅላላ እንጂ በሳጥን ተቆልፎባት እንድትቀበር አልፈለግም ። ምቀኞች ምሳዬን እንድበላት ትፈልጋላችሁ ። እኔ ግን በርሀብ ብሞት ይሻለኛል ።»

ሻምበሉ ድፍን አምስት ብር ከኪሳቸው አውጥተው ዳቦና ሙዝ ገዝቼ እንዳመጣለት አዘዙኝ። ተወልደ ከነ ጠይሜ ጋር ሲጫወት እሳቸው ተሰናብተውት ሄዱ ። መልስ ነፈጋቸው ። በዝምታ ራሱን በተመስጦ ውስጥ ከተተ ።

ሃያ አምስት የጠቋቆረ ሙዝ በሶስት ብር ገዛሁለት ። የአንድ ብር ዳቦ በፌስታል ያዝኩ።



@BOOKALEM

ሮንሰን የሚባል ሲጋራና ከብሪትም ሸመትኩለት ። ትራፊዋን ስሙኒ ኪሴ ከከርኳት ። እነ ጠይሚ ካልነቁብኝ በኋላ ማንጎዬን ገዝቼ እነፉባታለሁ ።

የገዛሁትን በሙሉ ለተወልደ አስረከብኩት ። አስቀድሞ ሲጋራውን ለኮሰ ። ጭሱን በአፍና አፍንጫው አቡለቀለቀው ። ሦስታችንም ዓይኖቻችንን ሙዝና ዳቦው ላይ ተከለናል ። ብናየው ብናየው አይበላም ። ትኩረቱን በሙሉ በጭሱ እየጠቀለለ ይረጫል ። ወደ አየር ፣ ወደ ሰማይ የማይጨበጠውን ጭስ እየጠቀለለ ይበትነዋል ።

«ሙዝ እኮ አሪፍ ነው ::» አለ ጠይሜ

« በጣም እንጂ !» ጠምቤ ዓይኖቿን ከዳቦና ሙዙ ሳትነቅል ምራቋን እየዋጠች መለሠች ።

« ተወልደ ሙዝኮ አሪፍ ነው አይደል ?» ጠይሜ የሰጠኝ አጠያየቋን በዘዴ አቀረበችለት ።

« አሪፍ ነው እንዴ ?»

« አዎ !» አልነው ሦስታችንም እንደሚሠጠን ተስፋ አድርገን ።

« እስቲ ንፋው !» አለው ጠይሜ እየተቁለጨለጨ ። መብላት ከጀመረ እንደሚሠጠን ርግጠ ኞች ሆንን ።

አንድ ሙዝ ልጦ ባንዴ ጎረሰው ። የኛ አፍ በምራቅ ተሞላ ። ሁለተኛውን ደገመው ። ዳቦ ጨመረበት ። ጨረጋገደው ።

« ሥጠኝ !» አለው ጠይሜ እጁን ዘርግቶ

« ሙዝ ለልጅ አይሠጥም !»

«ለምን?» ተልኬለትም ሳይሠጠኝ ብቻውን በልቶ እንዳይጨርሠው ሠጋሁ ።

« ልጅ ጡጦና እሹሩሩ እንጂ ሙዝ አይስማማውማ ::»

« ተው ስጠኝ !» አለው ጠይሜ በድጋሚ ።

የቀኝ ትከሻውን ወደ ላይ ሠብቆ እምቢታውን ገለፀለት ። ሦስታችንም ተናደድን ። ከያዘን ይገድለናል እንጂ መንትፈነው መሮጥም ሳያምረን አልቀረም ።

« እኔም ግን ነገ እንዳንተ ምሳዬን ስበላ አልሠጥህም ::» አልኩት

የነከሰውን ዳቦ ሳይገምጥ ከአፉ አወጣው ። ሙዙንም ዳቦውን ወደ ዓይኖቹ አቅርቦ ተመለከታቸው ።አፈጠጠባቸው ። ዓይኖቹ እንባ አቀረሩ ።

« ልጆች !»



@BOOKALEM

« አቤት !»

« ምንድን ነው እየበላሁ ያለኹት ?»

« ምሳህን !»

«ምሳዬን ?»

« አዎ ! ምሳህን ነው እየበላህ ያለኸው ::»

« እውነታችሁን ነው ምሳዬን በላሁ ?» ዓይኖቹ እንባ አዘነቡ ::

« አዎ !»

ሙዝ የያዘ እጁን ወደ ጠይሜ ዘረጋ :: የምንተፋ ያህል ተቀብሎት ጨረገደው :: ዳቦውን ወደ ጠምቤ ዘረጋላት ::

« በጥርሱ ነከሶታል አልበላም ::» አለች

«ጥጋበኛ ! የለማኝ ቁብራራ !» አልኳትና መንትፌያት ነፋሁት::

ዓይኖቹ እያዩ ሙዙንም ዳቦውንም ሲጥ አደረግንበት :: ፊስታሉን ጠይሜ ጠቅልሎ በኪሱ ያዘው ::

« ልጆች!»

« አቤት !»

« ምሳዬስ የታለች ?»

« ንፏት ብለህ ሠጠኸን ነፋናት ::» አልኩት

« ነፋናት ?»

« አዎና !»

« ምሳዬን_የኔን ?»

« አዎና ! ምሳህን ነፋንልህ ::» አለው ጠይሜ

« ለስንት ሆናችሁ ነፋችኋት ?»

« ለሦስት ሆነን...ጥግብ እስከንል ነፋናት !» ጥጋባችንን ለማሳየት እኔና ጠምቤ ሆዳችንን ዳበስን ::

አፈር ዘግኖ እየበተነብን አሯሯጠን :: « እናንት ርኩሶች...አንዷን ምሳዬን ለሦስት ነፋችሁብኝ!»



@BOOKALEM

እያለ ተከተለን ::

ተወልደ ቡና ይወዳል :: የፈለገበት ቤት ገብቶ ቡና አስፈልቶ ይጠጣል :: የሚነፍገው የለም:: የመቀወሱ መንስዔ ሚስቱ በመሆኗ መንደርተኛው « ዓይንሽ ሳፈር » ብሏታል :: እሱን ግን ያገኘው ሁሉ ከንፈር ይመጥለታል ::

እኛ ቤት ቁጭ ብሎ ከአባቴ ጋር እየተጫወተ ቡና ይጠጣል :: የፈለገ ቢመጣ ወንበር ላይ አይቀመጥም :: ማንም ቢለምነው «በጄ» አይልም :: ወፍራም ሸራ የለበሰችው የጥይት ሳጥናችን ደሞ ሁሌም በቡና ሰዓት የእማማ ልኬ መጋደሚያ ነች ::

« ተወልደ እስቲ ምግብ ብላ !» አለችው እናቴ እንጀራ በዱባ ወጥ እያቀረበችለት ::

ካቅሜ በላይ የሆነውን አሮጌ ብረት ድስት አቅርቤ እጁን እንዲታጠብ ውሃ ይገፍ ለመንኩት::

« አልታጠብም !» አለኝ

«ለምን አባቴ...ታጠብ እንጂ...ጭንቅሎ'ኮ ነው የሚያስታጥብህ :: ጭንቅሎን ትወደው አልነበር እንዴ ጌታዬ ?» እማማ ልኬ ለመኑት ::

« አልታጠብም ካልኩ አልታጥብም :: የምትወዱትን ሰው አሸከር አድርጉ የሚል ሕግ አለ እንዴ ? ደሞስ... በገዛ ቆሻሻዬ ምን አገባችሁ !»

« እሰይ ! ይበልሽ ... በገዛ አፍሽ !» አለቻቸው እናቴ እማማ ልኬን እየሳቀችባቸው ::

በልቶ ሲጨርስ ሠሀኑ ላይ የቀረውን ወጥ ጠራርጎ ላሠው :: ለእጁ የመታጠቢያ ውሃ እንድሠጠው ጠየቀኝ ::

« ቅድም ለምን አልታጠብም አልከኝ ?» አልኩት ውሃ እየጨመርኩለት ::

« ደፋር ! ያንተ ያልሆነ ቆሻሻን መውሠድ ያምርሃል ?»

አስታጥብበት የነበረውን የመወዘቻ ጣሳ ተቀብሎኝ ውስጡ የነበረውን ውሃ ጨለጠው :: ጢሙ ላይ ጨሌ የሠሩትን የውሃ ጠብታዎች በእጁ አባበሰና በጀርባው ተኛ ::

« እሺ ! ሻለቃ ...ኑሮ እንዴት ነው ?» አለው አባቴ

« እዚህ ምቀኛ ሠፈር ተቀምጨ ምን ኑሮ አለኝ ጌታው ?»

« ምቀኛ ደሞ ምንድን ነው ተወልድዬ ?» እማማ ልኬ ከተኙበት ቀና ብለው ጠየቁት ::

« ምቀኛ አታውቂም እሜቴ ?»

« ኧረ ! እኔ አላውቅም ::»



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

« እንግዲያውስ ...ምቀኛ ማለት እንዳንቺ ያሉት የምታውቀውን አላውቅም ብላ የምትክድ ሴት ነች ። ምቀኛ አሮጊት !» ስደባቸው ።

ከተወልደ በስተቀር ሁላችንም ሳቅን ። እኔማ እማማ ልኪ ሲሰደቡልኝ በጣም ነው ደስ ያለኝ። ምክንያቱም ሁልጊዜ በጭንቅላቴ ቅርፅ ደስተኝነት እንዳይሰማኝ ከሚያደርጉኝ ሰዎች አንዷ እሳቸው ናቸውና ። እሳቸውን በጣም ከመጥላቴ የተነሳ አንዳንዴ ቡና ጥራቸው ተብዬ ስላከ እቤታቸው እያሉ የሉም እላለሁ ።

« ለመሆኑ ምቀኞች ምን አረጉህ ሻለቃ ?» አለው አባቴ

« ቢላዋ ከለከሉኝ !»

« ቢላዋ !» አባቴ ደንግጧል ።

« አዎ ! ቢላዋ ከለከሉኝ ።»

« ቢላዋ ደሞ ምን ያደርግልሃል ?»

« በቀደም 'ለት እዚህ ታች ሠፈር አንዲት የሞተች ፍየል አግኝቼ ቢላዋ አጣሁ ። ስጡኝ እመልሳለሁ ብላቸው 'ለሞተች ፍየል ቢላዋ አንሠጥህም' ብለው ከለከሉኛ...ምቀኞች !»

« ፍየሏ በሕይወት ነበረች ?» የአባቴ አጠያየቅ መገረሙን አጉልቶበታል ።

« ኧረ ! ሞታለች ። ደሞኮ ነግሬያቸዋለሁ ።»

« ምኑን ?»

« ፍየሏ ስለሞተች ሳርዳት አትንፈራገጥም ። ካልተንፈራገጠች ደሞ ቢላዋችሁ በደም አይ ጨማለቅም ። አይዶለዱምም ። ዝም ብላ ነው የምትታረድልኝ ። በፍቃዷ ነው የምትገፈፍልኝ ብያቸዋለሁ ።»

« ግን አንተ ...ቢላዋውን ቢሠጡህ ፍየሏን ምን ልታደርጋት ነበር ?»

« በቁርጥ ፤ በጥብስ ፤ በቅቅል አድርጌ ልበላት ነበራ !»

« ያንተ ያለህ ! ምነው ተወልደ ? የሞተ ፍየል ነው እንዴ የምትበላው ?» አሉ እማማ ልኬ ።

« አንቺ በቁሟ ...እ ...ከነ ሕይወቷ ነው እንዴ የምትበያት ? እስካሁን በምድር ላይ በቁሜ ከነ ሕይወቴ የተበላሁት እኔ ብቻ ነኝ ።»

ሁላችንም ሳቅን ።

« ሆሆይ ...መቼም አታመጣው ጉድ የለህ ። አንተን ተወልደ ሳይሆን እያልቅበት ነበር ማለት። ለመሆኑ አንተንስ ማነው በቁምህ የበላህ ?» አሉችው እናቴ ።

«የሚስቴ ባልና የመሥርያ ቤቷ ሰዎች በቁሜ በሉኝ። የሚስቴ ባል ሕይወቴን ሳያጠፉ እንደ ፓፓዬ በቁሜ በላኝ።» ይኼን ተናግሮ ወጥቶ ሄደ ።

***

መሊ እብዱ ገጣሚያችን ነው ፤ የሰድብ ስንኝ ቋጣሪያችን ። ስሙን «መሊ» ሳይሆን «ሚሊ» ማለት ይገባን እንደነበር ዘግይቼ አወቅኩ ። ምክንያቱም « ሚሊዮን » እንጂ « መሊዮን » አይ ባልማ ።

ሚሊ የሚታወቀው በተላካፊ እብድነቱም ነው ። በተለይ ሴትና ወንድ ሲሄዱ ካጋጠሙት እየተከታተለ መከራቸውን ያበላቸዋል ።

« እዩልኝ ስሙልኝ ኧረ ምን ይመስላል

ለቂጡ ጨርቅ የለው ቆንጆ ያማልላል ።» አለው አንድ ቀን አንዱን ወጠምሻ ጎረምሳ ።

እኛ ሳቅን ። ልጅቱም ሳቀች ። ጎረምሳው ግን ተናደደ ። ንዴቱን በውስጡ አምቆ የውሸት ተቀላቅሎን ገለፈጠ ። ልጅቱን ሸኝቶ ሲመለስ ሚሊን አስገባለት ። ሁለት የማይከ ታይሠን ዓይነት ቡጢዎችን ለጉንጮቹ ሲቸረው ሚሊ አፈገፈገ ። « በሕግ አምላክ » እያለ ሸሸ ። ለካንስ ደፋር የሚመስል ሠካራም ብቻ አይደለም እብድም ዱላ ይፈራልና ። ለካንስ እብድም ሕግ አምላክ እንዳለው ያውቃልና ...ወይንስ ሲሉ ሰምቶ ።

የምሽት ተማሪዎችንም አይወድም ። በተለይ አምረው ደምቀው በቄንጥ የሚራመዱትን አምርሮ ይጠላቸዋል ።

« የማታ ተማሪ ምኑን ተማረችው

ጎንበስ ቀና እያለች ና ንፋኝ አለችው ።» ይላቸዋል ። እንዲህ

የሚለው ሴት ሴቶቹን ብቻ ነው ።

ሴቶቹ ይፈሩታል ። ዞረው መልስ ሊሠጡት ይቅርና ተረከዙ ብቻ ሕፃን ልጅ የሚያክል ታኮ ጫማ ቢጫሙ እንኳን በነጠላ ጫማ ያሉ ያክል ይፈረጥጣሉ ። ውሻ እንዳየ የበግ መንጋ ፊት ፊታቸውን ብቻ እያዩ ይበ'ናሉ ።

ሚሊ በቤተሰብ ጣጣ ምክንያት እንዳበደ ይነገርለታል ። ቤተሰቦቹ ድህነታቸውን መሸሽ ፈለጉ ። ከድህነት ለመውጣት አንድ አማራጭ ታያቸው ። የታወቀ ሀብታም የሚያደርግ አማራጭ። አማራጫቸው ወስዶ የባለ አውሊያዋ የእናቴነሽ አገልጋይ አደረጋቸው ።

አባትየው የአልጋ ቁራኛ ከሆኑ ቆዩ ። እህትየው ባል ባገባች በስድስተኛው ቀን በጭነት መኪና ተገጭታ ሞተች ። በእህትየው ሠልስት ታናሽ ወንድሙ የጠረጴዛ ጠርዝ ጭንቅላቱን መትቶት ዓይኑ ብቻ የሚቁለጨለጭ ፤ መላ አካሉ የማይታዘዝለት በድን ሆነ ። የቀረው ሚሊ ነበር ።



@BOOKALEM

ለቤተሰቡ ተስፋ አንድ ሆኖ እንደ ሚሊዮን ይበቃናል ያሉትም አበደ ፡፡

ተወልዶ ባደገበት ከተማና መንደር እርቃኑን የሚሄድ ፣ ሲያሻው ሽክ የሚል መሆኑ በገሀድ ታየ ፡፡ ይማርበት ከነበረው ዩኒቨርሲቲ ዲግሪ የጠበቁት ወላጆቹ ባዩት አልተደሰቱም ፡፡ ሊቆጣጠሩት የማይችሉት ልጅ ሆነባቸው ፡፡ በስተርጅና በሮጠበት ሮጠው ማገድ ሲያቅታቸው በአግረ ሙቅ ጠፍንገው አስቀመጡት ፡፡ የሚያበሉት ሲያጡ ሞቱንም ቢሆን ተጋፍጦ ሆዱን እንዲሞላ ከእስራት ነፃ አደረጉት ፡፡

እንደተለቀቀ ሰሞን ያገኘውን የሚደበድብ ፣ የሚፈነክት ፣ የሚነጥቅ ፣ የሚሳደብ ፣ ሰው ሁሉ ያለፈ ያገደመው የሚፈራው ሆኖ ነበር ፡፡ በተደጋጋሚ ጥፋት በፖሊስ ቆመጥ የተወገረው መማርያ ሆነውና የባህሪ ለውጥ አመጣ ፡፡ ያልተቀየረበት የሕይወት መስመሩ ስድቡ ብቻ ሆነ ፡፡ በግጥም ግጥም አድርጎ መሳደብ ይችልበታል ፡፡ አልፎ አልፎ ዝንጥ ያሉ ሴቶችን ሲያገኝ ማሯሯጥ ይቀናዋል ፡፡

የጠይሜ ወንድም እንደነገረኝ ከማበዱ በፊት የነበረው ሚሊ ሌላ ነበር፡፡ በጤናው ብቻ ሳይሆን በፀባዩም «ሸጋ» ብሎ ሠፈርተኛው የመሠከረለት ወጣት ፡፡ ሴትን ልጅ ቀና ብሎ ማየት የሚፈራ ፣ የዩኒቨርሲቲን ደጃፍ እስከረገጠበት ጊዜ ድረስ ከሱስ ያልተዋወቀ ፣ ጭምትነቱ መገለጫዎቹ ነበሩ ፡፡ ዛሬ ዛሬ ግን ያኛው ሚሊ በነበር ተተክቷል ፡፡ በነበር ከንፈር የሚመጥለት ሰው ሚሊዮን ተሾመ ፡፡

የሠፈር ጎረምሶች የሚመጣባቸውን ጣጣ ሲፈሩ ሚሊን እንደ ጋሻ ይጠቀሙበታል፡፡ መላከፍ ሲያምራቸው የሱን አፍ ይዋሳሉ ፡፡ እየተከታተለ ተሰዳቢውን እያሸማቀቀ አስተኳሹን ያስፈነድቃል፡፡ እያሳሳቀ የሚያሳቅቀውን ሚሊን እኔ ጠይሜና ጠምቤም አብዝተን እንገለገልበታለን፡፡ ሚሊ የፈለገ ይመጣል እንጂ አርጊትና ሽማግሌ አይነካም ፡፡ ዕቃ ከያዙ ተቀብሎ ያለ ክፍያ ያደርሳል ዣንጥላም ቢሆን ፡፡

የፖሊሱን የሽመልስን ልጅ ሊሻንን ታክሲ ሹፌሩ ረመዳን እቅፍ አድርጎ እያሳሳቀ ይዟት ሲሄድ ሌሎቹ ጎረምሶች ሚሊን ጠቆሙት ፡፡ እነ ሊሻንን ከገቡበት የደስታ ማዕበል ያወጣቻው የሚሊ ግጥም ነበር ፡፡

« አንቺ ልጅ አንቺ ልጅ አንቺ ልጅ ያሙሻል

እሱ እየወሠደ ለሦስት ያስነፋሻል ፡፡»

ሊሻን በረገገች ፡፡ ተሸማቀቀች ፡፡ ረመዳን የግንባሩ የደም ሥሮች ሲገታተሩ አልታወቀውም፡፡ ተሰብስበን የሰማነው ሁሉ ሳቅን ፡፡ ልጅቱ ከረመዳን ሥር ሮጣ አመለጠች ፡፡ ደግሞ ሊያገኛት እንዳይሞክር አስጠንቅቃው ተመለሠችበት ፡፡ ቢለምናት ቢለምናት ከተጠጋት እንደምትጮህ አስጠነቀቀችው ፡፡ የጎረምሶቹ ሳቅ መንገዱን አረዘመባት ፡፡ እያለቀሰች ፣ እጇን እያወናጨፈች ከዓይናችን ራቀች ፡፡ ረመዳን የሸሸችው እሷን ትቶ ወደኛ ተጠጋ ፡፡ እኔና ጠምቤን አንድ አንድ ጥፊና ቻባ አቀመሠን ፡፡ ጠይሜ ሮጦ ጎረምሶቹ መሀል ገባ ፡፡ ወንድምየው ስላለ ከጎረምሶቹ መሀል



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

መንጥቆ ሊያወጣው ሲሞከር ተቃወሙት ። ፈራቸው ።

« እነሱን ስለማትችላቸው ነው አይደል እኛን የምትመታን ?... እኛም እናድጋለን አሺ !» አለችው ጠምቤ ቅንድቧ ላይ የተንጠለጠሉትን የእንባ ኳሶች በአይበሉባዋ እየጠራረገች ።

አሳደዳት ። ሮጣ ጎረምሶቹ መሀል ተወተፈችና ምላሷን አወጣችበት ።

በደዝ ደዝ አራራጡ ስስቅበት አይቶኝ ወደኔ ተንደረደረ ። ወደ ጎረምሶቹ የሚወስደውን መንገድ ዘጋብኝ ። ወደ ግራ ወደ ቀኝ እያኮበኮበ መሮሚዬን እያጠበበ ጨምቆ ሊይዘኝ ተጠጋኝ። ከያዘኝ እንደሚደፋኝ ፣ የነ ጠምቤን እልህ እንደሚወጣብኝ ገባኝ ። ከኋላዬ አጥር ብቻ ቀረ።

ቢመታኝም ይምታኝ ብዬ እንደ በግ ተንደርድሬ ሆዱ ላይ በቴስታ ገባሁለት ። ሆዱን ይዞ ተንቆራጠጠ ። « ብራቮ ጭንቅሎ ! ድገመው !» የሚል የአድናቆት ቃል ከጎረምሶቹ ተሰማኝ ። ልደግመው ተንደርድሬ ስመጣ ኮሌታዬን ጨምድዶ ወደ ሰማይ አነሳኝ ። አየር ላይ አንጠለጠለኝ።

« ኧረ ምን ሆነህ ነው የጠብደል ኮሳሳ

ጎረምሳ ሲያቅትህ ልጅን የምትበሳ ?» አለው ።

የሚለን ግጥም ተከትዬ እራሴን መሬት ላይ አገኘሁት ። ወገቤን ይዤ በጀርባዬ እየተንደባለልኩ ጮህኩ ። ረመዳንና የጠይሜ ወንድም በቦክስ ተፈሳፈሱ ። ገላጋይ መስለው መሀል የገቡትም ልጆች ለጠይሜ ወንድም እያገዙ አንድ አንድ ጉንጭ ቡጢ ሠጡት ። ጠይሜና ጠምቤ በድንጋይ ነረቱት ።

ረመዳን ደሙን እያዘራ በወደቅኩበት ሊመታኝ ተንደረደረ ። የጠይሜ ወንድም የሟሟጠጫውን ቦክስ አገጩ ላይ አስቀመጠለት ። በዚያ በግዙፍ አካሉ ተዝለፍልፎ ተከመረብኝ። እንዳልፈርጥ ፈራሁ ። ትንፋሽ አጠረኝ ።

እንደምንም ብዬ ከሥሩ አፈተለከኩኝ ። ረመዳን ሜዳው ላይ ሲንደባለል እኛ እግሬ አውጪኝ አልን ። ከዚያ በኋላ የሚሆነውን ተደብቀን ብቻ ነበር የተመለከትነው ።

ሜዳው ላይ ከወደቀው የታከሲ ሹፌርና እብዱ ሚሊ በስተቀር ማንም አልነበረም ። ሚሊ ግንባሩ በደም ርሶ ፣ፊቱ በገዛ ደሙ ተልኮስኩሶ የሚንደባለለውን ረመዳንን ይንከባከበዋል። ደቃቅ አፈር ዘግኖ ፍንከቱን ይደፍንለታል ። በልብሱ ደሙን ያደራርቅለታል ። ያለ አንዲት ተጨማሪ በባለሞያ የተደገፈ የሕክምና እርዳታ ሳያገኝ ሲንደባለል የነበረው ረመዳን ከወገቡ ቀና አለ ። የሚሊ እጅና ልብስ በደም ቆሽሾ ተመለከተው ። እየገደለው ያለ መሠለውና ተነስቶ ለመሮጥ ሞከረ ። ሁለት ሳይራመድ ይወድቃል ። እያዞረው እየተንገዳገደ ከሞት ለማምለጥ ይሸሻል ። ሚሊም እንደተለመደው በግጥሙ ይለፈልፋል ።

« አትምን ሳያውቁ ደርሶ እምቡር እምቡር



@BOOKALEM

ትርፉ ኪሳራ ነው እራት መሆን ላፈር ::

አይጢቱን ፈርተው ዳዋው ላይ ሲሮጡ

ዳዋው አይጥ አለው አርፈው ይቀመጡ ::

ጉድ በል ሐረር !

በወፈረ ስጋ በረዘመ ቁመት

በደደረ ጡንቻ ት'ቢት በሞላበት

ቀጭን እየናቁ አጭር እያጥላሉ

ደርሶ በየሜዳው ወድቀው ይገኛሉ ::

ጉድ በል ሐረር !

አመላቸው ግራ ለሰው የማይመች

አልጋ ሲሉት መሬት በከንቱ የሚቧች

እንዴት ያለ ፍጥረት ምን ይሉት ምርት ነው

የሰው ልጅ ከጥንቱ አምላኩ ሲፈጥረው ?

ጉድ በል ሐረር !

ጉድ በል የሐረር ሰው ደርሠህ ጉዴ ጉዴ

እኔ እንደሁ ከንቱ ነኝ ቀርቶብኝ ልማዴ ::

አቅሜን የማላውቅ ከንቱ ፍልስፍና

አምቄ በውስጤ ይገለሁኝና

ይ ገ ለ ሁ ኝ ና

ይ ገ ለ ሁ ኝ ና

ይ ገለሁ...

ይ ገ ለ...

ይ ገ...

ይ...»



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ አስራ ሦስት

## ስጥ እንግዲህ

« የዚህ ሠፈር ልጆች ባለሞያ ናቸው

ወሬ ማስቀመጫ አገልግል አላቸው ::»

( ስማቸው የተዘነጋኝ ለማኝ )

ስንሠጥ ሰብሰብ እንላለን :: በተሰበሰብንበት በተለይም እየተሣጣጠን ከሆነ ሳቅ ሁካታው ይደምቅልናል :: የሆነ ሰው የማይመስለንን ሃሳብ ከሠነዘረ «ስጥ እንግዲህ !» እንለዋለን :: ተረኛ አድማጭ በሆንበት ሰዓት እሱም በተራው « ሥጥ እንግዲህ !» ማለቱ አይቀርምና ::

ታላቋ ሰጪ ታላቃችን ነው :: ታላቃችን ቢሆንም በቅፅል ስሙ ስንጠራው አይከፋውም :: እንዲያውም ሌሎች ሠጪዎች « ዋናውን ቤተሰብ ያወጣለትን መጠርያውን ረስቶታል » ይሉታል:: « ዲሽ » ብሎ ለጠራው ጆሮውን ይቸራል :: የምንወደው በቅፅል ስሙ ፣ የሚጠሉት ቤተሰቦቹ ባወጡለት የሚጠሩት ይመስለዋል :: በመንደራችን ሁለት «ዲሾች » ብቻ አሉ :: አንደኛው እነ ፍሬ ሕይወት ቤት ጣራ ላይ ተሰቅሏል :: ያለ ሰው እገዛ አይንቀሳቀስም:: ሁለተኛው ዲሽ ግን ሰጪ ነው-የሥጥ እንግዲህ መሪ ::

ቤተሰቦቹ ግን በቅፅል ስሙ ይናደዳሉ :: በተለይ አባትየው በቅፅል ስሙ ስንጠራው ከሰማ በድንጋይ ያሳድደናል :: አቤት ተቀምጦ እያየነው « ሂዱልኝ ከደጃፌ ...እዚህ ቤት መልካሙ እንጂ ዲሽ የሚባል ልጅ ገና አልተወለደም !» ብሎ ያባርረናል :: « ዲሻችሁን ጣራ ላይ ፈልጉት !» ይለናል ::

ዲሽ የማይለቃቅመው ወሬ የለም :: ወሬ ከተባለ እሱ ጆሮ ፈጥኖ ይደርሳል :: ተበርዞ ፣ ተቀይጦ ፣ ተለጥጦ ሠፍ ብለን ወደምንጠብቀው ወደኛ ይመጣል :: ማንም ሳይቆሠቁሰው የወሬ ከረጢቱን ይፈታል :: ያለ ስስት የተዘረገፈው ወሬ ለቆይታችን ድባብ የፈገግታ ምንጭ ይሆናል ::

በተለይ ከአቢቲ ጋር አይግባቡም :: አንዳቸው አንዳቸውን ውሸታም እያሉ ይኮንናሉ:: በዕድሜ ብቻ ሳይሆን በጉልበትም አቻ ናቸው :: ጡንቻ ማጠንከርያ ብረትና የተቀመጠ ዕቃ ሲያነሱም አይለያዩም :: እንዲህ በየወሬዎቻቸው ባለመግባባት ይናቆሩ እንጂ የጓደኝነት መስመራቸው ያስቀናል :: በልዩነት ውስጥ ተቻችሎ መኖር እንደሚቻል ከአኗኗራቸው መረዳት ለፈለገ ቀላል ነው ::

« ይገርማችኋል ... በቀደም ለታ ምን ሆነ መሠላችሁ ?» አለን አቢቲ ተሰብስበን እንደተቀመጥን



@BOOKALEM

« አ ! ምን ሆነ ?»

« አቤት ተኘቼ የሆነ ሌባ በአጥር ዘልሎ ወደ ግቢያችን ቸስ አይልም !»

« ከዚያስ ?» ጠይሜ ደንገጥ ብላለች ::

« ከዚያማ...ካየኝ በርግጎ ይሮጣል አልኩና ተከከርኩኝ :: አሊጋው ሥር ተከከሬ ብርድ ልብሱን ፣ አንሶላውን ፣ የአባዬን ኮትና ሱሪ ፣ የእማዬን አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ጥለት ያለው ጋቢ ሲሰበስብና በማዳበርያው ሲጠቀጥቅ ዘነዘናዬን በጥንቃቄ ይገፎ ሾፍኩት ::»

« ቤታችሁ ሲዘረፍ ነው እንዴ ተደብቀህ የምታየው ? እኔ ግን አንተን ብሆን ...» ጠምቤ ፎከረች ::

« አስጨርሠኝ እንጂ ጠምቤ ... እንዴ ምነው ሺህ ዓመት አላወራ ... ሆ ! ከዚያ ሌባው በማ ዳበርያ የጠቀጠቀውን ልብስ ተሸክሞ ሲወጣ ከኋላው ተከትዬ ...»

« ስጥ እንግዲህ !» አለው ዲሽ

«ባከህ ምንም አልሠጠሁም :: አታዳምጥም እንዴ መጀመርያ ?» ዲሽ ላይ አፈጠጠበት ::

« እና በዘነዘናው ግንባሩን ፈለጥከው ?» ገርሞኝ ጠየቅኩት ::

«ሆ ! ጭንቅሎ ! ማን ' fool ' አለ ... ሌባው ተመልሶ ከመጣ የቀረችውን ዕቃ ጠራርጎ ይወስዳታል አልኩና በሩን ከውስጥ በዘነዘናው ቀረቀርኩበታ !»

ሁላችንም ሳቅን ::

« እኔኮ ዘነዘናውን ያነሳኸው አናቱን ብለህ ልትደፋው መስሎኝ ነበር ::» አልኩት

« አይ ጭንቅሎ ... ደም በጂ ሠበብ ይሁን እንዴ ? ጭንቅሎ ... ዘነዘና ቡና መውቀጫ እንጂ አናት መፍለጫኮ አይደለም :: በዚህ ላይ ሃጢያቱን ፈራሁ :: እጄ ላይ ፀጥ ቢልብኝ እግዚሀ ርስ ምን ይለኛል !» አለ ::

« ይኼ ብቅብቅ ! በየትኛው ልቡ ነው የሚማታው ?» ዲሽ አለመጠበት ::

« ማ ! እኔ ? ከኔና ካንተ ብቅብቅ ?»

አቢቲ ተናደደ ::

« አንተ ነሃ ... ሌባ ቤታችሁን ሲዘርፍ እያየህ ዝም ያልክ የሌባ አጃቢ !»

« ቢታ ከዚህ በኋላ ከኔ ጋር ወሬ አቁም እሺ !» ዲሽን አስጠነቀቀው ::

« ባቆም ባላቆም ምን ታመጣለህ ?»



@BOOKALEM

« የማመጣውንማ አሳይሃለሁ ። ደሞም ታውቀኛለህ !»

« ባከህ አታስፈራራኝ ። እንኳን ይቺ ይቺን ያለ ሠፈሯ መጥታ እኛ ሠፈር የምታውደለድል ዝንብ ለይተን እናውቃለን እሺ።»

« ስጥ እንግዲህ !»

« ምንም አልሰጠሁም ።»

«ሰጠህ እንጂ ! በአምስተኛ ማርሽ ተረማመድከብንኮ ። ኧረ ! ነዳጅህን ቀንስ ። ደሞ ዝንብ ከመቼ ጀምሮ ነው ሠፈር የኖራት ?»

ሊደባደቡ ፣ ፍስፍስ ልናይ ነው ብለን ስንጠብቅ ዲሽ ሌላ ወሬ አመጣ ።

« ባይገርማችሁ ጠይሜ ... ... ... እነዚያ ግብዳው ጋሽ ሠይፉ ሲበዛ ቀሚጫ እንደነበሩ ታውቃላችሁ ?»

« የትኛው ናቸው ጋሽ ሠይፉ ?» ጠይሜ ጥያቄውን በጥያቄ መለሠበት ።

« እነዛ ናቸዋ ... ፎቶ ቤት እንኳን ያላቸው ? እ ... ትንሿ ኤሊ መኪናም አለቻቸው ።»

« አወቅኳቸው ።»

« እሳቸው ሰውዬኮ ቀሚጫ ፣ ዝንጀሮ አሯሩጠው የሚይዙ ፣ እንደ አቢቲ ሲቢጣ ነበሩ ።»

« ስጥ እንግዲህ !» አቢቲ የጠምቤን ትከሻ በመዳፉ መታ ፣ መታ አድርጎ ሳቀ ።

« የምሬን እኮ ነው ። ጋሽ ሠይፉ የወፈሩት ስጋ በልተው አይደለም ።»

« እና ? » ጠይሜ በጉጉት ጠየቀው ።

« አሁን ባለፈው ሳምንት ሰብስቦ ፎቶ ያነሳን ፈረንጅ አገር የምትኖር ምርጥ ልጅ ነበራቸው። ወደ ውጭ ሀገር ልትሄድ ስትል አሳድጌ ለማንም አልሠጥም አሉና ፣ ቢራና የፈረንጅ አረቂ አጠጡና ጠጧት ።»

« ልጃቸውን ?» ጠይሜ ደንግጦ አፉን ያዘ ።

« ወደህ ነው ! ከዚያ ... የዚያን ቀን እግዛቤር በጋሽ ሠይፉ ሥራ ተናደደና ከሰማይ ወረደ ።»

« ስ...ጥ እንግዲህ !» አቢቲ የመስማት ትዕግ ስቱ ተፈታተነው ።

« እንዴ ! እግዛቤር የኛን ሠፈር ያውቃታል ?» ደንግጬ ጠየቅኩት ።

« በጣም ነው እንጂ የሚያውቃት ። ትቀልዳለህ እንዴ ጭንቅሎ ! እግዛቤር እኮ መዋያና ማደር ያው እንደኛ ዓይነት የድሀ ሠፈሮች ውስጥ ነው።»



@BOOKALEM

« ድሀ ሠፈር ውስጥ ምን ያደርጋል ?»

« ድሆችን ከበሽታ ይጠብቃላ ::»

« ሀብታሞችንስ ማን ነው ከበሽታ የሚጠብቃቸው ?»

« ሐኪም ነዋ ::»

«ቆይ ዲሽ ... እ ... ከዚያስ ግን እግዛቤር ጋሽ ሠይፉን ሲያገኛቸው ምን አላቸው ?» አለው ጠይሜ ዲሽን ::

« በመጀመርያ አንበረከካቸው :: ቀጥሎ አርጩሜ ቆርጦ ልጥልጥ አደረጋቸው :: ከዚያ ረገማቸው :: በመጨረሻም የልጃቸውን ማሕፀን አውጥቶ ቦርሜቸው ውስጥ በግድ ከተተባቸው:: ለሷ ሌላ አዲስ ማሕፀን ሰጣትና እሳቸውን በተንበረከኩበት ጥሏቸው ሄደ ::»

« ፐ ! ፐ ! ፐ ...ኧረ ትንታኔ !» አቢቲ አባባሉ ያስቅ ነበርና ሳቅን ::

« በግሌ የተቀነባበረ ወሬ አይደለምኮ የምነግርህ የሰማኹትን እንጂ ::»

« እሺ ከዚያስ ? እግዛቤር ጥሏቸው ከሄደ በኋላ ምን ሆኑ ?»

« ጋሽ ሠይፉ በእግዛቤር ላይ ቂም ቋጠሩ :: በእግዛቤር ላይ ቂም የቋጠሩት ደሞ የልጃቸውን እርግዝና ሆዳቸው ውስጥ ስላስቀመጠባቸው ነው ::»

« ስጥ እንግዲህ ! ወንድ ሲያረግዝ ታየኝ እኮ !»

በአቢቲ አባባል ዲሽ ተናደደ ::

« ስጥ እንግዲህ ! ትላለህ እንዴ ? ይኼን ታሪክ እራስህ አይደለህ የነገርከኝ ? እንዲያውም ከፈለግክ ለራሳቸው ሄጄ 'እንደዚህ እያለ ያስወራብዎታል' ብዬ እንዳላስወግርህ ?» አለና ዲሽ የወሬውን ምንጭ አቢቲን አደረገው :: አቢቲ በዲሽ ተናደደ :: ያላለውን ብለሀል በመባሉ ተቆጣ:: ፊት ለፊቱ ያገኘውን ትልቅ ድንጋይ አነሳ :: ዲሽ በመቶ ሜትር ፍጥነት ነጠላ ጫማውን ጥሎ ሮጠ:: አቢቲ በሳቅ ተንከተከተ ::

« አላልኳችሁም ! ብቅብቅ እኮ ነው :: እኔኮ ድንጋዩን ያነሳሁት ልማታበት አይደለም :: ቆይ እስቲ መንገድ ላይ እንቅፋት ሆኖ የተጎለተን ድንጋይ የማንሳት መብት የለኝም እንዴ ?» አለና ድንጋዩን ወደ አጥሩ ጥግ ወረወረው :: በአቢቲ ነገረ ሥራ ተገርመን ሳቅን :: ዲሽ በሮጠበት ፍጥነት ተመልሶ መጣ :: የሮጠው የአቢቲን ድንጋይ ፈርቶ ሳይሆን እናቱ የጠራችው መስሎት ለማጣራት እንደሆነ ሳያፍር ነገረን :: ሳቅንበት :: ከአቢቲ ጋር ትንሽ በነገር ተወጋጉ ::

« ከዝንብና ከንብ ማን ይበልጣል ?» የሚል የመወያያ ርዕስ ከጠይሜ ቀረበ::

« ዝንብ ነዋ !» ዲሽ መለሠ ::



@BOOKALEM

አቢቲ ከትከት ብሎ ሳቀበት ፡፡

« ምን ያስቅህል ?»

«እና ላልቅስልህ ታድያ ! ወይ አለመማር ... እኔ'ኮ አያቶችህ ብቻ ነበሩ ያልተማሩ የሚመስሉኝ፡፡ ለካ አንቺም ሀ ገደሉ ነሽና ? በል ከዛሬ ጀምሮ ደረጃህን አወቅ ፡፡ ከኔ ጋር ለመዞር ከፈለግክ የፊደል ገበታ ከእጅህ እንዳይለይ ፡፡»

« ኧረ ባክህ ! ጅል ! ስለ ዝንብና ንብ መበላለጥ ለማወቅ የግድ መማር ያስፈልጋል ያለው ማን ነው ?»

« ሼክስፒር !»

« ውይ ብልጡ ! ባንተ ቤት ሼክስፒር ምን እንደሆነ የማላውቅ መስሎህ ነው ይኼኔ ፡፡»

« የት አባክ ታውቀዋለህ ?»

« አውቀዋለሁ ፡፡»

« እሺ ካወቅከው ማንነቱን ወይም ምንነቱን ንገረኝ ፡፡»

« አልነግርህም ! አውቀቴንማ በነፃ አ ልሠጥህም ፡፡»

ጠይሜን በጆሮው ስለ ሼክስፒር ማንነት ወይም ምንነት ጠየቅኩት ፡፡ አያውቀውም ፡፡ ጠይሜም ጠምቤን፡፡ ያለ ዛሬም ይህን ስም ሠምታው እንደማታውቅ ነገረችን ፡፡ በርካታ «ሼክ» በሚል ቅድመ ቅጥያ የሚጠሩ ሰዎች ሠፈራችን ቢኖሩም «ሼክ ስፒር» የሚባል ግን ኖሮ አያውቅም፡፡ እነ ሼክ ናስር ፣ ሼክ ህምዛ ፣ ሼክ ሳላህዲን ፣ ሼክ ታጁዲን እኛ ሠፈር ናቸው ፡፡ ሼክ ስፒርስ የት ሠፈር ይሆን ?

« አንተ ሼክስፒርን ብታውቅማ ጉራህ ሐረርን ያቃጥላት ነበር ፡፡ ቡፋ !» አለው አቢቲ

« ዝም በል አቦ ! ምን ታካብዳለህ ... ሼክ ስፒር ማለት መህል መጋላ ጉዶ ላይ ትልቅ ስጋ ቤት ያለው ሱማሌ አይደል እንዴ ?»

« ስጥ እንግዲህ !»

« ለነገሩ ስቀልድ ነው ፡፡ ሼክ ስፒር ማለት የሚገርም ተፈጥሮ ያለውና መልኩ ደማቅ አረን ጓዴ ሆኖ ጥሬውን የሚበላ የዱባ ዓይነት ነው ፡፡»

አቢቲ እግሩን አንስቶ ሳቀ ፡፡ እኛም ሼክ ስፒር ነጋዴው ይሁን ዱባው ሳንለይ ሳቅን ፡፡

« ኧረ ድፍረት ! ኧረ ድፍረት ! እንኳን ይኼ ሰውዬ ሀበሻ አልሆነ ፡፡ አንተ እንዴት ያለኸው ደፋር ነህ ባባትህ ! እንዴ አቢቲ ምን ሆነህ ነው ... ድፍረት ዕውቀት አይሆንም እኮ ፡፡ ወይ ጠይቀን



@BOOKALEM

ወይ ተማር ።»

« ኧረ ባክህ !»

« የምሬን ነው ። ለመሆኑ በዝንብና በንብ መካከል ያለው ልዩነት ገብቶሃል ? ይቺን ማስረዳት ከቻልክ አንተ የምር ተምረሃል ፤ ፈደልም ቆጥረሃል ።» አለው አቢቲ ዲሽን በትኩረት እያየው ።

«አቦ አታካብዳ አቢቲ ደሞ! ዝንብ ማር ትሰጣለች ንብ ደሞ ትናደፋለች ።»

ሁላችንም ሳቅን ።

« ምን ያስቃችኋል ?»

« እንዴ ዝንብ ከመቼ ወዲህ ነው ማር መስጠት የጀመረችው ? ምን ነካህ ዲሽ ? ዝንብ በታሪኳ ማርም ባለቤትም ኖሯት አያውቅም ። ኧረ ባክህ ! ኧረ ባክህ ! ቀኑን ሙሉ እንደ ባህር ዛፍ ቆመው ያስተማሩህን መምህራን አታሠድብ ።» አልኩት ።

« ውይ ለወሬ ስቸኩል እኮ እንዲህ ያደርገኛል ። ገለባበጥኩት አይደል ? እ...ዝንብ ትናደፋለችም ማር ትሠጣለችም ማለቴ እኮ ነው ። አይ የኔ ነገር !»

« ዝንብ ነች ንብ ?»

« አትሰማም እንዴ አንተ ቫንጣ ራስ ! ዝንብ አልኩህ እኮ !»

« ባክህ ተደበቅ ... ዝንብ አር እንጂ ማር ስትሠጥ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም ።» አልኩት ።

« እንዴ ?» ዲሽ የደነገጠ መሠለ

« ምነው ?» በጋራ ጠየቅነው

« ዝንብን ነው እንዴ ማር ትሰጣለች ያልኩት ?»

« ታድያ !»

« ምን ዓይነቱ ነኝ በናታችሁ ... ንብ ማለቴ እኮ ነው ።»

« T ! ብልጡ ... ሸውደህ ልብህ ወልቋል ።» አቢቲ አለመጠበት

« ሂድ ባክህ ! ምን ታካብዳለህ ። ዞሮ ዞሮ አንዷ ዝ ብትነሳ እኮ ያው ሁለቱም ንብ ናቸው ።»

« ስጥ እንግዲህ !»

በዲሽ ድርቅናና አልረታም ባይነት ተገርመን ሳቅን ።



@BOOKALEM

እንዷት አውሮፕላን ለሠፈራችን ቀረብ ብላ ስትበር ዲሽ ቀና ብሎ ተመለከታት ። ሮጦ አቢቲ ሥር ተሸንጠና « አቢቲዬ ከልለኝ ! በናትህ ከልለኝ !» አለው ።

« ከማን ?»

« ከአውሮፕላኑ !»

« ለምን ? እንዳ ይገጭህ ነው ?»

« አይደለም ።»

« እና ?»

« አጎቴኮ ነው የሚያበ ራት ። 'በዚህ ጋ ሳልፍ ሜዳ ላይ ስትንዘላዘል ካየሁህ ሴባ ጎማ ወርውሬ እገድልሃለሁ' ብሎ አስጠንቅቆኛል ። በቀደም ለታም ከሪከና ስኮርት ጎማ ወርውሮብኝ ለትንሽ ነው ያመለጥኩት ። በናትህ አቢቲዬ ከልለኝ ። አንገቱን በመስኮት አውጥቶ ስለሚያበር አንተን ካየህ መኖሬን ይጠረጥራል። ቀና እንዳትል እሺ።» አለው እግሩ ላይ ተጠምጥሞ ። አውሮፕላኗ ድምጿን ከጆሯችን አካሏን ከዓይኖቻችን አሸሸች ። የዲሽ እውነተኛው አጎት ተዘራ የተፈጨ ዱቄት በጋሪ እየገፋ መጣ ።

«አንተ አጎትህ አውሮፕላኗን መሬት አሳርፎ ይዞልህ ከች አለ ።» አለው አቢቲ

ሳቅንበት ። የኅብረት ሳቃችን ያሳቀቀው የዲሽ አጎት ዓይኖች እንባ አቀረሩ ። ድንጋጤያችን አስደነገጠው ። እጁን ወደ መሬት ልኮ ባነሳው አጥንት የእህቱን ልጅ ዲሽን ፈለጠው ።

« ስ...ጥ እንግዲህ !» አለ አቢቲ

የዲሽ አጎት የአቢቲን ጥያቄ ተቀበለ ። ተቀብሎም ለመስጠት እንደማይሠስት በተግባር አረጋገጠለት ። በደንብ ሰጠው ። ቴኒስ መጫወቻ «ራኬት» በሚመስል አጥንት... እስኪደማ ... እስኪያለቅስ... እስኪያነክስ ...



@BOOKALEM

# ምዕራፍ አስራ አራት

## ጋሽ በረደድ

ጋሽ በረደድ ተማሪ ነው ። የአራምዴ ጠጅ ቤት መደበኛ ተማሪ ። የወታደር መኪና ያሽከረክራል ። ኤኔትሬውን ከነ ተሳቢው ሲያንጸረጽረው ያስደስታል ። የግንብ ግንጣይ የሚያክል ውፍረት አለው ። በገዘፈ ቁመቱ ላይ የበዛ ሆድና ስጋ ተሸክሟል ። ሲሄድ ሞንደል ሞንደል ይላል ።

ከስከስ ጫማው የውሻ ቤት ያክላል ። ያን የሚያክል ጫማ ተሸከሞ ሲጓዝ ጥቂትም የሚከብደው አይመስለኝም ። ሁሌም ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊትም ሆነ ከሥራ መልስ ወደ ትምህርት ቤቱ ጎራ ማለት ለምዷል ። ፉት ፣ ጎንጨት ሳይል መዋል አይችልም ።

ኤኔትሬውን ይዞ ሠፈር ይመጣል ። በተለይ ከቀብሪ ደሀር ፣ ደጋ ሀቡርና ኢጋዴን መስመር ጭኖ ያመጣውን የደሬ እንጨት ፣ ከሰልና ፍየል ተረባርበን እንድናወርድ ያደርገናል ። ከመኪናው ያወረድነውን እያማተን ግቢው ውስጥ እናስገባለን ። ሚስቱ ትርሀስ ደሞ እጃችንን እርስ በርሳችን እንድንታጠብ ካደረገች በኋላ የትግሬ አምባሻ ትሠጠናለች ። ሁሌም አምባሻ ከቤታቸው አይጠፋም ። ነጭ ባለ መስመር አምባሻ ። በቡናማ ቀለም ጀርባውን በመንቀስ ምጣዱ የተጠበበበት አምባሻ ።

አምባሻችንን እየገመጥን ጋሽ በረደድ በመኪናው ጭኖ ምሥራቅ ዕዝ ድረስ ይወስደናል ። ወደ ግቢ ከመግባቱ በፊት ከአስፋልቱ ዳርቻ ያወርደንና የግራ መስመራችንን ተከትለን ወደ ሠፈራችን እንድንመለስ ይመክረናል ። እየጨፈርን በመኪና የሄድንበትን ከሶስት ኪሎ ሜትር ያላነሰ መንገድ ገጠመኞችንን እያወራን ፣ እየለፈለፍን ፣ በመኪናው ላይ ሆነን ስላጋጠመን ፣ ስለተሠማን ነገር እየተነጋገርን ስለሆን ድካም አይታሰብም ።

መንገድ ላይ...በተለይ አጂፕ ነዳጅ ማደያ አካባቢ የሚውሉ የቀበሌ አስራ ሰባት ጎረምሶች ካገኙንና የቀላድ አምባ ልጆች መሆናችንን ካወቁ እናት እናታችንን በኩርኩም ያቀስሱናል ። ስናለቅስ የመሰናበቻ ያቀምሱናል ። እኛም ታድያ እነሱን እኛ ከልል ውስጥ ካገኘናቸው እሸት እናሰጸርጋቸዋለን። ታላላቆቻችን ሲገርፏቸው አርጩሜ እየቆረጥን እናቀብላለን ።

« ውቃው በደንብ አርገህ ያስራ ሰባት ልጅ ነው

እናቱን በኩርኩም ትላንት ያነደደው ።

ውገረው ቀጥቅጠው ሲያገኝ አይለቅህም



@BOOKALEM

ዛሬ ከለቀቅከው በሳንጃ አይምርህም ::» እያልን እናፈሳፍሳቸዋለን ::

የሚገርመው የኛ ሠፈር ልጆች ከማንም ጋር ብንቀላቀል እንለያለን :: ስናወራ እንጮሃለን :: የቀስታ ወሬ አናውቅበትም :: ከባለቤቱ ካፈተለከ በኋላ ምስጢር የለንም :: ስንሄድ ነጠር ነጠር እናበዛለን :: የአብዛኞቻችን የፀጉር ቁርጥ ይመሳሰላል :: ፓንክ ቁርጥ ፣ የቱ ፓክ ካናቴራና ፍሬዘር ጂንስ ሱሪ መለያዎቻችን ናቸው :: ጂንሳችን ጉልበቱ ፣ ቂጡ ፣ ባቱ ፣ አካባቢ ይተለተላል :: በደንብ የሚሸት የጭቃ ቅባታችንን እንለቀለቅና ከባንክ የወጣ አዲስ ሳንቲም እንመስላለን ::

ሌላው ቀርቶ ያበጠ የደረት ጡንቻ ባይኖረንም እንኳን ያገጠጡ የደረት አጥንቶቻችንን በግድ ወጥረን ሳንባችንን ማስጨነቅ የውዴታ ግዴታችን ነው :: የቀላድ አምባ ልጅ ሆዱን ካልቆረጠው በቀር እንገቱን ደፍቶ አይሄድም :: ከጠላቱ የሚወረወርበትን ድንጋይ እንኳን ቆም እንጂ አጎንብሶ መሸወድ እንደ ፈሪ ያስቆጥረዋል :: ከሌሎች አንሰን ላለመታየት እንወጣጠራለን :: የማንችለው ፣ የማንጋፈጠው ፣ የማንሞክረው ምንም ነገር እንዳይኖር ታላላቆቻችን አስተምረውናል :: በየዕለት የተግባር ተሞክሯቸው ድብድብ ቀላልና ተራ ነገር እንደሆነ አሳውቀውናል :: ጭንቅላቱን ተፈንክቶ ጠባሳ የሌለው ፣ ፊቱን ተቧጭሮ ቡራቡሬ ያልሆነ ፣ እኩያ ጠላት ያላፈራ ልጅ ምኑን ልጅ ሆነው !

ከቀበሌ አስራ ሰባት ልጆች ጋር የሚከሰተው ግጭት በኛ ዕድሜ የተጀመረ አይደለምና በኛ አይቆምም :: ታላላቆቻችን በጠረጉት መንገድ ላይ ነው የኛም የነሱም ትንንሾች መጓዝ የያዝነው:: በጩቤ ፣ በዱላ ፣ በድንጋይ ፣ ተፈሳፍሠዋል :: ተከታዮቻቸውም ዕድሜና አቅማችን ለስለት ስላልደረሰ በወንጭፍ እንጠዛጠዛለን :: በወፍ ሰንጥር እንለጣለጣለን :: እስኪበቃን የውጊያ መሳርያችን እስኪሟጠጥና የጠላት ኃይል ተንፎሽፉሾ እስኪፈረጥጥ እንከሳከሳለን :: የትምህርት ቤት ምርጥ ጓደኞችን ቢሆንም እንኳን በመንደር ስንፈሳፈስ የአስራ ሰባት ቀበሌ ልጅ ከሆነ ምሱን ቆጥሮ መረከብ ግድ ይለዋል :: ወዳጅነቱ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ያከትማል ::

ከቀበሌ አስራ ሰባት ጉልቤዎች ዋነኛው ቦቸራ ሲሆን ማንም አይደፍረውም :: አባት አይፈራም ፣ ፖሊስ ይንቃል...በቃ የምር ጉልቤ ነው :: ርህራሔ ብሎ ነገር አልተፈጠረም:: ባገኘን ቁጥር ባገኘው ነገር ይቀጣናል :: የሱ ሴት አያትና የኔ ወንድ አያት ታናሽና ታላቅ ናቸው:: እሱ ግን የኛ ሠፈር ልጅ አይደለም :: እኔም የነሱ አይደለሁ :: ስለዚህ እነሱ ክልል ውስጥ ካገኘኝ ለሌሎች የኛ ሠፈር ልጆች ያዘጋጀውን ፅዋ ያስጎነጨኛል ::

አንድ ቀን ጠይሜና ጠምቤን ይዣቸው አያቴን ልንጠይቅ ወደነ ቦቸራ ቤት ሄድን :: አያቴ ቤት ለመሄድ የተነሳንበት ዋና ምክንያት ደሞ ፈጫሳ ስለነበረባቸው ቂንጬ ለመብላት ነበር :: የገብስ ቂንጬ በቂቤ ለመዋጥ ቋምጠናል :: በኪሶቻችን ዳቦና ቆሎ ሞልተን ለመመለስ ተስማምተናል ::

በአዲሱ ስታዲየምና ኩባ ካምፕ መካከል ባለችው ጢሻማ የማሳበርያ መንገድ ተደብቀን ስንሄድ ቦቸራ አገኘን :: ሆዳም ነው :: የአስራ ሦስት ዓመት ልጅ ቀቅለው ቢሰጡት ጥርግ አርጎ በልቶ ጨምሩልኝ የሚል ዓይነት ጅብ :: አሽከሮቹን በየሱቁ ልኮ ሳጥን ሙሉ ለስላሳ አሠርቶ



@BOOKALEM

ሲያበቃ አንድም ሳያተምሳቸው ብቻውን ጠጥቶ ጠርሙሱንና ሳጥኑን ሸጠው እንዲመጡ ያደርጋቸዋል ። አምስት ከኛ የሚበላለጡ ጎረምሶችን ፊት ለፊቱ አስቁሞ እንደ ጅብ ንጉሥ በተዘረጋ ማዳበርያ ላይ የቆለለውን የሩዝ ከምር እየናደ ቶሎ ወደማይሞላው ሆዱ ይጎስጉሳል ። ሩዙን ያወጡት ከኩባ ካምፕ ነው ።

ወታደሮቹ በሉተው የተረፋቸውን ገንዳው ውስጥ ይደፉታል ። ከገንዳው ውስጥ ደሞ አውደልዳይ ውሾችና የቦቸራ አሽከሮች ተሻምተው ድርሻ ድርሻቸውን ይወስዳሉ ። አሽከሮቹ በማዳበርያ ሞልተው የተሸከሙትን ቅባት የጠገበ ፣ ትላልቅ አጥንትና ድፍን ድንች አብሮት የተቀቀለ ሩዝ ውድማ ላይ ወቅተው እንዳኖሩት እህል ከፊቱ ይከምሩለታል ። አምስቱም አሽከሮች የባህር ዛፍ ቅጠል ቆርጠው ጠቅጥቀው እስኪጠግብ ዝንቦች ያባርሩለታል ።

ቦቸራ እግሮቹን በልቅጦ ሠሀን በሚያስንቅ እጁ እየዛቀ ጥቅጥቅ ባለ ጢም ወደ ተከበበው አፉ ያስገባዋል ። ሳያኝክ እየዋጠ ብሉ እስኪላቸው አሠፍስፈው የሚጠባበቁትን አሽከሮቹን ምራቅ ያሰውጣቸዋል ።

በጢሻው ውስጥ እየተሽሎከሎከን ስንሄድ አየን ። ዓይኖቹን ሲያጉረጠርጥብን ፈራነው ።

« እንሩጥ !» አለ ጠይሜ

« አንድ ፣ ሁለት ...» ጠምቤ በሹክሹክታ ቆጠራ ጀመረች ።

« አትፍሩት...የኔ ዘመድ ስለሆነ አይነካንም !» አልኳቸው ተማምኜበት ።

እኛ ስንከራከር አሽከሮቹን ልኮ አስያዘን ። ታገትን ። ቆልሎ ከሚንደው ሩዝ ፊት ለፊት ሦስታችንም ተደርድረን ቆምን ። ሠሀን የሚሞላ ሩዝ በጁ ዘግኖ ወደ ጠይሜ ተጠጋ ።

« አፍህን ከፈት !» ጮኸበት ።

እየተንቀጠቀጠ ጥርስና ጥርሶቹ እየተጋጩበት አፉን ከፈተ ። እኛንም አስከፈተንና ጭቃ እንደሚመርግ ሰው ሩዙን እያፈሠ አውቆ አፋችን እየሳተ ፊታችን ላይ ለጣጠፈው ። ጠምቤ አፏን ብቻ ሳይሆን ቦግ ቦግ ያሉትን ዓይኖቿንም በደንብ ከፍታለት ነበርና ተለበለበች ። አሽከሮቹ የኛን ፊት እያዩ ይስቃሉ ። እኔ ጠይሜን ፣ ጠይሜም ጠምቤን እየተያየን ለራሳችን እያለቀስን በሌላችን ገፅታ ብልሹነት እንስቃለን ።

ጉልቤው ቦቸራ አሽከሮቹን እንዲበሉ ፈቀደላቸው ። የተከመረው ሩዝ ላይ ተንበርክከው ተሻሙ ። ከምሩን ንደው ላይጨርሱት ሳያኙ ፣ ለምላሳቸው የማድቦልቦልን ኃላፊነት ነፍገው ዋጡ ።

« ሂዱ እናንተም አብራችሁ ብሉ !» ብሎ አፈጠጠብን

እየተንቀጠቀጥን ወደ ሩዙ ተጠጋን ። አሽከሮቹ ጠግበዋል ። ጠይሜ በነፃነት ሲውጥ ጠምቤ



@BOOKALEM

እጆቿ ሩዙን ለመዝገን ተንቀጠቀጡባት ። እንደምንም አደፋፍሬያት በላች ። ሦስታችንም ስንጠግብ ሙብላት አቆምን ።

« ቢመታንም እንድንችለው ጥቅጥቅ አርገን እንብላ !» ብሎ ጠይሜ በጆሮዬ መከረኝ ፤ እኔም ጠምቤን ።

« ምን አባታችሁ ነው የምትመካከሩት እናንተ ዲቃሎች ?» ቦቸራ በኘያ አስፈሪ ዓይኖቹ አጉ ረጠረጠብን ።

ደንግጠን ፀጥ አልነው ።

« ልታመልጡ ነው የምትመካከሩት ?»

« ኸረ አይደለም !» አልኩት አፍንጫዬን ነፍቼ

« ሂድ...ምን ይመስላል በናታችሁ ! ጭራሽ አፍንጫውን ሲነፋማ አይጥ የዋጠ እባብ'ኮ ነው የሚመስለው ። ቀውላላ...የሌባ መንሠላል ! የዝንጀሮ ግንጣይ ! መድኃኒዓለምን...አንተማ የኛ ዘር አይደለህም !» ብሎ የስድብ መዐት አዘነበብኝ ፡፡

አሽከሮቹ ሳቁብኝ ።

« ለመሆኑ ግዛቴን ጥሳችሁ ወዴት አባታችሁ ነው የምትሄዱት ?» አለና አፈጠጠብን ።

« አያቴ ጋ የፈጫሳ ቂንጬ ልንበላ !» አልኩት ስማቸውን ሲሠማ ቢራራልን ብዬ

« ኸ ! ጉድ ጉድ ...እነዚህን የቀላድ አምባ እንበጣዎች ይዘህ የአያቴን ቀለብ ልታስፈጅ ነዋ... አንተ ጋን ራስ !»

ጓደኞቼ አመዳቸው ቡን ሲል ታየኝ ። ዘመዴ ነው ብዬ ተማምኜበት ከዳኝ ።

« ና ! አንተ አብዲ...የአያቴ ቤት ሲዘረፍ ዝም ትላለህ እንዴ ? በል ፎጣ አቀብለኝ ።»

አብዲ ከቦቸራ አሽከሮች አንዱ ጠምቤን ኮሌታዋን ጨምድዶ እንደሚታረድ በግ እየጎተተ አቀረበለት ። በሩዙ ቅባት የተጨማለቁትን ሠፊድ እጆቹን እያገላበጠ ጠምቤ ፀጉር ላይ አዳረቀ ። ጠምቤ የነበራት የሰው መልክ ጠፋ ።

« እ ! እያ ጭንቅሎ... ጓደኛህ አላማረበትም ?» አለኝ እጁን መጠራረግ ሳያቆም

ጠምቤ ፊቷ ተኸገጎርጉሮ ፀጉሯ ውስጥ የተደበቁ የሩዝ ፍሬዎች ብቅ ብቅ ብለው ለተመለከታት ታስቃለች ። ሳቄን ችዬ ግን ፀጥ አልኩት ።

« ና ...አንተ ማሰሮ ራስ ! ጭራሽ ስጠይቅህም መልስ አትሰጠኝም እንዴ ? የምን አባከ ጥጋብ ነው አንተ ...ቋጥኝ ራስ ! ለነገሩ ጥፋተኛው እኔ ነኝ ። አንተማ ምን ታደርግ...ሩዜን ሆድህ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

እስኪቆዘር እብልቼ እጠገብኩህ አይደል? አሁን ንገረኝ ጓደኛህ እምሮበታል አላማረበትም ?»

« እምሮበታል !»

እሽከሮቹ ሳቁ ።

« በል አንተም ወደኔ ናና ላሳምርሃ !»

« ኧረ ! ውሸቴን ነው አላማረበትም !» በዘይት እንዳያጨማልቀኝ ተጠይፌ ሸሸሁት ።

እብዲ በቂጤ በኩል እጁን ሠቅስቆ እስገብቶ ሱሪዬን ይዞ እንጠለጠለኝ ። ሚዛኔን እንድስት ቀና እድርጎ እየገፋ እስጠጋለት ። በ'ጁ ፉዝ ዘገነና ጭንቅላቴ ላይ እንደ ቅቤ ደፈደፈው ። ጎንበስ ብዮ ብደፋው እናቴን በኩርኩም እንደሚያፈርሠው እስጠነቀቀኝ ። እናቴ ላይ የደፈደፈውን ደመደመውና የወፍ ቆሎ እበባ እስቀርጦ ሠካካብኝ ። ጠረጴዛ ላይ በብርጭቆ እንዳስቀመጠው እበባ ቆጠረኝ ። ጠይሚኒንም ለቀለቃት ።

በቃን ጠገብን ያልነውን ፣ ፀጉራችንን ባጨማለቀበት እጁ እየዘገነ ያቡካካውን ፉዝ ደግመን እንድንበላ እዘዘን ። ከአቅም በላይ ለመብላት አልቻልንም። ሦስታችንም አለቀስን ። በሱሪያችንና በሸሚዛችን ኪሶች ፉዙን እንድንሞላ እስገደደን ። ልብሳችን ተጨመላለቀ ። የገዛ ገላችንም ልብሳችንም እስጠላን ። ሁለመናችን ፉዝ ፉዝ ሸተተ ።

ቀጥሎ ተረኛ ተቀጪዎች ደሞ እሽከሮቹ ሆኑ ። እንጀታችን ቅቤ ጠጣ ። እርስ በርሳቸው ሲያፈላፍላቸው እያለቀስን ሳቅንባቸው ። ደም በደም ተደራረጉ ። እንዱ ቀረ ። እጭር ሆኖ ወፍራም ነው ። ቂጣም ዘረጦ ቢጤ ። በመጀመርያ ሆዱ እስኪቀበተት ፉዙን እስበላው ። መብላት ሲያቅተው ለሦስት እንድንደበድበው እዘዘን ።

ፈራነው ። የምንችለው እልመሰለንም ። ደሞ ሌላ ቀን ብቻ ለብቻ ሲያገኙን እንደሚያሸን እርግጠኞች ነን ። ግን ሺህ ጊዜ ታሪክ ቢቀየር የቀበሌ እስራ ሰባት ልጅ ስለሆነ መታነውም እልመታነውም ሲያገኙን ስለሚቀጠቅጠን ለውጥ እያመጣም ። ስለዚህ ብንወግረውስ ?

ቦቻራ ጠይሚን ገፍትሮ ልጁ ላይ ወረወራት ። ልጁ በጥሩ ጥሬ ጠይሚን ተቀበላት ። ጉንጪን እያሻሸች እርር ብላ እለቀሠች ። ሦስታችንም ተጠቃቀስንና ከበብነው ። ጠይሜ እልጓ እገጪ ጋ ደረሰ ። እኛ በጓደኛችን መመታት ተንገብግበን ልጁን ዘርጥጠን ጥለን ፈሰፈስነው ። በጀርባው ሲወድቅልን ጠምቤ ዘልላ ሆዱ ላይ ፊጥ እለችበት ። የበላውን ፉዝ መልሶ እወጣው ። የታባቱ !

እራቱ እሽከሮች እለብላቢት (ሳማ) ቆርጠው ከበቡን ። ልብሳችንን እንድናወልቅ እስገደዱን። ላለማውለቅ ታገልን ። ጠምቤ ቁምጣ ስላደረገች እግር እግሯን ጠበጠቧት ። ሲለበልባት ጮኸች። ራቴን በቅጠሉ እሹት ። ተቃጠልኩ ። ቃጠሎዬ ይቀልልኝ ዘንድ በጩኸት እበድኩ ።

ጀግናው ጠይሜ ሮጠባቸው ። እሱን ሊያሳድዱ ሲከተሉት እኔና ጠምቤ እቀበቱን ተከትለን በጁኒር ትምህርት ቤት እጥር ሥር ተፈተለክን ። ቦቻራ ስንሮጥ እየሳቀ ያየን ነበር ። « ቁሙም!



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ያዟቸውም !» አላለም ። ተገርሞ ብቻ ነበር ሩጫችንን በጎርናና ሳቁ ያጀበው ። እንዲህ ዓይነት ወንጀል የተሠራብን ከአስፋልቱ ሃምሳ ሜትር አካባቢ ብቻ ገባ በሚል ቦታ በመሆኑ ነበር ጠይሚ የማምለጥ ድፍረቱን ያገኘው ። ሰነገሩ በተፈጥሮውም ደፋር ነው ።

አስፋልቱ ላይ ከወጣ መንገደኞች ያስጥሉታል ። አባራሪዎቹን ይዘው ይፈሥፍሱለታል ። መንገደኞች ፣ ዱርዬዎች ፣ ወታደሮች ሁሉ ሊያስጥሉት ይችላሉ ። እኛን ግን ከእያቴ በስተቀር ሊያስጥለን የሚችል ማንም የለም ።

ሮጠን እያቴ ቤት ደረስን ። በሩ ተቆልፏል ። በገላጋያችንም ስንት መከራ በተቀበልንበት ቂንጮዎቻችንም ተስፋ ቆረጥን ። የምንሄድበት ግራ ገባን ። እግራችን እንደመራን ሸመጠጥን ። ስንሮጥ ያዩን በተለቀለቅነው ነገር እየሳቁ እየተዝናኑብን ያሳልፉናል ።

የሆነች ጢሻ ስናገኝ ገብተን ተደበቅንበት ። ማንም እንደማያገኘን አስበን አረፍ አልን ። ከድካማችን ብቻም ሳይሆን ከሆድ ቁርጠታችንም ተንፈስ ለማለት ። ብዙም ሳንቆይ የቦቸራ አሽከሮች እየሮጡ መጥተው ያለንበት ጋ ቆሙ ። ያለከልካሉ ። እየፈለጉን እንደሆነ ገመትን ። ከያዙን ለዚያ ጅብ ይሰጡናል እንጂ አይለቁንም ።

« ኧረ ! እናቱን ይኼ ቦርጫም  አሁንስ አበዛው እኮ !» አለ አብዲ

« አንተ ! ምን ዓይነት ጩካኝ ነው በገብርኤል ! አንደኛው ልጅ እኮ ዘመዱ መሠለኝ ።»

« የትኛው ?»

« ያ ! ነዋ ...ጭንቅሎ የሚባለው ሳጥን ራስ ! ታድያ ለዘመዱ ያልራራ እኛን ካገኘ ይምረናል እንዴ ?»

« ወይ መማር ...ባከህ ምሕረትን ከሱ አትጠብቅ ።»

« እኔ ግን ወይ ይኼን ሠፈር ጥዬለት እሄዳለሁ እንጂ ሁለተኛ አጠገቡ ዝር አልልም ።» የፈሠ ፈሰነው ወፍራሙ ልጅ ነበር የሚያወራው ።

ከቦቸራ አምልጠው እንደመጡ ተረዳን ። ከያዙን በሱ እልህ ይቀጠቅጡናል ። ወሬያቸውን አላቆሙም ። ዳግመኛ አጠገቡ ላይደርሱ ይማማላሉ ።

« እናታቸውንና ... እኔ ግን እነኚያን ዲቃሎች ባገኛቸው በጥርሴም ቢሆን እልለታቸውም !» አለ ተባብረን የፈሠፈሰነው ወፍራሙ ልጅ ።

ደነገጥን ።

« እነማን ናቸው ዲቃሎቹ ?» አብዲ ጠየቀው

« እነዚያ ናቸዋ ... እነ ጭንቅሎ ያላችኋቸው ። ጭንቅላት አባቱ ይፍረስና ... እንዴ በዚያ



@BOOKALEM

ቀንዳም፣ ጫማ የማያውቅ እግራቸው ሆዴ ላይ ቆመው አስተነፈሱኝኮ ።»

ሲሳሳቁ ተሰማን ። እኔና ጠምቤ ተያይተን ፈገግ አልን ። አውራ ጣቶቻችንን ወደ ኋላ አጥፈን « ወንዳታ !» ተባባልን በምልክት ።

« ከያዙን ይገድሉናል ። ስለዚህ ዘዴ ፈልገን እናምልጥ !» አለችኝ ጠምቤ ወደ ጆሮዬ ተጠግታ ።

የቦቸራ አሽከሮች ተሰብሰበው ይመካከራሉ ። ቦቸራ እጅ ውስጥ ደግመው ላለመግባት ማድረግ ያለባቸውን ይወያያሉ ።

« ቦቼ ! ቦቼ ! ቦቸራ ! እነዚውልህ...እዚህ ጋ ናቸው ያሉት !» አለና የውሸቱን ጮኸ ጠምቤ ድንጋይ እየወረወረባቸው ።

ልጆቹ ፈረጠጡ ። እኛም በተቃራኒ አቅጣጫ ፈረጠጥን ።

የጣሽ ጋራዥን የመኪና መንገድ ሳናስበው ደረስንበት ። መንገድ ላይ ጋሽ በረደድን ኤኔትሬውን ይዞ ሲመጣ አገኘነው ። እኛ ብናየውም እሱ አላየንም ነበርና ሊያቆምልን አልቻለም ። እናም ቀስ እያለ እያቀዘቀዘ በሚሄደው የጋሽ በረደድ ኤኔትሬ ላይ ተንጠለጠልን ። በአራተኛ ጉልት አድርጎ ወደ ቶታል ነዳጅ ማደያ ግራውን ይዞ ታጠፈ ። ወደ ከልላችን የቀላድ እምባ ወሰን ገባን ። እፎይ !

መኪናው ከአስፋልት ወደ ፒስታው መንገድ ሲሻገር ነጠረ ። ጠምቤ የረገጠችው የኋለኛው የመኪናው ግጭት መከላከያ ብረት ከዳት ። ጨብጣ የያዘችውን ስፖንዳ ለቀቀችው ። መኪናው ወደ ፊት ሲስፈነጠር መሬቱ ላይ ከደረቷ ተፈጠፈጠች ። እምቦጭ አለች እንደ ቀፀላ ማሰር። ቀስ ብዬ በአርፋ ወረድኩና ጓደኛዬን አንስቼ ልብሷን ያቆሸሸውን አቧራ አራገፍኩላት ። የተጋጋጠችው ላይ ትኩስ ሽንቴን ሸናሁላት ። ለበለባት ። የመጀመርያ ሕክምና እርዳታ በሽንቴ ሠጥቼ አረጋጋኋት። አንከስ አንከስ እያለች ተቃቅፈን ሄድን ።

ሠፈር እንደደረስን ጠይሜን አገኘነው ። የባህር ዛፍ ጉቶ ላይ ተቀምጦ ቀያይ ዘይቱና ይገምጣል ። ከያዘው ዘይቱና እንዳንድ ሠጠን ። የሆንነውንና ያደረግነውን ተረከንለት ።

ዘይቱና የሚበላበትን ገንዘብ ያገኘው ከጉልቤው ቦቸራ ኪስ ውስጥ ነበር ። ሩዙን ሲለቀልቀው እንደ መታከከ ብሎ ከኪሱ ነበር ቀስቴ ገብቶ ብሩን ያወጣበት ። ደፋሩ ጠይሜ ጉልቤውን ቦቸራን የሸወደበት መንገድ አሲደመመን ። ሁለተኛ ቦቸራን ዘመዴ ነው ብዬ ስሙን እንዳልጠራ አስማለኝና ሳምቡሳ ገዛልኝ ።

« በረደድ ዛሬ ትምህርት ቤት አትሄድም እንዴ ?» አለው ጠይሜ

« አልሄድም !»

« ለምን ? »

« ረፍዶብኛል !»



@BOOKALEM

« እናንተ ትምህርት ቤትም ያረፈደ አይገባም እንዴ ?»

« አዎ ! ደብተሬም አልቆብኛል ።»

« ቢያልቅብህ ታድያ ትርሀስ አዲስ ደብተር አትሰጥህም ?»

« ምን አባክህ ...እሷ አዲስ ደብተር መስጠት አትወድም ።»

የጋሽ በረደድ ደብተር የጠጅ መጎንጫ ብር ነው ። ብር ከኪሱ ስላጣ ነው «ደብተር ጨርሻለሁ!» የሚለው ። የሱ ደብተር ብር ነው ። በቋንቋው በደንብ እንግባባለን ። ጠይሜ ለሁለት ብርሌ መጎንጫ እንዲሆነው አንድ ብር ሰጠው ። ኢይበሉባውንና የውስጥ እጁን አገላብጦ ስሞ ተቀበለው ።

ጠጁን ጥግብ ብሎ እየተንገዳገደ ሲወጣ ጠብቀን « በረደድ !» ስንለው

« እናትከን ጠልዤ ልቀባልህ አመድ !» ይለናል እንስቃለን ።

በመጠጥ ሲደከም በሠፈ ቅንድብ አልባ ፊቱ ላይ የበቀሉት ትናንሽ ዓይኖቹ ብርሃን ማየት ይፈራሉ ። መከደንና መሸሸግ ያምራቸዋል ። ዓይኑ ውሃው ውስጥ ነጭ ቀለም ማየት ኢይቻልም። ራሱ ብቻም ሳይሆን ቅንድቡም በራ ነው ። ልክ እንደ «እንካ ሰላንቲያ» ያለ «ዴ በል እንዴ» የተሠኘ ጨዋታ ያጫውተናል። ተራ በተራ ከኛ ጋር ይሠዳደባል ። ሁሌም ጀማሪው ጠይሜ ነው። በነገራችን ላይ «ዴ በል እንዴ » የስነ ግጥም ሀ ፣ ሁዬን የጀመርኩበት የጥበብ እርምጃዬ ነው።

« ዴ በል እንዴ !»

« ዴ !»

« ትም'ርት ትማራለህ እንዴ ?» አላት

ጠይሜ ለመልስ ምት ተዘጋጀች ።

« ዴ በል እንዴ !»

« ዴ !»

« መስከር አይደብርም እንዴ ?»

በረደድ በኅብረት ሳቃችን እየተናደደ ጠምቢን ተረኛ አደረጋት ።

« እሱን አብሮኝ የሚጠጣውን አባትህን ጠይቀው እሺ ጠይሜ ። ለማንኛውም አንተኛው ... አንተ ባለ እንጨቱን ከረሜላ የምትመስለው ልጅ ... ዴ በል እንዴ !» ብሎ ሰድቦኝ ሲያበቃ ጨዋታውን ግን ለጠምቢ አሻገረው ።

« ዴ !» አለችው ።



@BOOKALEM

« አንት ድባኖ ዱባ ! ዲቃላ ነህ እንዴ ?»

ጠምቤ ፊቷ ተቀያየረ ። መበሳጨቷን አይቶ ፈሱን እየፈሳ ሳቀባት ። በረደድ ከሌሎቹ የሠፈራችን ሠካራሞች የሚለየው ሲሠክር በየመንገዱ እየፈሳ ፣ እያንዛረጠ ነው የሚሄደው - እንደ ጋሽ ሀምዛ የጭነት አህዮች።

« በረደድ !»

« አቤት !»

« ዴ በል እንዴ !»

« ዴ !»

« ቂጥህን ት ...»

« የታባክ አንት ወሮበላ ! እንዳትጨርሰው አሉን ቃል ! እንዳትጨርሰው !» እያለ አሳደደን። በድምፁ እንጂ በሩጫው የማይደርስብን ወፍራም ሯጭ -ጋሽ በረደድ ።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ አስራ አምስት

## ቁልቢ

ከረምት ስለሚሆንብን የሐምሌውን ጉዞ ብዙም አንደፍረውም ። የታህሳሱን ግን በተመቸን ዘዴ እየጠፋን እንሄድበታለን ። ቤተሰቦቻችን ከታህሳስ አስራ ስድስት እስከ አስራ ስምንት ባሉት ቀናት የጉዞና የእንቅስቃሴ እገዳ ይጥሉብናል ። ቤት ሥራሽ ቤተሰብ ተኮር ማዕቀብ። ፍርድ ቤት ያላፀደቀው በየመኖርያ ቤታችን ብቻ የፀደቀ የጉዞ እገዳ ።

ታላላቆቻችን ቁልቢ ሄደው ስለሆኑት ተሰብስበው ጀብዳቸውን ሲያወሩ እንሠማለን ። የምግብ ችግር አይታሠብም ። ለስዕለት ተብሎ በስለት የሚታረድ በሬ ፣ በግና ፍየል ተመጋቢ አጥቶ እንደሚትረፈረፍ ይደሠኩሩልናል ። የስዕለት መኪና እንደ ልብ ቢገኝም ሃምሳ ስምንቱን ኪሎ ሜትር በእግር ተጉዞ እንደመሄድ የሚያስደስት ነገር እንደሌለ ሲያወሩ በተመስጦ አፎቻችንን ከፍተን እናዳምጣቸዋለን ። በየመንገዱ ተጓዦች እንደማይጨካከኑ ፣ ከያዙት እያበሉና እያጠጡ በመተማመን እንደሚጓዙ ያወሩልናል ። ርሀብ ከሌለ ደሞ ምን አስፈሪ ነገር ይኖራል ። የወንድሞቻችን ቀደዳ ለቀጣዩ ዓመታዊ የቁልቢ ቅዱስ ገብርዔል የንግሥ በዓል ከቤተሰቦቻችን ጠፍተን ለመሄድ ያዘጋጀናል ።

ለመጀመርያ ጊዜ ወደ ቁልቢ ስንጠፋ ሦስት ነበርን ። እኔ ፣ አውሬና ወንድይፍራው ባርያው ። አውሬ ትክክለኛ መጠርያው ሳሙኤል መኮንን ይባላል ። ነገር ግን ፀጉሩን ሲላጭ አይቶ ፣ ሲያጎፍረው ኮኮኔው የረዘመ ከንፍ አልባ ዶሮ ፣ ልብሱን ሲያወልቅ ቅጥነቱ እግር ያለውና ቆሞ የሚሄድ ወስፋት ስለሚመስል ነው ይህ ቅፅል ስም የተሠጠው ። በባህርዩም አውሬ ነው ። ሲደባደብ እንደ ድመት በጥፍሩ የሰው ፊት ያበለሻሻል። እንደ ውሻ በጥርሱ ይናከሳል ። እንደ አህያ ይራገጣል ። እናቱን ሙልጭ አድርጎ ይሠድባታል ። እኛ ሠፈር ደሞ እናቱን የሚሳደብ ልጅ በመንደርተኛው ተወግዞ እንደ አውሬ ይቆጠራል ። የኛ ሠፈር ልጅ አንድ ሺህ አንድ ጊዜ ቢባልግ እናቱን ለመስደብ ድፍረት ያንሠዋል ። እናቱን ቀርቶ የሌላ ሰው ወላጅ የኾኑ ሰዎችን መስደብ ቢፈልግ እንኳን የሚጠቀመው ሆዱን ነው ። በሆዱ ነው የሚሞልጫቸው ።

ከሦስታችንም በዕድሜ ታላቁ እኔ ብሆንም በጉዞ ቡድናችን ላይ ግን ምንም ዓይነት የማስተባበርም ሆነ የኃላፊነት ሥልጣን አልተሠጠኝም ። አውሬ ደሞ ታናሻችን ነው ። ጉልቤ ስለሆነ ብቻ እሱ ሳያውቅ ምንም ነገር ማድረግ እንደማንችል አስጠንቅቆናል ። ሸቅለን ገንዘብ ካገኘን በመጀመርያ ለሱ ማስረከብ ከዚያ እሱ የሚሆነውን ወስኖ እንደሚሠጠን ነግሮናል። ከትዕዛዙ ውልፍጥ ካልን እንደሚቀጠቅጠን አስቦክቶናል ። ቁልቢ ስንደርስ በበሬ ቀንድ እንደሚወጋን ፣ በአኒሳው እንደሚፈልጠን ዝቶብናል ።

ገና ለጉዞ ስንነሳ ወንድይፍራው ኪሱ የነበረውን ማስቲካ ለአውሬ ሠጠው ። ግማሹን ለብቻው በላና ቀሪውን ለሁለት እንድንካፈል ሠጠን ። ወንድይፍራውም ባቅሙ « የማስቲካው



@BOOKALEM

ባለቤት እኔ ነኝ !» አለና ለኔ ልጣጩ ላይ ያለውን ስዕል ብቻ ሠጠኝ ። የማስቲካዋን ስኳር በሃሳቤ እያጣጣምኩ ስዕሏን አይበሉባዬ ላይ ልለጥፋት ስል አውሬ መንተፈኝና ወደ ቁልቢ ሲኬድ ኮተት እንደማይለጠፍ ነግሮኝ ኪሱ ከተተው ። ትንሽ እንደተጓዝን ግን ከኔ የመነተፋትን ስዕል ጉንጩ ላይ ለጥፏት አየሁት ። ጉልቤ ነው በሆዴ ከመንገብገብ በቀር ምን አባቱ አመጣለሁ !

ወንድይፍራው ባርያው አዳሪ ትምህርት ቤት ከእህቱ ጋር ነው የሚኖሩትም የሚማሩትም። አባቱን በአካል ሳያውቀው ሞቶበታል ። እህቱ ግን ትንሽ ትንሽ ታስታውሰዋለች። ሁለቱም እናታቸውን ነበር በሚገባ የሚያውቋት ። ለበርካታ ጊዜያት ታማ ፣ ከስትስት ብላ ግማሽ የሰውነት አካሏ መታዘዝ ተስኖት ሞተችባቸው ።

አቅመ ደካማዋ ሴት እያታቸው ዘንድ ስለሚኖሩ ችግራቸውን የሚገልፅ የድጋፍ ደብዳቤ ከቀበሌ ተፅፎላቸው አዳሪ ትምህርት ቤት ገቡ ። ቅዳሜና እሁድ እያታቸው ጋር የማሳለፍ ፍቃድ ተሠጥቷቸዋል ። ታድያ ወንዴ አዳሪ ቤት ውስጥ ስለሚመገቡት ምግብና ስለሚጠጡት መጠጥ እያወራልን ስለሚያስቀናን ወሬውን የምናደምጥ ሁሉ በየቅዳሜና እሁዱ የወላጆቻችንን ሞት እንናፍቃለን ። « ምናለበት እናትና አባቴ ቶሎ ድፍት ባሉልኝና አዳሪ ቤት በገባሁ ፣ ተደራራቢው አልጋ ላይ በተኛሁ ፣ ጠዋት ጠዋት ዳቦ በሻይ ፣ ዳቦ በእንቁላል ፣ ቂንጬ በቅቤ በበላሁ ፣ ወተት አርጎና ጭማቂ በጠጣሁ ፣ ምሳዬን ቀይ ወጥ ፣ ጎመን በስጋ ፣ ወፍራም ምስር ወጥ ፣ ፓስታ ፣ መኮረኒና ሩዝ በበላሁ ። ምናለበት ቶሎ አዳሪ ቤት ገብቼ እራቴን ከበላሁ በኋላ አጥሚቴን በትልቁ ኩባያ ጠጥቼ አልጋዬ ላይ ለሽ ባልኩ !» እንላለን ። የወላጆቻችን በሕይወት መኖር ያበሳጨናል ።

የወንዴ እህት ንግሥት የመስማት ችግር አለባት ። በጣም ጮክ ብለው እያወሩላት እንኳን « እ !» ማለቷ አይቀርም ። እያትየው ወደ ኾነ ቦታ ግቢያቸውን ጥለው ሲሄዱ ጠብቀን እንገባና እንጫወታለን ። እሳቸው ግቢ ውስጥ ካሉ መግባት አይፈቀድልንም ። « ጥፉ ከዚህ ልጆቼን ታበላሹብኛላችሁ !» ይሉናል ። ሊያበላሹን የተዘጋጀው የሳቸው የሆነው ወንድይፍራው ባርያው መሆኑን አያውቁም ። እኛም ለሳቸው አንናገርበትም እንጂ እዚያ አዳሪ ቤት ከገባ በኋላ እየተደበቀ ሲጋራ ሲያጨስ አይተነዋል ። እሳቸው እግራቸው ወጣ ሲልለትም እየጠበቀ ከቤት ዕቃ እያወጣ ለቆራሊዮ ይቸበችባል ። በሽጠበት ይጋብዘናል ።

ወደ ቁልቢ ጠፍተን ለመሄድ ስንመካከር ንግስት አጠገባችን ነበረች ። እንደማትሰማን ርግጠኞች ሥለነበርን ይዘን ስለምንጠፋው ነገር ተነጋገርን ።

« ቁልቢ ምን ልታደርጉ ነው የምትሄዱት ?» አለችን ።

ደነገጥን ። ትሰማለች እንዴ ?

« ባክሽ ዝም በይ ! ማን እሄዳለሁ ሲል ሰማሽ ?» ወንድይፍራው ታላቋ ብትሆንም አይፈራትም ።

« እ !»



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

« አ ! ትይኛለሽ እንዴ ? በቃ አንቺ ምስጢር ካልሆነ አትሰሚም ማለት ነው ?»

« ትንሽ ጮከ በልልኝ የምትለው አይሰማኝም ፡፡» ጆሮዋን በጣቶቿ ደግፋ አስጠጋችለት ፡፡

« ቀልቢ በኦሮምኛ ምን ማለት ነው ? » ጮኾ ጠየቃት ፡፡ አጯጯኹ የሹፈት ነበር ፡፡

« ነጭ ሽንኩርት !»

« በቃ እኛ የተጠያየቅነው እሱን ነው እሺ !»

« አ !»

ሦስታችንም ማሲኖዳችንን ከየቤታችን ይዘን መጣን ፡፡ «ማሲኖዳ» የወታደር ሻንጣ ነው ፡፡ ከለበስነው ውጪ ፎጣም ጋቢም አልያዝንም ፡፡ ስንመለስ ስጋ ይዘንበት የምንመጣውን ማሲኖዳችንን አዝለን መንገድ ጀመርን ፡፡ በአስፋልት ከሄድን የሠፈር ልጆች ያዩንና ያስመልሱናል ፡፡ ለቤተሰቦቻችንም ተናግረው ያስገርፉናል ፡፡ ስለዚህ የነበረን አማራጭ በጊዮርጊስ ቤተ ክርስትያን በኩል ቁልቁል በቁጥቋጦና በእርሻዎቹ ውስጥ እያሳበርን አማሬሳ መድረስ ነው ፡፡ የአማሬሳ ሰው ልጅ እንጂ የማን ልጅ እንሁን እንሁን ስለማያውቀን ከዚያ በኋላ በነፃነት በአስፋልት እንጓዛለን ፡፡

እረኞች ይዘው እንዳይገርፉን ለምነነው ቁልቢ ድረስም አብሮን እንዲጓዝ ግድግዳውንና ወለሉን ስመንለት የተማፀንነው ቅዱስ ጊዮርጊስ የመጀመርያ ግዳጁን በልመናችን መሠረት ፈፅሞልናል ፡፡ የአማሬሳን አስፋልት እንደረገጥን ወደ ኋላችን ዘወር ብለን ከነ ግርማ ሞገሱ ከፍታ ላይ ጉብ ያለውን ቤተ ክርስትያን ድምፅ ሳናወጣ በእጃችን ተሠናበትነው - ባይ ባይ ጊዮርጊስዬ !

አማሬሳ ላይ ያለውን ትልቅ ድልድይ በፍጥነት ተሻግረን ኬላው ጋር ስንደርስ አረፍ አልን ፡፡ የስዕለት መኪና ጥበቃ ፡፡ በርካታ ለማኞችና ሙጫጭሬዎች ተሠብስበው የሚመጣውን መኪና ይጠብቃሉ ፡፡ የተባለው የስዕለት መኪና መጣ ፡፡ አርጅቷል ፡፡ ሹፌሩ መኪናውን አጠገባችን አቁሞ በሩን ዘጋና ወደ ሠፈር ውስጥ ገባ ፡፡ አሮጌ የጭነት ኤኔትሬ ነው ፡፡ የሆነ ረዳት ነገር መኪናው ላይ ወጣና

«የስዕለት ! የስዕለት ! ወደ ቁልቢ በመኪና መሄድ የምትፈልጉ ! የስዕለት ! የስዕለት ! በነፃ ነው፡፡ ያለ ምንም ከፍያ ወስደን እንመልሳችኋለን !» አለ ፡፡

ሦስታችንም በፍጥነት ኤኔትሬው ላይ ወጥተን ቁብ አልን ፡፡ ዕድሜ ለጋሽ በረደድ መኪና በኤኔትሬ ላይ አወጣጥ የዳበረ ልምድ አግኝተናል ፡፡ ሌሎቹም ሰዎች እየተጋፉ ወጡ ፡፡ መኪናው ጥቅጥቅ ብሎ ሞላ ፡፡ ሰዎቹ ርስ በርሳቸው በገፋኸኝ ተጠጋልኝ መጣላት ጀመሩ ፡፡ ከትልልቅ ሰው ያውም ወደ ገብርዔል ከሚሄድ መንገደኛ የማይጠበቅ ሥድብ ይሠዳደባሉ ፡፡ ሁለት ለማኞች ተደባደቡ ፡፡ ረዳቱ መሬት ቆሞ መኪናው ላይ የሚሆነውን እያየ ይስቃል ፡፡

የሾኑ ትልቅ ኮተት የተሞላበት ማዳበርያ የተሸከሙ ወፍራም ለማኝ አውሬን እንዲጎትታቸው እጃቸውን ዘረጉለት፡፡ « በመኪና መሄድ ሲያምርህ ይትር !» እያለ አሾፈባቸው ፡፡



@BOOKALEM

« የኔን እንጀራ ይስጥህ !» ረገሙት ።

እጃቸውን ወደኔ ዘረጉ ። አስቀድመው ማዳበርያቸውን አቀበሉኝ ። ከወንዴ ጋር ተጋግዘን ጫንነው ። ከዚያ እኔና ወንዴ በሁለት በሁለት እጃችን አንድ አንድ እጃቸውን ይዘን ሳብናቸው ። ጥንብ ናቸው ። መኪናውን የምንጎትት መሠለኝ ። እግራቸውን ጎማው ላይ እያረማመዱ ከመሬት ከፍ ከፍ አሉ ። ከበዱን ። ጭራሽ በአየር ላይ ወደኋላቸው ተለጥጠው ወደራሳቸው ይጎትቱን ገቡ። አልቻልናቸውም ።

እጃችንን ጥፍንግ አድርገው ይዘውናል ። እግሬ ሥር ተቀምጦ የነበረ አንድ እግሩ ላይ የከረመውን ቁስል የጨፈለቅኩበት ለማኝ ከእግሬ ስቅስቅ አድርጎ አነሳኝ ። ሚዛኔን መቆጣጠር አልቻልኩም ። ከመኪናው ስፖንዳ አፈትልኪ እየወጣሁ ወንድይፍራው ተያይዞ ላለመውደቅ እጃቸውን ሲነከሳቸው አየሁት ።

« አፈር ብላ አንተ የቡዳ ዘር !» ብለው ለቀቁት ።

እኔን ይዘው መሬት አረፉ ። እሳቸው በጀርባቸው እኔ በግንባሬ ተተከልኩ ። በአወዳደቃችን ከመሳቅ ባለፈ የሚያዝን ፊት ማየት ተሳነኝ ። ከሁሉም ሰው ፊት ላይ ዕድሜ ለኔና ለሳቸው ፈገግታ ይታፈሳል ። « እናታቸውንና የጀምስ ቦንድን ፊልም የሚያዩ መሠላቸው እንዴ ?» አልኩኝ በሆዴ። ላለመፎገር አብሬያቸው ሳቅኩ ። እያመመኝ ፣ ግንባሬን እያሻሸሁ መኪናው ላይ ወጣሁ ። አባባ ግን አልተነሱም ። ተኝተው ያቃስታሉ ። እሳቸው ከወደቁበት ሳይነሱ ፣ ዕቃቸው ከመኪናው ሳይወርድላቸው ሹፌሩ መጣ ። ሕዝቡ በደስታ ጮኸ ። አጨበጨበ ።

ሹፌሩ ጭንቅላቱን ይዞ ቆመ ። ረዳቱ ሳቁ እያደናቀፈው የኋሊት እግሬ አውጪኝ አለ ። እያየነው በዘይት ፋብሪካውና በጉልቱ መሃል ወደ ላይ ሮጠ።

« ምድረ ኮተታም ! ከመኪናዬ ውረዱልኝ ። ማን ፈቅዶላችሁ ወዴት ልትሄዱ ነው መኪናዬ ላይ የሠፈራችሁት ?» ሹፌሩ ተቆጣ ።

የሠማው ፣ ጆሮ የሠጠውም የለ ። ይልቅ እየመሸ ስለሆነ በጊዜ ቁልቢ እንድርሰን ማደርያችንን እንድንፈልግ እንዲተባበረን ጠየቅነው « ልንሄድ ነው ! ሊነዳው ነው !» በሚል የጋራ ጩኸት ።

« አዳሚ የአጎትህ አህያ መሠለህ እንዴ ዝም ብለህ መኪናዬ ላይ የምትወጣው ? ና ውረድ አንተ ገንቦ ራስ !»

ከዛ ሁሉ ሰው እኔ ላይ ማፍጠጡ አናደደኝ ። መልሼ እንዳልሠድበው ድንጋይ መፍለጫ መራጃ በሚያክል እጁ ይደፈጥጠኛል ።

« ኧረ ባክህ ሹፌር በጊዜ እንሂድ ! የስዕለት ብለህ ስታበቃ ውረዱ ትላለህ እንዴ ? ወይስ በቁጥር ነው የተሳልከው ? እኔ እንደሁ ደጃ ሠላሙ ላይ ካላደረስከኝ ከዜች መኪና ወርጀ መሬትን አልረግጥም ።»



@BOOKALEM

« መኪና ብርቅህ ነው እንዴ ሰውዬው ? እኛም እኮ ወያኔ ለኢትዮጵያ ታግለን ስናበቃ 'የደርግ ወታደር' ብላ አሽቀንጥራ ጥላን ነው እንጂ አይፋና ካማዝን አስፋልት አስለቅቀን በአየር የምናበር ነበርን ። ደሞ ይኼን የቆሻሻ ገንዳ የመሠለ ሳጥንህን ነው እንዴ መኪና ብለህ የምትጠራው ? መኪና ብለህ ስትጠራው እየደነገጠ ይባስ አረጀብህ ። መኪና ማለት አየሃት ?» በእጁ አንዲት ፅዳ ያለች ስፖርቴጅ ሬንጅ ሮቨር አስፋልቱ ላይ ስትከንፍ አሳየው ። ሰውዬው ንግግሩ ያሲቃል እንጂ የተጋተው የጠላ ሽታስ ካጠገቡ ያስርቃል ።

ሹፌሩ ግራ ተጋባ ። በሠማው በኾነው ነገር አዘነ ። ሁላችንም « ቁልቢ ካላደረስከን አንወርድም ፤ ሰዓታችንን አቃጥለህብናል !» አልነው ።

ፖሊስ መጣ። ሹፌሩ ጭንቅላቱን በእጆቹ ይዞ ኡኡታውን ያስነካዋል። ሕዝቡም ገገመ። ታዋቂውን በውሻና በጅብ ሠገራ ፣ በቢርቢራ ፍሬ ፣ በሲሚንቶና ኖራ እንደሚቀመም የሚነገርለትን የአማሬሳ ጠላ ሲጋት የዋለ ፖሊስ መኪናው ላይ ወጥቶ በቆመጥ መማታት ጀመረ። ምድረ ሽማግሌና አሮጊት ከመኪናው እየዘለሉ መሬት ፣ መሬት ፣ መሬት ፣ መ ...ሬት ።

ወደ መሬት የዘለለ እንጂ ከመሬት የተነሳ ሽማግሌና አሮጊት የለም ። ይህን ሁሉ ያደረገው ረዳት በአንድ ሸርጥ ያገለደመና በጉንጩ ጫት የታጠቀ ፣ ዓይኖቹ ከመጠን በላይ የተበለጠጡ ጎረምሳ ጆሮውን ተይዞ እየተጎተተ መጣ ። ያሳዝናል ልጁ የመኪናው ረዳት አልነበረም ። ይልቅስ በመንደሩ የታወቀ ተንኮለኛ ነበር ። ተንኮል ጠምዛዛ የፊት ገፅታና አጭር ቁመት ያስታቀፈው ድዊ ።

ትርምስ ፣ ግርግርና ሁካታው አካባቢውን ሌላ ድባብ ሠጠው ። የለማኞቹ ስድብ ፣ ርግማንና ለቅሶ ቦታውን የጦርነት ፣ የጠብና የንትርክ ቀጠና አስመስሎታል ። ፖሊሱ የዚህን ተንኮል ጠንሳሽ በፕላስቲክ ቆመጡ ፊት ለፊታችን ለጠለጠው ።

አስፋልቱ ላይ የሚካኤልና የጨፌ ሠፈር ጎረምሶችን ተመለከትን ። አስራ ሦስት ወንዶች ናቸው ። ትልቅ ቴፕ ሪከርደር ተሸክመዋል ። ሁሉም ሻንጣዎቻቸውን አዝለዋል ። ጫታቸውን በፌስታል አርገው ሱሪያቸው ላይ የሚገኘውን የቀበቶ ማስገቢያ ተጠቅመው አስረውታል። ከፌስታል እያወጡ ይቅማሉ ። እግራቸውን ከመሬት በነቀሉ ቁጥር በፌስታል ያለው ጫት አብሮ ይወዛወዛል ። በእጃቸው ከያዙት ኮዳ ውሃም ለሰላሳም እየተጎነጩ በጥሩ እርምጃ ይጓዛሉ። አማሬሳ ሲደርሱ ቆም ብለው በሙዚቃቸው እየደነሱ ከብበ የሚመለከታቸውን ሕዝብ አዝናኑት። ብሬክ ለጉድ ተጨፈረ ። በሬጌ ሙዚቃ ተዘለለ ። በትግረኛው ተሽከረከረው በሸንዬው ቀንጠሰ! ቀንጠስ አሉ ። ሲያምሩ ! ጩኸት ትርምሱ ፀጥ አለና ዓይኖች ሁሉ ወደ ጎረምሶቹ ጭፈራ ተወረወሩ ። እጆች ሁሉ « ሞራል ! ኧረ ሞራል !» የሚል ቅስቀሳ ሳይሠሙ በፍቃደኝነት አጨበጨቡ ። ተቀላቀልናቸው ።

መጀመርያ አካባቢ ጎረምሶቹ የሦስታችንን መቀላቀል አልወደዱትም ነበር ። ከመሃከላቸው አንደኛው ልጅ « ቴፕና ሻንጣ ይሸከማሉ ፣ በእግራቸው እንጂ በኛ እግር አይሄዱ ፣ እናዝላቸው ለምን አትተዉአቸውም ?» አለ ። ሸክማቸውን እንደምንጋራቸው ሲገለፅላቸው ቀላቀሉን ።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ጸግራችን እየተንቀጠቀጠ አስጠሊታውን የደንገጎ ዳገት ጨርሠን ቀርሳ ከተማ ገባን። ከተማዋ በምሽት የጎዳና መብራቶቿ ደምቃለች ። የመንገድ መብራቶቿ ብዛትና ጥራት ለከተማዋ ውበት የበኩላቸውን አስተዋፆ አበርክተዋል ። ለከተማዋ ከተፈጥሮ ጨለማ ያልተላከላት አስመስለዋታል። የባላ ቅርፅ ያለው አስፋልቷ ቁልቁለቱን እንደርድሮ ወስዶ ሲያበቃ በዳገት አስምጦ ፣ ፈስ አስጨርሶ ነው የሚያሥናብተው ።

ርሀብ እያንገላታን ነው ። ጎረምሶቹ የማይቅም አብሯቸው እንደማይሄድ ስለነገሩን ሦስታችንም መቃም ጀምረናል ። ለጫት ስስት እያውቁም ። ሁሉም ይራብሱናል ። (ቆንጥረው ይሠጡናል ።) ከቦርሳቸው እያወጡ ከሚገምጡት ዳቦ ግን አያቀምሱንም ። ሲገምጡት ዓይን ለዓይን ስንጋጭ እንኳን ያፈጡብናል ።

« የለማኝ ልጅ ! ምን አባክ ታየኛለህ ? ገዝተህ አትበላም እኔ ላይ ከምታፈጥ !» ይሉናል ።

በጎረምሳ እርምጃና ጉርሻ ተሳቀቅን ። በዱብ ዱብ እየተከተልናቸው የቀርሳን ዳገት እንደጨረስን ቴፕ የመሸከም ተራው የኔ ኾነ ። የአባቴን የከት ልብስ ማስቀመጫ ሳጥን የሚያክል ቴፕ ትከሻዬ ላይ ጫኑብኝ ። ማይክሮፎኑ በጆሮዬ ትይዩ ስለነበር ጩኸቱ እንዳያደነቁረኝ ፈራሁና አዞርኩት። ጆሮዬ ትንሽ እረፍት አገኘ ። ቴፑ በግራ ትከሻዬ ስለነበረ በቀኝ ጆሮዬ አቅጣጫ ያሉት ልጆች ሙክ ብለው የሚያወሩት ይሠማኛል ።

« ባከህ እግሬ እየዛለ ነው ።» አለ ኮፍያውን ገደድ አድርጎ ሲጋራ የሚያጨሠው ልጅ

« እኔም እየደከምኩ መሠለኝ ። ልቤን እያጥወለወለኝ ነው ። ሚካኤልን ነው የምልህ መንገዱ ጋዝ ጋዝ ብሎኛል ።» ተመሳሳይ ስሜቱን ከጓደኛው ሠማ ።

« በዚህ ሁኔታ ግን ይኼንን ቴፕ ተሸክመን እንኳን ቁልቢ ላንጌይ የምንደርስ አይመስለኝም ።»

« ለምን ?»

« አንዴ ! ሕዝበኔ 'ኮ ደከሞታል ። አዳሜ መርቅና መሠለህ ፀጥ ያለው ?»

« እና ?»

« ደከሞት ነዋ _ ጎማ ተንፍሶበት !»

« እነዚህ ፈላዎች ግን ጠንካራ ሳይኾኑ አይቀርም ።»

« እውነትህን ነው ። አትሾፈውም እንዴ የሆነ ስልባቦት ነገር ! ሲያዩት በቆዳ የሠፉት የሰው ምስል እንጂ ሰው'ኮ አይመስልም ። እየኸው ግን ምንም የተሸከመ'ኮ አልመሠለውም ። ይኼ እንኳንስ ቁልቢ ሐርና አድርስ ቢባል የሚደከመው አይመስልም ። እንደ ጋሽ ሽፈራው እህዮች እየፈሳም ቢሆን ማድረሱ አይቀርም ። » አለና ተሳሳቁ ።

« አንተ ! የቴፑ ድምፅ ደሞ እንዴት ነው ሞቅ አላለብህም ?»



@BOOKALEM

«እንዴት ሞቅ አይልም ታድያ !ሁለት ቴፕ አይደል እንዴ የተሸከመው !»

« ኧ ! አልገባኝም ::»

« ምን አስደነገጠህ ? አንደኛው የኛ ንብረት የሆነው ፓናሶኒክ ሁለተኛው ደሞ የራሱ ተሸከ ሞት የሚዞረው ባናት ሶኒክ » አለና በእጁ ጭንቅላቱን ጠቆመው ::

ከትከት ብለው ሳቁ :: አረርኩ :: በተሸከምኩላቸው በጭንቅላቴ እንደሚያሾፉ ገባኝ :: እልህ ተናነቀኝ :: እንቅፋት የመታኝ አስመስዬ ቴፑን ያለ የሌለ ኃይሌን ተጠቅሜ ወርውሬ በጥንቃቄ በደረቴ ወደቅኩ :: የባትሪ ቤቱ ከዳን ተከፈተና ስምንት የባትሪ ድንጋዮች ተራ በተራ ተስፈንጥረው ተፈተለኩ :: እጀታው ተገነጠለ :: ማይክሮፎኖቹ ከተሠኩበት እየተነጠሉ እንደ በግ ገመዳቸውን እየጎተቱ በረሩ :: ሁሉም አፈጠጡብኝ :: የደነገጥኩ መሠልኩ ::

« አዳሜ ! አሁን ፓናሶኒክህን ከጥቅም ውጭ አድርጌልሃለሁ :: በባናት ሶኒኬ ትጨፍር እንደኾነ አይሃለሁ ::» አልኩ በራበው ሆዴ ::

ባትሪ ድንጋዩን ሲቃቅመው ቢያስገቡትም ቴፑ መናገር ተሳነው :: ማይክሮፎኖቹን ገጣጥመው ሞከሩት - ድምፅ የለም :: እንጀቴ በሃሳብ ቂቤ ጠጣ ::

አውሬ ጎረምሶቹ ሲመካከሩ የሰማውን መጥቶ ሹክ አለኝ :: ከከተማው ስንወጣ በቀርሳና በላንጌይ መሃል በሚገኝ ጫካ ውስጥ አስገብተው ሊሰጠልጡኝ እንዳሰቡ ነገረኝ :: የቴፑ ባለቤት ከመሃላቸው እንደሴለና ተውሠው ያመጡትን ቴፕ ማበላሸቴ እንዳስቆጫቸው የሠማውን አሠማኝ ::

መንገድ ላይ ሻይ ፣ ቡና ፣ ጠላ ፣ አረቂ ፣ ቢራ ፣ ለስላሳና ምግብ የሚሸጥባቸው ድንኳኖች ማየት የተለመደ ነው :: ድንኳኖቹ ለመንገደኞች እረፍት መውሠጃ ተስፋዎች ናቸው :: የተደረደሩ ጥቂት ወንበሮች ቢኖሩም አብዛኛው እግረኛ የሐረር ፣ ድሬዳዋና ጅጅጋ ሰው ነውና ቂጥና ከንዱ ለፍራሽ ይቀርባል :: የምሥራቅ ሰው ከወንበር ይልቅ ጫማውን ወለቅ አድርጎ ዘና ብሎ የሚያርፍበት ምንጣፍ ይመቸዋል ::

ከድንኳኖቹ በአንዱ ውስጥ የጉዞ ቡድናችን ተግተልትሎ ገባ :: ሁሉም ኪሱን እየፈተሸ ባለው ልክ ለራሱ አዘዘ :: ሁሉም እራሱን ብቻ ጋበዘ :: ይጋብዙናል ያልናቸው ጎረምሶች የሚበሉትም የሚጠጡትም ለየራሳቸው ብቻ ሆነ :: ለካ እኛ የማይከፈለን አሽከሮቻቸው ነን :: ከሥራቸው ለመጥፋት ተመካከርን :: ባለ ድንኳኗን ተጠግተን የፈለገችውን ሥራ አሠርታ ኡፋ (ቡሌ) እንድትሠጠን ለመንናት :: አባረረችን :: አውሬ ላይ ውሃ ደፋችበት :: ሠበብ አገኘንና ሮጥን ::

ከአንድ ዛፍ ሥር ባለ ባትሪ ሬዲዮ ይዘው ሁለት ጎልማሶች ተቀምጠዋል :: የቁልቢ መንገደኞች ናቸው :: ባጠገባቸው ስናልፍ ጠሩን :: ይዘው ሊያስቀጥቅጡን መስሎን ስናመነታ

« ልጆች ! ወደ ቁልቢ ነው አይደል የምትሄዱት ? ኑ ትንሽ እረፍ ብለን አብረን እየተጫወትን



@BOOKALEM
Scanned by CamScanner

እንሄሄዳለን !» አሉን አንደኛው ሰውዬ ።

ተጠጋናቸው ።

አጠገባቸው ተቀምጠን ቦምቦሊኖና በጣሳ የታሸገ ለስላሳ ሠጡን ። እስከዚያን ቀን ድረስ ኮካኮላ በጠርሙስ እንጂ በጣሳ ታሽጎ አይቼው አላውቅም ። አውሬም እይታው እንደማታውቅ ርግጠኛ ነኝ ። ወንዴ ግን አዳሪ ቤት የጌታ ልደትን ሲያከብሩ ጠጥቶ ሊሆን ይችላል ። ላለማቁለጭለጭ ብሎ ይኾናል ያልነገረን ።

ቦምቦሊኖውን እየገመጥን ኮካችንን ጠጣን ። ባዶውን ጣሳ ማሲኖዳዬ ውስጥ ጨመርኳት። እነ ጠምቤ ላይ ማናፈያ ትሆንኛለች ። ይኼን ምድረ የድህ ልጅ ጣሳውን በእማኝነት እያቀረብኩ፣ እያስሸተትኩ ቁልቢ እንዴት ስገዘናና እንደከረምኩ እየነገርኩ እስንመዝዋለሁ። ብፈልግ ደሞ ጣሳዋን እያስጎበኘሁ ከሠፈሬ ልጆች የቆሎና የሳንቲም ገቢዬን እሠፋለሁ ።

ሰዎቹ ከያዙት ሻንጣ ውስጥ ለኔ ጋቢ ፣ ለአውሬ ፎጣ ፣ ለወንዴ ደሞ ሸርጥ ሠጡን። ሁለቱም ፍፁም ትሁት የኾኑ ሰዎች ናቸው ። ለኛ ለትንንሾቹ የማይገባንን ትልልቅ ክብርና ትህትና አሸከሙን ።

ሁለቱም አዲስ አበባ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ሠራተኛ እንደሆኑና በአውሮፕላን ድሬዳዋ ድረስ መጥተው የእግር ጉዟቸውን ከድሬዳዋ እንደጀመሩት አጫወቱን ። አቶ ፍሠሀ ወልደ አማኑኤልና ስማቸውን የዘነጋሁት ሰው ናቸው ።

የዚህኔ ግራ ተጋባሁ ። ስለ ትራፊክ የማውቀውን ሁሉ በሃሳቤ ቧጠጥኩ ። እኛ ሠፈር እንዳሉት እንደነ ጋሽ መሀመድ ፣ ጋሽ ጠንክር ፣ ጋሽ ታደሠ የፈለጉትን መኪና በፊሽካ እያስቆሙ የሚፈትሹ፣ እንደልባቸው የፈለጉትን መኪና አስቁመው የፈለጉበት ድረስ ሳይከፍሉ ወይም እንደኛ ከሹፌሩ ተደብቀው ሳይንጠለጠሉ የሚሄዱ ባለ መብት አድርጌ ሳልኳቸው ።

ይህን የማውቀውን የትራፊክ ሞያ በሃሳቤ አየር ላይ ይዤው ወጣሁ ሰማይ ላይ ። እነ ጋሽ ፍሠሀ አየር ላይ ቆመው አውሮፕላኖችን እያስቆሙ የሚፈትሹ ። አብራሪውን በመስኮት በኩል ወታደራዊ ሰላምታ ገጭ አድርገው ሠጥተው ፣ አነጋግረው ፣ መንጃ ፍቃዱን ተቀብለው ፣ የቅጣት ካርኒ ሲቆርጡበት ፣ ፓይለቱ ሲናደድ ፣ በሩን ከፍቶ ወርዶ ሲለምናቸው ፣ የሠሌዳ ቁጥሩን ፈትተው ቅጣቱን ካልከፈልክ አይመለስልህም ሲሉት ፣ በሰማዩ ላይ በእግራቸው እየተዟዟሩ የመጣውን አውሮፕላን ሁሉ እያስቆሙ የፈለጉበት አገር በነፃ ... ቢፈልጉ « እነ እግዚአብሔር ሠፈር አድርሰኝ !» እያሉ አብራሪው ተሽቆጥቁጦ በር ከፍቶ አስገብቶ ሲያደርሳቸው ...

« አንተኛው ... ጋቢ የለበስከው ልጅ ማን ነበር ያልከኝ ስምህን ?» አሉኝ ስማቸውን የዘነጋ ሁት ሰውዬ ።

« ጭንቅሎ !»



@BOOKALEM

« ምንድን ነው የምታስበው ታድያ ... ቤተሰቦችህ ናፈቁህ እንዴ ?»

« አአይ ...ኸረ ገርሞኝ ነው ::»

« ምኑ ገረመህ ?»

« የአውሮፕላን ትራፊኮች ነን አላላችሁም እንዴ ?»

« እና ብንልህስ ?»

« አየር ላይ ቆማችሁ ...»

ንግግሬን ሳልጨርስ ሳቃቸው ቀደመኝ ::

«እውነትም ጭንቅሎ ! እንዴት ያለ ተመራማሪ ጭንቅላት ነው ያለህ በል !» ጋሽ ፍሠሀ አደነቁኝ ::

በሕይወቴ ውስጥ ከተደሠትኩባቸው በጣት የሚቆጠሩ ቀናት አንዱ ያ ቀን ነበር :: ባገኘኋቸው ሰዎች ዘንድ ሁሉ የሚያሰድበኝ ጭንቅላቴ ዛሬ ግን ከብር አጎናፀፈኝ :: ዕድሜ ለገብርዔል ስለ ጭንቅላቴ ቅርፅ መልካም ዜናና እፎይታ ሠማሁ :: ምናለበት የሠፈሬ ፎታቶች አብረውኝ ሆነው አድናቆቱን በሠሙልኝ :: ያውም ባዲሳባ ሰው መደነቄን ::

ጎረምሶቹ ባዱስ ጉልበት ያንን ሥራ ያቆመ ቴፕ ተከፋፍለው ተሸከመው ባጠገባችን ቁልቢ ሲያገኙን እንደሚዘለዝሉን እየዛቱ አለፉ :: ፍጥነታቸውም ቀድመናቸው በመሄዳችን የሆነ ቦታ ላይ ተዝለፍልፈን ወድቀን እንደሚያገኙን በመተማመን ነበር ::

ከሰላሳ ደቂቃ ቆይታ በኋላ ጉዞ ጀመርን :: ተራ በተራ የነ ጋሽ ፍሠሀን ሻንጣ እየተሸከምን የላንጌይ ከተማን አለፍን :: የሆነች ከሃያ አምስት የማይበልጡ የሳር ቤቶች ያሏት ቦታ ስንደርስ መንደርተኞቹ በምርቃት አጀቡን :: « ነገያን ገላ ! ጂብሪል ኢሲን ወጂ ሃተኡ !» (ሠላም ግቡ ! ገብርኤዔል ከናንተ ጋር ይሁን !) አሉን :: ለነ ጋሽ ፍሠሀ እየተረጎምንላቸው « አሜን ! አሜን !» አሉ :: አንዲት ድሪያና ጎገራ የለበሰች ትልቅ ሴትዮ ወተት በቅልና ጡፍጡፋ(የስንዴ እንጀራ) ይዛ ወደኛ መጣች :: በባለ ጆሮ የ«ፕላስቲክ» ኩባያ እየቀዳች አጠጣችን :: በወይራ ጭስ የታጠነው (ቆራሱማ የተደረገው) የወተት ዕቃ ወተቱን ይበልጥ እንዲጣፍጥ አድርጎታል :: ሆዴ ጢጥ ብሎ ሞላ ::

« ኹዳ ሜ መሀሊቃን ኩን ጂብሪሊፍ ኢቲከና :: (እንኩ እስቲ ይህን ገንዘብ ለገብርዔል ስጡልኝ::)» አለችና ድፍን አምስት ብርና ሁለት ሻማ ለጋሽ ፍሠሀ ሰጠቻቸው ::

የሐረር ኦሮሞ በአብዛኛው ሙስሊም እንደሆነ አውቃለሁ :: «ሙስሊሟ ሴትዮ እንዴት ለገብርዔል ስዕለት ታስገባለች» አልኩ ለራሴ::

ከተማዋን ወጣ እንዳልን በስተ ግራ በኩል ከአንድ ከፍተኛ ቦታ ላይ የመስቀል ቅርፅ ያለው ነጭ ፍሎረሠንት አምፑል ይበራል :: የአካባቢውን ጭለማ የጠረመሠ ደማቅ ብርሃን::



@BOOKALEM

በቤተ ክርስትያኑ ድባብ ዙርያም የተለያዩ ቀለማት ያላቸው አምፑሎች ተራ በተራ ብልጭ ድርግም ይላሉ። የመድረስ ተስፋችን ሙሉ ሆነ ። ተስፋችን ግን ተስፋ ብቻ ፣ የሚታይ ማንም እንዳይደርስበት ራቅ ተደርጎ የተንጠለጠለ ። በተለይ « አርብ ሮብ » የምትባለው ዳገት ፈስ ታስመልጣለች ። ሌሊቱን ሙሉ ተጉዘን አድረን ወፍ ሲንጫጫ ቤተ ክርስትያኑ ደጃፍ ደረስን። ተመስገን ። ያንን አስለቃሽ መንገድ አገባድደን የለኮሱት ጧፍ እየተንበለበለ ፣ ለአካባቢው ድምቀትና ሙቀት በሚያዋጡ ነጭ በነጭ ሰብሠው ተግተው በሚፀልዩ ሰዎች መሃከል ተገኘን ። እንዴት ያምራል ? ሙቀቱ ደስ ሲል ።

በምግብ ሳንንዳ ቁልቢ ካደረሱን ደግ ሰዎች ጋር ሲነጋ ተለያየን ። ቁርሳችንን አብልተው ለሦስታችንም አምስት አምስት ብር ሠጥተው ስመው ሸኙን ። እኔ ግን የፖስታ አድራሻቸውን በጽሑፍ ተቀበልኳቸው ። ምኑንም በማናውቀው መንገድ እየተሸሎከሎከን ዞርን ። የቁልቢ ብርድ ያለ ሙዚቃ ያስጨፍራል ። ቶሎ ቶሎ ያስርባል ። መንገዱ ለቸኮለ አይሆንም ። እንኳን ለቸኮለ ቆሞ ለሚያወራም አይሆንም ። ሕዝቡ እንደ ጎርፍ ተያይዞ ነው የሚሄደው ። መንገዱ ቆሞ ለማውራት ስለማይመች ወደ ታች እየሄዱ ወደ ላይ የሚሄድን ሰው ማውራት ቢፈልጉ በሚያወሩት ሰው አቅጣጫ ተጉዞ ወሬው ሲያልቅ መመለስ የግድ ይላል ።

አውሬ ብራችንን ተቀብሎ ከሥራችን ጠፍቷል ። ወንድይፍራውም ለስላሳ ተሸከመን ያገኘነውን ሁለት ብር ከስሙኒ ይዞብኝ ተሠውሯል ። ያለኝ ሀብት ባዶ ማሲኖዳ ብቻ ነበር ። ምን አልባት ሲጋ ካገኘሁ ብዬ የያዝኩት የተስፋ ሻንጣ ። ወደ ቤት ስመለስ በመጥፋቴ እንዳልገረፍ የሚከላከልልኝ ቤተሰቦቼን መሸወጃ ስጋ መያዣ ሥልቻ ጀርባዬን እንዳቀፈ ተቀምጧል ።

ከወደ ኋላዬ « ጭንቅሎ ! ጭንቅሎ !» የሚል የጥሪ ድምፅ ሰማሁ ። ስዞር ባየሁት ደነገጥኩ ። እምብርት – ደሳለኝ አስጨናቂ ነበር የጠራኝ ። እኛ ከሐረር ከመነሳታችን በፊት ሠፈር ከእህቱ ጋር « ምሳ አልሠጥሀም !» ብላው ተጣልቶ ሲያለቅስ እንደነበር ትዝ አለኝ ። በሠፈራችን የታወቀ ሌባ ነው ። የተሠጣ ርጥብ ልብስ ፀሐይን ወከሎ ያደርቃል ። ሲጥ የያዘ ቡሀቃ ሠርቆ ሊጡን ለእንጀራ ሻጭ ቡሀቃውን ለቆራሊዮ ያስረከባል ።

ሰው ኪስ ገብቶ ያላስቀመጠውን ብር ከወረቀት ለይቶ ያወጣል ። ባለቤቱ የማይዝናናበትን ኪስ እንደ ልቡ ይፈነጭበታል ። ሌብነቱን መንደርተኛው ሁሉ እንዲያውቅ ያደረጉት የገዛ እናቱ ናቸው ። ብዙ ሰዎችን በሳቸው ስም አጭበርብሯል ። እናቴንም አንዴ ጉድ ሠርቷታል ።

« እማዬ ለጠላ መጥመቂያ የሚሆን በርሜል ላኪልኝ ብላሻለች !» ብሎ በርሜሉን በግራዋ አሳጥጧት ፣ በወይራ አሳጥኗት ለቆራሊዮ ሸጦባታል ። ታላቅ ወንድሜ በድርጊቱ ተናዶበት የፊት ጥርሱን በቦክስ ሸርፎለታል። ለዚያም ነው አንደኛዋ የበቆሎ ጥርሱ ግማሽ የሆነችው ። ሸራፋዋ ጥርሱም በወንድሜ ስም የተጠራችው ።

እምብርት ከፍቶኝ ሲያየኝ አሳዘንኩት። እነ አውሬ ያደረጉኝን ነገርኩት ። ተናደደ ። ወደ ምግብ መሸጫ ድንኳን ይዞኝ ገብቶ ሁለት ዓሳ ጥብስ አዘዘ ። እንደዚያ ዓይነት ዓሳ ጥብስ በሕይወቴ ድጋሚ በልቼ አላውቅም ። አጥንቱን ሳይቀር ቁርጥምጥም አድርጌ በላሁት ። ከዛ ቀስ ብሎ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

የድንኳኑን መጋረጃ ገለጠልኝና ሾልኬ እንድሮጥ አዘዘኝ ። አደረግኩት ። ተከተለኝ ። እራቴን እንዲህ አበላኝ ። በኪሱ ብዙ ብር ይዞ እያየሁት ለምን ሲከፍል እንዳልፈለገ ግን ግራ ገብቶኛል ።

ከሥሩ እንዳልጠፋ አስጠንቅቆኝ አብረን እየዞርን ሳለ ሌሎች የሠፈራችንን ልጆች አየናቸው ። ሠክረዋል ። ይለፋደዳሉ ። በየድንኳኑ በር ላይ በትልልቅ ብረት ምጣድ ስጋ የሚጠብሱትን ሴቶች ይተናኮላሉ ። መንገደኛ ሴቶችን ያስበረግጋሉ ። ከኋላ ከኋላቸው እየተከተልን ስንሥቅ አንድ ጥይቱን አንግቶ በእጁ ዱላ የያዘ ፖሊስ ቂጥ ቂጣቸውን «ገጥ ገጥ !» አደረጋቸው ። ፈረጠጡ። ስካራቸው ጠፋ ። በአንድ ምት የበነነች ስካር ። ለካንስ ሲፎግሩን ነበር ።

ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ብርዱ አንዘፈዘፈን ። የተኛንበት ሳር ዝናብ ሳይዘንብ በውርጩ ብቻ ረሰርሷል ። የሚቋረጥ ጩቤ የሆነ ብርድ አንጀታችን ገባ ። ከእምብርት ጋር ተቃቀፍን ። ብርዱን አልቻልነውም ። ቀሰቀሰኝና ወደ አንዱ ድንኳን ሄድን ። ቀን በየድንኳኖቹ በራፍ የነበረው ትርምስ ፈንጠር ፈንጠር ብለው ተኮራምተው በተቀመጡ ጥቂት ሰዎች ተተክቷል ። አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀመጥን ። እየተንቀጠቀጥን ነው ፤ እየተንዘፈዘፍን ።

« ለኔ አንድ ዓዛ ... ለሱ ደሞ አሪፍ ሻይ ኮረንቲ ! ቀምሶት ስለማያውቅ በስኳር አቅምሱልኝ » ብሎ አዘዘ

« ሒሳብ ቅድሚያ ነው ።»

« ማን ያንቺን ብር ይዞ ይሄዳል ? አምጪው ይሠጥሻል ።»

« እንዲህ ብሎ ነገር የለም ።እራት እየበሉ የጠፉብን በርካታ ሰዎች ሒሳብ ቅድሚያ ስላል ተቀበልናቸው መሰሎኝ ። ከሠርን ። ብርድ እየጠጣን ፈግተን ባዶ እጃችንን ቀረን ። ዓሳችንን ለሌቦች መግበን አጨብጭበን ቁጭ አልን ።» አለች ሻጯ ።

ደነገጥኩ ። አስተናጋጇን አወቅኳት ። ዓሳውን ያመጣችልን ልጅ ነበረች ። ከነቃችብን ለፖሊስ እንደምታሲዘን ተጠራጥሬ በጆሮው ሹክ አልኩት ። ሁኔታዬ ያልጣመው እምብርት በሌብነት ሳይንስ ውስጥ መበርገግና መርበትበት የመጀመርያው እራስን የማጋለጥ ሒደት እንደኾነ አስጠነቀቀኝ ። የተረጋጋሁ ለመምሰል ሞከርኩ ።

« ዓዛ » ብሎ ያዘዘው አረቂውን ነበርና ደጋግሞ ጨለጠው ። እኔም ሻይ ኮረንቲዬን እየጣፈጠችኝ አስገባኋት ። ትጣፍጣለችና በቃኝ ብዬ መቃወም አልቻልኩም ።

« ጠጣ ባክህ ! ወንድ ልጅና ሲሚንቶ ካልጠጣ አይጠነክርም ።» እያለ እያደፋፈረኝ ጠጣሁ ። ዓይኖቼ የሌሉ ቀለማትን ማየት ጀመሩ ።

የወደቅኩበትን ሳላውቅ ነጋ ። ከእንቅልፌ ስነቃ ፀሐይ ፍንትው ብላ ወጥታ የሚያንዘፈዝፈው ብርድ ግን ከፀሐይዋ ይፎካከር ይመስል ቅዝቃዜው አይሏል ። በርካቶች ሻንጣዎቻቸውን እያዘሉ ወደ መኪና ተራ ይተምማሉ ። ከቤተ ክርስትያኑ አንድ ኪሎ ሜትር ባላነሠ ርቀት ላይ የሚገኘው



@BOOKALEM

ጊዜያዊ የመኪና ተራ በመኪኖች ግጥግጥ ብሎ ሞልቷል ። አቆልቁለን ስንመለከተው ጥቅጥቅ ተደርጎ የተሠራ የመኖርያ መንደር እንጂ የመኪና መንጋ አይመስልም ።

ዕለቱ ታህሳስ አሰራ ዘጠኝ ስለነበር ታቦቱ ወጥቶ ፣ ካህናቱ በፓትርያርኩ እየተመሩ ፀሎታቸውን ያካሂዳሉ ። ታቦት ንግሶ ወደ ማደርያው ከገባ በኋላ መኪና ስለማይገኝ አብዛኛው ምዕመን ገና ታቦቱ ሳይወጣ በሌሊት መንገድ ይጀምራል ። እምብርት ግን የመኪና ችግር እንደማይገጥመን ቃል ገብቶልኛል ። የራሱ መኪና ያለው ይመስል «የመኪና ችግር የለም» ሲለኝ የመኪና ችግር የለም ብዬ አመንኩት ።

አንድ ጥግ ላይ ውሻና ጅብ ንቀው የተዉትን ጨጓራ በማሲኖዳዬ ሸከፈያለሁ ። ለውሻችንም የኾነ የኾነ ነገር የሚሸት ጣፊያ ይገፎለታለሁ ። መግማግት ጀምሯል ። ውሻችን እንደሚገማ ቢያውቅም ከመብላት ስለማያፈገፍግ ጭራውን ቆልቶ ፣ እግሬን ልሶ ነው የሚቀበለኝ ። የቀረቡኝ ሰዎች ሁሉ ግን ይሸሹኛል ። ምራታቸውን ጢቅ አርገው ተፍተው አፍንጫቸውን እየያዙ ግማታምነቴን ይነግሩኛል ። ካለፉኝ በኋላ ዞረው በግልምጫ ያነዱኛል ።

እምብርት ስለያገዘኩት የስጋ ዓይነት ጠየቀኝ ። ነገርኩት ። አፉ ውስጥ ያለችውን ሸራፋዋን የወንድሜን ጥርስ እያሳየኝ ሳቀ ።

« ምን ሊያደርግልህ ነው ጨጓራ የተሸከምከው ጭንቅሎ ? ሽራ ጫማህን ልታጥብበት ነው እንዴ ?»

« ቅቅለን እንነፋዋለና !»

«አታፍርም ጭንቅሎ? ቁልቢ ድረስ መጥተህ ጨጓራ ይዘህ ትመለሳለህ?»

« እና ሌላ ስጋ አጣኋ !»

« በል ሌላ ስጋ እንፈልጋለን ። አሁን ሰው ሳይስቅብህ ይኼን ከጅብ የነጠቅከውን የበሠበሠ ጨጓራህን ያገኘህበት ጥግ ጣለው ።»

« ተለዋጭ ሳላገኝማ አልጥለውም ።»

« ግዴለህም እናገኛለን ።»

« ከየት ?»

« እዚያ ጋ የቆመው ለማኝ ይታይሃል ?»

« የቱ ? ያ ! እዚያ ጋ እድፋም ጋቢ የለበሰው ?»

« እ !»

« እዎ ! ይታየኛል ።»



@BOOKALEM

« እግሩ ስር የከመረውን ማዳበርያ ቆጠርልኝ ።»

« አንድ ፣ ሁለት ፣ሦ...ስት እና ግማሽ ።»

« ያ ሁሉ እንግዲህ ስልቻጅ እንዳይመስልህ...ስጋ ነው እሺ ።»

« ማርያምን !» እንዲምልልኝ እጄን ዘረጋሁለት ።

« እዚህ ቦታ ላይ በገብርዔል እንጂ በማርያም አይማልም ።»

« እናቱን ! ለካ የኛን ድርሻ ሁሉ ሰብስቦ ነዋ ሰጋ ያሳጣን !» የምር ተናድጄበታለሁ ።

« ወደህ ነው ።»

« አሁን ብንለምነው ይሰጠናል ?»

« ለማኝ ከለመነው እስከትጠግብ ሲያበላህ ይችላል እንጂ ከሆድህ የሚተርፍ ቁራሽ አይሰጥህም ።»

« ስለዚህ ?»

« እንደከለው !»

ደነገጥኩ ።

እምብርት ዘዴ ፈጠረ ። የለማኙን ስሜት አጥንቶ መኪና እንደሚፈልግና እንደማይፈልግ ጠየቀው ። ፊት ለፊታችን ሰዎች እየተጋፉ ከሚጫኑበት መኪና አጠገብ ያለውን የጭነት አይሱዙ ጠቆመውና እኔን ስጋውን እንድጠብቅ አደራ ሠጥተውኝ ተያይዘው ሄዱ ። ከእምብርት ቀድሞ በተላለፈልኝ ዘዴ መሠረት ስጋ እየጠበሱ ለሚሸጡ ሰዎች ሁሉንም ሰጋ በሰልሳ ብር ሸጥኩት። ብሩን ተቀብዬ እጥፍ አልኩ ። የገዙኝ ሰዎች ስጋቸውን በእጅ በሚገፉ ጋሪ ጭነው ወሠዱ። የባዶ ማሲኖዳና ሰልሳ ብር ጌታ ሆንኩ ። እምብርት ለማኙን ሸውዶት መጣና በቅርብ ርቀት ቆመን የሚኾነውን ማየት ጀመርን ። ዘለለ ። ጋቢውን ወረወረ ። ሰው በተሰበሰበበት ጮኸ ። ስለሸወድነው ደስታችን እጥፍ ሆኖ እየሳቅን አካባቢውን ጥለን ሄድን።

የቮነ ድንኳን ውስጥ ገብተን አሪፍ ጥብስ አዘዝን ። ተመጋቢው ቀስ በቀስ ድንኳኑን ሞላው ። መቀመጫችንን ጥግ ወዳሉት ወንበሮች ቀየርን ። አስተናጋጆቹ ሲዋከቡ ሾልከን ወጣን። እምብርት ተያዘ ። ተመትቶ በወደቀበት ቅፅል ስም ያስወጣለትን የሜዳ ቴኒስ መጫወቻ ኳስ የሚያከል እምብርቱን ሲረግጡት ተንፈራፈረ ። በተኛበት በቦክስ በርግጫ ሲፈሠፍሱት እግሬ አውጪኝ አልኩ ። ሩጫዬን ቀዘቀዝ እንዳደረግኩ በርከት ያሉ እጆች ተረባርበው ማጅራቴን ጨመደዱኝ ። ተያዝኩ ።

«... በናታችሁ ! እኔ አይደለሁም ። እምብርት እራሱ ነው በልተን እንጥፋ ያለኝ ። በድንኳኑ



@BOOKALEM

ውስጥ እንድሾልክ ያዘዘኝ እሱ ነው ። የለማኙንም ስጋ ሥርቀን እንሸጥበት ያለኝ እራሱ ነው። በናታችሁ እንዳትመቱኝ ! ስጋውን የሸጥኩበት ገንዘብ ኪሴ ውስጥ ነው ያለው ፣ ይኸው ብሩን ውሠዱና ተዉኝ ። በናታችሁ ! ...» ብዬ ብሩን አውጥቼ ሠጠኋቸው ። ተቀበሉኝ ።

« አሳዛኝ ቀና በል !» ሲለኝ የማውቀው ድምፅ

ተናደድኩ ። ጠይሜና ጠምቤ ሆዳቸውን ይዘው ሳቁ ። ድንጋጤዬ ከውስጤ ሊወጣልኝ አልቻለም ። መቼ መጡ ? ወደ ቁልቢ መምጣታቸውን ሳላውቅ ቁልቢ አገኘኋቸው ። ደስታና ድንጋጤ ተቀላቀሉብኝ ። የምንጊዜም ምርጦቼን ጓደኞቼን በማግኘቴ ብደሰትም ስላስበረገጉኝና ምስጢሬን ስላናዘዙኝ ግን ከፍቶኛል ።

« ጭንቅሎ !» አለኝ ጠይሜ

« ወይ !»

«አንተ ግን ቁልቢ ድረስ መጥተህ ትሠርቃለህ? ቆይ ገብርኤል ቢያሲዝህስ?»

« ገብርኤል ትላለህ እንዴ ? ከሱ ቀድሞ እምብርት ሊያሲዘኝ አልነበር !»

ጠምቤ ሆዷን ይዛ ሳቀች ።

« አሁን እምብርት የት ነው ?»

« ተይዟል ። እየከሸከሹት መሠለኝ ።»

« አላልኩህም ?»

« ምኑን ነው ያልከኝ ?»

«ገብርኤል ነዋ ያስያዘው ።»

« ገብርዔልን በል እስቲ !» ደንግጫለሁ ።

« በርሜልን !»

« ኢታሹፍ አበ !»

« ኣኣይ ግን የምሬን ነው ። ይቅር በለኝ ገብርዔልዬ ።» አለ ጠይሜ ወደ ቤተ ክርስትያኑ ዞሮና እጆቹን ሰልመና ዘርግቶ ።

« እና እኔንም እንዳያሲዘኝ እንዴት ልሸውደው ?»

« ማንን ?»

« ገብርዔልን ነዋ !» አልኩት ድምፄን ቀንሼ ። ድምፄን የቀነስኩበት ምክንያት የተናገርኩትን



@BOOKALEM

ገብርኤል እንዳይመጣብኝ ፈርቼ ነው ::

« ለምን ስልሳ ብሩን የስዕለት ብለን አናስገባለትም ?»

« ማርያምን !»

« እዚህ ድረስ መጥተህ ማርያምን ስትል ኢታፍርም ጭንቅሎ ?»

« እና ምን ልበል ታድያ ?»

« በገብርኤል ነዋ መማል ያለብህ ::»

« እሺ ብሩን የስዕለት ብለን ብናስገባለት አያስፎግረንም ?»

« ሊይዞህ ቢመጡ እንኳን አያሊዝህም :: ዓይናቸውን ይጋርድልሃል :: ፊት ለፊትህ እንደ ሀውልት አድርጎ ይገትርልሃል :: ኢሮችህን ዓይናቸው ደኛፍ አድርሥህ ብታወዛውዝባቸው እንኳን ከመድረታቸው የተነሳ ዓይኖቻቸውን አያርገበግቡብህም ::»

የገብርኤልን ተዓምር ሳላየው ተደነቅኩበት :: ገብርኤል የኔ ኢጋዥ እንደሚሆን ተማመንኩበት:: ተያይዘን ቤተ ክርስትያኑ ቅጥር ግቢ ገባን :: የስዕለት ገንዘብ ወደሚሠጥበት ቦታ ተጠጋንና ቆምን:: ዓይኖቻችንን እንድንጨፍንና በየልባችን እንድንፀልይ አስጠነቀቀን ::

« እኔ ገንዘቡን ወደ ጉድጓዱ ስከት ካያችሁ አውር ትሆናላችሁ :: ገብርኤል ገንዘቡን የሚያይበትን ሰው አይወድም :: ምሕረት አያደርግላችሁም ::» ብሎ አስፈራራን :: ፊቴን በመዳፊ ሸፍኜ በጣቶቼ መሀል አጮልቄ እያየሁ ታዘብኩት ::

« እንሂድ !» አለ ጠይሜ

« እሺ ብሩን አስገባሊታ !» ጠምቤ አፈጠጠችበት ::

« አስገብቼሊታለሁ ::»

« እውነት ?»

ሊባ ጣቱን በምራቁ አርሶ ፣ መዳፊ ላይ የመስቀል ቅርፅ ሠርቶ ሊምልልኝ ፈለገ ::

« እውነትህን ከኾነ በእናትህ ማልልኝ ... እስቲ እናቴ ትሙት በል !» አልኩት ለእናቱ ያለውን ፍቅር ስለማውቅ

« እናቴ ትሩጥ አባቴ ይከተላት ::»

ተናደድኩ :: ያሾፍብኛል እንዴ ? ገና እምብርት ሠፈር ሲያገኝኝ ብሩን ይጠይቀኛል ::

« ውሸታም ነህ :: ለምን እውነትህን ከኾነ አትምልልኝም ? ከኔ የባሰክ ሌባ ! ገብርኤልን ቆጮ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ስትመታው አታፍርም ?»

« ሽረ ... አኔማ በናቴ አልምልም ::»

« ለምን ?»

« ሽረ! እሱ ገንዘቡን እስኪቆጥርና እስኪያረጋግጥ እናቴ ብትሞትብኝስ ?»

« ሂድ ውሸታም !» ጠምቤ ብግን ብላለች ::

« እኔ እንዳውም ከነገርኳችሁ ትቀየሙታላችሁ ብዬ እንጂ ገብርዔል እራሱ 'ጠይሜ የሌባ ገንዘብ እንዳትቀላቅልብኝ :: ብሩን አንተ ብቻህን ተዝናናበት' ብሎኛል በጆሮዬ » አለ ::

አንደሸወደኝ እያወቅኩ ተያይዘን ወጣን :: ወደ ቤታችን ለመመለስ መኪና ፍለጋ ጀመርን ::

ድንገት መዐት ለማኞች በሠልፍ ተቀምጠው የሆኑ ቦርሜቻቸው የተጠቀለለ ደስታ ከረሜላ ያስመሠላቸው ሰውዬ አዳዲስ አንድ አንድ ብሮች ያድላሉ :: ለማኞቹ አጠገባቸው እንዳንቀመጥ ከለከሉን :: በጠይሜ መሪነት ለሰውዬው እጃችንን ዘረጋንላቸው :: ከንፈራቸውን በአዘኔታ እየመጠጡ ለሦስታችንም ሠጡን :: አሁንም ወደ ፊት ጠጋ ብለን ልብሳችንን ግንባራችን ላይ አስረን ቆምን :: ሁለት ሁለተኛዋን ብር ተቀበልናቸው :: የአንድ ባለ ከራንች ለማኝ ጣት ጭኔ ስር የማይበርድ እሳት ቀበረ :: በተቀመጠበት በርግጫ ጀርባውን ደልቄው ወደ ፊት ሄድኩ :: ጠይሜም ጨመረለት :: እንዴት አባቱ ሮጦ ይይዘናል ::

የሰውዬው ብር አለቀ :: እኛ ሁለት ሁለት ብር አገኘን :: ዋናዎቹ ለማኞች ግን ባዷቸውን ቀሩ :: የተረፋቸው ነገር ቢኖር ወረፋ ይዞ በትዕግስት መጠባበቅ ብቻ ነበር :: ሠልፉ ቀስ በቀስ ሲበተን ገንዘቡ ያልደረሳቸው ለማኞች ሠልፋቸውን ሳይለቁ ተቀመጡ :: እኛም ከመጀመርያ ሄደን ልንቀመጥ ስንል አራወጡን ::

ሌላ ገንዘብ ሠጪ ሊመጣ እንደሚችል ገምተን ከመጨረሻ ተቀመጥን :: በኪሳችን የያዝናቸውን ብሮች መሬት ዘርግፈን ስንቆጥር ጀርባውን የደለቅኩት ባለከራንች ለማኝ አጠገባችን ቆሟል :: ወደ ላይ ቀና ብለን ስናየው ውሃ ሆንን :: በከራንቹ መሬት ተደግፎ ተንጠለጠለና አሽማቅቆ በሚያንጠለጥላት ጉዳተኛ የቀኝ እግሩ ደረቴን ደቆሠኝ :: ደረቴ የተበሳች መሠለኝ :: ጮኽኩ ::

እነ ጠይሜ ገንዘቡን ጥለው ፈረጠጡና ድንጋይ አንስተው ማስፈራራቱን ተያያዙት :: ባለ ከራንቹ ገንዘባችንን ሰበሰበና ኪሱ ከተተው :: እኔ መሬት ላይ እየተንደባለልኩ ስጮህ ከየት እንደመጣ ያልታወቀ ፖሊስ በቆመጥ ለመጠው :: እነ ጠይሜ የፖሊሱን መምጣት ሲያዩ ተጠጉና ለምነን ያጠራቀምነውን ብራችንን ቀምቶ እንደወሠደብን ነገሩት:: ፖሊሱ ተናደደ ::

« መልስላቸው !»

« አልወሠድኩባቸውም እየዋሹ ነው ::» አለ



@BOOKALEM

« ወስዶብናል ::» ሦስታችንም ጮኸን ። እንባዬ በአራት አቅጣጫ ይወርዳል ። እነ ጠይሚም አለቀሱ ።

ሌሎቹም ለማኞች መሠከሩልን ። የወሠደብንን ብር በሙሉ ከኪሱ አውጥቶ ለፖሊሱ ሠጠው ። ፖሊሱ ብራችንን የፊልድ ጃኬቱ ኪስ ውስጥ ጨመረው ። ባለ ከራንቹን «ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሂድ !» ብሎ ሲያስገድደው ትግል ገጠሙ ። ፖሊሱን በቃርያ ጥፊ ዘረገፈው ። ከራንቹን ጥሎ በሁለት እግሩ መሬት በትከከል እየረገጠ ሮጠ ።

« ያዘው ! ያዙት ! ፖሊሱን ገድሎ ነው የሚሮጠው ... ኧረ ያዙት !» ለማኞቹ ሠልፋቸውን በትነው ጮኹ።

አጅሬው_ በመከላከያ አባላት ከበባ ተያዘ ። ፖሊሱ ውሃ ተደፍቶለት እራሱን ከረሳበት ሠመመን ነቃ ። ባለ ከራንች የነበረው ለማኝ ተባነነበት ። በትልቅ ፋሻ ጉልበቱ ላይ የጠቀለለው የበሬ ጉበት ነበር ። ትኩስ ጉዳት እንዲመስልለት ትኩስ ጉበት ለጥፎ ሕዝቡን ሲሸውደው የቁልቢን ተሳላሚ ከንፈር ሲያስመጥጥ ከርሟል ። በካቴና ጠፍንገው እየቀጠቀጡ ሌሎች ፖሊሶችና ጽሕፈት ቤታቸው ወደሚገኝበት ይዘውት ሄዱ ። የተዘረረችው ፖሊስም የኛን ብር በኪሷ እንደከተተች በጓደኞቿ ተደግፋ ሄደች ። አቅሟን በጓደኞቿ ኑሮዋን በኛ ብር ልትደግፍ መንገድ ጀመረች ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ አስራ ስድስት

## የግንቦት ልደታ

«አቦነሽ ባንቴ ማነች ?»ብላችሁ እንዳትጠይቁኝ ...እኔ እንደሆነ ይህ ስም የሠፈራችን አድባር መጠርያ መሆኑን ብቻ አውቃለሁ ። እናት አባቶቻችን ከነ ጊዮርጊስና መድኃኒዓለም ቀጥሎ በየወሩ ድግስ የሚደግሱላት ዋርካ ናት ። ሲወጡ ሲገቡ «አንቺ ታውቂያለሽ አቦነሽ ባንቴ!» እያሉ ኃላፊነት የሚሠጧት ወፍራም ግንድ ።

ከስሯ ትልቅ የእጣን ማጨሻ ሥርኮ አይጠፋም ። እስሯ ውሎ እያደረ ሌባ የማይደፍረው ጊርጊራ ። ጠዋት ፣ ቀትርና ሚስቲጃብ (አመሻሽ) ላይ እጣኗን ተራ በተራ እያንቦለቦሉላት ለአካባቢው ጠረን መልካም መዐዛዋን ከወላጆቻችን ኪስ ታዋጣለች ። ሙስሊም ክርስትያኑ እኩል የሚያምንባት ዕድለኛ ዋርካ ። በየወሩ ንፍሮ የሚቀቀልላት ፣ ቂጣ የሚጋገርላት ፣ ቡና እየተፈላ እጣንና ሠንደል የሚጨስላት ደጋሿ የበዛ ሀብታም ዛፍ ። የበተኑላትን ንፍሮ ለቅማ የማትበላ ፣ቦጭቀው የጣሉላትን ቂጣ የማትቀምስ ፣ የረጩላትን ቡና የማትልስ ፣ ያጨሱላትን ሉባንጃ የማታሸት ፣ ለሰዎች ከስረት የራሷን ዘዴ የምትጠቀም ጢማም ዋርካ።

ሁሌም ወር በገባ የመጀመርያው ቀን አድባራችን ገቢዋ ይጨምራል ። ደጋሽ ዘካሪዋ ይበዛል ። አባቶቻችን መገበያያ ገንዘቡን በመስጠትና ማበሳሰያ እንጨት በመፍለጥ የበኩላቸውን ያዋጣሉ። እናቶቻችን የንፍሮ እህል በማዋጣትና በመቀቀል ፣ ቂጣና እነባበሮ በመጋገር ፣ ኑግ በመውቀጥ ፣ ቡና በማፍላት ፣ ሥጋ በመጥበስ ፣ እንግዶችን በማብላትና በማጠጣት ለአቦነሽ ባንቴ ያላቸውን ክብርና ታማኝነት ያሳያሉ ። ልጅ ልጆቹ ውሃ በመቅዳት ፣ ስኒና ሠሀን በማጣጠብ ፣ ሰዎችን ከየቤታቸው በመጥራት እንሳተፋለን ።

አብዛኛው ሰው ያለ ጥሪ እየመጣ በሥራው ላይ የሚሳተፍ ቢሆንም እንደነ ጤናዬ ወላጆች ዓይነት ኩረኛ ሰዎች አይጠፉም ። ብዙ ጊዜ እንደታዘብኳቸው የጤናዬ ቤተሰቦች ለመደገሻ ገንዘብና ለመብያ ጥርስ ከማዋጣት አልፈው ሥራዎችን ተረዳድተው ሲያቃልሉ አልገጠሙኝም ። ተፍ ተፍ ብለን የታዘዝነውን ስንሠራ እናት አባቶቻችን ይመርቁናል ። አቦነሽ ባንቴ ትምህርታችንን እንድትገልጥልን እጣኑን እያጫጫሱ ይለማመኑልናል ። ትንንሽ መዳፎቻችንን ዘርግተን «አሜን፤ አሜን !» እንላለን ። አሜናችን እንዲሰማ አንዳችን ከአንዳችን በኃላ ድምፅ እንፎካከራለን ። «ድምፁ ጎልቶ የተሰማለት ምርቃቱ ቀድሞ ይደርስለታል » ተብሎ ስለተነገረን «አሜን !» ስንል በጩኸት ነው ። ጠይሚ ግን ብዙ ጊዜ ያሾፋል ። «ልጆች አሜን በሉ !» ሲባል «አሬን !» ይላል።

ጢማሚ ዋርካ ስር ልጆች ፣ ጎረምሶች ፣ ጎልማሶችና አዛውንቶች በየረድፋችን ተኮልኩለናል ። እኛ ልጅ ልጆቹ ዘንድ የሚሰማው ድምፅ ከፍተኛ ትርምስ የበዛበት ሲሆን ከአዛውንቶቹ አካባቢ የሚመጣው ግን ጎርናና ሳቅና ረጋ ያለ ንግግር ነው ። አልፎ አልፎም በወፍራም ሳል የታጀበ ሳቅ።

ጋቢያቸውን ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው ፣ ከፍያቸውን ሳያወልቁ በቆልማማ ከዘራቸው



@BOOKALEM

አገጫቸውን ደግፈው የሚወራላቸውን ያዳምጣሉ ። አድምጦ ዝም የለም ። መልስም ይሠጣሉ ። አዲስ ርዕስ ፈጥረውም ያወራሉ ። በማርማላታ ጣሳ ፣ በፕላስቲክ ኩባያና በሸክና የታደላቸውን ጉሽ ጠላ እየተጎነጩና አንትፍ እያሉ ወግ ይጠርቃሉ ።

በዝርግ ሠሀን ላይ ንፍሮ ፣ ዘይትና በርበሬ የጠገበ ግድግዳ የመሠለ አነባበሮ ፣ ድፎ ዳቦና የባቂላ እንዱሽዱሽ እየተደረገ ታደለን ። አባቶቻችን አንዴ ዘግነውም ቆርሠውም አፋቸው የከተቱትን ለረጅም ሰዓት ያላምጡታል ። ያላመጡትን ቁልቁል በጠላ ይገፉታል ። እኛ አካባቢ ግን ምግብን ተመልክቶ የሚታገስ ጥርስ ማንም ልጅ የለውም ። በተቻለ ፍጥነት እየሸረከትን በትግል መዋጥ ፣ እየተናነቀን ዓይናችን እንባ እያቀረረ ማስገባት እንችልበታለን ። በተለይ በተቀበለበት ሠሀን ላይ በልቶ የሚጨርስ ልጅ አይገኝም ።

መመነታተፍ ስላለ በሠሀን የተቀበልነውን በሙሉ በልብሳችን ገልብጠን እንይዛለን ። ካናቴራ ለዚህ ለዚህ ትመቻለች። በልብሳችን የያዝነውን ቀስ ቀስ እያልን ሌሎችን እያቁለጨለጭን እየቀነጠርን እንበላለታለን ። ይገርማል...የራሳችን እጅ የራሳችንን ንፍሮ ለመዝገን ሲጓዝ ተደብቆ ነው ። እጃችንን ወደ ንፍራችን ስንሠድ በዓይኖቻችን የሌላ ሰው እጅ ተከትሎ እንዳይገባ እንቆጣጠራለን ። ሲመነትፉኝ በመናከስ እታወቃለሁ ። የራሳቸውን በልተው ሳይጨርሱ የሚመነትፉን ጉልቤዎች ስላሉ በዓይነ ቁራኛ መጠባበቁ ያለ ነው ።

ለነገሩ ለጉልቤም ጉልቤ አለው እንጂ ጠይሜ በአንደኛ መንታፊነቱ ይታወቃል ። ሲመነትፉን ከሚወስዱብን የሚደፉብን ይበልጥብናል ። ጠምቤ ግን መርዝ ነች ። መጀመርያ ኪሶቿ ውስጥ ከሞላች በኋላ የተረፋትን በካናቴራዋ ትይዛለች ። ወዲያው ጉልበቷን ታቅፋ ተኮራምታ ትቀመጣለች ። የንፍሮ ካዝናዎቿን ያለ ቁልፍ ትከረችማቸዋለች ። በምንም መልኩ ኪሷ ውስጥ በጉልበት መግባት አይቻልም ። በካናቴራዋ የያዘችውን ንፍሮ ስትጨርሥና በተቀመጠችበት ከኪሷ ለማውጣት ስትሞክር አብዛኛው ይፈስባታል ። የኪሷ ስፋትና የመዳፏ መጠን አይጣጣሙም ። ጎላን ዘቅዝቆ በማንኪያ ለመቀበል እንደመሞከር ይከብዳል ።

ጠይሜ ደሞ ዳቦና አነባበሮው ላይ ኢያየነው ምራቁን ይተፋበትና ያስቀምጠዋል ። ማንም አይበላበትም ። አንድ ቀን ግን ሰሚር ምራቅ ያረፈበትን ቦታ ቆርሶ ጥሎ ሌላውን በላሰት ። ጠይሜ ምራቁን እንደተፋበት ነግሮ ሊያጥላላው ሞከረ። አልሆነለትም ። ይባስ ብሎ «ምራቅህ ይጣፍጣል!» እያለ በገዛ ዳቦው እያሰቀና ጨረገደበት ። ተናደደና እናቱን ሰደበበት ። ሰሚር የሞተችውን እናቱን ሲሰድቡበት አይወድም ። ሊመታው ሲያሯሩጠው ይቅርታ ጠይቆና የቀረችውን ቂጣ በኑግ ሠጥቶ ታረቀው።

ሰሚር ወላጅ እናቱን እንጂ የእንጀራ እናቱን ስንሰድብበት ምንም አይመስለውም ። እንዲያውም አብሮን ሆኖ ይሠድባታል ። በተለይ የመታችው ቀን እኛ ስር መጥቶ ወላጅ እናቱን እያስታወሠ ያለቅሳል ። «ዙቤይዳ ብትኖር አይርበኝም ፣ በራበው አንጀቱም አልገረፍም ነበር ። ሳልሠርቅ ሠረቅክ ተብዬ በሌብነት አልጠረጠርም ነበር ።» እያለ ሲያለቅስ ያስለቅሠናል ። ከዚያ ከሰሚር ጋር እንመካከርና የእንጀራ እናተ ቤቷን ዘግታ መሄዷን እናይና ኩሽና ገብተን ምጣዷንና



@BOOKALEM

አከንባሎዋን ስብርብር እናደርግባታለን ። ከሄደችበት ስትመለስ ጀሮዋን ይዛ ትጮሃለች ። አንጀታችን ቂቤ ጥጥት።

ይኼንን የኢደንጓሬና የባቄላ ንፍሮ እናስገባ እናስገባና ሌሊቱን ሙሉ የአርኬስትራችንን ድምፅ በጠረን ለውሠን ለቤተሰቦቻችን እናቀብላለን ። ሆዳችን ሲወጠር ፣ ሲቆርጠን ፣ ሲጨንቀን ድ...ው ! ስናደርገው ሲረግብ ተንፈስ እንላለን በፈስ ። ተሻምተን በልተን ፣ ተስገብግበን ጠቅጥቀን በሠሙብኝ አልሠሙብኝ እየተሳቀቅን እናስተነፍሳለን ። የሚጮኸው ፈስ የከፋ አፍንጫን የመረበሽ ችግር የለውም ። ያቺ ያለ ድምፅ «ሽ...ሽ...ሽ...» የምትለዋ ግን አፍንጫ ትቆርጣለች ። የበሉትን ከውስጥ ወደ ውጭ ትገለብጣለች። እንደ ትምባሆ ግድግዳና ልብስ ላይ ትለጠፋለች መሠለኝ በርና መስኮት ተከፋፍቶ እንኳን ዘና ብሎ ለመተንፈስ ታስቸግራለች ።

ከፊት ለፊታችን ከየቤቱ ተዋጥተው ፊት ለፊታችን የተደረደሩት ከመቶ በላይ ነጫጭ የቡና ሰኒዎች ጨለማውን በጉልበት ጥሠው ከአይናችን ስር ደርሰዋል ። ያምራሉ ። በርካታ ረከቦቶች ከተንዘነዘላቸው ቄጤማ ላይ ፈልሠሥ ብለዋል ። በትልልቅ ጊርጊራ እጣንና ሉባንጃው እየተቀላቀለ ይጨሳል ። ቡናውን በዋናነት የምታፈላው መይሙና ናት ። ባለቤቷ ረሻድ ደሞ እንደሌሎቹ አባቶች ጋቢውን ለብሶ ተቀምጧል ። ልጆቻቸው ሙከታር ፣ በድሪያና ዘምዘም ከኛ ጋር ተቀላቅለዋል ። የመጨረሻ ልጃቸው ፋሚ ግን የእናቱን ጉልበት እየታከከ ስር ስሯ ይላል ። የዕጣኑ ጭስ ዓይኖቹን እየለበለበው እየደጋገመ በአይበሉባው ያሻሻቸዋል ። አልፎ አልፎም ለቅሶ ቢጤ ያሰማል ።

ከቡናው በስተቀኝና ግራ ፈንጠር ፈንጠር ተደርጎ ትልልቅ ብረት ምጣዶች ጉልቻ ላይ ከሰራቸው ፍልጥ እየነደደባቸው ተቀምጠዋል ። በስተቀኝ በኩል ካለው ብረት ምጣድ ክርስትያኖች ፤ በስተግራው ጋር ደሞ ሙስሊሞች አሉ ። ለማበሳሰልና እኛን ለማብላት ተፍ ተፍ ይላሉ ።

የተዘለዘለው ሥጋና ሁለት ሁለት ቦታ የተሠባበረው የጎድን አጥንት በትሪ እየተሞላ መጣ። በየብረት ምጣዶቹ ላይ ተዘረገፈ ። የጋለው ብረት ምጣድ እርጥቡን ሥጋ ተቀብሎ «ቿ...ቿ...ቿ» እያለ ማብሰል ጀመረ ። ቀስ በቀስ የዕጣኑ መዐዛ በጥብስ ሽታ ተለወጠ ። የምናወራውን ወሬ እያቋረጥን ፣የሚወራልንን ችላ እያልን ዓይንና ቀልባችንን በሙሉ ትኩረት ወደ ብረት ምጣዱ ወረወርን ወደ ጥብሱ ። በዚህ ብርዳም ጨለማ ከጥብሱ እንጂ ከወሬው ሙቀት መች ይገኝና ።

« አንተ ጭንቅሎ ሚይረምን አየሃት ...ከዝልዝሉ ላይ ቦጭቃ ነፋችው እኮ !»

«ጠባሸ አይደለች እንዴ? መብሰል አለመብሰሉን እያረጋገጠች ይሆናላ።»

« እና ጠባሸ ብትሆንስ ...ግማሹን ዝልዝል እኮ ነው የነፋችው ። ይኼ መብላት እንጂ መቅመስ ይባላል ?»

« ደሞ ብትበላውስ ምን አገባህ ?»



@BOOKALEM

« እንዴት አያገባኝም ?»

« እሷ የምትበላው የሙስሊሞቹን ነዋ ። እነ መሃዲ ይጨነቁበት እንጂ አንተ ምን ቤት ነህ ?»

« ያምሃል እንዴ ጭንቅሎ !»

« እንዴት ነው የሚያመኝ ?»

« የሙስሊም ምናምን እያልከ ልትመርጥ ያምርሃል እንዴ...የደሀ ልጅ። ዓይንህ አያይም ማለት ነው ። ቀይዋና ቡራቡሬዋ ፍየሎች እኮ ናቸው የታረዱት ።»

« እና ቢሆኑስ ?»

« ስናግዳቸው ሙስሊም ነን ብለውሃል እንዴ ?»

« እነማን ?»

« ፍየሎቹ ?»

« ኧረ አላሉኝም...ደሞስ ከመቼ ወዲህ ነው ፍየል ማውራት የጀመረው ?»

«እኮ ስለዚህ... ?»

« ስለዚህ ምን ?» የጠምቤ አጠያየቅ መደንገጧን አሳብቆባታል ።

«ከሠጡኝ እነፋዋለኋ ።»

አፋችንን በድንጋጤ ያዝንበት ።

«ከዚህ በፊት የሙስሊም በልተህ ታውቃለህ እንዴ ?» ጠምቤ ተገርማ ጠየቀችው ።

« አዎና !»

« መቼ ?»

«ባለፈው ዓመት ነዋ !»

« የት ?»

«የሳፈያና የሠዒድ ሠርግ ላይ ።»

« እነ ሳፈያ ሠርግ ላይ ?»

«አዎና...ሦስታችንም ሩዝ በስጋ አልበላንም ?»

«ኧረ እኔ አልበላሁም ።» ተቃወምኩ



@BOOKALEM

«አስታውስ እንጂ ጭንቅሎ...የሦስት ሰው ጭንቅላት ብቻህን ተሸከመህ ሩዝ ውስጥ ባገኘነው አንድ የተጋጠ ቅልጥም የተጣላነውን ትረሳለህ እንዴ ?»

ትዝ አለኝ ። ሳፊያ ያገባች ጊዜ ሦስታችንም መሸትሸት ሲል ሄድን ። ድንኳን ስንገባ ጭፈራው ደምቋል ። እስኪወጣልን ልንደንስ ተነጋግረን ሄድን ሰናበቃ ወደ ኩሽና አካባቢ ስንዞር በአንድ ትልቅ አግራም ነጭ ጎድጓዳ ሠሀን ተሞልቶ የተቀመጠ ሩዝ ተመለከትን ። ግራና ቀኙን ፈታተሽንና ተጠቃቅሠን እርምጃ ወሰድንበት ። ወደ ጓሮ አስቀየስነው ። በድንችና ሥጋ የተሠራ ጣፋጭ ሩዝ ። ተሻምተን በላነው ። ለማን እንደተቀመጠ ፣ ለምን እንደተቀመጠ መጠየቅ ሳያስፈልገን ጠራርግነው ። እንደ ድንገት አፈፍ አድርጌ ያነሳሁትን የፍየል ቅልጥም በግራ እጄ ይዤ ሩዝና ድንቹ እስኪያልቁ ተሻማሁ።

ጠይሜና ጠምቤ እጃቸው ላይ የነበረውን የጎድን አጥንት ግጠው ጨረሱና « ብንጌ !» አሉኝ ።

« ባትጋሩኝ !»

«ቀድመን ብንጌ ብለንሃል ስጠን !» ብሎ ጠይሜ አፈጠጠብኝ

በጥርሴ ቦጨቅ ቦጨቅ እያደረግኩ ከአፌ እያወጣሁ ሠጠኋቸው ። እየተቀበሉኝ በሉ ። እኔ ምንም ሳልቀምስ ሦስት ሦስቴ ጎረሱ ። ከዛ ለኔ ልጎርስ ስል ጠይሜ ሊመነትፈኝ እጁን ሠነዘረ። ለአጥንት የተሠነዘረው እጁ ሽረሪት ሸንታብኝ በእማማ ካሱ ቱፍታ ምስር የተለጠፈበትን ከንፈሬንና የአፍንጫዬን ጫፍ ቧጨረው ። አበድኩ ። ጥፍሩ ቁስሌን ገሸለጠው ። እሪታዬን አቀለጥኩት። ጩኸቴን ሰምተው ድንኳን ውስጥ የነበሩ ሰዎች ግልብጥ ብለው መጡ ። ሁለቱም የፊላውን አጥር ጥሠው ጥለውኝ ፈረጠጡ።

« ምን ሆነህ ነው ጭንቅሎ ? ለመሆኑ እዚህ ጨለማ ውስጥ ምን ታደርጋለህ?» የሙሽራዋ የሳፊያ አባት አብዱላሂ ጠየቀኝ ።

« ሽንቴን ልሸና ስል የሆነ ሠይጣን ፊቴን ቧጭሮኝ ሄደ ።»

« የምን ሼይጣን ጭንቅሎ...ሠርግ ቤት መጥተህ ሼይጣን ትጣራለህ እንዴ... አኡዙቢላሂ !»

« አይቼዋለሁ ጋሽ አብዱላሂ ሠይጣኑ ነው የቧጨረኝ ።»

«ማንን ያከላል ?»

«ጠይሜን ነው የሚያከለው ።»

«ምን ሠይጣን ይቧጭርሃል...ይኼን የሩዝ ትራፊ ስትለቃቅም የያዝከው ቅልጥም ቧጭሮህ ይሆናል እንጂ ! ለቃቃሚ !» የሳፊያ አክስት አሻ ተቆጣችኝ ።

ደነገጥኩ ። ለካ ቅልጥሙ እጄ ላይ ነበር ። በጠይሜ ሳለመነጠቅ አጥብቄ ይዤው ቆይቼ። እንደጨበጥኩት ጩኸቴን ለቅቄ አራሴን አጋለጥኩ ። የሩዙ ሠሀን አግሬ ሥር ተጋድሟል ።



@BOOKALEM

ከሰዎች ተራርፎ ለውሾች ሊደፋ የተሰበሰበ ትርፍራፊ ፍገዘ መብላታችንን ሳውቅ በመብላቴ እንደማልመታ ገባኝ ::

« ጠይሜ !» ጠራሁት ከትውስታዬ ስባንን ::

« እ... ጭንቅሎ !»

« ባክህ እንንፋው ::»

« ምኑን ?»

« የሙስሊሞቹን !»

« አይሠጡንማ ::»

« ግን አይጨርሱትም...ምን ነበር ሙስሊም በሆንኩ...ይኼን ሁሉ ጥብስ በነፃነት እፎደፉደው ነበር ::»

« እንደማይጨርሱት በምን አወቅክ ?» አለኝ ::

« ትንሽ ናቸዋ ::»

« ግን እነ አባዬ ቢያዩንስ ?» ጠምቤ አባቷን ፈርታቸዋለች ::

« ምናችን ሞኝ ነው እያዩን የምንበላው ::» አለ ጠይሜ

« እና እንዴት እንበላለን ? እንዴትስ እናገኘዋለን ?»

« ሥራ እንፍጠር ?»

« ምን ዓይነት ሥራ ?»

« አስተናጋጅ እንሁን ::»

« ምርጥ ሀሳብ !» የጠይሜን ሀሳብ አደነቅኩለት

ሦስታችንም እጆቻችንን በቦከስ አገሚጭተን የየራሳችንን ሳምናቸው :: እነ ሚይረም በሳህን እየሞሉ ይሠጡናል :: እኛ ሙስሊም ሙስሊሞቹን እየመረጥን እናድላለን :: ከዚያ ሁለት ሁለት ሠህን ሙሉ ጥብስ መቀመጫችን ሥር ለሙከታር አደራ ሠጠተን ደበቅን :: ተጨብጭቦልን፣ ተመርቀን ፣ እጃችንን በሳሙና ሙልጭ አድርገን ታጥበን የራሳችንን ድርሻ ከከርስትያኖቹ ብረት ምጣድ ተዘግኖ ተሠጠን :: የምንበላው በዛ:በን :: ከጥጋብ በላይ የሆነ አበላል :: መምረጥ ጀምርናል:: በነፍስ ወከፍ የሦስት የሦስት ሠህን ባለቤቶች መሆናችንን አረጋግጠናል ::

የያዝነውን ከከርስትያኖቹ የተቀበልነውን ጥብስ ከፊታችን ተቀምጠው ለነበሩት ልጆች ለምነን



@BOOKALEM

ሠጠናቸውና መቀመጫችን ሥር አሥቀምጠናቸው ወደነበሩት ሠህኖች እጆቻችንን ሠደድን ። ለጥብስ የተላኩት ጣቶቻችን አፈር ቧጠጡ ። የሦስታችንም ሠህኖች የሉም ። ከመቀመጫችን ተነስተን ፈለግናቸው የሉም ። ሱራፌልና ተሾመ እንዳናያቸው ጀርባቸውን ሠጥተው ይበሉታል ። የኛኑ ሠርቀው ፤ ከኛው ተደብቀው እየበሉብን እንደሆነ ርግጠኞች ሆንን ። ምክንያቱም እኛ ገና እያስተናገድን እያለ ነበር ድርሻቸውን ጨርሠው ሠህኖቻቸውን የመለሱት ።

ጠይሟ ፍየሎቹ ሲታረዱ ተቆርጦ የተጣለውን የፊት እግር አንስቶ ሱራፌልን በኮቴው አናቱን ቀወረው ። ሆዳሙ ሱሬ ግን ጭንቅላቱን እያሻሸ ጥብሱን ከመዋጥ አልተቆጠበም ።

ተሾመ አከራሪ የሚባል ዓይነት የቤተክርስትያን ልጅ ነው ። የወጣት መዘምራን ኅብረቱ ዘማሪም ጭምር ። ጠምቤ ስለበገነች እግሯ ሥር ያገኘችውን ዝርግ ሠህን አንስታ የሠህን ጥፊ አቀመሠችው ። ተነስቶ ጉሮሮዋን አነቃት ።

« ተሺ የሙስሊሞቹን ጥብስ እኮ ነው የበላችሁት !» አልኩት።

ደንግጦ ለቀቃት ። ምራቁን ደጋግሞ ተፋ ።

«ጊዮርጊስን በል እስቲ !»

ሻካራ መዳፉ ላይ የመስቀል ቅርፅ ሠርቼ በጊዮርጊስ ማልኩለት።

የበላውን ሊያስመልስ ታገለ ። ጣቱን ወደ ጉሮሮው ሠደደና ዘረገፈው ። ሱሬም በፊናዋ እየደጋገመች ምራቋን ትተፋለች ። እጇን በአፈር ትጠራርጋለች ። የታባታቸው ሠራንላቸው ። የበሉትን አስተፋናቸው ። በእጃቸው ሠርቀው እንደበሉ በእጃቸው ከደበቁበት ጎርጉረው አወጡት ።

በዓመት ውስጥ ለየልደታዎቹ ከሚቀቀሉት ንፍሮዎች የግንቦቱን የሚያክል የለም ። በብዛት ብቻ ሳይሆን በጣዕምም የግንቦቱ ለየት ይላል ። መንደርተኛው ጠቅላላ ገንዘብ ማዋጣት የሚጀምረው ቀድሞ ነው ። ለምሳሌ ለሚቀጥለው ዓመት ልደታ የዛሬው በዓል ላይ ገንዘብ ማዋጣት ይጀምራል ። ዶሮም ፤ ፍየልም የሚሳል በሕዝቡ ፊት ቃል ይገባል ። «ጠላ እጠምቃለሁ። የሀበሻ አረቄ አውጥቼ ለታዳሚው አጠጣለሁ ።» የሚሉ እናቶችም ብዙ ናቸው።

ሁሉም ከመቀመጫው እየተነሳ ስዕለት ይሳላል ። ትልልቆቹ ሰዎች ለቀጣዩ ዓመት በዓል ድምቀት መዋጫቸውን ተናግረው ሲጨርሱ ለልጆች ታሪክ የሚነገርበት ጊዜ ይሆናል ።

በግንበኝነት ሞያው በሠፈራችን ታዋቂ የሆነው አንተነህ ተነሳ ። ጭብስ ብሏል ። ቢድብድብ ያጣቸውን ሁለት የፊት ጥርሶቹን « የተፈጥሮ ፍንጭቶቹ ናቸው » እያለ ያስወራባቸዋል ። ጭንቅላቱ ላይ ፀጉር አለ ከተባለ ከጆሮዎቹ ጥግ ጥግ እንደተጠቀለሉ በቅለው የሚቆጠሩት ገብስማ ፀጉሮቹ ብቻ ናቸው ።

« ወገኖቼ ! በዚህ የእመቤታችን ልደት ላይ የምሳለው ስዕለት ለየት ይላል ። ምክንያቱም እኔ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ለአድባራችን ገቢ የማደርገው ሽራፊ ሳንቲም እንደሌለኝ ሁላችሁም ታውቃላችሁ ::»

ጉርምርምታ ተሰማ :: በተለይ ከበስተግራችን በኩል ያሉት ጎረምሶች አጠገብ የተቀመጠችው ቀለሟ በአንተነህ ንግግር ታለምጣለች :: አሷንም መጠጥ አሙቋታል ::

« አፈር ጠጣና...እንደ ስፖንጅ የቀረበልህን በሠኮንድ እየመጠጥከበት ቼስታ ነኝ ትላለህ እንዴ... ደፋር !»

ጎረምሶቹ ይስቃሉ ::

« እ...» ጉሮሮውን ጠራረገና « ርግጠኛ ነኝ የአድባራችን መልካም ፍቃድ ከሆነ ወር ከወር ሳላቋርጥ ከሠራሁ የሚቀጥለው ዓመት ላይ ለአቦነሽ ባንቴ የማደርግላትን እኔ አውቃለሁ ::»

«እስከዛ ስትቆይ አይደል ስዕለትህን የምታደርሠው አንተ ሠካራም :: ደሞስ ዕድሜ ነው ወይስ ሥራ እየለመንክ ያለኸው ? ይልቅ ያለህን አውጣና ቀብድ አስይዝ !» ቀለሟ አንተነህ ሳይሰማት ታንሾካሹካለች ::

«ስዕለቱ ይነገረን !» የጎረምሶቹ የኅብረት ድምፅ አስተጋባ

« ልናገር እኮ ነው :: ቀደም ሲል እንደተናገርኩት ዓመቱን ሙሉ ሳላቋርጥ ከሠራሁ አንድ ጠርሙስ የሀበሻ አረቄ...»

ሁሉም ሰው አጨበጨበ :: ሴቶቹ እልልታቸውን አቀለጡት :: ከረምት ከረምት ሲመሸላቸው ሠፈራችን መንገድ ላይ የተጠራቀመው የኩሬ ውሃ ውስጥ ተደብቀው በጩኸት የሚረብሹንን እንቁራሪቶች አስታወሠኝ እልልታው::

«መች ተናግሬ ጨረስኩና...ስዕለቴን አልጨረስኩም ዝም በሉልኛ ዘመዶቼ?»

ፀጥታ ሠፈነ::

«ከሀበሻው አረቄ በተጨማሪ የእማማ ኩሪን አንድ ገንቦ ጠላ ...»

«እልልል...ል»

«ኧረ ቆይ ቆይ ...ምን ይኼ ብቻ...አንድ አገልግል ለስለስ ያለ የዶሮ ፍትፍት...»

«እልልል...ል»

« አቤት አቤት አቤት ! እናንተን እንዲህ ሰብሰብ አድርጌያችሁ...»

«ብራቮ አንቴ ! ለዚያ ያድርሰን እንጂ አንቺ ብትረሺውም እኛ እናስታውስሻለን ::»

በጠይሟ ንግግር ሁሉም ሳቁ ::



@BOOKALEM

«እምዬ ማርያም እንዲህ ሰብስብ ብለን ልደቷን በአድባራችን ሥር እንዳከበርንላት ለቀጣዩም ዓመት አትነጣጥለን እንጂ የተሳልኩትን ስዕለት ፊት ለፊታችሁ...እያያችሁኝ ፤ እንደዛሬው በዕልልታና ጭብጨባ እያበረታታችሁኝ ጥብስቅ አድርጌ ብቻዬን ለመብላት ፤ ጭልጥ አድርጌ ለመጠጣት ታብቃኝ !»

የጎረምሶቹ ሳቅ የአካባቢውን ድባብ ቀየረው::

«አፈር ብላ ! አቦነሽ ባንቴ አፈር ድሜ ታስበላህ ። እኛ ነን እንዴ ያንተን ስዕለት የምናስገባው አምቡላም !» ቀለሚ መስከሯ በግላጭ ታወቀባት ።

እንተነህ እየሳቀ የቀለሚን ሰድብ ታጠቀ ።

ሌላኛው ደግሞ መራቂ ኾኖ ነበር ወደ መድረኩ የወጣው ። ክብሩ ደበበ ይባላል ። ወታደር ነው:: እስኪጠግብ ሲጠጣ እያመሸ ሌሊት ተነስቶ «ራበኝ » ብሎ ይጮሃል ። ጪኒንቷም ነው ። የሐረር ሰዎች ከእንቅልፉ ተነስቶ «ራበኝ» የሚል ሰውን « ጪኒንቷም» እንለዋለን ።

ክብሩ ወደ ጊዜያዊ መድረኩ ወጣና ከቡናው ረከቦት አጠገብ የተቀመጠውን በጠርሙስ የተሞላ አረቁ ብድግ አደረገው ። በወርቃማ ከዳኑ ቀነሠና ተጎነጨለት ።

« መጀመርያ መርቅ እንጂ የምን ማስጎምጀት ነው ?»

የእትዬ በለጡ ንግግር ብዙዎችን ፈገግ አሠኘ ።

«እሺ አመርቃለሁ...እጆቻችሁን ዘርግታችሁ አሜን አሜን በሉ ።»

እንዳለን ለማድረግ ተዘጋጀን ። ቡና ቀጂዋ መይሙና እንኳን ጀበናዋን አስቀምጣ ነበር ምርቃቱን ለመቀበል የተጣደፈችው::

«ልደታ ማርያም ከየቤታችን አውጥታ ፣ አቦነሽ ባንቴ ስር አስጥታ እንድንዝናና ስላደረገችን ክብር ምስጋና ይግባት ።»

« አሜን !» በሳቅ የታጀበ አሜን

«የዓለም የሲሳይ ቤት ታድርግልን !»

« ያምሃል እንዴ ወታደሩ ? አሁን የት እንዳለህ እንኳን አታውቅም ? ኧረ እባክህ ምርቃትህን አስተካክል ጃል ። ካልቻልክ አርፈህ መቀመጥ ነው እንጂ መዘላበድማ እያስፈልግም ። ሆይ... የዓለም የሲሳይ ቤት ይበልብን እንዴ !» በለጡ ቁጣዋ ገንፏል ። ምንም ነገር ስትናገር ጮክ ብላ ነው ። ፍርሃት ፤ ይሉኝታ ብሎ ነገር አይገባትም ።

« ምን ብዬ ልመርቅ ታድያ ወይዘሮ ቀበጡ ?»

«ምን አልክ አንተ ልብስ የለበሠ የወፍ ማስፈራርያ የመሠልክ ወታደር !»



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

« ምን ብዬ ልመርቅ ንገሪኛ !» ከሕዝቡ ጋር እየሳቀ መልሶ ጠየቃት ።

« ወዴት ወዴት...ለመሆኑ ስሜን ማን ብለህ ጠራኸኝ ?»

« ውይ አልሰማሽኝም እንዴ....በስምሽ ነዋ ! »

« ቀበጡ በለጡ ፤ በለጡ ነወጡ ብዬ !»

« ምን አባክ አልክ አንተ ስንጥር !»

«ውይ ቀበጡ ደሞ ነገር ማቋረጥ ትወጂያለሽ ። ምን አለበት ዝም ብትይልኝና ምርቃቴን ብቀጥልበት ?»

«ያንተ ቢቴ የቀበጠ ሠካራም በብርሌ ቅጥቅጥ ያርግህ ። አንት እከካም ! እናትና አባቴ ያወጡልኝን ስም የምትሠርዘው አንተ ማነህ ?»

ሳቅ ሹከሹከታው ደመቀ ። ትልልቅ ሰዎች በለጡን ለምነው አበረዷት ። ነገር ከያዘች አትለቅም። በተለይ «ቀበጡ» ካሏትማ ታብዳለች ። ትዳርና ልጅ የላትም ። ደግ ነች ። ብዙ ቀን እሷ ቤት አረቄ የሚጠጡትን እነ ጋሽ በላይን ፤ጋሽ መኮንንን ፤ ጋሽ ፌይሰልን ፤ ጋሽ ዚያዶን እና ስማቸውን የማናውቃቸውን ወታደሮች ተራ በተራ አልጋዋ ላይ ታሳድራቸዋለች ።

« እንግዲህ ወገኖቼ ምርቃቴን ቀጥያለሁ ...አሜን አሜን በሉ ሰዎች !» ከብሩ አረቄውን እንደጨበጠ ነው ።

የአንድ ሰው የዝም በሉ ጭብጨባ ጎልቶ ተሰማ ። ከበለጡ አጉረምራሚ ድምፅ ሌላ ድምፅ የለም ። «ለዛሬው በዓል ያደረሠን አምላክ በሕይወት ያሉትንም የሌሉትንም ሰብስቦ ለቀጣዩ ልደታ ያድርሰን ።»

ሳቅ በዛ።

« ምነው ? መልካም መመኘት ያስቃል እንዴ ? » ከብሩ የደነገጠ ይመስላል አጠያየቁ ።

«እኒ'ኮ መጀመርያውኑ የምትናገረውን ካላወቅክ አርፈህ ተቀመጥ ብዬሃለሁ።» በለጡ ልታስቅበት ፈልጋለች ።

« ምን አልኩ ? ምን ከፉ ቃል ከአፌ ወጣ ? ምን አጠፋሁ ወገኖቼ ?»

« አታፍርም እንዴ ?»

« ለምን አፍራለሁ ወይዘሮ ቀበጡ ?»

« ብለህ ብለህ ከሙታን ጋር የልደታ ንፍሮ ልታብላን ቀጠሮ ትይዛለህ ?»

« ኧረ በስመ አብ በይ ቀበጡ ...ኧረ የሠይጣን ጆሮ ይደፈን በይ !»



@BOOKALEM

«የባቴ አምላክ ጥቅጥቅ አርጎ ጀሮህን ይድፈነው ። ይኼኔ'ኮ እንደለመድከው አላልኩም ብለህ ልትከድ ይሆናል ። ለነገሩ መች ለከህደት አዲስ ሆንክና ። ወደፊት ማጅራትህን የሚሉህ በርካታ የኔ አይደሉም ብለህ የካድካቸው ልጆች እንዳሉህ የማናውቅ አይምሠልህ እሺ ! እናውቃለን ብንናገር እናልቃለን ብለን ነው ዝም ያልነው እሺ ንገሩኝ ባይ !» እጆቿን እያወራጨች ፣ ዓይኖቿን እያጉረጠረጠች ተውረገረገችበት ።

«አንቺ ጆሮሽ አይሰማምና ያላልኩትን ብያለሁ ብዬ ልመንልሽ እንዴ ?»

ተሰብሳቢው በሳቅና ሹክሹክታ ተተረማመሠ ። ጎረምሶች ሳቃቸውን በፉጨት አጀቡት ።

« አይ ከብሩ...አንተን ብሎ ከብሩ ! ቀብሩ ነበር መባል የሚገባህ ። በየትኛዋ ልደታ ላይ ነው ሙታን ከሕያዋን ጋር ተሰብስበው ንፍሮ ሲበሉ ያየሃቸው ?» አሉ ፀጉር ቆራጩ አባባ ደሰለኝ ።

ሌላ ሳቅ...ሌላ ሽሙጥ...ሌላ ተረብ...ሌላ ፌዝ...ሌላ ሌላ...

« ለዚህ ያደረስከን አምላካችን ከበር ተመስገንልን !»

« አሜን !»

« የታመሙትን ፈውስልን ፣ ደህነኞችን ከከፉ ደዌ ጠብቅልን ። በሥጋ የተለዩንን መንግሥተ ሰማያትን አውርስልን !»

« አሜን ! እልልል...ል»

« ያረገዙት ወልደው ፣ የተወለዱት አድገው ፣ ያደጉት ለቁም ነገር በቅተው ስማችንን የሚያስጠሩልን ጀግኖች ይሆኑ ዘንድ ባርከልን !»

« እልልል...ል»

« መንደራችንንና ሀገራችንን ባርከህ ዘመኑን የጥጋብ ፣ የሰላም ፣ የተስፋና የልምላሜ አድርግልን !»

«አሜን ! እልልል...ል»

የአባባ ደሰለኝ ምርቃት ከፍተኛ ፉጨት ፣ጭብጨባና እልልታን ተቀበለ ።

«ቀብሩ ! ምርቃት ሰማህ አይደል ?» የበለጡ ለከፋ ከብሩን አላስከፋውም ። እጇን ይዞ እየጎተተ ወጣቶቹ ወደ ጀመሩት ጭፈራ መሃል ይዟት ገባ ። እየተነሜነጨች የተንተተችለት ሴትዮ « ያዝ እንግዲህ » እያለች በጨለማ እስኪያልባት ትወዛወዝ ጀመር ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ አስራ ሰባት

## የቡዳ መድኃኒት

« ሸግዬ ቡዳነች ብለሽ ያወራሽው

ሰውን ሰው ሲበላው የታባሽ አየሽው ?»

እማማ ሸጌ

ከቁርጭምጭሚታቸው ተገልጦ እስከሚታየን ጉልበታቸው ድረስ ወጥ ነው ። ሙሉ ድፍን ያለ ፤ እንደ ስልክ እንጨት ተመሳሳይ የውፍረት መጠን የያዘ ፤ መርገጫቸው በጣም ወፍሮ ሸፍን ጫማ አያስጠልቃቸውም ። እንደ መጅ ባበጠው መርገጫቸው ቢረግጡን ያፈርጡናል ብለን እንሠጋለን ። « ሸጌ ዘነዘና እግር !» እንላቸዋለን እየተደበቅን ። ሁልጊዜ በነጠላ ጫማ አገር ሲያካልሉ ይውላሉ ። የተረከዛቸው ስንጥቅ ለልጅ ዓይን ያስፈራል ። ተረከዛቸውን የሆነ ነገር ቢገጨው ወይም ከዲብ ላይ ቢዘልሉ እንደ ምጣድ ተፈረካክሶ የሚወድቅ ይመስላል ። ከመሠነጣጠቁ መድረቁ ። ከመድረቁ መቆሸሹ ።

እማማ ሸጌ ምንም የቀጠነ አካል የላቸውም ። ሁሉ ነገራቸው በወፋፍራም ስጋ ተመርጓል። ከጉንጫቸው እስከ ጡታቸው ፤ ከቂጣቸው እስከ እግራቸው ባላስፈላጊ የስጋ ክምር ተበላሽተዋል። በርግጥ የእግራቸው ጉዳይ አንዳንዴ ሙሙት ይላል ። ልክ እንደኛ እግር ቀጫጫ ይሆናል ። ብዙውን ቀን ግን የወፍራም እግር ባለቤት ናቸው ። የባታቸው መቅጠንና የታፋቸው መወፈር ሲደመር ቅርፁ የዘነዘና ስለሚሆንብን ነው ሸጌ ዘነዘና የምንላቸው ።

እማማ ሸጌ ግን ይገርማሉ ።

« ሸጌ ዘነዘና ፤ ሸጌ ዘነዘና !» ስንላቸው

« አባትከን አቅፌው መደብ ላይ ልዝናና ።» እያሉ ወደ ድምፃችን አቅጣጫ ድንጋይ ይዘው ይመጣሉ ።

ወደኛ መጠጋታቸውን ሲያይ ጠይሜ ጠጠርና አፈር ይሰበስብና ከኋላቸው ይበትንባቸዋል። ቅጠላ ቅጠሉን ጠሠስ አድርጎ የሚወርደውን ኮሽታ ሲሠሙ ይበረግጋሉ ። ወደ ኋላ ያፈገፍጋሉ። ደግመን እንለከፋቸዋለን ።

« ሸጌ ዘነዘና !»

« ዲታላ ሁላ ! አንዩ ዶሮ በንፋስ የተወለድከ የሴት ልጅ ። አባት ቢኖርህ መች እንዲህ ሥርዓት ትለቅና ! ልቅ የልቅ ልጅ !። ይሳደባሉ ።



@BOOKALEM

« ሸጌ ዘነዘና እስቲ ልብ ካለሽ ወደኔ ተጠጊ ። ደምሽን መጥጬ ፣ ስጋሽን ቀርጭጬ ፣ አጥንትሽን አድቅቄ ነው የምለቅሽ ።» ይላቸዋል ጠይሜ ድምፁን ቀይሮ

« ለመኾኑ አንተ ማን ነህ ?»

« አወቂኛ !»

« እኮ ብቅ ብለህ አናግረኛ...ሳላይህ እንዴት ላውቅህ እችላለሁ ጌታው ?»

« ሳታዪኝ ልታውቂኝ አትችይም እንዴ ?»

« እንዴት አድርጌ ሳላይህ ማወቅ ይቻለኛል ?»

« ቡዳ አይደለሽ እንዴ ?»

« ምን አልክ አንተ ?»

ሦስታችንም ተንከትክተን ሳቅን። እያየናቸው ነው የምናዋራቸው ። ወደ ድምፁ አቅጣጫ ጠጋ ሲሉ በሌላ አቅጣጫ ጢሻውን ጠሥስ እናደርግባቸዋለን ። ወደተንኮሻኮሸበት ሲዞሩ በሌላ በኩል ያለ ሰው ድምፅ ያሰማቸዋል ። አስፈሪ የማናውቀው አውሬ ድምፅ ።

« ለመኾኑ ስንት ናችሁ ?»

« ማ እኛ ?»

« አዎ እናንተ !»

« ሰላሳ ሦስት ፣ ስልሳ ስድስት ፣ አንዳንዴ ዘጠና ዘጠኝ ፣ አንዳንዴም ከዚያ በላይ ።»

« ምንድን ናችሁ ?»

« የቀትር ጋኔሎች ፣ የዲያቢሎስ ቁራጮች ፣ የሠይጣን ግልገሎች ነን ።»

«ሉ !» እማማ ሸጌ ደነገጡ ። ደረታቸውን በመዳፋቸው ደገፉ ።

« ምነው ደነገጥሽ ? ነቃንብሽ አይደል ? አትፍሪን ...የኛና ያንቺ ሥራኮ አንድ ነው ።» ጠምቤ ነበር ድምፁን ቀይሮ ያናገራቸው ።

« ኧረ ! እኔ ከናንተ ጋር የሚያዛምድ ምንም ነገር የለኝም ።»

« ቡዳ አይደለሽ እንዴ ?»

« አይደለሁም !»

« እናውቅሻለን እኮ አልም ያልሽ ቀርጣፊ ቡዳ ነሽ !»



@BOOKALEM

« አይደለሁም ! እኔ ሸጊቱ ታፈሠ እህል እንጂ ሰው አልበላም ::»

« ቡዳ ነሽ ! የመንደሩን ልጆች እንደ እሸት በቆሎ በዓይንሽ ጥርስ ግጠሽ የጨረስሻቸው አንቺ ነሽ !»

« አይደለሁም !»

« ነሽ !»

« አ...ዉ...ዉ !» ሦስታችንም እንደ ጅብ ጮኽንባቸው ::

እማማ ሸጌ ሁለት ጆሯቸውን በጣቶቻቸው ደፍነው ጮኹ :: በጢሻው ውስጥ እየተሽሎከሎከን ሮጥን :: በርካታ ሰዎች ተሰበሰቡ :: እኛም ከሌላ ቦታ የመጣን መስለን ሰዉን ተቀላቀልነው ::

« አሂሂ ! ይኼኔ አንዱን አንከታው ይኾናል የሚያስለፈልፋት ::» አሉ የጠይሜ አባት

« እነሱኮ ጠበል መንፈሳቸው ላይ ሲያርፍባቸው እንዲህ ያደርጋቸዋል :: ጠበል እንደ አሲድ ነው የሚለበልባቸው ::» እማማ ካሱ በጀርባቸው የተዘረሩትን እማማ ሸጌን በእጃቸው እያመላከቱ ተናገሩ :: ሁሉም ሰው የየራሱን መላ ምት ሠጠ ::

እማማ ሸጌ በመንደራችን ዕውቅና የተሠጣቸው ቡዳ ናቸው :: ሰውን በተለይም ቆንጆ ልጅንና እርጉዝ ሴትን ቅርጥፍጥፍ አድርገው እንደሚበሉ በሠፈው የሚነገርላቸው :: የሚቀራቸው ምንም የሌለ ፣ ሕፃን አዋቂው የሚፈራቸው ሴት ::

ቡና አጣጭ ጎረቤት የላቸውም :: ሰዎች መልካቸውን ፣ ልጆቻቸውንና ምግባቸውን ከእማማ ሸጌ ዓይኖች ይደብቃሉ :: እናቶቻችን ከእማማ ሸጌ ሲገናኙ ቢያንስ ሦስት ጊዜ ምራቃቸውን ይተፋሉ :: አንዳንዶች ደሞ ፊት ለፊት ሲገጣጠሙ « ቡዳ !» ብለው ተሳድበው ያስደነግጧቸዋል:: ሲደነግጡ አይበሏቸውም ::

እናቴ ሁልጊዜ ከኪሴ ሽምብራና ነጭ ሽንኩርት እንዳይጠፋ ታስጠነቅቀኛለች :: ሽምብራው ለጥርሴ ጥንካሬና ለሆዴ ሙሌት ያገለግላል :: ነጭ ሽንኩርቱ ደሞ የቡዳ መድኃኒት ነው :: እማማ ሸጌ ይገኙበታል በሚባልበት መስመር ስደርስ ተልጣ የተዘጋጀችውን ሽንኩርት ከኪሴ አውጥቼ በእጄ እይዛለሁ :: ከእሳቸው ጋር ስገጣጠም ቶሎ ብዬ ወደ አፌ እጨምርና በጥርሴ ዶሽ አድርጌ አፈርጠዋለሁ :: በልቤም ሦስት ጊዜ « ቡዳ ! ቡዳ ! ቡዳ !» እላለሁ :: እንዲህ ካላደረግኩ እማማ ሸጌ እንደሚበሉኝ ተነግሮኛል ::

ከነ ጠይሜ ጋር ካልሆንኩ በስተቀር በምንም ተዓምር አልደፍራቸውም :: እናቴ ስለ እሳቸው የነገረችኝ ታሪክ በሕልሜም ጭምር እየመጣ ያስበረግገኛል :: ሲጨልም እፈራለሁ :: በጨለማ ውስጥ የእማማ ሸጌን ምስል አያለሁ :: እንደ ጅብ እየጮኹ ፣ በትልልቅ ጥርሳቸው ሊቦጭቁኝ ሲሮከሩብኝ ፣ ከእናቴ እጅ ነጥቀው ሊወስዱኝ ሲታገሉኝ እያየሁ እቃዣለሁ ፣ እባንናለሁ ::



@BOOKALEM

« እማዬ !» አልኳት አንድ ምሽት ገላዬን በሳፋ ውስጥ እያጠበችኝ ሳለ

« ወዬ ጭንቅሎዬ !»

« ቡዳ ምንድን ነው ?»

« ቡዳማ...ቡዳማ እንደ ሸጊ ያለ ነዋ ::»

« አግሩ ወፋፍራም ሁላ ቡዳ ነው ማለት ይቻላል ?»

« እንዴታ !»

« እንዴታ ምን ማለት ነው ?»

« ውይ አንተ ልጅ ምነው ጥያቄ አበዛህብኝ ?»

« በደንብ እንዲገባኝ ብዬ ነዋ እማዬ ደሞ ::»

« ይኸውልህ ጭንቅሎ...ቡዳ እንደ ሸጊ በዓይኑ ቅርጥፍጥፍ አድርጎ ልጅን የሚበላ የሰው ጅብ ማለት ነው ::»

« የሰው ጅብ ሰው የሚያረባው ጅብ ማለት ነው ? ቆይ ግን ሰው ውሻ እንጂ ጅብ ያረባል እንዴ ?»

« ኤድያ ! አንተ ነገር አይገባህምና ለእያንዳንዱ ጥያቄህ ትንታኔ ስሠጥህ መዋል አለብኝ ማለት ነው ?»

« ቆይ ምን አለበት እማዬ ?»

« እኔ'ኮ ያልገባኝ ...ቆይ አንተ ስለ ቡዳ ማወቅ ምን ያደርግልሃል ?»

« በቃ ፈለግኩኖ :: በናትሽ ንገሪኝ !» በርጥብ እጆቹ ጉንጮቿን እያሻሸሁ ለመንኳት ::

« ምኑን ልንገርህ የኔ ልጅ ?»

« እንዴት ነው ቡዶች ልጆችን የሚበሉት ? በጥርሳቸው እንደ ውሻ ዝንጥል ያደርጋሉ እንዴ ?»

« ምን አለ መሠለህ ጭንቅሎ...የነሱ ጥርስ ዓይናቸው ውስጥ ነው :: ዓይናቸው ውስጥ ባለው ጥርስ ቅርጭጭ ያደርጉሃል ::»

« ኧ !» በድንጋጤ ጮኽኩ ::

« ምን ያስደነግጥሃል ? ንገሪኝ አላልከም እንዴ የምን መንፈሽፈሽ ነው ? እንደ ወንዶቹ ደንደን ብለህ አዳምጥ እንጂ !»



@BOOKALEM

በድንጋጤ እየተንቀጠቀጥኩ ስለነበር ትከሻዋን ተደግፌ ሳፋው ውስጥ ቆምኩ ። ትኩስ ሽንቴን አጉራሽ እጇ ላይ ለቀቅኩት ። ውሃ ረጨት አደረገችብኝ ።

«ቆይ ሲበሉኝ ያመኛል? እ...ደሜ ይፈሳል? የተበደሠው ጮማዬ ይታያል ?»

« አሂሂ ! ሲሉ ሠምታ አሉ ጭንቅሎ...አሁን አንተ ገላ ላይ እንዲህ ጮማና ቀይ ሥጋስ ተፈልጎ ይገኛል ? አሆሆ ...መቼስ ወግ አይቀር !»

« እንዴት አይገኝም ?»

« አብልቼ አጠጥቼህ ለውጥ ባጣብህ መስሎኝ ‹ጥሬ ሽምብራ ስጪው ይወፍርልሻል› ተብዬ ጥሬ በኪስህ የማሳቅፍህ ።»

« ስለዚህ እማማ ሸጌ ቀሚጫ ስለሆንኩ አይበሉኝማ ?»

« ታነክትህ !»

« እና ምን ይሻለኛል እማ ?»

« የሚሻለውማ እግርን መሰብሰብ ፣ የትም ሲንቀዋለሉ ከመዋል እቤት ተቀምጦ ማጥናት ፣ እንደ ሰዉ ልጅ ጨዋ መኾን ፣ እንደ አህያ ያገኙትን አለማመንገር ።»

« እህ ! መንገድ ላይ እንዳልበላ ከፈለግሽ ለምን ሽምብራና ነጭ ሽንኩርቱን ሠጠሽኝ ?»

« ጅሎ ! እሱማ መድኃኒትኮ ነው ጭንቅሎ ።»

« የምን መድኃኒት ?»

« የቡዳ !»

« መድኃኒት የሚወሠደው ሳይታመሙ ነው እንዴ ?»

« አዎ ! የቡዳ መድኃኒት ቀድመህ ካልወሠድከው ከተበላህ በኋላ ዋጋ አይኖረውም ልጄ ።»

« ደሞኮ የሠጠሽኝ ነጭ ሽንኩርት እንጂ ኪኒን አይደለም ።»

« ጅል ! የጅል ዘር...መድኃኒት ሁሉ የሚቀመመው ከምን ሆነና...የባህል ሐኪሙ አባ ገብረ ሕይወት 'ነጭ ሽንኩርት ከሁለት መቶ በላይ በሽታዎችን ያድናል ። ከዚህ ውስጥ አንደኛው ቡዳን መከላከል ነው' ብለዋል ያለፈው ዕድር ስብሰባ ላይ ።»

« በምን ይገናኛል ?»

«ይኸውልህ ጭንቅሎ...አንተ ሸጌን ስታያት ቶሎ ብለህ ነጭ ሽንኩርትህን በጥርስህ ዶሽ ስታደርግባት ልቧ ቀጥ ትላለች ፣ ትደነግጣለች ። የዚያኔ ተርበትብታ ካጠገብህ ትጠፋለች ።



@BOOKALEM

ያለዚያ ግን ትበላህና ትገድልሃለች ::»

« ከገደለችኝስ በኋላ !»

« ከገደለችህ በኋላማ አሽከሯ ታደርግሃለቻ ::»

« ኧ ! ከሞትኩ በኋላ ?»

« አዎ ! ሞተህ ከተቀበርክ በኋላ በጥበቧ ታስነሳሃለች ::»

« እህ ! የሞተ ሰው ይነሳል እንዴ ?»

«ወደህ ነው እንዴ የምትነሳው? እነሱ'ኮ የሚያስነሱበት መተት አላቸው ::»

« መተት?»

« አዎ ! መተት !»

« መተት ምንድን ነው እማ ?»

« አዚም ፤ አፍዝ አደንግዝ ነዋ ልጄ ::»

« አዚምስ ምንድን ነው ?»

« ሆሆይ ! ምናለ ዝም ብለህ የምነግርህን ብታዳምጥ !»

« ሳይገባኝ ?»

« ቆይ ቢገባህ ባይገባህ ምን አሳጨነቀህ ? ፈተና ላይ ይመጣል ያለህ አስተማሪ አለ እንዴ ?»

« እሺ ! ጨርሺልኝ ::»

« ምኑን ?»

« ቡዶች በልተውኝ ከሞትኩ በኋላ ከመቃብር አስነስተው እንዴት አሽከራቸው እንደሚያደርጉኝ ::»

« ይኸውልህ ቡዶች በማኅበር ተሰባስበው እሸት አተሩን በድንጋይ ወፍጮ መቃብርህ ላይ ይፈጩና እዚያው ጉልቻ ጎልተው ቂጣ ይጋግራሉ ። የዘንጋዳና ጤፍ ንፍሮ ይቀቅላሉ። የንፍሮውን ውሃ መቃብርህ ላይ እያጠነፈፉ በፈላው ውሃ ያቃጥሉሃል ። ከዚያ የጋገሩትን የአተር ቂጣ ሁለት እኩል ቦታ ሲቆርሱት መቃብርህን ፈንቅለህ ፤ አፈርህን አራግፈህ ትነሳለህ ። ስታያቸው ትደነግጥና ትሰግድላቸዋለህ ።

« ስትደነግጥላቸውና ስትሠግድላቸው ደስ ይላቸዋል ። በገመድ አስረው እንደ በግ እየጎተቱ ወደ ቤታቸው ይወስዱህና የከብቶቻቸውን እበት ያስጠፈጥፉሃል ። ማገዶ ከዱር ያስለቅሙሃል።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

የማንንም እርሻ ከበሬ ጋር እየጠመዱ ያሳርሱሃል ። ምግብ በቀን አንዴ እየሠጡህ በቀን ሦስቴ በሽበ ጅራፍ ይገርፉሃል ። ውሃ ከሩቅ ወንዝ ያስቀዱሃል ። ሲፈልጋቸው እጅህን ፣ እግርህን ፣ አንገትህን ለብቻ ለብቻ እየገነጣጠሉ በእሳት ይጠብሱሃል ።»

ደነግጥኩ ። የሰማኹት ታሪክ የደረሠብኝ ያከል እንባዬ አልቆም አለኝ ። በምሽት የተነገረኝ የቡዶች ታሪክ ጣፋጩን እንቅልፌን ነጠቀኝ ። ኮሽ ባለ ቁጥር ስበረግግ ነጋ ። እማማ ሸጌን ከኮሽታ ጀርባ ስፈልጋቸው አደርኩ ። ነግቶም ማመን አቃተኝ ። የምሬን ጠላኋቸው ። የፈለገ ነገር ይመጣል እንጂ ብቻዬን በደጃፋቸው አላልፍም ።

በመሽ ቁጥር ስለ ሠይጣንና ቡዳ ሲወራብኝ እፈራለሁ ። የሚወራልኝ ወሬ እንዳይቋረጥብኝ እየሠጋሁ እያለቀስኩም ቢሆን አዳምጣለሁ ። ማልቀሴ የሚታወቀኝ የአንባዬ ኳሶች ማየት ሲጋርዱኝና ንፍጤ ሲዝረበረብ ነው ። በሹራቤ እጅጌ የአፍንጫዬን ፈሳሽ ሞዥርቄ ሳነሳው እያለቀስኩ እንደነበር ይገባኛል ።

እማማ ሸጌን የሚዳፈረው ልቤ እነ ጣይሜ ዘንድ ተቀምጧል ።ከነ ጣይሜ ጋር ከኾንኩ በምንም ተዓምር አልፈራቸውም ። እየተደበቅን እናስጮሃቸዋለን ። እንሠድባቸዋለን ። ሲያለቅሱ እንስቅባቸዋለን ።

እንደ ልማዳችን ተደብቀን ስናስለቅሳቸው «ተራመድ» የሚባለው ገጠሬ የትምህርት ቤታችን አትክልተኛ ያዘን ። ሦስታችንንም እንደ በግ አስተሳስሮ እየነዳ ለእማማ ሸጌ አቀረበን ። አልመቱንም ። አተኩረው ከተመለከቱን በኋላ ወደነ ጠምቤ ቤት ሄዱ ። ከኋላቸው ተከትለን የነ ጠምቤን የወፍ ቆሎ አጥር ተከልለን የሚሉትን ለመስማት ጓጓን ።

« ምን ኾነሽ ነው የምታለቅሺው ሸጌ ?» የጠምቤ እናት ጌሿቸውን በጠማማ መጥረቢያቸው እየቀረጠፉ ጠየቋቸው ።

« ልጅሽ እየሠደበኝ እንዴት አላለቅስ እሜቴ ።» እንባቸውን በነጠላቸው ጫፍ ያብሳሉ ።

« የማን ? የኔው ልጅ ?»

« አዎ ! ያንቺው ልጅ !»

« የትኛው ?»

« መልኩን እንጂ ስሙን የታባቴ አውቄው ።»

« ትልቁ ነው ትንሹ ?»

« ኸረ ትልቁ ምን በወጣው እናቴ !»

« እና ጠምቤ ሰደበኝ እያልሽኝ እንዳይኾን ብቻ ?»



@BOOKALEM

« እንዴት አልልሽ ? ሙልጭ አር ጎ በስድብ ሳሙና በገዛ ዳሮዬ አጥቦ አሠጣኝ እንጂ ።»

« ምን እያልሽ ነው ሸጌ ? እርግጠኛ ነሽ የኔው ጠምቤ ነው የሰደበሽ ?»

« ምን እርግጠኝነት ያስፈልገዋል ? ያንቺ ልጆች ጠፍተውኝ ነው እንዴ ትዘላብዳለች ብለሽ የምትጠረጥሪኝ ?»

«ሥነ-ሥርዓት ሸጌ ! እኔ የልጆቼን ጠባይ አውቀዋለሁ ። ዓይኖችሽን ከልጆቼ ላይ አንሺ ። እሱ እንኳንስ ሊሰድብሽ ቀና ብሎም ሊያይሽ አይደፍርም ፤ ይፈራሻል ።»

« እኮ ! ጨዋው ልጅሽ ቀና ብሎ እንደማያየኝማ ታየልሽ ።»

« ማነው ያየው ?»

« እኔው...ተደብቆ ሲሞልጨኝ በዓይኔ በብረቱ አየሁልሽ ።»

« ምን ! በዓይኔ በብረቱ ትይኛለሽ እንዴ በቀስቱ በይኝ እንጂ ። ሸጌ አባከሽ ልለምንሽ ልጄ ላይ ትፊበት ። የሰንት ሰው ፊት ገርፎኝ ፣ ዝናብና ፀሐይ ተፈራርቆብኝ በመከራ ያሳደግ ኩት ልጄን እንዳትበይብኝ ። እሱን ከምትበይብኝ እኔን እናቱን እንደፈለግሽ ቀረጣጥፊኝ ።»

እማማ ሸጌ ተናደዱ ። ፊት ለፊታቸው ያገኙትን ጌሾ የሚቀረጥፍበት ጉቶ አንስተው ወደ ጠምቤ እናት ተጠጉ ። የነ ጠምቤ ጎረቤት ገላጋይ ኾነው መሃል ገቡ ። ሳለመመታት እየተጠነቀቁ ከእማማ ሸጌ ላይ ታግለው መጥረቢያውን ነጠቋቸው ።

« ትልቅ ሰው ሲደባደብ አይተህ ታውቃለህ ?» ጠምቤ ለእናቱ ሊያግዝ ሲል ጠይሜ እጁን ያዘና ጠየቀው ።

« አላውቅም ።»

« በቃ እናትህ ሲደባደቡ እንያ ?»

« እ !» ጠምቤ ደነገጠች ።

« ከተወገሩ'ኮ እናግዝላቸዋለን ።»

ተስማማ ።

« አንቺ ሙቅ ዓይን ! ሰንቱን ፊጅተሽ ስታበቂ ደሞ በልጄ መጣሽ ?» የጠምቤ እናት የጌሾ መቀርጠፊያውን ጉቶ እያምዘገዘጉ ፣ በገላጋዩ ትከሻ እየተንጠራሩ ተሳደቡ ።

ተራመድ ለእማማ ሸጌ አግዞ ቀጥቅጦናል ። ገላችን ሠምበር በሠምበር እስኪኾን ገርፎናል ። ያን ያክል ቢጎዳንም ለቤተሰቦቻችን አልተናገርንም ። ከተናገርን ምክንያት እንጠየቅና እንገረፋለን። አልቅሠን ፣ አልቅሠን ሲወጣልን ተራመድን የምናጠቃበትን አሪፍ ዘዴ ጠይሜ ጠቆመን ።



@BOOKALEM

ሦስታችንም እነ ጠይሜ ግቢ ገብተን ኡኡታችንን አስነካነው ። እየተንፈራፈርን « በላኝ ! በላኝ! ቦጨቀኝ ተራመድ ዘለዘለኝ !» እያልን ጮህን ። ጠይሜ በሥጠን መመሪያ መሠረት መፍራትና መንቀጥቀጥ አይቻልም ።

ጋሽ በቄ ደንግጠው ሚታቸውን በትንው ተነሱ ። ማናችንን ይቆጣጠሩ ? ማናችንን ያባብሉ ? ዝም አንለ አልናቸው ። ለዚህ የፈጠራ ጥበባችን ውጤታማነት ጋሽ በቄን የመረጥንበት ምክንያት ከሳቸው የተሻለ ነገርን ሳያጣራ ፈጥኖ እርምጃ የሚወስድ ሰው ስለማናገኝ ነው ።

« የት ነው የዋላችሁት ?» ጋሽ በቄ ጠይሜ ላይ ጮኹበት ።

« ቢጫ ሜዳ ኳስ እየተጫወትን ነበር ።»

« እና ምን ኾናችሁ ? ወደቃችሁ ? ከሰው ተጣላችሁ ?»

« አልተጣላንምም ፤ አልወደቅንምም ።»

« እና ምን ሆናችሁ ?»

« ተራመድ ፍጥጥ ብሎ አየን ።»

« እና አፍጥጦ ቀርቶ አግጥጦ ቢያያችሁስ ?»

« ሲያየን ሦስታችንም ልባችንና ዓይናችንን ወጋንና ወደቅን ። አ ! አ ! አ !» አለና ጠይሜ ደረቱን ደግፎ አቃሠተ ።

« ምን !» ጋሽ በቄ በድንጋጤ ጮኹ ።

እኔና ጠምቤ ተርበተበትን ። አንገታችንን ደፋን ዓይናችን ሥር ምራቃችንን እየቀባን ያለ እንባ አለቀስን ። ዓይኖቻችን እንዲቀሉ ፍትግ አድርገን አሸናቸው ። ጋሽ በቄ አባብለው እቤታቸው አስገቡንና የከሰል ፍም ላይ ሳይላጥ የተጠበሠ ድንችና ሻይ ሠጡን ። ከግቢ ሳንወጣ እንድንጫወት አዘዙን ። እኛ ግን የልባችን ስላልደረሠ የተንኮል ሸረባችንን ጀመርን።በሌላ ዘዴ ተራመድን ልናስወቅጠው ተመካከርንበት ።

ድንገት እየተጫወትን ሳለ « ኡ ! ኡ ! ተራመድ መጣ ሊበላን ነው !» እያልን ወደ ጋሽ በቄ እየሮጥን ሚታቸውን በሰላም አርፈው እንዳይቀመጡ ረበሽናቸው ። ቂም እንዲቋጥሩ አደረግናቸው ። እኔም ጠምቤም ወደ ቤታችን ብቻችንን አንሄድም ብለን እግራቸው ላይ ተጠመጠምን ። አባብለው በየቤታችን እያደረሱ ስለኾነው ጉዳይ ከወላጆቻችን ጋር አወሩ ። ስለ ተራመድ ዘር ማንዘር በጋራ ሊያጠኑ ተስማሙ ።

በምክክራችን መሠረት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ጠይ ሟ ጮሆ እድርን ጮኸ ። ሠፈርተኛው ግልብጥ ብሎ ለያኘ ያስተገረውን ጠይሜን ያግብላል ። እኔና ጠምቤም ከወላጆቻችን ጋር ሆነን ከጩኹቱ ቦታ ተገኘን ። መሬት ላይ እየተንፈራፈረ የሚጮኸውን ጓደኛችንን አገዘነው ።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

የተራመድን ስም እየጠራን « በላኝ ፤ በላኝ ! እኝከኝ !» እያልን ጮህን ። የኛ ቤተሰቦችም ከጋሽ በቂ የተነገራቸውን በተግባር አረጋገጡት ። የጠይሜና የኔ ታላላቅ ወንድሞች ጭንቅላቱ ድቡልቡል የኾነ ዱላ ይዘው ወደ ተራመድ ቤት ሄዱ ። ሁለቱም ተደብቀው ሲቅሙ ውለው ማምሻውን ጠላ ስለሚጎነጩ ሞቅ ብሏቸዋል ። የተራመድን ቤት ገንጥለው ገብተው በዱላ እስኪበቃው ወገሩት ። እየቀጠቀጡ ያለነበት ድረስ አመጡት ። የቡና አተላና አመድ በግድ ጋቱት ። እያለቀሠ ያለ ስሙ ስም ሰላሣጠነው እያረረ «ተፋባቸው !» ሲባል በአመድና አተላ የላቆጠ አከታውን ሊደፋብን ። ሠፈሩን ትቶ እንዲሄድም ማስጠንቀቂያ ተሠጠው ። እያነከሠና እያለቀሠ በመንደራችን ሰዎች እየተወገዘ ወደ ቤቱ ገባ ።

አፍሮ ፣ እንገቱን ደፍቶ ቡዳነቱን በግድ ለጥፈንበት በሩን ዘጋ ። ሲነጋ የሠማነው ዜና ግን ይቀፋል ፡ ተራመድ የቤቱ ወራጅ ላይ እራሱን በገመድ አንቆ ሞተ ። ያዘነለት አልነበረም ። «ልጆቻችን ከመበላት ተረፉልን ፤ የታባቱ ይሄ ቡዳ !» ተባለ።

ከነጭ ሽንኩርት በተጭማሪ ሦስታችንም እንገታችን ላይ የምናንጠለጥለውና በሰው ዓይን ከመበላት የምንድንበት ክታብ አለን ። ገላችንን ስንታጠብ ወይም ስንዋኝ ካልኾነ ከአንገታችን አይወልቅም ። « ውሃ ከነካው መድኃኒትነቱ ያከትምለታል ፤ ይረክሳል !» ስለተባልን ከውሃ አናገናኘውም ። አንገታችን ላይ አንጠልጥለነው እየዞርን እንፈራዋለን ።

ጠይሜ ድፍረትና ምርምር ያበዛል ። የዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጠን በእምቧይ ብይ ተጫውተን ስናበቃ « ክታባችንን ፈትተን ለምን ውስጡ ያለውን እውጥተን አንመራመርበትም ?» አለን ። ፈራን ። ስናንገራግርበት እንዳንፈራ አበረታታን ። የራሱን በትኖ አሳየን ። በሰስ ወረቀት ላይ በቀይ ብዕር ጥቅጥቅ ተደርጎ የተጻፈ ነገር አነበብንበት ። ያነበብነው ምንም አልገባንም ። ፊደሉ እንጂ ቃሉ አማርኛ አይደለም ። የጠምቤ ክታብ ሲፈታ ምንም ጽሑፍ የሌለው ባዶ ነጭ ወረቀት ኾነ፤ ሳቅን ።

ሞራሌ መጣና የኔን ከፈትኩት ። የቆዳ ሽፋኗን በጥርሴ ቀስ ብዬ አላቀቅኳት ። በቢጫ ወረቀት ላይ በሚያምር እጅ ጽሑፍ የሚከተለው ሃሳብ ሠፍሯል ።

« ...አይ የጭንቅሎ እናት ለመኾኑ እኔ ማን የሚሉኝ የቡዳ መድኃኒት ሠሪ ነኝና ነው ወደኔ የመጣሽው ? ደሞስ ቆንጆ ልጅ እንዳለሽ ከቡዳ ለመከላከል መድኃኒት ስታሠሪ አታፍሪም ? ደፋር ነሽ ! ማርያምን ደፋር ነሽ ! ይኼን እንኳን በዓይን በጥርስ ተግጦ ሊበላ የሚችል ስጋ አላዩ ላይ ያልበቀለ ልጅ ይዘሽ የቡዳ መድኃኒት ማሠራት ያምርሻል ? እኔ የጭንቅሎ ወላጅ ብኾን እንኳን የቡዳ መድኃኒት ላሠራለትና እንደተወለደ ነበር የሰው መሳቂያ ሳልኾን እንደ ጦስ ዶሮ ጉሮሮውን አንቄ የምደፋው !»

ጠይሜና ጠምቤ ሆዳቸውን ይዘው ሳቁብኝ ፤ ተንፈቀፈቁብኝ ። አኮረፍኩ ። ለዓመታት ስድቤን በአንገቴ ላይ አንጠልጥዬ መዞሬን ሳስበው ቀፈፈኝ ። የተበታተነውን ክታብ በእጄ እንደያዝኩ ወደ እናቴ በረርኩ ። ደጃችን ላይ ብቅል እያስጣጣች አገኘኋት ።



@BOOKALEM

« አንቺ እማዬ !» አልኳት ።

« ምን ሆነህ ነው ደሞ ውሃ ውስጥ እንዳደረ ባቄላ ጠፍጣፋ አፍንጫህን የነፋሀብኝ ?»

ዝም አልኳት ።

« ከማን ተጣላህ ?»

« ከማንም አልተጣላሁም ።»

«እና ምን አባክ ሆነህ ነው ታድያ የተነፋኸው ?»

« እንገቴ ላይ ያደ ረግሽልኝ ምንድን ነው ?»

« የቱ ከታቡ ?»

« አዎ !»

« ከታብ ነዋ የኔ ልጅ ።»

« ከታብ ምንድን ነው ?»

« የቡዳ መድኃኒት !»

የተፈታውን አሳየኋት ። ደነገጠች ።

« ቱ ! ቱ ! ቱ ! ማነው የፈታበህ የኔ ልጅ ? አንተው ራስህ ከሆንክ የፈታኸው ይቅር በለኝ እያልክ ተንበርከከህ ፀልይ ጭንቅሎ ! ያለዚያ መሞትህ ነው ። ጉድ ! ጉድ ! ጉድ !...ጉድ ሳይሠማ መስከረም አይጠባም አሉ ። በል እንገትህን ደፍተህ ፀልይ !»

« አልፀልይም ።»

« ካልፀለይክ እንደ ዶሮህ ትፈነገላታለህ !»

« ማነው የሚፈነግለኝ ? እስቲ ልብ ያለው ይፈንግለኝ ።»

ታላቅ ወንድሜና እህቴ ከቤት ውስጥ ዘለው ወጡ ። እህቴ ወረቀቱን ከእጄ ነጥቃኝ ለአካባቢው እንዲሠማ ጮክ ብላ እያነበበች ሳቀች ። ወንድሜም ተቀብሏት በራሱ ዓይኖች እያነበበ ሆዱን እስኪያመው ሳቀ ። እማዬ ግን አሁንም « ተዉ ! ተዉ ብያለሁ እናንተ ልጆች እንዳትቀሠፉ!» እያለች ታስጠነቅቀናለች ። ወንድሜና እህቴም የቡዳ መድኃኒታቸውን ካንገታቸው እያወለቁ ፈቱት ። በኔ የተጀመረው ከታብ የመፍታት አቢዮት ወንድምና እህቴን አስከተለ ። የወንድሜ የተጠቀለለ የጋዜጣ ቅዳጅ ሆነ ። የእህቴ ደሞ የኮከ ፍሬ ሳቅን ።

« ተዉ እንዳትቀሠፉ !» እማዬ አሁንም ሠግታልናለች ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ አስራ ስምንት

## የፍቅር ደብዳቤ

የቦኖ ውሃ ያለበት አጥር ግቢ ውስጥ ተሰባስቦ መፈተል ያስደስተናል ። እዛች በአሾካም ሽቦ በተከለለች ግቢ የሌለ ተረብ ፣ የማይሸረብ ተንኮል ፣ የማይደመጥ አሉባልታ የለም ። ዕኩያዎች ብቻም ሳንሆን የሚያንሱንም የሚበልጡንም እንሰበሰብበታለን ። ወሬ መስማትም ማሰማትም የፈለገ ግቡን የሚመታበት ቦታ ነው ።

ጠይሜ በክርስትና አባቱ ልጅ በመዐዛና የአስተማርያችን ልጅ በሆነው በምስከር መሃል የፍቅር ደብዳቤ ያመላልሳል ። በዚህም ምክንያት የጠይሜና የምስከር ወዳጅነት ጨምሯል ። የጠይሜ ገቢም አድጓል ። ምስከር ከሚበላው ነገር ለጠይሜ ሳያካፍል መብላት አቁሟል ።

ምስከር የሚፅፈውን የፍቅር ደብዳቤ ጠይሜ በፖስተኝነት ለመዐዛ ያደርሳል ። እሱ የፃፈላትም እሷ የምትፅፍለትም እየተሰበሰብን ይነበብልናል ። በፍቅሩ ተነድፋ እንዳበደች ፣ ልታገባው የምትፈልገውም እሱን እንደሆነ ትገልፅለታለች ። ስሙ ሲነሳ እንባዋ እንደሚመጣ በደብዳቤዋ ትነግረዋለች ። ብዙ ቀን ለሆነ ጉዳይ ገንዘብ ስለቸገራት አስር ብር ፈልጎ እንዲልክላት ጠይቃዋለች ። እሱም ብዙ አስር ብሮችን ከእናቱ እየሠረቀ ልኮላታል ።

መዐዛ ከቤት መውጣት ስለማይፈቀድላት በቅርቡ በአካል ሊገናኙ እንደማይችሉ በደብዳቤዋ ነግራዋለች ። አንድ የሆነ ቀን ግን ሠበብ ፈልጋ ያለበት ድረስ እንደምትመጣ አሳውቃዋለች ። ያቺን ቀን መናፈቁን የጉጉቱን መጠን ጨምሮ ገልፆላታል ። ማስቲካ ፣ ከረሜላ ፣ የፀጉር ማስያዣ እየገዛ ልኮላታል ። በየምሽቱ በሕልሙ ሲያያት እንደሚያድር ነግሯታል ።

፣ በፖስተኛው በጠይሜ በኩል መዐዛና ምስከር በርካታ የፍቅር ደብዳቤዎችን ተለዋውጠዋል ። የእያንዳንዳችን ልብ በፍቅር እስኪነደፍ ድረስ የፍቅር ደብዳቤዎቻቸው ተነበውልናል ። በግጥም፣ በስድ ፅሁፍ የተፃፉላትን ደብዳቤዎች ሃሳብ አድምጠናል ። የተፃፉላትን ጥቅሶች ፣ የተሳሉላትን ስዕሎች ፣ የተላኩላትን ፖስት ካርዶች ተመልከተናል ። ተመሳሳይ ስዕሎችን ለመንደፍ ደብተራችንን ገነጣጥለናል ። ደብተራችንን በመገንጠላችን በአስተማሪዎቻችንም በወላጆቻችንም ተገርፈናል። የሁለቱ ፍቅር በወረቀት ላይ ገነነ ። በአካል ሳይተያዩ እንደምታፈቅረው ቀድማ በገለፀችለት ደብዳቤ መሠረት ፍቅረኛሞች ሆነዋል ። እኛም ባልና ሚስትነታቸውን አረጋግጠንላቸዋል ።

ጠይሜ ከአባቱ ጋር ወደ ጅጅጋ አክስቱን ለመጠየቅ ሄደ ። ከመሄዱ በፊት ግን እስከሚመለስ ድረስ ምንም ዓይነት ደብዳቤ እንዳይልክላት ምስከርን አስጠንቅቆታል ። ሌላ ሰው ምስጢሩን እንደማያውቅ እንደነገራት ነገረው ። ተስማማ ። እሱ ሳይመጣ ምንም ዓይነት ደብዳቤ እንደማይልክላት ቃል ገባለት ።



@BOOKALEM

በሦስተኛው ቀን ምስከር አልቻለም ። በየቀኑ ይሰዋወጡ የነበረው ደብዳቤ ሲቆርብኝ ማግስ ማስቲካና አሰራ አምስት ሳንቲም ሠጥቶ ደብዳቤውን እንዳደርስላት ላከኝ ። ማስቲካዬን እያኘኩ፣ አልፎ አልፎ እንደ ፊኛ እየነፋሁ እነ መዐዛ ቤት ደረስኩ ። ወንድሟና እሷ ከወላጆቻቸው ጋር ተቀምጠው ምግብ ይበላሉ ። በኩራት ጀነን ብዬ ዓይኖቼን ከምግቡ ላይ ሳልነቅል ደብዳቤውን ወላጆቿ ፊት ሠጠኋት ። ተንቀጠቀጠች ።

« የምን ደብዳቤ ነው ያመጣኸው ጭንቅሎ ?» ሲል ጠየቀኝ ወንድሟ ጉልቻ የሚያክል ጉርሻ ጠቅልሎ የያዘ መዳፉን ወደ አፉ እያንጣጠረ ።

« ምስከር ልኮኝ ነው ።»

« የቱ ምስከር ?»

« የጋሼ ልጅ ።»

« የዚያ የአስተማሪው ልጅ ?»

« አዎ !»

« ምን ብሎ ፃፈልሽ እስቲ እናንብበው ።» አለና ወንድምየው ደብዳቤውን መንጭቋት ማንበብ ሲጀምር እናትየው ሊያጎርሱኝ የጠቀለሉትን እንጀራ በምስር ወጥ ፊቴ ላይ መረጉት ። በርበሬው ዓይኔን አቃጥሎኝ ጮኽኩ ።

አባትየው በሚስታቸው ድርጊት ተናደዱና « ምነው ሆዴ ! ይኼ የእግዜር እንስሳ ምን አረገሽና ነው ዓይኑን የምታጠፊው ?» አሏቸው ሚስታቸውን ።

« ...መዐዚ የኔ ፍቅር ለዘላለም እወድሻለሁ እሺ ። ጠይሟ ወደ ጅጅጋ ከሄደ ጀምሮ ላገኝሽ ባለመቻሌ ጭንቅሎን ላከኩት ። የፃፍሽልኝን የፍቅር ደብዳቤዎች ሁሉ በክብር አስቀምጫቸዋለሁ። የኔም ደብዳቤዎች አንቺ ዘንድ በክብር እንደሚቀመጡ ተስፋ አደርጋለሁ። መቼ በአካል እንደማገኝሽ ግን ጨንቆኛል ። እወድሻለሁ እሺ !»

ወንድምየው በጥፊ አጮላት ። በዝብጫ ቀረቀረላት ። አባትየው በከዘራቸው አቀመሷት። ደብዳቤዎቹን በሙሉ እንድትሠጠው ወንድሟ ሲጠይቃት የምታውቀው ታሪክ እንደሌለ ተናገረች ። « ዋሽተሻል !» ተብላ ተቀጠቀጠች ። እኔም የማውቀውን ተናገርኩ ። ያደረገችውን የፀጉር ማስያዣ የገዛላት ምስከር መሆኑን ፣ ገንዘብም ጠይቃው ብዙ ቀን እንደላከላት ፣ ፖስት ካርዶችና ስዕሎች ሁል ጊዜ እንደሚልክላት ፣ አመላላሹም ጠይሟ እንደሆነ አሳበቅኩ ። የማውቀውን ከደበቅኩ መቀጥቀጤ ስለማይቀር ዝክዝክ አድርጌ ተናገርኩ ። ስታለቅስ ብታሳዝነኝም እራሴን ነፃ ለማውጣት ግን ከመናገር የተሻለ አማራጭ አልነበረኝም ።

ጮኸች ። ውሽታምነቴን ተናገረች ። የፀጉር ማስያዣውን ጠይሟ እንደሠጣት አመነች ። « ስለ ምስከርና ስላወራሁት ነገር ግን ምንም አላውቅም !» አለች ። ውሽታምነቴን ለማጋነን አፈን



@BOOKALEM

ያዘኩ ። የወንድሟ እጅ በሌላ ጥፊ ፊቷ ላይ አረፈ ። እንባዋን እያዘራች እነ ምስከር ወዳሉበት ቦታ ከቤተሰቦቿ ጋር ተያይዘን ሄድን ። ምስከር ገና ሲያየን ፈረጠጠ ።

የመዐዛ ወንድም እንዳይመታው ለመነውና ኪሱ ውስጥ የጎሠጎሳቸውን ደብዳቤዎች በሙሉ አስረከበው ። በደብዳቤው ቅደም ተከተል መሠረት የመጀመርያ ጠያቂዋ እሷ ነበረች ። እናትና አባቷ ባያነቡትም ደብዳቤውን አንድ በአንድ አገላብጠው ተመለከቱት ። ወንድምየው ፅሁፉን ከደብተሯ ጋር አመሳክሮ የሷ እጅ ፅሁፍ አለመሆኑን አረጋገጠ ። የዚህ ሁሉ ተንኮል ጠንሳሽ ጠይሜ ነበር ። ለምስከር ደብዳቤዎች እራሱ እንደ መዐዛ እየሆነ መልስ እየፃፈ ገንዘቡን ሲበላበት የሠነበተው ጠይሜ ሆኖ ተገኘ ። እኛን ጓደኞቹን ሳይቀር ሲያጃጅለን ከረመ ።

***

« የኮነ ሰው ደብዳቤ ፅፎ ቢሠድብህ ፣ ቢንቅህ ምን ታደርገዋለህ ? » አለችኝ አክሮባቲስቷ ብዙነሽ

« ማንን እኔን ?»

« አዎ ! አንተን ።»

« ኧረ እናቱን ! በቦክስ እገባለታለኋ !»

« ጊዮርጊስን በል እስቲ !»

የዘረጋችልኝ መዳፏ ላይ መስቀል ስዬ ከመማሌ የቀኝ እግሯ አፍንጫዬ ላይ አረፈ ። ዞረብኝ። እንዳልወድቅ ኮሌታዬን እንቃ በጥፊ ደጋግማ ወለወለችኝ ። አስተኝታኝ ወገረችኝ ። ሆዴ ላይ ተቀምጣ በግራ እጇ አፌን እንዳልጮህባት አፍና ጭኔን በቁንጥጫ መዘለገችኝ ። አጥወለወለኝ ።

የሠጠኋትን ደብዳቤ አነበብኩት ። ሙሉ ለሙሉ በብልግና ቃላት ታጅቧል ። « አንቺን ብሎ ካራቲስት ። ልብ ካለሽ ከኔ ጋር እንደባደብ ። መሬት ላይ አንጥፌ እግሬን ነው የምጠርግብሽ። በአንድ ምት ብቻ ያለ ምላጭ ልብስሽን ቀዳድጄ እራቁትሽን ላስሮጥሽ የምችለው ጀግናው ጭንቅሎ ነኝ ከፊትሽ የቆምኩት ። ቀና ብለሽ ብታዩኝ አንበርክኬ አገርፍሻለሁ ።» ይላል የደብዳቤው ሃሳብ ። ሌሎችም ፀያፍ ስድቦችም አሉት ።

ስድብ የሞላውን ደብዳቤ በራሴ ስም እንዳዘጋጀሁት ተደርጎ ተፅፏል ። ሙሉ ስሜና ወልጋዳ ጭረት ፊርማ መሆኑ መሠለኝ ከበስተመጨረሻው ሠፍሯል ። ተናደድኩ ። ጠይሜ ወንድሙ ለብዙነሽ የፃፈው የፍቅር ደብዳቤ እንደሆነ ፣ ከሷ ጋር ስለተጣላ እንድሠጥለትና ጠብቄ መልሱን እንዳመጣለት አዲስ ብይ ሠጥቶ ላከኝ ። ጠብቄ ያመጣሁለት መልስ ግን በቆዳዬ እንጂ በወረቀት የተፃፈ አልነበረም ።

***



@BOOKALEM

ጠይሜ ከአባቱ ሳጥን ውስጥ አንድ የተደበቀ ደብዳቤ ሠረቀ ። ጡረታ የወጣውና የአማርኛ አስተማርያችን የነበረው የጋሽ ሙላቱ ደብዳቤ ነበር ። ደብዳቤው ለጋሼ የሚሠጠው ቅዳሜ ጠዋት እንደኾነ አባቱ ሲያወሩ ሠምቷል ። የጋሼ ሚስት ስለ ደብዳቤው ምስጢር ታውቃለች ። በምስጢር ጋሽ በቂ ጋ እንዲቀመጥ የተስማማችውም እሷው ነበረች ።

ደብዳቤው የጋሼ ሚስት ለጋሼ የፃፈችለት አሪፍ የፍቅር ደብዳቤ እንደኾነ ጠይሜ ነግሮኛል። ጋሼ ቤት ስንደርስ ጋሼ ምሳውን እየበላ አገኘነው ። ስለመጣንበት ጉዳይ ሲጠይቀን በስሙ የተፃፈለትን ደብዳቤ ወድቆ ስላገኘነው ልንሠጠው እንደመጣን የውሸታችንን ነገርነው ። አመስግኖ ተቀበለንና ሃምሳ ሳንቲምና እንጀራ የያዘውን ትሪ ገፋልን ። እንደራበው ውሻ እየተስገበገብን ተሻምተን ጥርግ አድርገን በላንለት ። በአንድ ብርጭቆ ተቀባብለን ውሃችንን ጠጣን ።

ጋሼ ደብዳቤውን በትኩረት ሲያነብ ቆየና ድንገት « ኡ ! ኡ ! ኡ ! እናቴ ! እናቴ !» እያለ ማልቀስ ጀመረ ። ትከሻው ላይ ጣል አድርጎት የነበረውን ጋቢ ወደ መሬት ወረወረው ። ደነገጥኩ። ጠይሜ « እንዲህ ነኝ እኛ ! ብድሩን የማይመልስ ወንድ አይወለድ አላልኩኝም ያኔ ?» አለና ከትከት ብሎ እየሳቀ ወጥቶ ሮጠ ። ጋሼ ጠይሜ ያለውን አልሠማውም ። ጠይሜን ተከተልኩት ። እያለከለከ በደረቱ ሳር ላይ ተዘረረና ያደረገውን ነገረኝ ።

አራተኛ ክፍል እያለ የቤት ሥራ ስላልሠራ ሠንበር በሠንበር እስኪኾን ገርፎት ነበር ። ያቺን ቂሙን የሚወጣበትን መንገድ ሲፈልግ እናቱ መሞታቸውን የሚያረዳውን ደብዳቤ አገኘው ። ከዛ እነ ጋሽ በቂ ቅዳሜ ሌሊት ከሚነግሩት ሲያለቅስ እያየው ሊስቅ ወስኖ እንደዚያ እንዳደረገ ሲነግረኝ ደነገጥኩ ። እቤት ምን እባል ይሆን ?

***

የስድተኛ «ቢ» ክፍል ተማሪዎች ሆነን ነበር ጠምቤ የመጀመርያ የፍቅር ደብዳቤውን ለቆንጅዬዋ የክፍላችን ልጅ የፃፈላት። ትዝታ ጌታቸው የምትለብሰው ልብስ ሁሉ («ታይት» ም ብትለብስ) የሚንቧለልባት ቀጫጫ ትሁን እንጂ ታምራለች ። ፀጉሯ በተፈጥሮው ቡናማና ረጅም ነው ። ስትስቅ እንባዋን ታንጠባጥባለች ። የቀልድ መሳቅ አይሆንላትም ። ሳቋ ሁሌም እውነት አለው ። በዚህ ላይ ጨዋታ ታውቃለች ። ከሴት ወንዱ ተስማምታና ተግባብታ መዋል ትችልበታለች ። ከሴቶቹ ጋር ገመድ ዘለላ ፣ ሰኞ ማክሰኞ ተጫውታ ፣ በጠጠር ቅልልቦሽ እብዳ ስትፎርሽ ወደኛ መጥታ ለአንዱ ቡድን ተመርጣ እግር ኳስ ትጫወታለች ።

ከትዝታ ጋር ኳስ መጫወት የማያስደስተው የክፍላችን ወንድ የለም ። የሚገርመው ትዝታ ኳስ የመጫወት ፍላጎት እንጂ የኳስ አጨዋወት ጥበብ አልተቸራትም ። ላስቲክ አድቦልቡላ ፣ በክር ጠቅልላ ፣ በቁርጥራጭ ጨርቆች ለባብዳ በቄንጥ የምትሠፋልን የሚነጥር የጨርቅ ኳስ ግን ልዩ ነው ። እንኳንስ አብዶ ሠራርታ ፣ ሸዋውዳ ፣ አጣጥፋ ጎል ልታስገባ ይቅርና ራሷ ለመምታት ተንደርድራ ኳሱን ሥታ መሬት የምትጠርግ አካፋ እግር ነች ። የቀኝ እግሯ አውራ ጣት መፈንቀል መብቀሉ ስልተ ብሎት ጥፍሯን ነስቷታል ። በምትኩ ወፍራም ስጋነቱ ወይም ቆዳነቱ ያልለየ ነገር በጥፍሯ ግዛት ተኝቷል ። በጨዋታ መሃከልም ቢሆን ወደ'ሷ የመጣን ኳስ ድንገት ኳሱ



@BOOKALEM

እራሱ ደርሶ ካልመታት በስተቀር በብቃት መልሳው አታውቅም ። ለመምታት እግሯን ስታነሳው ኳሱ በፍጥነት በሎጪው አልፏት ይሄዳል ። « ወሰደች !» እንላታለን ያኔ ፤ ትስቃለች ።

ማንም ወንድ እንኳን ሪጎሬና በቅብብሎሽ ግብ አካባቢ ደርሶ ወይ ለበረኛ ካስቀለበ ወይ ከሳተ ከየአቅጣጫው የስድብ መዐት ይወርድበታል ። « ሁለት ግራ እግር ! ጎሉን እናንቋቅልህ! ጎሉን ሳታይ ትመታለህ እንዴ ? ዓይንህ ከሸቀለ ለምን እጉሊ መነፅር አርገህ አትጫወትም ?» የማይዘንብበት የስድብ ዓይነት የለም ። ትዝታ ስትሆን ግን ጥፋቷ በሳቅ ይቀየርላታል ። በረኛና ተከላካይ ባሉበት ቀርቶ በረኛ የሌለበት ባዶ ጎል አግኝታ ብትስት ለስህተቷ የማይስቁላት ጥርሶች የማያገጡላት ድዶች አይገኙም ። ወላቃ ፣ ሽራፋ ፣ ድርብ ፣ ብልዝ ፣ ገጣጣ ጥርሶች ሁሉ ይስቁላታል ።

ጨዋታ ከመጀመራችን በፊት ስንቦዳደን ለመመካከር እንተቃቀፋለን ። ብዙ ጊዜ እኔና ትዙ ተቧዳኝ ነን ። እንደተቃቀፍን ወደ ቡድን አባቶች እንሄዳለን ። መለያ ምልክቶቻችንን ለቡድን አባቶቹ እንነግርና የሚመርጡትን ይወስዳሉ ። ከቡድን አባቶች አንዱ ጠምቤ ከሆነ ዘዴ ፈልጎ ትዝታን ይወስዳታል ። ለምሳሌ « ከፓፓያና ከኮከ ?» ብለን ስናስመርጥ « ኮከን » ጠርቶ « ኮከ» የኔ መለያ በመሆኑ ወደ ቡድኑ ልቀላቀል መንገድ ስጀምር « ቸኩዬ ፣ ፓፓያ ለማለት ፈልጌ ነው» ብሎ በእፍርት ይጠቀልላታል ።

የሆነ ቀን ታድያ የአማርኛ ደብተሯን ተዋሠና የፃፈውን ደብዳቤ ጨምሮ « ለብቻሽ ስትሆኚ አንብቢው !» ብሎ ሠጣት ። መልሷን መልሳ በደብተሯ ውስጥ እንድትሠጠው ጠየቃት ። ጠዋት ወደ ክፍል ከመግባታችን በፊት የሠጣትን ደብዳቤ ቤቷ እስከትደርስ አላስችል ብሏት በሒሳብ ከፍለ ጊዜ ከፍታ ማንበብ ጀመረች ።

« ማዳመጥ ይሻላል ወይስ ሌላ ወረቀት ማንበብ ?» አለቻት አስተማሪያችን በትዝታ አለማዳመጥ በሽቃ ።

« አያነበብኩ አይደለም ። ስታስረጂ የምጠቀምበት የማስቢያ ወረቀት እያወጣሁ ነው ።»

« ጎበዝ ልጅ ! በይ እሺ አሁን ምንም ዓይነት ወረቀት አያስፈልግም ወደ ቦርሳሽ አስገቢ ።»

ጠዋት ለጠምቤ መልስ መጣለት ። እንዳስጠነቀቃት በአማርኛ ደብተሯ ውስጥ የመልስ ደብዳቤዋን አቀበለችው ። ደብዳቤዋን ኪሱ ከተተና አመስግኖ ደብተሯን መለሠላት ። የወደቤት መለቀቂያዋን ደወል መናፈቅ የሁለታችን ልቦች ፍላጎት ሆነ ። የጠምቤን ደብዳቤ መልስ ፍጥነት ሰመለከት እኔም ለትበልጪ ማታ ፅፌ ጠዋት እንደምሠጣት ነገርኩት ። ሰዓቱ አልሄድ ሲለን « ሽንት ቤትና ውሃ » ብለን አስፈቅደን ወጣን ። ደብዳቤውን ረጃጅሙ ሠንበሌጥ ውስጥ ተደብቀን ከፈትነው ። ጠምቤ ማዳመጥ ካልሆነ ማንበብ እጅግም ስለሾኑች በጀርባዋ ተንጋልላ ትዝታን ማሰብ ጀመረች ፤ እኔ ደሞ ማንበብ ።

« ሰማ አንተ ! ጠምቤ ነህ ጥምቤ ? ደፋር ነህ እሺ ። ለመኾኑ ከመሬት ከፍ ሳትል የምን አባከ ፍቅር ነው የሚይዝህ ? ኤሌትሪክ ይዞ ድፍት ያርግህ እሺ ! በዚህ ዕድሜህ ትምህርትህን ማፍቀር



@BOOKALEM

ሲገባህ 'ትዙ አፍቅሬሻለሁ ! ያላንቺ መኖር አልችልም' ስትል አታፍርም ? ለመኾኑ 'ያላንቺ መኖር አልችልም' የምትለው እስከ ዛሬ ከማን እባክ ጋር ነበር የምትኖረው ? ባለጌ ! ሙታንቲህን አስተካክለህ መልበስ ሳትጀምር ፣ የገላ ጭቅቅትህን ማፅዳት ሳትለምድ ሴላ ገላ ሲያምርህ ቅር አይልህም ?

« ስማ ጥምቤ የአንድ ከፍል ተማሪዎች መሆን ማለት የእህትነትና የወንድምነትን እንጂ የፆታ ፍቅርን አይጋብዝም ። ደርሶ ቆለጥህ ሳይጠነክር ‹ፍቅር ያዘኝ› ማለት አያዋጣህም እሺ ። እስቲ ከሁሉም አስቀድመህ የሽንት ቤት ቀዳዳ ውስጥ አነጣጥረህ መሽናት ልመድ ። ...»

« እንዴ ! አንተ ጭንቅሎ የተፃፈውን ወይስ ፈጥረህ ነው እያነበብክልኝ ያለኸው ?» አለኝ ደብዳቤውን አንብቤ ሳልጨርስ ።

« ኧረ የተፃፈውን ነው የማነብልህ ። ይኸው ካላመንከኝ ።» ፅሁፉን አዙሬ አሳየሁት ።

« እገድላታለሁ !» አለ ጭኑን በገዛ ቡጢው እየተመተመ ።

« ማንን ?»

« ትዝታን !»

« ለምን ?»

« ለምን ትለኛለህ እንዴ ! ቅቤ የቀባችኝ መሠለህ ? በስድብ እኮ ነው የሞለጨችኝ ። ሲድባኝማ ዝም አልላትም ፤ ማርያምን እገድላታለሁ !»

እንባዬ መጣ ። የምወዳት ትበልጨን ሆኖ ሳለ የትዝታ የመገደል ዛቻ ለምን እንባ እንዳሰቀረረኝ እንጃ ። « እሺ ጨርስህ አንብብልኝና ከዚህ ቦታ እንሂድ ።»

« ... እና አያ ጥምቤ ከዛሬ ጀምሮ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ እንዳታነሳ ። ሌላው ቀርቶ በሙሉ ዓይንህ ትኩር ብሎ መመልከት ተከልክለሃል ። ይልቅ የሌሎች እጃቢ ከምትሆን በርትተህ አጥናና እንደ ጓደኞችህ አንደኛ ውጣ ። እምቢ ብለህ በማስቸገርህ የምትቀጥል ከሆነ እኔ ስናፍቅሽ አይደለሁም እስር ቤት ወርውሬ አርባ ባላስገርፍህ ፣ ከትምህርት ቤት አሰባርሬ ከጓደኞችህ ሥር ባላስቀርህ ። ተጠንቀቅ !»

ሁለታችንም ደነገጥን ። ደብዳቤውን የፃፉት ፖሊሷ እናቷ ናቸው ። ጠምቤ ወደ ከፍል ተመልሶ መግባት አፈረ ። የትዝታን ዓይኖች ማየት አልደፈረም ። ደብተሩን እንዳመጣለት ላከኝ። ከፍል ገብቼ ለአስተማሪያችን ጠምቤን የወሰፋት ትል በአፏ እየመጣ ስላስቸገራት ወደ ቤቷ እንድትሄድ እንዲፈቅድላት ጠየቅኩት ። ፊቱን ጨምድዶ ምራቁን እየተፋ « መቼም እንዳይመጣ ንገረው ። ወደ ሰባተኛ ከፍል አልፏል !» ብሎ ሸኘኝ ። በፈጠራ ወስፋት ምክንያት ገና በሚያዝያ ከከፍል ከፍል ማዛወሩን ያረጋገጠው ተማሪ ጠምቤ ሆነ ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

## ርችት

ግንቦት ሃያ አምስት ቀን አስራ ዘጠኝ ሰማንያ ሦስት ዓመተ ምህረት ሐረር ከተማ በኢህአዴግ ሠራዊት ተያዘች ። ሰሞኑን በመንደራችን እንደ ፈንዲሻ ሲንጣጣ የከረመው ጥይት ሌላ ነበር ። ጠዋት ጠዋት በተለያዩ የተቃውሞ ሰልፎች ስትናጥ የምትውለው ከተማችን እፎይ የምትለው ተሲያት ሰዎቿ በግራ ከንዶቻቸው ትራስ ደገፍ ብለው ፣ በቀኝ ጉንጫቸው የጫት ተርዚና ሲወጥሩላት ነው ። ጉንጫቸው ውስጥ እርጥብ የጫት ተራራ አኝከው ሲገነቡ ።« መጣሁ መጣሁ!» እያለ በሕዝብ ልብ ውስጥ ሽብር የቀበረውን የወያኔ ሠራዊት የሚቃወም ሰልፍ የከተማዋ መገለጫ ከሆነ አስር ያከል ቀናት አልፈዋል ።

በተለይ ከተሸሸጉበት የራስ ሆቴል መኝታ ክፍል ተይዘው የተገደሉትና በየመንገዱ የተጣሉት የወያኔ ባለሥልጣናት ሬሳ እንቅልፍ ከነሳኝ ቆየ ፡፡ በትምህርት ቤታችን በራፍ ሬሳቸውን በዋዝ መኪና መሬት ለመሬት እየጎተቱ ፣ እንደ ሠርግ በመኪና ጡሩንባ አጅበው ሲያልፉ የደነገጥኩትን ድንጋጤ ዛሬም ሳስታውሰው ያስበረግገኛል ፡፡ አስፋልቱ ላይ ደማቸው ጥቁር መስመር እየሰራ ማየት ይከብዳል ፡፡ ቆዳቸው እየተፋቀ ፣ ስጋቸው እየተጋጠ ... ውይ ይዘገንናል ፡፡ ግን ምን ዓይነት ጭካኔ ነው ለልጅ ሬሳ ማሳየት ?

« ጢ ! ዲ ! ጓ !» ባለ ቁጥር ጎንበስ ማለት አብዝቻለሁ ። በተለይ ከወንድሜ በቀር ወጣቱ ጠቅላላ ጠብ መንጃ መታጠቁ ቢያስደስተኝም ለቀልድ ሲተኳኮሱ የተገዳደሉትን የምንዳዩ ንና ከፍ ያለውን ሞት መንደራችን ካስተናገደች በኋላ ፍርሀቴ ጨምሯል ። « ከማርያም ጣቱ በግማሽ በምታንሠው የጥይት ፍሬ በአንዲ አይደለም በአስሩ ብመታም አልሞትም !» እያልኩ ሰፎክር የነበርኩት ልጅ በተግባር እነ ምንዳዬን እየሁና ሠከንኩ ። ከኔ በዕድሜም በጡንቻም የሚበልጡትን ጎረምሶች አፈር አስለብሳ ፣ ድንጋይ አንተርሳ አስፈራራችኝ ። ምንዳዬ በቀኝና በግራ ፈርጣማ ክንዶቹ ላይ ከነተነቀሳቸው የኮብራና የሳንጃ ምስል ጊዮርጊስ ጓሮ ተቀበረ ። መቃብሩ ላይ በቁልቋል ግንጣይ ስሙ ተፅፎ ተተከለ ። የምንዳዬ ሀውልት እምነ በረድ አይደ ለም ። ሀውልቱ ሕይወት አለው ። እሱን እየበላ የሚወፍር ፣ እሱን እየመጠመጠ ሕልውናውን የሚያረጋግጥ ሕያው የቁልቋል ሀውልት ።

ኢህአዴግ ሐረርን ከመቆጣጠሩ ሁለትና ሦስት ቀናት በፊት በርካታ የጦር ግምጃ ቤቶች በጠባቂዎቻቸውና በነዋሪው ተዘርፈዋል ። አብዛኛው ሰው ጠብ መንጃ ፣ ጥይት ፣ ቦንብና ፈንጂ ሲዘርፍ እንዳሻው ግን ማካሮኒ ፣ ረጃጅሙን ፓስታ ፣ ሩዝ ፣ ደቂቃ (ፉርኖ ዱቄት) ፣ ስኳር ፣ ዘይትና በርበሬ ነበር በአህያዎቹ እየጫነ ያጋዘው ።

አባቴ የዘረፋትን ታጣፊ ክላሽ በበቆሎ ቀራ ውስጥ ደብቆ ገበሬ ማኅበር ወስዶ ሸጠና



@BOOKALEM

ቀይዋን ጊደር ገዛልኝ ። ስሟንም « ምስጢሬ» አላት ። የሚገርመው ነገር የሠፈራችን ወዘደሮች ሕዝቡ ሲዘርፍ ተባብረው አልዘረፉም ። የዘራፊዎችን ድርሻ ግን በገንዘብ እየተሸከሙ በየቤቱ ያደርሱ ነበር ። ጥቂት ነገር ዘርፈው የብዙ ብር ጌታ መሆን ሲችሉ ብዙ ነገር ተሸክመው ጥቂት ብር ሲቀበሉ ከርመዋል ።

እንዳሻው በዕድሜው በሰል ያለ ሲሆን አቻ አብሮ አደግ ጓደኛ የለውም ። በኢትዮ ሶማሊያ ጦርነት ጊዜ ከፊዲስ ከተማ ከእናቱ ጋር ተማርኮ ሄዶ ሶማሊያ እስር ቤቶች ውስጥ ያደገ ጎልማሳ ነው ። እናቱን በሶማሊያ ምድር ቀብሮ የተመለሰ ምስኪን ። ከአማርኛ ይልቅ ለሶማሊኛ ያደላ ቅላጼ አለው ሲናገር ። ጋራ ላይ በሚገኘው የአያቶቹ ግቢ ውስጥ የራሱን ጎጆ ቀልሶ ይኖራል። ከዚያው ከሶማሊያ አብራው የመጣችን ሴት አግብቷል ። ምርኮኛ ሳለ ያለፈውን ወርቃማ የወጣትነት ዘመን ለማካካስ ይመስላል ሩጫው ። በዓመት በዓመት ብቻ የሚበላለጡ ሦስት ሴት ልጆች አሉት ። መዝፈንና መጨፈር ይወዳል ። ማንንም በንቀትም ሆነ በክፋት የማያይ ጭምት ፣ «ሰዎች ሁሉ የሚያጠፉት ጥፋትነቱ ሳይገባቸው ነው» ብሎ ያምናል የዋኹ እንዳሻው። ሰው ሁሉ የሚያዝንለት ፣ «ልጅነቱን መከራ ውስጥ የጨረሠ ፣ ልጅነቱን ያለ ወላጅ እንዲጨርስ የተፈረደበት ፍጥረት !» እያሉ የሚራሩለት ሙሉ ሰው ።

በጣም በሚገርም ሁኔታ አዲሱ ጦር ከተማችንን በተቆጣጠረ ሰሞን የበርካታ ሰዎች አስከሬን በየሥርቻው ወድቆ ይገኝ ነበር ። ገዳዩ ማን እንደሆነ ባይታወቅም የሞተ ግን ይገኛል ። በርካታ የከተማችን እብዶችንና ሌቦችን ያፀዳው ጥይት የተተኮሰው በአዲሱ ጦር እንደሆነ በየቤታችን ይወራል ። የሰማነውን ለልቦናችን ካልሆነ ለማንም እንዳንናገር ማስጠንቀቂያ ይሠጠናል ። ሰዎች የወደቀውን ሬሳ አንስተው ለመቅበር ፈርተዋል ። ከነ ጠይሜ ጋርም ለመገናኘት አልቻልኩም ። ምክንያቱ ደሞ « ወያኔ ልጆችን የሚበላ አውሬ ፣ በተረት ከምናውቀው ጭራቅ የበለጠ ከፉ !» ተደርጎ በአስተማሪዎቹ አስተምህሮ ውስጤ ተቀርጿል ። እንዲያውም ጨበሬያሞቹ ወታደሮች በአካል ሳላያቸው በፊት ሁለት እግር ፣ ሁለት እጅ ያላቸው ፣ እንደኔ በሰው አምሳል ተቀርፀው በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ሁሉ አይመስለኝም ነበር ።

አባቴ የትም ሲሄድ እንደ መታወቂያው የማትለየውን ሬዲዮ ጆሮው ላይ ለጥፎ ያመሻል ። ከቀኑ በአስራ አንድ ሰዓት የጀርመን ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛውን ዝግጅት ያዳምጣል ። መሽትሽት ሲልለት ደሞ የአማፅያኑን ጣቢያ ይጨመጭማል ። መሽቶ እራታችንን በልተን ሦስት ሰዓት ሲሆን አባቴ ሲጋውን እኛ ቤት መንፈሱን አሜሪካ ይልካል ወደ VOA ።

እሱ ሬዲዮ ጆሮው ላይ ለጥፎ መስማት ከጀመረ ምንም ዓይነት ወሬ አይፈልግም። ቡና እንኳን ሲቀዳ ጩርጫሬው እንዳይረብሸው ተብሎ የጀበናው ጡት ስኒው ውስጥ ይገባል። እነኚህን ሁሉ ጣቢያዎች አዳምጦ ወደ ኢትዮጵያ ሬዲዮ ሲመለስ ሬዲዮዋን ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጣታል ። የዚያኔ የጋራችን ትሆናለች ። አባቴ እያወራ ፣ እየተሳደበ ከሚያዳምጣቸው ጣቢያዎች የመጀመሪያው አንድ ለእናቱ የሆነውን የኢትዮጵያ ሬዲዮ ነው ።

የወያኔ ጦር ከተማዋን የተቆጣጠረ ዕለት እናቴ ኩሽና እንጀራ እየጋገረች ነበር ። የምታነደው



@BOOKALEM

የጃምቦ ቅጠል በመሆኑ ሲነድ እየተንጣጣ ጭሱ ይበዛል ። የጋመ የሚመስለው ፍም አመድ ሊሆን ስለሚችል በላይ በላዩ ማጉረስን ይጠይቃል ። ለአቅመ ረመጥነት ሳይደርስ አመድ የሚሆን ማገዶ ጃምቦ ነው ።

« ወያኔዎች ደንገን ደርሠዋል !» ስለተባለ እማዬ « ምናልባት እንጀራ በልተው የማያውቁት ወታደሮች መጋገር ሊከለክሉኝ ስለሚችሉ » ብላ ያገር እንጀራና ቂጣ ነው የምትጠፈጥፈው ። የከባድ መሣሪያ ፍንዳታ ድምፅ ብሰማም በሰማይ የሚፈጠር ነጎድጓድ እየመሠለኝ ተቸግሬያለሁ። አልፎ አልፎ ግን እቤት ውስጥ ተቀምጬ ባየር ላይ የሆነ ነገር በፍጥነት ሲምዘገዘግ ግድግዳና ጣራችን በንዝረት ይናጣል ።

የደንገጎው ውጊያ በጣም ከፍተኛ ነበር ። « በኢትዮጵያ እግር ኳስ ዕድገት ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣሉ » ተብለው ተስፋ ከተጣለባቸው ወጣቶች አንዱ የሆነውን ፊሊጶስ ሰለሞንን የበላ የጦርነት አውድ ሆኖ አልፏል ። እኚያን ኳስ ለመምታትም ለመሮጥም ፈጣን የነበሩ እግሮች ከባድ መሣርያ ጎመዳቸው ። ፊሊጶስ በቅፅበት ያፈረሱትን መልሠው መገንባት በማይችሉ ሰዎች በተተኮሰ ከባድ መሣርያ ተመትቶ ግማሽ ሰው ሆነ ። ከወገብ በላይ እንጂ ከወገብ በታች አካል የሌለው አዲስ ፍጥረት ። ከመሠቃየት እንዲገላገል አብረውት በውጊያ ተሠልፈው የነበሩት አባቱ ሻምበል ባሻ ሰለሞን ገብረ ኢየሱስ ዓይኖቻቸውን ጨፍነው «ቻው! ልጄ ...ልጄ እጄ እንጂ ልቤ መቼም አይጨክንብህም !» ብለው እያለቀሱ ጨረሱት ። በቀጣይዋ ጥይት የራሳቸውን ጭንቅላት በራሳቸው ጣት በተሳበ ቃታ አፈንድተው የልጃቸው ሬሳ ላይ ወደቁ ።

እማዬና እኔ በመሶብ የተሞላውን እንጀራ ለሁለት ይዘን ከኩሽናው ወደ ቤት እያስገባን ሳለ ቀውጢ የሆነ ተኩስ ቤታችን አካባቢ ተጀመረ ። ሁለታችንም መሶቡን ጥለን ወደ ቤት ገባን። አባቴ ከጡረታ በፊት የነበረው ወኔው ተቀስቅሶበት ፋቲኩን ለብሶ መሣርያውን አቀባብሎ በተጠንቀቅ ቆሟል ። እናቴ በሩን ከውስጥ ቀርቅራ ፣ እግሩ ላይ ወድቃ ፋቲኩንና ከስክሱን አስወልቃ የከት ልብሱን አለበሠችው ። አባቴ ላይ አይቼበት የማላውቀውን የተስፋ መቁረጥ ገፅታ አነበብኩበት። ፋቲኩን አውልቆ የከቱን እንደለበሠ ወኔው ብቻ ሳይሆን ልቡም ፈቱም አረጀ ። ለወትሮው ያፈካው የነበረው የከት ልብሱ ሠብብ ጠብቆ እርጅናውን አሳበቀበት ። ሞጭሙጬው አንባ ያቀረሩ ዓይኖቹንና የተኮማተረ የግንባር ቆዳውን አጎላበት ።

ልብሱን ጠላሁት ። አባቴን ሲያስጨንቀው የአባቴ ጭንቀት አስጨነቀኝ ። መሳይ ፣ ወንድሜና እኔ ዓይኖቻችንን ከማቁለጭለጭ ባለፈ ምንም ማድረግ አልቻልንም ። ግን ቆጨኝ ። ለአባቴ ምንም ማድረግ አለመቻሌ አናደደኝ ። በኔ ልክ የተሠራች ወያኔ ብትኖር አንገቷን አንቄ ለአባዬ እንደፈለገ እንዲያደርጋት አቀብለው ነበር ። ወንድሜ ለጎረምሳ ጉንጭ የሚበረቱት እጆቹ ተንቀጠቀጡበት ። አልጋ ሥር ተደበቀ ። በተለይ ጫት የቃመ ቀን እንዲህ ያደርገዋል ። ወኔውን ይሸናዋል ።

ቤታችን በአዲስ እየተሠራ ስለነበር ለመስኮት የሚሆን ጣውላ እስከሚገኝ ድረስ በሳጋው ፍሬጥ እንዲቀመጥ የተወሠነበት በአባቴ ነበር ። ለነገሩ ሌባን ለመከላከል አስተማማኝ ነው።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

መጋዝ ያልያዘ ሌባ እኛ ቤት በመስኮት መግባት አይችልም ። አይሞከረውምም ። አካልና ፍጥነቱን ተማምኖ በመስኮት እየሾለከ ቤታችንን በመዝረፍ ያስቸገረን ሌባ « ሰው ጤፉ » ብላ እናቴ ስም ያወጣችለት አይጥ ብቻ ነው ። ሰው ጤፉ መልኩ ከአይጥ ፣ ጭራው ከድመት የተገጠመለት ይመስላል ። ሰው ኖረ አልኖረ ግድ አይሠጠውም ። ድመታችንም ብትሆን ከሰው ጤፉ ጋር ተስማምታ እኛን እያዘረፈችና እየዘረፈች መኖርን መርጣለች ።

በራችንን ዘግተን ተቀመጥን ። « ጥሡው የሚገቡ ከሆነ አባቴ ገድዮ እሞታለሁ እንጂ እጄን አጣጥፌ በምድረ ቅማላም አልበላም !» አለ ። ይህ ንግግሩ ከእማዬ ጋር አላግባባውም። ደርግ መሸነፉን መቀበል እንዳለበትና እንኳን እሱና « አንድ ሰውና አንድ ጥይት እስኪቀር ለእናት ሀገራችን አንድነት ወንበዴዎችን እንዋጋለን !» እያለ ወጣቱን ሲፈጅና ሲያስፈጅ የከረመው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሀገር ሙሉ ወታደር ሜዳ ላይ በትኖ እንደፈረጠጠ ተናግራ ልታሳምነው ሞከረች ። ሰድቡን እንዲያቆም አስጠነቀቀችው ። « ልጆቼን ላሳድግበት አፍህን ሰብስብልኝና አርፈህ ተቀመጥ !» አለችው ።

« ወንድ አላየሽ ! ወንድስ ማለት መንጌ ! አህ !» አባዬ ጉልበቱን እየቀጠቀጠ ቁጭቱን ገለፀ ።

በመስኮት በኩል በሳጋው ከፍተት መሀል ቁልቁል መመልከት ጀመርኩ ። ቤታችን ዳገት ላይ በመሆኑ ሁሉን ነገር ወለል አድርጎ ያሳያል ። እንዲያውም አንዳንዶች የኛን ቤት « የአግዚሀር ቤት» ነው የሚሉት ። እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ምድር ቁልቁል ሁላችንንም ስለሚያይ እኛም የፈለግነውን አቆልቁለን እንደልባችን ማየት ስለምንችል እንደ ዕድለኛ ይቆጥሩናል ።

አይገርምም ከወያኔዎቹ አንዱን የማውቀው መሠለኝ ። ረጅም ልጅ ያለው አጭር አባት። ግንባሩ ላይ በጠባሳ የተሠራ ገዳዳ መስቀልና ሁለቱም ቅንድቦቹን ከፊል ፀጉር አልባ ያደረገ ወፍራም ጠባሳ ባለቤት ። ልጁ ከኔ ጋር ይማር ነበር ። ከወራት በፊት ግን ትምህርቱን አቋርጦ የት እንደሄደ አይታወቅም ። ግርማ ገብረ መስቀል ከአፍንጫው ንፍጥ የማያጣ ፣ በንፍጥና ለሀጩ ሁሌ የሚቀጣ የከፍሌ ልጅ ። አባቱ በልዋጭነት ከተማዋን ሲያካልላት የሚውል ፣ የወታደር ልብስና ጫማዎችን በጥሩ ጥሩ ዕቃዎች ይቀይር የነበረ ፣ ዛሬ ደሞ ከጠፋበት መጣ ። የወያኔዎች መሪ ሆኖ የኖረበት ሠፈር ገባ ። ወያኔው ገብረ መስቀል በዕቃ የተሞላ ካርቶን በሚሸከምበት ትከሻው ላይ ጠብ መንጃ አንግቶ አየሁት ። የከፍሌ ልጅ ግርማስ የት ይሆን ? አሁንም አፍንጫው አልደረቀ ይሆን ? በጦርነቱ መሀል የግርምሽን አፍንጫ ማየት ናፈቀኝ።

« አባዬ ! ገብረ መስቀል !» አልኩ ደንግጬ ።

« የማነው ደሞ ገብረ መስቀል ?»

« ልዋጩ !»

« ል...ዋጩ !»

« አዎ ! ያውልህ ። ና ሳያመልጥህ እየው ።»



@BOOKALEM

ቀስ ብሎ እንገቱን አስግጎ በቀዳዳ አየው ።

« እውነትም ልዋጭ ! ...ልዋጭ ባልና ሚስት አቆራራጭ የምትሉት ለካ ወዳችሁ አይደለም ልጆቼ! ይኸዋ ኢትዮጵያን ከኤርትራ ልዋጩ ገብረ መስቀል አቆራረጣት !...እስራትን ተቀምጦ፣ ልብስና ጫማችንን አማርጦ ወስዶ እያለበሰ ወንበዴዎችን ጎትቶ አመጣብን ። ወይኔ ወንዱ ! ገና ቂም ቋጥሮ ሊያስፈጀን ይችላል ።» አለና ወደ መቀመጫው ተመለሰ።

በቀዳዳው ስመለከታቸው ወታደሮቹ መንገዱ ላይ ይርመሰመሳሉ ። እነ ኃይሌ ግቢ ተከራይቶ የሚኖረው ልብስ ነጋዴው ሐጎስ ቅጠልያ የመስከ ጃኬቱን እንደለበሰ ወጣ ። ሐጎስ ሰሞኑን ከፉኛ ታሞ ነበር ። ትግርኛ ሥለሚችል በቋንቋው ሊያዋራቸው እንደሚችል እገምታለሁ ። በእጁ ነጭ ጨርቅና ነጭ ወረቀት ይዞ ሁለቱን እጆቹን ወደ ላይ ሡቀለ ። ሦስቱ ወታደሮች መሳርያዎቻቸውን ደግነውበት ቆመው አንደኛው ተጠጋውና ወረቀቱን መነጨቀው ። ወረቀቱን እያገላበጠ ተመለከተና በሦስት ጥይት ገለበጠው ። ሐጎስ ተንገዳግዶ እጆቹን እንደሡቀለ በጀርባው ወደቀ ።

« ወይኔ ገደሉት !» አልኩ ።

«ማንን ?» አባቴ አስተኳሹ አርጎኛል መሠለኝ መልሶ ጠየቀኝ ።

« ሐጎስን !»

«ይበሉት የታባቱ ! እሱስ የገብረ መስቀል ሌላኛው ግልባጭ አለመሆኑ በምን ይታወቃል ?» አባቴ የገብረ መስቀልን በደል ቁጭት በሞተው ሐጎስ ላይ ተወጣ ።

« አንተ ልጅ...ውረድ ከመስ ኮቱ ላይ ብዬሃለሁ ! አነጣጥረው የሚያዩበት መነፅር አላቸው ። ዋ! እንዳይደፉህ !» አለችኝ እናቴ ።

እማዬ ተናግራ ሳትጨርስ መሬት ደረስኩ ።

ጨረቃዋ ፍንትው ብላ ወጥታለች ። ወጋገኑን እየተከተልኩ ከመኝታዬ እየተነሳሁ የሃጎስን ሬሳ በቀዳዳ አያለሁ ። የተጠቀጠቀውን ጨርቅ ከመስኮቱ እያነሳሁ ምስኪኑ ሐጎስ ከሞቱ በኋላ እንዴት እንደሆነ ለማወቅ በጭለማ ውስጥ እፈልገዋለሁ ። በሕልሜም በውኔም ሐጎስ እየመጣ « ጭንቅሎ ! ሰንት ቀን ብስኩትና ከረሜላ ገዝቼልህ የለ ? አንተ ግን ወያኔዎች ሲገድሉኝ እያየህ ዝም አልክ አይደል? ትዝብት ነው እሺ ትርፉ !» እያለ አስቸገረኝ ።

ለሦስት ቀናት ሬሳውን ከመንገድ ላይ የሚያነሳው ጠፋ ። ከቤቱም ወጥቶ እንደ ልቡ የሚዟዟር ሰው ማግኘት አልተቻለም ። እንደ ልቡ እየለፈለፈ ሲዞር የከረመው ዓለማየሁ ብቻ ነበር ። ሳይጠጣ ፣ ሳይሰክር ብቻውን የሚቀባጥር በቅርቡ መንደራችንን የተቀላቀለ የጎንደር እብድ ነው ። ዓለማየሁ « የጀግናው ቴዎድሮስ ልጅ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ እኔ ነኝ !» እያለ ስለሚለፈልፍ ነው ስሙ የተሠጠው ።

፩ አብዛኞዎቹ በደርግ ይመሩ የነበሩት ተሸናፊ ወታደሮች የጥይት አገልግላቸውን አውልቀው

በፌስታል እየያዙ ፣ አፈ ሙዙን ቁልቁል እየዘቀዘቁ ወደ አጋዴን አንበሳ የጦር ካምፕ እየሄዱ ጠብ መንጃዎቻቸውን አስረከቡ ። ስማቸውን እያስመዘገቡ ፣ አንገታቸውን እየደፉ ወደ ቤታቸው ተመለሱ ። በየቀኑ በቀበሌ የድምፅ ማጉያዎች ሕዝቡ በእጁ የሚገኙትን መሣርያዎች እንዲያስረክብ ይገለፃል ። የፈራ እየወሠደ ያስረክባል ። የፈራ እቤቱ ጉድጓድ ቆፍሮ የዘረፈውን ይቀብራል ። ፈሪው ዓይነቱ በዛ ።

ለምሳሌ አባቴና ጋሽ ቦጋለ ሁለቱም የጦር መሣርያ ግምጃ ቤቱ ሲዘረፍ ከዘረፉት ከላሽ በተጨማሪ ከቀበሌ « አካባቢ መጠበቂያ » ተብሎ ያለ ፈርማ የተሠጣቸው ፓፓሽ የተባለ መሣርያ ነበራቸው። አባቴ ሁለቱንም መሣርያዎች በጨርቅና ላስቲክ ጠቅልሎ በአበት የተለቀለቀ ጓዳችንን ቆፍሮ ቀበራቸው ። ይህን ያደረገበት ምክንያት « መሣርያ ላስረክብ ብዬ ተሸክሜ ስንከረፈፍ ቢደፉኝስ !» ብሎ ፈርቶ ሲሆን ጋሽ ቦጋለ ደሞ « እቤቴ ውስጥ መሣርያ ከተገኘ ይገድሉኛል !» ብለው ፈርተው ነበር ። የፍርሀታቸው መንገድ ቢለያይም ሁለቱም ፈሪዎች ናቸው ። « ደፈር በል እንጂ ! የምን መንበቅበቅ ነው !» እያለ ያሳደገኝ አባቴ በተራው ሲንበቀበቅ አየሁት ።

አሰሳ ተጀመረ ። ፀጉራቸው የተንጨባረረ ፣ የተለባበደ ...ከስጋቸው ጋር የተሠፋ ይመስል ጥብብ ጥብቅ ያለ ቁምጣ የለበሱ ፣ በተለያየ ቀለም ባለው ፕላስቲክ የተደረተ በረባሶ ያጠለቁ ፣ ወይም ሰማያዊ አንገት ልብስ አንገታቸው ላይ የጠቀለሉ ወይም ጭንቅላታቸውን የሸፈኑ ፣ ፈገግታ ከፊታቸው ላይ ተፈቅፍቆ ያለቀባቸው አስፈሪ የወያኔ ወታደሮች የጠረጠሩትና የተጠቆሙት ቤት ሳያስፈቅዱ እየገቡ ይፈትሻሉ ።

ሲያዩዋቸው የሚያስፈሩ ፣ የሚያያቸውን በጥርጣሬ የሚያዩ ፣ የሚያወሩት አማርኛ የሚያስቅ ፣«ከላ ! ወዲ ሸርሙጣ ! ወዲ ጨናዊት !» እያሉ ልጆችን የሚሳደቡት ሰዎች እኛ ቤት መጡ ። እናቴ በእጇ የያዘችው ዕቃ እስኪያመልጣት ተንቀጠቀጠች ። በቤተሰባችን ለፈሪ በሚሰጥ መግለጫ « እማዬ ተንበቀበቀች »። አባቴ እንደ ድንገት እቤት የለም ነበር ። ሳይጠይ ቋት የሚፈልጉትን ጠየቀቻቸው ። መሣርያ ደብቆ የተቀመጠ ሰው በሠፈሩ ካለ እንድትጠቁም ለኔ የፈገግታ ምንጭ በሆነው አማርኛቸው ጠየቋት ።

በጊዮርጊስ ምላ ምንም አለማወቋን ተናገረች ። እናቴ በጊዮርጊስ የማለችበት ዐቢይ ምክንያት ወያኔዎች ለጊዮርጊስ ያላቸውን ከብር ስለሰማች ነበር ። « ጦሩ ደርግን አሸንፎ ወደ ከተማችን ሲገባ በየአርሻው ውስጥ በቆሙት የወፍ ማስፈራርያ የሰው ምስሎች ፣ የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ምስሎችና ሀውልቶች ፣ እ… በሦስቱ ጢማሞች ማርክስ ፣ ሌኒንና ኢንግልስ ፎቶዎች ሁሉ ላይ ይተኩሱ ነበር ። ከኢሠፓ ቢሮ ፊት ለፊት (በነገራችን ላይ የኢሠፓ ቢሮ አንድ ግጥም ተገጥሞለት ነበር ።

« የኢሠፓ ቢሮ እንዳልተበላበት እንዳልተጠጣበት

ወያኔ መጣና ሙታንቲ አሠጣበት ፡፡») ካለው አደባባይ ላይ ሲደርሱ ግን ደነገጡ ። ጦርና ጋሻ ይዞ ፣ አንድ የፊት እግሩን በአየር ላይ ባደረገ ፣ ግርማ ሞገሱ በሚያስፈራ ፣ ወርቃማ ካባን በተጎናፀፈ መልከ መልካም ሀውልት ፈዘዙ ። ሁሉም ለመተኮስ ሳይሆን ለማማተብ ቸኮሉ ።



@BOOKALEM

ሀውልቱን ተሳለሙት ፡፡» ተሸውደዋል ፡፡ ሀውልቱ የጊዮርጊስ ሳይሆን የልዑል ራስ መኮንን ነበር ፡፡

ጊዮርጊስም አራዳ ስለሆነ እንጂ ውሽታሟ እማዬን ያሲዛት ነበር ፡፡ ደሞምኮ « ጊዮርጊስን» ብላ ማለች እንጂ « ጊዮርጊስ ይሙት !» አላለችም ፡፡ ስለዚህ በውሸት እንዲሞት ካልማለችበት ምን አስጨንቆት ያስይዛታል ?

የእትየ ቀፀላ ቤት ሲፈተሽ በርካታ የወታደር ልብስና ጫማ በማዳበርያ ተጠቅጥቆ ተገኘ ፡፡ አንደኛው ወታደር ተናደደና ሁለት ጥይት ወደ ሰማይ ሲተኩስ ተሠብስበን የነበርን ወሬ ፈላጊዎች ሁሉ በረገግን ፡፡ ሴትየዋ « ኡ ! ኡ !...እኔ ነፃ ሰው ነኝ !» አሉ ፡፡ ሲጮኹ የገደሏቸው መሠለን ፡፡ ለካንስ የሞተ አያወራምና ፡፡ ሁለቱ ወታደሮች የቤታቸውን ግድግዳ ተደግፎ የተከመረውን የወፍ ቆሎ ጨሬታ መናድ ጀመሩ ፡፡ አስራ ሦስት ጠብ መንጃዎች በወታደር ልብስ ተጠቅልለው ተገኙ ፡፡ ወታደሮቹ በጣም ተናደዱ ፡፡ ሌሎች በርካታ ጥይቶችን ወደ ሰማይ ተኮሱ ፡፡ በከፍት ጂፕ መኪና መትረየስ ጭነው መንገድ ከጀመሩ በኋላ ተመልሠው መጡና እትዬ ቀፀላንም መኪናቸው ላይ ጭነው ወሠዷቸው ፡፡

ሠፈርተኛው በሙሉ በፍተሻ መከራውን ሲጋት እንዳሻው ግን የዘረፈውን ፓስታና ማካሮኒ በነፃነት እያገነፈለ ይበላ ነበር ፡፡ ጥቆማ ሲካሄድበት እንኳን « ምግብ እንጂ መሣርያ አልዘረፈም ፡፡ እሱ ሰላማዊ ሰው ነው ፡፡ ሰው ሰውን በመሳርያ እንጂ በምግብ አይገድለውም ፤ አያጠፋውም !» ብለው ችላ አሉት ፡፡ የመንደራችን ብልሁ ዘራፊ እንዳሻው መሆኑ ተመሠከረለት፤ ሰላማዊ ሌባ ፡፡

***

ጊዮርጊስ ጋራ ላይ የነበረው የአየር መቃወሚያ ክፍለ ጦር ሲፈረጥጥ መሣርያዎቹን በየጢሻው አዝረክርኮታል ፡፡ ትልልቅ ቀለሃ ያላቸው የከባድ መሣርያ ጥይቶች በየእርሻውና በየመቃብሩ ውስጥ ይገኛሉ ፡፡ የኛ ሠፈር ሰዎች ሬሳ ለመቅበር ሄደው ሲመለሱ ከእጃቸው ቀለሃና የነብስ ይማር ንፍሮ አይጠፉም ፡፡ ጥይትና ባሩዱ ከውስጡ ወጥቶለት ቂጠ ድፍን ያልተተኮሰ ቀለሃ በየቤታችን ደጃፍ በዝቷል ፡፡ ቆራሊዮ ከሠፈራችን ሰዎች ቀለሃውን በርካሽ እየገዛ ለወርቅ ቤቶችና ለአንጥረኞች ይሸጣል ፡፡ እነርሱ ከወርቅ ጋር እየቀየጡ ለሕዝቡ በውድ ዋጋ ይቸበችቡታል ፡፡

ትናንሽ ምግብ ቤቶች ተመጋቢዎቻቸው እጃቸውን እንዲታጠቡበት ከወደ ቂጡ በስተው የቧንቧ ጫፍ ይገጥሙበታል ፡፡ መታጠብ የፈለገ እየታጠበ ይገባል ፡፡ ያልፈለገም እጁን « እፍ! እፍ !» ብሎ በትንፋሹ አጥቦ ምግቡን አስቀርቦ ይበላል ፡፡ እኛ ቤት የነበረው ቀለሃ ጥቅሙ ለየት ይላል ፡፡ ከሚካ ተገንድሶ ከመጣ ስድስት ወራት ያለፉትን የጥድ ቅርንጫፍ አዝሎ ይውላል ፤ ያድራል ፡፡ ጥዱ ላይ ከነ ፍሬው የተንደፈ ጥጥና የኮንዶም ፊኛዎች ተሠቅለውበታል ፡፡ በከረሜላ ልጣጭ የተጠቀለለ ጠጠርም በክር እየታነቀ ተንጠልጥሏል ፡፡ የቅድመ አያቴ እናት የእጅ ሥራ ፎቶ ግራፍም ፊት ለፊት እያየን ተሠቅሎበታል ፡፡ ቀለሃ በኛ ቤት የገና ዛፍ መያዣ ነው ፡፡

እነ አሚና ቤት ውስጥ ደሞ የቀለሃ ጥቅሙ ሌላ ነው ፡፡ በቤቱ ሰባት ልጆች ፤ እናት ፤ አባትና ወንድ አያታቸው ሆነው በጋራ ይኖራሉ ፡፡ ወንድ አያትየው አባባ ሙራድ ኮሚክ ሰው ናቸው ፡፡



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

እና...እነ አሚና የተቆፈረ ሽንት ቤት ስለሌላቸው የሽንት ቤታቸውን ኮታ ወከሎ የሚተውንላቸው ቀለሃቸው ነው ። ቀን ቀን ጥላ ሥር የሚውለው ቀለሃ ሲመሽ ወደ ቤት ይገባል ። መሽቶ ሲተኙ ሲሉ እንቅልፍ ባልጣለው በአንዱ የቤተሰቡ አባል ወደ ቤት ታቅፎ ይገባል ።

ወንዶቹ ቀጥታ ቆመው ይሸኑበታል ። እነ አሚና ግን ሌላ ዕቃ ውስጥ ሸንተው ወደ ቀለሃው ይገለብጡታል ። ሴቶቹ የቆመው ቀለሃ ውስጥ ለመሽናት ስለሚቸገሩ የቀድሞውን የአባትየውን ጭንቅላት ከጥይትና ረብሸኛ ድንጋይ ሲታደግ የኖረውን ወ.ፖ (ወታደር ፖሊስ) የሚል ሔልሜት (የብረት ኮፍያ) ይጠቀማሉ ። አባትየው ቀርቶ የቀጠራቸው መንግሥትም ከሥልጣን ስለተባረረ የሚሊቴሪ ፖሊስ የብረት መለዮአቸው ሔልሜቱ ጥቅም የለውም ። ለዚያም ነው ሌላ ጥቅም እንዲሠጥ መላ ተዘይዶለት የፍርሀት ምንጭ የነበረው ሔልሜት ፖፖ የሆነው ።

ጠዋት ጠዋት ታድያ ሽንት የመድፋት ኃላፊነቱ በአሚናና በታናሿ በሳድዮ ላይ ያርፋል። እንደ ሰው የቆመውን ፤ እንደ ሰው የማይተጣጠፈውን ቀለሃ ወገቡን አቅፈው ተራ በተራ የሚደፉበት ቦይ ጋ እስኪደርሱ ይወስዳሉ ። ቦዩ ጋ እስኪደርሱ ገሚሱ የቤተሰቡ ሽንት ልብሳቸውን ያበሰብሳል። ሲንቦጫቦጭ አፋቸው ውስጥ እየገባ ደጋግመው እንትፍ እንዲሉ ያደርጋቸዋል። የነ አሚና ቤት ታድያ ብዙ ጊዜ ሽንት ሽንት ይሸታል ። ምክንያቱ ደሞ በሔልሜቱ ሲሸኑ ቅርጹ ለመቀመጥ ስለማይመች እየተደፋ ፤ የተደፋው በአፈር ወለሉ እየተመጠጠ ሽታውን ለባለ አፍንጮች ስለሚያሳልፍ ነው ።

እነ አሚና ቤት ውስጥ ቀርቶ ግቢያቸው መቀመጥም ፤ መጫወትም አይቻልም ። የቀለሃው ቅርናት ለዘላለም የመተንፈሻ አካል ችግር ያጋልጣል ። እናትየው ብዙ ጊዜ አስማቸው እየተነሳባቸው ከሞት የሚተርፉትም በዚያው በቀለሃው ምክንያት ነው ። ሌላ አማራጭ ግን የላቸውም ። ሲገድላቸው እየፎከረባቸውም ይሸኑበታል ። አፍንጫቸውን በጨርቅ ሸፍነው በየምሽቱ ሌላ አፍንጫ መቁረጫ ያጠራቅሙበታል ። ሁሌም ግን የሚገርመኝ የነ አሚና ቀለሃ ሥርኪ በቤተሰቡ ሽንት መሞላቱ ነው ። ያለ እንቅልፍ ሲሸኑ ብቻ ይሆን እንዴ የሚያድሩት ? ወይስ በፉክክር እየሸኑበት?

ቀለሃን ቆርጦ ለቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስነት እንዲውል ካደረጉት ሰዎች አንዱ ፈለቀ ከንዴ ነው ። ወታደር ነበር ። የሁለት ጎረምሶችና የአንዲት ሴት ልጅ አባት ። የሚስቱን እናትም በቤተሰብነት አቅፎ ያስተዳድራል ። ከሁለቱ ጎረምሶች ጋር ዘወትር ማለዳ ወደ ጊዮርጊስ ጋራ እየወጡ በመቃብር ውስጥ አሰሳ ያካሂዳሉ ። በየጢሻው የወዳደቁ የከባድ መሳርያ ቀለሃዎችን ይፈልጋሉ ። የፈነዱም ያልፈነዱም ቢሆኑ ግድ የላቸውም ። ቀለሃን ቆርጦ የቡናና የቅመማ ቅመም ሙቀጫን የሚፈጥር ጥበብ በአባትየው እጅ አለ ። ልጆቹም የአባታቸውን ሞያ ለመቅሠም ከሥሩ አይጠፉም ። ቢሥራ ያግዙታል ። የቤተሰቡ ጉሮሮ የሚሸፈነው ቀለሃ ተቆርጦ ፤ ሙቀጫ ሆኖ ተሸጦ በሚገኘው ገንዘብ ነውና ለስንፍና እጅ አይሠጡም ።

ዘናጭ ሙቀጫን በርካሽ ዋጋ ከፈለቀ ከንዴ ቤተሰቦች ላይ ይገዙና ዘና ብለው በቀን ሦስቴ ከጎረቤት እየተጠራሩ ቡናቸውን ይጠጣሉ ። ወረት ሆኖባቸው ብዙዎች የእንጨት



@BOOKALEM

ፍልፍል ሙቀጫቸውን ፈልጠው እንድደዋል ። « ሙቀጫ አውሱኝ !» ብሎ ለጠየቃቸው ጎረቤት የብረቱን ትተው ቀን የጣለውን የእንጨት ሙቀጫ አውሠዋል ።

ታሪክ ተበላሸ ። ስመጥሩ የሙቀጫ ባለሞያ ፈለቀ ከንዴ ሁለቱን ጎረምሶች የቀለሃውን አፍና ቂጥ አሰይዞ በብረት መጋዝ ይቆርጠዋል ። ሌሎች ተቆርጠው የተሠናዱ ፣ አፋቸውን ብቻ የማስዋብ ሥራ የሚቀራቸው ሙቀጫዎች ተደርድረዋል ። እናትየው ለባሏ ቡናውን በአፍ በአፉ ታገርሠዋለች ። ለልጆቿም ብርታት ስኳር ሞቅ ያለው ሻይ ታጠጣቸዋለች ። በርና መስኮቱ ተዘግተው በከሠል ማንደጃው ላይ ያለው ፍም ከሰዎቹ ገላ ላብን ያፈልቃል። በቤቱ ውስጥ ያሉትን ቁሶች ያሞቃል።

ተቆራርጠው ዘነዘና ሊሆኑ የተዘጋጁ ድፍን ብረቶች ፣ ጥይታቸው ወደ ፊት የሚነቀልላቸው የአየር መቃወሚያ ጥይቶች ቤቱን ሞልተውታል ። ድንገት የመንጣጣት ድምፅ ተሠማ ። ቤቱ በንዝረት ተወዛወዘ ። እናትየው ትንሿን ሴት ልጇንና እናቷን ይዛ በሩን በርግዳ ከመውጣቷ ሠፈራችንን ያነቃነቀ ፣ በከተማዋ የሚገኘውን ጦር በተጠንቀቅ ያቆመ ፣ የታጠቀ ጦር በመኪና አስጭኖ ወደ አደጋው ቦታ የወሠደ ፍንዳታ ተከሠተ ። ፈሌ ከሚወዳቸው ልጆቹ ጋር በቤቱ አልተገኘም ። ኢደጅም አልወደቁም ።

በአንፃሩ ሠፈሩን ያሳዘነው የመንደርተኛው ዋይታ ብቻ አልነበረም ። « እባካችሁ ስትሮጡ ስጋ እንዳትረግጡ መሬት እያያችሁ !» የሚለው ማስጠንቀቂያ የብዙዎችን ልብ አሸነፈ ። ታታሪው ፈለቀ ከንዴና ልጆቹ ወደ ብጥስጣሽ ስጋና ስብርባሪ አጥንትነት ተለውጠዋል ። መንደርተኛው ከተት አውጆ ሌሊቱን ሙሉ እስኪነጋ ውሻ ፣ ጅብና ድመትን ከአካባቢው ሲያባርር አደረ ። ሲነጋ ወንጭፍና ወፍ ሰንጥር እየያዘን የጭልፊት ዘሮችን አሳደድን ። ጭልፊት አብዝቶ ባንዣበበት የሆነ ቁራጭ ይገኛል ። ቁንጫጭ ሰብሰብ ባለበት ከሦስቱ የየትኛው መሆኑ ያልታወቀ ብጣሽ ስጋ አለ ። እጃቸውን በፌስታል የጠቀለሉ ሰዎች « አድነን ከመዐቱ !» እያሉ እየፀለዩ ቁንጫጩን አራግፈው ያነሱታል ። በየዛፉ ፣ በየጣራው የተገኙት ብጣሾች አቅም በፈቀደ መጠን ተለቀሙ ።

ማለዳ የተጀመረው የስጋ ለቀማ እስከ ቀትር ስድስት ሰዓት ቀጠለ ። የተገኘው ስጋና አጥንት ሁሉ ተሰቃቅሞ በአንድ ሳጥን ተከተተ ። በአንድ ጉድጓድ ፣ በአንድ ዓይነት የሐዘን ስሜት በታጀበ የሕዝብ ለቅሶ አባትና ልጆች ተቀበሩ ። የማያውቋቸው ሰዎች ሁሉ የመኖር ጥያቄ ከሞት ኢጋፍጦ ጥያቄያቸው በሞት ለተደመደመው ሦስት ነፍሶች አለቀሱ ። መንደራችን ለቅሶዋ የየዕለት ሆነ ። የፈሌን ሙቀጫ ሁሉም ፈራት ። ሞቱን ማፋጠኛ አጠገቡ እንዳስቀመጠ ጠረጠረና ሕዝበኔ ከቤቱ ኢያወጣ አርቆ ጣላት ። ቆራሊዮ እየዞረ ያለ ገንዘብ ሰበሰባት። የተናቀችው የእንጨት ሙቀጫ እነ ፈሌን ገፍታ የቀድሞ ክብሯን አስመለሰች ።

***

የሠፈር ልጆች ተሰብሰበን ወደ ጊዮርጊስ ጋራ ወጣን ። ርችት ልናፈነዳ ። የኛ ርችት ባሩድ ነው ። ከመቃብር ሥፍራው አጠገብ በሚገኘው ሠፌ አርሻ ውስጥ ገባን ። ዋነኛው የባሩድ መገኛ ቦታ ነው ። አፈር ላይ ውሎ እያደረ ንጣቱ በሚያስገርም ነጫጭ ከረጢት የተሞላ የአይጥ



@BOOKALEM

አር የሚያካክልና የሚመስል ባሩድ ለፈለገው ሞልቷል ። ሠፈር ውስጥ በባሩድ መጫወት ስለማይፈቀድልን ጋራ ላይ ክብሪት ይዘን ወጥተን እንጫወታለን ።

ባሩዱን አንድ በአንድ እየገጣጠምን መሬት ላይ በተለያየ ቅርፅ እንደረድርና የመጀመርያዋን ክብሪት ስንጭርባት በፍጥነት አጠገቧ ያለውን ትለኩሳለች ። ያቺኛዋም ያቺን ፣ ያቺም ያቺን እያለ የሠራነው ቅርፅ ግም እናየዋለን ። አቤት ደስታችን ! ሽታውንማ ስንወደው ! ጥቁሩ ባሩድ ሲቀላ ሲያምር !

ጠይሜ « ብዙ ባሩድ በከረጢት ስላገኘን ቆልለን የአባብ ቅርፅ እንሥራና የኛና የድንግል ማርያም ጠላት የሆነውን እባብ እናቃጥለው !» አለ ። ተስማማን ። እባቡ ለውቂያ ወደተከመረው የስንዴ ነዶ ሮጦ ሲገባ አስመስለን ቀረፅነው ። ከጭራው አቅጥነን እያወፈርን ፣ እያወፈርን ሄድንና ጭንቅላቱን ቆለልንበት ።

በስምምነት ክብሪቱ ጭራው ላይ በጠምቤ ተለኮሠ ። እሳቱ በዛ ። ወፍራም ግንድ የሚነድ ይመስላል ። ያስፈራል ። ግን ደሞ ያስደስታል ። ባሩዱ ብቻ ሳይሆን የምንጫወትበት እርሻ ላይ ያለው የስንዴ ቆረን ዙርያውን በእሳት ተያያዘ ። እባቡ እየነደደ ፣ በፍጥነት ገላው እየተቀጣጠለ፣ ከጭራው ወደ ወገቡ ፣ ከወገቡ ወደ ደረቱ እያለ ጭንቅላቱ ላይ ደረሰ ። ጭንቅላቱ ከፉኛ ተንጣጣ። የተከመረው ባሩድ ብዙ ስለነበር ፍሙ በዛ ። ተስፈነጣጠረ ። ሁላችንም በደስታ እጨበጨብን። ጮኽን ። አፏጨን ። ብዙም ሳይቆይ ደስታችን በድንጋጤ ተተካ ። ያላሰብነው ነገር ተከሠተ። በርና መስኮት የሌለው ጎጆ ቤት መስሎ የተከመረው የስንዴ ነዶ በእሳት ተያያዘ ።

በእሳት መያያዙን እንደተመለከተ መሮጥ የጀመረው ጠይሜ ነበር ። ማንም አልቆመም ። ከጊዮርጊስ ጋራ እስከ ሠፈራችን ሮጥን ። እሳቱን ይሁን የእርሻውን ባለቤት የፈራነው ሳይታወቅ በአንዳችን ፍጥነት አንዳችን እየተነዳን ፣ ቁልቁለቱ እያዳፋን ፣ ልባችን ድው ድው እያለች ሰላም ወረዳ ደረስን ። ሠላማዊቷ ሠፈራችን « ኑልኝ ልጆቼ !» ብላ እጆቿን ዘርግታ ተቀበለችን ።

ከቀናት በኋላ ከወላጆቻችን የሰማነው ወሬ ያስደነግጣል ። እሳቱ ሌሎች አምስት ተመሳሳይ ክምሮችን አመድ አድርጓል ። የእርሻው ባለቤትም በድንጋጤ ታሞ እጅና እግሩ በገመድ ታስሮ ኪዳነ ምሕረት ጠበል ተወስዷል ። ብቻውን እያወራ « ወያኔ እህሌን አቃጠለው ! አመድ አመድ!» እያለ ይለፈልፋል አሉ ።

***

በከሰዓት በኋላው ፈረቃ የመጀመርያው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ላይ ነበርን ። የጠዋት ተማሪዎች ሆነ ብለው በጠመኔ ዱቄትም ፣ በጫማቸው አቧራም መቀመጫችን ላይ ያተሙትን እያፀዳን ተቀመጥን ። ከቀኑ በስድስት ሰዓት ተኩል የሚጀምረው ትምህርት መምህራችን ጋሽ ዘውዱ በሰዓቱ ባለመገኘቱ ለሰባት ሃያ ጉዳይ አካባቢ ሆኗል ። የዘወትር አርሩጁ ሸዌ ቢዘገይም ጋሼን ቀድሞት ክፍል ገብቷል ። አብርት ከሚቀመጠው ሙሉቀን ጋር ሆነው ጫፏ ላይ ቀለበት



@BOOKALEM

ባላት የትራፊክ ፊሽካ በምትመስል ነገር ይጫወታሉ ።

« እያችሁት ሸዌ ያገኘውን ፊሽካ ?» አለ ሙሴ ፊሽካውን እያሳየን ።

ሁላችንም ወንበራችንን ትተን ወደ ፊሽካዋ ተጠጋን ። ትርምስ ሆነ ። ለመንካት ባንታደልም በዓይናችን ለመዳበስ ዘለልን ። በሰው ትከሻ ተንጠላጠልን ። መቀመጫችን ላይ ቆምን ። ጫጫታ ሁካታችን የጎረቤት ክፍል ተማሪዎችን እንደሚረብሽ አልገባንም ። ሸዌ ፊሽካዋን እንዲያስነካን በእናቱ ፣ በአባቱ ፣ በቅዱሳን ስማፅታት ለመንነው ። አቅም ያለው ነጥቆ ለመንፋት ታገለ ። ትርምስ ሁካታው በዛ ። በዚህ መሀል የጋሽ ዘውዱ ጉማሬ የአቤል ፈንዳዳ ቂጥ ላይ ተለጠፈች ። ሳንባል ፀጥ አልን ። የአቤል ለቅሶ ብቻ በክፍላችን ይሰማል ። ጋሼ አቤልን መትቶ አልረካም ። ልጁን ስምረትን ብቻ ሲተው ሁላችንንም ለጠለጠን ። ስምረትን ግን « ካንቺ ጋር እቤት እንገናኛለን !» ብሎ ብቻ አለፋት ። እንባችንን ካየ ስለሚጨምርልን ወደ ውስጣችን ነው የምናለቅሰው ።

ጋሼ እያስተማረ ሸዌ ፊሽካውን እየነካካ ሳለ ድንገት የፊሽካው ሙቀት ጨመረበት ። ጭስ ቢጤ አየ ፤ ሸተተንም ። ፊሽካው ግለቱም እየበዛ ጭሱም እየተቡለቀለቀ ተወጣጠረ ። ደንግጦ ወደ ሠሌዳው ወረወረው ። ፊሽካው ከሠሌዳው ተጋጭቶ መሬት እንዳረፈ ክፍላችን በጭስ ታፈነ። ማንም ማንንም ማየት አልቻለም ። የሆነ ከፍንዳታ የማይተናነስ የግጭት ድምፅ ከፍላችንን እንዳናጋው ጋሼን ሲያቃስት ሰሠማነው ። ጋሼ «ልጄ !» እያለ አለቀሠ ። ከልጁ ከስም ረት ድምፅ ቀድሞ የጋራ እሪታችን አካባቢውን ረበሸው ። ቀስ በቀስ ጭሱ እየተቃለለ መጣ ። መምህራንና የጥበቃ ሠራተኞች ክፍላችን ገብተው ግንባሩ በደም ተጨማልቆ መሬት የሚንደባ ለለውን ጋሼን አነሱት ። ጋሼ ከበሩ ጠርዝ ጋር ተላትሞ ነበር የወደቀው ። እኛን ለሞት አጋፍጦ ሽል ሲል ሲል በሩ መለሠው ። የኛ ክፍል መዝጊያ ለተማሪ ያዳላል ።

ለነገሩ ዓይናለምና ፀሐይም ከዚህ ቀደም ጉድ ተሠርተዋል ። ለዓይናለም የአካል ጉዳት ለፀሐይ ሞት መንስዔው ወድቆ ያገኙት ትንሽዬ አናናስ ነበር ። ሁለቱም ከነ በድሉ አጥር ላይ ኮሽም ሊቆርጡ ሄዱ ። ኮሽም ሲበሉት ይኮምጥጥ እንጂ በስሎ በቢጫነቱ ሲያዩትና ቆርጠው ወደ አፍንጫ ሲያስጠጉት ደስ ይላል ። ቶሎ ከአፍንጫ የማይወጣ መዐዛው ተኙትውም ውልብ ይልብናል ።

ዓይናለምና ፀሐይ የኮሽሙን ግንድ ነቀነቁት ። በስሎ ግንዱ ላይ ተንጠልጥሎ ሠበብ የሚናፍቀው ኮሽም ተራ በተራ ረገፈ ። የሚረግፈውን እየተሻሙ ለቀሙት ። ድንገት የዓይናለም ዓይኖች አንድ ነገር ላይ አረፉ ። ጥቁር አናናስ አየች ። እንደ መኪና ጎማ ፍንክትክት ያለው የብረት አናናስ ። አንስታ ወደ ጉያዋ ከተተችው ። ከፀሐይ ቅሚያ ለመሸሸግ ሞከረች ። ከጉያዋ አውጥታ በጥርሷ ነከሠችው ። እንደ ኮክ አይገመጥም ። እንደ ዘይቱና በቀላሉ አይቦደስም። እንደ ጊሸጣ ተልጦ አይበላም ። እንደ ቁርቁራ ተመጥጦ አይዋጥም ። እንደ ጅልቦ ሽፋኑ በትንሹ ተቦርቡሮ ከተበላ በኋላ ቅል መሰል ሽፋኑ መጫወቻ አይሆንም ። የማይበላ ሲሆንባት ወደ ጓደኛዋ ተመለሠች ።

የአናናሱን ምንነት ለማወቅ ታገሉ ። ቀለበቱን ዓይናለም ይዛላት ፀሐይ በድንጋይ መቀጥቀጥ



@BOOKALEM

ጀመረች ። እየላላ እየላላ ቀሰበቱ ተላቀቀላቸው ። ከዚያ በኋላ አካባቢው በፍንዳታ ተናወጠ ። እናናሱ በምብ ሆነ ። እናናሱ ፀሐይን አጠናቅቆ የዓይናለምን አምስት የቀኝ እጅ ጣቶችና የቀኝ ዓይን ወሠደ ። ከጦርነት በኋላ የተፈጠረ ሌላ ጦርነት ። በራስ እጅና መሣርያነቱ በማይታወቅ መሣርያ መካከል የሚፈጠር ጦርነት ። በየስርቻው የወደቁት መሳርያዎች የብዙ ጓደኞቻችንን አካል አጎደሉ ። በርካታ እኩያ ትንንሽ ነብሶችን በሉ ። ስንጣላ በጉዳታቸው እያሾፍንባቸው የምናስለቅሳቸው ልጆች ተፈጠሩ።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ ሃያ

## ዱርዬው ባንድ

በሺህ ዘጠኝ መቶ ስንት ዓመተ ምሕረት እንደተመሠረተ አይታወቅም ። ለመመሥረቱ የመጀመርያውን እንገር ሃሳብ ያመነጨውን ሰው ማንም አያውቀውም ። የሚታወቅ ዓላማ ግን አለው ። ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን መከላከል ። መታቀብ ፣ መወሠንና መጠቀም በሚሉ መርሆዎች የሚመራ ዓላማ ።

በቁመቱ ልክ ተገምሶ ስጋ የለበሰና አፅመ አጥንቱ ያገጠጠ የሰው ምስል ከከበባችን የውጨኛው ግድግዳ ላይ ተሠቅሏል ። ወደ ከበባችን የመጣ ሁሉ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ብቻ ሳይሆን ቫይረሱ በደማቸው የሚኖረውንም ወገኖች እንዲፈራ ፣ እንዲሸሽና እንዲያገላቸው ምክንያት የሆነ ምስል። ሕፃን ይሁን አዛውንት ፣ ወጣት ይሁን ጎልማሳ እንዴ ብቻ ዓይኖቹን ወደ ምስሉ ይወርውር እንጂ ተመርምሮ እራሱን ያወቀውና ቫይረሱ በደሙ እንደሚገኝ የተነገረው የወደፊት እሱነቱን እያሠበ ሽምቅቅ ፣ ያላወቀውም በምስሉ ፀያፍነት ብሽቅ ማለቱ አይቀርም ።

እንደ ቢሮ የምንጠቀምበት አንድ ጠባብ ከፍል አረንጓዴ ግድግዳው በተለያዩ ፎቶ ግራፎች ተለብጦ የምክክር አገልግሎት የሚፈልጉ እንግዶችን ሲያስተናግድ ይውላል ። አጠገቡ ሊወድቅ ያዘመመ ርዝመቱ አስር ሜትር የሚጠጋ ከፍል ይገኛል ። የቲያትር ፣ የሙዚቃና ዳንስ ቡድኑ አባላት ተራ በተራ ልምምድ የምናደርግበት ቦታ ነው ።

የዚህ ቤት አቋም ይገርመኛል ። በተለይ የውዝዋዜ ከፍል አባላት ልምምድ ሲያደርጉ ደብተር የሚያካከል የግድግዳ ቁራሽ መሬት ላይ ይዘረዘፋል ። የኦሮምኛና ጉራጌኛ ውዝዋዜ ሲሠሩ የአፈር ወለሉን እየደበደቡ ፣ በርና መስኮት ዘግተው አቧራ እያጨሱ በአየር እጦት ብዙዎች ተዘርረዋል። አሠልጣኙ ለተወዛዋዦቹ አለቃ ይመርጥላቸውና አለቃው እንዲያሠራ ትዕዛዝ ሠጥቶ እጁን ወጥቶ ይናፈሳል ።

ታላላቆቻችን በመሠረቱት የፀረ-ኤድስ ከበብ ውስጥ የ «ቢ» ቡድን አባላት ተብለን ተመልምለን ተካተትን ። በተመሳሳይ ዕድሜ ላይ የምንገኘውን ልጆች አንድ ላይ ያደርጉንና የሕይወት ከህሎት ያስተምሩናል ። ትምህርቱን እንደጨረስን የተደበቀው ተሰጥዖ ፍለጋችን ይጀመራል ። እኔ ሁለገብ ሞያተኛ ነበርኩ ። እዘፍናለሁ ፣ መድረከ እመራለሁ ፣ ድራማ እሠራለሁ ፣ እወዛወዛለሁ። ግጥም እየገፍኩ ዜማ ከእንግሊዝኛና ሕንድ ዘፈኖች እየወሠድኩ እዝናናለሁ። እስቂኝ የመድረከ ሥራዎችን አቀርባለሁ ።

በተለይ በራሴ ላይ ብዙ ቀልዶችን እፈጥራለሁ ። እራሴን እየቀለድኩበት በሚገኘው ጭብጨባ እቤቴ ገብቼ አልተኛም ። ለራሴ ከመድረከ ስወርድ መሠደቢያ የሚሆኑ ቀልዶችን



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

እፈጥራለሁ-ለነገ ። ለነገሩ በራሴ ላይ እራሴ ስቀልድበት ካልሆነ የሌሎች ፉተታ አይመቸኝም ። እስከ መደባደብ እደርሳለሁ ። « ተው ጭንቅሎ አርቲስት አይደባደብም !» ይሉና ይገላግሉኛል። አርቲስትነቴ በገላጋዮቼ ዘንድ ዕውቅና እንዲያገኝ ረገብ እላለሁ ። ሌላው ቀርቶ መድረክ ላይ በራሴ የቀለድኩትን ይዘው ከመድረክ ውጪ ሊያስቁብኝ ሲሞክሩ ለጠብ እነሳለሁ ። በፍጹም በራሴ ላይ ከራሴ ውጪ ማንም እንዲቀልድብኝ አልፈልግም ።

በ« ቤ» ቡድን ውስጥ ከነበርነው ልጆች ተለይቼ በፍጥነት ከታላላቆቼ ጋር ወደ « ኤ» ቡድን እንድቀላቀል ተደረገ ። መድረክ ተሠይሜ መነጋገርያ ማይክሮፎን ከጨበጥኩ በኋላ እፍረት የሚባል ነገር አላውቅም ። ዓይን አፋርነቴ በዓይን አውጣነት የሚተካው መድረክ ስይዝ ነው ። ሰዎችን ፈገግ እያደረጉ ቁም ነገር ሊያስጨብጡ የሚችሉ ሃሳቦችን በግጥም መልክ በእ ንቅስቃሴ አጅቤ እንደሚከተለው አቀርባለሁ ።

እግዚሀር ሲፈጥረኝ ለከፋ እወዳለሁ
እናም በቀደም 'ለት ተቀምጬ እያለሁ
አንዷ ተከናንባ ባጠገቤ ስታልፍ
አፌን አሞጠሞጥኩ የልምዴን ልላከፍ ።
ሃይ ነፍሴ ቆንጂቴ ወዴት ታገድሚያለሽ ?
ካሴትሽ ማን ይሆን ኧረ የማን ዴክ ነሽ ።
ገርቅ ያለ ሰውነት አጠር ያለ ቁመት
አሪፍ መቃመጫ ያካሄድሽ ውበት
ቢለካ ቢሠፈር ቢቆጠር ቢመተር
እንዳንቺ ድቡልቡል ጠፋ ከኛ ሠፈር...ሮቶ ።
ትንሽ እንኳ አታፍሪም እንዲህ ተከናንበሽ
ከነ ሳምንት ቂቤሽ በዚህ ትሄጃለሽ ?
እስቲ ተመልከቺው ያረገሽውን ጫማ
እንኳን ከጎረቤት ካገር አያስማማ...እፍፍ ።
እያልኩኝ ስሳደብ አፌ እንዳመጣልኝ
ዞር ብላ ሾፋ አወረደችብኝ ።



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

«አንት ቅማላም ሌባ ቡትቶ እከካም
እኔን ስትዘለፍ ትንሽ እንኳ አታፍርም ?
ቆየኝ ትመጣለህ ልጄ ጋ ሁለተኛ
አንተ የእንጀራ ጠንቅ የእህል ቀበኛ ፡፡ »
ሲሉኝ በመገረም ደንግጬ ባያቸው
የጓደኛዬ እናት 'ትየ ጌጤ ናቸው ፡፡

በዚች ኮሚክ ግጥሜ ከታዳሚው ሞቅ ያለ ጭብጨባ ስሸለም ጠምቤ ደሞ ታኮርፈኛለች ፡፡ «በእናቴ ለምን ትቀልዳለህ ?» ትለኛለች ፡፡ እኔ በሱ እናት በእማማ ጌጤ ለመቀለድ አስቤ ሳይሆን ግጥሜ ቤት እንዲመታልኝ ስፈልግ ነው ባጋጣሚ እንዲህ የማደርገው ፡፡ ጠምቤን አሳምኜ ከታረቅኳት በኋላ በቀጣይ መድረክ እንደምቀይረው ቃል እገባላታለሁ ፡፡

« ደብሬ » ብዬ ስሠራም እለታችን የአያቱ ስም ስለሆነ ይናደድና ከመድረክ ጀርባ በጥሩ ኩርኩም ይቀበለኛል ፡፡ ዓይኖቼ ማየት እስኪከብዳቸው ብይ የሚያካክል እንባ ያዝላሉ ፡፡ የእንባ ቋጠሮዎቼ ከተዘረገፉ መድረክ ስለሚከለክለኝ ለመድረኩ ስል ወደ ውስጤ እለቅሳለሁ ፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የተለያዩ እናቶችን ስም እየተጠቀምኩ ስሠራ የተለያየ ኩርኩም እናቴን ይነድላል፡፡ ምን አባቴ ላድርግ ? የፈረንጅ አሮጊቶችን ስም ፈልጌ ግጥሜን እንዳላስተካከል ሠፈራችን የፈረንጅ አሮጊት ኖራ አይደለም ጎብኝታን አታውቅም ፡፡

ምርር ሲለኝ አንድ መድረክ ላይ «እትየ ዳሽ ናቸው» ብዬ ዘጋሁት ፡፡ አንዱ የለበሠው ሠፊ ካፖርት የሚንቀሳቀስ ድንኳን ያስመሠለው ጠውላጋ ከተመልካቹ መሀል ተንደርድሮ መጣ ፡፡ ሕዝቡ ሞቅ አድርጎ እያጨበጨበ አፏጨ ፡፡ ለማንኛችን እንደሆነ ያልለየ አድናቆት ፡፡ ሰውዬው ሊሸልመኝ መስሎኝ ጉንጬን ለከንፈሩ ሳሰናዳለት አይጥ የቀረደደው ሠፊድ በመሠለው ቫካራ መዳፉ በጥፊ አላሠኝና መነጋገርያውን ነጥቆኝ « የኔ እናት አረጋሽ ያንተ ማሾፊያ አይደለችም እሺ! ገንቦ ራስ !» ብሎኝ ሄደ ፡፡ በቃ ይቺ ከለከፋ ጋር የተያያዘች ግጥሜ ለታዳሚው ሳቅ ለኔ ዱላ ለጋሽ መሆኗ ሲገባኝ «ዳሽ» እና «አረጋሽ»ን አጣርቶ ለማያዳምጥ ታዳሚ ያቺን ግጥም ከማቅረብ ታቀብኩ ፡፡

ሳላውቅ የዱርዬው ባንድ ዓይን ሆንኩ ፡፡ በየመንገዱ « ኮሜዲያን ጭንቅሎ አድናቂህ ነኝ እሺ!» የሚለኝ በዛ ፡፡ በርግጥ ወንድሜ «ሰዎቹ ስለማያውቁህ ነው እንጂ አንተ «ኮሜዲያን» ሳይሆን «ኮመዲኖ» ነው መባል ያለብህ !» እያለ ያስለቅሠኛል ፡፡ ባንዱ በሄደበት ሁሉ እኔ ፣ የሙዚቃ መሣርያውና በጨርቅ ላይ የተሳለው የክበቡ አርማ አንጠፋም ፡፡ የክበባችን የበላይ የሆነው ሰውም በሁለ ገብነቴ ስለሚወደኝ እንደ ቁልፍ መያዣው በሄደበት ያንጠለጥለኛል ፡፡ በጣም ዝነኝነቴ ከሙብዛቱ የተነሳ ሌሎች ከበባት ተመሳሳይ ዝግጅት ሲኖራቸው በትውስት መድረክ እመራላቸዋለሁ ፡፡ ሰዉም በምፈጥራቸው ቀልዶች ይሁን በተፈጥሯዊው የጭንቅላቴ



@BOOKALEM

ቅርፅ እንጃ እንጂ ገና «ማይክ» ስጨብጥ መሳቅ ይጀምራል ።

ሠርግ ፣ የተማሪዎችና የቤት ምርቃት ፣ የተለያዩ ዓመታዊ ከብረ በዓላት ሲኖሩ ፣ የከተማዋ ዕዳት ሲታወጅና በሌሎችም ዝግጅቶች ላይ ዱርዬው ባንድ አለ ። ባንዳችን አስራ ሦስት ተወዛዋገሮችን አሠልጥኖ ለመድረከ አብቅቷል ። ከአስራ ሦስቱ አንዱ ውዝዋዜ የማይችለው ተወዛዋዥ ነው ። ውዝዋዜ የማይችለው ተወዛዋዥ ጭንቅሎ ይባላል - እኔ ። እስከ ዛሬም ውበት ያለው ውዝዋዜ አልችልም ። እስከስታዬ እንኳን የሚያምረው ከድሬዳዋ ያመጣኋት ወባዬ ስትነሳብኝ ነው ። አንድ ጊዜ በየ ዓመቱ ኅዳር 22 ቀን የሚከበረውን የፀረ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ቀንን ከዓለማያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋር ለማከበር በመኪና ተጭነን ሄድን ። መድረኩን ያደመቁ በርካታ ዝግጅቶቻችንን አቀረብን ። ቀልደን ፣ ሳቅ ፈጥረን አስቀን ፣ ዘፍነን አስደንሰን ስናበቃ ምርጥ ድራማ አሳየን ። ግጥሞች በዓይነት በዓይነት አሰደመጥን ። ኅብረ ዝማሬዎችን በትወና አጅበን ጀባ አልንና ታዳሚው አንጀት ውስጥ ከነ ጫማችን ገባን ። ፉጨት ጭብጨባው በረከተብን ።

የብሔር ብሔረሰቦች ዘፈን መቅረብ ጀመሩ ። « ደባለ ኬይሠን » የሚለው የአሲ ቢራ የሠርግ ዘፈን በአይጤ ቀረበ ። አይጥ የምታከለው አይጤ በጨፋሪዎች ተሸፈነች ። አይጤ በድምጿ እንጂ በአካሏ ራቀችን ። ብዙም ሳይቆይ የሙዚቃ መሣርያውና የዘፋኙ በ«ማይክ» የታጀበ ድምፅ ጠፉና የጨፋሪዎች የኅብረት ዜማ ብቻ በአዳራሹ ገነነ ። ለካንስ መብራቱ ድርግም ብሎ ጠፍቷል ። ችግሩን ያወቅነው የባንዱ አባላት ብቻ ነበርን ። መብራት እስኪስተካከል ድረስ ታዳሚውን ሸዋውጄ ማቆየት አማረኝ ። ግን ያደመጠኝም የለ ። የኅብረት ዘፈናቸውን ቀጠሉ። እኔም ሁለቱን እጆቼን ከፍ አድርጌ እያወዛወዝኩ ታዳሚው ሳይነቃ መብራቱ እስኪስተካከል ዘፈኑን እንዳያቆም አበረታታለሁ ። የዩኒቨርሲቲው የመብራት ባለ ሞያም የተቋረጠውን መብራት ችግር አጥንተው የዘገየ መፍትሔ ሠጡን ። ትግርኛ ሲዘፈን ሁሉም ተዋናይ ይሆኑና ተመልካች ይጠፋል ። ሙዚቃውን የምንሠራው ለማን እንደሆነ ማወቅ እስከንቸገር ድረስ ወንበር ይዞ ተመልካች እናጣለን ። በባንዳችን አቅም ሱማልኛ ፣ አደርኛ ፣ አፋርኛና አማርኛ ጨማምረን ተማሪውን አዝናናነው ።

ሦስት የዩኒቨርሲቲው ሴት ተማሪዎች ወደኔ መጡና በዝግጅታችን ቅር እንደተሠኙ ገለፁልኝ ። የቅሬታቸው መነሻ በነሱ ብሔር ቋንቋ ዘፈናቸው ባለ መቅረቡ ነበር ። እኛ ከሐረር ከተማ ወጥተን የማናውቅ ልጆች ጉሙዝኛን እንኳን ዘፈኑን ንግግሩን ሰምተነው እንደማናውቅ ገለፅኩላቸው ። « እስካሁን የሰማናቸውን በልቦናችን አሳድርልን !» ብላችሁ ፀልዩ አልኳቸው በቀልድ ለማዋዛት ፈልጌ ።

አንደኛዋ ከአልጋ ትንሽ ጠበብ የምትል አርበ ሠፊ ተማሪ ጫማዋን አውልቃ በጥፊ ብታጮለኝ «made in china » የሚለው ፅሁፍ ሞጋጋ ፊቴ ላይ ታተመ ። ጥፊው ሲለበልበኝ አልሄ መጣና የመታችኝን ልጅ ይለይላት ዘንድ « ይኺ ባንድኮ የፀረ-ኤድስ ማኅበር እንጂ የብሔር ብሔረሰቦች ባንድ አይደለም እሺ ! ከብት የከብት ሐኪም !» አልኳት ጉንጩን እያሻሸሁ። አጅበውን የነበሩት ገላጋዮችና ወሬ አድማቂዎች ሁሉ ሳቁ ። ልትመታኝ ስታሳድደኝ በሰዎች መሀል ሽሉከሉከ



@BOOKALEM

እያልኩ፣ ምላሴን እያወጣሁባት እርር አደረግኳት ።

ልጆቹንም አረጋግተው እኔም ወደ መድረክ ተመልሰኩ ። የመድረኩን በፈገግታ የታጀበ ድባብ ለመመለስ ስል አንዷት በአለቃዬ የተነገረችኝ አሸሙረኛ ቀልድ ከተማሪዎች ውጤት ጋር እያይዤ አቅርቤ ልጅቱን ለማሳበድ ፈለግኩ ።

«አንዷት ጣፋጭ ቀልድ ትፈልጋላችሁ?» ስል ጠየቅኩ ታዳሚዎቻችንን ።

« አዎ !» የኅብረት ድምፃቸው ከጭብጨባ ጋር ተሰማኝ ።

« እናላችሁ ወዳጆቼ ምን ሆነ መሠላችሁ ። እ...አንዷት የመጀመርያ ዓመት ተማሪ እዚህ ግቢ ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ መደባደብ እንደ ኮርስ እስኪመስልባት ከሴት ወንዱ ትቧቀሳለች ። ፊትና አንገቷ በጭራሮ የጠረገት የድህ ደጃፍ እስኪ.መስል በጥፍር ተቦጫጭሯል ። እና ልጅት አገርና ቤተሰብ ጥላ ከመጣችበት ትምህርቷ ይልቅ ስለ ድብድቧ ስታስብ ትውል ታድር ነበርና የፈተና ውጤት ሲመጣ ጉድ ተሠራች ። አምስት “F” እና አንድ “G” አመጣች ።»

ታዳሚዎቹ በጣም ሳቁና « ውጤቱ ይደገም !» አሉኝ ።

« አምስት «F» እና አንድ «G» » ደገምኩላቸው ።

የሚያደምጡኝ በሙሉ አኩል ሳቁ። ስለሳቁልኝ ደስ አለኝ። ምርጥ ቀልድ እያቀረብኩ እንደሆነ ገባኝና ሃሳቤን ለመጨረስ ካቆምኩበት ቀጠልኩ።

« እናላችሁ ...» አልኳቸው ።

ፀጥ አሉ ።

«እናላችሁ ልጅቷ ውጤቷን ተመልክታ 'Fantastic Female Food Fighter From Gumuz'! ( ድንቋ የምግብ አጥቂ ከጉሙዝ ) ብላ ተረጎመችው ።»

ሳቅ ፣ ፉጨትና ጭብጨባው በአዳራሹ ደመቀ ። ኦርጋኒስቱ ጠራኝና እየሳቁልኝ ሳይሆን እየሳቁብኝ እንደሆነ ነገረኝ ። ለካንስ በዩኒቨርሲቲው የሚሠጠው ውጤት “G”ን አያካትትም ። "A,B,C,D" እና " F " ብቻ ናቸው ። “E” እንኳን ተዘልላለች ።

ኀንበስ ብዬ ያሳለፍኩት የተወረወረ ጫማ ኦርጋኒስቱን ደረቱን ደቁሶ ኦርጋኑ ላይ አረፈ። ተመቺው አፍንጫውን በካናቴራው ሸፍኖ ጫማውን በጣቱ አንጠልጥሎ አነሳና ወደ ልብስ መቀየርያ ከፍሎ ወረወረው ። በኦርጋኒስቱ ድርጊት ታዳሚው ሲስቅ ልጅት እኔን በሰድብ አጨማለቀችኝ ። « ካልገደልኩት » ስትል ፎከረችብኝ ። መጀመርያ መግደልን በበረሮ እንድትማር መከርኳት ። አበደች ። ዝግጅቱ ተረበሸ ። ሹፌራችን እንድትተወኝ ለመናት ። አልሰማችውም ።

« ከዚህ በኋላ አልለምንሽም ...እጠፈጥፍሻለሁ !» አላት



@BOOKALEM

«Who are you ?»( አንተ ማነህ ?) አለችው በእንግሊዝኛ ።

« ሂጅ ! አንቺን ብሎ እንግሊዝኛ ተናጋሪ …ይቺኔ ስምሽን ከነ አያትሽ የሚፅፍልሽ ያ የፈረደ በት አስተማሪሽ ይሆናልኮ…ወሪዳ ! » በንዴት ብግን እንዳለ ያስታውቅበታል ።

«ሂድ ወደዛ ! እንዳንተ መሀይም መሠለኩህ ! የዩኒቨርሲቲ ተማሪኮ ነኝ-ደደብ ! »

« አልቀረብሽም አቱ ! ከዘሮችሽ የዩኒቨርሲቲ ደጃፍን የረገጥሽው አንቺ ብቻ ነሽ መሠለኝ። ዩኒቨርሲቲ መግባትን ብርቅ አረግሽው እንዴ ? ግቢው ውስጥ ለመግባት ለመግባትማ ይኸው እኔም ሰውና ከበሮ ጭኜ ገብቻለሁ! ይታይሻል…ቆም ነገሩ ይቺን እንደ ምሁር ማሠራት ነው እቢ! » አላት በሌባ ጣቱ ጭንቅላቷን እየደነቆለ ።

ለገላጋይ ያስቸገረችው ልጅ ቆመው ሲያጋግሉ በነበሩ ተማሪዎች በኃይል እየተገፋች ከአዳራሽ ወጣች ። ፊቷ በእንባ ታጥቧል ። የረብሻውን ድባብ ለማጥፋትና ሁሉንም በደስታ ለማራጨት ትግርኛ ዘፈን ሠራን ። አሮምኛ አስከተልን ። ወንበሮቹ የተቀማጭ ያለህ እያሉ ሲጮኹ መድረኩ በርግጫ ተጨናነቀ ።

ከዱርዬው ባንድ ጋር በዞርኩበት ሁሉ ገጠመኝ አላጣም ። ቀደም ሲል እንደገለፅኩት ባንዳችን የማይሠራበት ቦታ የለም ። እስካሁን ለቅሶን ብቻ ነው እንጂ ያላጀብነው ከሀብታም ልጅ ልደት እስከ ተማሪዎች ምርቃት አድምቀናል ። እኔ ግን ሁሌም የሚያናድደኝ ሠርግ ቤቶች ውስጥ አጫጭር ጭውውቶች የማይሠሩበት ምክንያት ነው ። ቆይ ግን ምናለበት ስለ ቤተሰብ ምጣኔ ፣ ስላልታቀደ እርግዝና ፣ ወይም ስለ ኤድስ አጠር ያለ ጭውውት ቢሠራ ?

አንድ ጊዜ ሃያ አራቱም የባንዱ አባላት የተሳተፍንበት ዝግጅት ተሠናዳ ። ሠፈራችን አካባቢ ከሚገኘው ደሴ ሆቴል ትንሿን አዳራሽ ሌላ ተስተናጋጅ እንዳይገባ አድርገን ያዝን ። የመዝናኛ ገንዘቡን በአበል መልክ ያገኘነው በእንግሊዝ ሕፃናት አድን ድርጅት ስፖንሠር አድራጊነት ቁልቢ ከተማ ላይ በሠራነው ፀረ- ወባ ዘመቻ ምክንያት ነበር ።

ትዝ ይለኛል ቅዳሜ አመሻሽ ላይ ሁላችንም በሆቴሉ አዳራሽ ተገኘን። የሙዚቃ መሣሪያችን ተጠምዶ በመሣሪያ ብቻ የተቀነባበሩ ዜማዎችን ማስደመጥ ተጀምሯል ። አራት ቀርቦ በሳን ። ስምንት ሳጥን ቢራና አንድ ሳጥን ለስላሳ ተከምሮልናል ። ባለኝ መረጃ መሠረት ከግማሽ በላዩ ተሳታፊ ቢራ አይጎነጭም ። በብዛት የቀረበው ግን ቢራ ነው ። ለስላሳውን ከሴቶቹ ጋር እየተሻማሁ ጠጣሁ ። ሆዴ ከአቅም በላይ እንደጫንኩበት ቁንጣንን ምልክት አርጎ ገለፀልኝ ።

የምግብ ሳህን ከተነሳ በኋላ ዘፈን ተጀመረ ። የመጀመርያውን ዘፈን አይጠጤ ምርጥ አርጎ አቀረበ ። ቀጥላ ሳራ ፣ ቀጥሎ ዘውገ ፣ ከዚያም ሣልሳዊት…በራሳችን ባንድ እራሳችን ጨፈርን ። ቀደም ሲል ለስላሳ ተሻምተው የጠጡት ሴቶች ሁሉ የቢራ ቡትሌ አንቀው አፋቸውን እያለቀለቁ ይጎነጫሉ ። ከሴቶቹ ማራናታ ከወንዶቹ እኔ አንጠጣም ። እየመሸ ሲሄድ ስካር መጣ ። ቀድሞ ጢምቢራዋ የዞረባት ሳራ ናት ። ያለ አባቷ በገፍ አገኘሁ ብላ ሲድስት ቡትሌ ቢራ ለግታ ለግታ መቆም አቅቷታል ።



@BOOKALEM

ሴት ወንዱን ትሳደባለች ። « እናትክን...!» ትላለች በተቀሠረው የመሀል ጣቷ ምልክት እያጀበች። ጨዋ ፣ ጭምት የነበረችው ልጅ ብልግናዋን አዳራሽ ውስጥ ፊት ለፊታችን አሠጣችው። እየተንገዳገደች መጥታ አቀፈችኝና ሽንት ቤት እንድወስዳት ጠየቀችኝ ...ማለቴ አዘዘችኝ። አፈርኩ። እኔ ከነ ጠይሜ ጋር ካልሆነ ከሴቶች ጋር ሽንት ቤት ሄጄ አላውቅ - ምን አባቴ ልሁን ?

እላዬ ላይ ሃሳቧን ጥላ በቁሟ ተኝታብኝ ኩንታል የተሸከምኩ ያክል እያንገዳገደችኝ ሽንት ቤት ደረስን ። በሩን ከፍቼ አስገባኋት ። እንዴት አባቷ ትቀመጥ ። ከለቀቅኳት መሬት ላይ መፍሰሷ አይቀርም ። የመፀዳጃ ሠሀኑን እየጠቆምኩ « ያው ቁጭ በይ !» አልኳት ።

« እሺ ሱሪዬን አውልቅልኝ !» አለችኝ ዓይኖቿን ጨፍና ።

ልቤ ትርትር ። እንኳንስ የሴት ሱሪና የራሴንም ሱሪ ሳወልቅ ግራና ቀኙን አይቼ ፣ ማን አለ ማንስ የለም የሚለውን አጣርቼ ነው ።

« ጭንቅሎዬ በናትህ ወጠረኝ...ልፈነዳ ነው ! በናትህ ቶሎ አውልቅልኝ !»

ለታለቅስ መሠለኝ ። የኔንስ ወደ ውስጥ በፍርሀት የማለቅሰውን መች አየችልኝ ። ቀስ ብዬ ፊቴን ወደ ኋላ አዞርኩና የሱሪዋን ቁልፍ በዳበሳ ፈታሁላት ። እየተንቀጠቀጥኩ ቻርኔላውን ወደ ታች ተረተርኩላት ።

« ቶሎ አውልቅልኝ በናትህ ?» አለችኝ እጇን እያርገበገበች ።

የት አባቴ ልግባ ? ፈራሁ ። ምን ይዋጠኝ ? ሱሪዋን እስከ ጉልበቷ ዝቅ አደረግኩላት እያፈርኩ ።

«በናትህ ጭንቅሎዬ ቶሎ አውልቅልኝ !» አለችኝ ስካር ባሳሰረው አንደበቷ።

« እንዴ ! ከዚህ በላይ ምኑን ላውልቅልሽ ?»

« ፓንቴን አውልቅልኛ !»

« ኧ !» ደነገጥኩ ።

« ጭንቅሎዬ በናትህ ልፈነዳብህ፣ኮ ነው ። ቶሎ ብለህ ፓንቴን አውልቅልኝ ...ስሞትልህ !»

ገና ዝቅ ሳደርግላት እጄ ላይ ለቀቀችብኝ ። እንደ ኮካ ኮላ ቶሸሸ እያለ የወረደው ሽንቷ እጄንና ልብሷን አረሠረሠው ። መመገቢያ እጄ ላይ ሽንታ ስታበቃ «እፎይ !» ብላ ተነፈሠች ። አናደደችኝ ።

« እናትሽ በብር ከሃምሳ የገዛችልሽ ፖፖ መሠልኩሽ እንዴ እጄ ላይ ሸንተሽ እፎይ የምትዪው!» አልኳት ።

« ምናባክ ያነጫንጭሃል ? የወንዝ ውሃ መሠለህ ? ቢራ'ኮ ነው የሸናሁልህ ፣ ቀዝቃዛውን ጠጥቼ አፍልቼ ያወጣሁልህ ። ከፈለግክ ቅመሰው እሺ ! ማርያምን ቅመሰውና ቢራ ቢራ ካላለህ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

ቅጣቴን እቀበላለሁ !» ከትከት ብላ ሳቀችብኝ ፡፡

እናደደችኝ ፡፡ ለቀቅኳት ፡፡

መቆም አልቻለችም ፡፡ እንደ በሰለ ፓስታ እየተጥመለመለች የሽንት ቤቱ ወለል ላይ ወፌር ብላ እንደ አጥሚት ፈሰሰች ፡፡

« ከየት መጣህ ?» ያላልኩት የአንድ ሰውዬ ጥፊ ጆሮዬን ሲወለውለው ተሰማኝ ፡፡

« ገና በዚህ ዕድሜህ ከሴት ጋር ...ያውም ሽንት ቤት ውስጥ ? ሠከራሎች ብለህ ትጫወትባታለህ አይደል ? ወይ ዘመን ! ኧረ ፈጣሪ እባክህ የጥፋት ውሃህን አውርድ !» አለ ወደ ሰማይ አንጋጦ፡፡ እሷንም ሰደባት ፡፡

የመሀል ጣቷን ቀስራ ያለ ድምፅ ሞለጨችው ፡፡ ሊምታት ሲጠጋት አስመለሳትና ልብሱ ላይ አከናነበችው ፡፡ ሮጬ ወደ ጓደኞቼ ሄድኩና የውሽቴን « አንድ ሰውዬ ሳራን ሽንት ቤት ውስጥ ሊደፍራት ነው ! እኔንም ቀጥቅጦ አባረረኝ !» አልኳቸው ፡፡ ተሯሩጠን ስንመጣ ሰውዬው እዚያው ሽንት ቤት ውስጥ ቆሞ ይሳደባል ፡፡ ጉልቤው ጓደኛችን በአንድ ቦከስ ከመሬት አዋሃደው፡፡ ደስ አለኝ ፡፡ የታባቱ ባልችለውም በሚችሉት አስወገርኩት ፡፡ ሆ ! የተሸናብኝ እኔ ሆኜ ሳለሁ በምን ዕዳዬ ዱላ ልቅመስ ?

ዱርዬው ባንድ የማይገኝበት ቦታ የለም ፡፡ የተጠራበት ቦታ ድረስ የሙዚቃ መሣርያዎቹንና አባላቱን ይዞ ይገኛል ፡፡ ከኪነ ጥበቡ ባሻገር የተለያዩ የባህሪ ለውጥ አምጪ ሥልጠናዎች ላይ ትኩረት አድርጎ ይሠራል ፡፡ የተለያየ ሀገር ዜግነት ያላቸው ቀለመ ነጭ ሰዎች በየጊዜው እየመጡ ምስልና ጥያቄዎቻችንን ይወስዳሉ ፡፡ ሰዎቹ ከመምጣታቸው አስቀድሞ ኃላፊያችን የመጡበትን ሀገር ይነግረንና የምናቀርብላቸውን ጥያቄዎች በቃላችን እንድንሸመድድ ያስጠናናል፡፡ ጥያቄዎቻችን በሙሉ ችግርና ልመና ተኮር ናቸው ፡፡ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ ሃሳቦችን ብቻ እናቀርባለን ፡፡ የግል ሃሳብን ማቅረብ አይፈቀድም ፡፡ ሁሌም የምናቀርባቸው ችግሮች የኃላፊያችን እንጂ የኛ አልነበሩም ፡፡

እውነት ለመናገር ብዙ ጊዜ የሚያስጨንቀኝ « ኤድስ የጠፋ እንደሆን ገንዘብ ከየት አባቴ አመጣለሁ?» የሚለው ጥያቄ ነው ፡፡ አሁን ጓደኞቼን ጠይሜና ጠምቤን እየያዝኩ የምዝናናው'ኮ « ውሎ አበል » ተብሎ በሚሠጠኝ ብር መሆኑን አውቃለሁ ፡፡ ኤድሱ ከጠፋ ግን ገንዘብ ከየት አባቱ ይመጣል ? ወይ ለእግዜር « እባክህ ሌላ በሽታ ላክልን !» ብለን ካልተሳልን በስተቀር አለቀልን ፡፡ የገንዘብ ድርቅ ይመታናል ፡፡ ለነገሩ ፈጣሪስ ቢሆን የለመኑትን መች ይሠጥና ፡፡

ኃላፊያችን ቢራና ወሬ በጣም ይወዳል ፡፡ እኛ የምሽት ልምምዳችንን እየሠራን ሳለ እሱ የመጠጥ ጋን ጋን እየሸተተ ፣ በኪሱ ሌሎች ተጨማሪ ቢራዎችን ሸጉጦ ይመጣል ፡፡ ተከራይቶ የሚኖርበት ቤት ከከበባችን ሃያ ሜትር አይርቅም ፡፡ ነገር ግን በከበባችን ስልከ ጆሮውን እየቀያየረ ከልጆቹ ጋር ይጫወታል ፡፡ ረጅም ሰዓት ያለ ማቋረጥ ያወራል ፡፡ ያውም ደሞ የማይረባ ወሬ ፡፡



@BOOKALEM

« እንቺ አልናፈቅኩሽም እንዴ ?» ይላታል ትንሿን ልጁን ።

« ናፍጠሽኛል እንጂ !»

« እና ታድያ የናፈቁትን ሰው እንዲህ ነው ሰላም የሚባለው ?»

« ኧለ አደለም !» ትልና በሰልከ ውስጥ ትስመዋለች ። ረጅም የደስታ ሳቅ ይስቃል ።

« ሰማችሁ አይደል እናንተ የዱርዬው ባንድ ዱርዬዎች ...ልጂኮ ሳመችኝ !» ብሎ ይነግረናል ። በራበው አንጀታችን የውሸታችንን ጥርሳችንን እናገጥለታለን ። ትኩስ ዳቦ ከተስፋ ጋር ይገዛልናል። « ዛሬን ደረቁን ብሉት እንጂ በቅርቡ ከጥብስ ወይም ከቅቅል ጋር ነው የምጋብዛችሁ !» ይለናል ። የማይደረግ አዲስ ቃል ይገባልናል ።

አንዳንዴ ረዘም ያሉ ከሳምንት በላይ የሚፈጁ ሥልጠናዎች ሲመጡ በከበባችን ፀብ ይነግሣል። ታላላቆቻችን ከአለቆቻችን ጋር ግብግብ ፈጥረው አቧራ ያጨሳሉ ። ለሥልጠናው የሚላኩት የማይታወቁት « የከበቡ አባላት » ናቸው ። አንድም ቀን ከበቡን ዘወር ብለው አይተው የማያውቁ ፣ የአባልነት ዝርዝር ውስጥ ስማቸው ያልተካተተ ፣ የከበቡን ስም እንኳን አስተካክለው መጥራት የማይችሉ ፣ ከከበቡ ሳይሆን ከአለቆቻችን ጋር በስጋና ደም የተሳሰሩ ሰዎች የሥልጠናው ተካፋይ ይሆናሉ ። ከሥልጠናው መልስ ሌሎቹ መደበኛ የከበባችን አባላት እንደሚያደርጉት የማያደርጉ ፣ የሠለጠኑበትን ሥልጠናውን ላላገኙት የማያሠለጥኑ ሰዎች የፀብ መንስዔ ይሆናሉ ። የዚያን ሰሞን ቢያንስ ለአስር ቀን ከበባችን ይዘጋል ።

« እኛ ለፍተን እዚህ ባደረስነው ከበብ ለምን ሌሎች ተጠቃሚ ይሆናሉ !» በሚል አምባጓሮ ይነሳል ። ድብድብ በጎደለው ፀብ የከበቡ ቢሮ ይነቃነቃል ። አንዳንዶቹ የልባቸውን ተናግረው በዚያው ይቀራሉ ። ወደ ሌላ ከበብ ወደ ሌላ ጥበብ ይሄዳሉ ።

ከዱርዬው ባንድ አባላት በርግማን ያደገው ፣ ርግማን ምርቃት የሆነለት ሰው መርከቡ ይባላል ።

«ሸሮ ገመዳ

ቢሞት አይጎዳ

ቢሠበር ዕዳ !» ይሉታል የገዛ አያቱ ።

መርከቡ የሚለውን ቅጥያ ስም የሠጡት አያቱ አባባ ኢስማኢል ናቸው ። የእግሩን ስፋት አይተው ስሙን ሠጡት ። ተንኮሉ በእግሩ ስፋት ልክ ነው ። የሊስትሮ ሳጥን የሚያካክሉ እግሮቹን መሬት ለመሬት እየጎተተ ሸር ሲተበትብ ይገርማል ። በተለይ በተለይ በለማኞች ማሾፍ ይወዳል።

ዕለታዊ ልምምዳችንን ስንጨርስ ሁሌም ከተማችንን በዙረት አካልለን ስናበቃ ነው ወደየቤታችን የምንገባው ። አዘውትረን ከምንሄድባቸው ቦታዎች ዋና ዋናዎቹ ሸዋ በር ፣ ሥላሴና



@BOOKALEM

መድኃኔዓለም ቤተ ክርስትያን ይጠቀሳሉ ። በነዚህ ቦታዎች ላይ እጅግ ብዙ ለማኞች ይኖራሉ። በተለይ የሥላሴ ቤተ ክርስትያንን የግንብ አጥር ዙርያውን በላስቲክ ቤቶች ሸፍነውታል። ወጣት፣ ጤነኛ ፣ አካል ጉዳተኛ ፣ ወንደ ላጤ ፣ ሴተ ላጤ ፣ ፈት ፣ ባለ ትዳር ፣ የተዋለዱ ፣ ከፉ ፣ ደግ... በዓይነት የበዙ ለማኞች አሉ ። ቡና ፣ ስኳር ፣ ፈንዲሻ ፣ ከሰልና ፣ ፍርፋሪ የሚሸጡትም ብልጦች እዚያው ይገኛሉ ። ያለ ቤት ኪራይና ንግድ ፍቃድ ይቸበችባሉ ።

ታድያ ለማኞቹ ለሥራ ዝግጁ ሆነው ለወጪ ወራጁ እጅ በሚዘረጉበት ሰዓት እንደርስና ባጠገባቸው እናልፋለን ። የዚህን ጊዜ መርከቡ ጠጋ ይልና እጁን ወደ ኪሱ ይሠዳል ። ሆን ብሎ ዘርዝር የሚያስቀምጣቸውን ሳንቲሞች እጁን ከኪሱ ሳያወጣ ያንቃጭላቸዋል ። ለማኞቹ ገና ሳንቲሙ እጃቸው ሳይገባ እጃቸውን ዘርግተው

« እደግ ተመንደግ ! ያሰብከው ይሙላልህ ! ገቢህን አጥፍ ያርግልህ ! ወልደህ ኩብደህ የምትስም ያርግህ ! ትምህርትህን ይግለጥልህ !» እያሉ ይመርቁታል ።

አይሠጣቸውም ። ሳንቲሙን እዚያው ይተውና አንድ ላይ የታሠሩ አሮጌ የበር መከፈቻ ቁልፎችን ያወጣል ። የቁልፎቹን መያዣ ቀለበት በጣቱ ይከትና እያሽከረከረ ፣ እያፏጨ ያልፋቸዋል ። እኛ በድርጊቱ እንስቃለን ። እነሱ ይናደዳሉ ። ስላሾፈባቸው ይረግሙታል ።

« ይድፋህ ! ይኼን አይሱዙ የገጨው ከርካሳ ጋሪ ያስመሰለህን ሸፋፋ እግርህን ጎምዶ ይጣልልህ !»

«ከሞቀ ጎጆህ አውጥቶ ከኛ ጋር በቀብር ለመቀላቀል ያብቃህ!»

« ዘርህ አይባረክ !»

« አሜን ! አሜን !» እያለ ይሄዳል ።

« ስማ መንግሥት በሸፋፋ እግር ሥራ የሚቀጥርህ እንዳይመስልህ እሺ ! ዞረህ ዞረህ እኛ ጋ መምጣትህ አይቀርም !» ትለዋለች ሌላዋ ።

መርከቡ ከዱርዬው ባንድ ታዳሚዎች ይልቅ የበለጠ ዕውቅና ያለው ዘወትር በሚያማርራቸውና በሚያቁለጨልጫቸው ለማኞች ዘንድ ነው ። ውዝዋዜ ይሠራል ። ችግሩ ግን በከበባችን የሚገኙት ሰድስቱም ተወዛዋዥ ሴቶች አብረውት አጣማጅ ሆነው ላለመሥራት አድመውበታል። ለማደማቸው ምክንያት አላቸው ። በሚጨፍሩበት ጊዜ ሸፈፍ በሚሉት እግሮቹ እየፋቃቸው እግራቸውን ገጣጥጧቸዋል ። ብዙ ጊዜም የመርከቡ አጣማጅ የሆነች ተወዛዋዥ በቅድመ ሥራ ምደባ የደረሳትን የሥራ ዝርዝር ሙሉ ለሙሉ አትተገብርም ። የመጀመርያውን ውዝዋዜ ከሠራች ቀጣዩን አትደግምም ።

«በዚህ አካፋ እግሩ የገጠበኝ እስኪድን ወደ መድረክ አልወጣም !» ትላለች ።

መርኪ ከሰዎም ብሶ ሰው ሲሳደብ ይገርመኛል ። የሚገርመው መሳደቡ ሳይሆን « ሸፋፋ!» ብሎ



@BOOKALEM

መሳደቡ ነው ። በለከፋ ጠርቷት አልመጣ ያለችውን ሴት በግጥም ይሞልጫታል ።

« ስሚኝማ ሲስተር ! ሰምተሻል...

ቢቸግር ነው 'ንጂ ምጣዱ ቢሠበር

እንዳንቺ ዓይነቱማ እግር አጣቢ ነበር !» ይላታል ። ነገር የገባት ተሰዳቢ ከሆነች ምላሽ አትነፍገውም ።

« ምን አልክ አንተ ሁለት ግራ እግር ...ምንስ የሚታጠብ እግር ቢጠፋ እንኳን ያንተን ያረጁ ማረሻዎች የማጥብ ይመስልሃል !» ትለዋለች ። ሲሰደብ አብሮን ይስቃል።

ሴቷ ስትለከፍ አብሬ ከሳቅኩ «ምን አባክ ያስገለፍጥሃል ? አንተ ካብ ራስ !» የሚል ስድብ እኔም አይቀርልኝም ።

ከመርከቡ ጋር ከተሄደ የማይገጥም ነገር የለም ። ወጪ ወራጁን በዓይኑም በአፉም ስለሚለክፍ ገጠመኝ አያጣም ። የከበባችን ሴቶች ሁሉ የጠሉት ሰው ፣ መቼም ቢሆን «ገርል ፍሬንድ አያገኝም» ተብሎ የታማው ልጅ ከሁሉም አጣማሪዎች እጥፍ የምታምር ብርከቲ የምትባል ተማሪ ጠበሰ ። ነገሩ የሆነው እንዲህ ነበር ።

አንድ ቀን እኔና እሱ ወደ ሸዋ በር ገበያ ተልከን እንሄዳለን ። ቤተሰቦቼ ያዘዙኝን ሥራ ትቼ የተከተልኩት የተቀቀለ ሚጣጢስ(ስኳር ድንች) እና ጮርናቄ እንደሚገዛልኝ ቃል ገብቶልኝ ነበር። የሚገዛልኝን እያሰብኩ ደረቁን የሳጠራ ዘንቢሉን አንጠልጥዬለት ከአስፋልቱ ግራና ቀኝ ሆነን የጨርቅ ኳሳችንን እየጠለዝን እንሯሯጣለን ። መኪና ሲመጣ በጎማዎቹ ሥር ሳይገጭ እያሾለክን ፣ ሾፌሩ በእጅ ምልክት በሳቅ እየተቆጣን ሞቢል ነዳጅ ማደያ ስንደርስ የጎዳና ተዳዳሪዎቹ ኳሳችንን ነጠቁን ። ብንለምናቸው ፣ ብንለማመጣቸው ጭራሽ ሲሞቱን ፈለጉ ።

ደሞኮ ከጎዳና ተዳዳሪዎቹ አንደኛው የምናውቀው የሰፈራችን ልጅ ነው ። ሺመከት ባዩ ይባላል ። በዘራቸው እቤት ውስጥ ያደገ ልጅ የለም ። የነሱ ዘሮች እቤት ይወለዳሉ እንጂ የሚያድጉት ጎዳናን ተከትለው ነው ። ወላጆቻቸውም ልጆቻቸውን ጎዳና እየበተኑ ሌላ ይወልዳሉ ። ሚስትየው በመውለድ ባልየው በማስወለድ ብቸኛ ሥራ ተጠምደዋል ። መውለድ እንጂ ማሳደግ የቤተሰብ ድርሻ የማይመስላቸው ባልና ሚስት ሺመከት ጎዳናን ወልደው ኳሳችንን አስነጠቁን ።

«ኳሴን ስጡኝ !» አላቸው መርኬ

«ሑንሰጥህም ! ጥፋ ከዚህ !» ያለው ሺመከት ነበር ።

«ኳሴን ካልሰጣችሁኝ የፈለገ ነገር ይመጣል እንጂ ከዚች ንቅንቅ አልልም !»

ዘንቢሉን መሬት አስቀምጬ ሁለት ተለቅ ተለቅ ያሉ ድንጋዮችን አነሳሁ ።



@BOOKALEM

«ምናባክ ልትሆን ነው ድንጋይ ያነሳሽው ?» አለኝ ተለቅ የሚለው ጥርሱ እንደ ተረሳ አንጀራ የሻገተው ልጅ ::

«እንዳትጠጋኝ ! የማመጣውን ማወቅ ከፈለግክ ደሞ ቀረብ በለኝ ::ግንባርህ ላይ ተኩሼ ቀይ ባህርን ፊትህ ላይ ነው የምደፋው !» አልኩና አፈጠጥኩበት :: ይህን ያክል ድፍረት ከየት አባቴ እንዳመጣሁት እንጃ...እራሴ መናገሬን ተጠራጥሬ ዞር ዞር ብዬ አካባቢዬን ተመለከትኩ :: የኔን ድምፅ የመሰለ ወይም ያስመሰለ ማንም አጠገቤ የለም :: ድፍረቴ ቢገርመኝ ድራማ እየሠራሁ ሁሉ መሰለኝ ::

ልጁ ፈርቶኝ ባለበት ቆመ :: መርከቡና ሺመክት በቦከስ ተፈሳፈሱ :: ልጆቹ ተረዳድተው መርኬን ወገሯት :: ከስር ሆና «ኢ...ሪ !» አለች :: ደነገጥኩ ::ልጁ ተንደርድሮ ወደኔ መጣ :: በቀኝ እጄ የጨበጥኩትን ድንጋይ ወርውሬ ወደኔ ሊያደርሰው መንገድ የሚመራውን እግሩን ቀለጠምኩለት :: ተሸመድምዶ እየጮኸ ቁጢጥ አለ ::

ያልተደገመ የፖሊስ ቆመጥ ቂጤ ላይ አረፈ :: ከየት እንደመጡ ያላየኋቸው ፖሊሶች እኔንም መርኬንም አዳኑን :: ሁላችንንም አንበረከኩን :: ምክንያታችንን ተናገርን :: ኳሳችንን እንዲመልሱ ሲጠየቁ ቀደም ሲል ወደ ኮምቦልቻ እየሄደ በነበረ የጭነት መኪና ላይ እንደሰቀሉት ተናገሩ :: ፖሊሶቹ ኳሳችንን የወረወረውን ልጅ በተለይ ቀጠቀጡት ::

ሰዉ ተሰበሰበ :: መርኬ «ብር ጠፍቶብኛል ፤ ከኪሴ ውስጥ አሰር ብር ወስደውብኛልና ይመልሱልኝ!» ሲል ጮኸ ::

ደነገጥኩ :: ልጆቹም ሲነቃባቸው ከው አሉ ::ባዶ ዘንቢል ይዘን ወደ ቤት ከተመለስን የመርኬ ቤተሰቦች ምን እንደሚሉን እንጃ ::

ፖሊሶቹ ሁላችንንም ኪሳችንን ፈተሹ :: ከኔ ኪስ ውስጥ አስራ አምስት ሳንቲምና አራት ሽራፋ ብዮች ወሰዱ :: ከሺመክት ባዩ ኪስ ደሞ ድፍን አስር ብር ተገኘ :: «የራሴ ነው» እያለ ቢጮህም ሲባነቱን እየነገሩትና እንዲያምን እያስገደዱት ቀጠቀጡት :: እንባው በአራት መዐዘን ተንቆረቆረ። መርኬ ብሯን ተቀብላ ዘንቢላችንን አንስተን ወደ ሸዋ በር ሄድን :: ድንች ፤ ሽንኩርት፣ ቃርያና ጨው ገዛንና ዘንቢላችንን ለሁለት ጎን ለጎን አንጠልጥለን ፣ ሚጣጢሳችንን እየነፋን የሰፈራችንን መንገድ ጀመርነው ::

ሠፈር ከመድረሳችን በፊት ደሴ ሆቴል ጋ የትሩማን ትሪ ዛፍ ጥላ ሥር ቁጭ አልን :: መርኬ አሮጌ አስር ብር አወጣና «እንካ አሽትተው !» አለኝ ::

አፍንጫ የሚቆርጥ ሽታ :: ምራቄን ደጋግሜ ተፋሁ :: ሽታው ሆዴን አጥወለወለው ::

«ከየት ነው ያገኘሽው ?» ስል ጠየቅኩት ::

«አይ አርቲስት ጭንቅሎ...እንቺኮ መቀለድ ብቻ ነው የምታውቂው ::»



@BOOKALEM

«እንዴት ?»

«ይቺ ብር የማን ትመስልሻለች ?»

«የቤተሰቦችህ ናታ !»

«አይደለችም ...ሌላ ገምች ::»

«ኢ...ትዝ አለችኝ :: የራስህ ...ኢ...በቀደም ውዝዋዜ ስትሠራ የተሸለምካት !»

«ተሳስተሻል ጭንቄ...የሺመከት ጎዳና ብር ናት ::»

«እንዴት የሱ ሊሆን ይችላል ?»

«ቆይ ! ስታሸሺው ምን ምን አለሽ ?»

«አር አር ነዋ ! ከሽንት ቤት ነው እንዴ ያወጣኸው ?»

«አይደለም ባክህ ! ቅድም'ኮ ከቤት የተሰጠኝን ብር ቂጤ ውስጥ ከከሬ ነው ሳይጠፋብኝ ጠፋብኝ ያልኩት ::»

«ማርያምን በል እስቲ !» አልኩት መዳፌን ዘርግቼለት ::

መዳፌ ላይ የመስቀል ቅርጽ ሠርቶ ማለልኝ :: ቤተሰቦቹም እሱም ሙስሊሞች እንደሆኑ ባውቅም በማርያም ሲምልልኝ አመንኩት :: ለነገሩ እሱም አንዳንዴ «ወላሂ !» በል እስቲ ብሎ ሲያስምለኝ እምልለታለሁ ፤ ያምነኛል ::

«ግን ጨካኝ ነህ :: እነሱ ለምነው ያመጡትን አልቅስህ ታስቀማቸዋለህ ? ጊዮርጊስን ግፍ ነው ::»

« እና ታድያ የእንቁጣጣሽ ከበሮ መስልኩህ በነፃ የሚቀጠቅጡኝ !» አለኝ ::

በመርኬ ብልጠት ተደንቄ እየሳቅኩኝ ሳለ አንዲት በጋራ የምናውቃት ቆንጆዬ የሸንኮር ልጅ መጣች :: የሀብታም ልጅ ነች :: ብርከቲ ትባላለች :: በማልታውያኑ ካቶሊኮች በተቋቋመው ማልቴዝ ትምህርት ቤት ትማራለች :: እኛ በትክክል ለማንሰማው ፣ ለማናነበው ፣ ለማንፅፈው እንግሊዝኛ ቤተሰብ ነች :: ጥሎባት ሙሉ አማርኛ አታወራም :: የምንረዳት እንግሊዝኛዋን ተከትለው በሚመጡት ትራፊ የአማርኛ ቃላቷ ነው :: መርኬን ቂጧ እስኪቃጠል ትወደዋለች። እሱ ግን ለሷ ከጥላቻ የተሻለ ስጦታ የለውም ::

«ሃይ !» አለችን ቅንድቦቿን ወደ ግንባሯ አቃንታ :: ከዚያ በቀኝ ዓይኗ ድብን አድርጋ ጠቀሰችው ::

«ሂጂና የጎረቤታችሁን አህዮች ‹ሃይ› በያቸው እሺ !» አላት ::



@BOOKALEM

ተንከትክታ ሳቀች ::

«Alright ! በስምህ ‹ሃይ› እልልሃለሁ :: ይልቅስ ሰዓት ከያዝክ ንገረኝ ::»

ዝም አላት ::

«እያናገርኩህ አይደል እንዴ ...ሰዓት ይዘሃል ወይ?»

«አዎ ! ይዣለሁ ::»

« ስንት ሆኗል ?»

«ምኑ ?»

«ሰዓቱ ነዋ ! ጊዜው :: መቼስ ነጋዴ አይደለህ ዋጋውን የምጠይቅህ ::»

በዝምታው አበገናት ::

«Oh My God ! ንገረኝ እንጂ :: እየጠበቅኩህ አይደል እንዴ ?»

«ምኑን ልንገርሽ ?»

«ስንት ሰዓት ሆኗል ?»

«ሰባት !»

«ሰባት ሰዓት ብቻ ? ደቂቃ ምናምን የለውም ?»

«አለው ::»

« እና ሙሉውን ንገረኛ ::»

«አንቺ መች ሙሉውን ጠየቅሽኝ :: ሰዓት አልሽኝ ሰዓቱን ብቻ ነገርኩሽ ::»

«ውይ መርኬ...ምን ዓይነት አድከም ነህ በናትህ ! እሺ ስንት ሰዓት ፣ ከስንት ደቂቃ ፣ ከስንት ሰኮንድ ሆነ ?» ወገቧን ይዛ ፊት ለፊቱ ቆመች ::

የግራ እጁን ወደ ዓይኑ በጣም አስጠግቶ ዓይኑን አንሸዋርሮ ተመለከተና «ሰባት ሰዓት ከአስራ ሰባት ደቂቃ ፣ ከአስራ...» አለና ሰኮንዱ ሲሮጥበት ተወው ::

« እሺ ! አንተም ሙሉውን ንገረኛ ::»

«አቦ ምን ትጨቀጭቂኛለሽ ሳ ! ነገርኩሽ አይደል እንዴ ?»

« እህ ሰኮንዱስ ?»



@BOOKALEM

«ቁንጫ ይያዛል ?»

«What ? የምን ቁንጥጫ ?»

ሳቅንባት ::

«ሂጅ ! ቁንጫና ቁንጥጫን የማትለዩ...ደሞ አንቺን ብሎ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ! የሀገርሽን ሀብት ሳትለዪ ነው እንዴ አይችሉም ብለሽ በእንግሊዝኛ የምታዋክቢን !» አለመጠባት ::

«ቀልዱን ተውውና መርኪ ...ቁንጫ ምንድን ነው ?»

«ቁንጫ አታውቂም ?»

« I swear...ቁንጫ አላውቅም :: Do you mean ቁንጥጫ ?»

« ተይ እንጂ !!መናይ ! አይሻልሽም ፍጥጫ ፣ ወይስ ይቀየርልሽ በግልምጫ ?»

ሳቅንባት :: ቁንጫ ባለማወቋ ተገረምን :: ፊቷ ሳይ የነበረው ፈገግታ በግራ መጋባት ተተክቷል ::

«እሺ ! ትኋንስ ታውቂያለሽ ?» አልኳት ::

«Oh Lord ...ኧረ እኔ አላውቅም በናታችሁ ::»

«ከምን ዓይነቷ ጤባ ጋ ነው የምናወራው ጭንቅሎ !» ሲለኝ በጣም ሳቅኩኝ ::

የሀብታም ልጆች በሙሉ ቁንጫና ትኋን አያውቁም ጤባዎች ናቸው ብዬ ደመደምኩ ::

«መርኬ please ንገረኝ !»

« ደሞ ምን ቀረሽ ? ምን ልንገርሽ ?»

«አሁን ስለጠራሃቸው ነገሮች ምንነት ነዋ ::»

«ኢ...ስለ ቁንጫና ትኋን ?»

«Yeah !»

«ኪጅ ወደዛ ባከሽ ! ምን እንደ ካራቲስት ያ ያ ትይብናለሽ !»

«Ok ! በናትህ ንገረኝ ::»

«እንዲሁ በቃል የሚነገሩ ነገሮች አይደሉማ ::»

«So , እንዴት ነው ማወቅ የምችለው ?»



@BOOKALEM

«ልብስሽን አወላልቀሽ እኛ መደብ ላይ መተኛት አለብሻ !»

«Wow ! መርኬ...አግኝቼክ ነው...ካንተ ጋ ከሆነ እንኳን ልብሴን ቆዳዬን አወልቃለሁ እሺ !» ብላው በረጅሙ ሳቀች ::

ለወሬዋ እፍረት ተሰማኝ ::

በዚህ ሁኔታ ተግባብተው ባገኘችው ቁጥር ገንዘብ እየሰጠችው መርከቡን ጠበሰችው :: ማታ ማታ እየተገናኙ አብረው ሲዞሩ ያመሻሉ :: ጨለምለም በሚለው ሠፈር ውስጥ እሷ ወገቡን እሱ አንገቷን ተቃቅፈው «ዎክ» ይበላሉ ::

«ቺስታው መርኬ የሀብታም ልጅ የሆነችውን ብርክቲን ጠበሳት !»ተብሎ በሠፈራችን ተወራለት:: እኔ በማውቀው መረጃ መሠረት ግን መርኬ ጠባሽ ሳይሆን ተጠባሽ ፣ ገዳይ ሳይሆን ተገዳይ ነው :: ተፈቃሪ አማተር አርቲስት :: ከዱርዬው ባንድ መድረክ የተገኘ ተፈቃሪ ተወዛዋዥ::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ ሃያ አንድ

## ኤልፓ

የሰማይዋ ፀሐይና እሷ አንድ ናቸው ። ሁለቱም በጠዋት ከቤታቸው ወጥተው ካልመሸላቸው ወደ ማደርያቸው አይመለሱም ። ለሀገር ውስጥ ቋንቋዎች የታደለ ምላስ አላት ። አማርኛ ፣ አደርኛ ፣ አርጎብኛ ፣ኦሮምኛና ሱማልኛን አጣርታ አዳምጣ አጣፍታ ትናገረዋለች ። ከአማርኛና አደርኛ በስተቀር ግን ተንገዳግዳም ቢሆን የምታነበው ቋንቋ የላትም ። እርሳስና እስክርቢቶ ጨብጦ መጻፍን ሁሉም ቋንቋዎች ላይ አልታደለችም ። ስታወራ «Ok !» የሚል የእንግሊዝኛ ቃል በብዛት ትጠቀማለች ። ወደ ሦስተኛ ክፍል ከተሻገረች በኋላ የትምህርት ቤትን ደጃፍ ረግጣ አታውቅም ። ከቤተሰባቸውም ከፍተኛ የከፍል ደረጃ ያስመዘገበችው እሷ ናት ። መደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው ፊደል ባልቆጠሩ ዘመዶች ተከብባለች - አዚዛ አብዱልዋሲ ።

እልም ያለች አጭበርባሪ ናት ። ስታምታታ ዕድሜና ጾታ አትለይም ። ተላላኪ መስላም ሆነ ጤንነት ጠያቂ አጋጣሚ ጠብቃ በእጇ ያስገባችውን ገንዘብ ይዛ ከሰፈር ትሰወራለች ። ብዙ ጊዜ ወደ ጀይላን አብዱልቃድር የአምልኮ ስፍራ ትኮበልላለች ። ጀይላን አብዱልቃድር ከሐረር ከተማ በግምት አስራ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ገጠራማ መንደር ውስጥ ይገኛል። በተለይም ሐረር ቢራ ፋብሪካ ሶፊ ለተባለው ከአልኮል ነፃ የሆነው መጠጡ መጥመቂያ የሚጠቀምበት ውሃ መገኛ ሥፍራን ተሻግሮ ይታያል ።

ያታለለችውን ብር አውድማ ስትጨርስ ከሳምንትም ሆነ ከወር በኋላ ትመለሳለች ። ያጭበረበረችው ነዋሪ በተሰበሰበበት መንደር የሌብነት ዓይኗን በጨው አጥባ ስትመጣ አታፍርም ። የሚሠነዘሩባትን የስድብ ፣ ርግማንና ዱላ ውርጅብኝ ተንጂዎችን በሚያበሳጭ ገጽታ ትቀበላለች ።

ለነገሩ አዚዛ የሰፈሬ የቀላድ አምባ ልጅ አይደለችም ። ወደ ጀጎል አከስቴ ጋ ስሄድ የማውቃት ከአርጎባዊት እናትና ከአደሬ አባት የተገኘች አጣቢ ናት ። በዕድሜ እኩዮቿ ሆኑ አልሆኑ ሊታጥባቸው ከፈለገች ተለሳልሳ ትቀርባቸዋለች ። ለአከስቴ ልጅ ለሰላም ግርማ በጣም የቅርቧና የሠፈሯ ልጅ ነች ። ሰላም መሳቅ ስለምትወድ ምሳዋን ለአዚዛ ሠጥታ በቀልድ ትቀይራታለች። ፈገግታዋን ተከትሎ የሚመጣውን ስርጉድ ጉንጯን ለማየት ሁሌም ሳቋን እናፍቃለሁ። በዘራችን ሥርጉድ ጉንጭ ያልታደለ አንድ ሰው ብቻ አለ ። የእናቴ ታናሽ ወንድም ፣ የኔና የሰላም አጎት ፣ የመጽሐትና ለፀሎት አባት የሆነው ይነበብ ዘላለም ።

አዚዛ የሆነ ነገር ስትፈልግ ትህትና ትጨምራለች ። የማታከብረው የዕድሜ ደረጃ የለም ። የፈለገችው ነገር በጇ ከገባ በኋላ ግን ዞር ብላም አታያቸው ። ለበርካታ አማወራዎች የመብራት ወርሃዊ ክፍያ ለመፈፀም የመከፈያ ደረሰኝና ገንዘብ ከየቤቶቹ ሰበሰበች ። ትባረከ ዘንድ



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

እየመረቋት ፣ ሲጎርሱት ካሰናዱት እያጎረሱ ፣ ከሚጠጡት እያስጎነጩ ሆድና ኪሷን ሞልተው ወደ ሙብራት ኃይል (ኤልፓ) ሸኟት ። ብትጠበቅ ብትጠበቅ አትመጣም ።

ብዙዎች እናቷ ቤት ድረስ እየሄዱ ፈለጓት ። የውሃ ሽታ ሆነች ። መንደርተኞቹ ተራ በተራ እናትየውን የውርደት ካባ አከናነቧት ። አዚዛን «አየሁ» የሚል ታጣ ። መብራት ኃይሎችም ለመቁረጥ የሚጣደፍ ሞያተኛ እጃቸውን ይዘው ከተፍ አሉ ። መንደርተኛው ጮኸባቸው ። ታዛገሮቹ የድርጅቱ ሠራተኞች ከአዚዛ ሰለባዎች ጋር ተጣሉ ። በፖሊስ ታጅበው ተልዕኳቸውን የፈፀሙት ሠራተኞች መንደሬውን በጨለማ አሳደሩት ። በድቅድቅ ጨለማው ሲበሳጭ ያደረው ሕዝብ ንጋቱን ተከትሎ ወደ ድርጅቱ ተመመ ። ሕዝቡ ሲመለስ ግን የከፍያ ደረሰኝ ብቻ አልነበረም የጨበጠው ። ለአዚዛ አብዱልዋሲ የሚሆን ያለ ተጨማሪ የአባት ስም ብቻውን ሙሉ የሆነ አዲስ ተቀያሪ ስምም እንጂ – « ኤልፓ » ።

« ኤልፓ » በሐረር ከተማ ውስጥ ገናና የልጅ አጭበርባሪ ነች ። በተለይም ሕዝቡን በጨለማ ካሳደረች በኋላ እሷ አንገቷን ባትደፋም አንገት የሚያስደፉ በርካታ ክስተቶች ግን ተፈፅመውባታል ። ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር እንዳትውል አግልለዋታል ። ሌላው ቀርቶ ከኤልፓ ጋር ሲጫወት የተገኘ ልጅ « የኤልፓ ግብረ አበር ፣ ትንሹ ኤልፓ ፣ ኤልፓ ቁጥር ...» የሚሉ ቅፅል ስሞች ይለጠፉለታል ። ይህ ታርጋ የተለጠፈለት ልጅ ደሞ ከሌሎች ልጆች ጋር መቀላቀል ስለማይፈቀድለት መነጠል አማራጭ አልባ መሸሸጊያው ይሆናል ።

« ኤልፓ » እንደ ኤሌትሪክ ነች ። ማግኘት የፈለገችውን በጁ ለማስገባት ማዘናጋት ብቻ በቂዋ ነው ። እንደ ኤሌትሪክ ፈጣን በሆነው ንዝረቷ ስትሞጨልፍ ትገርማለች ። ዓይን በዓይን እያይዋት ሞጭልፋ « አላየሁም » ካለች አላየችም ። መሀላ ፣ ዱላ ፣ ዛቻ ምናም አይደሉም ። ፖሊስ መጣ ቀበሌ ፣ እናቷ ሆነች አከስቷ በአዞ እንባዋ ታሳምናቸዋለች እንጂ ሃሳቧን አትቀይርም ። የማጣራት ሒደት አብቅቶ ፣ ድርጊቷ ሳምንት አስራ አምስት ቀን ካለፈው በኋላ ግን እውነታውን እየሳቀች ትነግረናለች ። ስንቱን ያስለቀሰችበትን በዳይ ገመናዋን እየተፍነከነከች ትተርከልናለች። በፈገግታ ታጅበን ፣ አፋችንን ከፍተን እናዳምጣታለን ።

ወሬዋ ተመችቶን አቀብቁበን ቀጥሎ ያደረገችውን ለመስማት መጓጓታችንን ስትረዳ ትረካዋን ትቀጥላለች ። ልባችን ለወሬዋ ሲንጠለጠል ደስ ይላታል ። ልባችን ለወሬዋ ከተንጠለጠለ እጃችን ላይ የሚገኘን ማንኛውም ነገር ለመረከብ ዕድል ታገኛለች ። በተለይ ብስኩትና ዳቦ በማር አከስቴ ቤት ስለማይጠፉ ብዙ ጊዜ እኔንም ሰላምንም በፀባይ ትቀማናለች ። የሚበላ ነገር ካጣች አፋችን ውስጥ ባለና በምናኘከው ማስቲካ ትመጣብናለች ። በተለይ የሚነፋው ማስቲካ ከሆነማ « ዛሬ በጣም የሚያስቅ ፣ ቶሎ በትኩሱ መነገር ያለበት አሪፍ ወሬ ይገፎላችኋለሁ ። ማስቲካችሁን ስጡኝና ልንገራችሁ ! » ትለናለች

ሁለታችንም ማስቲካችንን ከአፋችን አውጥተን ቆሻሻ መዳፏ ላይ እናስቀምጥላታለን ። ከአፋችን ያፎጣነውን ማስቲካ በልብሷ ትጠራርግና ጉ...ርስ ታደርገዋለች ። ወሬውን ሳትነግረን ማስቲካችንን አፍንጫችን ሥር ነፍታ እያፈነዳች ፣ በመዐዛው እያወደች ታቁለጨልጨናለች።



@BOOKALEM

መዐዛው ሲያውደን ፣ ወሬውን « ለነገ » ብላ ስታሳድርብን ፣ ማስቲካችንን እንድትመልስልን እንለምናታለን :: እናለቃቅሳለን :: እሷ ግን ታሾፍብናለች :: የሁለታችንን ማስቲካ አንድ ላይ ጨፍልቃ ስለበላችው « ተቀላቅሏል መመለስ አልችልም » ትለናለች :: ሲያሻት ደሞ «ቢላዋ ወይም ምላጭ አምጡና እኩል ቆርጬ ላካፍላችሁ» ብላ ታላግጥብናለች ::

ወሬውን በእንጥልጥል ይዛው እያቁለጨለጨች ዳቦ በማር ሠርቀን እንድናመጣ ትልከናለች። ዳንቴል ተሸፍኖ ሠፌዱ ላይ የተቀመጠው ዳቦ ያልተቆረሠ ከሆነ ሳይፈቀድልን መንካታችን ቁጣ ስለሚያስከትልብን ከቀለጠው ማር ብቻ ዝቀን በፌስታል ጠቅልለን እናቀብላታለን :: ማሯን ልክክ አድርጋ ልሳ ፣ ፌስታሉን ከመጋጥ ባልተናነሠ አፅድታ ስታበቃ ማንም ሳይጠራት የውሽቷን « አቤት ! እየመጣሁ ነው ! » ብላ ካጠገባችን ትሠወራለች :: ይህ የ«ኤልፓ» ድርጊት ለሰላም ሳቅን ለኔ ሊልህና ብስጭትን ያጎናፅፋል :: ምክንያቱም በመከራ የማገኘውን ማር አጭበርብራ እየበላችብኝ እንዴት ልታገሳት?

« ኤልፓ » የቀላድ አምባ ልጆችን አትወድም :: እኔንም ያቀረበችኝ የሰላም ዘመድ በመሆኔና እንደፈለገች ስለምሸወድላት መሠለኝ :: ጠይሚንና ጠምቤንማ ለዓይናም አትፈልጋቸው :: እንኳን ልትሸውዳቸው ድንገት እግር ጥሏት ወደኛ ሠፈር ከኼደች መንገዷን ዘግተው የያዘችውን ታግለውም አስቦከተውም ይቀበሏታል ::

ጠምቤን « ድዊ !» ትለዋለች አጭርነቱን ስታጎላበት :: እጥረቱንና ሁሌም ከቂጡ ላይ የማይጠፉትን የሱሪ መነፅሮች እያስታከከች ደሞ

« ጠምቤ ኩሩሩ

ባለ መነፅሩ

ሚስቱ ኤልሳን ሲያያት

መደነባበሩ

ሲጨልም ሲጨልም

አቅፏት መሽከርከሩ...» ትለዋለች ::

ይናደዳል :: ጠምቤ « የኤልሳ ሚስት ! » የሚለውን ሰው አይወድም :: ኤልሳ የክፍላችን ልጅ ነች :: አፍንጫዋ በንፍጥ ግግር ምክንያት ሁሌም የሚደፈን ፣ ስትተነፍስ እንደ ድመት ኩርኩር የምትል ፣ መሀረቧ የአስተማሪ ዱላ የሆነ ፣ ባለ እርጥብ አፍንጫ ዝርክርክ ልጅ ነች። ጠምቤ በጣም እንደሚጠላት ስለምናውቅ « የኤልሳ ሚስት ! » እንለዋለን :: ያሯሩጠናል :: መሮጥ ስንፈልግ ስለሆነ የምናበሽቀው ሲያሯሩጠን ደስታችን እጥፍ ይሆናል :: ይህንን ገመናውን ለሰላም ስነግራት ነበር « ኤልፓ » የሠማችው ::

ጠምቤ ድንጋይ አንስቶ ሊጨረግዳት ሲል ትለምነዋለች :: « ኤልፓ » ድንጋይ ትፈራለች።



@BOOKALEM

ድንጋይ ሲያነሱባት መሬት ተቀምጣ ፊቷን በጉልበቶቿ መሀል ደብቃ የልመና መዐት ታዥጎደጉዳለች ። እንዲህ የምታደርገው ኪሷ ውስጥ ምንም ከሌላት ነው ። የሆነች መሸወጃ ከሠነቀች ግን ገና ድንጋይ ሲያነሳባት « ይህንን ካልፈለግክ ወርውር ! » ትለዋለች ሳንቲም ወይ የሚበላ ነገር እያሳየች ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ እየሠደበችው እየከፈለችው ትቆይና ትልቅ ሰው በሱ አቅጣጫ ሲመጣላት ጠብቃ « እሪ !» ብላ ትጮሀለች ። ለስድቧ የከፈለችውን አስኮርኩማ ታስቀማዋለች ።

ጠይሜን ግን የምትጠላው ትመስላለች እንጂ ትወደዋለች ። ሰው ሲመታው እንኳን ከሱ ቀድማ ነው የምታለቅስለት ። ጠይሜንም ታበሽቀዋለች ። አከስቴ ግቢ ውስጥ ከጓሮ ካለው ሳር ላይ ተሰብስበን እየተጫወትን ሳለ እንዲህ ተባባሉ ።

« ቆይ አንተ ግን ትክክለኛ ስምህ ማነው ? »

« ጠይሜ ! »

« ጠይሜ ምን ማለት ነው ? »

« እህ ! ጠይሜማ ጠይሜ ነዋ ! »

« በስምህ ግን ደስተኛ ነህ ? »

« አዎና ! »

« አላህ ! እንዴት ሰው በእንዲህ ዓይነቱ ስም ደስተኛ ይሆናል በናታችሁ ! »

« በቃ ይሆናላ ! በዓለም ላይ በዚህ ስም የምጠራው እኔ ብቻ'ኮ ነኝ ። ስለዚህ ደስተኛ መሆን የለብኝም ?» አላት በኩራት ።

« ኡኡቴ ! »

« ምነው ኡኡቴ አልሽ ... እስቲ ሌላ ጠይሜ የሚባል ፈልገሽ አገናኚኝ ! »

« ሞልቷል ባከህ ! »

ወሬያቸው ተመችቶን እያዳመጥናቸው ነው ።

« እኮ ከሞላ ጠርተሽ አስተዋውቂኝ ! »

« መተዋወቅ ትፈልጋለህ ? »

« እንከት ! »

« ምን አሪፍ ስም እንዳለው እንከት ፣ ፍንከት ትላለህ ። ይኼ ስም ካላቸው አንተ ብቻ'ኮ ነህ ሁለት እግር ያለህ ! »



@BOOKALEM

« ኧ !...እንዴት ?»

« ምን እንዴት ትላለህ ? ይኼ ስም ካላቸው የምታወራው ፣ እንጀራ በወጥ የምትበላውም አንተ ብቻ እንደሆንክ አታውቅም ? ይገርማል !»

« አልገባኝም !»

« ለነገሩ እንዴት ይገባሃል :: ምከሺዎችህኮ ሳር እየጋጡ ፣ ፋንድያቸውን በየሜዳው እያንጠባጠቡ ፣ ፈሳቸውን እያንዛረጡ የሚኼዱ አህዮች ናቸው::»

« አህዮች !»

እኛ ሳቅንበት :: ተናደደ :: የአፈር ድንጋይ አነሳ ::

« ጠይሜ የአህያ እንጂ የሰው ስም አይደለም ብለሽ ጓደኞቼ ፊት ታዋርጂኛለሽ ?»

«አዎና ! እውነቴን እኮ ነው:: ጠይሜ የአህያ እንጂ የሰው ስም አይደለም!»

አልፈራች አላፈረች በአዎንታ ራሷን ነቀነቀች ::

ጠይሜ የአፈር ድንጋዩን ጥሎ ምን የሚያክል የጉልቻ ስባሪ አነሳ :: « ኤልፓ » ሰላም ስር ተደበቀች :: ድንጋዩን ለመወርወር እየቃጣ እሷም በግራ በቀኝ ለሽወዳ ብቅ ጥልቅ እያለች ፣ እንደ መከላከያ ግድግዳ የተጠቀመችባትን ሰላምን እያንገላታች

« ጠይሜ በአላህ ይሁንብህ ... የሆነ ነገር እሠጥሀለሁ እንዳትመታኝ ! » አለችው ::

« ምንም እንድትሠጪኝ አልፈልግም :: እንዲህ ሰድበሽኝማ አልለቅሽም !» እያለ ፎከረ ::

በመጣጣ ፊቱ ላይ የደም ስሮቹ ተገታትረው ፣ ዓይኖቹ ተጉረጥርጠው አፉ እንዳያፈስ በዛፍ ልጣጭ የታሸገ ቀጭን የከሰል ጆንያ መሠለ ::

በመጨረሻ በምትሠጠው ነገር ተስማሙ :: ንዴቱ በውስጣዊ ደስታ እየተለወጠ ሲሄድ ፊቱ ላይ ያስታውቅበታል :: ዓይኖቹን እንዲጨፍን አዘዘችው :: ሰላምን መሀላችን አድርገን እኔና ጠምቤ ቆመናል :: የሰላምን ፈገግታ ተከትሎ በግራና በቀኝ ያጀቧት የጉንጯ ስርጉዶች ምን ያህል እንዳሳመሯት ከኔ ከወንድሟ በቀር ያየላት የለም ::

ጠምቤ « ኤልፓ » ለጠይሜ ልትሠጠው ያዘጋጀችውን ነገር ለማየት ጓጉቷል :: አስር ጊዜ እንደ ቀጭኔ አንገቱን እያሰገገ ሁሉን በርቀት ለማየት ይጣጣራል :: ጠይሜ ጉልቻውን እንደጨበጠ ሽልማቱን ለመቀበል ይጠብቃታል :: ስትጠጋው ሊፈነክታት እንደሚችልም ጠርጥሬያለሁ:: ከሠፈራችን ስንመጣም ከሦስት አንዳችን ሰበብ ፈልገን እንደምንፈነክታት ተነጋግረን ነበር:: ጠይሜ ግን ዕድለኛ ነው ቡድስ ሊያደርጋት ፊቱ ቀርባለታለች :: ከዚህ በፊት ሰው ፊት ለፊት በጉልቻ ሲፈነክት አይቼ ስለማላውቅ የ«ኤልፓ » ደም ከግንባሯ ጢን ሲል ለመመልከት ጓጓሁ::



@BOOKALEM

« ቶሎ በፈነከታትና የምትሆነውን እያየሁ በሳቅኩ » አልኩ በልቤ ::

«ኤልፓ» በእጇ ምንም ነገር ሳትይዝ ተጠጋችው :: ዓይኖቹን ከገለጠ ምንም እንደማትሠጠው፣ እያስጠነቀቀችው ቀረበችው :: በጣም ተጠጋችው :: በተጠጋችውና አንድ እግሯን ባንቀሳቀሰችው ቁጥር « ከገለጥክ ይኼን የመሠለ ውድ ነገር እንዳታጣው ፣ ዋ ወላሂ እንዳትገልጥ !» ትለዋለች ::

እግሮቹን ለመርገጥ ፣ እጆቹንም ለመያዝ አንድ እርምጃ ያክል ብቻ እንደቀራት ጠይሜ የጉልቻ ስባሪውን ሊወረውር እጁን አቀባበለ :: ሁላችንም ደነገጥን :: በሃሳቤ « ኤልፓ » ተዘርራ አየኋት:: ሰላም ጮኸች :: ዓይኖቼን ስገልጥ « ኤልፓ » ጉንጮቹን በሁለት እጆቿ ደግፋ የጠይሜን ከንፈር በከንፈሯ ትስማለች :: በእጁ የያዘውን የጉልቻ ስባሪ ለቀቀው :: ጉልቻው ከጫማ ያልተዛመደ፣ በቀጭ የሻከረ ከርዳዳ እግሩን ደቆሠለት :: ያቺ ደስታው በእግሩ ሕመም ሳቢያ ወደ ሀዘን ተለወጠች::

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሠብብ ፈልጋ እያበሸቀችው «ዓይኖችህን ጨፍን !» እያለች ትስመዋለች:: ያልፈለገ እየመሠለ ፣ ስለ ተሳመ እንደደበረው እያስመሠለ በከንፈሮቿ ለመዳበስ ሁሌም በሩን ይከፍትላታል :: እሱ ወደ ጆኅል ካልመጣ እሷ ቀላድ አምባ ትሄዳለች :: ዘመዶች አላት:: የአባቷ ታላቅ ወንድምና ጠይሜ የ«ኤልፓ» የቀላድ አምባ ማረፊያዎች ናቸው :: ቀላድ አምባ ላይ ያሉት ተቀባዮቿ አጎቷ ጉንጯን ጠይሜ ከንፈሯን እየሳሙ ያስተናግዷታል :: አጎቷ አገር እያየው ጠይሜ እሷ ብቻ እያየችው ይስማታል ::

የ«ኤልፓ» ጉድ ብዙ ነው :: እንዲያውም ስለሷ ከተነሳ ጉዷ ልጓም ስለማይኖረው «የኤልፓን ነገር ወዘተርፈ ብለን ካልተውነው አያልቅም :: በያንዳንዱ አዳዲስ ቀን አንድ አንድ አዳዲስ ጉድ አስመዝግባ ታድራለችና» ይላሉ በጥልቀት የሚያውቋት :: እኔ ግን ቢያንስ አንድ ጉዷን ጨምሬላችሁ ነው «ወዘተርፈ ...» ብዬ የማበቃው ::

የማይደበቅ አንድ ነገር አላት :: «ኤልፓ» ቆንጆ ናት :: በተለይም የአደሬዎችን ባህላዊ መዋቢያ ቁሳቁሶችን አድርጋ ለተመለከታት ትንሽዬ ጠይም ንግስት ነው የምትመስለው :: እናም አንድ ቀን ከአዲስ አበባ ለመጡት ሁለት ሰዎች ጆኅልን አስጎብኚ ሆና ቀረበች :: ሰዎቹ ከሃሳቧ ይልቅ ለውበቷ ተማርከው «ኮድ-04» መኪናቸውን መድኃኒዓለም ቤተ ክርስትያን ፊት ለፊት ከሚገኘው ወሰን ሰገድ ሆቴል ደጃፍ አቁመው በመጋላ ጉዶ (የገበያ ቦታ ነው) በኩል ወደ ውስጥ ዘለቁ ::

በገበያው ውስጥ የሚገኙት አንጥረኞች የሚሠሩትን እያስጎበኘች ሠሪዎቹን በአደርኛና ኦሮምኛ እያዋራች ለአዲስ አበቤዎቹ ደም ጥርት ባለ አማርኛ እየተረጎመች የአስጎብኚነት ደረጃዋን ከፍ አደረገች :: ሰዎቹ በጣም ተገረሙባት :: ሃያን ባልተዳፈረ ዕድሜዋ ያካበተችው የቋንቋና የገለፃ ብቃት ተደናቂነቷን አጎላላት :: ገበያ ውስጥ ያሉትን ተጎብኚ ነገሮች ከጨረሰች በኋላ ግራዋን ይዛ ቁልቁል አመራች :: ብዙም ሳትርቅ ከአንድ ቦርቃቃ መስኮት ካለው ሱቅ ደጃፍ ደረሡ :: ቆብ ከጭንቅላታቸው የማይለየው የሼከ በድሪ ሱቅ ::



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

በሱቁ ውስጥ ያሉትን የአደሬዎች ቤት ማስጌጫ ቁሳቁሶች ሲመለከቱ እንግዶቹ ተገረሙ። በጥቁር መደብ ላይ እንደ አልማዝ በሚያንፀባርቁ ትናንሽ ጨሌዎች ያጌጡትን ቁሶች ወደዷቸው። የአበባ ማስቀመጫዎቹን ፣ የፊት መስታወቶቹን ፣ የጌጣ ጌጥ ማስቀመጫ ሙዳዮችን ተከየፉባቸው። በያንዳንዱ ቁስ ውበት ተደነቁ ። ዕቃዎቹን ከመግዛታቸው በፊት ጌጣ ጌጦቹ ግድግዳ ላይ ሲሰቀሉ ውበታቸው ምን እንደሚመስል ለማሳየት በሚል ሰበብ ወደ ሼኩ በድሪ መኖርያ ቤት አስፈቅዳ ጎብኚዎቿን ይዛ ገባች ። አሮጊቷ የሼኩ ሚስት ኡማ ዱንያ ቤታቸውንና ጌጣ ጌጣቸውን ለ«ኤልፓ» አሳልፈው ሰጡ ። «ኤልፓ»ም የአንገት ሀብሎችን ፣ ከንድ ላይ የሚጠለቁ ሸዋሊያዎችን ፣ የጣት ቀለበቶችን ፣ ግንባር ላይ የሚታሠሩ የወርቅና የብር ጌጣ ጌጦችን እንደ ልቧ ለሙከራ እያጌጠችበት በጎብኚዎቿ ካሜራ ብዙ ፎቶዎችን ተነሳች ።

እንግዶቹ ጉብኝታቸውን እንደጨረሱ ጫማቸውን አውልቀው ዙርያውን በትራስ ከታጠረው ቀይ ቀለም የተቀባ መደብ ላይ እንዲቀመጡ ተደረገ ። ኡማ ዱንያና «ኤልፓ» እጅግ በጣም ጣፋጮቹን የአደሬዎች ምግቦች ሀለዋ ፣ መለዋ ፣ ቁሬማ ፣ ሙሽበክ ፣ ፎልፎሌ ፣ እንዲበሉ ጋበዟቸው ። ቆራሱማ ከተደረገ (በወይራ ከታጠነ) ቅል ውስጥ ጥሬ የላም ወተት በጌባ (ከቅል የተሠራ ኩባያ) አቀረቡላቸው ። የማይጠግቡ መስሏቸው ከየዓይነቱ መሻማት ጀመሩ ። ብዙም ላይበሉ ተስገበገቡ ።

«ኤልፓ» በቤቱ ከአሮጊቷ ኡማ ዱንያ በቀር ማንም እንደሌለ ስትረዳ የቤቱ ልጅ ይመስል ተፍ ተፍ ትል ጀመር ። አሮጊቷ ከእንግዶቹ ጋር በጣፋጭ አማርኛቸው ሲጨዋወቱ እሷ ወደ ጓዳ ገብታ ወተት የተጠጣባቸውን ጌባዎች አጣጠበች ። በአሮጊቷ ተመረቀች ። ቱፍታ ጨመሩላት ።

እንግዶቹ የቤቱን ባለቤቶች አመስግነውና የተወሰኑ ጌጣ ጌጦችን ለማስታወሻ ሸምተው ለሌላ ጉብኝት ወደ አብዳል ትምህርት ቤት መስመር ግራ ቀኛቸውን እየቃኙ በአዲሱ አስፋልት ላይ በ«ኤልፓ» ቀዳሚነት በፍጥነት ወረዱ ።

በስተቀኝ በኩል ወደ አገበር ሜዳ የሚወስደውን መንገድ ተከትለው መጓዝ ጀመሩ ። «ቀስ እያላችሁ እየሄዳችሁ ጠብቁኝ...አከስቴን አናግሬ ልምጣ » ብላቻው በአንድ ቀጭን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ገባች ። ጀጎልን የማያውቅ ማንም ሰው ከጀጎል የውስጥ ለውስጥ መንገዶች የትኛውንም ያለ መሪ ባይሞክረው የተሻለ እንደሆነ የቀደመ መረጃ ነበራቸውና እሷን ከመጠበቅ ወይም ገብቶ ከመፈለግ ይልቅ መንገድ ጀመሩ ። አልፎ አልፎ ወደ ኋላቸው መለስ እያሉ አስጎብኚያቸውን መናፈቅ አልተውም ።

እንግዶቿ የጀጎል ግንብን የውጨኛ ክፍል በአግራሞት እየተመለከቱ ቡዳ በር ጋ ሲደርሱ ባዩት ነገር ተገርመው ቆሙ ። ከበሩ ዳርቻ ላይ በቅሎ ለአካባቢው ጥላ ብቻ ሳይሆን ለአንድ ምስኪንም ቤት የሆነውን የሾላ ዛፍ ተደነቁበት ። በጣም ወፍራሙ ግንድ ተቦርቡሮ ውስጡ ሰው ያድርበታል ። ተቦርቡሮ ያልደረቀው ፣ ከዓመት አመት አረንጓዴ ቅጠልና ነዋሪ ወፎች የማያጣውን ፣ በበጋ አካባቢውን በቢጫ ርጋፊ ቅጠሎችና ወፍ የጠረጠራቸው የሾላ ፍሬዎች



@BOOKALEM

Scanned by CamScanner

የሚሞላው የሾላ ዛፍ አስደንቋቸዋል ። በተለይ ሰውን ያክል ነገር ሕይወት ያለው ዛፍ ውስጥ መሽጎ መኖሩ ተዓምር ሆኖባቸዋል ። ምስኪኑን ሰው ከነ ሕይወታዊ ቤቱ በካሜራው እንጉል አኖሩት ። እሱ ተረጋግቶ የሚተኛበትን ቤቱን እነሱ ፎቶ ግራፍ ለመነሳት ፈሩት ፡፡ እየተንቀጠቀጡ ተራ በተራ ከምስኪኑ ጋር ቤቱ ውስጥ እየገቡ ፎቶ ተነሱ ፡፡

ልጅት «ኤልፓ» ከነ ጥላዋ ጠፍታለች ፡፡ እነሱም ከፊት ለፊታቸው የሚታያቸውን የቀበሌ አምስት ዳገት እየገፉ መጓዝ እንደጀመሩ ሳያስቡት ዱላ ፣ ጎራዴ ፣ ጦርና ገመድ በያዙ ሰዎች ተከበቡ ፡፡ ሳያስቡት የአንድ ጎረምሳ ዱላ የሁለቱንም ሰዎች እግር ቀለጠመ ፡፡ አእምሯቸውን በዕውቀት ፣ መንፈሳቸውን በሀሴት ፣ ሆዳቸውን በጣፋጭ ምግብ የሞላው ኅብረተሰብ አካል ለምን ሊደበድባቸው እንደፈለገ አልገባቸውም ፡፡

እጃቸውን የፈጥኝ አስረው በረጅም ገመድ እንደ በግ እየጎተቱ ሸዋ በር ዳቦ ተራ ጋ ወዳለው ፖሊስ ጣቢያ አደረሷቸው ፡፡ በፖሊስ ጣቢያውም ሼክ በድሪና ኡማ ዱንያ እያለቀሱ ተመለከቷቸው ፡፡ ኡማ ዱንያ ወደ እንግዶቹ ተጠግተው ሊገባቸው ባልቻለው የአደርኛ ቋንቋ ተማፀኗቸው ፡፡

« ስምህ ማነው ?» አለው ፖሊሱ አንደኛውን እያለቀሠና እያነከሠ የተቸገረውን ተጠርጣሪ

«ስለ ምንም ነገር ከማውራታችን በፊት የታሠርንበትን ገመድ ፍታልን !» ሲል መለሠ ያልተጠየቀው። ፖሊሱ ቀለም በጠማው አመዳም ከስክስ ጫማው የሚያነክስ እግሩን መታው ፡፡

«የመምታት መብት የሠጠህ አካል የለምና አትምታው ! » አለ ሌላኛው እልህ እንዳንገበገበው ያስታውቃል ፡፡

ፖሊሱ ወደ ተናጋሪው ለቦክስ ያሰወነጨፈው ሥርዓት ቢስ እጁ ተመክተበት ፡፡ አጠገቡ ያገኘውን ዱላ አንስቶ ሠነዘረ ፡፡ ዱላው የእንግዳውን ተጠርጣሪ ዘራፊ ግንባር ነረተ ፡፡ ግንባሩ እየተነፋ ፣ እየተነፋ ኡብጠቱ ዓይኖቹን ሸሸገበት ፡፡ ግንባሩ ለብቻው ወደ ፊት እየተነፋ ሰውዬውን ሹል ጫማ በጭንቅላቱ ያጠለቀ አስመሠለው ፡፡ ፖሊሱ ባየው ነገር ተደናገጠ ፡፡ የተጠርጣሪዎቹም «ሕግ ፣ ሕግ » የሚል ወሬ ረበሸው ፡፡ ፍርሀት ፍርሀት ሸተተው ፡፡

በከብ ቀዳዳው ሌባ ጣትን እያስገቡ ፣ እያሽከረከሩ በሚደወለው ስልክ ወደ አንደኛ ፖሊስ ጣቢያ ተረኛ ፖሊስ ደውሎ የሚልከለትን እስረኞች ከማንም እንዳይገናኙ እድርጎ እንዲያሳድራቸው መልዕክት አስተላለፈ ፡፡ በኪሶልዲ (በረባሶ) ተራ ወደ ውስጥ በጀጎል ሾሎክሏኳ መንገድ ወደ አንደኛ ፖሊስ ጣቢያ ወሠዷቸው ፡፡

እንግዶቹ ፖሊስ ጣቢያው እንደ ደረሱ ሦስት ሦስት ኮኮቦች በግራና በቀኝ ትከሻው ላይ ጭኖ ፣ ሽጉጥ የታጠቀ የፖሊስ መኮንን ተመለከቱ ፡፡ ሞተር ሳይክሉን አስነስቶ ሊሔድ ሲል መሬት ተኝተው መንገድ ዘጉበት ፡፡ ይዟቸው የመጣው ፖሊስ ሊመታቸው ዱላውን ሲያቀባብል መኮንኑ በእጅ ምልክት ከድርጊቱ እንዲታቀብ በዓይኑ ግርፊያ ጭምር አስጠነቀቀው ፡፡ የሞተር ሳይክሉን መደገፊያ ወደ ነበረበት የመለሰ መስሎት ተጠጋቸው ፡፡ መደገፊያ ምርኩዙን ያጣው



@BOOKALEM

ሞተር ሳይከል እንደ ሰዎቹ መሬት ተንጋለለ ::

መኮንኑ የት እንደሚያውቃቸው ተደናገረው እንጂ ሁሉቱንም ሰዎች በደንብ ያውቃቸዋል። የማንከሳቸው ፣ በትላልቅ ፊታቸው ላይ የደረቀ የእንባ መስመር ማየቱ ፣ የአንደኛው ግንባር ተለጥጦ ሰውዬውን ሌላ ፍጥረት ማስመሰሉ እንጂ የሆነ ቦታ አንዳያቸው በጣም እርግጠኛ ነው :: ፈራ :: ምን ብሎ የት እንደሚያውቃቸው መጠየቅ እንዳለበት ግራ ገባው :: ትኩር ብሎ እየተመለከተ ወደ ኋላው ማምሠልሠል ጀመረ ::

አዎ ! ትዝ አለው :: በትክክል ያውቃቸዋል :: የት እንደሚያውቃቸው በሚገባ አስታወሠ። ያስታወሰው ትክክል ነበር :: ከአንድ ቀን በፊት በምልሠት ወደ ድሬደዋ ራስ ሆቴል ነጎደ :: የስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ገብቶ ወንበር ያዘ ::

«...የምሥራቅ ኢትዮጵያ አጎራባች ክልሎች የፖሊስና የደኅንነት መኮንኖች ታሪካዊ ስብሰባ ነበር። ከፌደራል መንግሥት በተላኩ ከፍተኛ ባለሥልጣናት የተመራ ስብሰባ :: የስብሰባው መሪዎች ከሕዝቡ የደረሳቸውን ቅሬታ አጠረቃቅመው ተወያይተዋል :: የየክልሎቹ የፖሊስ መኮንኖችና የደህንነትና ፀጥታ ኃይሎች አባላቶቻቸው ሕገ-መንግሥቱን የሚቃረን ተግባር እየፈፀሙ በመሆኑ አደብ እንዲያስገዟቸው ሲነግሯቸው ከሕዝብ የቀረበው ቅሬታ ውሸት እንደሆነ ተከራከረዋል። በተለይ እሱ 'በኛ በኩል ያሉ አባላት ፍፁም ናቸው' ሲል ነበር :: ተጨብጭቦለታል :: የሥራ አመራር ጥበቡም ለሌሎች አርአያ ይሁን ተብሏል :: ዘገነነው ::»

መኮንኑ ከፍዘቱ ተመለሰ :: ፊት ለፊቱ መሬት ላይ የተጋደሙት ሰዎች ከአንድ ቀን በፊት በነበረው ስብሰባ አወያዮች ነበሩ :: ከፍተኛ የደኅንነት ሥራ አመራሮች :: ዛሬ ከእግሩ ስር ወድቀዋል :: ያውም ተበለሻሽተው :: በጉልበቱ መሬት ተንበርክከ የታሰሩበትን ገመድ ፈታላቸው :: የፖሊስ አባላቱ ተገርመው የሚያዩት የመኮንናቸው አድራጎት አስደነገጣቸው :: ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ቆሞ እንኳን የማይፈታው ፊቱ ለተጠርጣሪዎቹ ዘራፊዎች ተለማማጭ ሆነ። በዙሪያው የቆሙት የፖሊስ አባላትና ተዘራፊዎቹ አንዴ ቁጡውን መኮንን አንዴም ተጠርጣሪ ዘራፊዎቹን እያዩ በ «ሕሱ እንዲህ የተርበተበተላቸው እነሱ እነማን ይሆኑ ?» ጥያቄ ተብሰለሰሉ ::

በፖሊስ ላንድ ሮቨር መኪና ወደ ሆስፒታል ከመወሠዳቸው በፊት ፖሊሳዊ ተግባሩን ባግባቡ ከመወጣት ይልቅ የዱላ ውርጅብኝ ያከናነባቸውን የሸዋ በር ፖሊስ በካቴና ጠፍንገው አምጥተው ፊታቸው ገተሩት :: እየተንቀጠቀጠ እንገቱን ደፍቶ ቆመ :: መኮንኑ የፖሊስ ቆመጥ ከአንደኛው ፖሊስ ነጥቆ ሊገርልጠው ሲል ተጠርጣሪዎቹ በአንድ ቃል «እንዳትነካው ! » አሉት ::

ሰዎቹ የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ አግኝተው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከመኮንኑ ጋር ተመለሱ። አንዲት ቆንጆዬ ወጣት ከመርማሪው ፊት ለፊት ተቀምጣለች :: በመርማሪው እና በሷ መካከል ባለው ሠፊ ጠረጴዛ ላይ በርካታ የብር ኖቶችና ጌጣጌጦች ተዘርረዋል :: ቆንጆዬዋ ዘራፊ በሰራዋ ያፈረች አትመስልም :: ኤልፓ ስታስጎበኛቸው የነበረችውን ሰዎች ስትመለከት ልብ የሚያርደውን ፈገግታዋን ቸረቻቸው ::



@BOOKALEM

«በጣም ቆንጅዬ ልጅ ! ምርጥ አስጎብኚ ! » አላት ጫማ ግንባሩ ሰውዬ

«ስለ አድናቆትህ አመሰግናለሁ ! ግን ያስጎበኘሁብትን አልከፈላችሁኝምኮ ስጡኛ ! »

«ስንት ይበቃሻል ? »

«ሁለት መቶ ብር ስጡኝ... ፀሐይ ለፀሐይ ስታንከራትቱኝ አይደል እንዴ የዋላችሁት ? »

ፈጣጣነቷ ሳይገርማቸው አልቀረም ፡፡

እጁን ወደ ኪሱ ሰድዶ ሦስት መቶ ብር አውጥቶ ሰጣት ፡፡ ሁለት መቶውን ወስዳ መቶውን መለሰችለት ፡፡

«የተሰጠሽን ብር ለምንድን ነው የምትመልሽው ?»

«ሒሳቤ ሁለት መቶ ብቻ ነዋ ! »

«እና ሦስት መቶ መስጠት ሲፈልጉስ ? »

«ወላሂ ! ሀራም ነው ... እኔ የሰው ሀቅ አልፈልግም ፡፡»

የኤልፓ ነገር «ወዘተርፈ » ነው አላልኳችሁም ? ይኸው ወዘተርፈ ፡፡



@BOOKALEM

## ... እንደ ‹ናና› ከረሜላ የሚጣፍጡ ታሪኮች!!

ደግሞ የኢትዮጵያዊ ልጅነት ቀለሞች መመሳሰላቸው !! ... በልጅነቱ ‹ጋዝ ግዛ!› ተብሎ የተላከ፣ ገላውን በሳሙና የታጠበ፣ ጢቢኛ የበላ፣ አሹቅ ያነከተ፣ በወተት ላስቲክ ኳስ ያንጠባጠበ (ያንቀረቀበ)፣ በካልሲ ኳስ ‹ምትትሮሽ› የተጫወተ፣ የወደቀ ዕቃ አግኝቶ ‹ብጌ - ባትጌ› የተባባለ፣ ጀላቲ የጠባ- የላሰ- የመጠጠ፣ ‹ቡቲካ› ተባብሎ የተኳረፈ፣ የማርያም ጣቶችን አቆላልፎ እርቅ የፈጸመ፣ ፔፕሲ ኮላ የተገዛለት፣ ፔፕሲው እንዲበዛለት በውሃ የበረዘ፣ ለዓመት በዓል አዲስ ልብስ የተገዛለት፣ ልብሱ እንዳይቆሽበት አብዝቶ የተጨነቀ፣ ፊኛ (እፉፉ) የተሸለመ፣ ጎረቤት ወለል ላይ ቁጢጥ ብሎ ቲቪ ያየ፣ ‹ዕቃ- ዕቃ›፣ ‹ሹሌ›፣ ‹እርግጫ›፣ ‹ሰኞ- ማክሰኞ›፣ ‹ሱዚ› ‹ፔፕሲ›፣ ‹ወደም›፣ ‹ቅልምልሞሽ›፣ ‹አባሮሽ›፣ ‹ቃጤ-ቃጤ›፣‹አቦሰም›፣‹ጢባ- ጢቤ›፣‹ሌባና ፖሊስ›፣ ‹እኩኩሉ› የተጫወተ፣ ‹እሚ- ቀሊጥ› ያለ፣ ያስባለ፣ የተባባለ ...ይህንን ሸጋ መጽሐፍ ቢያነበው በደስታ ይሞታል፡፡

መሐመድ ሰልማን

(የ‹‹ፒያሳ ማሕሙድ ጋ ጠብቂኝ›› ...


አከፋፋይ፡- ሊትማን ጀኔራል ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር
አድራሻ፡- ጥቁር አንበሳ ፪ኛ ደረጃ ት/ቤት ፊት ለፊት ትራኮን ህንፃ
ስልክ 0911 89 94 68 / 011 1 26 20 21

የገፅ እና ሽፋን ዲዛይን - ባሴ
አድራሻ፡- ስልክ፡ 0911-93-00-51
ኢ-ሜይል፡- basse444@gmail.com

አታፍዞር አታሚዎች

ዋጋ፡- 39.45 ብር